# እቴሜቴ
# ሎሚ ሽታ



አዳም ረታ

1165

# እቴሜቴ ሎሚ ሽታ

አዳም ረታ

© አዳም ረታ
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አምስተኛ ሕትመት 2012

የሽፋን ስዕል መነሻ ኃሳብ፣ ሜዝ ኬ ጆን ዊቲንግ (2001)
www.knottedlines.com/oval/%20maze.htm.

# ስጦታ

**ለእናቴ**

ለላቀች አላምነህ

(ነፍሷን ይማር)

**ለአባቴ**

ለረታ ብዙነህ

(ነፍሱን ይማር)

# ይዘት

መች ትመጣለህ? ....................................................................7
የስብሐት ጢም ....................................................................23
እቴሜቴ ሎሚ ሽታ ....................................................................77
በለስ ....................................................................127
ለድልህ ....................................................................177
ሁለት ተኩል የውስጥ ሱሪዎች ለአዲስአባ ....................................................................217
(ሽልንጓ) የመጨረሻዋ የቀበሌ 01 ድንግል ....................................................................263

*ምናባዊ ማጣቀሻ መፃሕፍት ....................................................................315*
*ማጣቀሻ ቃላቶች ከነገፀ አድራሻቸው ....................................................................317*

እነዚህ ልብወለዶች ውስጥ ያሉት ገፀባሕርያት በሙሉ ምናብና ሃሳብ የወለዳቸው ናቸው:: በአንዳንዶቹ ውስጥ የሚያጋጥሙን የታዋቂና የሚታወቁ ግለሰቦች ስም መግባት ጊዜን በሚመጥነው ድባብ ለማጀብ የተሰራ ኪነታዊ ጥረት እንጂ ሌላ ዳራ የለውም:: ከዚህ ውጭ የተቀረው 'ድብን' ያለ ልብወለድ ነው:: ከግለሰቦች ታሪክ ጋር መመሳሰል ድንገት ቢከሰት የአዳም ሳይሆን 'የእዝጌር' ስራ እንደ ሆነ ይቆጠር:: በተጨማሪም ከድርሰቶቹ ጋር እንደ መግለጫና እንደ ማብራሪያ በሚቀርቡት ሕዳግ ማስታዎሻዎች(ሕማ) ውስጥ (አ) ማለት አርታኢ (ደ) ደራሲ ማለት እንደሆነ አንባቢ እንዲያውቀው ይሁን::

አረ

# መች ትመጣለህ?

## ቅዳሜ

በዚያች የለጋ[1] ዕድሜያችን የምትንቧች አቅሚቲ.......

አዛውንቱንና ጎልማሶችን እኒህን እነኝያን ምድር ላይ አርባ ዓመታት-ያውም ቢያንስ—አየር የተነፈሱትን......

በእግሮቻቸውም ረዥም የጊዜ ሂሳብ የተጓዙትን......

ባዘገመ፣ በሚጠወልግ ብርታት ሌላ ቅስማቸውንም እንደ ጡት ያለቡትንና የሚያልቡትን......

በትንንሽ የሽወዳ ኪነቶችና ኪነታት (ይባላል እንዲህ?) ፊቶቻቸው ላይ ዐይነ-ዕርግብ ልንጥል ብልጠት ወይም ቴክኒክ ጉነጉንን:: 'ጉነጉንን' አልኩ? ጉንጎናም አይደርስ:: ቀላል፣ ጠውላጋ ውሽክሽክ ኩሸት ናት::

አተኩሬ የማየው ቤት ሁለት ሜትር ተኩል ከፍታ ባለው ግንብ ታጥሯል:: ጠርዙ ዙሪያ ጠርሙሶች በደረቀ የሲሚንቶ ሊጥ ውስጥ ተከስክሰውና ተተክለው አጥሩን የተበሳጨ አስመስለውታል (መከላከያ መሆኑ ነው?) ......(ከራሳቸው?):: ቀርበው ሲያዩት ደ'ሞ ትዕይንቱ ይከፋል:: በቀትር ፀሐይ ውስጥ የተለያዩ

---

1 'እምቡጥ' ሲሉኝ እጠላለሁ—«ገና እኮ እንቡጥ ነህ» ስባል:: ቃሉ ከ 'ልጅነት' ይልቅ ወደ አካል ጉዳት ስለ ሚቀርብ ይሁን እንጃ:: 'እብጠት' ሲሉ/ሲሉ ይመስለኛል:: ከ 'ዕምቡጥ' ይልቅ 'ለጋ' የሚለውን ቃል የመረጥኩት ለዚህ ነው::

የጠርሙስ ቀለሞች ተባድነውና ተጋጭተው የሚፈነጥቁት ብርሐን የሚያስፈራራ ነገር አለው:: ቀርቤ ለመጀመሪያ በትኩረት ያየሁትም ዛሬ ነው:: ቅዳሜ::

ገና ሪዝ አላቆጠቆጥኩም:: ግማሽ ዕርግማን ነው......የእሷም (የኩረሪማ) ደረቷ ላይ ግራና ቀኝ እንደ ትንንሽ ጣቶች የቆሙት እነሱ ጡቶቿ ለጋ ናቸውና አልወደቁም:: መቼም ብዙ ባላውቅ የሰው ዕድሜው ሲገፋ በትከሻው ከተሸከመው የኑሮ ጣጣ (ውስጡ ጎምዛዛነትን እንደ ኮክ ጠጠር የወተፈ) የበለጠ የመሬት ስበት ይገንበታል አሉ(የወደቀ እንጨት ምሳር ይበዛበታል):: 'አሉ' ነው እንጂ ገና ምንጭሩ ላይ ጭገር ያልከሰከሰ ወጠጤ ስለነዚህ ዓይነት ሚስጢራት ምን አውቅና......

ግን ያ ሲደርስባት ማየታችን አይቀር......(እቱ ኮረሪማን)

ከቤቱ አጠገብ ሠፈ አስፋልት መንገድ አለ......በነጭ ደማቅ መስመር (የበልግ ዝናብ አጥቦት ስላላለፈ ይሆናል አቧራና ጭቃውም ደማቅ የሆነው) በቁመቱ ለሁለት የተከፈለ:: ይኼን መንገድ ተሻግሮ የቀለጠ ሠፈር ነው:: ሠፈሩ ደ'ሞ ከጀርባው በሆነ ትንግርትና ሐይል እንደተገፉ ሁሉ ቤቶች፣ ተፈጥሮና ኑሮ የሰጡትን ንጥረ-ነገሮቹን ሰባስቦ የመንገዱን ጠርዝ ታኮ ከዳር ዕዳር ቆሞአል:: አይገፉት ነገር::

ታዲያ እዚህ ግንብ ሥር ስቆም ከወዲያ በኩል ብዙው ዜጋ ከሠፈረበት ከሰፈሩ ማንም ያየኛል:: የዚያ ሠፈር የእግር ኳስ ክለብ ብሌን ነኝ:: ታዲያ ይኼ ብሌኑን ከላይ እስከ ታች የሚተላለፈው የሠፈሬ ፈጣጣ ከዚያች ዕርቀት በግልፅ ያየዋል:: ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ደ'ሞ ሠፈሩ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ሕይወት...... ሕይወት ልበለው ወይስ ረብሻ......ይሰፍንበታል:: ከሁለንተናው ድምፅ ያወጣል:: አይቼአቸው የማላውቀው የማርቆስ እናት እንኳን ጀርባቸውን ለመንገዱ ሰጥተው የሆነ ነገር ይወቅጣሉ:: ባለ አበባ ቀሚሳቸው የሰረሰራቸውንና የወቀጣቸውን መስመር ተከትሎ ከፍ እያለ ይወርዳል:: እየወረደ ከፍ ይላል::

ታዲያ በዚህ ዕድሜዬ ኩረሪማ የተባለች ልጅ ብወድ......ሳይሆን እንኳን ማማለል ፈልጌ እዚህ አጥር ሥር ስቆም ልቤ ውስጥ ከፍ ያለ ምኞት እንጂ ሁለታችንም የቀየስነው ቴክኒክ ይሠራል ብዬ አምኜም አይደለ::

ቴክኒኩ ምንድን ነው?

ኩረሪማን ገና ሳያት የወደድኳት ጠይም ናት:: ነጭ ጉርድ ካናቴራ ለብሳ:: ቀይ አጭር ሽንሽን ቀሚስ ለብሳ:: ጡቶቿ ያለመያዣ ብይ ብይ መስለው:: የዕውነት ይሁን የውሸት ደቃቃ የወርቅ ቀለም ያላት ድምብል አንገቷ እርግብግቢት መሐል አቁራ::......የቀጠኑ ክንዶቿ...... ትላልቅ ሊስቁ የፈለጉ ዓይኖቿ (ግን እናቷ እንዳይስቁ እንዳይገላምጡ እንዳያተኩሩ የከለከለቻቸው)...... በዚያ ላይ በችኩላ እንደተሠራ ሁሉ የተልቆሰቆሰ ጉንጉኗ እና አ! ጠይምነቷ:: የቀሚሷ በጨዋታ መሃል ከኋላ ፊኒር አባባልና ከዛም ስር ሰርቄ የማያቸው(ዘራፍ ዓይነ ሌባው) ጠይም ወዛም ጭኖቿ......አላፈቀርኳትም ግን በዓይኔ በብሌኑ ገባች:: ጠይም ጦር::

ያኔ ኳስ ጨዋታ ሊያዩ መጥተው ነበር......ከነወዳጆቿ......

ሜዳው ከእነሱ ቤት ብዙ ያልራቀ ማዶ ነው እንግዲህ:: የእነሱን ቤት አልፈን አምስት ደቂቃ ከተጓዝን በኋላ (እየተላፋን፣ ወደ ኋላ እየተባረርንና ወደ ፊትም እየሮጥን፣ ቆመንም እያወራን......ይሔ ሁሉ ተደምሮ) በእሷ መማረኬን ለማንም ሳልነግር ዝም አልኩ:: እንዴት አንድ ወንድ ያውም የተከላካይ ቦታ የሚጫወት፣ ስንቱን ጉረኛ አጥቂ በሸርተቴና በትከሻ ግፊያ ድባቅ የመታሁ ወንዳ ወንድ፣ አንድ እንዲህ ላፍታ ባየኋት ልጅ ስሟም ባልተጠራ ጠይም ልጃገረድ የምረታው? ስለዚህ ይኼ እንደ ወሬ ተቆጥሮ ለማንም አይነገርም::

አንድ ቀን ለልምምድ ስወጣ......(ከጥቂት ቀናት በኋላ) ቤቷ በር ላይ (የቤታቸው በር ቀይ ሠፊ ብረት ነው:: ብረቱ መሐል ደ'ሞ ሌላ ትንሽ ቀይ የብረት በር አለች......ቀይ በቀይ) ይህቺን ሶረኔ በዚያች ቀይ የበር ቀዳዳ ከጣዕመ ቢስ ልጃገረዶች ጋር እየገባችና እየወጣች ቤቷ ፊት ፊት ያለ ወደ ቤቷ የሚያስገባ አስፋልት ላይ ገመድ ዝላይ ስትጫወት አገኘኋት:: እሷም ያኔ ቀይ የመሰለ ነገር ለብሳ (እሷ ከበሩ ቀዳችው? ወይስ በሩ ከእሷ ቀዳ?) ወዲያ ወዲህ እያለች ከመሰሎቿ ጋር ስትራበሽ «ዝላይ አስገቡኝ» አልኳቸው:: ልጃገረዶቹ በሙሉ ፀጥ አሉ:: እሷን አየኋት:: ተሽኰረመመች:: ዓይኖቿን አየሁ:: እያችሁ መሽኮምኮም[2] ድባብ ነው:: በእሱ ከተወናበድኩ መሸሼ ነው:: ከመሽኰርመም ጀርባ ብዙ ጊዜ አላዋቂነት ያለ የሚመስለው አንዳንድ ቀሽም ሰው አይጠፋም:: መሽኰርመም ውስጥ ፍፁም ባይሆንም ዕውቀት አለ:: የዚያ ዕውቀት ዋና ዓላማ የድንቁርናና ጠንበል ልጃገረዲቷ ገፅ ላይ መጣል ቢሆንም:: ይኼን ድባብ ለማለፍ አሳድጂ ያየሁት ዓይኖቿን ነው:: ዓይኖቿንና አፏን ነው::

መሽኰርመም ከእግር ኳስ አብዶ ጋር ይማሰላል:: የአብዶ ሰሪው ዋና ጥበቡ በእግሮቹና በሌላ አካሉ እርስ በርስ የሚቃረኑ፣ የሚጋጩ ምልክቶች ለባዕድ ቡድኑ ማስተላለፍ ነው:: ግራ ክንፉችን ተዘራ ከሆነ ደ'ሞ በአፉ:: ዋናው ጉዳይ ግን ኳሱ ነው:: አረፍ ተከላካይ ያደረገኝ የአብዶ ሰሪውን ዝላይ፣ ዳንስ፣ ትርምስና ጩኸት ችላ ብዬ ኳሷን ብቻ አተኩሬ ስለማይ ነው:: መልዕክቱን:: "the message" ነው ዋናው:: (የሚገርመኝ ኳሷን እንደዚያ ሳያት ብዙ ጊዜ ንፁሕ ግዑዝ ነገር ትሆንብኛለች:: እዚያ ሜዳ ላይ እግሮች ዙሪያዋን እየተራኮቱ እያየኋት፣ አእምሮዬ ውስጥ ያለቦታዋ ጠረጴዛ ላይ፣ ወንበር ላይ፣ ሰው/ፍጡር የሌለበት ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ብቻዋን ያለች ትመስለኛለች:: የምይዛት ያኔ ነው::) አጠቃላይ ገላዋን (የኳሷን ሳይሆን የኮረሪማን) እንደፈራኝና እንደሸሸኝ ሁሉ ሲሰበሰብ የዓይኖቿን አገላለጥ ብቻ አየሁ:: በከንፈሮቿ ልትለቀው ወይም ልታስቀረው (እንደ ሞናሊዛ) የምትሞክረውን ፈገግታ በዓይኖቼ ቆንጥጬ ያዝኩ::

ታኬታዬን ትከሻዬ ላይ እንደ አንጠለጠልኩ አብሬአቸው ዘላለልኩና ስሔድ......

«ዛሬ ውድድር አለ እንዴ?» አለች አንዷ ዕድሜዋ ለድሪያ ያልደረሰና ገና ፍርሐት ያልገባት::

---

2 'ኸግሪቴ ኸግሪቴ/ እመለ ደጎኒቴ/ ነይ እሽኩምኩም ከእኔ' ወይም 'ሶረኔ ሶረኔ/ ነይ እሽኩምኩም ከእኔ' ይላል እረኛ በተረት (እንቅልፍ ለምኔን እይ)

«አዎ» አልኩ ውሽቴን:: ተያዩ:: ኮረሪማን አየኋት:: በዓይኖቼ እንድትመጣ ለመንኳት:: 'ባክሽ ነይ አሳ መሳይ' አልኳት:: 'ነይ በእናትሽ አንቺ እንደ ኳስ......እኔም እንደ አስር ቁጥር አጥቂ የፍቅር ማራዶና ሆኜ ኋላሽ ኋላሽ ልከተልሽ' አልኳት:: (ይኼ በዓይኖቼ ያሰብኩትን፣ በፊቴ ንቅናቄና በደም ግባቴ የፃፍኩትን ጓደኞቼ ድምፅ ሆኖ ቢሰሙት በታኬታ ቀጥቅጠው ይገሉኝ ነበር::) እየተግደረደረች እየተግደረደረች ልክ ያኔውኑ በቃል ኪዳን ላገባት አራዳው ጊዮርጊስ እንደምወስዳት ሁሉ ወይ ቅድስት ሥላሴ ወይ እዚህ ጨርቆስ......ብቻ እየፈራች ከቤቷ እስከ ሜዳው ዓላማችን ጉዟችን ለኳስ ጨዋታ እየመሰለ እያለ ተግባባኋት:: ስሟን ነገረችኝ («ኮረሪማ!»[3]):: የምታምር ቅመም:: ብታውቀውም ስሜን ነገርኳት:: የት እንደምትማር፣ ጠየቅኋት:: በመጨረሻ ከት/ቤት በስንት ሰዓት እንደምትወጣ ጠየቅኋት......ከዛ ደ'ሞ እንዴት ከቤቷ ልትወጣ እንደምትችል::

«አንተ ውሽታም......የታለ ውድድር......ደረቅ» እያሉኝ ገና ያልኩረደዱት፣ ማፈር መሽኩርመም ያልጀመሩት ልጃገረዶች እየሰደቡኝ ሔዱ::

ኩረሪማ ሁሉ ነገር ገብቷታል......ከማያቸው ዓይኖቿና ከማይነጋገረው አፏ ቅርፅ:: ቀድሞ እንዳልኩት ስሜቷን የምትደብቅበት ጠንበል የሚገለበው እነዚያ ጋ ነው:: ጠንበሉ ከተነሳ እዚያ ብዙ ድርሰት አለ:: የሆነ ድርሳን (ያ የቄስ ልጅ ማርቆስ እንደሚለው) አለ:: ታዲያ ታዲያ ከት/ቤት ወደ ቤቷ እሷን መሸኘት የምችልበት ሁኔታ ውስጥ አይደለሁም:: አንድ፡ የተራራቀ ትምህርት ቤቶች ነው የምንማረው:: ሁለት፡ የተለያየ ሽፍት ምድብ ነን:: ሶስት፡ ዕድሜዬ ለዚህ ገና የደረሰ አይመስለኝም:: እኔ ገፍቼው ብሰራው እንኳን፣ እሷም እድሜዋ እንደ ደረሰ ብታምንም ባታምንም ብቻ አብረን የሚያየን የሠፈር ሰው 'ደረሰ?' 'ደረሰች?' 'ደረሱ?' ብሎ እንዲያሽሟጥጠን አልፈልግም:: እነዚህ ቃላት አያስጠሉም?......

'ደረሰ' 'ደረሰች':: ምን ጋ ደረስን? ነገርዬው ራሴን ያዞረኛል::

ቴክኒኩ የተፈጠረው ይኼኔ ነው::

ከላይ ወጌን ስጀምር 'ቴክኒክ' አላልኩም?

እሱ::

ይህቺን ሙና ከቤቷ አውጥቼ ፒያሳ አንድ ኬክ ቤት ወስጄ እንደ እሷ የሚጣፍጥ ነገር ልገዛላት እፈልጋለሁ:: በታክሲ ወዲያ አምባሳደር አውርጄ ሲኒማ እጋብዛታለሁ:: እጅ ለእጅ ተያይዘን በጎዳና ሽር እንላለን፣ ይኼን ምኞቴን ስነግራት......

«መኝታቤቴ ውስጥ ነው ብዙ ጊዜ የምቀመጠው:: መኝታቤቴ ማድቤቱ

---

3 *'ወጤን ልወጥውጥ በአንቺ ሉጋ፣ እየበላሁ እስኪነጋ'* የሚል ግጥም በታወቀው ዘፈን በ*'ሉሚ ማሉላት በደረቷ'* ዜማ ስልት ከዚያን ጊዜ ጀምሬ ለሚቀጥሉት ብዙ ወሮች እዘፍን ነበር:: ልቤ ጠፍቶ እሱን ሳፏጭ እዚህ ግቡ የማይባሉ በዓይኑ ማዝ የተጨፈኑ አጥቂዎች ሸውደውኝ ጎል አግብተዋል::

አጠገብ ነው:: ማድቤቱ መንገድ ዳር ነው:: መንገድ ዳር ሆነህ ብታፏጭልኝ እሰማለሁ»

*ሒድ እንግዲህ!* አለ ተገራሚ::

በልቤ በዚህ ዘመን የዚህ ዓይነት ነገር ይደረጋል? አልኩ

«ሦስቴ አፏጭልኝ» አለች

ይታያችሁ ከመሽኮርመምና ገመድ ከመዝለል ሌላ ምንም አታውቅም ያልኳት ልጅ ስለፉጨት ጠቃሚነት አንድ ነጥብ ብጉራም ዕውቀቴ ላይ ጨመረችልኝ:: ቀድሞ ጠንቅቄ የማውቀው ፉጨት የጎል ኪፐራችንን[4] ነው...... 'አቀብለኝና እኔ ልለጋው' ሲለኝ::

ከዚያ ሆኖልን የተገናኘን ቀን......

እኔ ኋላ ኋላ፣ እሷ ፊት ፊት:: እዚያ እዚያ የሚያይ መስዬ እዛች ሚኒ[5] ቀሚስ ስር የማላውቀውን ሁለመናዋን እየጎመጀሁ:: ከአፏ ላይም ለሆነ ማታ የሚሆነኝ ቅዠት ልለቃቅም:: ደ'ሞ አለፍ ብለን እኔ ራቅ ራቅ ብዬ እሄዳለሁ እሷ ትከተላለች:: አንድ አምስት ደቂቃ ከቤቷና ከሰፈራችን ከሸሸን በኋላ በተገኘው መሳፈሪያ ፒያሳ እንገባለን:: ፒያሳ ማን ያውቀናል? ፒያሳ ውስጥ 'ለብልግና' የወጡ ሳይሆን በአጠቃላይ 'ባለጉዳይ' እንሆናለን:: ለምሳሌ: የትምህርት ቤታቸው አድራሻ የጠፋባቸው:: በዘመኑ የተገኘው ምክንያት ይፈለሰፋል......ዓለማችን ስለ ተሰላቸ ያምናል::

ግን ለመሆኑ ስንት አይነት ማፏጨቶች አሉ? ከሩቅ የሚሰማ አለ፣ እሱ ጩኸት ነው:: በቀስታ ሹሹ የሚደረግ አለ—ለሚስጢር ወሬ ቅብብል የሚደረግ:: ይኸ ሁሉ በአካል ቅርበትና ዕርቀት ይወሰናል:: ጉኒ ላለው ሰው 'በብርቂያ' አላፏጭም:: በ'ሹሹ' ነው:: እዚህ ግንብ ሥር ስቆም በየትኛው ስልት ነው የማፏጨው? ከፍ ካደረኩት ሰው ይሰማል:: ዝቅ ካደረኩ የፉጨቱ ጉላት ግንቡን ዘልቆ እሷ መኝታ ቤት ላይሰማ ይችላል:: ታዲያ ሳምንቱን ሙሉ አማሃይ ፉጨት ስለማመድ ቆየሁ:: ያዋጣል?

ብልህ ሰው ይኼን ቢሰማ:

«ምን ነካችሁ? ይኼ ነገር ልምድ አይጠይቅም እኮ:: ከመጀመሪያ የምትገናኙበትን ቀን ሰዓትና ቦታ ወስናችሁ መገናኘት......ምን እንደ ቁራ አጥር ላይ ሆነህ ትጮሃለህ?»

«አልፈለገችም እሷ!»

«እንዴት?»

«በቃ አትፈልግም»

«ይኼ በሽታ ነው»

---

4 goal keeper=ግብ ጠባቂ(እንግሊዘኛ)(እ)

5 mini=ደቃቃ(እንግሊዘኛ)(እ)

«እንጃ እሱን እንኳን ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል:: ሲያፏጩላት የምትወድ ከሆነስ? ለፉጨት የተለየ ፍቅር ቢኖራትስ? ቁጭ ብላ ልክ ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ ሲፏጭላት መስማት 'አፒታይዘር'[6] ከሆነላትስ? በዕድሜ የምትበልጣት ጓደኛዋ በፉጨት ስትጠበስ አይታ በዚህም ስትቀና ኖራ ለእሷ እንዲሆንላት ፈልጋ እንደሆነስ? ምን ይታወቃል ጋሼ? በዚያም ላይ እኔ ሰፍሳፋ ሆኜላት የተፈለገውን ቂላቂል ነገር አድርግ ብትለኝና አድራጊ ከሆንኩስ? እወዳት አልወዳት እንደሆነ መፈተኗ እንደሆነስ? ዋናው በተፈለገው መንገድ ከቤቷ ማስወጣት ነው:: አይደለም?»

«አይ የራሳችሁ ጉዳይ፡ ሌላውን ሰው ብቻ ሳይሆን ራሳችሁንም ማሳቅ ፈልጋችሁ ይሆናል»...........

......ታዲያ ቅዳሜ ዕለት ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ የግንቡን አጥር ጥግ ተከልዬ መነፅሬን አድርጌ የሸሚዝ እጀ-ታዎቼን ጠቅልዬ ሦስቴ አፏጨሁ:: ጉላ ያሉ መሐላቸው እንደአማረበት ሕብስት ክፍተትና አየር ያላቸው፣ በቀላሉ እንደ ኳስ የሚነጥሩ ሦስት ድምፀ-መልካም ፉጨቶች (ንርሲስ ናልባድያን ቢሰሟቸው ክብር ይሰጧቸው ነበር):: ጉዞዬን ለመጀመር ስነቃነቅ የማርቆስ እናት ወደ ቆምኩበት አዩ:: ከዚያ ግራና ቀኝ አዩ:: እኔን አዩ:: ግራና ቀኝ አዩ:: ማፏዋጨቴ መሰማቱ ማረጋገጫ ቢሆንም......

በመጀመሪያ ይወቅጣሉ:: ሁለተኛ ልጃቸው ማርቆስ ሳንባውን ቲቢ ታሞ ሆስፒታል ነው:: ታዲያ የሙቀጫው ድምፅ በጆሮአቸው፣ የልጃቸው ሕመም በልቦናቸው......እንዴት እኔን ሰሙኝ? ከአፌ የወጣው ከባድ ሚዛን ፉጨት ነበር ማለት ነው:: ይኼን ፉጨት ከኮረሪማ ሌላ፣ ሠራተኛዋ ወይ እናቷ ቢሰሙ......ይኼን ሰምተው የልጃቸው ፊት መቀያየሩን ሲያዩ፡ የአለባበሷን መለዋወጥ ሲያዩ--መዘጋጀት መውጣት ማኩብኮብ መምሰሉን ቢጠረጥሩና ቢያስቀሯት......ከአለባበሷ፡ ነጭ ካናቴራ፣ ባለገመድ ቆዳ ጫማ፣ ስትቀመጥ ልጥፍ የሚል ጭኗ ግማሽ የሚደርሰው ያ ቀይ ሽብሽብ ቀሚስ እና እንደ ትንንሽ መንታ የሸሚዝ አዝራሮች የቆሙ ጡቶቿ (ጡቶቿ ስፔሻል ልብሶች ይመስሉኛል) እየታዩ ባልተለመደ መልክ......

እንደገና ደ'ሞ የማርቆስ እናት መስማታቸው አጠራጠረኝ:: እኔንና ዙሪያቸውን እየተገላመጡ ደጋግመው አዩ ማለት ፉጨቴን ሰሙ ማለት ነው? እንዲህ ያደረጉበት ምክንያት ሌላ ቢሆንስ? በመጀመሪያ የልጃቸው መታመም አድክሟአቸዋል እንበል:: ሁለተኛ ወላድ እናቶች ደ'ሞ እንደ ኮረዶች ወገባቸው፣ ክንዶቻቸው፣ እግሮቻቸው ጠንካራ አይደሉም:: ቀጥሎ በርበሬ እየወቀጡ ነው:: በርበሬ መውቀጥ ማለት ደጋግሞ ማንጠስ ማለት ነው:: ታድያ እየወቀጡ ሲያነጥሱ ድንገት 'ቁቅ' አድርገው እንደሆነስ? አገሬ 'ቁቅ' ማድረግ 'ከማስመለስ' የሚያሳፍር ስለሆነ ታዲያ የተሰሙ መስሏቸው ማን ሰማኝ ብለው ለመሰለል ተገላምጠው እንደሆነስ?

---

6 appetizer=ቅመመን፣ ለወስፋት መከፈቻ መጀመሪያ የሚበላ ምግብ፣ የሚጠጣ መጠጥ (እንግሊዘኛ)(አ)

ኸረ ከላይ ያልኩትስ ሁሉ ባይሆን? በሆነ አጋጣሚ የእኔ ሦስተኛው ፋጨትና የእሳቸው ቀቀታ በጊዜ እንድነት ፈልቀው እንደሆነስ? ታዲያ ይኼ ወደ ምን ወሰደኝ......ፉጨቴ በደንብ ያልተሰማ እንደሆነስ ወደሚለው ጥርጣሬ:: ደግሜ ላፏጭ? ሊሆን አይችልም:: ድንገት የመጀመሪያውን ሦስት ፉጨቶች ኮረሪማ ከሰማች ደግሜ ከማደርገው ጋር ተደምረው ስድስት ሊሆኑ ነው:: በስድስት ፉጨት ደ'ሞ አልተስማማንም:: ታዲያ ምን አደርጋለሁ? መነፅሬን አድርጌ እጆቼን አጣምሬ ምንም እንደማይሰራ ምንም ጉዳይ እንደሌለው ማንንም ምንም እንደማይጠብቅ በፀሐይ እየተቃጠልኩና በግንብ ጥላ እየበረድኩ (ሳይደግስ አይጣላም' ነው የሚሉት) ለግማሽ ሰዓት ያህል ቆየሁ:: ኮረሪማ ከቤቷ አልወጣችም::

## እሁድ

ማታ ቤቴ ስመለስ ተበሳጭቼአለሁ:: መበሳጨት ፀባዬ አይደለም:: ኳስ ሜዳ ጎል ሲገባብን 'አትረበሹ' የምለው እኔ ነኝ:: ሁለት ሦስት አጥ ቂዎች እየተንጋጉ ሲመጡብኝ እረጋጋለሁ:: ይኼ ብዙ ተከላካዮች በመወናበድ የሚያበላሹትን ነገር በፍጥነትና በትክክል ማጠናቀቅ ያስችለኛል:: አሁን ትናንት ቅዳሜ አንዲት ሴትዮና ሦስት ፉጨቶች ረበሹኝ:: ራቴን በልቼ አንድ ሌትር ውሐ ጠጥቼ፣ አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ አንድ ጥያቄ በአእምሮዬ ሽው አለ:: ኸረ ለመሆኑ ቅዳሜ ነው እሁድ ነው ኮረሪማ ጥራኝ ያለችኝ? ይኼ በዕርግጥ መሰረታዊ ጥያቄ ነበር:: ይኼን ሳላረጋግጥና ሳልመልስ ከቤቴ መጀመሪያውኑ መውጣት አልነበረብኝም:: ብዙ ጊዜ ኳስ የምጫወተው ቅዳሜ ቅዳሜ ነው:: ይኼንን ታውቃለች:: ስለዚህ ቅዳሜ 'ና' አትለኝም:: ዛሬ እሁድ መስሎኛል፣ ምክንያቱም እሁድ እሁድ አንጫወትም:: ስለዚህ ልማዴ ወይም ነሁላላነቴ ቀጠሮዬን አወናከሯል:: ዛሬ ጨዋታ አለመኖሩን አታውቅም፣ እንደነገርኳትም ትዝ አይለኝም:: ማስታወስ ከማትኩር፣ ማትኩር ደ'ሞ እሷን ከመውደድ ጋር ላይገናኝ ይችላል:: ቢያንስ ከሦስቱ አንዱ ከሌሉ 'ነገሩ ነገሩት' ይበላሻሉ:: ስለዚህ ቢያንስ ጥርጣሬዬን ለማጥፋት እሁድ ተመልሼ እዚያው ግንብ ሥር ማፏጨቴን መቀጠል እንዳለብኝ ገባኝ::

ቀኑ እሁድ ብቻ ሳይሆን (ግንቡ ሥር ቆሜ እያለሁ የታዘብኩት ነው) መንገዱ እንግዳ በሆነ ጥልቀት ጭር ያለ ነበር:: የገባኝ፣ ዛሬ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ ነጫጭ ለብሰው ወዲያ ወዲህ የሚሉት ጥቂት ሰዎች ያስታወሱኝ፣ ፋሲካ መሆኑን ነው:: ፋሲካ እንዴት ትዝ አላለኝም? ትዝ ብሎኛል ግን ልቤ አልገባም ወይም ቸል ብዬዋለሁ:: እሁድ ላይ ፋሲካ ተደረበና(ወይስ ፋሲካ ላይ እሁድ ተደርቦ ወይስ ከጥንቱም አይነጣጠሉም?) ቀጠሮዬን የተለየ ያደርገዋል? ሠፈሩም ፀጥ ስላለ በተረጋጋ ማንንም ባልፈራ ስልት ያው እዛ የፈረደበት አጥር ስር ቆሜ ሦስት ቅላጼአቸው የሚያምር ፉጨቶች ለቀቅሁ::

ለምንድነው ከነኮረሪማ ማድቤት ሳያቋርጥ ጢስ የሚወጣው?......

ቀለም ቢኖራቸው ፉጨቶቼ አንዱ ከአንዱ የማይለይ ሐምራዊ ናቸው:: ፋሲካም ስለሆነ ቅርፃቸው የቅልጥም ወይም በስለታም ቢላ ተስተካክለው እንደ

ተቆረጡ የድሮ ዳቦ ቁራሾች ወይ እንደ ጠላ መስሪያ ጌሾ ይሆኑ ይሆናል:: እንደ አረቄ መጠጫ መለኪያ መስታወትም ለስላሳ ናቸው:: ግን ለጆሮ አይከብዱም:: እና ከአፏ ሲወጡ ኋላና ፊት ሆነው ተከታትለው፣ ወደ ትምህርት ቤት እንደ ሚሰደዱ ሕፃናት ወይ ለሱቅ አገልግሎት ቀበሌ እንደ ተሰለፉ የከተማ በላተኞች ወይም ከአክስፋም ስንዴ ለመሰብሰብ እንደ ቆመ ተጎጂ:: በአጥሩ ላይም ይመስለኛል እንደ ሣሙና አረፋ እየተንሳፈፉ ሄደው የቤቷ ግድግዳ ላይ ሲለጠፉ ወይም በሯን ወይም መስኮቷን እየኮረኮሙ ሲወድቁ:: ይታወቀኛል::

በዚህ መሐል ራሴን ጠየቅሁ......

እንዴት ለፋሲካ ትቀጥረኛለች......? ወይስ እቀጥራታለሁ?

ይኼን ማንም የሚጠይቀው ነው::

እስላም ወይ ክርስቲያን መሆኗን ባላውቅም ብዙ ጊዜ ሰዎች ፋሲካን ቤታቸው ውስጥ ማሳለፍ ይፈልጋሉ:: ኩረሪማም ሁኔታዋ ሁሉ እንደዚያ ይመስላል::

'ከቤት ልውጣ' ብትል እንኳን በዝምታ፣ በቸልታ፣ በግድየለሽነት፣ 'እንዳሻሽ' የሚላት አባትና እናት አይኖርም:: ቤት ውስጥ የተቀናበረ በዓልና ዝግጅት ትታ ስትወጣ ትርጉሙ ምን ይሆናል?

'ከዚህ የተሻለ ድግስ የታለ? መናቅሽ ነው? መጎርመስሽ ነው? መድረስሽ ነው?'

ስለዚህ ፉጨቴን ብትሰማም፣ ሰምታ ቢያምራትም ከተቀመጠችበት ወደ የትም መንቃነቅ አትችልም:: እኔ ከአደገችበት የቤተሰቧ ባሕል እበልጣለሁ እንዴ? ይኼ ሁሉ እንቅፋት እንደሚያጋጥማት እያወቀች ታዲያ እሁድ ልትቀጥረኝ ትችላለች? ባይሆን በዓሉን አሳልፋ ሊሆን አይችልም? በዓል አሳልፎ ስለመገናኘት ይቅርና ስለ በዓል አላነሳችም:: ግን እኮ አንድ ሰው(እኔን ማለቴ ነው) የባሕል ደደብነት ካላሰረው በስተቀር ጀማሪ የሆነች ትኩስነቷ የታወቀ ልጃገረድ የፋሲካ ቤቷን ትታ በእናቷ ቀሚስ ስር ሾልካ ባዕድ ክንድ ላይ ትወድቃለች ብሎ አይጠብቅም(የቀመሰችና ያልቀመሰች ሴት ስለ በዓል ያላቸው ግንዛቤ ይለያያል):: የፋሲካ ትርጉም ፍፁም የመብላት ነው:: ከተክሎች እስከ እንስሳት የሚበሉበት ነው:: አንዳንዴ እንደ እኔ ዓይነት ሞላጫ ወይም የመሰለው፣ እንደ ኮረሪማ ዐይነት የዋሕ ወይም የመሰለች የፌሽታ ሜኗቸው ላይ ልጃገረድ መሳምና መሳሳም የመሳሰለ ቢጨምሩበትስ?

እና እየቆየ (ብርቱ ባይሆንም) ስህተት እንደሰራሁ ገባኝ::

ኩረሪማ የቀጠረችኝ ከበዓሉ በኋላ ነው::

አንድ ሰዓት ጠብቄ (ካፏጨሁ በኋላና ፉጨቴ አድማጭ እንዳጣ(?) ከተረዳሁ በኋላ) ከቤቷ የወጣ ሰው እንደሌለ አየሁ:: ዞሬ ከፊት ለፊት የቤቷን አጥር በር ባይ፣ ባይ......ብረቱ ላይ ባፈጥ፣ ባፈጥ......ያው እንደ ተለመደው ቀይ ደፋር ግድግዳ መስሎ ቆሞአል......እንደ መልካም አግች (ዘፋኙ እንዳለው)::

ቤቴ ተመልሼ ለበዓል የተዘጋጀ መዓት ቅባት ያለው ዶሮና በግ ወጥ ነከነክሁ:: ጉርሻዬ......ትሪ ዳር ቆሞ ሳየው ጥላ የሌለው የኮካኮላ ጠርሙስ

ይመስላል:: አባቴ መስኮት በአበላሌ እየተበሳጨ 'ጉርሻህ እኔን ያክላል፡ ስለዚህ ስታጎርሰኝ መጠኑን ትንሽ አድርግልኝ' ይለኝ ነበር:: አባቴ የታወቀ ሰዐሊ ነው ('የታወቀ' ስል እፍራለሁ):: እናቴንና ጉርሻዋን መውደዱ ምክንያት ሆኖ የስዕል 'አጣጣል' ጥበቡ እንደተለወጠ[7] ደጋግሞ ሲናገር ሰምቼአለሁ:: በቅርብ ስዕል

---

7 ከባህላዊና ዘመናዊ የኢትዮጵያ ያሳሳል ፋናዎች አስር ቃለ መጠይቆች በአለማየሁ ሌንጮ(አርታኢ) 1970 እአ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት(ሁለተኛ እትም):: ከገፅ 27 እስከ 35 ተነቅሰው የወጡ::

እ.ሌ.(አለማየሁ ሌንጮ)፡ በአሁኑ ወቅት አንተ የምትከተለው የእንተን አባባል ልጠቀምና የብሩሽ አጣጣል ዘይቤ ተንካናኪ ይባላል፡ ተንካናኪ ምን ማለት ነው?

መ.ገ.(መስኮት ገረሱ)፡ ተንካናኪ የአጣጣል ፈርጅ በሌላ ስሙ ቅርባዊነት ይባላል:: በአገራችን የባህል አሳሳል የበላይነት ቦታ ያላቸውን ዐይንና ፊትን በተለይ ዐይንን በሌሎች የስሜት ሕዋሳትና ብልቶች ቀስ በቀስ መተካትና ቢቻል እኩል ለማድረግ የሚሞክር የአሳሳል ዘይቤ ነው:: በባህል ስዕሎቻችን ዐይን ትልቅ ቦታ አለው:: ዐይን ማለት ርቀትና ሃሳባዊነት ሲሆን፣ የየቀኑ ኑሮአችን ግን የቅርብ፣ አፋአዊና ተንካናኪ(የሚነካና የሚነካካ ውህደት የሚያሳዩበት) ነው:: ተንካናኪ የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የመጣው ከዚህ ነው(ባለቤትና ተሳቢ/ ሳብጀክትና እብጀክት ሐተታዊ በሆነ መልክ ሲዋሃዱ):: (............)ባህላዊ ስዕሎቻችን በርቀት የስሜት ሕዋስ(ዐይን) የተመሰጡና በማሰብ ስርዐት ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: የማቅረብ የስሜት ሕዋሳትን (የመንካት፣ የማሽተት፣ የመቅመስ) ከስተር ባለ መልክ አጥንተን ቀድሞ ያዛባነውን ውክልና(ሬፕሬዘንቴሽን/ representation) ለማስተካከል መጣራችን ያረካኛል:: ወደዚህ ሃሳብ እንዴት መጣሁ? (............)ሐሳፊነቱ የባለቤቴ የበረካ ነው:: የአንድ ደራሲ ወዳጄ ጎረቤት ነበረች:: ገና ከመጀመሪያ ሳውቃት እንደ ሌሎች ዜጎች 'ድንክ ነው' ብላ በመናቅ ሳታገለኝ እቤቷ አስገብታ 'ተቀመጥ:: ምን ልጋብዝህ?' አለችኝ:: (............)በውበቷ ተማርኬ ነበር:: ገና ሳያት ፍቅር እንደ ያዘኝ ገብቶኝ ነበር:: ምንም መመለስ አልቻልኩም:: 'የሚበላ ትፈልጋለህ?' አለችኝ:: መልስ አልነበረኝም::(ሳቅ) 'ምሳዬን አልበላሁም......ኩላሊት ጥብስ ልበላ ነበር፣ አብረኸኝ ትበላለህ? ልስራ?' አለችኝ:: ቆንጆ ስትጋብዝ እምቢ ይባላል? አይባልም:: ካልክ ወንጀል ነው:: ማን ነው/ናት በደንብ የማያውቀውን/የማታውቀውን 'ተቀመጥ' ብሎ/ብላ ኩላሊት ጥብስ የሚጋብዝ/የምትጋብዝ? 'እሺ' አልኩ:: በግማሽ ሰዐት ሁሉ ደረሰ:: ኩላሊት ጥብሴን አንዴ እንኳን በእጄ ሳልነካ እንደ ትንሽ ልጅ እሷ እያጎረሰችኝ ጠግቤ በላሁ:: (............)ስስናበታት ያጎረሰኝ እጇን ከነለበሰው መረቁ አገላብጬ ሳምኩት:: ጣቶቿ ዛሬ ድረስ ለእኔ የፍቅር ምንጮች ናቸው:: ቅርባዊነት ወይም ተንካናኪ የመጣው ከዚያን ቀን በኋላ ነው:: የዚህ የኪነጥበብ ረድፍ ምንጩ ፍቅር ነው:: በመተሳሰብ ስለ መነካካት ነው:: የዚያን ዕለቱ ጉርሻ አንዳንድ መሰረታዊ የሆኑ ግን ችላ ያልኳቸውን ነገሮች እንዳጤን አደረገኝ:: መጀመሪያ ጉርሻ ምንድነው? አልኩ:: ቀላል ጥያቄ ነበር:: መልሱ ግን ሰፊ ነው:: (......) ይሄን በሚመለከት ለበለጠ ማብራሪያ ነቢዩ ጎበናን ብታነብ ደስ ይለኛል:: ጉርሻ የሚያቀራርበን ነው:: በጉርሻ ዐይኖቻችን የፈጠሩት ዕርቀት ይጠፋል:: በኋላ እንዳየሁት መጎራረስ ወደ ወሲብ የሚጠጋ ኢትዮጵያዊ ድርጊት ነው:: በማዕድ ዙርያ እንዲቀመጥ የተገደደው ተከፋፍሉ ግለሰብ የሆነው ቡድንና ማህበረሰብ በሚዘረጋው የበላተኛ እጅ ድልድይነት ይቀራረባል:: 'አብረን በልተን' ሲባል እውስጡ ከባድ የጉርሻ ይዘት አለ:: ጉርሻ አገናኝ አቀራራቢ ድርጊት ነው:: (............) ሌላም ዝርዝር ረድፍ አለው:: በርበሬና ሚጥሚጣ በመብላት ሂደት ውስጥ ዜጋ ያልበዋል:: በዚህም በእያንዳንዱ እንጀራ ሰበከት ላይ የአብሮ በላተኞችን የወዝ አሻራ ይታተማል:: ይሄ አስገራሚ የሆነ ግላዊ ማህተም ያለው (እያንዳንዱ ሰው የራሱ ከማንም ግለሰብ የሚለየው የጣት አሻራ ስላለው) የተቀናበረ ድራማ በሚጠጋ 'ማጉረስ' ተብሎ በተሰየመ ድርጊት ማሕበራዊ ቅንጅት ይከናወናል:: በጉርሻ ድርጊት የግልና የማህበራዊ አላማዎች ሳይጋጩ ይቀርባሉ::(............) ይሄ ሁሉ አማካይ ወደ ሆነው ብልት ወደ አፍ ያመጣናል:: ጉርሻ በአፍ መግባት አለበት:: የጉርሻ አጉራሽና ጎራሽ የሚረካከቡበት ታላቁ ቀዳዳ አፍ ነው:: ለሕይወት የሚያስፈልገው ምግብ የሚገባበት፣ ቋንቋ የሚሰራበትና ሰዎች በራሳቸውና በሌላው መሃል ያለውን ልዩነት የሚያጠቡት ወይም የሚያሰፉት(ሃሃሃሃ)

በአፍ ነው:: አፍን ሴቶችና ወንዶች የሚጋሩት ቀዳዳ ነው:: ይሄ ማንዛቤአችንን ጠንካራ ሁለንተናዊነት ይሰጠዋል:: ጎራሽ አፉን ሲከፍት አጉራሽ ሕይወት እንደሚሰጠው እምኖ ነው:: እኔና አንተ፣ አንተና አንቺ.........ወዘተ በስምረት ውስጥ የሚጠፉበትና 'እኛ' የሚሆኑበት ነው:: የቦታ ዕርቀት የሚወድምበት ነው:: (............) አብረው ተቀምጠው ሲበሉ የማይጎራረሱ ሃበሾች ቁጥራቸው ከበዛ ኢትዮጵያ የምትባል እንደሌለች ወይ በመለወጥ ላይ እንዳለች ምልክት ነው:: ይሄ የሚያሳየን አንድ ቅራኔ የባህል ሕልውናችን ውስጥ እንደተከሰተ ነው:: አንዳንድ በቅርብ መወለድ የጀመሩ ልምዶቻችንን እዚህ ባጭሩ እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ:: እዚህ አዲስአባ ውስጥ አንዳንድ ቦታ እንጀራ በቢላ ሲቆረስ እናያለን:: ይኼን በቢላ የመቁረስ ባህል የጀመረው ማን ነው? ለምን ጀመሩ? እንጀራን በቢላ መቁረስ እንጀራን ወደ ዳቦ ለማውረድ መጣር እንደሆነ አልተረዱም? የእኛ ትልቁ ችግራችን ዕውር ኮፒ አድራጊዎች መሆናችን ነው:: ፈረንጅ ዳቦ ሲቆርስ ዐይተን ከዛ ያን በጭፍን ያለ ጥየቃ ያለ ትንታኔ ተበደርን:: የዚህ ችግር መነሻው በራሳችን ማመን አለመቻላችን ነው:: በራሱ የማያምን ሕዝብ ወደ ባርነት የሚንዝ ነው:: ተነካናኪ የስዕል አጣጣል ንቅናቄ አላማው ባያያዛችን ባሮች መሆን ባይቀርልንም የመሆኛ ጊዜውን የማዘግየት ነው:: ቢያንስ ስለ ራሳችን እያወቅን ራሳችንን በቁጭት እየነቀነቅን ወደ መቃብር እንድንወርድ ነው:: (............) ለመሆኑ እንጀራ ለመቁረስ እጅ አነሳትና ነው ቢላ የመጣባት? በእንግሊዘኛ አቨርኪል (overkill) ይባላል:: ዝንብ ለመግደል ታንክ ስታወጣ ማለት ነው:: እንጀራ ቢደርቅ እንኳን አይፈነክትም:: እንጀራ ጥፊ እንኳን አይሆንም:: ምኑ ሰይፍ ያስመዝዛል? ግን እንጀራ አገር ያቆማል:: ይሄ እያኖ የሚያምር ነው:: አሁን አሁን ወደ ሕብረተሰቡ በደንብ የቀረብኩ ይመስለኛል:: አንዳንድ ሰዎች ሶሻሊስት ሪያሊዝም ነው ይላሉ:: የምስላቸው ሰዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ኢትዮጵያዊነት ያለበትን የገባበትን እላይ የጠቀስኩትን ቀውስ ለመፍታት መሞከር ነው ስራዬ:: ግለኛነትም አይደለም:: የእኔ ሕይወት ለሌላው ምሳሌ ነው:: በሁለት በኩል የተባደኑትን የስሜት ሕዋሳት አንድ ላይ ለማምጣት ነው ሃሳቤ:: በባህሌ የሚሳሉትን ትላልቅ ዐይኖች ለማሳወር አይደለም:: ከአብስትራክት ኤክስፕረሺንዝም ወደ ተነካናኪነት ወይም ቅርበኛነት የመጣሁት አሁን ያለውን የግልብ ፖለቲካ ፋሽን ተከታይ ሆኜ አይደለም:: ብዙዎቹ ስዕሎቼ ከተሳሉ ከርመዋል:: አይገናኝም:: ሲገባኝ ኪነጥበባችን በትንሹም ተንባይ ሊሆን የሚችለው ይሄን የርቀትና የቅርበትን ክፍፍል ሲያቃልል ወይም በሃቲታዊ መንገድ ጭምቀት ወይም ሲንቴሲስ ሲፈጥር ነው::

<u>እ.ሌ.:</u> ባለፈው ሁለቱ ኤግዚቢሽኖችህ <u>በ '18'</u> እና <u>'እንደገና 18'</u> በተባሉት ውስጥ ሁለት ሴቶች እንደ ሞዴል ተጠቅመሃል:: እንዳየነውም በተለያየ ደረጃ እነዚህ ቆንጆጆች ገላቸውን ያሳዩናል:: ታዲያ የአንዳንዱ ግልፅነት በቅርብ 'ይታተም' ወይስ 'አይታተም' እየተባለ ከሚያከራክረን ሁለት ምዕራፎቹን በመፅሔት ካነበብነው ከደራሲ ገብሬ ገብርዬ *'ቃይ ሌሊት'* ልብ ወለድ ጋር የሚያመሳስሉት አሉ፣ አንተ ግን በሌላ ቃለ መጠይቅ 'አይመሳሰልም' እንዳልከ ሰምቼአለሁ:: ብታብራራልን::

<u>መ.ገ.:</u> *በቃይ ሌሊትና* በ18ቶች መሃል ያለው ልዩነት የዕውቀትና የፐርፎርማንስ ነው:: *ቃይ ሌሊት* ግልፅ የወሲብ ቋንቋ ይጠቀማል:: ይሄ በአገራችን የተለመደ አፃፃፍ አይደለም:: ስላልተለመደ ኋላ ቀር ነን ማለትም አይደለም:: ከባድ የስለላና የጭቆና ስርዐት ባለባቸው አገሮች የዚህ ዐይነት የወሲብ ግልፅነት አለ:: እንደውም እንዲኖር ይገፋፋል:: ስለዚህ ግልፅ የወሲብ ቋንቋ ማስክ ማለት ጭምብል ሊሆንም ይችላል:: 'ግልፅ' የሚለው ቃል የተራማጅነት ወይም የቀዳሚነት ምልክትም አይደለም:: ወይም 'እንደ ወረደ' ማለት ኩመካ ነው:: ማንም ስነፅሑፍ በአርትኦት ጎዳና ነው የሚያልፈው('ግብታዊ' የተባሉ ድርሰቶች እንኳን ከመነበባቸው በፊት በእታሚ/በአርታኢ 'ይነካካሉ'):: ቀይ ሌሊት መዋቅር ያለው ልቦለድ ነው:: መዋቅር እንደ ወረደ አይመጣም:: ቅንነት ቢርበንም እዚህ ድረስ አንሸወድም:: 'እንደ መጣልኝ ፃፍኩት 'ብሎ ሸወዳ የለም:: እንደወረደ የሚመጣው ያለቀ መዋቅር እግዜር ሲሰራው ብቻ ነው:: እኔ አጠቃላይ ማህበራዊ ሁኔታን ነው የማየው፣ የሴትና የወንድ ብልት ብቻቸውን ቦታ የላቸውም:: በቅዱስ መፅሐፍ ከወሲብ በፊት ጉርሻ ነበር:: በለስን መብላት:: እስፈሪውና ሰው የተነፈገው ዕውቀት ነበር:: ያን ስጦታ መጠቀም አለብን:: የእኔ ስዕሎች ጥናቶች ናቸው:: አላማዬ ዕውቀት የመስብሰብ

ነው:: *ቀይ ሊሊት* የውስት ድርጊት ወይም ኮፒ ፐርፎርማንስ ነው:: (...........) ለምሳሌ በእኔ አንድ ስዕል 'ከቁርስ በፊት' በተባለው በጎን የተሳለች ሴት አለች:: ይህቺ ሴት የውስጥ ልብሷን ታወልቃለች ወይም ትለብሳለች:: ውስጥ ልብሷ ሳይሸፍናት በፊት በጨረፍታ ግልፅ ባልሆነ መልክ የአፍረቷን ፀጉር እናያለን:: ከሴቷ አጠገብ (foreground) አንድ ሰውዬ ራቁቱን ተኝቷል:: የምናየው ግን ከወገቡ በላይ ነው:: እዛ አልጋ ላይ ምን ይደረግ እንደነበረ ወይም ምን ሊደረግ እንደ ታቀደ ነጋሪ አንፈልግም:: በተለያየ መጠን እናውቃለን:: ሁለቱም የስዕል ኤግዚቢሽኖቼ 80 በመቶ የዚያን ጊዜ ወዳጄ ከነበረችው ዛሬ ባለቤቴ ከሆነችው በረካ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው:: መነሻዬ ናት:: ዕውቀትና ጥናት ነው:: *ቀይ ሊሊት* ግን ፐርፎርማንስ ነው:: የገብሬ ገብርዬን *ቀይ ሊሊትን* ከማንበብህ በፊት የእኔን ስዕል ማየት አለብህ:: ዕውቀቱ ይቀድማል:: ዕውቀት ሂደት አለው:: በማወቅና በፐርፎርማንስ መሃል አፍታ ወይም የጊዜ ክፍተት አለ:: (...........) *የቀይ ሊሊትን* ፐርፎርማንስ የቀደመው ነገር የለም:: በፐርፎርማንስ ካልሆነ በምን እናውቃለን? አይነት ጥያቄ ሊኖር ይችላል:: ልምድ እኮ ፐርፎርማንስ ነው ከማለት በመነሳት:: ታያለህ፣ ታውቃለህ እና ታደርጋለህ:: እነዚህ በአንድ የጊዜ ነጥብ ውስጥ ተደራርበው ሲከሰቱ ሰብአዊ ሳይሆን መለኮታዊ ናቸው:: ለምሳሌ ስዕሎቼ በአብዛኛው የአንዲት ሴት ናቸው:: ይህቺ ሴት 'ገበና' የሚባል የገላዋን ክፍል አታሳየንም:: ግን የገላዋ ክፍሎችን ለየብቻቸው እናጠናቸዋለን:: መጀመሪያ ትንታኔ ነው ወይም ብትንታኔ በለው:: ይሄ ሁሉ ግን በኋላ ይሰበሰባል ይሄን 'ስብሳቤ' በለው:: ለምሳሌ በ18 ውስጥ ያለው እንደ መነሻዬ የምቆጥረው የመጀመሪያው «የአለፈለገ ሰላም ጋቢ» የተባለው ስዕሌ የሴትዮዋን ጀርባ የሚያጠና ነው:: የሴቶቻችን ጀርባ ተጠንቶ አይታወቅም:: ትዝ ይልህ እንደ ሆን ስስ ቀሚስ ደርባለች፣ ባቷና ቂጥዋ ይታያል:: በግልፅ ግን አይታይም:: ከፊት ለፊቷ ጋቢ አለ:: ጋቢ እያሰጣች ነው:: ጋቢ የምታሰጣ ሴት አገራዊ ናት:: ቀሚሷ ረጥቦ ገላዋ ላይ የተጣበቀ የቂጧ ክፋሎት የሚታይ፣ የውስጥ ሱሪዋ ዝርዝር ብሎ የሚታይ፣ ባዶ እግሯ ጭቃ የሆነ ከአጥር ጀርባ ብዙ ጊዜ የምናገኛት የአገሬ ልጅ ናት:: አይደል?(...........) ሌላ ምሳሌ ልስጥህ:: 'ባለጎፈሬ' በተባለ ስዕል ላይ ይህቺው ሴት ፀጉሯን ስትታጠብ እናያለን:: እዚህ ስዕል ላይ የምታየውን ፀጉር የተበደርኩት ከአባይ ፏፏቴ ነው:: የአባይ ፏፏቴ ፀጉሯ ነው:: ይሄ ስዕል በጣም ተወዳጅ የነበረ ነው:: ተወዳጅ የነበረበት ምክንያት ፀጉሯ በእርጥበት የሚንጀላጀል አንገቷና ደረቷ የረጠበ የኢትዮጵያዊ ሴት ስዕል ተመልካቾች አጋጥሞአቸው አያውቅም:: 'እርጎ' የተባለውን ከሁለተኛ ኤግዚቢሽኔ ምሳሌ እንውሰድ:: ይሄ ስዕል ላይ በአብስትራክት ኤክስፐረሺንዝም ተፅዕኖ ስር በመጠኑ የወደቀ የልጅቷ ምስል አለ::(...........)ልበልህ በአገራችን አንዲት ቆንጆ ስትወደስ ቁንጅናዋ ከማን ጋር ይወዳደራል? ብዙ ጊዜ ከማርያም ጋር:: ማርያምን አንበናታል በመልካ ማርያም ወይም በስዕሎቻችን ላይ አይተናታል:: ፈረንጆች (እንዲህ ዐይነት ማወዳደር ባልወድም፣ ልገደድና) 'እንትና ኤልዛቤት ቴይለርን' ትመስላለች፣ 'እንትና ባርዶን' ትመስላለች ወይም 'ቬኑስን ትመስላለች' ይላሉ:: የእኛ ሴቶችስ? አስበኸዋል? ለምን መሰለህ? ከጊዜ፣ ከታሪክ ጋር የተገናኙ ታላቅ እንስቶች ኪነታችን አልወለደም:: ኪነታችን አልፈጠራቸውም:: እንተኛቸዋለን እንጂ አላወቅናቸውም:: ወደ ዋናው ጉዳይ ልመለስ (...........)ከፈጠጠ ደፋር በሆነ መልክ ይህቺ ቀደም ብዬ ያነሳሁልህ 'እርጎ' ላይ የተሳለች ሴት ግራ ጡቷን ብቻ ታሳየናለች:: ግራ ጡቷን በግራ እጇ ከስሩ አቅፋ ይዛ የስዕሉን ተመልካች በምናቀውና በባህላችን በተመዘገበው በትልቁ ኢትዮጵያዊ ዐይን ታየናለች:: ጡቱ ፎቶግራፍ ይመስላል:: ዝርዝሮቹ በሙሉ የትም ብትኖር ለጠይም ልጅ ፍቅርና አድናቆት እንዲሰማህ ያደርጋሉ:: ይሄ ባለቤቴ የመጀመሪያ ልጃችንን ልትወልድ አንድ ወር ሲቀራት የሳልኳት ነው:: ሁለት መልዕክት አለው:: አንደኛ እናትነትን ያሳያል:: የጡቷ ጫፍ ላይ የምታየው ነጭ ፈሳሽ የዕውን የነበረ ነው:: ከዚህ ጡት የምታገኘው ግን ወተት አይደለም እርጎ ነው:: እርጎ መርጋት ነው፤ በዕውቀትና በድርጊት መሃል እርጋታ የመውሰድ ነው:: ማሰብ ነው:: ማሰብ ወደ ልብ መግዛት የሚወስደን ነው:: ሁለተኛ ለወሲብ ተመልካቹን ሁሉ የምትጋብዝ ይመስላል:: ከዚህ ግብግ በፊት ግን 35 ስዕሎች ነበሩ:: እውቀናታል:: ከሻፊድን በትክክል ነው:: ስዕሉን በእጃቸው ለመንካት የሞከሩ ተመልካቾች እንዳየ አንድ አሊያንስ ፍራንሴ የሚሰራ ወዳጄ ነግሮኛል:: ብዙ አንባቢዎች በጋዜጣ 'የመስኮትን 'እርጎ' የተባለ ስዕል ካየን

**ትምህርት ቤት በነበረው ኤግዝቢሽን ያቀረበው አንድ ስዕል ትልቅ ጉርሻ ጎርሳ ዐይኖቿ በዚህ ሰበብ ያነሱና ሊጠፉ የደረሰች እማማን ነበር:: በእኔ ግምት ሰዐሊ**

---

ጀምሮ ጠይም ወደድን ይላሉ ሃሃሃሂሂ::

<u>ኢ.ሌ.:</u> ጋቢው 18 ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አለ:: ለምን?

<u>መ.ገ.:</u> ጋቢ ማሕበራዊ አውድ ነው:: ማለት ኮንቴክስት ነው:: ስዕሉ የግሌ ትዝታ ነው ግን የተጠቀለለው በጋቢ ነው:: የአገሬን ልጅ ከባህሏ አውጥቼ ማየት አልፈልግም፣ ለምሳሌ ከቤቶች ጋር ማዕድ ከተቀመጥኩ ካላጎረሱኝ እቀየማለሁ:: እለምናለሁ::

<u>ኢ.ሌ.:</u> እንዲያጎርሱህ ትለምናለህ?

<u>መ.ገ.:</u> ምን አለበት:: ያን ያማረ እግር አይተህ አትለምንም? ሃሃሃሃ

<u>ኢ.ሌ.:</u> ሃሃሃሃ ከገብሬ ገብርዬ ጋር በዚህ ምክንያት አልተስማማችሁም ይባላል:: ምን የማያስማማ አለ? ስዕልህ በቴክኒክ ጠንካራ ቢሆንም ወግ አጥባቂ ነህ ይባላል::

<u>መ.ገ.:</u> ዕውቀት ይቅደም ነው ያልኩት:: ያውም ሰፊ ዕውቀት:: ከአትኩሮት ጠባብነት እንውጣ ማለቴ ነው:: ከደቃቃዊነት (minimalism) ወይም አሹራዊነት (ከአስሩ አንዱን ብቻ ማየት) ለመሸሽ ነው:: በሌሎች አገሮች እዚህ *ቀይ ሌሊት* ዐይነት ስራ ከመድረሳቸው በፊት ታላላቅ ስራዎች ተደጋግመው ተሰርተዋል:: ድልድዩ አልተገነባም:: ለምሳሌ ስለ ቅኔ ብዙ እናወራለን ግን ስለ ቅኔና ስለ ግጥም የተፃፉ የጥናት ነገሮች አሳዩኝ:: አባባሌ ገባህ? በግዕዝ ብዙ አቀኞችንት እንዳለ እንሰማለን እነዛን ወደ አማርኛ አሸጋግረናል? ምንስ ይመስላሉ? ትልቅ ታሪክ አለን ይባላል:: እንደዚያ የሚል ሕዝብና ምሁር በተከለፃድቅ መኩሪያ ሁለት ሶስት መፅሐፎች ብቻ አይቆምም:: ዕውቀቱ የለም:: ወይም ይሄ ዕውቀት የተባለው ነገር ማብራሪያ ሊሰሩልን ባልቻሉ ጅምላ አውሪዎች ቁጥጥር ስር ነው:: ስዕል ቢያንስ ከፅሁፍ የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው ያለው:: ሰዐሊዎች ድልድዩን እየሰሩ ነው:: ዘሪሁን፣ እስክንድር ድልድይ ሰሪዎች ናቸው ከሌሎችም ጋር ሆነው አዲስ ፓራዳይም(የአመለካከት ዕቅድ) እያበጁ ነው፣ ስነጽሑሁፍ ግን የለንም:: ምናልባት ዳኛቸው? ምናልባት ፀጋዬ:: በአማርኛ ተፅፎ በእንግሊዘኛ ሂስ የሚሰጥበት ዓለም ነው እኮ ያለነው:: ንቅናቄ የለንም:: ደብዛዛ ነገር ነው:: ያሉትም ስለ ፍልስፍናቸውና ስለ ቴክኒካቸው ሳይነግሩን፣ ሳያስተምሩን እንዳያልፉ ነው የምፈራው:: ስለዚህ ለእኔ *'ቀይ ሌሊት'* ጋሪ ነው ከፈረሱ የቀደመ:: በማህበራዊ የድርጊት አለም ውስጥ ተስተካካዩ ምሳሌ የተማሪዎች ንቅናቄ ይመስለኛል:: *ቀይ ሌሊት* የተማሪ ንቅናቄ በጋለበት ሰሞን መፃፉ የመመሳሰሉ ምልክት ይሆን? የአገሬቷን ሕብረተሰብ የምትለውጠው 'ጭቆና' በሚል ካልተጠናና ካልተብራራ ፅንሰሐሳብ ወይም ኮንሴፕት ተነስተህ አይደለም:: እዚህ ፕላኔት ላይ ጭቆና ያሌለበት ቦታ የለም:: የበለስ በይዎች ዝርያ ነን:: ግን ያለህበትን ማወቅ አለብህ:: ምንድነው ጭቆና? ኋላ ቀርነትስ? ምን ዓይነት ባህል አለን? ጠላታችን ማን ነው? የጠላታችን ጠባይ ምን ዓይነት ነው? ከዚህስ ጋር ተያይዞ የመንግስታችን ጠባይ ምን መምሰል አለበት? ቋንቋችንስ? ቋንቋችን ውስጥ ምን የተደረገ ነገር አለ? የውስጣችን የባህል ሲነርጂ ምን ይመስላል? የባህል ውርስት ጥናቶች አሉ ወይ? ከውጭው ዓለም ጋር የምንቀራረብበት ሊቃዊ መንገድ ምንድነው? ወዘተረፈ......ብዙ ጥያቄዎች አልተመለሱም በጥናት ማለቴ ነው.....

<u>ኢ.ሌ.:</u> *'ቀይ ሌሊት'*ን ጥናት ነው የሚሉት አሉ

<u>መ.ገ.:</u> አይመስለኝም:: በድርጊት ጀምሮ በድርጊት ያልቃል:: ባለታሪኮቹ ፈረንጅ ሊሆኑም ይችላሉ:: ካመሉትራን ያነበቡ፣ ዘ ፐርፌዩምድ ጋርደንን ያነበቡ ወይም ሄነሪ ሚለርንና አናይንስ ኒን ያነበቡ፣ ማርኪ ደ ሳደን ያነበቡ የሚያመጡት ነው:: ሜካኒስቲክ ነው:: እንደኛ ባለ አግላይና መራጭ፣ እንደገና ኋላቀርና ጎጠኛ ሕብረተሰብ ጥናት ይቀድማል:: በመጀመሪያ ቢያንስ ቢያንስ በጥንት ጊዜ የነበረውንና የረሳነውን ምሉዕ ዕውቀት እዚህ ማምጣት አለብን:: እስኪ ዘርአያዕቆብን እናጥና:: 18 ወደ'ዛ በትንሹ ይመልሰናል:: ስለዚህ ለእኔ ጉርሻ ቀላል ድርጊት አይደለም:: በመውደቁና በመነሳቱ ውስጥ ጨለማና ብርሃን አያለሁ:: የባህሌን መውደቅና መነሳት አያለሁ:: ጉርሻ ለእኔ እንደ ሐይማኖት ቀኖና ነው::

<u>ኢ.ሌ.:</u>አመሰግናለሁ

<u>መገ:</u> እኔም

(አ)

ስለ መብላት ሲስል ስፖርተኛ ደ'ሞ ለጤንነቱና ለጥንካሬው የዕውነት መዓት መብላት አለበት:: ዝንደዳ[8] አይደለም:: ምን ያህል በላሁ ያን ቀን? ሁለት እንጀራ ተኩል በዶሮ ወጥ ከሁለት ቅልጥም ጋር፣ በጣም በመቀቀሉ ባዘቶ የሆነ አንድ የበግ እግር (ከመጨረሻው ይገፔ ቀጥ አድርጌ ትሪ ላይ ስይዘው ስጋው በውሃ እንደ በሰበሰ በራሱ ክብደት እንደሚወልቅ ቦላሌ ሱሪ በጉልጥምቱ ላይ ወደ ታች ይገፈፋል)፣ ሦስት የተቀቀሉ መረቅ የጠጡ ዕንቁላሎች፣ ይኼ ሁሉ ሆዴ ውስጥ ተሰባስቦ ካበቃ በኋላ እንዳይንቦጫቦጭ ተክሎ የሚይዘው እንደ ሸክላ የደደረ የድፎ ዳቦ ስባሪ(ከገባ በኋላ ቀልጦ ሲሚንቶ ይሆናልና):: ሆዴ ደ'ሞ እህል ገብቶበት የሚያውቅ አይመስልም:: አንዳንዴ የተቦረቦረ ጭን ባትና እግር ያለኝ......ይኼም የተቦረቦረ ገላ ከሆዴ ጋር በደም ስር ሳይሆን በቱቦ የተያያዘ...... እና የምበላው እህልና ሥጋ ጥቂት ሰዓታት ሆዴ ከርሞ እየተንሸራተተ ወደ ጭኖቼ የሚሔድ ይመስለኛል:: እየቆየም ከጭኖቼ፣ ከባቶቼና ከእግሮቼ በላብ ተመስሎ የሚተን:: ታዲያ ለምን ከበላሁ ከሁለት ሰዓት በኋላ መልሶ እንደ አዲስ ይርበኛል? ለራሴ ጉንጩን በጉርሻ አሳብጬ የምግቦቹን አካሄድ በባለጌ ምናቤ እየቃኘሁ እስቃለሁ::

ከቤት ወጥቼ ሻይ ለመጠጣት ምናልባት ከጓደኞቼ አንዳንዶቹን ባገኝ ብዬ ፒያሳ ለመውጣት (እዛችው የለመድኳት ቼንትሮ ባር) ታክሲ ስጠብቅ ፀሐይ ያለ ይቅርታ ለግማሽ ሰዓት ያህል በጨረሯ ፊቴንና ሁለመናዬን መታችኝ......

እሁድ ሌሊት ለሰኞ አጥቢያ ከእንቅልፌ ባነንኩ:: ከንፈሮቼ እያሳከኩኝና እያቃጠሉኝ ቀሰቀሱኝ:: በዚህ ላይ ነሐስ ማጣመም የሚችል ራስ ምታት ግራና ቀኝ ጆሮ ግንዴን ይሰረስረኛል:: መምጫ ጎዳናው አለቀበት? በጆሮ ግንድ? የአባቴን መርዶ ብሰማ እንኳን ይኼ ዓይነት ራስ ምታት በጆሮዬ በኩል አይመጣብኝም:: የራስ ምታቱን መነሻ ባላውቀውም ከንፈሮቼን ግን ምች እንደመታቸው ገባኝ:: አካክኬና ተበሳጭቼ ተመልሼ ተኛሁ:: መኝታ ቤቴ ሰርቪስ ቤት ውስጥ ነው:: ሰርቪስ ቤቱ አራት ክፍሎች አሉት:: የእንግዳ መኝታ፣ ማድቤት፣ እኔ የምተኛበት ክፍልና እና ወና:: ወናው ያረጀ ቁሳቁስ ማጎሪያ ነው:: በሕልሜ እሱን አዕድቼ ደክሞኝ ሳለከልክ ነበር:: በሕልሜ ያፀዳሁት እዚህ ወና ክፍል ውስጥ እጥግ የሆነ ጨለማ ስርቻ ጠይም ቀጭን ልጅ ጀርባዋን

8 በደራሲ ገዳም ማርታ ከተፃፈው መፅሐፍ ተመዞ የወጣና በዚያን ሰሞን ፋሽን ሆኖ ሲጠቀስ የነበረ ቃል:: 'መዘንደድ' ማለት 'ዘንዶ' መሆን ማለት ነው:: ዘንዶ በገዳም አባባል በልቶ ጠጥቶ የሚተኛ ማለት ነው:: 'ዝንደዳ' በጭራሹ አገርን መርሳት፣ ለአገር የሚችሉትን አለማድረግ፣ ግን የአገሪቷን ምግቦች እያሳደዱ በመብላት በዛ ብቻ ዜግነትን ለማሳየት መጣር ማለት ነው:: ገዳም 'መዘንደድ' ከህዲ መሆን ነው ይላል:: ገዳም በአባቱ ስም አይፅፍም:: 'ገዳም አባተ' ተብሎ ከመጠራት፣ የባለቤቱን ስም እንደ አባቱ ስም አድርጎ 'ገዳም ማርታ' መባልን መርጧል:: በዚህ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል ገዳም ገፀ-አስቀያሚ ቢሆንም ብዙ ሴት አንባቢዎች የነበሩት?
ገዳም መፅሐፉ አንድ ምዕራፍ ውስጥ እንዲህ ይላል:
«......የምናደርገው ነገር ቢኖር የልኳንዳ ስጋ በርካሽ ገዝተን እምብርታችን እስኪ ፈርስ እሱን በልተን በየአልጋችን መውደቅ ነው:: የዚህ ድካም ሲያልፍ እሷና እኔ፣ እኔና እሷ ይቀጥላል:: እሱና እሷ ይቀጥላል:: ጠላት መጥቶ በር አንኳኩቶ አገራችንን ቢወስድ አንሰማም:: ይሄን 'ዝንደዳ' እለዋለሁ::» ከ ገዳም ማርታ <u>የጨርቆስና የአገርሽ ዛንታ: ግልፅ ደብዳቤ ለአዲስ አባ ጃሌዎች</u> 1978 ኩሉ አሳታሚዎች:: ገፅ 111(አ)

ወደ እኔ አዙራ ተኝታ አየሁ:: ራቁት ሰውነቷ ላይ በሰረሰሯ መስመር በቾክ 'ኤፍሬም' ተብሎ ተፅፎአል:: ፊት ለፊቷ የሆነ ነገር እንደሚጠብቅ ሁሉ ሒጂ ቁጭ አልኩ::

ማነው ኤፍሬም?

እኔ:: ይኼን የምፅፈው ልጅ::

**ሰኞ**

ጠዋት ስነሳ ከንፈሮቼ አብጠዋል:: ለምቦጬ በግራ በኩል ተነፍቶ ውሐ ቋጥሯል:: ለመፈተሽ በአመልካች ጣቴ ስነካው ውስጡ ፈሳሽ ሲውለገለግ ይሰማኛል:: ስፈጠርም ከንፈረ-መልካም አይደለሁም:: 'ለምቦጫም' ከመባል በማርያም ልምምጥ የቀረልኝ ነኝ ('እባክህ እሱን እንኳን በልክ አድርግለት' ብላው......ፈጣሪን):: አሁን በማበጡ ከለምቦጫም አልፌ አህያ መስዬአለሁ:: ኩረሪማ እንዲህ ሆኜ እንድታየኝ አልፈልግም:: እንዲህ በተበላሹ ከንፈሮች የሚያምሩ ከንፈሮች ካሏት ልጅ ጋር በመሃል ከተማ 'ተወረገረግኩ' ማለት ይከብዳል ('ተለናጨጭኩ' ሊሆን ይችላል/ ከለንጨጭ የመጣ):: እሷም መተረቻ ትሆናለች ('ኮረሪማ ከከንፈር ጋር ፒያሳ ዋለች'):: ለዛሬ ብቻ ሳይሆን በምቾ ማበጡ የከንፈሬ የወደፊት ዋና ታሪኩ ሊሆን ይችላል:: (ቆይቶ በትዝታ ወሬ፡ 'ያኔ ከንፈርህ እንዲህ ያበጠ (ቡጢ እያሳዩ) ዕለት ተገናኝተን......' ተብሎ ትዝታው የሚቀር......አውቶሚክ ቦንብ እንደተጣለባቸው ሂሮሺማና ናጋሳኪ በአሳዛኝ የታሪክ ትዝታ ረድፍ የሚሠፍር):: በመጀመሪያ ዕለተ-ቀጠሮ በምቾ የቆሰለ ከንፈር ይዞ በከተማው መንጦልጦል 'የጠበሳን' ኪነትና ስም የሚያንቋሽሽ ነው:: ግን ቃል ደሞ መከበር አለበት:: 'የተናገሩት ከሚጠፋ ያሳደጉት......' ነው ያሉት ሽበቶዎች? (እየዋሹ ሲያረጁ ብናያቸውም በተረት ግን ሊያርገበግቡን):: ታዲያ......

ታዲያ ኩረሪማ ቤት ግንብ ሥር ቆሜአለሁ:: እወዲያ ወደ ግራ የሚያልፍ አሮጌ ፔገጕ ተሰብሮ ሞተሩ ይጨሳል:: ባለቤቱ ጠበቃው ታደሰ ፍቅረ ስላሴ ነው:: የሚጠብቀው ነገር እንዳለ ሁሉ ወገቡን ይዞ ወዲያ ወዲህ ይላል:: ያቺ ቁሊ ሚስቱን ሎሚ ሽታን ጎረቤታችን አስናቀ ወስዶበታል ይላሉ:: አንዳንዱ ሲበሳጭ (በመኪናው ይሁን በሚስቱ) ዝም ብሎ ወገቡን ይዞ ወዲያ ወዲህ ይላል:: ሌላው ወዲያ ወዲህ የሚለው መንገደኛም ፋሲካን ያሳለፈ አይመስልም:: ትንሽ መጥገብ እንኳን አይፈለቅቀውም እንዴ? ከኩረሪማ ቤት ድምፅ እሰማለሁ:: የድንች ጥብስ ይሸተኛል:: *ፋሲካው አልቆ በምኔው ድንች ውስጥ ገቡ?* በሀሳቤ የተንገለጠጠ የከሰል ፍም ላይ ድንቾች ከነጥብቋቸው ሲድበለበሉ ታየኝ:: ሦስት......የእኔን ቡጢ የሚያካክሉ ድንቾች:: አንድ በጥልቅ ተጠብሳ የጠቆረች፣ አንድ የተጀመረች ገና ቢጫነቷ ያልጠቆረ፣ ሦስተኛዋ አንድ ጐኗ የጠቆረ:: ኮረሪማ ለባብሳ ተቀምጣለች:: እናቷ ድንቾቹን በማንኪያ እያገላበጠች፡

«የት ልትሔጂ ነው የለባበስሽው?» (ለምን ይለባብሳሉ? ለምን ያስጠማሉ? ቤት የምትጠርግ መስላ ወይ ተጠርጋ የወጣች ቆሻሻ መስላ አትመጣም? ጉዳዩ ደረቷ ላይ ያሉትን ቁልፎች አርፈው ከተቀመጡበት የማላቀቅ፣ የገጠሙ

ከንፈሮቿን በከንፈሮቼ የመክፈት እንጂ የላውንደሪ ባለቤቶችን ወይም የልብስ ሱቆችን የማወዳደር አይደለም)

«እስኪ የበሰለውን ስጪኝ» ትላታለች ኮረሪማ አለ አይደለ የወሬ አርዕስት ለመለወጥ::

ይኼኔ አፏጫለሁ:: ስህተቱ የቴክኒክ ይሆናል:: ዕቃ ሲያንጋጉ ባፏጭ ወይ ማራኪ ወሬ ይዘው ባፏጭ ወይ እያናወዙ ባፏጭ ድንች ይወዳሉና (አለ ነገር የፋሲካውን ስጋ ቶሎ አልረሱም) እሱን ሲግጡ ባፏጭ ባይሰሙ ስህተቱ የማነው?

ግን አልቻልኩም::

አልቻልኩም::

ከንፈሮቼን በጡጦ ቅርፅ መሰብሰብ አልቻልኩም:: የመጀመሪያው ፉጨት የሚሰማው ለራሴ ብቻ ይመስል ነበር:: ከአፌ ላይ እንደ ላባ ቀስ እያለ በእፍረት አንገቱን ደፍቶ ሲወርድ በዓይነ-ሕሊናዬ አየዋለሁ ወይም በአባጣ ለንቦጩ ላይ እንደ ወፍራም ዘይት እያዘገመ ሲፈስ:: ቀስ ብሎ መሬት አርፎ የሆነች ጥቁር ድንጋይ ተደግፎ ወደ ባቡር ጣቢያ ተጠርጎ ለመሄድ ነፋስ ሲጠብቅ:: ሚያዚያ ደ'ሞ የት ነፋስ አላትና::

ሁለተኛ ፉጨት ሞከርኩ::

ሌላ ላባ::

ሦስተኛ......

ሌላ ላባ::

ከንፈሮቼ ላይ ያጎነቆለው በመግል የተሞላ ፊኛ ሲፈነዳ ሰማሁት::

ሂሮሺማ::

*ጳጉሜ 1987 ሆላንድ*

# የስብሐት ጢም[9]

## (ተረት ሠፈር)

ስብሐት ከዕንቅልፉ በድንገት ሲባንን በተከፈተው የበር ቀዳዳ በኩል እውጭ ያየው የነሐሴ ዝናብ የሚረግፍበት ግራጫ የተረት ሠፈር መልክአ ምድር ነው:: እያንዳንዱ ነገር ረጥቧል:: እንደ ሽንት ሳቦት የሚሰነፍጥ ቀዝቃዛ የደፈረሰ አየር ከተበጣ ቁስል እንደሚወጣ መግል ወደ ቤት ውስጥ ሲሳብ ለአተኮሩ ዓይኖቹ ይታየዋል፣ ለአፍንጫው ይሰማዋል:: ሌሊት ሲፅፍና ሲያነብ እንዳደረ ሲደክመውና መቀጠል ሲያቅተው ሳሎን ባነጠፋት (ማንጠፍ ማን አለ እንደ እሱ የሚጠሳ!) ረጋ ሰራሽ አልጋ ላይ በድካም እየተሳበ ሄዶ ነው የተኛው:: እስከ ትከሻው በዕድሜ ርዝመት ባዘቶ የሆነ ስፊ አልባሌ አረንጓዴ ጥለት ያለው ጋቢ ተከናንቦአል:: ይኼን ጋቢ ዛሬ ለብቻዋ ጨርቆስ ለምትኖረው ለመጀመሪያ ሚስቱ ለሳባ ከዝነኛው የተምቤን ሸማኔ ከአለማየሁ ሐጎስ የገዛው ነበር:: ይኼ ጋቢ (የጋቢ ነገረኛ) ሰበብ ሆኖ የዛሬ ሚስቱ ፋኖስ ላይ ተፎካካሪ ትዝታ እየቀሰቀሰባት ወይም ገና ለገና 'ይቀሰቅስብኛል' ብላ በመገመት፣ ባገኘችው አጋጣሚ ስብሐትን ፀባያቸው በሚለዋወጡ ዓረፍተነገሮች (ቀልድ፣ ምክር፣ የጋቢው አሰራር) እንደወረፈችው ነው:: ከማታውቀው የተማሪነቱ ዘመን አንከብክቦ ያመጣውንም ታጣፊ ሽቦ አልጋ አትወደውም:: 'የደራሲነት ዕብደቱ' ሲነሳበት እሷ ባልጠበቀችው ወቅት ከዋናው ከሚጋሩት አልጋ ወጥቶ ከዚያው ከሳሎን ጋቢውንም አልጋውንም አጣጥፎ ወደ ማይገኝበት 'የቢዝ

---

9 በዚህ ልብወለድ ውስጥ ስለ ስብሐት እውነተኛነት ያላቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው: የደረሳቸው መፃሕፍት አርዕስትና ጥቂት ይዘቶቻቸው፣ የሚኖርበት ሠፈር፣ ፈረንሳይኛ መናገሩና አልኮል መውደዱ:: ይህም ደራሲው ከስብሃት ለአብ ገ/እግዚአብሄር ጋር ከ1980 ዓም በፊት በነበረው ትውውቅ ያያቸው ቁንፅል መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው:: የተቀረው በሙሉ ፈጠራ፣ ስብሐትም ልዋጭ ነው::

ዓለም'[10] ውልቅ ብሎ የሚጠፋ ይመስላት ነበር። ታዲያ ይኼ ዓይነት ጋቢ እና አልጋ በትዘታ ለማንቋለጥ፣ በሆነ ሕልመ ዝሙት ለመንጠባረርና ስሚቷን በሾርኔ ለመውጋት ካልሆነ......ምኑ ይፈይዳል? ምኑ ይመቻል? ምኑ ይሞቃል? ስብሐትንም እዚያ ላይ በጠዋት ተጋድሞ ስታየው ልትነካው የማትፈልገው የዝተት ካብ ይሆንባታል። ታዲያ በር ፊት ለፊት ተተክሎ በብርድ የሚገረፈው ለሌላ ጠማማ ጉዳይ ካልሆነ ታትሞ ሳልታየ ልብ ወለድ ተብሎ!? ስብሐት ደ'ሞ ማንበብና መጫር ሲያዳክመው ሰበገናም ደረቱን በቀጫጫ እግሮቹ ተሸክሞ እዚህች የጋቢ ስብሳቡ ተንኳቶ ካልገባ ስራው የተጠናቀቀ አይመስለውም። እንደ መነኩሴ በአካል ካልተበደለ መንፈሱ ከሠፈረችበት ደንገዝጋዛ ጨለማ ወደ ብርሃን የምትመጣ አይመስለውም። በቤት ውስጥ ቤት ይሰራል። በድንኳን ውስጥ ድንኳን። ማንንም የሚጎዳ ነገር የሌላት በግሉ ለመተከዝ የምትመቸው ዔላም።

ፋኖስ ብዙ ጊዜ ልታበሽቀው፣ የረሳች አስመስላ በር ሳትዘጋለት ወደ ምትሄድበት ትሄዳለች። በዚህ በቀለጠ የነሐሴ ዝናብና ብርድ የበሩን ሁለቱንም ተካፋቾች (ግራና ቀኝ) እስከመጨረሻ በርግዳቸው ስትሄድ መዝጋት ረስታ አይደለም። ድንገት እሷን ሊፈልግ የመጣ እንግዳ ሰው ይኼን ስሙ-ጥር መሆን የጀመረ ደራሲ እንደ ምስኪን የተንጋለለበትን እንዲያየው፣ እናም ከመንገድ ኳስ አምልጧቸው ግቢ ውስጥ የሚገቡ ልጆች ያለጥንቃቄ በየቦታው የረገፈ ልብሱንና የእሱንም አሮጌ ጋቢ ስር ምስኪን አወዳደቅ ተመልክተው እንዲያጠኑና ወሬ አናኝተው የሠፈር መተረቻ እንዲያደርጉት ነው። በሩን ከፍታ ስትተወው መዝጋት ዘንግታ ወይም በቤት እመቤትነቷ ያደረውን አየር ልታስወጣና እፁብ አየር ልታስገባ አይደለም። አንዳንዴ ለብቻዋ ትል ነበር፡ 'በዚህ የውስጥ እጅ በምታክል <u>ደረትህ</u> የሳንባ ምች ገብቶብህ፣ በስርዓት <u>እንደ ሌላው ወንድ</u> እቤትህ አርፈህ ብትቀመጥ። እኔ የምልህን ሳይሆን፣ የምትሰማው <u>ድምፅ</u> ሌላ ነው......'። ይኼ ለአፍ ማላቀቂያ የአበሻ ሴቶች አጥር ተደግፈው ዝንብ ከፊታቸው ላይ እያባረሩ ወይ ከጠራራ ፀሃይ ለመጋረድ ነጠላቸውን ጭንቅላታቸው ላይ ጣል አድርገው መተላለፊያ መንገድ ዘግተው የሚወረውሩት ዕርግማን አልነበረም። ትንሽ ምኞት አለው። ታዲያ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ቤቱ መጥቶ እስከ ሌሊቱ አስር ሰዓት ዴስኩ ላይ የፊት ጭገሩን እያከከ ሲቀመጥ ሰምታዋለች። ምን ለመፍጠር ነው? ስታገባው ይኼ ጢም አልነበረውም። ከብዙዎች ጎልቶ የሚታይ ቁንጅና ነበረው። ከርሞ ከርሞ ጢም አወጣ። የሚሰነብት ጢም አልመሰላትም ነበር። ጢሙ ባደገ ቁጥር ከእሷ እየራቀ ሰፈሩን ዴስኩ አካባቢ አድርጎ ሌላ ወረዳ የሠፈረ፣ በሌላ አገር ፓስፖርት የሚንቃነቅ ሆነባት። ይኼን ይኼን እሷ አትወድም። ልዩ ነገር......በሐር የተጠቀለለ ከረሜላ አልጋ ላይ አስቀምጣለት.....በ'ጠራራ' ሌሊት በፍትወት የምትቀጣጠል ሚስትን ለቆ ለብቻ ጠረጴዛ ላይ ምን ያስደፋል ነው። ያጠያይቃል።

---

10 ሲቆፍ ፊቱ ላይ የምታይበትን መነኩለል አንዳንዴ እንደ ጨዋታ አድርጋ፡ 'ብኾ ያለብህ ትመስላለህ' ትለዋለች። እሷ በልቧ እንደ ስድብ የምትቆጥረው፣ እሱ ግን ኩመካ የሚመስለው። እሷ በቃሉ አጠቃቀም የተካነችበት ስለሆነ(ስለ ፈጠረችው) በተለያየ መልክ ትለዋለች፡ *'ቢ ዠ ማድረግ ፈለግህ?'* (መጻፍ)/ *'በር ሳንኳኳ አልለማህም? ቢ ዠ ዓለም ነበርክ እንዴ?'* /የምናብ ዓለምህ ወይም የድርሰት ዓለምህ ሄደህ ነበር?

## (ደረትህ)

ፋኖስ ስለደረት ስታስብ በዓይነ ሕሊናዋ የሚመጣው ለበን ነው:: ከእሱ መለያየቷ ትንሽ ይቆጫታል:: በመንገድ ላይ ሲሄድ ግዙፍነቱን የማያጤን የለም:: እንዲህ በዓይኖቿ ለክታው የማያልቅ፣ ቢያልቅ ሳምንት የሚወስድ ደረት ነው ያለው:: ጠጋ ብሏት ከላይዋ እያንዣበበ 'ፋኑዬ ደኽና ነሽ?' ሲላት ጡቶቿ እንደ ደረሰ የፓፓያ ፍሬ ከደረቷ ላይ ተንቀጥቅጠው ሊወድቁ ይቃጣቸዋል:: ለገሃር አካባቢ ካፌቴርያ አለችው:: ለምን ከእሱ ጋር ተስማምታ እንዳልቀረች አሁን ድረስ ይገርማታል:: ደብተራው ስብሐት ከቄስ ጋር ስለሚውል መስታድርት ሳያደርግባት እንዳልቀረ አንዳንዴ ትጠራጠራለች:: ግን ታስታውሳለች እዚያች የስብሐት ጠባብ ደረት ላይ ትንሽ ዞማ ራሷን አስቀምጣ አስደናቂ ሕልሞች እንዳለመች:: ያንበረከካት ደግነቱን ታስታውሳለች፣ ሰዎች ሁሉ በዓይኑ ሞገስ እንዳላቸውም አይታለች:: እሷ እሱን ስትወድ በሕሊናዋ የገነባችው ግን እሱ በአንደበትና በድርጊት ስብከቱ ያስተዋት በሰዎች መሃከል ተዋረድ የማውጣት ስልጣኔዋ ተመልሶ እየመጣ ያንገላታታል:: ወይስ የእሱን ትንሽነት እንድትቀበል ከክርስቶስና ከሰብአዊያን የሰበሰበው ሀሳብ ወይስ የደራሲ ተራማጅነት? አታውቅም:: ግን ዛሬ ተዋረዷ ረቆ ስለ ደረት ስታነሳ ሁሉ ለበንና የመሳሰሉት ትዝ ይሏታል:: በተለይ ለበን::

## (እንደ ሌላው ወንድ)

'እንደ ሌላው ወንድ' ስትል ለበንን ማለቷ ነበር:: ቤቱ ዘውዲቱ ሆስፒታል አጠገብ ነው:: ስለደረት ስታስብና 'ስለ ሌላ ወንድ' ስትናገር ለበን ትዝ አላት (ወይስ ለበን ትዝ ብሏት ከዚያ ደረት ትዝ አላት?):: ከተረት ሠፈር ዘውዲቱ ሆስፒታል ሩቅ አይደለም:: በእግሯ ወይ በታክሲ መሄድ አለባት:: ስብሐት እንኳን መኪና ሊገዛ የጫማው ጠረን ቅርኔው ከካዛንቺዝ ይጠራል፣ ከዛ ከባምቢስ:: ጠዋት ላይ (የቤቷን በር ግራና ቀኝ በርግዳ) ያን ለበን የተባለ ወንድ ልትፈልገው ወጣች:: ለበን የጠዋት ልማዱ የቤቱ ፎቅ በረንዳ ላይ ትንሽ ጠረጴዛ አስመጥቶ (የሞላለት) ቁርሱን ይበላና (የሁለት ዕንቁላል ኦመሌት፣ የሾላ እርጎ የለበሰ የተላጠ አንድ ድፍን ሙዝ፣ አረፋ የደፈቀ ትኩስ የብርቱካን ጭማቂ፣ ቡና በቅቤ(ከእናቱ የቀዳው ልማድ)፣ የተፈጨ ድንች፣ ኩርማን እንጀራ የለበሰች የግማሽ ጤፍ እንጀራ ፍርፍር ጓል፣ በግራ በኩል የሄራልድ ጋዜጣ እና ጋዜጣውን የተደገፈ አዲስ ፓኮ ዊንስተን ሲጋራ (ይኸቺ ናት ቁርስ):: ታዲያ ለባብሶ ከቤቱ እስኪወጣ እግሮቹን መከዳ ላይ ዘርግቶ ፊቱን ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል አዙሮ ፒጃማ የለበሱ በሽተኞች ይቆጥራል (የለበሰና ያልለበሰ:: ካለበሰ......'ያ ጥጋበኛ የማነው?' ብሎ ይጠይቃል ራሱን):: የእሱን ቤት ምቾት ስታስብ የጠዋት አልጋዋ ውስጥ ጠይም ገላዋ ተንዘረዘረች::

## (እና ድምፆችን)

ስብሐት ቀስ በቀስ በዕንቅልፍ ጥጥ የተደፈነ ጆሮው እየተከፈተ......

ፋኖስን ጠርቶ በር እንድትዘጋለት ያስባል......

ተረት ሠፈር ጋኔን እንዳደረባት፣ ራሷን እስክትስት የሚያገዝፋት ከሲታ መርካቶ ናት:: የማትሸጠው የማትለውጠው የለም:: ከሰው ጥሬ ስጋ እስከ ከብት ጥሬ ስጋ:: ሁሉ ሕይወቱን ለማዳን ለጦርነት ይወጣል:: ፋከራው ይቀልጣል:: ስብሐት የድምፅ ዱካ እየተከተለ እሱን እያዳመጠ ያስባል......

**......ቆርቆሮ ያለው!**[*11]

*(መልካም ድምፅ ያለው ጎረምሳ ይመስላል......ምናልባት ለሰንበት ለሰንበት ቅዳሴ እንደ ሚማር ዲያቆን ለማኝ ሳይከስ ተነስቶ ቃሪያ እየቆረጠመ ይለማመድ ይሆናል......አጋፋሪ እንደሻው ቆርቆሮ ሺያጭ ቢያጋጥማቸው ምን ይሉታል?......'ቆርቆሮ እየሸጥክ እዚህ ከምታልፍ በርትተህ ከሞት አምልጥ!')*

**......ጣሳ ያለው!***

*(የቅድሙ ሰውዬ ወንድም ወይም ዘመድ መሆን አለበት......ለምን አብረው ተቃቅፈው እየዞሩ አይሸጡም?)*

**......ጠርሙስ ያለው!***

*(ድሮ ወታደር የነበረ ነው......ይኼ ወንዳወንድ ድምፅ ሲጀመር ለወታደርነት የተሰራ ነው......ለምንድነው ይኼ ሰውዬ ሁልግዜ ተኝቼ የሚመጣው...... ለቀስቃሽነት አልቀጠርኩት......ጠርሙስ እንደ ማላደንቅ ያውቃል......መጠጣት እወዳለሁ ብርጭቆ መርጬ ግን አላውቅም......ከአፍ የሚወጣ እንጂ ወደ አፍ የሚገባ አያስረግምም......ይዘት አስፈላጊ ነው......የማይረባ ወደ ላይ የሚል ጠላ ከንፈሩ ወርቅ ቅብ በተነከረ ብርጭቆ ስጥተውኝ የሆንኩትን አውቃለሁ......ንጹህ የምንለባብሰው ትንሽ የምንደብቀው ነገር ቢኖር ነው.....'ሳይኮሎጂካል ኖቨል'[12] በአገራችን የማይታዩት ለዚህ ይሆናል......በልብወለድ መሳቅ የማንፈልገው ድንገት በጣም ከሳቅን ከላይ የለበስነው ምናምን ተተርትሮ ጀርባችን ላይ የበቀለው የተረት ሠፈር ዓይነት ቁስል እንዳይወጣ ፈርተን ይሆናል......በፀጥታ ወደ ሞት እየተጓዝን ነው......አቤት ስንክድ!! አቤት! እኔ ጠዋት ስነሳ በዚህ በር ቀዳዳ ማየት የምመኘው ቆርቆሮ ሊሸጥ የሚጮህ እንጎለ ጥፍር ጎረምሳ ሳይሆን ንፁሕ የለበሰች፣ ያልተረበሸች ሕፃን በልቡ-ቅን እናት ፀጉሯ......ሲጎነጎን ነው......የተራቆተ አማላይ ጭን......ሳንሱር የሌለበት ፍቅር......የትዕዛብት ጥላ ያላረፈበት ......)*

**......ደላላ ያለው በገመድ!***

*(በደላላ የታሰርን......አንተም እኔም......በሐር ገመድም አይደለ..... ያማረበት ነው እሱ በዚያ የሚታሰር......በጭንብል ያን በችግር የተከሰከሰ ፊቱን የጋረደ......ቆዳዬን ወስደህ ሽጥ......እዚያ ሚስቴ ናት ሕልሜን በዕትብቱ እንዳይወለድ አድርቃ የያዘች......ወይ ወደ ሞቱ እየጎተተችው......ደላላ እትብትና ቃጫ ሽጥ......ሐብታም ያደርግሐል ጃን......በሚያምር ብርጭቆ ጠላ ንፋ......የው መጭም የትም አትደርስ ......የእኔም ይኸቺ ብሽቅ ሚስትህ ትሁን......እንዳንተ*

---

11 * ይሄ ምልክት ያለባቸው ነጠላ መስመሮች ከበዐሉ ግርማ ልብወለድ ከደራሲው የተወሰዱ ናቸው::

12 ስነልቦና ላይ ያተኮሩ ልብ ወለዶች(እ)

*ሳትጮህ እንዳንተ 'አለሁ' ሳትል ከአደባባይ......ሕቡዕ ሆና ወደ ጉድጓድ የምትስበኝ.....)*

**......ፍራሽ አሳዳሽ!***

*(መቼ አርፈን የተኛንበትን......እንደ አጋፋሪ እንደሻው ምትን ለመሸሽ ስዞር ቤት ተኛሁና......ከሚስቴም ጋር ከተንደባለልኩ ከረምኩ......ፍራሹ ለጋ ነው......በአፍንጫዬ አትራስ ላይ ስተከል የማሸተው ሳሙና ነክቶ የለቀቀው ተንዳሆ ነው......ከፍቅር የዘነበ ላብ መሆን ነበረበት......ወዝ......የፈረደበት የእኔ ላብ ወደ የትም ይተናል......የሚስቴ ደ'ሞ ወደ ውስጥዋ ይሰርጋል......እዚህ ምድር ላይ ይኼን ሁሉ ዘመን ኖሮ ፍራሹን ያሳሳደሰ ያልደላው ነው......ፀጥ ያለ ድምፅ የሌለው እርግማን......ተረት ሠፈር የሚኖር መንግስት ሰራተኛ ዓመት ፈቃድ ሚስቱ ጭኖች መሃል ነው......የት ሄደች ፋናስ......)*

**......ከሰል ፈላጊ!***

*(ለምን አንተርክከህ አትጠበስበትም......እንደ በግ ኩላሊት......የእኔ እሳት ጠፍቷል......ቡሄ ነው ዛሬ......ቡሄ......ቡሄና አርብ......አጋፋሪ እንደሻው ለቡሄ ብገላቸው......በቡሄ ቂጣ አሳንቄ ነው......ቡሄ በክረምት ባሕር ላይ የሚያሻግረን የቂጣ ድልድይ ነው......ሃሃሃ......ድልድዩ ከእግሬ ስር እየፈረሰ ነው......ታዲያ እንደሻውን ከሚፈርስ መሬት ወደ ቆመ መሬት እንዴት ላምጣ......እሳቸው እኔን ተከተው ቢያመልጡስ? ብወድስ ራሴን......አአአ......ለመሆኑ ቆሪጥን የሸወደ አጋፋሪ እንደሻው የነሐሴን ቡይ መሻገር ይከብደዋል......ምን እየሸተተኝ ነው......የሚሸጠው ከሰል ላይ እየጠበሰ ይሄዳል እንዴ......ሃሃሃ)*

**......እሳ ትኩስ እሳ!***

*(ሀሀሀሀ......እንኳን ዳንክ......እሱን ስታጠምድ አዞ አላወጣህም? እንኳን ለማጥመድ ልንወጣ ማሰቡም አልሆነ......መርቆሃል......የወንድነት መንጠቆዬን ስወረውር ከዚህች አገር የቤት ባሕር ማንን አወጣለሁ......ማንን......ቆሌ ታምና ደደብ የሆነችዋን......ፍቅር ዕውር ነው ሲል ፈረንጅ ሌላ መጨመር ነበረበት......ፍቅር ዕውር ከመሆኑ በላይ ብሽቅ ነው......ድምፁን ምን አሻከረው......ከበላ በኋላ ጠላ አይጠጣም? ከከሰል ሻጩ ጋር ተመካክረው መንገድ ዳር ተዘርፍጠው አሳውን እየጠበሱ አይበሉም......የእንኩሮ ጠጠሮች ጉሮሮ እንደ ብርጭቆ ወረቀት ይልጋሉ እኮ......ባላገር ሲናገር ከቋንቋው ዜማ የሚያወጣው ጉሮሮውን በጠላ ጠዋት ማታ ስለሚያጥበው ሳይሆን ይቀራል?)*

**......ልዋጭ! ልዋጭ! አለ ልዋጭ!***

*(ሚስቴን ወስደህ እንደሻውን አምጣ......እየደበቱ የወረቀት ነቢቤን የሚገፉትን ወሲብ ሰጥተው የመፍጠር እሴታችንን የሚገፉንን ወስደህ መልካም ብዕር ስጠኝ......ምነው ቀጠነ ድምፅህ በረሃ ቆላ ይመስላል......ድምፅህ ምነው ከፍየል ጋር ብዙ የዋለ እረኛ የነበርክ አስመሰለህ.....)*

**......አካሌን አጥቼ ብርሃኔን አጥቼ!**
**እለፈልፋለሁ ጨለማ ገብቼ!***

*(የኔም ነው እሱስ......ኢጋፋሪ እንደሻው ለቡሄ ሊታ ይሞታሉ......እልምትም ያሉ ሰው ያውም ለቡሄ ሲሞቱ ከባድ ነው......ከዚህ በኋላ ለእኔ ጨለማ ነው...... ፋኖስ በር ዘግታ እዚህ ጎኔ ብትመጣና በኩል ቆዳዋ መልካም የሚነድ ፂሚን ብታቅፈውስ......የጡቶቿን ቆብ ባወልቅስ ትንንሽ ጣቶቼስ ቢበረብሯት...... ወፍራም ከንፈሮቿ ላይ ፍቅሬን በሊጋጌ ብገግምላት......እኩራሌ ቤት......መልኬ በቃኝ ቤት......ብሸቅ ቤት......ለሆነ ለሆነ ነገር ሰውር ነኝ......)*

ወደ ቤቱ የሚፈሰው የድምፅ ዓይነት ባይከስምም ረብሻውን ንቆ ከአልጋው ተነስቶ በሌላ ሀሳብ እየተነዳ ጢሙን ይልጋል:: ብቻ ጢም ይሁን ፊት የሚያምታታ:: ከከበበው ጎፈሬና ሪዝ መሃል የዕንቅልፍ ማስክ የለበሰ የተሰላቸ ጮሌ ፊት ይታያል:: እንደ ቆመ ማንም ወደ ሌለበት ውጭ እየ......የሚያውቀውን ዘፈን ይሰማል:: ግን መሰየም ከብዶታል......*ምን ዘፈን ነበር......ሂሂ......የሃበሻ ዘፈን አንጎራጉሬ አላውቅም::* አንጎራጉሮ አያውቅም...... ትንሽ ቢያንስ ከአስናቁ ክራር......*እምም......ሂ......ሃም*......ልብ ሳይለው የቤቱን ውስጥ አድራሻ ለወጠ:: ከእሱ አንፃር በስተቀኝ አሮጌ ወንበሮችና አንድ ጠረጴዛ በእርጅና ብርድ መሃል እየተንቀጠቀጡ ቆመዋል:: ጠረጴዛው ላይ ወረቀቶች ተዘረግተዋል:: ሦስት የዶሉዶሙ እርሳሶች ጎን ለጎን ድርድሮሽ ተኝተዋል...... *ሰው ምንድነው ሰራው ከሞት መሸሽ አይደለም እንዴ...... ታዲያ አጋፋሪ ሁሉ ሰው ናቸው......በሽተኛ ካልሆኑ::* በተቃራኒው ያስፈራዋል አላፊ ሰው መሆኑ:: አጋፋሪ ውስጥ ተሳፍሮ ሳይሞት ማለፍ ይፈልጋል:: አጋፋሪ ታዲያ ነጠላ ኢምንትነቱን ሊሸከሙ አልቻሉም......ጠቅላላ ናቸው:: ስብሐትነቱን ሊቀባቸው ይሞክራል:: ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ጠረጴዛው ሄደና የፃፈውን ከፍ ዝግ ባለ ድምፅ ቆሞ ማንበብ ጀመረ......

በቀስታ ገላው እየላላ ወደ አጋፋሪ ዓለም ሲንሸራተት ይሰማዋል......'ሽሽቴ ራሱ ሕይወቴ ነው' እንዲሉ አምላጮችና ፈሪዎች:: ስብሐትን በዘልዛላ የውስጥ ሱሪው ላየው የተቺ ሳቅ የሚፈለፍል የተጨማደደ በርጨማው:: ከምን ቁስ ከምን ዓይነት ድርና ማግ እንደተሰራ የማይለየው::

የቡሄ አየር ጢሙን እንደ ረግረግ አብርዶታል:: በለሆሳስም ይነቃነቃል:: ወንበሩን ስቦ ሲቀመጥና እግሮቹ ቀዝቃዛ ሲሚንቶ ሲታከኩ ጭንቅላቱ ውስጥ የመፍጠር ዕርግዝና ይሰማዋል:: በቀስታ ተራገመ:: *ብሽቅ ወንበር:: እርሳስ ለምን ቀርጬ አላስቀምጥም::* ከተቀመጠበት አጓጉል መነቃነቅ አልፈለገም:: *እናቴ ድረስ በድንገት የሞላው ሀሳብ ተዘርግፎ ቢደፋስ......እዚህ የሚያደነቁረኝ ተረት ሠፈር ወጣ ገባ ላይ::* የዶለደመ እርሳሱን ተጋድሞ ከሚያንቀላፋበት በቀስታ አንስቶ መጫር ጀመረ............

**ትንሳዔና ኢጋፋሪ እንደሻው::**

***......ኢጋፋሪ ቀለስ ብለው ጭንቅላታቸውን ብቻ ከሳጥኑ ብቅ አድርገው ቢመለከቱ ሞት በወዲያ በኩል ጥቁር በጥቁር ለብሶ......***

ሦስቴ ምራቁን ዋጠ:: ከውስጡ እንደሚጣፍጥ ጉም፣ ያለድምፅ የሚነሳውን ውበት ያዳምጣል:: በጢሙ ክንፍና ዘርፍ ተጋርዳ አትታይም እንጂ ትንሽ

ፈገግታ አፉ ላይ ተጣብቃለች:: ከየት ተነሳች? ሁልጊዜ አድባሩ ቆርጣ ሲቀመጥ ምራቁን ሦስቴ ይውጣል:: *ለምን ሦስቴ......ለምን አራቴ አልውጥም......*ከዚያ ግራ እጁን ወደ ጢሙ ያስገባል:: ትናንሽ ጣቶቹ ጢሙ ደን ውስጥ እንደ ሕፃናት ይጠፋሉ:: የሚታየው በገቡበት አኳያ ጢሙ ሲላወስ ነው:: ወጥተው በአደባባይ መታየት ያላማራቸው ትንንሽ ዕባቦች የሚርመሰመሱ ይመስላል:: ይኼ ፍተጋ ጢሙን ያሞቀዋል፣ እናም ከስር የዛሬና የሰሞኑ ብቻ ሳይሆን ልጅ እያለ የጠጣው የጠላ ጠረን ይወጣል:: እስከ ዛሬ እስከ ጉልምስናው ደጋግሞ አጥቦታል፡ ግን በልጅነት አክሱም ፅዮን አስር ዓመቱ እያለ ትንሳኤን ሲያከብር እላዩ ላይ የተጣበቀው የእጣን ጠረንና ከወዳጁ <u>ከመስኮት ገረሱ</u> ጋር ከአራት ዓመታት በፊት ወላይታ ሶዶ ወርዶ የጠጣው ቦርዴ ዛሬ ድረስ ይሸቱታል:: ተሸንፎ በዕድሜ ተመቶ እስኪወድቅ ይኼን <u>ጢም</u> አይላጨውም:: *ለምን እላጨዋለሁ......ሰዎች ስለገላመጡት......እንኳን ጢም የእግዜርን ልጅ ክርስቶስን የምንገላምጥ ብዙ ነን......*

**እጋፉሪ ተመልሰው ወደ ሳጥናቸው ጥልቅ፣ ታዲያ እንዴ እንዴት ነው ይኼ ነገር የሳጥኑ እንጨት እንዴት ነው የማይከልላቸው......**

*በጢሜ እንድደነግጥ ይፈልጋሉ:......በወዳጅነት ዓይተው አድንቀው በአደባባይ ግን ባሉባልታቸው ጢሜን ያጣጥሉታል......ምን አደረጋቸው...... ማየት የፈለጉትን ከለላቸውን.....ንፋሳቸውን ቀማቸውን.....ድምፃቸውን ነጠቃቸውን......እሱን እያለብዙ ፊደል ብገጣጥም ይጎዳቸዋልን......*

**(ጢም)**

የግሪኩ ፈላስፋ አርስጣሊስ ተፈጥሮ ባዶ ቦታ ትጠላለች ይላል:: ፊትም ተፈጥሮ ናትና ባዶ እንዳትሆን ትጥራለች:: ያ ራሷን የመሸፈን ጥረቷ ጢም ይሆናል:: ጢም ምንድነው? ዝምብሎ ፊት ላይ ያለ ፀጉር ነው? ከዚያ በላይ ነው:: ሰው ምኑንም ነገር ባሕል ወፍሮ ከቶ እሱን ስልቆ ተምሳሌታዊ እሴት የመፈልቀቅ ልማድ አለው:: ጢም ማስክና ልቦና ነው:: ልክ እንደ ኪነት:: ኪነት ማስክ ናት:: ከሚታየው አታላይ የምትሃት ጠንበል ጀርባ ያለውን ግን የማይታየውን ፍሬ ነገር ክሱት ማድረግ:: እየከደኑ የመክፈት:: በኪነት የሚገለፀው ዕውነት፣ የልቡና ዕውነት ነው:: ከተረሱ ሐረጎችና ቃላት፣ ሰው ፈርቶ ከወረወራቸው፣ የውሸቱን እንደሌሉ ሁሉ ወደ ጎን ከገፋቸው ተረቶችና ቃሎች የታነፀ:: ባልጠበቀ ጎዳና ላይ ብርሃን ሾልኮ እንኳን ባልደረሰበት ወይም መርሳት ከደበቃቸው ወይም ሽፍጠኞች ከሸወኩብን የትርጉም ግብ ለመድረስ መንከራተት::

ከረዥም ጊዜ በፊት (ምናልባት ሦስት ወይም አራት ወራት) ስብሐት ከፋኖስ ጋር እንደተኛ ፊቱን የሆነ ነገር ያሳከከውና ይባንናል:: ከባነነም በኋላ ማሳከኩ አልተወውም:: አልጋ ላይ ካከከ ፋኖስን የሚቀሰቅሳት መስሎት ፊቱን በስሜት እየፈተገ ተነሳ:: ለሩብ ሰዓት እንዳከከ በመገረም የሆነውን ለማጤን ግድግዳ ላይ የተሰቀለ መስታወት አውርዶ ሲያይ ከላይ እስከ ታች በድንጋጤ

ተመተረ:: ጢሙ በርበሬ መስሏል፣ ይሞቃል ትኩስ ነው:: መንካት ፈራ:: 'ምን ሆንኩ?' አለ ለራሱ በጎላ ድምፅ:: ጢሙ መቅላትና ትኩስ ብቻ ሳይሆን ነፍስ እንዳለው ነገር፣ ነፋስ እንደሚያነቃንቀው የጋሸበ ጤፍ፣ ወይ ሞገድ እንደሚጫወትበት የባሕር አረም በቀስታ በተለያየ አቅጣጫ ይላወሳል:: ከቆመበት ተቀመጠና ሁኔታውን ያጠና ጀመር:: ፋኖስን እንዳይቀሰቅሳት ደ'ሞ (ሴቶች ስለማንኛውም ዓይነት ፀጉር ያውቃሉና) የማይፈልገውን ነገር ታደርግ ይሆናል (ለምሳሌ ኡ!ኡ!ኡ!ኡ!! ማለት)

ጢሙን በቀስታ ነካው:: ለጣቶቹ ደስ የሚል ለስ ያለ ሙቀት ያወጣል:: ጨረራ:: ከነቃ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ማሳከኩን እንዳቆመ ተገነዘበ:: ምን ጥያቄ ማቅረብ እንዳለበት አልገባውም:: ከሳይንስ ውጭ እንደሆነ ይረዳል:: የሚነድ ጢም? ለብቻው ያለነፋስ የሚንቃንቅ ጢም? ከዚያ ድምፅ የሰማ መሰለው:: እንደ ሹክሹክታ:: መጀመሪያ ፋኖስ መስላው ነበር:: ፋኖስ አልጋ ላይ መርፌና ክር ሲሆኑ ካልሆነ ድምፅዋ ቃጠሎ ነው:: እንደገና ሲሰማው ቃሎቹ ከፊቱ በትክክል ከጢሙ ላይ እንደሚመጡ ተገነዘበ:: በድንጋጤ ጨብጦ ያዘው:: ድምፁ ግን በለሆሳስ ሜዳ ላይ እንደሚወርድ ውሃ፣ ወደ ባሕር ሊወተፍ እንደ ቋመጠ ዓባይ ሲፈስ ይሰማዋል:: ሊያስቆመው አልቻለም......

*ኢጋፋሪ እንደሻው*

*ኮምቡጠር*

*በስመአብ ወወልድ በመንፈስ ቅዱስ::*

*በስመአብ ወልድ በመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ:: በመጀመሪያ የአቶ አሳዛር አባት ስለሆኑት ስለ ኢጋፋሪ እንደሻው ባጭሩ እንፅፋለን::*

*እንደሻው......*

ራሱን እንደሳተ ሁሉ ፊቱን ጠረጴዛው ላይ ደፋ::

እስኪነጋ አልተነሳም::

ጠዋት ላይ ለፋኖስ ስለ ጢሙ ሲነግራት......

«በላ በላ በጢምህ እየተመራህ መፃፍ ጀምር:: ብሎ ብሎ ምን ዓይነት ደዌ መጣ» አለችው፣ ብዕር ማንሳቱንና መፃፉን እንደ በሽታ ጠቅሳ......

**(ፋኖስ)**

ትልቅ ሀብቷ መልኳ ነበር:: ዛሬም ነው:: ከቤቷ ወጥታ የማታውቅ ልጅ ነበረች:: የአዲስ አባን ወንድ የብረት በር አያግደውም:: ይኼም በከተማዋ ብሉይ ተፅፎአል:: እና በረቀቀ ድለላ ዘመናዊ ነን ባይ ወንዶች ተረባርበው ከቤቷ መደብ ላይ እንደ ሽንኩርት ነቀሏት......

'ፋኖስ የላምባ ዕንቡጥ' ይላት ነበር ስብሐት:: ታስታውሳለች መጀመሪያ ያያት ጊዜ ስለእሷ ወደ ሰዎች ጠጋ ብሎ ሲጠይቅ እሷም ጆሮዋን ጥላ እያዳመጠች፡

«ማን ናት ያቺ ቆንጆ በእግዛብሄር?»

«የቷ»

«ያቺ <u>በአረንጓዴ ሚኒስከርት</u>[13] ወዲያ ወዲህ የምትል?»

«ፋኖስ ትባላለች»

«ቀሚስ ብሎ ዝም:: እግር ብሎ ዝም»

«ወደ እሷ እጠጋለሁ ብትል እዚህ የተሰበሰበው ወንድ ሁሉ ሮኬት ይወረውርብሃል»

«የምትታይ እንጂ የማትበላ ፍሬ?»

«ምናልባት»

«እናያለና»

ያን ጊዜ ደማቅ አረንጓዴ ቀሚስና አጭር ጥቁር ቆዳ ጃኬት ለብሳ ነበር:: ሰውዬውን ከዛ ማታ በፊት በዐይን ስጋ አላየችውም:: ታስታውሳለች ለብቻዋ የስብሐት ግጥም ለሌሎች ሲነበብ–ባታውቀውም፣ አይኖቿን ጨፍና በልቧ እንደ ተመኘችው:: ስለ እሱ በምትሰማው ወሬ ሳይሆን በብዕሩ መመስገን ቋምጣ እንደነበር:: ያን ዕለት ማታ ሰው በተሰበሰበበት ድርቅ ብሎ ሰፊ ግንባሯ ላይ አፍጦ እንዲህ አላት:

> *«ዓይንስ ለምደናል ያደግንበት......አንገትም::*
> *ማን ናት ይሽቺ እሷ በረቂቅ ቀሚስ የምትለትም»*

ውስጥዋ ቁጭ አለ::

ወእፍተዋ[14]......

ውኖሙ ሀቡረ[15]......

ስብሐት በፍቅር ምላሱ እንዲህ ገርፎአታል ያኔ:: ፒያሳ እስኪሰማ......ሾጥ::

የሚፅፍባቸውን ቃላት ምላሱ መከዳ ላይ እንደ በጨጨ ሾላዎች ደርድሮ በእሱ ሁለመናዋን ስሟታል::

የአሳሳም ቁንጥ ወይም ግጥም ገጠማ ዳቦ አይሆኑም:: ወይ የእንደኛው ከሞት የማምለጥ ፋንጣዚ:: ልብስና መልካም ምግብ አይሆንም በወረቀት ላይ ከሞት ማምለጥ:: ሞት በውርደት ሊያሳስራት እዚህ ደጃፏ ቆሞ:: ጠርጎ በአፍታ መውሰድ ቢከብደው እያሳሳቀ ሊነዳት፣ ሊገፋት:: ለስለስ ባለ ደሃነት:: እያባበለ:: *መጀመሪያ በእርዛት ቀጥሎ በረሃብ ከዚያ በብርድ በሽታ......ታዲያ እንዲህ በአፉ ያቀርበኝና ማን 'እስኪ ልየፍ' እያለ ይሸሸኛል:: ሌላ ሴት ጋ የሄደ አይመስለኝም......አያደርገውም...... ገንዘብ ያላመጣ ድርሰት ምን ይረባል...... ይጭራል ይጭራል ቀሚስ መለወጫ ገንዘብ እንኳን አያመጣም......ነጫጭ የውስጥ*

---

13 miniskirt = በጣም አጭር/ደቃቃ ቀሚስ(እንግሊዝኛ)(አ)

14 (ግዕዝ) አነሳሳትም......ከክብረነገስት ምዕራፍ 23

15 (ግዕዝ)አብረውም ተኙ......ከክብረነገስት ምዕራፍ 30

*ሱሪዎቼ በአረንጓዴ ክር ተሰፍተዋል......ለነጭ ክር እንኳን ገንዘብ የለን......ከዚያ ይስመኝና ምናባቱንስና 'ላምባዬ' ይለኛል......እሱ ምን መሆኑ ነው......ውሐና ነፋስ......የቺ በረካ የምትባል ቤትዮ ምንድን ነበር ያለችኝ......'ታዲያልሽ የ ማነው እንዲህ ሲቆላው ያስገዛሁትን ላሳይሽ' ብላ ከቤቷ አምጥታ ያሳየችኝ የነጠረ የጣሊያን ቆዳ ጫማ......ስብሐት ምን ነበር ብሎ ያጣጣለው......'ይኼን ጫማ የተሰራበትን ቆዳ እዚህ ሰበታ በሬ ሆኖ አውቀዋለሁ' ነው ያላት...... ቀልዶ ሞቶአል......ያልምባለት......*ከዚያ የሠፈር ሴቶች ቡና ሲጠጡ አብረዋት አንዷ ቤት ለበዓል ስለገዙት በግ ማማገር ሲያወሩ......ልክ ቦይ ፍሬንዳቸውን ወይም ውሽማቸውን እንደሚጠሩ እየመሰሉ......እሱ ደራሲያቸው እየቀለጠ ደሙ የሚንጠባጠብ የሉካንዳ ስጋ በጋዜጣ ወረቀት ጠቅልሎ በብብቱ አቅፎ ያመጣል:: ይኼንንም 'ቶሎ ጠብሰሽ እንብላ' ብሎ መበጣጠስ የጀመረውን የረጠበ ጋዜጣ እየገላለጠ እያነበበ 'ወይ ጉድ' ይላል:: *የሚረባ ጋዜጣ ቢሆን ኖሮ የከበሩና ስለ ዓለም የሚያውቁ የስጋ ነጋዴዎች የሞተ......የሚፈስ ስጋ ይጠቀልሉበት ነበር? ከዚያ ሽሚዙን ማጠብ......ከዚያ ቅቤ በሌለበት ቤት በዘይት መጠበስ......ሲበላ ሲል መከራ......ሲበላ መከራ......ከተበላ በኋላ ደ'ሞ የአንጀት ድርቀቱ መከራ...... ለምን እንዳፍርበት ያደርጋል......ለምን እኔን ሊያስከፋኝ ይለፋል......የሚተርፋት* ማንም ወንድ የሚፈልገው ገላዋ የበዓል ዕለት በመልካም ምግብ አለመሞላቱ ነው::

## (አረንጓዴ—1)

አረንጓዴ ለጥንት ግብፆች ቅዱስ ቀለም ነበር:: አረንጓዴ የሚያባብል መንፈስን የሚያለሰልስ ቀለም ነው:: የሚጠርስ ሕፃን አረንጓዴ ቀለም ቢያይ ወይ አረንጓዴ ቀለም የተቀባ ክፍል ውስጥ ቢቀመጥ የሚያነጫንጨው ሕመሙ ይቆምለታል:: ሆዱ ተውሳክ ያለበት ሰው አረንጓዴ ቀለም የተቀባ ነገር ቢያሳዩት ይሻለዋል:: በጥንት ግብፃውያን የትኩሳትና የብርድ በሽታ የሚድኑት ባልደረቁ አረንጓዴ ቅጠሎች መድሃኒትነት ነበር:: ምች የመታውን በሽተኛ እዚህ የተረት ሰፈሯ ወይዘሮ አልታዬ በለጋ ዳማ ከሴ ቅጠል ያድኑታል:: አዲስ ዘመን ሲመጣ የሰፈሩ ኮረዶች ዛሬ 'ለማኝ' የተባሉት፣ ለየቤቱ አረንጓዴ እንግጫ የሚሰጡት ልምላሜ ሲመኙልን ነው:: የማሕፀናቸውን ረግረግ በሐመልማል መስለው ሲሰጡን ነው:: ፍሬ የማብቀል ተስፋ በትናንሽ ጭኖቻቸው መሃል እንዳስቀመጡ ሲነግሩን ነው:: የመራባት ተስፋ ነው:: አረንጓዴ ሚዛንና ስምረትም ነው:: የቡዲሂስቶች ካርማ[16] ወይም የተላለፈ/የተወረሰ ድርጊት የሚወከልበት ቀለም አረንጓዴ ነው:: ታላቁ ድርጊት መከየን አይደለምን? ከየና ታላቁ ድርጊት አይደለምን?

የፋኖስ ቀሚስ ከአልኔሰታ ቡቲክ የተገዛ አስገራሚ አረንጓዴ ነበር:: ልቡን የወሰደችበት ሰሞን (ባትወስደውም ገብታ ሌላ እንዳያስገባ የከለከለችው ሰሞን) የስብሐት አንጎል ውስጡ ጎመንና ቆስጣ የተዘራበት ተዘርቶም የበቀለበት መሰለ:: አይኖቹ የሚቀላውጡት አረንጓዴ ነገር ብቻ ሆነ:: ይኼ ውጣ ውረዱን የሚያውቅ

---

16 karma= ካርማ(ሳንስክሪት)

አንድ ወዳጁ በዚያን ሰሞን ከሚያነበው የዕዝራ ፓውንድ[17] ግጥም አንዱን በስልክ አነበበለት:: 'ከዚህ ከፋሺሽት ገጣሚ ምን አገናኘህ' ብሎ ቢተርበውም በስልክ የሰማውን ግጥም በማስታወስ ለፋኖስ በራሱ ቃላት ወደ አማርኛ ሊተረጉምላት ሞከረ:: ብዙ ወረቀት ላይ ጫጭሮ ለፍቶ ወጥቶ ወርዶ ተሰላችቶ ሲቆም እጁ ላይ ሁለት የአማርኛ ኢሜጂስት[18] ግጥሞች ቀሩ:: የት እንዳስቀመጣቸው የፃፈባቸውን ወረቀቶች ዛሬ ቢረሳም ወይ ቢጠፉም ስንኞቹ ትዝ ይሉታል:

*ቀዝቀዝ ያለች ደብዛዛ የሸለቆ ቅጠል[19]*
*እዚያች ጎኗ ለጎሕ ለጎሕ እፈነገል*

ወይም

*ሊነጋ ሲል ጎኔ ተዘልቃ[20]*
*ለግ ለግ እንዳለ እርጥብ ቅጠል፣ እንደ ቀዝቃዛ*

**(ቤሳ ቤስቲን)**

በዚህ ጠዋት ትንንሽ የቋንጣ ስጋዎች የተነሰነሱበት፣ ንጥር ቅቤ ያሳመረው፣ ኩንስንስ ፍርፍር መብላት አማራት:: መልካም ቀይ ሽንኩርት ያም በጥልቅ የተቆላ:: የውስጥ ፍላጎቷ ነው:: ጎረቤቷ ሙሴ ቡዙሃንያን ዘመድ ጥየቃ ግሪክ ሄደው ሲመለሱ ያመጡላት ሦስት ሊትር የለውዝ ዘይት አለ(ፍርፍር በዘይት?):: ያውም ፖማስ ሳይሆን ድንግል:: ቦርሳዋን አየች:: እንደገና የስብሐትን ሱሪ ከወደቀበት አንስታ ቦርሳውን አውጥታ ውስጡ አየች:: ወደ ስድስት ብር ለቃቅማ ወጣች:: ግን አይበቃትም:: ስብሐት ጥሬ ስጋ ይወዳል:: ቢያንስ አስር ብር ያስፈልጋል:: ቢያንስ:: ጓደኛዋ በረካ ቤት ሄደች:: ጓደኛዋ ያቺ ሐብታሞች 'ነዘነዙኝ' የምትለው የሚገርም መልስ ሰጠቻት:

«ቤሳ ቤስቲን የለኝም»

ይገባታል በብዙ ቀዳዳ አሾልካ እንደ ፈተሸቻት ስብሐት ባሏ በመሆኑ እንደምትቀና:: ስብሐት ደ'ሞ በረካን ቀና ብሎም አያያት:: ምን ታድርግ ከደራሲ የተጋቡ ሴቶች ስንት ናቸው? ትልቅ ፉክክር ነበረው ድሮስ:: እስር ቤት፣ ጭቅጭቅና ቺስታነት ሳይቀንሳቸው:: በትዕዝብት አየቻት:: ተግባብተዋል ገልጸው ባያወሩትም:: ቢያንስ አፋታት ስብሐትን ለመውሰድ፣ ያ ባይቻል እንኳን ቀማምሳ 'የደራሲ ባል አያድርስ ነው እቴ ያቺ ወዳጄ......' መቅመሷን ልታወራ::[21] 'እኔ ያልተኛሁት ወንድ ምኑ ወንድ ነው' ዓይነት ጉራ:: ሴቴ እህያ

---

17 እዝራ ፓውንድ እእእ ከ1885 እስከ 1972 የኖረ አሜሪካዊ ገጣሚ:: ኢሜጂስት የተባለ የግጥም አፃፃፍ ረድፍ መስራቾች አንዱ::

18 imagist= የአገጣጠም ዘይቤ፣ ፍልስፍና(እንግሊዘኛ)

19 የእዝራ ፓውንድ ግጥም ( as cool as the pale wet leaves
of the lily-of-the-valley
she lay beside me in the dawn......*alba*)

20 ዝኒ ከማሁ

21 ዛሬ አንድ ቀጠና ሶስት ወይም ሼል አካባቢ የምትኖር አንድ ወዳጄ እንዲህ ዐይነት

ስራ......ከሩኖስ ሕይወት ስብሐትን መዛ ልታወጣባት::

'ቢሳ ቢስቲን' ስትላት ግን ቃሏ ገረመቻት:: ቢሳና ቢስቲን ምን አገናኘው? ምንድነው ቢስቲን? ቢሳ ምላጭ ነው:: *ምላጭ......ምላጭ?*

'ቢሳ' መጀመሪያ ፀጉር፣ ቀጥሎ የስብሐትን ጢም አስታወሳት::

## (ከለበን ወንዝ መውረግረግ ይቀጸል)

ቂጥዋ ግራና ቀኝ ይጋረፋል:: የመንገደኛውን ሁሉ ገና ታጥቦ ያልተዝናና የጠዋት ዓይን......ቀላዋጩን ምንትሲውን በቀይ ሰንበር ሞላችው:: ግን የማይቋምጣት የለም:: ቤተመንግስት ጣሪያ ላይ ቆሞ የሚያጤናት ማንቀላፊት የተሳነው ጠ/ሚኒስቴር እንኳን ሳይቀር በፍትወት ዙፋኑ ላይ ያረገርጋል:: ኢጲስቆጶሱ ካባቸውን ጥለው አሳዛ የመሰለ ደረታቸውን በኩራት ከፍተው ራቁታቸውን ቆመዋል:: ያያት ሁሉ አፉን ይከፍታል:: ተንጠራርተው እንዲህ ዓይነቱን አፍጣጭ ቢያዩ ከቡላ ምላሱ ጀርባ በዕንጥሉ ልሳን የተጋረደ (በደንብ ሳይሆን) ገና ያልተፈጨ የሚጤስ ክትፎ:: ይኖራሉም ከጥርሳቸው አይበሉባ ሉካንዳ የሚጎበኝ፣ ወይ ጎመን የሚቀነጠስ፣ ወይ ዶሮ ያለቀሰችለት የሳፍራን አበባ የመሰለ የዕንቁላል ፍርፍር የሚረግፍ:: ጉሙን እንደ እሷ የሚያይ የለም:: ጠይም አንገቷ ላይ ረቂቅ የጥርስ ዱካ አለ:: እነዚህ ተራርቀው የተሰሩ የጥርስ ዱካዎች የለበንን ምራቅ አቁረዋል:: እነዚህ ረቂቅ ገበቴዎች ውስጥ በርበሬ ያቀላው እርጎ አለ:: ከነዚህ የቆሬ ጠለሎች ላይ ረቂቅ የዊንስተን ትንባሆ ጢስ በቀስታ ይነሳል:: ማንም ተጠግቶ ፊቱን ትከሻዋ ላይ ደፍቶ ሊያይ አይችልም እንጂ—ቢችል:: እንደተከተበች ታውቃለች ሩኖስ:: ከቤቷ ተንደረድራ ወጥታ ደርሳ ስትመለስ:: ታውቃለች:: ማሕፀኗ ውስጥ የለበን መርዝ ይዋልላል:: ቁጭት እጇን ሰዶ ሲነካት......*ስብሐት ተሳስቷል......እሱ ነው እንዲህ የሚያስደርገኝ...... የአንተ ጢም ባይኖር እንዲህ አልሆንም* ትላለች ለራሷ:: *አንተ ብትረባ እንዲህ አልቀማህም......*የዛሬውን ለጓደኞቿ ትንገር? ያልረባ ባሏን ትታ ልክ እንደነሱ ባሎቻቸው ላይ እንደሚያደርጉት ለተሻለ ወንድ ስብሐትን እንደ ከዳችው? *ወረቀት ላይ ጎብጦህ ያሌለ ነገር ስትፈጥርና ስትጠነቀል እኔ በቁም ያለሁትን ስትረሳ ልጅት ምን ላድርግ......ላይፍ ኢዝ ሾርት*[22]:: የማታመልጠው ነገር ግን ከቂጥዋ ላይ የመርከስ ቢጫ ጉም ይነሳል:: የመጣችበትን መንገድ ዞር ብላ ስታይ በወገቧ ከፍታ አደይ የመሰለ የሚሸት ቀጭን የጢስ መቀነት:: ይገባታል:: በሚውረገረግ አካሄዷ ውስጥ በስልት ደብቃዋለች እንጂ ጭኖቿ ተነቅለው ለብቻቸው መሬት ወድቀው በቁጭት መንፈራፈር ይፈልጋሉ::

ስትነከስ (እንደሚሉት) የምትቀላ ጠይም አዲስ አባ ውስጥ እሷ ብቻ ናት:: የወጣትነት ፍላቷ ተቀስቅሶ ደም ስሮቿ ከላይ እስከታች አረግርገዋል::

---

አጠባበሱን 'ማርከስ' ነበር የምትለው:: 'እስኪ ላርከስ' ስትል ሊፋቀሩ የሚንጠራሩ ፍቅረኞች መሃል ገብታ፣ ወንዱን ለአንድ ቀንም ቢሆን ጠልፋ፣ ሰው እንዲሰማው ተጨባጭ መረጃ አስይዛ፣ ከፍቅረኛው ለማራቅ 'ጀብዱዋን' ማስወራት ማለቷ ነበር::

22 life is short = ሕይወት አጭር ናት (እንግሊዝኛ):: ልዝናናበት፣ እንዝናናበት(አ)

ለበን ቋጥሮ ነው የለቀቃት። ስህተቱ ይኼ ነው። መፈታት ፈልጋለች። ለበንን ሴቶች ለምን እንደሚያደንቁት አልገባትም። ሴቶች ቂጡ ቂጡ ሲልከሰከሱ ነው የሚውሉት። ለገንዘቡ? ለመኪናው? በዚህ በረጠበ ነሐሴ፣ ባኗን በከዳችበት እርሩጃ ጠዋት......ዓይኖቿ በቁጭት ጠበው ዳመና ያሸሞነሞናት የተላጠ ዱባ የመሰለች የፈዘዘች ፀሐይ ያያሉ። ፈዛ ቆማለች። በትክክል መሂጃዋ ጠፍቷታል......

## (ዝናቡ መጣ ከወዳንገጣ..........)

ልብሱን እንኳን አለበሰም። ጭገራም ቀጫጫ እግሮቹ ብርድ ጠርጓቸው አቡጀዲ መስለዋል። አይኖቹ እንዳለቀሰ ሁሉ በሰንባ ዓይነ-ርግብ ተጋርደዋል። ከውጭ ቆማ አጠናችው። ብትርቀው የሆነ የሚጎል ነገር እንዳለ ይታወቃታል። ደካማ ቁመናውን ስታየው......እፍ ቢሉት የሚጠረግ የመሰለ......ልቧ ትር ትር አለችባት። እንዴት ነው እንዲህ 'የመሰከነ' እንዴ ቢገፉት ሦስቴ የሚወድቅ ልቧ ውስጥ እንጥፎ የተኛው? እንዴትስ እሷን የሚያክል ጠይም ዓሳ በውበትና በቁመና ያጌጠች[23] በዚህች ትንሽ ሰውዬ ገላ ውስጥ ትጎዘጎዛለች? *ያስወማኝ ለዚህ ይሆን......ቦታ ስለማይበቃው......* ፊቱን እንዳልታጠበ አየች። ገጹ በእንቅልፍ ወዝ እንደ ተጠመቀ ነው። ይኸቺ ቤታቸው በቂ ንፁሕ አየር አይገባትም። ከላይ የቤተመንግስት ጉብታ ከእንጠጦና ከየረር የሚመጣላቸውን ኦክሲጂን ግማሹን መጥጦ የሚያስቀር። ከወዲያ የፒያሳ ዳገት ነው የገዳም ሠፈርን፣ የሰራተኛ ሠፈርን የእሪ በከንቱን ካርቦን እንደ ጅረት የሚያፈስ......ወደ ፍልውሀ። ለኦክሲጅን እንኳን አሮባቸዋል። አያወሩትም። እሱ ደ'ሞ ደራሲ ነው። እታሚ የዘጋው። ግራና ቀኝ ውድቀት።

«የእኔ አንበሳ» አለችው ገና ከደጃፍ

በአራዊት መስላ ስትጠራው ደነገጠ። እንዲህ ጠርታው አታውቅም።

«ምነው?»

እየተውረገረገች ገብታ ፌስታሏን ወንበር ላይ ከእሱ እርቃ አስቀመጠች።

«ድርሰትህ ሆነልህ?»

ግድ የላትም። መግባቧ ነው። በዚህ በዓል በመሰለ ቀን ዶሮ አርዷ ላባ መንጨት ካልተፈቀደላት ስብሐትን ብትነጨውስ?

«ምነው?»

ደስታ ድምፁ ውስጥ የለም። እንዴት ነው የረካና የተረጋጋ ከመሰለ ፊት ላይ የሚወጣ ድምፅ ተጠራጣሪ የሚመስለው?

«ትዝ ይልሃል? አንድ ላይ እንዲህ ፊት ለፊት ተቀምጠን ወሬ የምናወራው? እየጠጣን»

«እና?»

---

23 ከሆነ የዘፈን ስንኝ ላይ የተወሰደ(አ)

«ምን ሆንክ? ደስ ያለህ አትመስልም:: እኔ ከየትም ከየትም ቆጥቤ ......» ወደ ፌስታሏ ሄዳ: «ያመጣሁትን እይ:: ትንሽ እረፍና ትሰራለህ»

ጆኒ ወከር ዊስኪ አወጣች:: ቀጥሎ አንድ ኪሎ ተኩል ስጋ::

«ብራቮ ብራቮ:: ግን ታውቂያለሽ አሁን የሰከርኩ ይመስለኛል:: አየር ላይ እየበረርኩ ነው:: የዛሬው ልዩ ነው:: ከጢሜ የሚወጣው ድምፅ ጠዋት የጀመረ እስከ አሁን አላቆመም»

«አብደሃል? ይልቁን ክትፎ እሰራልሃለሁ ለእኔ ጥብስ እሰራለሁ:: ተዘጋጅ»

«ውሽቴን መሰለሽ? ተጠጊኝና አዳምጪ»

«እንደኛውኑ ካንቺ ጋር መጠጣት በቃኝ አትልም?»

«ምን ሆንሽ ማ ሶለይ[24]?»

«አላውቅም? እኔ ልጅ መሰልኩህ?»

«ምንድነው የምታውቂው?»

መንገድ እየሳተባት የኬደ መሰላት:: ለዚህ አይደለም የመጣችው::

«ረሃቡ ሊገለኝ ነው:: ይልቁን ክትፎውን መስራት ጊዜ ይወስዳል አይደል?»

«ጥሬ ይሻልሃል ለብለብ?»

ምን እንደሚፈልግ ታውቃለች:: ወሬ በማራዘም ቀድሞ የጀመረችውን የተበላሸ መንገድ ልታድስ ነበር::

«የምፈልገውን ታውቂያለሽ»

«አውቀህ እንደሆነ የምትረብሸኝ»

«ክትፎ ቁርስ ይሆናል? ቁርሴንም አልበላሁ:: ቡናም አፍዪ አስኝቶኛል»

«ያውም ያማረ»

ዞራ ስትመለስ ወደ ጠረጴዛው አጎንብሷል:: ለባዶ አየር እየተናገረ ይፅፋል:

***አጋፋሪ አይናቸውን መልሰው ዘጉ:: አሰቡ:: መልሰው አይናቸውን ከፈቱ:: ደጃዝማች ዳኛቸው ከላይ ወደ ታች ያዩዋቸዋል እንባ ባዘሉ ዓይኖች:: እሳቸው ወለሉ ላይ ተንጋለዋል......***

***«ምን ሆንኩ?» አሉ አጋፋሪ......***

ፋኖስ የምትናገረውን የሚፅፍ ይመስላል:: ግራ ተጋብታ አየችውና:

«የምናገረውን እየቀዳህ ትፅፋለህ እንዴ?» አለችው::

«እ»

---

24 Ma Soleil = የእኔ ፀሐይ(ፈረንሳይኛ)

«የምናገረውን ት....»

ተወችው::

ከአንድ ሰዓት በኋላ ፍም የመሰለ ጥሬ ክትፎ በትንሽ የሸክላ ሳህን ላይ፣ ጥብሱ በትሪ (ግራና ቀኝ ጠይም ክንፍ የመሰሉ ስጋዎች ያንጠለጠሉ ቀጫጭን የበግ ጎድኖች) ሁለት ዓይናማ ስርገኛ እንጀራዎች ላይ ተዘርግፎ:: ስብሐት ቀና ብሎ ከሰማይ የወረደ የመሰለውን ብርጻም ጥሬ ክትፎና የሚጤስ ጥብስ አየና ከተቀመጠበት ተነስቶ ዊስኪውን ከፈተ:: ዓይኖቹን ከማዕዱ ላይ ሳያነሳ(ርቦታላ) የምግብ ወንበር ሳበና(አሁንም ዓይኖቹ ከማዕዱ ላይ አልተነሱም) በልቡም...... *ምነው ጠኔ እስኪይዘኝ አጠብቃለሁ*......በጠረጴዛው ስፌ ጎን ተቀመጠ::

«እስኪ በውስጥ ልብስ ተቀምጠሽ ብዪ ሁሉ ነገር እንዲያምረኝ:: ደ'ሞ በሩን ዝጊው:: ብርድ ቢገባሽስ?»

ቤቱ ውስጥ ቀዝቃዛ ግራጫ ጨለማ ነበር:: የሚነቃነቅ የሚመስል:: ትንሽ እንግዳ የመሰለ......ማለት ከሌላ ቦታ ተጉዞ ለትንሽ ቀን ለማረፍ እዚያ ገብቶ የሠፈረ......እንቅልፍ እምቢ ስላለውም ስብሐትና ፋኖስ ዙርያ የሚበሉትን እየቀላወጠ የሚንገላወድ ትርጉሙን የደበቀ ጨለማ......የብርሃን ነጠብጣብ የወደቀበት ግስሌ ጨለማ:: ከምግብ ጠረጴዛው ከፍ ብሎ የተንጠለጠለውን አርባ ሻማ አምፖል አበራች:: መሃል ከመሃል ከላይ እስከ ታች በአስር ቀያይ ቁልፎች የሚዘጋ ነጭ ቢጃማ ለብሳ ፊት ለፊቱ ተቀመጠች:: ትልቅ ስሜት ውስጥ እንዳለ ይገባታል:: ስሜቱ አይገባትም እንጂ......ውስጡ እንዳለ ይገባታል:: የሆነ ፊቱ ላይ ሰላምና ትኩረት የዓፈ:: ሰማያዊ ነገር:: እዛ ውስጥ ደራሲው እንደ ተጠማ ዓሳ:: ክትፎው በንፁህ ትሪ ላይ በዓይናማ እንጀራ ተከቦ......ፋኖስ የቀመረችው ብርብራ::

ለራሱ ከመብላቱ በፊት ቀድሞ ትልቅ ጉርሻ ጠቀለለና:

«እንኪ የእኔ እመቤት» አላት ሊያጎርሳት::

ለመብላት አለመቻኮሏ ገረመው:: የሆነ እቅድ እንዳላት ጠርጥሯል:: *እኔን እስኪጠግብ የማብላት ዕቅድ? እኔን አብልቶ አጥግቦ የመዳራት የፍቅር ዕቅድ? ምን ያሴራልስ ያሳቅዳልስ?* ከጣቶቹ መሃል ጉርሻውን በቀስታ በአፏ ወሰደችና አናቱን ወደ እሷ ስባ ባበጠ ጉንጭዋ ጢሙን ታከከችው......

ውስኪውን በብርጭቆ ሞልታ ሰጠችው:: ሃሳቧ ወደ ነበረችበት ይሸሻል......*ለበን ለምን አልኮል አይጠጣም*......*አፉ የሸተተኝ ቅቤ የተነከረ የእንጀራ ፍትፍት ነው......ጉያው ስጎሰጉስ የሸተተኝ መልካም ዲኦደራንት ነው:: ምላሴ አፉ ውስጥ ሲያርፍ የቀመስኩት በትኩስ ቡና ተጉመጥምጦ ጨርሶ ያላጠበው የማር ወለላ ነው*......ስብሐት ረሃቡን በችኮላ አስታገሰና ከውስኪው ደጋግሞ እያጣጣመ ጨለጠ:: ገንዘብ ከየት እንዳገኘች ሊጠይቃት ፈለገና ስለ ሴት የመቆጠብ ጥበብ አሰበ......*ሴቶች አንድ ነገር ማድረግ ከፈለጉ እንኳን ሳንቲም ሌላም ይቆጥባሉ*......አልኮል እየጠጣ ስብሐት ስለ ስነፅሁፍ ወይም ስለ ፃፈው ማውራት እንደሚወድ ታውቃለች::

«እንዴት ነው ድርሰትህ? ስለምን እየፃፍክ ነው?» አለችው ቅንድቡን በጣቶቿ እንደሚያበጥር ሁሉ እየዳበሰች::

«ደኽና ነው:: ስለ ሞት እየፃፍኩ ነው»

«እንዴት?»

«የሰው ልጅ ስራው ከሞት ማምለጥ ነው:: እና ከሞት የሚሸሹ ሰውዬ ታሪክ እየጻፍኩ ነበር:: እሱን ጨርሼአለሁ እና ያሰብኩት እኚህ ሰውዬ ልጅ ቢኖራቸው ልጃቸው ምን ይመስላሉ? እያልኩ ነው:: ስለ ልጃቸው ለመፃፍ እያሰብኩ ነው»

«እና ምን ይሆናል?»

«ገና እየጀመርኩ ነው:: የት እንደሚደርስ አላውቅም:: እኔ እኮ ሳይገለ እንደሚፅፍ አቅጄ አልፅፍም:: ሁኔታው በራሱ ይመጣል»

«እንዲሞቱ ታደርጋለህ?»

«ሰው ታዲያ ለምን ተሰራ:: አጨራረሱ ሁልጊዜ ሞት ነው»

«እና?»

«በቃ:: ጥረቱ ይፃፋል:: ሁሉ ነገር ጥረት ነው:: ሰው ሞትን በተለያየ ጊዜ በተለያየ ስልት በዓመታት፣ በሰዓታትና በደቂቃ ይሸውዳል»

«እህ»

«አይመስልሽም?»

«ይመስለኛል:: ታዲያ ይኼንን ሁላችን እናውቀው የለም እንዴ? ምን ያፅፋል?»

«የተለያየ ዓይነት የመኖር ጥረት አለ አየሽ:: አንዳንዱ ያለፍቅር ይኖራል:: አንዳንዱ ሌላውን በመግደል ወይም ሌላውን በማጥፋት ለብዙ ዘመን መኖር ይፈልጋል:: አንዳንዱ ዝም ብዬ ለዘለአለም ልኑር ይላል:: አንዳንዱ ብዙ ለመኖር እግዜርን ይለምናል:: አንዳንዱ ጥሩ ይበላል ጥሩ ይጠጣል......ሞትን ሊያሸንፍ»

«ይኼንንም እናውቃለን»

«ማወቅና መገንዘብ ይለያያል:: ስነፅሁፍ የሚያደርገው የምታውቂውን ነገር ባልጠበቅሽው መንገድ በማቅረብ እንድትገነዘቢው የማድረግ ነው:: ስለዚህ ሁልጊዜ ሕሊናሽ ውስጥ እንዲኖር ያደርጋል:: በተቻለ መጠን አእምሮአችንን በተለያየ ሀሳብ የመሙላትም ነው:: ይኼ በሰዎች መሃል መግባባት ይፈጥራል:: አሁን አየሽ ትንግርታዊ ቴክኒክ በመጠቀም ለመስራት ነው የምፈልገው:: ሰውዬው ሐሳባቸውና ነገረ-ስራቸው ማንንም ይመስላል:: ብዙ ሰዎችን ይመስላል:: ድርጊታቸው ሊያስቀን ይችላል:: ማለት በትንሹም ቢሆን በራሳችን እንስቃለን እንደ ማለት ነው:: ራሳችንንም እናያለን:: ይኼ ብቻ አይደለም......ሌላ ዘርፍም አለው:: የሰው ልጅ ዛሬ እዚህ የደረሰው ትውስታውን እየተቀባበለ ነው፣ የታሪክ

መቀጠልና አለመቀጠል፣ መጥፋትና መልማት በምንቀባበላቸው የትውስታዎች ፀባይ፣ ዐይነት እና ይዘት ይወሰናል:: የሰው ልጆች የሚረሳ እናስታውሳለን፣ የሚታወስ እንረሳለን:: ንጉሥና ፕሬዝዳንቶችን በታሪክ ዕሑፎች እናስታውሳለን:: ትንንሽ የመሰለችዋን ግን መሰረታዊ ነገር ግን ከማንም የበለጠ እንረሳታለን:: ከልጅነታችን ጀምሮ ስንት መሃረቦች እንደ ነበሩን አናስታውስም:: ከልጅነታችን ጀምሮ ስንት ጊዜ አባታችንን 'አባባ!' እናታችንን 'እማማ!' ብለን እንደጠራን አናስታውስም:: በመጠኑም ቢሆን ግን ተራ መስለው የመረሳት እርግማን የተጣለባቸውን አስፈላጊ የሆኑ ልምዶቻችንን ትውስታ የምናስቀምጠውና የምናስታውሳቸው የፈጠራ ድርሳኖቻችን ውስጥ ነው......ይህቺን ብርጭቆ አንስቼ መጠጣቴ የእኔ ታሪክ ነው፣ እሱንም ከአንቺ ብርጭቆ ጋር ሳጋጭ አየሽ እሱም ታሪካችን ነው፣ ከአንቺ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳሳምንበት አመት፣ ቀን፣ ወር፣ ሰዐትና ደቂቃ እናውቀዋለን? ግን ይሄን በድርሰታችን ሳንረሳ እናሰፍራለን:: ያበሰበሰን ዝናብ ትንሽ ነገር ይመስላል:: ግን እሱን ልናሳልፍ ስንጠለል እዛ ስብሳብ ስር ወደ ፊት ሚስታችን ከምትሆን ደግ ወይዘሪት እንተዋወቃለን አይደል? ታዲያ እሱ የእያንዳንዱ ሰው ታሪክ አይሆንም?...... to live is to remember. Art is the highest form of rememberance. Through play and wit»

«ብሳ ምነው»

«እየበላሁ ነው:: እስኪ ውስኪዋን ጠብ አድርጊ»

«ብዙ አትጠጣ በኋላ መፃፍ ይከብድህና በእኔ እንዳታመሃኝ:: ድርሰትህን እንደ ጨረስከው ላነበው ቸኩዬአለሁ»

«እንዲህ ጓጉተሽ አታውቂም»

«ስለሞትና ስለ ሕይወት አይደለም እንዴ?»

«አለንበታ»

«አዎ»

ስብሐት ወንበሩን ደገፍ ብሎ ከውስኪው እየደጋገመ ትንሽ ትንሽ እየተጎነጨ ሚስቱን ባስገረማት ፍጥነት ሃሳብ ውስጥ ገባ:: አሁን አለ:: ቀጥሎ የለም:: ቀስ ብሎ ወደ ማታገኘው ቦታ ዓይን ዓይኑን እያየች ሽርተት ብሎ ይጠፋል:: የምናብ ዓለምና ያለችበት ዓለም እንዲህ ተቀራርበው አጥር ሳጥር በጉርብትና የሰፈሩ አይመስላትም:: ሁልጊዜ ያጋጥማታል:: ግን ትረሳዋለች:: አባብሎ እንደሚወስድ ጎርፍ መሆን አለበት እንጂ ታዲያ ዓይኖቹ ለምን የረጠቡ መሰሉ? የሚያበሽቃት ይኼ ይኼ ነው:: አእምሮው እያሴረ ነው:: ስለድርሰቱ እያሰበ ነው:: ለምን አርፎ አይቀመጥም? ምናልባት ሞትን የሚያጠፋ መድሃኒት እየፈለሰፈ ቢሆን አይገርማትም:: ጢሙ ነፋስ እንደ ነካው ሁሉ በቀስታ ይላወሳል:: የሚያስፈራ ነገር አለው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ እጆቹን ማነቃነቅ አይኖቹን እየጨመቀ የሆነ ሕመም ሊቆጣጠር የፈለገ መሰለ:: ከራሱ ጋር እየተነጋገረ ነው:: እሷ እዚህ ፊቱ በከፊል ተራቁታ ተቀምጣ ቅቤና ሚጥሚጣ የተነከረ እጁን እያነሳና እየጣለ

ለራሱ ይነጋገራል:: ከመሃል እንደተጎሰመ ሁሉ ነቃ:: ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነሳና (ሽንቱ እንደወጠረው ሰው) ወደ መፃፊያ ጠረጴዛው ተቻኩሎ ሔደ:: ያላለቀ ምግብ ያለበትን ትሪ ፋኖስ በሃዘን እያየች ተቀመጠች:: የውስኪውን ጠርሙስና መለኪያዎቹ ብቻ ሲቀሩ የበሉበትን ከጠረጴዛ ላይ አነሳሳችና ጓዳ ሄዳ ስትመለስ ስብሐት በግንባሩ ጠረጴዛ ተደግፎ ያንኮራፋል:: አልኮል ከጠጣ ብዙ ጊዜው ነው:: በተለይ ውስኪ:: የቆየ አልኮል አንድ ቀን ብቅ ካለ እንደ ፈጣን ዝናብ ነው......ይኼ 'ከወዳንጋጣ' የሚመጣው--እንዴ ከወረደ ጎርፍ የሚሆነው:: ከወንበሩ ላይ አቅፋ አነሳችው:: ከባድ አልነበረም:: ስታውቀው ጀምሮ የአካል ሚዛኑ ከባድ አልነበረም:: መኝታ ቤታቸው አስገብታ በጀርባው አስተኛችው:: ጥ ልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያለ ይመስላል:: በልቧ ትንሽ ፈራች:: ምናልባት የሰጠችው መድሃኒት ከልክ በላይ ሆኖ በዚያው ሕይወቱ ብታልፍስ? ስለሞት የተናገረው ትዝ አላትና የሃሳቡ እውነትነት አበሸቃት::

ወደ ጓዳ ገብታ ለስ ያለ ውሃ፣ ምላጭና መቀስ ይዛ መጣች:: በመጀመሪያ በመቀሱ ቀጥሎ በምላጩ ጢሙን ካስወገደች በኋላ ለጥቂት ደቂቃዎች ልጅ የመሰለው ባሏን አየች:: ያለመጨማመር ያን ጊዜ ስታውቀውና መጀመሪያ ስታየው የነበረው ዓይነት መልክ አለው:: ውብ ነበር:: ልትስመው ፈለገች:: ለመሆኑ ሲነሳ ምን ልትለው ነው? ስለሚወዳት ሁሉን ነገር ያምናታል:: የፈለገውን ውሸት ብትነግረው ያምናታል:: የሞቀ ውሃ ውስጥ በተነከረ ርጥብ ፎጣ ፊቱን ጠራረገችና ከክትፎው ቅባት ያልተላቀቁ ከንፈሮቹን በቀስታ ሳመቻቸው:: አልተነቃነቀም:: ማልቀስ ፈለገች:: መመለስ ብትችል ጢሙን:: አጠገቡ ተቀምጣ ጢሙን በሁለት እጆቿ መሃል እንደ ሰበሰበች ግድግዳ ላይ በሰፊ መስታወት ውስጥ የተሰቀለውን እሷና እሱ ሳር ላይ ተጋድመው የተነሱትን ፎቶግራፍ አየች:: በትክክል እሷ ተጋድማ ነው:: እሱ ከኋላዋ መሬት በግራ እጁ ተደግፎ ካሜራ ፊት ለፊት እየሳቀ ያያል:: የለበሰችው ያ የተማረከበትን አረንጓዴውን ቀሚስ ነው:: ጭኖቿ በግማሽ ራቁታቸውን ናቸው:: በዚያ ውበትና ልጅነት እነዚያ ሁሉ የሚያማልሏትን ሰዎች ንቃ ያገባችው ትንሽ ምቾት ከማታውቀው ቦታ ከወደ አንገጣ የሚጠብቅ ደራሲ ነው......*ደራሲዎችን ማን ፈለሰፋቸው.....ማን እግዛቤር ነው የደረሳቸው.....ለምንድነው ድሮ ያልገባት.....ለምንድነው የምታውቀው ደራሲ ሁሉ ኪሱ ጠንጋራ የሆነው*......እተኛበት እንደ ገና በለዘብታ ሳመችውና የላጨችውን ፀጉር አጠናቅራ ሰባሰባ ሰው እንዳያይባት በትንሽ የስኳር መያዣ ቡናማ የወረቀት ቦርሳ ውስጥ አድርጋ የቤቷን በር ዘግታ ወጣች::

**(ሳምሶን ዘብሄረ አዲስ አባ)**

የስካሩ ፍጥነት ገርሞታል:: ምንአልባት አልኮል ከጠጣ ብዙ ጊዜው ስለሆነ መስሎት ራሱን በመገረም ይነቀንቃል:: ምን ያህል ሰዓት አልጋው ላይ እንደተኛ ትዝ አይለውም:: ምናልባት አልኮሉና የስጋ አበላሉ ፍጥነት ተዳምረው ይሆናል እንዲህ የጣሉት:: ሺህ ምክንያቶች ይኖራሉ:: ወዲያ ወዲህ አየ:: ፋኖስ የለችም:: *የት ሄደች.....እንዲህ ሆኜ እንዴት ትታኝ ሄደች....* ጀርባውን አሞታል:: ሳይገላበጥ ለብዙ ሰዓታት ስለተጋደመበት:: ደረቱ እርጥብ

ይመስላል......ላብ ይሆናል:: ብዙ ጊዜ ሲተኛ ያልበዋል:: የቤቱ በርና መስኮቶች ዝግ ናቸው......*ፋኖስ ማር የት ሄደች*......ግን ደ'ሞ ገላው የቆሰለ ይመስለዋል:: ተኝቶ ሲነሳ እንዲህ አይደለም:: ብዙ ጊዜ ተኝቶ ሲነሳ ትኩስ ይሆናል:: የሚፋጅ ይሆናል......*መጠጥ የማይስማማኝ ደረጃ ደርሼአለሁ......መጠጥ የሚባል መተው አለብኝ*......ራሱን አካከከና አልጋው ዳር ተቀመጠ:: አልጋው ዳር ተቀምጦ የሚጫጫነውን እንቅልፍ አልቦ እንደሚያስወጣ ሁሉ ጢም ለመነተት እጁን ወደ አገጩ ሲልክ ደነገጠ:: ደጋግሞ ዳበሰ:: ፊቱን የከበበው የፀጉር ዘርፍ የለም:: በግራ መጋባትና ባለማመን አገጩን ይዞ መስታወት ፍለጋ ሳሎን ሄደ:: በቂ ብርሃን እንዲያገኝ በርና መስኮት ከፍቶ ፊቱን ሲያይ ክው አለ:: ድምፅ ሊፈጥር ትንሽ የቀረው ክውታ ነበር:: የደነገጠው ፊቱ ኡኡታ ነበረው:: *እንዴ..... እንዴ.....*

«እንዴ!?» አለ ጮክ ብሎ::

ወደ ጠረጴዛው ሄዶ እፉን በመገረም ይዞ ተቀመጠ:: እግሮቹ ሳይቀሩ ተደናግጠዋል:: ብስክሌት ፔዳል ላይ ያሉ ይመስላሉ:: እያነሳ ይጥላቸዋል:: ከመሃል ራሱን ጠየቀ......*በስካር ግፊት ገሽልጬው እንደሆነስ......ማለቴ በድንገት ምቅ ብሎኝ ሳላስበው ተነስቼ*......ምላጭ ወደሚቀመጥበት መታጠቢያ ክፍል ሄደ:: የተለመደ መላጫውን አገኘው:: ገና እርጥብ ፀጉር ውስጡ ተጠቅጥቆአል:: በጣቱ ነካው:: የጺሙ ዓይነት ቀለም ያለው ፀጉር ነው:: በስተግራ የተቀመጠውም ሳሙና እርጥብ ነው:: እጆቹን አየ:: ፀጉሮች መዳፉ ላይ እንደ ዘመሚት ተዘርተዋል:: ፀጉሮቹ የተለጠፉት በሚላጭበት ጊዜ ይሁን ወይ አገጩን ሲዳብስ ግራ ገባው:: እንደ ገና ወደ ጠረጴዛው ተመለሰ:: ፊቱን እጆቹ መሃል ደፍቶ አሰበ......*በሕልሜ ከሆነስ......ወይስ ፅላሎት ነው*......ስለ አጋፋሪ እንደሻው ልጅ ስለ አላዛር ሊፅፈው ያቀደው የተበገረ ሃሳብ ነበረው:: ያ ሃሳብ ከሚሞቅ፣ ደስ ከሚል ሕልዮ በላይ ግን አልተነሳም:: ከዕንስ በላይ ገዝፎ ወረቀት ላይ ወጥቶ አልወደቀም:: በብዕሩና በወረቀቶቹ መሃል ለጋ ስሜት ሆኖ እየተርገበገበ፣ እንደ ትንኝ ልብ እየመታ ነበር:: በምናቡ ሊይዘው፣ ወደ ድርሳን ሊበትነው ሲፍጨረጨር እንደ ትኩስ አሁን እንደተቆረጠ የቁልቋል ዘር እያዳለጠ ይሸሸዋል:: ወይም ሌላ ከነፋስ የተሰራ፣ ጠረን እንኳን የሌለው ልዕለ-ሰብአዊ እጅ ሳያቋርጥ ከእንኅሉ ኪስ የሚያወልቅበት:: *ምን ሆንኩ ከመተኛቴ በፊት እንደ አዋሽ እየፈሰሰ አልነበረም?*

## (መስኮት ገረሱ)

ገረሱ ዘበኛ ነበር:: አንድ ማታ እሚሰራበት ቦታ በጨለማ መስኮት አጠገብ ቆሞ ሳለ አንዲት ሴትዮ ፊት ለፊቱ ያለ መንገድ ላይ ወዲያ ወዲህ ስትመላለስ ያያል:: እሷው ቀድማ አይታው ኖሮ ቆም ብላ፣ ፈገግ ብላ፣

«አንተ ሰውዬ ምን ትሰራለህ እዚህ?» ትለዋለች:: እንዳልገባት::

«ቤት እየጠበቅሁ ነዋ! ሌላ ምን ይመስላል?» ይላታል::

«መግባት እችላለሁ?» ትላለች::

«ግቢ» ይላታል::

ሴትዮዋ ወይዘሮ ስንዱ ነበረች:: ማለዳ እጅግ ማለዳ (ማለዳ ማለዳ ጀግና ሰው ማለዳ እንደሚለው ዓይነት ዘፋኝ) ስንዱ ከዚያ ገረሱ ከሚጠብቀው ቤት ወጥታ ወደ ምትሄደበት ትሄዳለች:: በሚቀጥለውም ማታ ሲመሽና ገረሱ በሚያድርበት ቤት በኩል የሚያልፈው የመንገደኛ ብዛት ሲስነስን ስንዱ ተጣጥባ የሱዳን ሽቶዋን ነስንሳ ትመጣለች:: እንዲህ እንዲህ እንዲህ ሲል በመጨረሻ ይጋባሉ:: ትንሽ ቆይተውም ይወልዳሉ:: የወለዱት የመጀመሪያ ልጃቸው ስሙ መስኮት ተባለ::

መስኮት ለምን አሉት?

«መስኮት ለምን አልኩት መሰለሽ?» ትላለች ስንዱ ያለማፈር ሰው እንኳን ሳይጠይቃት::

«ገረሱዬን ያጠመድኩት መስኮት አጠገብ ቆሞ ነው:: አይ ሲያምር:: ጥርሱ አጀራን[25] የመሰለ፣ አሸርባ[26] ካቦርታው እንደ እሱ የሚያምርበት የለም:: በትከሻው መስኮቱን ድፍን አድርጎ ይሞላው ነበር:: የአምቦ ልጅ ደረት:: አፍረቴን ጥዬ አነጋገርኩት:: ሁልጊዜ መስኮት አጠገብ አታጭውም:: ሙች»

ገረሱ እስከ ዛሬ ስንዱን:

'ለምን ማታ ማታ ሰው በሌለበት ተደብቀሽ እኔ ጋ እየመጣሽ አብረሽኝ ታድሪ ነበር?' ብሎ ሲጠይቃት እሷ ለእሱም ለማንም የምታወራው ትከሻው ስለማረካት ነበር:: ቁመቱም ስለማረካት ነበር......ያ ኡታ[27] የመሰለ:: ይሄ ብቻ አልነበረም:: ስንዱ ግን ታውቃለች ገረሱን በራዕይ እንዳየችው:: ከመዝሙዕቱ ራዕዩ[28]: በሕልሟ አንድ መልኩን ማየት የተሳናት ብርሃን ውስጥ የተቀመጠ ሰውዬ: 'መስኮት ጋ በጨለማ የቆመ ትከሻው ሰፊ ሰው ታገኚያለሽ:: ሁልጊዜ መስኮት አጠገብ የቆመ ነው(ለምን እንደሚቆም ራሴ አይገባኝም):: የምታገኚውም መስፍን ሐረር መንገድ ላይ አዲስ የሚሰራ ቤት ውስጥ ጨለማ ለብሶ ነው:: ስራው ጨለማ ውስጥ ነው:: ትከሻውም ላይ ዱላ እንደ ውዥግራ ይሸከማል:: እሱ የወደፊት ባልሽ ነው:: ከእሱም መልካም ትወልጂያለሽ'

ብታወራው ስለማትታመን አፏን ይዛ ራዕይዋ በጠቆማት ጎዳና በሚቀጥለው ምሽት መመላለስ ጀመረች:: ስትመላለስ ገረሱ ከመስኮት ኋላ ቆሞ በመሰራት ላይ ያለ ትልቅ ቪላ ቤት እየተንጎራደደ ሲጠብቅ ታያለች:: መጀመሪያ ላይ ብትፈራም የራዕይዋን ምክር ግን ተከተለች::

መስኮት ልጇስ?

መስኮት ግን ሲያዩት በራዕይ የሚነገርለት አይመስልም:: ከረከንድና

---

25 በወላይታ አውራጃ በበለሰ ወረዳ የሚገኝ ፏፏቴ

26 (ወላይትኛ) ወፍራም ደጎስ ያለ

27 (ወላይትኛ) እንሰት

28 (ግዕዝ) ራዕዩም እንደዚህ ነው

አስቀያሚ ነው። የአባቱን ትከሻም ይሁን የእናቱን ድምብላልነት አልወረሰም። እናቱ 'ልጄ እጥር ምጥን ያለ ነው' ትበል እንጂ ደረጃ ለመውጣት ሲውተረተር፣ በመንገድ አብራው ስትሄድ ሰው ሁሉ በመገረምና በማዘን ሲያየው፣ ደጋግማ ራዕይዋን ትጠራጠራለች። ራእዩ ያታለላትም ይመስላታል። በብርሃን የተከበበው ሰይጣን ራሱ ይሆናልም ትላለች፡

'ሰይጣን እኮ ያው እንደ እግዚአሔር ክንፍም ብርሃንም ይኖረዋል እሱው እንደዬው ካልጠበቀን' ትላለች፣ ስለ አየችው ራዕይ ሳትናገር።

መስኮት ዕድሜው ሃያ ሲደርስ ቁመቱ አራት ጫማ ተኩል ነበር። ግን ይኼን የአካል ጉድለቱን የሚቀናቀን የተባ አእምሮ ነበረው። በሃያ ዓመቱ የአገሪቷ ታላቅ ሰዓሊዎች ከሚባሉት አንዱ ነበር። እስክንድር፣ አፈወርቅና ዘሪሁን በአንድ ቃል፡ 'በዚህች ዓይነት ትንሽ ገላ የዚህ ዓይነት ታላቅ ሰዓሊ መኖሩ ትንግርት ነው' ብለዋል። 'ዘ ጃይንት ኦፍ ኢትዮጵያን አብስትራክት ኤክስፐረሺኒስት ፔይንቲንግ' ብለው የጠሩት ጋዜጠኞች ብዙ ነበሩ።

ይኼ ታላቅነቱ ቢወሳም ልቡ ግን በደስታ አልሞላም። ድንክ መሆኑና ነጋ ጠባ በጎሪጥ መታየቱ ሳይሆን መነሾው፤ ብዙ መስራትና መሳል ፈልጎ ባልጠበቀው ወቅት የመፍጠር አቴቴው የት እንደሄደች ሳትነግረው መጥፋቷ ነበር። ቀድሞ ለሳምንትና ለሁለት ሳምንታት ተሰውራ አሰቃይታው አሰቃይታው ተመልሳ ትመጣ ነበር። እንደ ድብብቆሽ። እየቆየ ለወርና ለሁለት ወር ከእሱ መሰደድ ጀመረች። በመጨረሻ ፍሬ ያለው ነገር ሳይወጣው፣ ገና ከጉብኝቷ ያገኘው መረጋጋት መልክና ስር ሳይዝ፣ ፍሬም ሳያፈራ፣ ፍርሃት ፍርሃት እንዳለው እተቀመጠበት የመከነ ብሩሹን እንደያዘ እንደኛውኑ ተወችው። ሲመስለው ይኼንን ሁኔታ ከሚያመቻቹት ነገሮች (ነገር ከተባለ) አንዱ ከተወለደ ጀምሮ እስከዛሬ ፍቅር ያልያዘው መሆኑ ነው። እንደ አስገራሚ ፍጡር አይተው ከሚያወጡት 'አርቲስት እንወዳለን' ከሚሉ ቀለብላባ ወይም አስቀያሚ ሴቶች በስተቀር ልቡን የያዘችው እንስት አልነበረችም።

በተለያየ ጊዜ ይኼን እጥረቱን ሲናገር፡ 'ሲያምርሽ ይቅር' ዓይነት ያሽሟጥጡታል። ወይም በሙያ ልዕልናቱና በዝንኝነት ስፋት የበለጣቸው ወይም የቀኑበት 'አስፈላጊ አይደለም' ይሉታል። እንዲህ እያለ እያለ ጊዜ ሲያልፍ የስዕል ችሎታው እየቀነሰ የሚስላቸው ስዕሎች ጉልበትና ግፊት እያጠራቸው መጡ። የተደበረ ዝነኛ ሆነ። ቀንም ይመጣል ሲመስለው 'ብሩሽ መጣል'[29]

29 ስዕል መሳል(መስኮት የሚጠቀምበት ቃል)። 'ሰዓሊ ነኝ' ለማለት 'ብሩሽ ጣይ ነኝ'፡ 'ልሳል እስኪ' ሲል 'ብሩሽ ልጣል እስኪ' ይል ነበር። ይሄን አባባሉን ሰዎች ሲተቹት ለማብራራት ሲል ሁለት ሃሳቦች ወርውሯል። አንደኛው ሃሳብ ይሄ ነው፡ '......በሌላስ አባባል *የፊደል አጣጣል* እንላለን ማለት የፊደል ግራፊክስ ውበት ስንጠቅስ። ለምን ይሄን ለሰዓሊዎች ወስደን *ቀለም አጣጣል* አንልበትም። ከፊደል በፊት ስዕል ስለ ነበረ የፊደል አጣጣል የሚለው አጠቃቀም ከጥንት ሰዓሊዎች የተወረሰ ሊሆን አይችልም? ቀለም ደግሞ ያለብሩሽ አይሆንምና ብሩሽ አጣጣል ብንልስ? ሰዓሊነትንስ *ብሩሽ ጣይነት* ብንለው?' በስነድምፅ (phonology) በአንድ ትንፋሽ የሚነገር ድምፅ ወይም የድምፅ ስብስብ 'ቀለም' ይባል የለ። 'ሆሄ' ወይም ፊደል ሌላው ስሙ 'ቀለም' አይሆንም? እነዚህ ሆሄዎች ተሰብስበው ትርጉም ይኑራቸው አይኑራቸው ብቻ ያው 'ቀለም' ይባሉ የለ። በዚህ በኩል የቋንቋ ጠቢባን ቢረዱኝ ደስ ይለኛል። ገና የተዋጣለት ተነካናኪ አይደለሁም። ሁለተኛው ሃሳብ ደሞ ይሄ ነው፡ 'ስዕል መሳል ከጠጠር መጣል ጥንቆላ ጋር ስለሚመሳሰልብኝ ነው። አንዳንድ ኪነታዊ ውጤቶቼን ሳይ በአብዛኛው ሳላስባቸው የመጡ ናቸው። ከየት መጡ?

ተስኖት ነገር ተስኖት እንደ ጎርፍ የሚወርዱ አዲስ ወጣት ሰዓሊዎች እላዩ ላይ ተደፍተው በአዲስ ደለላቸው ከታሪክ ዓይኖች ጋርደውት:: እዚህ ዓለም ላይ ችግሩን የሚሰማው አላገኘም:: አባቱ ገረሱ ስዕል እየሸጠ ባመጣው ገንዘብ ቁጭ ብሎ ወፍራም ጠላ ከመመግመግ፣ እናቱም ባለቻቸው ትርፍ ጊዜ በየሰፈሩ እየዞሩ ስለ ልጃቸው ያለፈ ዝነኛነት ከማውራት በስተቀር 'እህ' ብለው አያዳምጡትም:: ለማውራት ብሎ ካወራቸው ቢብስ ቢብስ 'እሱ ያመጣውን እሱ ይመልሰዋል' ይሉታል:: ግን አንድ ሰው አስቀምጦ ችግሩን ጭንቀቱን ይሰማው ነበር:: ስብሐት:: ለመስኮት ልዩ ፍቅር ስላለው ሳይሆን የስብሐት ጆሮ ማንንም ለማዳመጥ ሁልጊዜ እሱ ራሱ ስብሐት እንደሚለው 'እንደ ጋለሞታ ቤት በር ክፍት ስለሆነ ነው':: ሊዘጋው አይፈልግም:: 'ትዕግስተኛ ነህ እባክህ ተቀምጠህ የሰው ጣጣ ስትሰማ' ሲሉት......'ምክንያቱም' ይላል እሱ፡ 'በብዛት ስለድምፆች ስለምፅፍ ነው' 'ድምፅን በቃላት መመዝገብ እወዳለሁ' ይላል:: ወይም እሱ ባይለውም......ተራ ድርጊት መስሎት–ያው እንደ አገሩ ባሕል ወሬ ይወዳል:: በተለይ በአፍ የሚነገረውን::

ይኼ ሁሉ ተሰባስቦ በአጠቃላይ ሲታይ መስኮት ድንኩ ብቸኛ ዝነኛ ነበር::

መስኮት ገረሱ የገረሱ ዘበኛው ልጅ ያ በራዕይ መሪነት የተወለደው የግል ሕይወቱ ራዕይ አልነበረውም ወይም እየተበለሻሸ ነበር:: ከሁሉ ከሁሉ ግን ከሚያፈቅረው የስዕል ስራ መለያየቱ ለልቦናው ይከብደዋል:: ስዕል ከሳለ ጥቂት ዓመታት ቢያልፉትም ኤግዚብሽን ባለባቸው ቦታዎች ግን ቀርቶ አያውቅም:: የኪነት ፍቅሩ የሚፈራውን ያህል ከነፍሱ መስክ ላይ ተነቅሎ አልተሰደደም......

አንድ ዓርብ ከሰዓት በኋላ አራት ኪሎ ጀርመን ካልቸራል ኢኒስቲትዩት የስዕል ኤግዚብሽን ሊያይ ሄዶ ስብሐትን ያገኘዋል:: በመጀመሪያ ስብሐት አልመሰለውም:: ቀዝቃዛ ውሃ የፈሰሰበት መስሏል:: ስብሐትን የሚያውቀው በብብቱ መፅሐፉን ይዞ (የሚያዋራው ሰው ካጣ ቁጭ ብሎ ሊያነብ) ወዲያ ወዲህ እያለ ከሰዎች ጋር በከፍተኛ ድምፅ ስለ ስዕል ሲያወራ (በተለይ ስለ ስፓኒሹ ሰዓሊ ማነው እሱ እቴ አዎ ሳልቫዶር ዳሊ) ሲስቅና የሪሴፕሺኑን ወይን (ይኸቺን እንደሚወድ ሁሉ ያውቃል) ሲሻማ ነው:: ዛሬ ስብሐት ቀዟል:: ለብዙ ቀናት ዕንቅልፍ ያልተኛ ይመስላል:: መስኮት ስብሐትን እንዳገኘው እየጨበጠ አቀፈውና ስለመጥፋቱ ሲናገር:-

«በል ተወኝ አንተ ድንክ ልረፍበት:: እዚህ ለምን እንደመጣሁም አይገባኝም» ይለዋል:: መስኮት እንደቀድሞው ሊቃለደው መስሎት:

«ምን? ምነው ከሞት የሚሸሸው አጋፋሪ ሳትጠብቀው ሞተብህ እንዴ? አጋፋሪ ሸወደህ እንዴ?» አለው

ስብሐት መስኮትን ከላዩ አላቀቀና

---

ማን መራኝ? እነዚህ ጥያቄዎች ያገሬን ጠንቋይ ያስታውሱኛል፡ የኪነት የፈጠራ ሂደትን የአስማታዊነት ፈርጅ አያለሁ:: ከየት እንደ መጡ ካላወቅሁ ከጠጠር ጣይና ከኮከብ ቆጣሪ ምን ይለየኛል?':: (አብዘርቨር መፅሔት፣ ቅፅ:? ቁ:?) እነዚህን አገባቦች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ብዙ ሰዎች ይጠቀሙባቸው ነበር::

«ምን የተለየ ነገር ታያለህ ፊቴ ላይ?» አለው

«ምን ሆንክ? ምንም:: እንጃ አንድ ነገር ጎሏል»

«አንድ ነገር?»

«ምን? ምን እንደሆነ አላውቅም»

«ጢሜ የለም»

«ምን መሆንህ ነው? አለ:: ይኼውና»

«አብደሃል? ከጢሜ ጋር ብዙ ዓመት ኖረኻል:: ግን ተገፎ እያየኸው እንኳን 'የት ሄደ?' ብለህ አትጠይቀኝም»

«ምነው ከመቼ ወዲህ......»

«ለጢም አሰብክ?» ብሎ ጨረሰለት::

«ኖ ኖ ኖ ለገጽህ ውበት ተጨነቅህ? ለእኔ ጢምህ ይታየኛል:: ይኼ ምንድነው?» ብሎ ከስብሐት አገጭ ዝቅ ብሎ የሆነ ነገር ጎተተ::

«መከመክህ ነው? ጢሜ የለም:: አንተ ብትሆን ኖሮ.......ችግርህን አምኖ ተህ ትዘረግፍብኝ ነበር:: አንተ ብቻ አይደለህም:: ሰው በሙሉ ገፄ ተለውጦ እያየ ያላየ ይመስላል»

«መስከት ነኝ አልዋሽህም»

«እንደውም ስዕል ስራህን የገደለው ውሸትህ ይሆናል»

«ምን? ምን ሆንክ ስብሐት?»

«ጢሜ እኮ ተራ ጢም አልነበረም»

«ምን ሆንክ ስብሐት? ጢም ሌላ ስም እስካልተሰጠው ድረስ ጢም ነው»

ጭቅጭቃቸውን የሰሙ አንዳንድ ሰዎች ዞር ዞር እያሉ ሲያዩ ለመጀመሪያ ጊዜ መስከት ፍርሐትን ስብሐት ፊት ላይ አነበባት::

«ምን ሆንክ?» አለ ደገመና

«ጢሜ ጠፋ» አለ ስብሐት ወደ መስከት ጆሮ ጠጋ ብሎ ድምፁን ዝቅ አድርጎ

«አለ:: ምን ብሎ ይጠፋል? ሳትላጨው ይጠፋል?»

«ተኝቼ ስነሳ ጢሜ የለም» አለ:: አሁንም እጆቹን ኪሱ ከቶ ቆመው የሚያዩትን ሌሎች ሁለት ሰዎች የሚያናግር እየመሰለ

«በል ወጣ እንበልና አየር እንቀበል»

ያዩአቸው ሰዎች ስለ ሳንሱር ያወራሉ:: ስብሐትና መስከት ሊመውጣት ወደ በር ሲያመሩ ማውራታቸውን አቁመው ወደ እነሱ ዞር አሉ:: ስብሐት ተገርሞ ያያቸዋል:: ሊናገር እንደፈለገ ሁሉ ግራና ቀኝ አየና ሳሉን ሳለ::

መስኮት ያየዋል::

ከዚያ:

«ምነው? ሳንሱር ሳንሱር:: አበሻ አንድ መፅሐፍ ይፅፍና ለሳንሱር ይጨነቃል:: የፈረደበት መንግስት:: ሳንሱራችን ምቀኝነት እንደሆነ አይገባውም:: ሳንሱር ማለት መውደድ የለበሰ ምቀኝነት ነው:: ደራሲ ለደራሲ ሳንሱር ነው:: ፖለቲከኛ ለፖለቲከኛ ሳንሱር ነው:: ራሴ ውስጥ ሳንሱር አለ:: ሚስቴ ሳንሱር ናት......»

መስኮት በመገረም አየው:: ስብሐትን ባልተጠራበት ቦታ ተቀናቃኝ ሃሳብ ሲያቀርብ አይቶት አያውቅም:: 'ጨዋ' ተብሎ በራሱ ማጉተምተም ተጋርዶ ያልሰማ መስሎ ያልፋል እንጂ::

«እንሂድ» አለው መስኮት

«ምን ያያሉ? የማይረባ ወሬአቸውን እዚያው በየጓዳቸው እንደለመዱት አይተረትሩትም? ብሽቅነት ነው»

ስብሐት ከተረባቸው ሰዎች አንዱ መስኮትን እያየ ጣቱን ቅንጡ ላይ ተክሎ 'ስብሐት አብዶአል ወይ?' ብሎ ያለ ድምፅ ለመናገር ሞከረ::

«ምን ማለትህ ነው?» አለ መስኮት ሰውዬው ላይ አንጋጦ አፍጦ:: ሰውዬው ተደናገጠ::

«ምንድነው በጣትህ የምትቆፍረው? የተናገረው እኮ ልክ ነው:: እንድንወጣ ስመክረው ጊዜ ጠላቱ የሆንኩ መሰለህ? ስንት ስዕልና ድርሰት ሆነ ብለህ አሳስተህ ተርጉመህ አርቲስት አበሳጭተሃል?»

ሰውዬው በድንጋጤ ፊቱን ሲያዞር የቀሩት አብረውት የነበሩት ሁለት ጓደኞቹ የመስኮትን ድንክነት ለማንጓጠጥ ከፍ ዝቅ አድርገው አዩት::

«ጠንጋራ ሁሉ:: እኔ አጥንቴ ድንክ ነው እናንተ ደ'ሞ ልቦናችሁ ጠንጋራ ነው:: ሃሜተኛ ሁሉ»

ስብሐት እየሳቀ መስኮትን ወደ ውጭ እንዲወጣ መጎተት ጀመረ

«መስኮት እኮ ነኝ አታውቅም? አቃጣሪዎቻችሁ ለዘመናት የዳከሩበትን ሽራ በጥቂት ወራት የለወጥኩ:: ደደብ ሁሉ:: ዝም ብላችሁ ወግና ነገር ጠምጠሙ»

ስብሐት ሁሉ ሰው ፊት ያለ እፍረት አንጀቱን ይዞ ይስቃል:: መስኮትን ጎትቶ ካወጣው በኋላ:

«አበድክ?» ይለዋል

«ለአንተ ነው የምከራከረው»

«እኔ ልነጅሳቸው ነው:: መነጀስ እኮ መጣላት አይደለም»

«ልካቸውን ሰጥቼአቸዋለሁ:: እስ ሆልስ[30] የአንዱ የቅርብ ጓደኛው ሳንሱር እኮ ነው የሚሰራው:: ጉቦ እየተቀበሉ ያሳልፋሉ እማምላክን......ጉቦ እየተቀበሉ ይጥላሉ:: የምትጠላው ደራሲ ካለ ጉቦ ሰጥተህ እንዲጥሉበት ማድረግ ትችላለህ:: ይኼን ነው ወደ ፊት ለወጣቱ የሚያወርሱት:: በቅቧቃ ሁላ:: ከዛ እንደማያውቁ......ልክ እለ አይደለ ያማርራሉ ፊውዳሊዝም ያማርራሉ ወይ ኢምፔሪያሊዝም:: ማርያምን:: ሆ ሆ ሆ:: ምን ይደብሩናል? መርዝ ሁላ»

«ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም:: በሰላም የምጠጣበትን ጊዜ አበላሸህብኝ»

«እንመለስ ከፈለግህ»

«በል ተወኝ»

«አንተ ነህ ጢሜ ጠፋ እያልክ!......» መስኮት ጮኸ

«ምን ሆነ?» አሉ እውጭ ተደርድረው ከቆሙት ሰዎች አንዱ::

«ምንም:: ፀሐይ ላይ አትቀመጥ ስለው ስብሐት ቢነግሩት አይሰማም»

«የፀሐይ ምች ይሆናል» አለ አንዱ ኮስተር ብሎ የዕውነት ለመምከር::

«መሆን አለበት:: ከአምባሳደር ቲያትር እዚህ ድረስ በእግሩ ነው የመጣው ይታያችሁ:: ያ የፖሊስ ጋራዥ ዳገት እንኳን ሰው ፍየል ይገላል» አለ መስኮት እየሳቀ::

«ሃሃሃ» አሉ ሰዎቹ በሳቅ

መስኮት ስብሐትን እየጎተተ ወደ ውጭ ወጣ:: ብዙ የስዕል ተመልካች ገና እየገባ ነው:: መንገድ ዳር በስተግራቸው ሁለት የሚያውቋቸው ሰዓሊዎች ፈገግ ብለው ቆመው ወደ አዳራሹ የሚገቡ ጎብኚዎችን ያያሉ:: ሲመቻቸው ያስተናግዳሉ::

«ምነው መስኮት ወደ የት ነው?» አለ አንዱ ስሌን ባርኔጣ ያደረገ ሰዓሊ

«አታይም ስብሐት የፀሐይ ግላጭ አግኝቶት ተዳክሞ:: እቤቱ አስተኝቼው መጣሁ»

«እንደ እኔ ሳር አታደርግም?» ብሎ ሳቀ ሰዓሊው......መስኮት እየገለፈጠ አለፈው......

«ምንድን ነው የምትለው?» ይለዋል ስብሐት......

መስኮት ዝም ብሏል......

ብዙ ሳይርቁ አንድ ቡና ቤት ገቡ:: እንደ ተቀመጡ ስብሐት ቢራ፣ መስኮት ቀዝቃዛ ኮካ አዘዙ::

«የሆንከውን ንገረኝ» አለ መስኮት በለሆሳስ፣ ወለል የማይነኩ እግሮቹን በጉጉት እያንቀሳቀሰ::

«ሰዓሊ እንደ ደራሲ ወሬኛ ነው እንዴ?» አለ ስብሐት ቢራውን እስከ ግማሽ በአንድ ትንፋሽ ጨልጦ:: ስብሐት የመጀመሪያ ቢራውን ሁልጊዜ የሚጠጣው እንደ ውሃ ነው:: ቀጥለው ያሉትን ቁጥሮች እንደ ቡና::

«አትቀልድ አሁን»

«ችግሬን ድንክ ሊያቃልለው አይችልም:: መቀለዴ አይደለም:: በዚያም ላይ ብሩህነትህን እጠራጠራለሁ:: የሂንዱዎች አምላክ ሺቫ እምን ላይ ቆሞ እንደሚደንስ ታውቃለህ? ድንክ አናት ላይ» አለ

«ምን ይጠበስ?» አለ መስኮት

«ድንክ የድንቁርና ተምሳሌት ነው»

«በስመአብ በስመአብ:: ዘመዶቼ ሂንዱ ያልሆኑት ለዚህ ነው:: አይመለከተኝም:: እንኳን እኔን መሃታማ ጋንዲን አይመለከትም»

«ብትሰማው እና ብታምነኝ የሆንኩትን ያኔ የዕውነት በስመአብ ትላለህ»

«እሺ ንገረኝ»

«ጢሜ አልኩህ»

«ጢምህ አለ:: ጢም ባይኖር ጢም አያድግም?»

«ያ የተለየ ጢሜ ካሌለ የጀመርኩትን ልብወለድ መጨረስ አልችልም፣ ከጠፋ በኋላ ደሞ አላደገም......እያየኸው?»

«መቼ ጀመርከው? ጢምህስ መቼ ጠፋ?»

«ሁለት ሳምንት ሆነኝ ከጀመርኩት:: ጢሜ ከጠፋ ሁለት ሳምንቱ»

«ሁለት ሳምንት? እርግጠኛ ነህ? መፃፍ ያልቻልከው ጢምህ ጠፍቶ ሳይሆን ሌላ ሊሆን አይችልም?»

«ግምት ነው? ስለ ግምት አይደለም የማወራው»

«እንበለው ግምት»

«አንተ ምን ሆነህ ነው ለብዙ ጊዜ ያልሳልከው? ወይ ብሩሽ ያልጣልከው?»

«ምናልባት የሚቀሰቅሰኝ ነገር ስለጠፋ»

«ምን ይቀሰቅስሃል?»

«ስለ አንተ ነው የምናወራው»

«ችግርህን መፍታት ሳትችል እንዴት የእኔን ችግር እፈታለሁ ትላለህ»

«ነገርኩህ የሚመስለኝን»

«የሚቀሰቅስህ ምንድን ነው? አንተ የሚመስልህ»

«አንተን ምን ይቀሰቅስሀል?»

«የእኔ ቀስቃሽ ፋኖስ ነበረች»

«ነበረች?»

«እዎ:: ከመሃል ጢሜ መጣ:: ጢሜ ይቀሰቅሰኝ ጀመር»

«ለምን ወደ ጢምህ ሄድክ?»

«ራሱ መጣአ»

«ምናልባት ፋኖስን መውደድ አቁመህ እንደሆነ»

«እምልህ እንደ ድሮው አላፈቅራትም:: ትዳር የሚያደክም ነገር አለው»

«መሰልቸት በለው:: የእኔ ችግር ደ'ሞ መውደድ አለመቻል ይሆናል»

«ሴቶች ድንክ አይወዱም»

«ምን ታሾፋለህ? የሴት አጭር የለውም ልትለኝ ነው?»

«ስለ ድንክ ነው የማወራው......እውነቴን ነው......ድንክ ሴት እንኳን አለአቅሟ ረዥም ወንድ ትፈልጋለች......ትርጉም የለውም:: ግን እንደዛ ነው»

«አንተን ብሆን ፋኖስን እፈታታለሁ:: ከለበን ጋር እንደምትወጣ ታውቃለህ?»

«የአሉባልተኞች ወሬ ነው:: አንተም እዚህ ውስጥ ገባህ? ስዓሊዎች መፍጠር ሲያቅታቸው ወሬኛ ይሆናሉ፣ ማነው እንዲህ ያለው?»

«ማንም አላለም:: በአይኔ ነው ያየሁት:: አንተም ይገባሃል:: እንደምታውቅ አውቃለሁ:: አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ ነው»

«እንደ ምትወደኝ አውቃለሁ:: ከእኔ የበለጠ ማንን ትወዳለች ቢሉህ እኔኑ ነው»

«ችግራችን አንድ ቢሆንስ? የቅርፁ ነገር እንጂ:: አንተ በትክክል የማትቀርብህን ውስጥ ቤተኛ አድርገህ ስትሸሽህ፣ እኔን ደ'ሞ ከውጭ ሴቶች ድንክ ባለመውደዳቸው ወይ እኔ ቀሽም ሆኜ ስለ ራቁኝ:: ሁለቱም የርቀት ነገር ይሆናል:: የአንተ አይታይም እንጂ. ቢታይና ቢጠና ከእኔ ያልተለየህ ከሆንክስ»

«ስዕል አድርገው ከመሰለህ»

«በአጭር ጊዜ ውስጥ ራስህን የምትቃረን ሰው ሆንክ? የፋኖስን ጉዳይ በአይኔ ያየሁት ነው፣ ከሁለት ነው ከሦስት ሳምንት በፊት በጠዋት የት ነበረች? ጠዋት ላይ ዘውዲቱ ሆስፒታል አጠገብ ከፍልውሃ ስወጣ አንድ ግቢ ስትገባ አይቼአታለሁ:: እማን ግቢ ነበር የገባችው? ለበን ቤት ነው፣ በዚያ ሰዓት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ወይም አንድ ሰዐት ተኩል ላይ እሱ ቤት ምን ትሰራለች? ሁኔታውን ለማጣራት በቤቱ አጠገብ ሳልፍ ተቃቅፈው አላየኋቸውም? የለበን ቤት ፎቅ ላይ ነው:: ፎቁ በረንዳ አለው ሳታውቀው አትቀርም:: ተቃቅፈው ያየኋቸው በረንዳው ላይ ነው:: አሁን እንዳትዋሸኝ:: በጣም ስለምትወዳት እንዲህ ዓይነቱን መረጃ ትክዳለህ»

«አሁን የምትነግረኝ ውሸት ሊሆን አይችልም?»

«ማመን አለማመን የራስህ ጉዳይ ነው»

ስብሐት አተኩሮ አየው:: ቀኑ ጢሙ የተገፈፈበት ዕለት እንደሆነ ገምቶአል......*በዚያ ሰዓት አካባቢ ፋኖስ ቤቷ አልነበረችም:: ቤት ውስጥ ካልነበረች የግድ ለበን ጋ ነበረች ማለት ነውን......ፍልውሃ አይቷት ሊያማላኝ ለበን ቤት አየኋት ሊል አይችልም? ማነው ይሼ ድንክ ስለ እኔ ብዙ ማወቅ የሚጓጓ የሚያውቅስ......*

«እንዴት ልመንህ?»

«አንተ ባለህበት አነጋግራታለሁ ከፈለግህ»

«አፏን አትችለውም»

«መረጃውን አቀርብላታለሁ:: ካልሆነ ታብራራለች»

«ቤቴ ጉዳይ ውስጥ አትግባ ተው:: የፈለጋትን ታድርግ:: ግን ማመን ይከብደኛል:: አይመስለኝም»

«መዋደዳችሁ ቢቆምም እንድትለያት አትፈልግም:: እንዲህ እንደ አንተ ያየሁትን እውነት ክጄአለሁ:: አድርጌዋለሁ በፊት»

«ደ'ሞ ከማን ጋር አደረግህ?»

«ሌላ ጊዜ እንጫወታለን»

«ቦቅቧቃ»

«ታውቃለህ ቤትህ መጥቼ እንደማላውቅ?......»

«መጥቼ አላውቅም?» ስብሐት ያሰበ መሰለ

«ለምን?» አለ ቀጠለና

«ቤትህ ውስጥ ቢራ አይበቅልማ......»

«በል ዝም በል» አለ እጁን እያወናጨፈ

«እንግዳ ተቀባይ ባትሆንም እስኪ ቤትህ እንሂድና ቆንጆ ሚስትህን እንፈትሻት»

«ብታገኛት ትጠላለህ?»

«ማፍቀር ነው የምፈልገው:: መፈቀር ነው የምፈልገው»

«በል ይኼ ስኳርህን ጨርስና እንሂድ»

## (በረካ ስለሚኳት ሴትዮ)

የስብሐትና የፋኖስ ጎረቤት:: የንግድ ማተሚያ ቤት ሰራተኛ ናት:: ፀሐይ ምናምን:: ከአራት አመት በፊት ባሏን እየዘፈነች የፈታች:: እናትና አባቷ

የወለዱት ሦስት ሴቶችን ነው:: ሦስተኛዋ ናት:: ትልቅ እህቷ ከፖፖላሬ ወረድ ብሎ የታወቀ ጠጅ ቤት አላት(አቦሊ የሚሏት):: መሃከለኛዋ ደ'ሞ ሜታ አቦ ወረዳ አስተዳዳሪ አግብታ ትኖራለች(ረጃቲ የምትባል):: በረካ ሰፈሯ ውስጥ ከሰኞ እስከ አርብ ፊቷ ብዙ አይታይም:: ቅዳሜና እሁድ ከሰዓት በኋላ ባሏ የተወላት ትንሽ ቤቷና ግቢዋ ውስጥ ፀሐይ እየሞቀች ረዥም ቁጭራ ፀጉሯን በቅባት ስትነክር፣ ስትሞነጭር፣ ስትጎተት፣ ስትጎነጉንና ስትፈታ ትውላለች:: እንግዳ እንኳን ቢመጣ የምታስተናግደው የቆመ ፀጉሯን ያለ ማፈር አቁማ ወዲያ ወዲህ በማለት ነው:: ቡና የሚጠጡት ጎረቤቶቿ የፀጉሯና የገላዋ ቅባት በነካው ሲኒ መጠጣት ሰልችቷቸው ራሳቸው ቡና አፍዪ ሆነው ይቀመጣሉ:: ወይ የራሳቸውን ሲኒ ይዘው ይመጣሉ:: በእሷ የዕድሜ ክልል እንዳሉ ወጣቶች እዛው ቅርቧ 'ፒያሳ ወጣ ብዬ ልታይ' የመሰለ ነገር ሲያልፍ ከነካት ከረመ:: በረካ ገና ሃያ አምስት አመቷ ነው:: ግን ተሰላችታለች:: ምን እንዳሰለቻት ቢጠይቋት የምታውቅ አትመስልም......አንዳንዴ ጠጉሯን በቀስታ እየጎተተች ጀርባዋ ላይ የሰንበት ፀሐይ ጨረር እየወደቀ ጉልበቶቿ ላይ በክርኖቿ ተደግፋ ለሰዓታት አይኖቿን አንድ ቦታ ያውም አፈርና ጠጠር ላይ ተክላ ታስባለች::

ከአምስት አመት በፊት 'እህቴን ልጠይቅ' እያለች ሜታ አቦ ትወርድ ነበር:: እና እዛ የቢራ ቤቱ አስተዳዳሪ ከሆነ ሰው ጋር ትተዋወቃለች:: መተዋወቁ ከባድ አልነበረም:: እህቷ ከሕዝብ ግንኙነት ሃላፊው ጋር ተጋብታለች::

በተልፈሰፈሰ፣ በተዘባረቀ፣ በደበዘዘ እና በተሰላቸ ስሜት የምታስበው የዚያን ጊዜውን ደስታ ነው:: በወጣትነት ዕድሜ በባለጌ ወጣት የሚደረገውን ሁሉ ያደረገች ይመስላታል:: ብልግናዋን የጨረሰችው ከእሱ ከመጀመሪያው ባሏ ከታደለ ጋር በነበረች ጊዜ ሳይሆን እንዳልቀረ ትገምታለች:: ሁልጊዜ ግን ከትውውቃቸው ጀምሮ ትዳር ይዘው እስኪፋቱ በዕድሜ እጥፍ ከሚበልጣት ሰው ጋር ተኝታ መሸበት የጀመረ የደረት ፀጉሩን ስታይ የሆነ ነገር የጎደለ ይመስላት ነበር:: እና ትንሽ ከርሞ ባሏን እየዘነጋች መጀመሪያ አልፎ አልፎ ቀጥሎ በበረታ መልክ በተገኘው አጋጣሚ(ጊዜና ቦታ) በላዩ ትሄድ ጀመር......*በሰበታ ሜዳዎች ላይ ቂጤን ሳያይ ያደገ እረኛ የለም ብል......በእንጦጦ በወጨጫና በረጺ ተራሮች መሃል እኔን ወንድ ስር ባሌም ስር (ያኔ ወዳጄ) ተጋድሜ ያላየኝ እምራ የለም* ብል......ግን እሞራ ከላይ እየተንሳፈፈ ከመሬት የሚለቅመውን ግሳንግስ ለመምረጥ ሲያጤን የሚንሸራተት የውስጥ ሱሪ ቢያይ እውነተኛነቱን የመረዳት (ፍቅር ይሁን ባዶ ወሲብ)ተሰጥኦ የለውም:: እረኛ፣ አይቶ መሳቅ ወይ ፈርቶ መሸሽ እንጂ......እረኛ ረቂቅ አይደለም በልቦና ገብቶ አይሰልልም፣ አይመክርም፣ አይፈርድም::

ከርሞ መጋለጥዋ አልቀረም......

ስትፈነጭ በዚያን ጊዜ አባባሏ 'ስትደሰት' 'ስትዝናና' የባሏን እምነት ናቀች:: የብዙ ሆቴሎችና ቤቶችን ጣራቸውን አየች፣ የኮርኒሶቻቸውን ዕድሜ በጀርባዋ ሆና አነበበች፣ ወለል ላይ አፍጣ ስለ ጫማዎች አሰራር ተገረመች፣ ሳር ላይ ተንጋላ ወንዶች ደረቷን እያዩ አመልመሎ ደመናዎችንና የአምባላ ሰራዊት ወደ አዋሳ ሳንጋኖ ሸኘች:: ሴት አውሉና የቅኔ መኳንንት ነኝ ባይ ገጣሚው

መስፍን ዘላለም[31](የብዕር ስሙ 'ሳተናው') መኪና ውስጥ ታየች ሁሉ:: መገኘት የማይገባት ቦታ በባሏ እጅ ከፍንጅ ዐይነት ተያዘች:: አንድ ቀን ከዋለችበት ማታ ሁለት ሰዓት ላይ ቤቷ ስትመለስ፣ ታደለ ከግቢው ውጭ አቁሞ ትንሽ ቤት እንደሚገዛላት፣ ስራ እንደ ሚያስገባት ነግሮ፣ ለሌላ ጊዜ እንድትጠነቀቅ መክሮ፣ ከእሱ ጋር ያላት ትዳር ያበቃ መሆኑን ተናትሮ፣ ቤቷ ሳትገባ በዛው ደህና እደሪ አላት:: ደህና ሁኚ::

አዲስ የሴቴ ላጤ ኑሮዋን ጀመረች::

*የሚገርመው ግን ቅር አላለኝም......እንዴት ቅር አይለኝም......ምን ነበር የምፈልገው......የኖርኩትን ኖርኩ እንጂ......ሲባል እየሰማሁ እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረግ መዝናናት ነው ሲባልና በሚያደርጉት ሲቀና ላይ ለራሴ የምፈልገውን አላውቅም ነበር......ይኼ ትንሽ ያሳዝነኛል......ለሃያ ስንትስ ዓመታት ራሴ የምፈልገውን አላውቅም......የሰው ፕሮፓጋንዳ ስከተል ነው የኖርኩት......የራሴ አንጎል የለኝም......የቀድሞ ባሌን እንድጠብሰው የገፋፉኝ ሁለት አረፍተ ነገሮች ነበሩ......እህቴን ልጠይቅ መስሪያ ቤቷ ሄድኩና ባሏን ሰላም ልለው ቢሮው ስገባ ከማናጀሩ ጋር ተቀምጠው ሲያወሩ ደረስኩ...... ተዋወቅሁት......ሃያ ዓመት የሚበልጠኝ ሰው ነው......ያለ አልመሰለኝም...... ሰላምታ ሰጥቼ ስወጣ ሲናገር ሰማሁት: 'የማናት ሸንኩርት'*

*አንድ......*

*አንድ ልበል እንጂ......*

*ይኼን በሆዴ ይዤአለሁ ግን ትንሽ ያስፈራኝ ስለ ነበር ልርቀው እፈልጋለሁ......ታደለ ይረዝምብኝ ነበር......አለ አይደለ ወንድ ሲረዝምብኝ እፈራ ነበር......የግድ ታኮ አድርጌ ማስተካከል ነበረብኝ ቁመቴን አለ አይደለ ግን እሱ አይወድም......አለ አይደለ ይበሽቃል......ቤት ስትረዝም ጥሩ አይደለም ምናምን......አንድ ቀን ምናልባት በዚያው ሳምንት እህቴ ጋ እዛው መስሪያ ቤቷ ምሳ ለመብላት ስሄድ ስራ አስኪያጁና ሾፌሩ መኪና ተበላሽቶባቸው አገኘኋቸውና በእግር እያወራን ስንሄድ......ስለተናገራት 'ሸንኩርት' እያሰብኩ መስሪያ ቤት ደረስንና ሰላምታ ሰጥቶኝ......ግራ እጁን ትከሻዬ ላይ አድርጎ ትዝ ይለኛል...... ወደ እህቴ ቢሮ ስንዝ ከቀኝ በኩል......'ታድላ......ታደለን ጠበሰች እንዴ'...... ምናምን የሚል ጣያቂ አረፍተ ነገር ሰማሁ......በእነዚህ በሁለቱ ተጠመድኩ...... መልካም ሰው ነበር......ብዙ ሳይቆይ ደ'ሞ የእኛ ሰው በተገላቢጦ አለ አይደለ አይ የሰው አፍ......እንዴ እዚህ......እንዴ እዚያ......ዘለባብዳ ሁላ......ያለ እኩያዋ ሽማግሌ የምታገባው ምን ነክቶአት ነው አለ......በቃ ስንት ኀረምሳ እየፈለጋት ከዚህ ሊሞት ከደረሰ መቃብሩ ከተማስ ጋር......ምናምን ማለት ጀመሩ......ደም የሚያፈሉ ሕዝቦች ዘበራራቂ......ዘበራራቂ ሂሂሂ......*

---

31 መስፍን ዘላለም (ኢጆሌ ኮፌሌ) ነው:: የየቀኑ ወሬና ስንተረት የሆነ የታወቀ ግጥም አለው: *'አገርሽ ደጋ......ፍቅር እንኪ*
*ከዛ ሌላ......ለኪ ለኪ'*
መስፍን ዘላለም (ኢጆሌ ኮፌሌ) የሻሸመኔ ማታዎች የግጥም መድብል 150 ገፆች:: (አሳታሚ የለም) 1965

*ሰው በራሱ መንገድ ካምገሰ ያው ሰለጠንኩ እያለ 'ቤቢ' ከሚለኝ ያንሳል እንዴ......'ቤቢ' እያሉ......ስንት ጎረምሶች አፋቸው ኮልጌት ኮልጌት የሚሸት የኮሌጅ ፊልተሮች ደብረዘይትና ናዝሬት በታኑስና በሬኖ ጭነው ርካሽ አልጋ ውስጥ በወሲብ የደፈቁኝ......ከናዝሬት ሜዳ እስከ ሶደሬ ረባዳ ከደብረዘይት ሆራ እስከ ላንጋኖ ውሃ ሳያቋርጥ የሚፈሰው ማለክለኬ ነበር ......አፍና ምላስ ይገፋፍና ስናይ ስናይ አይተን አይተን ከውስጥ የቀረው ያው ስጋ ነው......*

*ግን......ታደለ ይወደኝ ነበር......ደ'ሞስ 'ሸንኩርት' ተብሎ መሞገስ...... ተሞገስኩ እቴ......አያስቅም ሸንኩርት ከጠረን ጠረን ከቅርፅ ቅርፅ የለው......ሌላ ዕቃ ጠፋ ......ሂሂ አይ ድሮ......ሸንኩርት ነፃ ቁስ እኮ አይደለም ሸንኩርት ሌላ አጃቢ ነው......ምን አጅቤ ይሆን?*

ከእሱ ያያያሏት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ቢሆኑም ያለያዩዋት ሁለትና ከሁለት በላይ ነበሩ:: በረቀቀ መንገድ በሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ጭንቅላቷ ይታዘዝ እንደ ነበረ መገመቷ በሚስጥር ያሳፍራታል:: እና አፏን ይዛ ለራሷ ብቻ ሕሊናዋ እስኪደነቁር *'የእኔ ስሁተት ነው'* ትላለች:: ሳያቋርጥ ቁጭት ውስጧን ይመዘምዛታል......

*......አልፈልግም ማለት ስችል......ጎድቼዋለሁ አለ አይደለ......ካለቀ ዕድሜው ጥቂት ዓመታት ዘርፌበታለሁ......እኔ ልጅ ነበርኩ......ተሳስቶ መታረሚያ ጊዜ ነበረኝ......ሁሉን ነገር ረስቼአለሁ......ቆይቶ ቆይቶ ወደ ኋላ ሳይ የተሰማኝ ባዶነት ነው......ወደ ፊት የሚመጣውን ስገምት የሚሰማኝ ባዶነት ነው......አለ አይደለ አላቂ ደስታን የጨረስኩ ይመስለኛል......ሁሉን ያለፍኩ ይመስለኛል.....ሕይወት ማታለልንና መታለልን ብቻ የያዘ ይመስላል...... ካታለልኩና ከተታለልኩ ኖርኩ ይባላል ዐይነት......ላይፍ ምናምን የሚሉት እነ ስብሐት......የኖርኳቸውና ያልኖርኳቸው ጊዜያት በባሕርያቸው መመሳሰላቸው ይገርመኛል......ከፍቼ ላይ ምንም አልነበረም የቅሬታ ፍርፋሪ......የሚጣፍጥ የድስት ጥራጊ*

*......ትዝታዎቼ ያምሩኛል......*

*ትዝታዎቼ ውስጥ ግን እሱ የለም......*

*ትዝታዎቼ ውስጥ ጣዕም የለም......*

*አብሬው ወንዝ ዳር ቆሜአለሁ ግን እሱ በትዝታዬ ውስጥ የለም......*

*በሰበታ ዛፎች መሃል በታኑስ ተንከባለናል ግን እሱ የለም......*

*እንደውም ያቺ ጎጆ ቤትና ሁልጊዜ አጠገብዋ ታስራ የማያት ጥቁር ላም......*

*እነዚያ ወለቴ ሱቅ የማያቸው ጥቂት በጎች ሳር ሲግጡና ሲወጣጡ...... ጠጠራቸውን ከኋላቸው ሲያራግፉ......*

*ነፋስ ስልክ ቤቱ ከጠዋት እስከ ማታ አብሬው ተኝቼአለሁ ግን የደረቱን ዘርግ ረስቼአለሁ......*

*ፒኮክ ካፍቴርያ በጨለማ ተሰሜአለሁ......ምን መጠጣት ይወድ እንደ ነበረ የአፉም ጠረን ምን ምን እንደሚል ግን ልቤ ማስታወሻ የለውም......*

ጠዋት ስራ ገብታ አስራ ሁለት ሰዐት ላይ ስራዋን ጨርሳ እስክትወጣ ከሰው መገናኘት አትፈልግም:: በየመሃሉ ትንሽ ያስቸገራት ወንድ ካለ አንዳንዴ ሰውዬውን ላለማስጨነቅ ትወጣለች እንጂ ግድ አይሰጣትም...... *ዞሪያው ነበር የሚመስጠኝ......ፍቅር ሳይሆን ፍቅር መምሰሉ......አጀቡ ቲያትሩ መደነቁና ሌሳውን በዘመኑ ስሌት መብለጤ......ከሌላዋ ቤት መሻሉ......ፍቅር ምንድነው? መስለምለም ምንድነው......*

ከሰፈዋ አዲስአባ ይልቅ ትንሽ ግቢዋ ውስጥ የሞላ የሚያረጋጋት ነፃነት አላት:: ከፈለገችም ለብቻዋ ታወራለች:: 'ብዙ ሰው አውቃለሁ፣ ዘናጭ ነኝ ከማንም እበልጣለሁ......' እያለች የተወችውን የማትፈልገውን የረሳችውን ውድድር የምታመጣባት ፋኖስ ናት......*ከፈለግሽ ካላረፍሽ እያልኩ በልቤ ያላደረግሁትን አደረግሁ ብዬ እዋሻታለሁ......*ፋኖስ አንዳንዴ በባሏ በስብሐት ልታስቀናት ይሁን አይገባትም እሱን ስለሚያውቁት 'ትልልቅ' ዝነኛ ሰዎች ታወራታለች:: እሷም ፋኖስን ለማናደድ የውሽቷን ብዙ ሐብታም ወንዶችና ባለሥልጣናት በማውጣት ላይ እንደ ሆነች ታወራታለች:: ከልቧ ግን ሰው አትፈልግም:: ለጉጉት አንድ ሰሞን ስብሐትን ከጅላው ነበር:: የፋኖስ ነገር እያበሳጫት:: የፋኖስ ጉራ:: 'ባሌ ከባልሽ ይበልጣል እስኪ ሽሮ አበድሪኝ' እያለች ብትላት:: በቤታቸው መሃል እንኳን የወደቀውን የእንጨት አጥራቸውን ለሁለት ተጋግዘው ማቆም ያቃታቸው ናቸው:: መፎካከር ያበሳጫታል......

*ምን አፎካከረኝ......እሷም ምኞት የምትወድ ለምን እሱን አገባችው...... እኔን ለምን ሰላም ትነሳኛለች......አንድ ወዳጄ ስታስጠነቅቀኝ ነበር......ያለ እኩያሽ ምን ትንጠራሪያልሽ......አንቺ ሃያ ያልሞላሽ እሱ አርባ የሆነው......ማለቷ ነበር እንዴ......ቀን ሲደርስ ቢከድሽ አይግረምሽ......ቀን ጠብቆ ዕድሜሽ ያሳስትሻል...... ቀን ሲደርስ እሱ ወደ እኩያው ዕድሜውን ቆጥሮ ይኼዳል ማለቷ ነበር...... ሁላችንም በዕድሜ ወጥመድ እንገባለንና......ይኼን ማለቷ ነበር እንዴ......ለምን አታብራራውም......አይገባትም ብላ ይሆን......ካልደረሰበት ሰው አይገባውም በተለይ አበሻ......ሲመክሩት የቀኑበት ይመስለዋል......እንደዚያም አስቤ ነበር እሱስ......ስብሐትን እንደ ወንድሜ እወደዋለሁ......በተለይ ሲያዳምጠኝ...... እሱ ብቻ ነው ያወቀው ወሬ መሃል ተደብሬ ዝም እንደምል......ፋኖስ ወንድ ያጣሁ የወንድ ችግር ይመስላታል......ምን ቀረኝ? ውስጤን አጠናለሁ...... የሰዎችን ንቅናቄ አጠናለሁ......ቀና ብዬ በቀትር የፀሐይን ንጣት አያለሁ...... በክረምትም ቀና ብዬ የዳመናዎችን ንጣት የውሃዎችንም ቤት አያለሁ...... በአዲስ አመት አየር ውስጥ እየነፈሰ የሚመጣውን መልካምነት ብቻ ሳይሆን ኢንፉሌንዛንም አያለሁ......በዓል ሲሆን ትኩስ ጉበቴን ገዝቼ ይቀልዱብኛል እና ፋኖስ ጥሬውን በሚጥሚጣ እህቴ አቦልዬ በሰራችልኝ እየተመተምኩ በአየ አወራርጄ እግሮቼ መሃል ሽቶ እበትናለሁ......አንዳንዴ እተኛሁበት ስከናነብ ከታች እየተነነ የሚመጣው ጠረን የሻላ አይደለም ሂሂሂ......በጥጥ ውጋገን ስር የተሰላቸ ገላዬን አያለሁ......የዕንብርቴን ጎድጓዳነት የጭኖቼን ግዝፈት*

*እናም እነዛ መሃል ያለቀሱትን ወንዶች ብዛት......ሳንባቸውን አልጋዬ ላይ ጥለውት የሄዱትን እነዛን የአዲስአባ የወንድ ሽርሚዎች......ሂሂሂ እቆጥራቸው እጀምርና......የጣሙኝንና የመሳሰሉትን......አሳፋሪና የማያሳፍረውን......በመደነቅ አያለሁ ከዚያ ጥቁር ደን ስር የአዲስ አባን ምሁር ሥርዐት ያውገረገረና የፈተሸ ሰርባዳ......የገመተና የጣለ......ይህቺ ናት መማር ይህቺ ናት መሰልጠን ያሰኝ......በደረቴ ላይ እየተንከባለለ እምብርቴን ዘሎ እዛ ሸለቆ የጠፉ የእጮኞች ቀለበት......የእኔም ትዳር......አልጋዬ ላይ ተጋድሜ ጎረቤቶቼን ቡና እንዲጠጡ ስጠብቅ ሌላ ጊዜ ተቻኩለው የሚመጡት በየቤታቸው የተዘረጋው የበግ ዱለትና የበሬ ምላስና ሰንበር ይጠምዳቸዋል......አውቃለሁ እንደማይመጡ......ደንብ ነውና ግን ተጋድሜ እጠብቃለሁ......በር በር አያለሁ......*

ሳሎን ጋቢዋን ደርባ ሶፋ ላይ ተኝታለች:: የተደገፈቻቸው ሶስት ትናንሽ ትራሶች በከፊል የተቀመጠች ያስመስሏታል......አንድ ጥቁር ሬድዮ በዝቅተኛ ድምፅ ስሞች ይጠረጥራል፣ ከዚያ ቀጥሎ የተመረጠ ዘፈን ከኪስ እንደሚወጣ አዲስ ብር ቤቷ ውስጥ እየተንኳኳ ይዘረጋል......የቀኑን ብርሃን ከተቀመጠችበት/ከተጋደመችበት ሆነው ሲያዩት የቆሸሸ አፈር የተከለሰ ኖራ ነው......ከበሩ በስተቀኝ ቀደም ብላ ያጠበችው ውሃውን አንጠፍጥፎ የጨረሰው ጋቢ የተሰጣበት ሽቦ መሬት ሊነካ የደረሰ ትልቅ የሀሌታው 'ሀ' ቅርፅ አለው......*ልብስ ማስጫዬ ሊበጠስ እኮ ነው ለዚህ ለዚህ ወንድ ያስፈልገኛል*......ከምታውቃቸው ውሽሞቿ ሽቦ መጎተት የሚችሉትን ጠብደሎች በልቧ ትመርጣለች......ይሄ ሲደርቅ ሌላ ሁለተኛ ማጠብ አለባት......የሆነ ነገር አሳከካትና......*ፍልውሃ መሄድ አለብኝ*...... ወደ ውጭ ማፍጠሟን ቀጠለች:: በሩን ወፋፍራም የተረት ሡፈር ዝንብ ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ ያቋርጠዋል:: መሔጃ የጠፋው ብቸኛ ጨረባ አጥር ላይ ቆሞ ድምፁን ተኩሶ ይሄዳል......የደከመ፣ ያለ ጊዜውና ያለ ቦታው የሚናፈስ እሳት ራት እየተንገላወደ ያልፋል:: ዝንቦች እንደ ደቃቃ ጥላ ሽው ብለው ይገቡና የት እንደሄዱና እንዳረፉ ይጠፉታል:: የበሩ መቃን ላይ ተባዮች ሲላወሱ ታያለች:: ይንፏቀቃሉ ይገላበጣሉ:: ሳያቋርጡ ወደ ሚጠፉበት ይኼዳሉ:: አትነካቸውም......ከተጋደመችበት ሁሉን ታስተውላለች......

ስብሐት እየተንገዳገደ ከቤቱ ሲወጣ ታየዋለች:: ጎብጦአል፣ ሰክሯል:: እንዲህ ሆኖ አይታው አታውቅም:: በስሙ ጠራችው:: ዞር አለ::

«ስብሐት ምነው ደኸና!» አለች በችኮላ አልጋዋ ላይ ቁጭ አለችና......

አጉረመረመ:: የሆነ የጎደለ ነገር ያለ መሰላት:: ፋኖስ ብታበሽቃትም ስብሐት ጎድቷት አያውቅም:: ከተቀመጠችበት ተነስታ አጥሩን ማቋረጥ ስትጀምር ዞር ብሎ አያት::

«ና አረፍ በልና ቡና ላፍላልህ»

«ሰክሯል ብለሽ ነው?»

«አዎ ሰክረሃል:: ትንገዳገዳለህ፣ ማንም ያየዋል ልዋሽህ ትፈልጋለህ?»

«ኑሮ ከባድ ነው»

«ቡና ከጠጣህ ይቀልሃል»

ከት ብሎ ሳቀ፡፡

«በይ እሺ»

«ና»

ደግፋ ከእሱ ግቢ ወደ እሷ ግቢ በፌረስ አጥር ላይ እየመራች ወሰደችው

«ምን ጠጣህ?»

«ከመቼ እለት የቀረ ውስኪ ነበር እሱን በአንድ ትንፋሽ ጨለጥኩ»

«እንዲህ የሚያስጨልጥ ምን ነገር መጣ? በል ግባና እረፍ፣ በኤሌክትሪክ ነው የማፈላልህ ቶሎ ይደርሳል፡፡ ላምባሽ የት ሄደች?»

«እንጃ የኼደችበትን አልነገረችኝም»

ዝም አለች፡፡ የት እንደሄደች ትጠረጥራለች፡፡  ግን ዘነጋቻት፡፡

ሁሉን ነገር አቀነባበረች፡፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የሚቆላ ቡና ጠረን ቤቷን ሞላት፡፡ ደጃፍ ላይ ከቆመ ስንዝር እርዝመት ካለው የቀንድ ዋንጫ እንደ ሪብጣ አቡጀዲ እየተተረተረ የሚያልፍ የሰንድሮስ ጢስ ይመነጫል፡፡ ስብሐት ከአካባቢው ጋር በሆነ በማይገባው ምክንያት የተሰናሰለ መሰለው...... እንደ ሚያናውዝ ዐይኖቹን ጨፈነ......

«ሴቶች ጥሩ የምትሆኑት መቼ ነው?» አለ ባልሰከረ በማይንተባተብ በረካ በምትወደው መልካም ድምፅ፡፡ ዐይኖቹን አልገለጠም፡፡

«አየህ ስታርፍ ለቀቀህ፡፡ ወፍራም ቡና ትጠጣበታለህ ይጠፋል፡፡ ያን ጊዜ የፈለግህበት ትሄዳለህ»

«አልመለስሽልኝም፡፡ ምን ትሸሺያለሽ?» ዐይኖቹን ገለጠ፡፡

«አንዳንዴ እኛም አናውቀውም፡፡ ስናረጅ ነው የምናውቀው፡፡ ያን ጊዜም ላናውቀው እንችላለን፡፡ ጥሩ መልስ ነው?»

«አሃ አሃ ሌላ መልስ ናት፡፡ እንዳንቺ አይነት ጮሌ ልጅ ለምን ባል አታገቢም?»

«አንተን የመሰለ አላገኘማ»

«እውነት?»

«ማፍቀር የለብኝም?»

«ታዲያ ቁጭ ብለሽ ትጠብቂያለሽ?»

«ተሯሩጬ መች አገኘሁ ብለህ፡፡ መዝናኛ አልሆንም»

«ሃሃሃ የጋራ እኮ ነው»

«ላምባዬን አትወዳትም?»

«ለምን አልወዳትም?»

«መታደል ነው»

«መቼ ነው ላምባ የነገረችኝ የድሮ ባልሽ አሁንም ይመጣል ያለችኝ»

«ሚስቱ ስታማርረው። ይጠይቀኛል። በጣም ደግ ሰው ነው። ሌላ ነገር አይደለም አየህ። ወተት ላድርግልህ?»

«በምኔው ደረሰ»

«ደራሲዎቻችንን ስንንከባከብ»

«ደራሲ ሲንከባከቡት አይወድም። መከራ ራሱ አሸትቶት ይመጣል፣ እሱም ሳይፈልግ አይቀርም፣ ካልቸገረው አይፅፍማ»

«አሁንስ በሬድዮ ድምፅህ አይሰማም። ምነው?»

«አይመጣማ። አይመጣማ። የፈለግሽው አይሆንም። የፈለግሽው ነገር ይመስልሽና ግን በኋላ እንዳልሆነ ታገኝዋለሽ። ያስለፋል። አሁን ደ'ሞ ጢሜ ጠፋብኝ። አየሽ ያ ጢሜ የለም»

«ምን አልክ?»

«ጢሜ»

«ጢምህ ምን ሆነ?»

«ጠፋ»

«ይኼስ የማየው? እንዴት ጢም ይጠፋል?»

«ጠዋት ስነሳ ጢሜ የለም። የተላጨሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ላምባን ብጠይቃት 'በእንቅልፍ ልብህ አድርገሽው ይሆናል፣ ወይ ሰክረህ አድርገሽው ይሆናል' አለችኝ። ይኼው ሁለት ሳምንት አለፈ አንዲት ፀጉር በምትኩ አልበቀለም። ታዲያ ይኼ......»

«ስብሐት አልጠፋም። እንዲህ እንዳትል ሰው ፊት። 'አበደ' ይሉሃል። እመነኝ። ያ የሚያምረው ጢምህ አለ። ማንም አላጨውም»

«ላምባ እንዳሌለኝ ነው የምታውቀው»

«አውቃ። ብትከራከራትና ብታሸንፋት 'ላዝናናህ ብዬ ነው የዋሸሁህ' እንደ ምትልህ አውቃታለሁ»

«በሉ እሺ በሉ እሺ አለ ዘፋኝ»

«በሉ እንጂ በሉ እንጂ»

«አይያዝልኝም። ዘፈን አልችልም። ማንጎራጎር እንኳን አልችልም። ምንም። አሁንማ መፃፍም አልችልም»

«ትንሽ ሰክረሃል ለዚህ ነው......ይልቁን ልጨምርልህ ሲኒህን አምጣው።

ልብህን እንዳይመታህ ቀስ ብለህ ጠጣ»

ስብሐት አተኩሮ አያት:: ነጭ የጥፍር ቀለም የተቀቡ ጥፍሮቿን:: እንደ አጥቅ ያህል በውሃ እርጥበት የተነከሩ ጣቶቿን:: የጉልበቶቿ ሙላት:: በተወጠረ ረጋ ስራሽ አጭር ቀሚሷና በተገረበቡ በነዚህ ጉልበቶቿ መሃል መልካም ለስላሳ የሚያንጉ ጠይም ጭኖች ተደጋግፈው እየሞቃቸው ተቀምጠው:: በሻሽ የተያዘ ከራራ ጠጉሯ:: አይንም አላት የሚያቆላምጥ:: እንዴት እንዲህ አላያትም ቀድሞ? ከውጭ የሚፈስው የፀሐይ ብርሃን ውጋጋን ስፊ ደረቷ ላይ እንደ ወርቅ ውሃ ተከንብሏል:: ሊጠይቃት ዳዳው:: ወረድ ብሎ ወደ መሬት 'በይ እስኪ' ሊላት:: አላደረገውም:: በዝምታ በጉጉት አደነቃት:: ቡና አቀዳዷ ለስላሳ ነው:: ከፍ ዝቅ ይስባል:: ጀበናውን ወደ ላይ ከእናቷ በላይ አንስታ ስትመልሰው:: *እያንዳንዱ ቤት ዘማሪ ገላ አለው......ራሱን የቻለ ዜማ......የራሱ ቅኝት ያለው:: ወንድ ለቤትም እንዲያ ይሆናል......ለለ አይደለ እኔ ክላሲክ ብሆን የሆነ መልካም ክራር የምጫወት......አንዳንዱ ሁኔታው ጃዝ የሆነ......አንዳንዱ እንደ ቫግር...... እኔን የምትሸሽኝ ለዚህ ይሆናል ፋኖስ......ዳንዴው*[32] *ምላ ሆኜባት......የእኔን ዘፈን ብቻ ስሚ እያልኩ......ሁለተኛ ቡናዬን ጨርሼአለሁ......እ?.....*

«ስሚ በረካ ስምሽ ለምን 'በረካ' ተባለ?»

«እስከ ዛሬ አታውቅም?»

«በፊት የጠረጠርኩት ሌላ ነበር»

«ምን ጠረጠርክ?»

«የተባረክሽ ለማለት»

«ተሳስተህ ነበር»

«አሁን የጠረጠርኩት ግን......»

«ቡናውን ስታይ መጣልህ?»

«አዎ»

«ሦስተኛ ልጅ ስለነበርኩ ነው»

«ገባኝ......ይኸቺን ለወዳጆቼ አጫውታለሁ»

«ቁም ነገር ነው?»

«ታዲያስ ትልቅ የመፍጠር ችሎታ እኮ ነው:: ይታይሽ ከቡና ዓለም ወደ ሰው፣ ያውም ቆንጆ ጠይም ስየማ:: ሌላ ነው»

«እናቴ በጣም ተጫዋች ነበረች:: አሁንም ሰውን በሳቅ ትገላለች:: የጠጅ ደንበኞቿ ለጠጁ ብቻ ሳይሆን ለቀልዷም ነው የሚመጡት»

«አባትሽስ?»

---

32 ሞላ የተባለ የእንጨኒ ልጅ ከዘፈነው ዘፈን የተወሰደ:: ዘፈኖቹ ሁሉ ጠቅላላ ቀልድ የሆኑ::

«አባቴ ይደሰትባታል እንጂ. እሱ በጣም ዝምተኛ ነው:: ከባድ ርሂ. አለበት»

«እንዴት ተግባቡ? መቼም የምላስ ርሂ. የለም»

«ሂሂሂሂ......ቀልዷን ያደንቃል:: እሷም የእሱ ነገር አይሆንላትም:: እሱን ቀና ብላ የምታይ ሴት ተገደለች:: ሰው በጣም ትወዳለች:: መጫወት ማውራት ትወዳለች:: እሷ ሰው የማታየው መቼ መሰለህ እሱን ሲያመው:: ንግዷ ሁሉ ይቃወሳል:: ደንበኞች አባቴ እንደ ታመመ ይገባቸዋል:: ሊጠጣ የመጣ ሁሉ የአባቴን መኝታ ቤት ለጥየቃ ያጠባል:: ታዲያ ሲመራት 'እዚህ ተሰብስባችሁ ባሌ ላይ ጠጃችሁን አትተንፍሱ' ትላለች:: 'ሁይ እቴ ምን አባቷን ይኸቺ:: አድማ እንዳናረገብሽ' ይሉዋታል:: 'በየቤትሽ እየመጣሁ ነዋ የምገትሽ' ትላለች»

«ሂሂሂ......ግሩም ታሪክ ነው»

«ሦስተኛህን ለባብስና እንግዲህ ውልቅ ነው»

«ምን አስቸኮለኝ:: ከስንት ጊዜ አንድ ቀን ብመጣ ታባርሪኛለሽ?»

«ማባረር አይደለም:: ፋኖስ ሌላ ሌላ ታስባለች:: ግድግዳው ሁሉ ዓይን ነው:: እትዬ አልታዬን አታውቃቸውም? ስራቸው የወሬ ጫፍ ፈልጎ መቀጠል፣ ማመላለስ ነው»

«ግድ የለም ስጭኝና ልሂድ»

«የት ልትሄድ ነበር?»

«ጀርመን ካልቸራል ኢንስቲትዩት ኤግዚብሽን ነበር»

«የምን?»

«የስዕል:: ምን የመሰሉ ልጆች አስተዋውቅሽ ነበር»

«ይቅርብኝ ሰላሜ ይበልጣል»

---

*'ዳንዴው ደነባ ዳንዴው ደነባ*
*ትውልዴ ገጃ ሞቴ አዲስአባ'*

እንደገናም በሌላ ዘፈኑ ላይ:

*'አይ ላቭ ዩ ቆንጆ አይ ላቭ ዩ ቆንጆ*
*ላይሽ በእግሬ መጣሁ ከቡራዩ ሞጆ::'*

ብሎ የዘፈነ:: የሚዘፍነው ጠቅላላ ስለ ራሱ ስለ ነበር(ስለ ራሱ ቀንጆና፣ ጉብዝና፣ ብሩህነት፣ ዝነኛነት፣ ተጫዋችነት፣ ወዘተ...) በዚያን ሰሞን 'ዳንዴው' ማለት 'ራስ ወዳድ' ማለት ነበር:: ምሳሌ: 'ሊጋብዘን ይችል ነበር ገንዘብ አለው፣ ግን ታውቀዋለህ እሱን...... የሆነ ዳንዴው ነው':: ከረዥም ጊዜ በኋላ ምናልባት በሰማኒያዎቹ መጀመሪያ ላይ የሞላ ዘፈኖች እንደ ገና ከተዘነጉበት ወጥተው ገበያ ላይ ሲውሉ የሰሟቸው አንዳንድ ጋዜጠኞች 'ዳንዴ' የተባለውን ቃል ለፖለቲከኞችና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ስየማ ሊጠቀሙበት ሞክረው ነበር:: ሁልጊዜ አሪፍ ነን፣ ነበርን፣ እንሆናለን፣ ተሳስተን አናውቅም (ቢሳሳቱም እየካዱና እየዋሹ) የሚሉትን 'ዳንዴዎች' ብለው ሊሰይሟቸው ሞክረው ካልታወቀ አቅጣጫ እጅ አዙር ስድብና ማስፈራሪያዎች ስለ ደረሳቸው መጠቀም አቁመዋል::(አ)

«ትገርሚኛለሽ:: ብቸኝነት ጥሩ አይደለም:: ቢከፋም የህይወት ልምድ ነው»

«ለእሱ አይደለም:: ምንም ነገር አልፈልግም»

«በይ እግዜር ይስጥልኝ:: ግሩም ቡና ነበር:: ቡና ቤት እንዲህ ዓይነት አታገኚም እኮ:: የቡና ቤቱ እኮ ቀልድ ነው:: የሰከርኩ እመስላለሁ?»

«ፀሐይ ውስጥ አትሂድ:: መጥፎ ፀሐይ ነው ያለው»

ተነስቶ ቆመ:: ቤቱን ለመጀመሪያ እንዳየው ሁሉ ቆሞ አጠና::

*ልሳማትን......ምኗን ልሳማት......እግዜር ይስጥልኝ ብል እግዜር ምን አገባው......*

ጎንበስ ብሎ እተቀመጠችበት ግንባሯን ሳማት:: ለመከላከል እጇን አንስታ ነበር:: ግን ዘገየች:: እየሳቀ ወጣ::

## (የአለ ፈለገ ሰላም ኩታ/ጋቢ)

በእግር ወደ ተረት ሠፈር ሲወርዱ:: አንድ ድንክና አንድ አጭር ቀጭን ባለ ሽርግግ ጢም ሰውዬ:: አንዳንዱ ተሳስቶ 'ጎራው'[33] እያለ ይጠራዋል መስኮትን:: አይበሳጭም::

«የጎራው ዘመድ ልትመስላቸው ትችላለህ» አለ ስብሐት እያሾፈ::

«ቅን ስህተት ነው፣ ግድ የለም:: የተበደልኩ አይመስለኝም»

«እሺ የምትለን ከሆነ አንድ ጎረቤቴ አለች ቡና አፍይልኝ እንላታለን:: አሁን ወደ ኤግዚቢሽን ልመጣ ስል አፍልታ ጠጥቼ ነው የመጣሁት:: ቡናዋ የእኔ ወዳጅ ሌላ ነው:: በነገራችን ላይ ቤት ስንደርስ ዝም ብለህ ተቀመጥ:: ከፋኖስ ጋር ያልከኝን አታውራ:: ነገሩን ማንሳትም አልፈልግም:: ቀስ ብሎ ይገባታል»

«የለመደ አይተውም አልኩህ»

«እስኪ ተው ይቅር:: አለመደባትም:: ብዙው ሰው ይፈልጋታል:: ለመሆኑ ሲጋራ አለህ? ቤት ሳልደርስ የማጨሰው? ሳጤስ ካየች ሳምባ ትጮሃለች»

«በል እኔም እሻለሁ:: ለአንተ አስብልሃለሁ ልትል ነው አታጢስ የምትልህ? ለበን ያጤስ የለም? ከማንም አጢያሽ ጋር ዘወጥአ ዘገብአ ትጫወታለች አንተን ግን አታጢስ ትልሃለች:: በነፍስህ ነው የምትጫወተው:: ለማንኛውም አንድ አንድ እንግዛና እዚች ሱቅ ተጠልለን እናጤሳቸዋለን»

እዚህ መቆም የማይፈቀድ ይመስላል:: አካባቢው ፓርላማ ነው:: ፖሊስና ወታደር በየቦታው አለ:: ስብሐት ወታደሮቹን እያየ:

*ደራሲ መሆኔ መልካም መሆኑን የማውቀው አሁን ነው......አውርቶ አደር*

---

33 በዚያን ጊዜ አዲስአባ ውስጥ ይኖር የነበረ ተዋናይ ድንክ:: ዘግይቶ በእሱ ስም የሚጠራ ሌላ ድንክ ብቅ ብሎ ነበር(አ)

*ወይ ከትቦ-አደር መሆን......ትንሽ ሰድሜ ሳያረዝም አይቀርም......*

መስኮት ወታደሮቹን እያየ:

*ከእነዚህ ያንዱን ቁመና ቢሰጠኝ ምን ይጎድልበት ነበር......*

ከሁለት የተለኮሱ ሲጋራዎች ነጫጭ ጢስ እየተከነበለ ይወጣል:: አንደኛው የጢስ ቀጠና ከመሬት አጠገብ ይነሳል ግን ከሌላው ይሰፋል:: ስብሐት የመግፍ ቆሌው እንደ ተሰወረች ትዝ ሲለው ውስጡ አሁንም ይኮማተራል:: በአጠገባቸው ሲያልፉ ሰዎች መስኮትን በድንጋጤ አይተውት በድንክነቱ ተገርመው ይኼዳሉ::

«ድንክ አይተው አያውቁም? ቢያንስ እያንጓንዱን ሰው ለሳምንት ድንክ ማድረግና ምን እንደሚሰማቸው መዝግቦ ማስቀመጥ:: በራሪ ነፍሳት ጢንዝዛ ምናምን አደረጉኝ እንዴ?»

«መንፈሳቸው ድንክ ስለሆነ ነው» ይላል ስብሐት:: መስኮት በሳቅ ይንፈራፈራል:: ስብሐት ይቀጥላል:

«ረዥም ብትሆን በተንኮል ማሳጠራቸው ላይቀር»

መስኮት በሳቅ ይንፈራፈራል::

«ሁሉን ነገር ቧልት ታደርጋለህ:: ብሽቅ»

መስኮት ይንከተከታል::

ሲስቅም አሳፊ አግዳሚው ያየዋል::

«አንድ ቀን በቴሌቭዥን ለአዲስ አባ ሁሉ ታይቼ ጎራውን አለመሆኔን ማሳወቅ አለብኝ» ይላል::

«ምን አገባቸው ብሽቅ ሁሉ» ይላል ስብሐት::

«የሚያበሳጨኝ ድንክ መሆኔ ሳይሆን አሁን የሚያበሳጨኝ 'ጎራው' መባሌ ነው:: ቲያትር አልወድም»

ይስቃል ስብሐት::

«ሁላችሁም ማስመሰልን ኪነት ያደረጋችሁ ናችሁ»

«ቲያትረኛ ድርቅና ያበዛል......ሃሃ» መስኮት እየሳቀ ሲጋራውን ይመጣል::

ከመሃል መስኮት በሲጋራው ጢስ መሃል አንድ ነገር ላይ ዓይኖቹ አረፉ:: ነገርዬው ሱቁ ውስጥ ነው:: የስብሐትን ወሬ አቋርጦ ወደ ሱቁ ተጠጋና ወደ ውስጥ አየ::

እንደ ምንም ተንጠራርቶ ቀና አለና ባለ ሱቁን:

«ስማ ጂሚ እስኪ ያን ስዕል አሳየኝ»

ባለ ሱቁ ያናገረው ሰው ድምፅ ከየት እንደ መጣ ካረጋገጠ በኋላ፣ ሳይከራከር ስዕሉን ከተሰቀለበት አውርዶ ሰጠው::

«ስብሐት አየህ? የአለ ፈለገ ሰላም ስዕል»

«ማን?»

«አለ ፈለገ ሰላም»

ስብሐት ስዕሉን ሲያይ ደነገጠ:: ትልቅ ጢም አለው ሰውዬው::

«ይኼ ሰው አስደናቂ ነው ታውቃለህ:: ይኼ ሰልፍ ፖርትሬይት[34] ነው_ ታውቃለህ?» አለ መስኮት በነደደ ስሜት

«ጋቢ ለብሶ ነበር የሚስለው?» አለ ስብሐት:: በማላገጥ::

«የድሮ አርቲስቶች ናሺናሊስት[35] ነበሩ» ሲጋራውን ወደ መሬት ጥሎ...... መስኮት

«ድንቅ ስዕል ነው:: ግን ኩታውን እያንጀለጀለ እንዴት ይሰራዋል...... ይቀባል ማለቴ ነው:: ይታይህ በቀለም የተበላሸ ጋቢውን ስታገኘው ሚስቱ 'ማን ሊያጥብ ነው? ገረድህ መሰልኩህ' ብላ ትነዘንዘው ይሆናል» አለ ስብሐት::

«ሴቶች ሁሉ እንደ ፋኖስ አይደሉም:: ጋቢውን ራሱ ነው የሚያጥበው:: አርቲስት ነው:: መደረግ የሚገባው ስውነት መደረግ እንዳለበት ያውቃል:: ሕይወት ላይ አይኮራም:: የድሮ ወንድ ወንዝ ይወርዳል:: እድሜ ለእንዶድ:: ከለመድክ ትችላለህ:: መጀመሪያ ፊቱን ስርቶ ቀጥሎ ጋቢውን ከሃሳቡ ሊስለው አይችልም? መአት መንገድ አለ»

«አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ዓይነት ሰዎች በህይወት ቢኖሩ እላለሁ»

«ለምን? ልንገላቸው? ጠልፎ ለመጣል ነው? እሱ ስለቀረብን ቀድሞ ሞት ስለወሰዳቸው ተበሳጭተን ወይ በሞት ቀንተን ይሆናል:: የሞት ጓደኞች ነን አብረን ሰንበቴ የምንጠጣ......ማጭዱን መሸከም ሲከብደው እኛ ቤት ትቶት ይሄዳል እንድንጠብቅለት......እሱን በጋቢያችን ደብቀን እንወጣለን ደራሲ ልናሳጥርበት አርቲስት ልንቀጥፍበት:: ውሸቴን አይደለም:: ወጣት ሰዓሊ ይጠላሉ......ድንገት የማይወዱትን የማይፈልጉትን እንዳያስብ......እንደ እኔ ዓይነት የበቃው አሮጌ በየቀኑ ይደነቃል፣ ይፃፍለታል:: ለምን? ሞቼአለኋ:: አላስቀናም፣ አላስፈራም»

«በል ስዕሉን መልስለትና እንሂድ:: ምን ነካህ አንተ?» አለ ስብሐት

«አዎ ይመስለኛል ኔክሮፊሊያዎች[36] ነን:: ምናልባት:: የቆመውን እንገልና የሞተውን እናደንቃለን:: ወጣቱን እንዳሌለ እንረሳና ሊሞት የደረሰ ሽማግሌ እናደንቃለን......ምቀኝነት ከሆነስ? አለ አይደለ ቆሞ ከሰራ ይበልጥሃል፣ ስለዚህ ምንም በማይሰራ ሊሰራ በማይችል ሽምትር ለውጠው:: በቀላሉ ያለ ጭቅጭቅ ያለ ጥይት ያለ እስር ቤት ገለኸው ትገላገላለህ ዐይነት:: ተንኮሉ ሁሉ ረቂቅ ነው......በነገር የሚነኩህ እኮ አይታዩም ጃን:: በነኪ ነው የሚጠቀሙት:: ነኪዎቹ ድንክነቴን አጋነው ያወራሉ:: ታዲያ የምፈልጋቸው ሴቶች እኔን ይሸሹና አንድ

34 Self portrait= የገዛ ራስ ስዕል(እንግሊዘኛ)(አ)

35 nationalist= አገር ወዳድ(እንግሊዘኛ)(አ)

36 necrophilia= ምውት አፍቃሪ (በሞት የሚያምኑ፣ ሞት የሚወዱ)(እንግሊዘኛ)(አ)

ስንዝር ብቻ ከእኔ የሚረዝም ሰው ያወጣሉ:: በብቸኝነት እንድትሞት ይደረጋል፣ ይሄ ሁሉ ሆኖ ስለ ስዕልህ እንፃፍ ይላሉ፤ እኔ እርጅና ሬሳ ላይ ቆመው የስዕል ሐያሲ ይሆናሉ......»

ስብሐት አገጩን እያሸ በሳቅ ተንከተከተ::

«አያስቅም:: ስማ ባለሱቅ! ይኼን ስዕል ልግዛህ» አለ መስኮት::

«አይሸጥም»

«ተውኺ ልመልስልህ እሺ»

«የት አውቅሃለሁ»

«እሱ ስብሐት ይባላል በሬድዮ ድርሰቱ የሚነበብ»

«አውቄአለሁ:: አይሸጥም:: እህቴ ናት ያስቀመጠችው»

«አየህ ስብሐት ምክንያቱን ሲለዋውጥ»

«ስማ አንተ ድንክ......ምክንያት እንደ ሌላ መረጃ ይረሳል እኮ:: ለምን ነበር ይኼን ነገር ያደረግሁት ብለህ ራስህን አትጠይቅም?»

«ጎበዝ እህት አለህ» አለው መስኮት ለባለ ሱቁ:: ስብሐት የሚናገረውን በከፊል ልብ እየሰማ::

«ተወው በቃ:: ለምን ታስቸግረዋለህ:: ስዕሉ ያለው ሰው ይጠፋል እንዴ? ፕሪንት[37] እኮ ነው ይኼ:: ፕሪንት ስዕል ትምህርት ቤት ብትሄድ ታጣለህ? አታጣም ቤትህ አይደለም እንዴ?»

«ይኼ ስቦኛል፣ እዚህ ጠርዝ ላይ ያሉት የቅባት ነጠብጣቦች፣ ይሄ ጥቁሩ ነገር......»

መስኮት የስዕሉን ፎቶ ከላይ እስከታች አየው:: እያንዳንዷን ነገር የሚያጠና ይመስላል::

ባለሱቁ:

«አቶ ስብሐት ምነው በሬድዮ ማንበብ አቆምክ?»

«እምቢ አለ:: ያቺ የምታፅፈን አድባር ሸፈተች»

ሰውዬው ከት ብሎ ሳቀ::

መስኮት ሱቁ ደረጃ ላይ ራሱን እያከከ ተቀመጠ::

«እንሂድ:: አንተ አይተኸው የማታውቅ አትመስልም?»

«ጊዜ ጊዜ አለው በዚህ አንከራከር:: ታውቃለህ:: አብረኸው ኖረህ የማታየው የማይታይህ ነገር አለ:: ከሌላውም፣ ከራስህም፣ ከኪነት ስራም ይሁን ከዕውነታ»

---

37 print= እትመት(እንግሊዘኛ)(እ)

«በል እሺ» ስብሐት የጨረሰውን ሲጋራ ቡሽ ወረወረና ለአፍታ አተኮረ፡

በዝምታ የአስር ሰዓቷን ቀን ያያል፡፡ እንግዳ በሆነ መልክ ውብ ነው፡፡ የለመደው ሰማይና መሬት ነው፡፡ ግን ሁልጊዜ ባልጠበቀው ሰዓት በአዲስነቱ ይደዘዋል፡፡ የቀኑ ግለት ከመሃል ሳያስጠነቅቅ በሚመጣ መነሻውና መድረሻው በማይለይ ቀዝቃዛ ነፋስ ይበረዛል፡፡ የአዲስ አባ'ን ሙቀት የሚያማርሩ ያበሽቁታል፡፡ ለምሬት አዲስ አባ ጊዜ አትሰጥም፡፡ መስኮት ከተቀመጠበት በዝምታ ተነስቶ ስዕሉን ለባለ ሱቁ መልሶ መሄድ ሲጀምሩ ባለሱቁ፡

«አቶ ስብሐት ሌላ ተረት እንጠብቃለን» አለና ጮኸ፡፡

## (ከስጡ ላይቀር ይንጋለሉ)

እንዳባረሯት ያህል ትሮጣለች፡፡ ታች ቆሻሻ መጣያው ላይ በትንሽ ስኳር መያዣ የካኪ ወረቀት ቀረጢት ውስጥ ከታ የጣለችው የስብሐት ጢም አካባቢ የጎዳና ውሾች ይንገላወዳሉ፡፡ ብዙ ሳይቆዩ የበሉት ይመስላታል፡፡ ውሾች ፀጉር ይብሉ አይብሉ አታውቅም፡፡ በአካል ከጥፋቷ ብትሸሽም ሕሊናዋ ሰይፉን መዞ እንደሚያባርራት ያደርጋታል፡፡ በጠሉት ሰው ፀጉር ማስጠንቆልና የሚያፈቅራትን ሰው ጢም ላጭቶ ሜዳ መጣል ልዩነታቸው ምንድን ነው? *ማነኝ እኔ......ፊቱን እንዴት ብዬ አየዋለሁ......*መነን ጎዳና ላይ ወጣችና ታክሲ ያዘች፡፡ እሱም ትንሽ አስጠብቋታል፡፡ ንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል ስትደርስ ወረደችና ወደ ለበን ቤት ጉዞዋን ጀመረች፡፡ ያቺ የለመደቻት አጭር ጉዞ አሳልቅ አለቻት፡፡ *ምነው ይኼ መንገድ አዳከመኝ......*በእርግጥ እንዲያ ተጨንቃም አስደንጋጭ ውብ ናት፡፡ ዞሮ የማያያት ወንድና ሴት የለም፡፡ ሴቶች ለመቅናት፡፡ ወንድ ከሚስቱና ከወዳጁ እያወዳደረ ሊጨነቅ ሊጠበብ፡፡

አንኳኩታ ስትገባ ለበን በመገረም አያት፡፡ ምሳ ሊበላ ተቀምጦ ደረሰች፡፡ የዘገየ ምሳ፡፡ *በቀን ሁለቴ?* ባልተራራቀ ሰዓት አከታትላ ስትመጣ የሆነ ችግር እንደ ደረሰባት ገብቶታል፡፡ ፊት ለፊቱ ፍፁም ነጭ የሆነ ጠፍጣፋ ሰሃን ላይ ሬድዮ የሚያክል መዝለፍለፍ የጀመረ፣ የሳልሳ ወጥ ባርኔጣ የደፋ ላዛኛ ቆሞአል፡፡ ግራና ቀኙ ከሳህኑ ውጭ ጠረጴዛ ላይ አንድ ቢላና አንድ ሹካ ተጋደመዋል፡፡

«ተቀመጭ ተቀመጭ» አለ ለበን፣ አጠገቡ ያለ ወንበር በቀኝ እጁ እየጎተተላት፡፡

ፋኖስ በቀላል እያለከለከች ተቀመጠች፡፡ ለበን ሰራተኛውን ጠርቶ ሌላ ላዛኛ አዘዘ፡፡ በቀን አንዴ እሱ ጋ ከመጣች በዚያው ቀን ተመልሳ እንደማትመጣ ያውቃል፡፡ ዛሬ የተለየ ነው፡፡ የጠዋቱ ልፊያዋ ገና እንዳደከመው ጡንቻዎቹ እንደ ላሉ ነው፡፡ ሁለት ሞርቶዴላ ሳንድዊቾች አልመለሱትም፡፡

ነጭ ሸርጥ የለበሰ አንድ ሰራተኛ ትኩስ የሚጤስ ላዛኛ ፊት ለፊቷ አምጥቶ አስቀመጠ፡፡ ምንም ሳትናገር መብላትም ሳትጀምር በፀጥታ አበባ የታተመበትን የጠረጴዛውን የጨርቅ ልባስ እያየች፡፡ እዛ የምታያቸው አበቦች የሚያስታውሷት ምግብ፣ መጠጥና ስቴክ አይደለም፤ ግራ በሆነ መልክ ሜሪ አርምዴንና የሆነች

የማታውቃትን ልጅ እያለች መንገድ ላይ ድሮ ያየቻትን ቂጠ ትልቅ ሴት ወይዘሮ ነው::

«ምን ሆንሽ ፋኑ?» አለ እሷና እሱ በሚያውቁት ቁልምጫ::

«ከስብሐት ጋር ተጣላሁ»

«ምን አጣላችሁ?»

«በዛብኝ»

«ምኑ?»

«ሁሉ ነገር»

«ምን ሁሉ?» ለበን መብላቱን አቆመና የሚጠጣ እንዲያመጣ ሰራተኛውን ጠየቀ::

«ፀባዩን አልቻልኩትም:: የሚቻል አይደለም:: እኔ እንዳለሁም ትዝ አይለውም:: በዚህ ሰሞን ደ'ሞ ብሶበታል:: ላስቆመው ብሞክር አልቻልኩም:: በፍፁም» ከእሱ የወሰደችውን ውስኪ በመድሐኒት አጠጥታው እንቅልፍ ሲጥለው ጢሙን እንደላጨችው አትነግረውም::

«እና»

«ከእሱ ጋር መኖር አልፈልግም:: የሚያስብልኝን ነው የምፈልገው»

«እያንዳንዱ ወንድ የራሱ መውደጃ መንገድ አለው» አለ ለበን::

ይኼን እንኳን የሚለው 'ጨዋ' ለመምሰልና ከስብሐት ጋር ለፋኖስ በፀባይ እንደተዋጋ ለማሳየት......'እሷ ሚስቱ አፍጣ ስትመጣ እኔ ምን አድርግ ትሉኛላችሁ' ዓይነት ሊል ነው::

«የታለ ታዲያ» አለች በቁጣ::

«እና እኔ ጋ መሆን ትፈልጊያለሽ?» አለ ባፈጠጠ ቃል::

ፋኖስ በዝምታ አየችው:: ከእሱ ጋር ለመሆን ልመና የመጣች እንደ መሰለባት ገባት:: ያልጠበቀችው ዓይነት ቀጥተኛ ጥያቄ ነው:: በዝምታ ሹካዋን አንስታ ለመብላት እንደሚፈልግ የላዛኛውን ክምር እየወጋጋች ሌላ ለስላሳ ነገር ከለበን አፍ እንዲወጣ ጠበቀች:: አልተናገረም::

«እንጃ......እንጃ ዞሮብኛል» አለች ፀጥታው በእሷ ቃል መገሰስ እንዳለበት ተረድታ:: ላታመልጥ::

«ታውቂያለሽ:: እኔ ጋ ለመሆን ከፈለግሽ ኤኒ ታይም[38] መምጣት ትቺያለሽ:: ቤትሽ ነው:: እወድሻለሁ ታውቂያለሽ:: አንቺ እንደምትወጂኝ ግን እርግጠኛ መሆን አለብሽ» ራቅ ብሎ እጆቹን ወደ ኋላ አጣምሮ ይኼን ንግግር የሰማው ሰራተኛ የአርባ ዓመት ሰው የሚዘረዝረው የፍቅር ኑዛዜ ያልጣመው ዓይነት የኋልዮሽ በቀስታ እየተራመደ ሌላ ክፍል ገባ::

---

38 any time= በማንኛውም ጊዜ(እንግሊዘኛ)(እ)

«ራስ ሕመም ነው የሆነብኝ» አለች ካቀረቀረችበት ቀና ሳትል::

«በይ አሁን ምሳሽን ብይና እኔ ለስራ እሄዳለሁ ከፈለግሽ እዚሁ እረፊ»

«ገላዬን ብታጠብ ደስ ይለኛል:: ትንሽ ቢሻለኝ»

«ምን አለበት:: ስማ አንተ ጋኑን አሙቅላት!» ከዓይኑ ቢሰወርም ሌላ ክፍል ውስጥ ብዙ ሳይርቅ ወሬአቸውን ሰራተኛው እንደሚሰማ የጠረጠረው ለበን::

ከወይኑ ለራሷ ቀዳች:: እስከ ግማሽ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠች::

ከዛ ሳቅ ብላ:

«አጠጣጤ እንደ ስብሐት ሆነ» አለች::

እንዲህ ተናግራ አታውቅም:: ስብሐትን ሌላ ወንድ ፊት አምታው አታውቅም:: ለበን ይኼን ጠባይዋን ያውቃል:: ስብሐት ምን መብላት እንደሚወድ እንዴት እንደሚጠጣ ተናግራ አታውቅም:: ስለ ስብሐት የአልጋ ሥረት ተናግራ አታውቅም:: ጨዋነት ነው:: ለመጣላቷ መለኪያ ቢኖረው ይኼ ነው:: 'ውሽማህ ባሏን ጠርታ ልምዱን ከነገረችህና ካማችልህ አንተን የበለጠ ወዳሃለች' የተባለ የወንደ ላጤዎችና የውሽሞች ፍልስፍና አለ:: ወደ ስድብ የቀረበ ነው:: ከስድብ የሚበልጥበትም አቅጣጫ አለ::

«ተይ አትጨልጪ» አለ ለበን አተኩሮ እያያት:: በአባባሏ እንደ በቃት ገባው:: ግን እንዲያ አላላትም:: ጠይም ራቁትነቷ እሱ ሰፊ አልጋ ላይ ያለቀጠሮ እንዳሻው እንደሚገኝ ሲያውቅ ለበን በእርካታ አይኖቹን ጨፈነ:: መገፋፋትም ነበረበት::

«መቼ ትመጪያለሽ?»

«እንጃ የሚመች ጊዜ ማግኘት አለብኝ»

«'ላይቀር ሞቱ ምንድን ነው ፍርሃቱ ይባላል'» አለ::

አተኩራ አየችው:: አፉ ልቅ ነው:: ሁልጊዜም ነው:: መናገር የማይፈልገውም ለዚህ ነው:: ክፉ አሳቢ ሆኖ ሳይሆን መመዘን አይችልም::

«ትንሽ ልቆይ»

«እንደ እሱ በዝምታ አላገባሽም:: ድል ባለ ሰርግ ነው»

ዝም አለች::

መብላት ጀምሮ ቀና ብሎ እያያት:: እየደጋገመ እያያት......*እንዴ!! የማረችው ከማን ከማን ተወልዳ ነው......ያያታል--በጎን፣ በቀጥታ:: ላዛኛ አፉ* ውስጥ እያላቆጠ እሱንም በወይን እያጠበ ያስባል:: የተለያዩ ነገሮች ያስባል...... ስብሐትን ያስባል......*የታደልኩ ነኝ......የቆንጆዎች ቆንጆ እዚሀ 'አግባኝ' ብዛ ስትመጣ......እሷን ባገኝ ሁሉ ነገር ተሟላ......ግንባሬ ላይ ከውስጥ እንደ ሙጫ ተጣብቆ የማየው ነድ የመሰለ ጭኗ ነው......የሚያምር የእግር አሳሳቧን*

*ነው......ቆርጣ የመጣች ዕለት የቤቴን በር ከውስጥ ለወር እዘጋለሁ ዕድሜዬን የሚያረዝመው ያ ነው......*ከእሱ ክምር ስር ትኩስ ሾርባነቷን ደቅና እስከ ዓለም መጨረሻ ስትፈጀው......*ፊቱም ላይ ፀሐይ የወጣ ይመስላል:: በመንፈስ* ጥጋብ......

እናም በየተራ እንደ ደብተር የሚገልጠው ሳዛኛ በቅላቱ እያበራ......

«ብይ ትንሽ:: ስቴክ ይሰራልሽ? ስጋ ትወጂ.ያለሽ አውቃለሁ»

ታስባለች:: የስብሐትንና የእሷን ስህተት......

*እንዴት ለብዙ ጊዜያት ሲያነብና ሲፅፍ አልጋ ዳር ተቀምጬ እየጠበቅሁት መጣሁ መጣሁ እያለ እንደቀረብኝ......ወይ በችኮላ ወሲብ አንጠልጥሎኝ ለማንበብ ወደ ዴስኩ ሲዞር በእንቅልፍ ልቤ አቅፌ ላስጠጋው በደረቅ ሌሊት እጄን ስዘረጋ የሚያጋጥመኝ የተረት ሠፈር ቀዝቃዛ አየር......ካልገባው ይነግሩታል...... ነግረውት ካልሰማ ይተውታል......አፍቅሬ የልቤን ካልኖርኩ ምን ጥቅም አለው......የምኖረው እንዴ ነው......ልጅ ወልጄ መኖር እፈልጋለሁ......ድርስት ልጄ ነው ከሚል ጋር ምን አዳረቀኝ......የምትወጂው ሰውዬ ካልሰማሽ ጆሮውን ካልሰጠሽ የሚቀርብሽ ወንድ አንድ ነው......*

ታስባለች......

## (ትንሽ ቀባርዋ[39])

በረካ ለአንድ ሰዓት ያህል ፊትጋ ፊትጋ ሁለት ሦስቴ በጠራ ውሃ አለቃልቃ በረዶ የመሰለ ልዋጭ ነዚፋዋን ግቢዋ መሃል ያለች ሽቦ ላይ ዘርግታለች:: ፋኖስን ጠርታት ስታጫምቃት ከመሃል:

«ስብሐት ፈልጎሽ ፈልጎሽ ተበሳጭቶ የስዕል ኤግዝቢዥን ምናምን ልይ ብሎ ሔደ፤ የት እንደሄድሽ አትነግሪውም እንዴ?» አለቻት::

«አንቺ ደ'ሞ ዝም ብለሽ እጠቢና ኩታሽን እንደ ሚዘረጋ ዘርጊው» ትላታለች:: ምን አገባሽ እንደ ማለት:

«ይልቁን ፀጉርሽን ታጠቢና ልጎንጉንሽ»

ፋኖስ ቀይ ባለማንገቻ ካናቴራ ለብሳለች:: ከጉልበቷ ከፍ ብሎ የሚቀር ጉርድ ፓሪ አድርጋለች:: ሻንጣ ውስጥ ያላስገባቻቸው እነዚህን የለበሰቻቸውን ብቻ ነው:: ተረከዝ የሌላቸው ቆዳ ጫማዎቿ የባቶቿን ውፍረት አጉልተውታል:: የግራ እጇ ሦስት ጣቶች በውድ ቀለበቶች ታቅፈዋል(ያሏት ቀለበቶች እነዚህ ናቸው):: የታደሉ ብረቶች:: ከሁለመናዋ ማራኪነት እንደ ጨረራ ይወጣል:: ከመሃል ግን የሆነ ነገር እንደጠፋት ሁሉ ልቧ ይሰለብና ወደ ሚሄድበት ይኼዳል......*ምን ለማድረግ አስቤ ነበር......*የምትፈልጋቸውን ዕቃዎች በሙሉ ይዛለች:: ስብሐት ማደሪያውን ከተወችለት ለእቃ ግድ እንደ ማይሰጠው ታውቃለች:: ገብጋባ መሆንም አትፈልግም:: አልጋዎቹን አትፈልግም:: ኤልፒ ማጫወቻውን አትፈልግም:: ስኒዎቿን እንኳን አትፈልግም.....ታዲያ ግን ቅር

---

39 የጹላ ምክቶሽ ስፖርት(አ)

ይላታል የረሳቸው እንዳለ ሁሉ:: ፎቶዎቹን ሰብስባለች:: ከእሱ ጋር የተነሳቻቸውን ሁሉ ትታለታለች:: ለበን ጋ ይዛው ብትሄድና ቢያየው ምንም እንደማይላት ብታውቅም:: *ቆንጆዎች መብታቸው ይከበራል......አገሬ ውስጥ መብት ያለው ለቆንጆ ሴቶች ነው......*

«ምን አወራችሁ?» ቀንታለች......ያውም እየተወችው::

«ሦስተኛ ድረስ ቡና ጠጥቶ ሄደ»

«ከእኔ ጋር አይሆንለትም እንጂ:: ምን አለሽ?» አለች ፋኖስ:: ከእሷ ጋር ሲሆን መፃፍ አለበት:: ከሌላ ጋር ሲሆን ደ'ሞ ቁጭ ብሎ ማውራት ይፈልጋል::

«እንዴት ምን አለሽ?»

«ምን አወራችሁ ማለቴ ነው?»

«ብዙ አወራሁት:: ስለ እናቴ ምናምን......ረሳሁት»

«እንዴት ትረሺያለሽ?»

«በቃ ስለዚህ ስለዚህ አወራን:: ምነው ተጣላችሁ እንዴ?»

ጥርጣሬዋን በልቧ መያዝ አልፈለገችም::

«እውነቴን ልንገርሽ ደራሲ፣ አርቲስት የሚባል ሰው አትመኚ»

«ምን አደረጉ?»

«በቃ ከራሳቸው በተቀር ለሌላ ነገር ለሌላ ሰው ግድ የላቸውም»

«እሱ እንኳን አይመስለኝም:: ስብሐት በጣም ነው የሚወድሽ:: በማይሆን ጉዳይ አትበሳጪ:: ሁሉ የሚሰራው አለው:: አስተዳዳሪውም ዶክተሩም ሁሉም የሚሰራው አለው:: ተማሪም ጥናት አለበት:: አይደል እንዴ?»

«እኔ ነኝ የማውቀው አንቺ? ከሩቅማ አዎ ደስ ይሉሻል:: ትንሽ ስትከርሚ ግን......»

«ደራሲ ለመሆን እኮ መቀመጥ አለባቸው:: ብዙ ነገር ማድረግ አለባቸው:: ከራሳቸው ጋር መሆን አለባቸው:: ማንበብ የለባቸውም? አለበለዚያማ አይሆንም:: ይኼን ሳታውቂ ነው ያገባሽው?»

«አይ እቴ ያማርራል» ...አባባሏ ደስ አላት:: ከጥርጣሬዋ ወጥታ ፊት ለፊት ትዳሯን መተቸቷ፣ መለያየቱ ያለመወላወል በመፈፀም ላይ እንደሆነ ሙሉ ምልክት ሰጣት:: ድፍረቷ ደስ አላት::

«መንግስት ያሳድዳቸዋል:: ሚስቶቻቸው እንነጨንጫቸዋለን:: አንባቢ እንዲህ አደረገ አላደረገ ይላቸዋል:: የት ይድረሱ እነዚህ ሰዎች? ሌላ ሌላ የተደበቀ ምክንያት ከሌለሽ በስተቀር ሙያቸው እንኳን ያው እንደ ሌላው መሰለኝ:: ያው ጊዜ ጊዜ የምትይውን በሚመለከት»

«ማን ነጨነጫቸው? በግድ ፃፉ ያላቸው አለ? ወጥ ሰርተን፣ ጋግረን

አብልተን ነው:: ካልሆነ መተው ነዋ:: ማን አስገደዳቸው ፃፉ ብሎ?»

«ተይ በእናትሽ:: እኛ የወር አበባችንን ማስቆም እንችላለን? አላውቅም:: ግን እንደዛ ይመስለኛል:: ስንት ጊዜ ነው 'ወጥ አልሰራሁም' እያልሽ በድልህ በበርበሬ የምታብይው:: ምንም አላለም:: ምስክር ነኝ:: እንጀራ የሚጋግርልሽ ሌላ ነው፣ ልብስ የሚያጥብልሽ ጭሎ ነው......»

«በይ አንቺና እሱ አብራችሁ ስታወሩ የሆነ ነገር ብሎሽ ነው እንጂ ከባለቤቱ ያወቀ አትሆኚም»

«ምንም አላለኝ:: ያየሁትን ነው የማወራው......'የኬደችበትን ነገረችሽ ወይ?' አለኝ:: በልቤ 'ለባል ይነገራል ወይስ ለጎረቤት' ብዬ 'አላየሁም' አልኩ:: እንደዛ መሆን አልነበረበትም»

«የማያገባሽን:: ኑሮው የእኔ»

«በይ ተይው! ውሃ አፍሺልኝና ልታጠብ:: ፀጉሬ ቆሽሾአል»

«ቆይ አረፍ ሳሙናና ኮንዲሽነር አለኝ ላምጣው» በውሃ ሞልታ የያዘችውን ጆግ መሬት ላይ አስቀምጣ በከፊል ሩጫ ቤቷ ገባች:: በረካ መሬት መሬት እያየች የተፈታ ፀጉሯን እየሞነጨረች...... *ምንሽ ኮንዲሽነር ያስፈልገዋል እንዴት ነው የነጠሩ ቆንጆ ሴቶች በመኪያ ለቃዎች በቀላሉ እንደ መልክ ጥቆዎች የሚደለሉት......ራስን አለማወቅ.....ልጅነት......አሁን ምን ጎደላት...... ፀጉሯ በቅቶት የተፈጠረ አይደለም እንዴ......*

*ያኔ......*

በአጥር በር ስብሐትና መስኮት ተከታትለው ብቅ አሉ:: ስብሐት ቀደም ብሎ:: በቤቱና በአጥሩ መሃል ያለው የተነጠፈ የድንጋይ መንገድ ውስጥ እንደ ገቡ መስኮት ወደ ግራ እያየ ፈዞ ቆመ:: ስብሐት በዝምታ እየተራመደ ዞር አለ:: መስኮት አፉን ከፍቶ ቆሞአል:: *የድንኩች አፍ እንዲህ ስፊ ነው እንዴ......*መስኮት ወደ ሚያይበት ሲያይ በረካ ጀርባዋን አዙራ ፀጉሯን ስታበጥር ተመለከተ:: ፊት ለፊቷ በረዶ የመሰለ ኩታ ከዳር እዳር ተዘርግቶአል:: የሚያምሩ ታላላቅ ጭኖቿን ያለሳንሱር የሚያሳይ ለስላሳ አጭር አረንጓዴ ቀሚስ ለብሳለች:: እንዲህ ለብሳ አይቷት አያውቅም:: እንዲህ የተቀረፀ ሳካ የሌለበት ጭን እንዲህም ክቡ የሚያምር ቂጥ ያላት አይመስለውም ነበር:: *ይሄ ድንክ አለ ነገር አልፈዘዘም.....*

**(አረንጓዴ—2)**

ለስብሐት አረንጓዴ በር ነበር:: ግራና ቀኝ የሚከፈት በር:: ፋኖስን ከመገናኘቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ያየው ሕልም በአረንጓዴ በሮች የተሞላ ነበር:: አረንጓዴ ለእሱ ቀለም ሳይሆን ምናብ ነበር:: *ምን ልሆን ነው አረንጓዴ ሕልም የማልመው* ሲል ነበር ፋኖስን ማዘጋጃ ቤት ቲያትር ድልድይ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ገና የተቀጠፈ ቆስጣ መስላ እስኪያያት ድረስ:: ከሁለመናዋ ወለላ የሚያኝ መስላ:: ሊተዋወቃት ሲጨብጣት እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር:: ለማንም ያልሆነ::

ስትራመድ እንደ አናወዘ የወንዝ እባብ ያደርጋታል:: ምድርም የሚበቃት አትመስልም:: ያን ቀን ማታ ግጥም ፃፈ:: እሷን ባሰባት ቁጥር ልቡ ውስጥ ለጋ፣ በድርስት ብቻ የሚበስል ትዕንግርት ይፈላል:: ሁለመናው ለስ ያለች ፀሐይ ስር እንዳረፈ ውሐ ይሆናል:: በቢክ ስክሪብቶ ሰረሰሮች ጣቶቹ ታመሙ:: አረንጓዴም ባየ ቁጥር ለእሷ ባነነ:: አረንጓዴ ባንዲራ ላይ አለ:: አረንጓዴ መፀው ነው:: አረንጓዴ መስከረም ነው:: አረንጓዴ ቤንዚን እንደገባበት ሞተር ያቀጣጠለው ነው:: በረካን አረንጓዴ ቀሚስ ያውም የፋኖስን ለብሳ ሲያያት ዛሬ ስንት ዓመታት ከርሞ የሴትዮዋ ገላ እንደ ሚደነቅ ኪነት ብቻ እንጂ ሌላ ምኞት የሚቀሰቅስ ትዝታ አለኮሰበትም:: ይኼ አለመደንገጡ፣ ይኼ የፋኖስን ቀሚስ አስታውሶ ፋኖስን በልቡ አለመከጀሉ የበቃው ነገር እንዳለ ጠረጠረ:: *እንደ ሌሎች ነገሮች እንደ ጭቃ ቀለምና እንደ ጫማ እንደ እርሳስና እንደ ኮሌታ ፍቅርም እንዲህ ይሆን የሚያልቅ?*

የልጅነት ጥቁር ጢሙን በናሴት ገሮ እንዲያቅፋት የተመኛትን......በእጁ እየጎተተ በቸርችል ጎዳና አብሯት ሊፈስ ያሰባትን ልጅ እንዴት ያን አረንጓዴ ጎረቤቱ በረካ ገላ ላይ ሲያየው ይርሳት? ፊት ለፊት እዚያች አልጋው ላይ ተጋድመው ፊቷ ፊቱን ነክቶ በግንባሯ ግንባሩን እየገፋች ለስላሳ ውበቷን ሰጥታ በድንቅ ኪነት የሞላችው እሷ ልጅት፣ ድምፅዋን ሲሰማ ወይም ስሟን ሲሰማ ከውስጡ ተቀስቅሶ በብዕሩ ወረቀት እንዳልገረፈ ወይ አቅፋ ስትስመው እጆቿን ትከሻዎቹ ላይ አድርጋ በጃዝ ሙዚቃ በቀስታ ስታስደንሰው የጡቶቿ ክፋሎት ላይ እያፈጠጠ ሰባተኛው መልአክን[40] እንዳልገነባ......

ይኼ አረንጓዴ......

ዛሬ በትንንሽ ምሬት ይሞላና ጊዜ ይለወጣል:: ምንም የረባ ሳይደረግ ሰዎች ወዲያ ወዲህ ይራራቃሉ:: የተያያዙት ይፈታታሉ:: ፍቅር የገመዳቸው ይበታተናሉ:: ሁሌም ሚስጢር ነው:: ለምን እንደወደደም ለምን እንደ አልወደደም ሚስጢር ነው:: አስማትም እንደ ሰው ያልፋል::

ቀለም ሁሉ ያልፋል......አረንጓዴም ያልፋል......ምናልባት......

«ምነው መስኮት? ላስተዋውቅህ?» አለው ስብሐት::

መስኮት አልመለሰለትም::

በረካ በአረንጓዴ ጉርድ ቀሚስ ውስጥ ናት:: መቼ ቀን ፋኖስ ጠበበኝ ብላ ከልጅነቷ የጨርቅ ባንክ እየተጠራጠረች(ልስጣት አልስጣት) ያዋሰቻት:: እንግዶች ያውም ወንዶች በዚህ የግል ራቁትነቷ ተከፋፍታ እንዳለች ይመጣሉ ብላ አልገመተችም:: የስብሐትን ድምፅ ስትሰማ ዞር አለች:: ራሷን ለመሸፈን ጊዜ አልነበራትም:: ጥረቷ ራሱ ውበት ነበረው......ጠይምነቷ እዛ እዛ አላሰበችው ቦታ እዛ እዛ በየቦታው ለስላሳነቱ እየተጋለጠ......ዳንሷ ሆኖ......የሆነ ባዶ አየር ላይ እንደምታንቋልጥ ነገር......ወይ ከባዶ አየር ጋር ፋካቤ እንደምታደርግ ሁሉ:: ተስፋ ቆርጣ ዐይኖቿን ለአመል መለስ ስታደርግ አንድ ድንክ አንድ ድካካ አንድ

40 የልብ ወለድ መፅሐፍ አርዕስት(አ)

ድምቡሼ ቆሞ አፍጦ ያያታል:: በዚህ ጥረት መሃል ራሷን ለመጋረድ ባልተሳካ መልክ ተንደፋድፋ፣ ተስፋ ቆርጣ፣ በእጆቿ ፀጉሯን እንደ ምትነነጉን ሁሉ ከአናቷ በላይ ሰቅላ ይዛ መስኮትን እያየች ፈዛ ቀረች

*......እንዴት የምር ድንክ ነው......እንዴት ቅልብጭ ያለ......*

መስኮት ፊቱ ያንቀላፋ መስሏል......

*ምን ዓይነት ደረት ያላት ሴት ናት? የጭኗስ ጠይምነት እንዴት ጥልቅ ነው......ለስስ ብሎ የተቆላ ቡና......ከጋቢው ጋር ደምረው ሲያይዋት ከኩታው ንጣት ጋር......የከሰል ቅብ ትመስላለች......ስዕል ነገር......ይኼንን ኩታ ያጠበው እጅ......*

ስብሐት ሳቁ መጣ:: ትላልቅ ሰዎች እንደ ልጅ በወሸኔ ሲለከፉበት::

«በረካ ተዋወቂው 'መስኮት' ይባላል:: ዝናሽን ሰምቶ ነው የመጣው» አለ እየሳቀ:: የሰማው ያለ አይመስልም:: ሁለቱንም እያቀያየረ አየና ቤቱ ሊገባ ሲል ፋኖስ ከውስጥ ሳሙናና ጠርሙስ ይዛ ስትወጣ ተገናኙ::

ደነገጠ::

«መቼ መጣሽ?»

«አንተ ነህ......እኔ ልመጣ ስል የምትወጣው»

ብልጭ አለበት::

«ላነጋግርሽ እፈልጋለሁ»

«ምን አለ የምታናግረኝ?» አለች:: የንቀት አይነት:: ባዕድ መሰለችው::

«ምን ሆንሽ?»

«በረካ ፀጉሯን ታጥባ ስትጨርስ እመጣለሁ»

እየታከከችው አልፋ በረካ ግቢ ለመግባት ወደ ሚጋሩት የወደቀ አጥር ስታዘግም መስኮት ድንኩን በትኩረት አጤነችውና:

«ማነህ አንተ ደ'ሞ?» አለችው::

አልመለሰላትም:: ከላይ እስከ ታች አያት:: እራሱ ግቢ ያለ ይመስላል::

«ከስብሐት ጋር ነው የመጣው? የማያመጣው ዓይነት ሰው የለ» አለችና ፋኖስ በወደቀ አጣናና ቋሚ እንጨት ላይ ተረማምዳ በረካ ግቢ ገባች::

«ፀጉሯን ልታጥቢያት እንደሆነ ውሃ ማፍሰስ እንድረዳ ይፈቀድልኝ» አለ መስኮት:: በረካ እጇን ከፀጉሯ ውስጥ ሳታወጣ እቆመችበት አድርጋው የማታውቀውን፣ የረሳችውን፣ ትንፋሿ ቁርጥ እስኪል በሳቅ ተንፈራፈረች::

«ማነህ አንተ?» አለች ፋኖስ እንደገና በቁጣ......

ስብሐት ቤቱ እንደ ገባ ቀድሞ የሚቀመጥበትን ወንበር ትቶ ወደ ምግብ

ጠረጴዛው ሄደ:: ከመቀመጡ በፊት ከኮቱ ኪስ መፅሐፍ አወጣና ጠረጴዛው ላይ ጣለው:: ከዚያ ልዩ ስራ እንደሚሰራ ሁሉ ተስተካክሎ ተቀመጠ:: የፋኖስ መልስ ግራ አጋብቶታል:: ፋኖስ እንዲህ ግንባር ለግንባር ከባዶ ተነስታ ተቀናቅናው አታውቅም:: በቀስታ በሚንቃነቁ ዓይኖቹ ዙሪያውን አጠና:: ሳሎን ሶፋው አጠገብ የተቀመጡት ሁለት ሻንጣዎች ምን እዚያ እንዳመጣቸው ይጠይቃል:: ውስጡ ነቃ ያለ ጥርጣሬ ይሰማዋል:: ጥርጣሬውን ግን ማመን አይፈልግም:: በየግድግዳው የተሰቀሉት ፎቶ ግራፎችና ጌጦች ድሮ የነበሩበት ቦታ ናቸው:: ሳል ሳልና አገሳ:: የቢራ ግሳት......*ምን መሆኑ ነው እየከረመ ያገሳኛል እንጄ*......

ከተቀመጠበት ተነሳና ኮቱን አውልቆ ወንበር መደገፊያ ላይ ሰቀለ:: በቀስታ እየተራመደ ወደ መኝታ ቤት ገባ:: ብዙው ነገር እነበረበት ቦታ ነው:: ሲኒማ ኢትዮጵያ አጠገብ ለማስታወሻ ከፋኖስ ጋር በትልቁ የተነሱት ፎቶ ቁም ሳጥኑ በር ላይ እንደተሰቀለ ነው:: ፋኖስ ውብ ነበረች:: ዛሬም ናት:: ከጥቂት አመታት ወዲህ የሆነ ነገር ከመሃላቸው ገብቷል:: ምናልባት መሰላቸት:: ምናልባትም አያውቀውም:: አሁን የሚያውቀውና የገባው ነገር ቢኖር ተነጫንጫው ቤት ውስጥ ከገባ ጀምሮ ሊወጡ የተዘጋጁ ሻንጣዎቿን እንኳን ሲያይ አለመደንገጡ ነው:: አለመደንገጡ ነው ያሳሰበው:: ወንበር ላይ (በለሆሳስ......ቀስ ብሎ እንደ ደከመው ወይም ወገቡ እንደ ታመመ ሰው) ተቀመጠና በር በሩን ማየት ጀመረ:: የሚጠብቀው ጉዳይ እንዳሌለ ይገባዋል:: ቢጠብቅም አንድ ጉዳይ እንደ ሆነ ይገባዋል:: ደስ የማይል ግን ያላስፈራው:: የሆነ ነገር ትዝ ብሎት ወደ ግራ በፍጥነት ዞር አለ:: ግራማፎኑ አለበት ቦታ ነው:: እዚያው ግራማፎኑ ጎን በትንሽ መደርደሪያ የተሰለፉት አልበሞች አልተረበሹም:: ከተቀመጠበት ሄዶ አልበሞቹ ውስጥ ከሚወዳቸው የብሉስ ዘፈኖች አንዷን በርብሮ አገኘ:: የዱክ ኤሊንግተን *ብሉ ቤሪ ሂል*[41]:: ሙዚቃውን ለመስማት ሸክላውን ማጫወቻው ላይ አስቀመጠው:: ከ 'አረንጓዴዋ ልጅ' (ፋኖስን ከጓደኞቹ ጋር የሚጠራበት ኮድ) ጋር የከነፉ ሰሞን እንጦጦ ወጥቶ ከእሷ ጋር በመጀመሪያ የሰማው ሙዚቃ ነው::

*ያን ጊዜ......*

......የተውሶ መኪናው ታች ገደል ስር አህያ እያሸተታት ቆማለች:: ጸጉቱን አብረው ይወጣሉ:: በግራ ብብቱ ትኩስ ባትሪ ድንጋይ የጎረሰች ትንሽ ቴፕ አጣብቆ ይዟል:: ሳታቋርጥ 'የብሉስ' ዘፈን የምትነሰንስ:: ጆሮዎቻቸው ይኼን የዜማ ሰበዝ ካጥለቀለቃቸው የተፈጥሮ ሁካታ መሃል እየመዘዙ ያወጣሉ......ሲቀናቸው:: ፊት ለፊቱ እያጎነበሰች እያቀናች፣ ዞርም ብላ ጠይም የተማረከ ልጅነቱን እያየች:: በዚያች በለከፈችው አረንጓዴ ቀሚሷ:: ኋላ ኋላ ሆኖ ሊደርስበት የማይችለው የመሰለውን ትዕንግርት ያይ ነበር:: እሷ ቀሚሷን ትሰበስባለች ትሽኮረመማለች:: ይገባታል ያ ደራሲ በፍትወት እንደ ተለኮሰ:: ይገባታል ጭኗ መንጠቆ እንደሆነ:: ስብሐት ዓሳው ከደረቅ አዲስ አባ ወጥቶ ደረቅ እንጦጦ ስንደዶ መሃል እየተውተረተረ:: እሷ ዝዋይ ናት ይኼን ሰው ነክራ የምታድን:: ልትጠልቅ የጀመረችው ፀሐይ የእግዚአብሔርን የዓይን ገበር መስላለች:: ወገብ የሚደርስ ሳር መሃል ተቀመጡ:: ንፁሕ ቁልፎች የደረደረች አሮጌ የካኪ ኮት የምትመስለው አዲስአባን በፈዘዘ ዓይን እያየ እጆቹ ያቶከሱ ጭኖቿ ላይ አረፉ::

41 blue berry hill= የዘፈን ስም(የአጋም ኮረብታ እንደማለት)(አ)

ከወዲያ ወዲያ በኩብትና በጎርፍ ተግጦ ያለቀ መስከ እያቋረጡ......በጥብቆ የተጥለቀለቁ ገበሬ ሕፃናት ይመጣሉ:: ጭኑ ላይ ራሷን አስቀመጠች:: ፀጉሟ እንደ ድንቅ እጅ ስራ የተቆላለፈ ነበር:: እንዲህ እንዲያ እንዲህ የገባና የወጣ:: ያ ደፋር ቀልቃላ እጁን አይቷል በአረንጓዴ ቀለም ሲነድ:: ጉልበቶቿ ግራና ቀኝ ሆነው በእነሱም መሃል ያየው አጋም የሚቅሙ እረኞች ነው:: ራሱን ሲጠይቅ ነበር......*ለምን ኢጋም ኣልለቅምሳትም*......ለመጀመሪያ ጊዜ ሳማት:: ግንባሯን:: ሊረብሻት አልፈለገም:: ባለጥብቆው ኡራ ሁሉ እየተጯጯኸ ሳያያቸው አለፈ:: እወዲያ ጥቂት ጎጆዎች ይታያሉ:: ከተቀመጠበት ተነሳ:: ሲጋራ ማጤስ ፈለገ:: የአጋሙን ነገር ሊረሳው አልቻለም:: ዞር ብሎ ጋደም ያለችበት አያት:: በጉልበቶቿ መሃል የነጭ ሱሪዋ ውልብታ አረንጓዴ ውጋጋን ለብሶ......ጠይም ባቷ ይኼን ይኼን ከእንጦጦ የወረደ ቀጭን አየር የጠጣ......አስተያየቱን ፈርታ...... በጨዋነት እግሮቿን ስታነባብር......የበለጠ ደ'ሞ የጭኗ ጎን በስፋቱና በጠይምነቱ ደ'ሞ በዓይን የማይመጠነው ልስላሴው......ቆሞ ሊያያት አልቻለም:: ሁልጊዜም ቆሞ በፀጥታ በትዕዝብት ሊያያት አይችልም:: ጎኗ ጋደም ብሎ አንገቷን አቅፎ ሳማት......*ሳምኳት ያቺን የአዲስ አባ እመቤት......ሳምኳት ትዕንግርት ኢያልቅምና......ከእሷ የሸተተኝ ጠረን የኢጋም ነበር......ያልጠበቅሁት ነበር...... ምናልባት ዳገቱን ስንወጣ ሳላያት ጥቂት ለቅማ በልታ እንደሆን......እና ዳገቱ ላይ ቆመን ተደጋግፈን የመሬት ስበት ባዘመመው ቁመና......እንዲህ እተከፈተው ኢድማስ ጉያ ውስጥ ሚስጢር ከሚያሳየው የጣይቱ ኮረብታ ላይ እየሳምኳት...... ያን ሚስጢር አውቄ ባልጨርሰውም......ባልችልበትም ማወቅ......የሰማሁት የኤሊንግተንን ሙዚቃ ነው......ይኼን ዘፈን ነው......ዜማው ይወርዳል......ዜማው በጆሮዬ ነበር......እንደ ፋኖስ ገላ እንደ እንጦጦም ሸንተረር ነው......ቆንጆዎች በማንም ሰው ልብ የሚያሳድሩት ገና ያልመጣው የመከዳት ስሜት ይሰማኝ ነበር......ግን ያስታውቃል ሁሉ ነገር ተጠቃሎ እንደማይፈርስ......*

Though we are apart/You are part of me still/For you were my thrill/ on blueberry hill

እተቀመጠበት በትዝታ ሙዚቃውን እያዳመጠ ተወዛወዘ......

*ለመሆኑ ያ ሁሉ ኢጋም ይኖራል......ያ ሁሉ ያየን ኢጋም ዛሬ ቢያየን ምን ይላል......የመሞት ዓይነት ነው......ከሞትስ በኋላ ትንሳኤ የለም ያለ ማነው...... ፊታውራሪን ኢያቸዋለሁ ቢያሳግጡ ራሱ-ቀላል ጮሌ አፍሮአቸው እንደ ጨረር የቆመ......ዓይኖቻቸው ላለመሞት የሚሉ......ፋኖስ ያረፈችበት አረንጓዴው ሜዳ ላይ ጃን ድንኳን ተክሎ የተቀመጠ ሰው ኣለ......ከድንኳኑ በቀስታ እየገባ የሚወጣ ከመወፈሩ የተነሳ ድቡልቡሌ የሆነ......ጠቅላላ ጡንቻው በለዘብታ እንደታሸ ሎሚ ሁሉ ጎልቶአል......ዓይኖቹ* በከፊል ተጋርደዋል አይኖቹን ሲከድን አንጎሉ እየፈላ የሚያሳክከው ይመስለዋል......*በስብ የተጣጠፈ ቦርጩን ኢያከከ:: 'የሰው ሞት ልብ ወለድ ነው......ከተወለዱ በኋላ መሞት የለም.....ሌላው ቀርቶ በጨቅላነቱ የመጀመሪያውን ምራቅ ተፍቶ......የመጀመሪያውን ሽንት ሸንቶ ቢሞት አልሞተም:: እዚህ ነው'::*

*ብሉ ቤሪ ሂል ኦ ብሉ ቤሪ ሂል!!*

ተረጋግቶ እግሮቹን ዘርግቶ ተቀመጠ:: ያልጎደለበት:: ፋኖስ ስትገባ ኮቴዋ ይሰማዋል:: በዓይኑ ቂጥ አያት፣ ለንቀት ሳይሆን ከውስጡ የሚነሳው የሚጣፍጥ የፈጠራ ማዕበል እንዲነቃነቅ አልገፋፋውም:: አንዳንድ ውበት ከተቀመጡበት ከተኙበት ከተገኘው ስፍራ ሰፍቶ ይይዛል፤ መንዝ ትርጉም ያጣል፤ ማየትና መስማትም......ወደ ሻንጣዎቿ ቀረበች:: ያያታል ግን ሊያናግራት ፈቃደኛ አልሆነም::

«በል ስብሐትዬ እኔ መሄዴ ነው:: እንዲህ የሚሆን አልመሰለኝም ነበር» አለችው:: ማቆላመጧ አልገባውም:: ያልገባው የነገሩ ፍጥነት ነው:: ያለ አንድ ማስጠንቀቂያ መሆኑ ነው......*የማያውቀኝ ትራፊክ ፖሊስ እንኳን ያስጠነቅቀኛል......ተቦርቡረን ነበር እንዴ......*'ነገሩ ገብቶኛል' ለማለትና እንደ ተሰላቸ ለማሳየት እጆቹን ከጭኑ ላይ አነሳና አራገበ:: ግራና ቀኝ ሁለቱንም ሻንጣዎቿን እየጎተተች በር ጋ ስትደርስ፡

«አንዳንድ ቀን ባገኝህ ደስ ይለኛል»

«ማን ጋ ነሽ?»

ለመናገር አልፈለገችም:: ግን ነገ አዲስ አባ ጎዳና ላይ ማንም ሊሰማው::

«ለበን ጋ»

«ለበን ይኼ መሰላሉ?»

«አዎ»

«ለበን እኮ ገና ሰው አልሆነም:: እኔ ብሽቅ ከሆንኩብሽ ከብሽቅ ወደ ብሽቅ ምን አስኬደሽ?»

«ብሽቅ ነህ አላልኩህም:: እሱም ብሽቅ አይደለም»

«መልካም:: ምን ልበልሽ? ደስታ እመኝልሻለሁ»

ሌላ አልተናገረችም:: *ምን ልናገር......ምን ልመልስ......እኔው ትቼው እኔው ላግኝህ እለዋለሁ......አቀማመጡ ራሱ ስዕል ነበር......ደከመኝ ግን......ባር ባር ለምን ይለኛል......ሙዚቃውን አውቆ ነው አውቆ ነው......ያን ሙዚቃ አውቆ ነው የሚያጫውተው......*እሱ ከቤት ጨለማ ውስጥ ሆኖ የሚያያት ይመስላታል:: እሱ አያያትም:: ትኩረቱ ወደዚያች ጠረጴዛው ነው:: እርሳሶቹ እንደ ዶሎዶሎ እንደ ተበተኑ ናቸው:: መቅረጫው የለም:: ተናዶ እንደ ወረወረው ትዝ አለው:: ከንፈሮቹን መጠጠ:: የሚያምር ነገር ከውስጡ እየመጣ እንደሆነ ይገባዋል:: ከፋኖስ የወሲብ ቅስቀሳ ወይ አሳሳም ወይ የዳሌዋ ቅንፍ ወይ ከዕንብርቷ ስርጓጾ ወይ ከጢሙ--ቆዳው ላይ ከተንዠረገገ ግርማ ሞገስ ሳይሆን......ከውስጥ ማዕበል እየመጣ እንደሆነ ይገባዋል:: የአዲስ ኪዳኑ አላዛር ከሞት ከተነሳ በኋላ ወደ ገሊላ ወርዶ በወይን ሰከረ......የተረት ሰፈሩ አላዛር ደራሲው ነው ከምናቡ ጋር እሽኮለሌ ሊጫወት......

እስከ ዛሬ እንደ ነበረ ከማያውቀው ግን እውስጡ ካለ ስፍራ፣ ጨለማ ከለበሰች ሰደፍ ብብት ውጋጋን የከበባት ደንግ......

ልትፈነዳ የምትቅበጠበጥ ይመስለዋል......

*ማን አስቀመጣት እዚያ......*

የማልቀስ ጠርዝ ላይ ነበር......

*ሃብታም ነኝ......*

*ገና ሐብታም ነኝ......*

ወደ ጠረጴዛዋ ሄዶ በቀስታ ተቀመጠ:: አንድ ትንሽ የማስታወሻ ደብተር እጁ እንዳመጣው ሳበና እየገለጠ ከሸሚዙ ደረት ስክሪብቶ አወጣ:: ቢክ ይወዳል:: ውሐ የመሰለው የላስቲኩ ቱቦ የቀለሙን አካሄድ ያሳየዋል:: ቢክ ነው......

## *ስምንተኛው ጋጋታ*

***የኢጋፋሪ እንደኛው ዘመድ ልጅ አቶ አላዛር ያጋጠማቸው ምንትስ እንትን ስም የለውም..................***

***ከዕብደታት አንድ ቀን በአባ ኩኩሉ አቆጣጠርም ስምንተኛው ሺህ እንደ ነገ ቲቅሕ ሊነጋ እንደ ዛሬ.........***

የአራት መስመር ትልም ሰራ:: እርሻው እንደሚዘልቅ ይሰማዋል:: የምትቀልጠው ደንግ በነዚህ ጥቁር ፍልሞች መሃል እንደ ወተት እንደምትፈስ......

የምትቁለጨለጭ ሞላ ፈገግታ ከፊቱ ላይ ትነሳለች......

ይህቺም ፈገግታ እንደ ትንሽ ነጭ ዕርግብ አዲስ አባ ሰማይ ላይ ፈንድታ የሚያበሩ ተረቶች የምትበትን......

ሰዓታት ከርሞ መስኮት እየተናገረ ገባ.........

«ስብሐት!!»

ስብሐት አቀርቅሯል:: መስኮት እንደ ገባ ቤቱን እየተሽከረከረ አየ:: እዚህ መጥቶ አያውቅም:: ስብሐትን ያውቀዋል እንጂ ቤቱ መጥቶ አያውቅም:: ስብሐትን እተቀመጠበት አተኩሮ አየው::

«ሚስትህ ትታህ ስትሄድ ተቀምጠህ ትፅፋለህ?»

አልመለሰለትም::

«በረካን የመሰለች ልጅ እዚህ ተቀርቅራ እኔ......»

ስብሐት አልሰማውም:: የሰማው አይመስልም:: መስኮት ወደ ስብሐት ቀርቦ በትከሻው ላይ አሸጋገሮ ወደ ሚፅፈው አየ:: ያፈጠጡና የተሰረዙ ቃላት ገፆች ላይ ፈሰው:: ስብሐት ዞር አለ......

መስኮት ሸሸት አለና፡

«ይቅርታ ይቅርታ አልረብሽህም»

«ነገ ከመስሪያ ቤት እደውልልሃለሁ:: አሁን እዚህ አታጮልቅብኝ»

«ጥሩ ጥሩ:: በረካ ድንቅ ናት ልልህ ነው»

«አውቃለሁ»

«እንደ አለፈለገ ሰላም ኩታ ወይ ጋቢ አልብሼ ልስላት ነው:: በጣም የሚገርም ጋቢ አላት አይተኸዋል?»

«ሰማኸኝ አንተ ድንክ አናትህ ላይ ሳልደንስብህ:: አሁን ብቻዬን መሆን እንደምፈልግ አይገባህምና ነው? ይቅናህ ደ'ሞ»

«ይቅርታ……ደውልልኝ»

«ከገባሁ»

«ከገባሁ?»

«እም»

በድንካዊ ፈገግታ አየው:: መስኮት እየተውተረተረ ወደ ውጭ እየወጣ…… ለምን እንደሆነ ይገባዋል ደራሲው የሚያባርረው……

*ሚያዚያ 1987 ሆላንድ*

# እቴሜቴ ሎሚ ሽታ

ደፋር እኮ ነው:: ኡ! ደፋር:: እምባለምበት ቤተክርስቲያን ሴቶች ረድፍ መጣና፣ አይ ድፍረትና ብልጠት እቴ–እኔ ሴት መስሎኝ ጆሮዬን ሳውስው ጠጋ ብሎ፣ በዚያ በሚያምር ጎርናና እንደ ዳምጠው መኪና በሚካበድ ድምፁ:

«እሰይ!......ጠረንሽ እኮ የሎሚ ነው» አለኝ::

በእውነት ነው የምለው ድንግጥግጥ አልኩ:: ለምን አልደንግጥ:: የማውቀው ድምፅ ነበራ:: የራሴው ጉድ፣ የራሴው እስናቀ:: 'እንዴ!'ብዬ ዞር አልኩ:: ከአፍንጫው በስተቀር ፊቱን በምታምር ቀይ ጥለት ያላት ነጠላ ሸፍኖአል:: መሬት የሚያብስ የአገር ባሕል ቀሚስ ለብሷል:: ሊያርፍ ነው!?! ደነገጠች ብሎ እንኳን ቅር አላለውም:: እንግዲህ ቤተክርስቲያን ግቢ ሰው በተሰበሰበበት 'አባሩልኝ!' ብዬ አልጮህ:: ያላወቅሁት መሰለው:: ምንም እንዳላጠፉ ሁሉ ዙሪያ ገባውን ሳቅ ሳቅ እያለ አይቶ እንደ ገና ጠጋ ብሎ «እስናቀ ነኝ» ብሎ ሌላም ሌላ ደጀ ሰላም የማይባል ለስጋዬ የጣፈጠ ዝርዝር ነገረኝ:: ቀና ብዬ ሰው ማየትም ከበደኝ......እንዴት ሆኖ! አጠገቤ ያሉት ፀላዮችና ዳዊት ደጋሚዎች በሹክሹክታም ቢሆን የተናገረውን የሰሙ መሰለኝ:: ላስደነግጠው፣ ላባርረው እቃጣና ('አልጠገብክም? እዚህ ደጀ ሰላም የፀሎት ቦታ እንዲህ ያለ ነገር የምትናገረው? እንዲህስ ወንድ ሆነህ የሴት ለብሰህ ሴት ቦታ የምትመጣው? በል ወግድ' ልለው) አንጀቴ ሸፈተብኝ:: በፍርሃት ተኮማትሬ የሚለኝን ማዳመጥ ቀጠልኩ:: ረኸም የሚጣፍጥ ልብ የሚያሸፍት ነገር በዚያ ደብዛዛ የዓመቷ ማርያም ሌሊት እንደ ሚሞቅ የድምፅ ጣዝማ ነገር በጆሮዬ ቀዳዳ አንቆረቆረ::

አጎንብሼ ከማዳምጥበት፣ በሱ ወሬ ከምታደስበት (ወሬ እወዳለሁ:: ከሚያበላኝ ከሚያጠጣኝ ይበልጥ የሚያወራኝን አቀርባለሁ) ቀና ስል ተከትላኝ

የመጣችው ሁሉአገርሽ የተባለች ሰራተኛዬ የሚደረገው እንደ ገባት፣ ሁሉን ነገር እንደ ተረዳች፣ አጠገቤም እተንበረከኩበት አጎንብሳ የምታንሾካሽከው ሴት አስናቀ መሆኑን እንዳወቀች ዓይነት (አፏና ከፊል ፊቷ በጋቢዋ ቢጋረድም) ዐይኖቿ ተከድነው የዳርና ዳራቸው ቆዳ ሲሸበሸብ አየሁ:: ፈገግ ያለች መሰለኝ:: ይኼ ድርጊቷ አበሸቀኝ:: ምን ያስፈጥጣታል? ተዝናንቶ ነፋስ ሲቀበል የነበረውን የፊቷን ግማሽ ለምን በከፊል ጋረደች? ምንስ ያስቃታል? በጋቢ አቅም የራሷ ስለ ሌላት ሁልጊዜ የትምባኋም አባቷን ተበድራ ስለምትመጣ ሲጋራ ሲጋራ ትሸታለች:: በአጠገቤ ስታልፍ ወይ ስትታከከኝ ወይ አንጉል ስትጠጋኝ ይኼ የኒያላ ወይ የጉሬዛ ብቻ የሆነ የሚቀረና ትንባሆ ጠረን ሲሰነፍጠኝ ሊያመኝ ይደርሳል፡ ታዲያ ጉረኛነት ወይ ጥጋበኛ ሆኜ ሳይሆን በጣም ቀርባኝ ጎን ጎኔን እንድትሄድ አልፈልግም:: ከቤተክርስቲያን ስንመለስ ደ'ሞ ያን ጋቢ አባቷ ከእሷ ተቀብሎ ለብሶት አደባባይ እንዲወጣ ተቻኩላ ቤቷ ትገባለች::......የነጠሳዋን ይሁን የጋቢዋን ማጠብያ እሞ፣ ሆዷን የምትሞላበትንም የዶሮ ኩምቢ[42] የሚሰብር ዘንጋዳ ከእኔ ነው የምታገኘው:: የምሰጣትን ገንዘብ አባቷ ይነጥቃታል መሰለኝ አንድ ቀንም አምሮባት አያውቅ:: በዱርዬነቷ ደሃ ሆና ማርጀት የተፈረደባት ዕድለ-ቢስ:: ያን ቀን ጠዋት ያረጀ ዕድ ስር የጅብ ኩስ መስላ ተቀምጣለች:: አስናቀ ቂጥጥ ካለበት ቆሞ በተለወጠ አስመሳይ ሴትኛ አካሄዱ እየተንኳተተ እኔ ካለሁበት ቦታ ተነስቶ ሲሄድ በዕፍረትና በመገረም አየሁት:: ባለቤቴ ታደሰ እዚያው ቤተክርስቲያን ግቢ በወዲያ በኩል ዛፍ ስር ቆሞ እንደ መልካም መሪጌታ በሁለት እጆቹ ዳዊቱን ፊት ለፊቱ ዘርግቶ ይዞ ያንቸለችል ነበር:: አስናቀ ከእኔ ያለውን ጉዳይ ከጨረሰ በኋላ ቀስ ብሎ እየተሳበ ዳዊት ሲደግም ለመስማት እንደሚፈልግ ሁሉ ጆሮውን ቀጥ አድርጎ ታደሰ አጠገብ ሄዶ ሲቆም አየሁት:: መጀመሪያ አፈርኩ:: ቀጥሎ ግን በአስናቀ ደፋርነትና ጮሌነት ተደስቼና ተገርሜ እተንበረከኩበት ቦታ ጉልበቴን እስኪያመኝ በሳቅ ፍርፍር አልኩ:: ያው እያፈርኩ ነው መቼም......ሂሂሂ......

○

(ስሜ ሁሉአገርሽ ነው:: ግን በሙሉ እንዲህ ተጠርቶ ሰምቼው አላውቅም:: የሚያውቀኝ: ሁሉ፣ ሁሉዬ፣ ሁል፣ ሀሊ፣ ሃሌ ነው የሚለኝ:: (ቁልምጫ ከተገኘ ማን ይጠላል) ይኸቺ ሎሚ ሽታ ብቻ ናት 'ሁሉአገርሽ' ብላ ሞልታ የምትጠራኝ:: ታዲያ ቅር ይለኛል:: በመንፈስ የምታርቀኝ ይመስለኛል:: የሚያቆላምጠኝን እወዳለሁ:: 'ረዳቷ ነሽ' ስለተባልኩ ለድምፅዋና ለግልምጫዋ እንድቀርብ ከእሷ ብዙ እርቄ ተቀምጬ አላውቅም (በማላውቀው ምክንያት አንዳንዴ ስጠጋት ብትነጫነጭም):: ሁልጊዜ ስርስሯን ነው የምሄደው:: ስርስሯን:: የታዘዝኩትም እንደዚያ እንድራመድ ነው:: እንደ እንቅፋት:: ወይ ምን ልበል እንደ ውሻ:: ተከናንበን ስንጓዝ ግራና ቀኝ ተመልካች የሚያስበን ልጅና እናት እንደሆንን አድርጎ ነው:: ሎሚሽታ በጣም ረዥም ሴት ናት:: ደልደልም ያለች ናት:: እኔ ትራፊዋ እመስላለሁ:: እሷ ከሰማይ ብትወረወር እና ብትሰባበር ደቃቃዋ

ተፈናጣሪት እዛ ቦይ ወድቃ የምትገኘው እኔ ነኝ። ማርያምን። መጀመሪያ ጨዋ መስላኝ ነበር አጃቢ ስትፈልግ። በኋላ በኋላ ሳይ ለካስ ባሏ ያልበቃት የውሽት ዓይኖቿን የደፋች ቅሪ ናት። ያገባች ጋለሞታ።

እኔን ከአመት በፊት አባቴ 'ዲቦራ ነሽ' ይለኝ ነበር። ቶሎ ተመለስኩ እንጂ—እሱው አባቴ ይመስገንና። ወንድ አውል ነበርኩ። 'ዐይንሽን አንስተሽ ወደ ወናዎች ኮረብቶች ተመልከቺ፣ ያልተጋደምሽበት ቦታ የት አለ?'[43] የተባለልኝ። ሳዱላዬን ሳያርገፈግፍ ያለፈ የአዱ ገነት ጎረምሳ አለ?[44](የበቅሎ ቤት፣ የባምቢስ፣ የሜክሲኮ፣ የልደታ፣ የቡልጋርያ፣ የፖፖላሬ፣ የለገሃር፣ ወዘተ) ታዲያ ከልምድ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ቶሎ ይገቡኛል። ሎሚ ሽታ ቤተክርስቲያን የምትሄደውና የማይገባትን የግዕዝ መዝሙረ ዳዊት እየተውተረተረች የምታነበው ፍትወት የሚያቃጥላቸው ዘጠኝ ጎራሽ ዓይኖቿን ከጠርጣሪ ለመከለል ሳይሆን አልቀረም እላለሁ። መጀመሪያ መጀመሪያ አከብራት ነበር። ማለቴ ምንድነው እንግዲህ...... የምታደርገውና የምታስበው አንድ መስሎኝ። ዕውነቴን ነው እሷ እንደ እኔ ነፃነት ቢኖራት ትንሽ ባለ አንድ አልጋ ቤት ተከራይታ፣ በሩ ላይ በትልቅ ሰሌዳ ላይ መዓልትና ሌሊት በሚያበራ ቀለም (እዚህ አብዮት አደባባይ ለመስከረም አንድ/ሁለት እንደ ሚሰቀለው መብራት) 'የአገሬ ወንዶች ሆይ! ኑና ሒሳቤን ሰጣችሁኝ ወደ ምትሄዱበት ሂዱ' ብላ ትለጥፍ ነበር። ማጋነኔ አይደለም። ልጅ እስናቀ የምትለው......ያ ጥቁር ልጅ ደጀሰላም ሊያያት ሲመጣ (ገና ሲቀርባት ነው ማን እንደ ሆነ ያወቅሁት) እንደማያውቅ የሚያወሩትንም እንዳልሰማ--ድንገት ባሏ ቢነቃና እንግዳ ነገር ቢጠያይቀኝ ምስክር እንዳልሆን ፈርቼ--ገሸሽ ብዬ የቤተክርስቲያን ግድግዳ ተደግፌ ቆሜአለሁ(እያለሁ የለሁም)። ግድግዳው ይሞቃል። ቤተ ክርስቲያኖች የተለዩ መሆናቸውን ለማወቅ እዚያ መሄድና ግድግዳ ተደግፎ መቆም ወይም መቀመጥ ሳያስፈልግ አይቀርም። በሚበርድ ጠዋት ግድግዳው ይሞቃል። በሃሳቤ ሺህ መላዕክት ግድግዳው ውስጥ ከሲሚንቶው ጋር ተገንብተው ጀርባዬ ላይ ሲተነፍሱብኝ ይታየኛል። ያስፈራል፣ እና በመደመምም ይሞላል። ታዲያ ይኼ እስናቀ የሚባለው ሰው ከላይ እስከታች ኩታውን ተከናንቦ፣ ባለ መቀነት የባሕል ቀሚሱን አድርጎ መጣና እንዲያ ግርማ የሚያደፈርስ የማይሆን ነገር ደጀሰላም ውስጥ ያደርጋል። ከአካሄዱ እሱ መሆኑን አውቄአለሁ። እኔ ከመልክ ይልቅ አካሄድ ማስታወስና መረዳት እችላለሁ። ከድሮም ነው። በመጀመሪያ፣ ምንም ቢሆን ምንም የሴትና የወንድ አካሄድ

---

43 ከትንቢተ ኤርምያስ 3:2
(አንድ የሰፈሬ ልጅ ጴንጤ ይሁን ኦርቶዶክስ ወይ ፕሮቴስታንት ብቻ......ወደ እግዚአብሄር እንድመለስ እንዳነበው ከሰጠኝ አሮጌ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እየመረጥኩ ሳነብ ይኼን ጥቅስ ከወራት በኋላ በቀይ ስክሪፕቶ ከስሩ ተሰምሮበት አገኘሁት። ከጥቅሱም ጎን በሰማያዊ ስክሪፕቶ 'ወጣቱ ከኤች አይ ቪ እንዲርቅ ማስተማሪያ' የሚል ማስታወሻ ነበር። እንዳንዴ ሳስበው ልጁ ይሄን ቦታ ምልክት ያደረገበት ሆን ብሎ እኔ እንዳገኘው ይመስለኝ ነበር። ከእሱ ጥቅሶች ይልቅ ከመጥፎ ጎዳናዬ የመለሰኝ አባቴ ነው። አንድ ጠዋት ቁርሱን እንኳን ሳይቀምስ እተኛሁበት መጥቶ የለኮሰውን ሲጋራ እንዴም ሳይስብለት ጣቶቹ መሃል እስኪያልቅ ይዞ፣ ብዙ ብዙ የሚያስፈራና የሚያሳፍረውን የመሳሰለ ከአወራኝ በኋላ 'አንቺ ሞተሽብኝ ከማይ ቀድሜ እኔ ልሙት' ብሎ በለቅሶ ፈረሰ። ከዚያን በኋላ ዕውቀት ገዛሁ፤ ሁሉን ነገር ተውኩ)

44 ከሙሻ ሙሾ ዘፈን?(አ)

በቀላሉ እለያለሁ......ሁለተኛ: አካሄድ እንደ እጅ አሻራ ነው፣ ማንም ከማንም ተመሳሳይ አካሄድ የለውም......

የምኖረው መንገድ ተሻግሮ ከእሷ ቤት በስተግራ ሁለተኛው ቤት ውስጥ ነው--ከዘሩ ሱቅ ጎን--የከድር እህት ባል:: 'ሎሚ ሽታ' ቤተክርስቲያን መሄድ ትፈልጋለች፣ መሄድም አለባት:: ሌሊት ሌሊት ከቤት ወጥታ ያን ያህል ዕርቀት (እስጢፋኖስ ድረስ) ብቻዋን መሄድ ያስፈራታል (ቢያንስ እሷ ትላለች):: በዚህ ምክንያት አብሯት የሚሄድ ሰው መኖር አለበት:: ባለቤቷ አቶ ታደሰ 'ታዲያ ምን ይደረጋል አጃቢ ልቅጠርላት' ብሎ--(አጃቢ ብቻ መቅጠር በእሷ ዐይነት ጥጋበኛ ሳይጀመር አልቀረም) ከአባቴ ጋር ይነጋገርና በወር ሰባ ብር እየተከፈለኝ እሁድ እሁድ በጠዋት ቤተክርስቲያን አብሬአት እንድሄድ ተደነገገ[45]:: ቅዳሴ ጨርሰን ዘኬ ተናጭተን ረፋድ ላይ እሷም ወደ ቤቷ እኔም ወደ ቤቴ እንመለሳለን:: አንዳንድ ጊዜ ደ'ሞ ሳምንቱን ሙሉ......(ስለ ቤተክርስቲያን በዐሎች ብዙ አላቅም) ሲመሽ ወይ ሲነጋ አካባቢ ባሰኛት ሰዓት እየጠራችኝ ሳላንገራግር በስርዓት አጅባታለሁ:: ሴት ሴትን የሚያጅበው ለምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም እንጂ:: ከምን ላድናት ነው? ምክንያቷ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም ባለቤቷ መልካም ሰው ስለሆነ ፈቅዶላታል:: እኔ ባሏ ብሆን ኖሮ:

«አጃቢ ትፈልጊያለሽ?»

«አዎ»

«የዕውነት?»

«አዎ»

«ለምን?»

«ወንዶች አላስኬድ አሉኝ»

«ቀላል ነዋ ከአንዱ ጋር ተያይዘሽ ሂጂ:: በርቺ»

ግን ባሏ አቶ ታደሰ አላደረገውም::

በመጀመሪያ ይወዳታል:: ቀጥሎ በእሷ ዓይነት የወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ቤተክርስቲያን ካልተሳለምኩ ብለው የሚሟዘዙ ጥቂቶች ናቸው:: ይኼ ራሱ የሚያባባ ጨዋነት ነው:: እሁድ እሁድ በሌሊት ስንወጣ ከመኝታዬ በመቀስቀሴ እደሰታለሁ:: ቤታችን የኢኮኖሚ ችግር ስላለ ሎሚ ሽታ የምትከፍለኝ ሰባ ብር ያልተጠበቀ ትንንሽ ቀዳዳዎች ትደፍናለች:: ለሁለት ዓመታት ሁለተኛ ደረጃ ፈተና ማለፍ ከብዶኝ በድብርት ስሰቃይ ቆይቼ......የአባቴና የስፈሩ ሽሙጥ ሊገለኝ ደርሶ፣ መሞቴም የተቃረበ መስሎኝ እያለ......በዚህች ዓይነት ቀላል የአጃቢነት ስራ ትንሽ ሳንቲም የማገኝቴ ነገር ደቃቃም ብትሆን የመኖር ሞራሌን አነሳስታዋለች:: እንደገና የእቴሜቴ ሎሚሽታን ደካማነት ላይ በባለጌነቴ ስሰደብ የኖርኩት ልጅት በተሸፋፈነ ሁኔታ ከእኔ የባሱ ስዶች እንደ

45 መልካም ካልሆኑ ጎዳናዎች እንደ ራቅሁ አባቴ እንዲያውቅና እንዲረዳ በማለት 'አድርጊ' ያለኝን ሁሉ ማድረግ ጀምሬአለሁ:: ቢሳሳት እንኳን ቅር አይለኝም:: ብቻ ማድረግ:: ከእኔ እላፊ ፍሥሐ የበለጠ ሌሎችን ሰዎች የመስማት ልምድ እንዳዳብር ረድቶኛል::

ነበሩና እንዳሉ በዚህ አጋጣሚ መረዳቴ እንግዳ በሆነ መልክ ደስ አሰኘኝ:: እሷን የመሰሉ ቂጭበሉዎች እስከማገረር አጣጥለውኝ ስለነበር......('ያቺ? ሁሉ? እይ![46] ሁሉ ፈተናዋን ካለፈች አገር ተበላሽቶአል ማለት ነው፣ ዕድሜ ሰጥቶን ብናይ አራቴም ትወድቃለች' እንዳላሉኝ)

ታዲያ እዚያ ቤተክርስቲያን ግቢ ቆሜ እያየሁ ጎረምሳው አስናቀ ሎሚ ሽታን እየተንፏቀቀ ሲቀርባትና ሲያንሾካሽካላት የተረጋጋ ዓይን ያወጣ ፊቃደኛነቷን አየሁ:: መጋረጃውን ካልገለጡለት ወይም በሩን ካልከፈቱለት ማንም ወንድ ወደ ማንም ቤት ሰተት ብሎ አይገባምና......ወንድ ፊት ካላሳዩት ይፈራልና......(ይኼንንም ከልምዱ እመሰክራለሁ) እመቤቴ አጃቢ የፈለገችው......'ወንዶች አንድ ጊዜ ካዩኝ፣ ካላገኙንሽ ሞተን እንገኛለን! እያሉ ......('ውይ እቴ ደፍሮ ልንካሽ የሚል ሁሉ አለ!?')......እረፍት ስለማይሰጡኝ ነው' ብላ የምትለውን ነገር ማመን ግን ይከብደኛል:: እሷ ደ'ሞ ከባሷ ሌላ የምትፈልገውና የሚያስደስታት እንዳሌለ ሁሉ ከቤተክርስቲያን መልስ አንዳንዴ ለቁርስ ጠረጴዛ ከበን ስንቀመጥ፣ ባሷ አቶ ታደሰ ላይ ትሰራው የነበረው አስገራሚ ቲያትር (ባሷን ስታቆላምጠው ልትበላው የደረሰች ትመስል ነበር:: እየከዳችውም ስታቆላምጠው ወደ ላይ ይለኛል:: ትልቅ ጀብድና እውቀት እንዳጠራቀመች ሁሉ ድራማዋን አጠናቃ እንዳልታዘበት ወደ ጓዳ ከእሱ ታርቀኝና 'ወንዶችን ካላቆላመጥሻቸው ይከፋቸዋል:: ሂሂሂሂሂሂ' ብላኝ እንደ ማቆሸሻት ሁሉ ጎኔን በጨረፍታ ጎሰም አድርጋኝ ትሂዳለች) እንዲህ በማየው ተጨባጭ መረጃ ተናደ::

ጋለሞታነት ነበረብኝ ግን እንደዚህች የነጠረች ቲያትረኛ አልነበርኩም

*ዕድልሽ የዋዛም አይደል*
*ከፉ ፈተና ነው መምሰል*

እለ ገጣሚ::[47] በሬድዮ የሰማሁት ግጥም ነው:: ስለምን ጉዳይ እንደሚገጥም ምንስ መልዕክት እንዳለው ጠቅላላ ባይገባኝም እነኚህን ቁራጭ መስመሮች እስከ ዛሬ አልረሳኋቸውም::

*ዕድልሽ የዋዛም አይደል*......

እህም......*ከፉ ፈተና ነው መምሰል*......

*አያምርም?* ትንሽም ነበርኩበት::

ከዚህ ሁሉ በፊት ግን ይኼ ሆነ (ከዕውቀት በኋላ ዕውቀት እንደሚመጣ ከዕውቀት በፊትም ዕውቀት አለ):......

አንድ ቀን ግቢዬ አጥር ላይ ልብስ እያሰጣሁ (እውስጥ የተዘረጋው ሽቦ ላይ በቂ ቦታ አልነበረም) በዓይን የማውቀው አስናቀ የተባለ አንድ የሰፈራችን ጎረምሳ 'ታዲያስ' ብሎ ቀረበኝና ስለሴትዮዋ ስለእመቤቴ አጫወተኝ:: ማለት

---

46 'እይ!'–ይሄ ከነተጋነነ 'እይይይይይ..!!!' ይሆናል:: ሴቶች ፊታችንን መረር ከስተር አድርገን የምንጠቀምበት፣ የማንወደውን ነገር ማቃለያ ወይም ማጣጣይ ቃል ነው:: ከጀርባው ምንም በትንታኔ የፀደ ምክንያት የለውም:: ቃሉን ከእፌና ከልቦናዬ አጥቤ አውጥቼዋለሁ:: ራሰን መታገል የመሰለ ነገር የለም::

47 ቢራቢሮ(1961) ፀጋዬ ገብረመድህን <u>እሳት ወይ አበባ</u> (አ)

ስለዚችው ስለ ሎሚ ሽታ......አይ ስም እቴ:: እኔም ለልጁ ስለ ሴትዮዋ ባወራ አደጋ የሚያመጣ ስላልመሰለኝ እሁድ እሁድ ሌሊት አብረን ቤተክርስቲያን እንደምንሄድና ከሰው ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛ እንዳልሆነች ነገርኩት:: ብዙ ጊዜ አብረን ስላየን ሴትዮዋን አገናኘው እችል እንደሆነ ሊጠይቀኝ እንደመጣ ሲነግረኝ ደሜ ፈላ::

«ከመቼ ወዲህ ነው ጨዋ የሆንሽው? አላውቅ መሰለሽ» ብሎ አንጓጠጠኝና (ብንሸሽም አይለቁንም:: ብንለፋም አይተውንም:: ፀባያችን ተለውጦ ቢከርምም ድክመት ፍለጋ የረሳነውን ያመጡብናል:: የኛ ሰው አይገርምም? ሰማችሁ ከፋዎች ሆይ! ሰማችሁ ስዶች ሆይ! የሚምራችሁ የለምና ከክፋታችሁ አትመለሱ፣ ከስድነታችሁ ጋብ አትበሉ) በስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት በኩል በቅርብ ሕዝብ ቆጠራ ሲደረግ ሎሚ ሽታ መኖርያ መስመር ሊሰሩ የተመደቡት እሱና አንድ ባልደረባው እንደሆኑ ነግሮኝ ከዚያ ቀጥሎ ያለው ዓላማው ግልጽ ሳይሆንልኝ ተሰነባበትን:: አሁን ታዲያ በየት በኩል ተዋውቋት እንደ ሆነ አላውቅም እዚህ ቤተክርስቲያን መጥቶ እሷ እግር ስር ሲንሾካሾክ አየሁት:: ለእመቤቴ ያንሾካሾከውን ዋና ዋናውን ብሰማም ያልሰማ መሰልኩ:: ምን አገባኝ ብዬ ነው? ምን ያገባኛል! ከቤተክርስቲያን ስንመለስ ስለ አስናቀ እንደማላውቅና በሰው ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ፍላጎት እንደሌለኝ ሁሉ ላሳያት የውሽቴን ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያየኋት ሴትዮ ማን እንደሆነች ልጠይቃት አልኩ:: ቤቷ ገብተን ቁርስ ቆርሼ ወደ ቤቴ ከመሄዴ በፊት:

«እቴሜቴ ሎሚሽታ» አልኳት::

«'እቴሜቴ' ን ጨምረሽ ጥሪኝ» ስለምትል ነው:: የሚገርም አጠራር ነው:: በልቶና ጠጥቶ እናም በዚህች ደባሪ መሬት ላይ ቆሞ ለመሄድ ትንሽ መዋረድና መዋሸት ሳያስፈልግ ይቀራል?

«ምነው?» አለችኝ:: ፍርሃት ፍርሃት አለኝና፣ ሰባ ብር የማትሰራው ነገር አለ?

«አይ ምንም» አልኳት:: ጥያቄዬን በቡካት ደንብ ዋጥኩት:: አውቃለሁ ልጁ ምን እንዳላት:: ያልጠበቅሁትንና የማላውቀውን ነገር ከመቀስቀስ (ዓለ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል) ብዬ ቶሎ ዝም አልኩ::

እሷም: 'ምን ለመናገር አስበሽ ነበር?' ብላ አላፋጠጠችኝም)

## ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ

እቤት ተመልሰን ትንሽ እንጀራ አፈርፍረን ከሰራተኛዬ ወይም ከአጃቢዬ ወይም ከሁሉአገርሽ ጋር ስንበላ ሁኔታዋ አላምር አለኝ:: ያቀናጣታል:: ወገኖች ሆይ ዝቅ ያለ ሰው ሁልጊዜ ዝቅ ያለ ነው:: እኔ ብዙ ጊዜ ብቻዬንም ስለምሆንና እጫዋች ስለሚያስፈልገኝ ገረዴን ቀስ በቀስ ወደ ትንሽ ጓደኛ ለውጬአት አንዳንድ ነገር በተሳሳትኩ ቁጥር ከእኔ የበለጠ እንደምታውቅ ሁሉ (ማትሪክ ሁለቴ የምትወድቀው ብታውቅ ነውን?) ትችቷን እርማቷንና ለመመልከት

የሚቀፍ የሠፈር ግልምጫዋን ትቃጣብኛለች:: የዚህ ተፅዕኖ ልበለው ቀስ በቀስ እየተሰማኝ ነው:: ከጠዋት እስከማታ ቤት ውስጥ የሚያውል ነርቭ ስወለድም የለኝም ነበር:: ከዕድሜዬ በላይ ወፍሬአለሁ:: አንዳንዴ ከብዙ መቀመጥ ወይም መጋደም በኋላ ተነስቼ ስቆም እግሮቼ ይጠዘጥዙኛል:: ይኼ ዓይነት መጠዝጠዝ ብዙ ጊዜ አጥንቶቻቸው ለደከሙ አሮጊቶች ብቻ የተመደበ ምሬት ይመስለኛል::

ባለቤቴ ጠበቃ ስለሆነ ነገር ሲጥልና ሲያነሳ ጠዋት ከቤት የወጣ የሚመለሰው ሲመሽ ነው:: እሱን ራት አብልቼ፣ አልጋ ላይ አስተኝቼ፣ ከእኔም ነገር ጉዳይ ካለው እሷን አደራርሳ፣ ስለፍትሐብሄርና ስለወንጀለኛ መቅጫ እያሰበ ወይም እያለመ ይተኛል:: ጎኑ ተጋድሜ ገና ሳገባው አደርገው እንደነበረ ሁሉ ሆዱን እዳብስለታለሁ፣ ችፍ ያለ ቅንድቡን በአመልካች ጣቴ እካክክለታለሁ፣ በጆልጆላ ውስጥ ሱሪው ስር እጄን አስገብቼ ፀጉር የፈሰሰበት ጭኑን እነካካዋለሁ:: ከደስታ ይልቅ ውስጤ የሚሰማኝ አነጣጥሬ ያለመውደዴ ቁጭት ነው:: ታዲያ እሱ እንዳይሰማኝ አድርጌ ወደ ውጭ እተነፍሳለሁ፤ እተነፋፈሴን ከሰማኝም የፍቅር ስራው ያረካኝ ለመምሰል በወዛም ፀጉር የተሸፈነ ፊቱን አፌን ከፍቼ እስምለታለሁ:: ዕውቀቴ ደካማ ናት:: እምነቱን ተደግፌ ግን እንደ ልጅ እጥ ለዋለሁ:: ሳገባው ወድጄው ነበር:: ውሸት አይደለም:: አሁንም እወደዋለሁ:: ግን አንድ ቀን ከቤቴ ልወጣ ስል ደጃፌ ላይ ይኼን 'አስናቀ' የተባለውን ወጣት አገኘሁት:: ደነገጥኩ ሳየው:: ደነገጥኩ:: በሁለመናዬ::

«እዚህ ቤት ነው የምትኖሪው?» አለ::

«አዎ ምነው?» አልኩ::

«ከስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት ነው የመጣሁት:: ሰምታችሁ እንደሆነ የሕዝብ ቆጠራ እየተደረገ ነው»

«አልሰማንም»

«ለጥቂት ጊዜ ላስቸግርሽ?»

ወደ ግቢው ተመልሼ ገባሁ:: እቤትም ውስጥ የሚመች ቦታ መርጬ አስቀመጥኩት::

ያልጠየቀኝ ዓይነት ጥያቄ አልነበረም:: በሚፈለገው ስርዓት የያዘውን ፎርም ሞልቶ ከጨረሰ በኋላ ሻይ አፈላሁለትና በየቦታው ለስራ ሲዘዋወር ያጋጠመውን እያወራኝ በሳቅ ገደለኝ:: ያን ጊዜ ወደድኩት:: እንደ ጨዋታም አድርጎ እንዲህ አለ:

«አንቺ እዚህ ትኖሪ ነበር እንዴ? እንደ ዓላማ ስንደቅ ከሩቅ የምትታዪ[48] ማን ቢጋርድሽ ነው እስከ ዛሬ የተሰወርሽብን?»

የሚገርም ዓይነት ሕዝብ ቆጠራ ነበር:: በሚገርም ዓይነት መልክም ተቆጠርኩ:: እንደወደደኝ ያወቅሁት እንዲህ ቤቴ ከመጣ ከሦስት ቀን በኋላ ይመስለኛል ፒያሳ ጫማ ልገዛ ስወጣ ከተማ መሃል ስሜን እየጠራ ከኋላዬ እየተከተለኝ እየተከተለኝ ሊደርስብኝ ብሎ ሲሮጥ ሳየው ነው:: የሚያሳዝን ልብ

48 ከተለመደ ዘፈን(ምናልባት ሙሉቀን መለሰ)(አ)

የሚበላ አሯሯጥ ነበር:: ደግሜ ልክ እንደ መጀመሪያው ቀን ልዩ ድንጋጤ ደነገጥኩ:: ባለቤቴ ታደሰን ወይም እሱን የሚያውቀው ሰው ድንገት ቢያየን በሚል እኔ ፊት ፊት እሱ ኋላ ኋላ የማንተዋወቅ መስለን እያወራን (ነገርኩት ጎን ጎኔን እንዳይሄድ) ከፒያሳ እስከ ትልቁ ፖስታ ቤት ድረስ ሄድን:: ያን ያህል ዕርቀት በእግሬ ስጓዝ የመጀመሪያዬ ነበር::

«እንዴት ላግኝሽ? እንዴት ላነጋግርሽ? በፍቅርሽ መከራዬን አየሁ» ሲለኝ፣ ሲፈልገኝ ያሻውን መልዕክት በሰራተኛዬ በሁሉአገርሽ በኩል እንዲያስተላልፍ ነገርኩት::

«ሰራተኛዬን አይተሃታል? ሁልጊዜ እሁድ እሁድ ጠዋት አብራኝ ቤተክርስቲያን ትሄዳለች:: የምትኖረው እኔ ቤት ፊት ለፊት ነው:: ሁሉ አገርሽ ትባላለች:: ብዙ ባሕርዛፍ ያለበት ቤት:: አነጋግራት:: እኔ እነግራታለሁ:: ሁለተኛ አትቅረበኝ:: ባለትዳር እኮ ነኝ:: ረሳህ?»

እንዲህ ስለው ከፋጫው በርዶ አንገቱን እንደ ውሻ ቡችላ ሰበር አድርጎ ፈገግ እያለ እያየ ተወኝ:: በዓይን ከሚያጠኑኝ፣ በትኩረታቸው ሊገሉኝ ወይም ሊበሉኝ ከሚደርሱ ሺህ ወንዶች አንድ ደፋር ሲያጋጥመኝ ግን ደስ አለኝ:: ቁመቴን አድንቀው ከጉዳያቸው ተግ ብለው ስንቶች ያዩኝ ነበር? በቅላቴ፣ በእግሮቼ ቅርፅና በዓይኖቼ ጉላት ተማርከው (ስወጣ ስወጣ እኳኳላቸዋለሁ) ጉዳያቸውን ዘንግተው ዞር ብለው ከላይ እስከ ታች ያዩኝ የለም? ግን በፍርሐት ተሳስረው መቼ አናገሩኝ? በዓይኖቼ ብቀላውጥ ብቀላውጥ ያማርኩትና የፈለገኝ ወጣት ሊያናግረኝ ከመድፈር ይልቅ እንደ ጅል አገጩን ጥሎ አጠገቡ እንደ'ሱ ለተቂያቂያለ ሌላ ጓደኛው 'የማናት ቆንጆ?' ብሎ ሹክ አላለም? አስናቀ ግን እንዲያ አልነበረም::

ታደሰ ባሌን የተገናኘሁት ለቅሶ ቤት ነው:: የሳበኝና እዚህች ምድር ላይ መኖሩን የጠቆመኝ ሲነጋገር ስሰማው ነው:: እጅግ የሚያምር ድምፅ ነበረው:: ዛሬ ለምጄው አልባሌ መሰለኝ እንጂ:: እሱ ሲያወራ ውሎ ሌላ ወንድ ከመሃል ሲተካ አዲስ ገቢው ሴታሴት ይሆናል:: ታደሰ በጥልቅና በቀስታ ሳይንገዳገድ የሚፈስ ወፍራም ድምፅ አለው:: እሱን መስማት በሰፊ ማርቼዲስ እንደ መሳፈር ነው:: ታዲያ ለቅሶ ቤት እንዳየኝ (እኔም እንድታይ ፊት ለፊቱ ሄጄ ተጎለትኩ) ትክ ብሎ አፉን ከፍቶ ሲያጠናኝ ቆየና ሰላምታ ሰጠኝ......ከአምስት ዓመት በፊት:: ቤቴ በአሮጌ ፔጆው ሸኘኝ:: ለስድስት ወር አብረን ወጣንና ለመጋባት ወሰንን:: አያችሁ ሰው ጣዕሙ እንደ ከረሜላ የሚያልቅ አልመሰለኝም:: ሁለት ዓመታት መጠጥኩት:: በትልቅ አፌ አስገብቼ አንገላታሁት:: ትልቅ ከንዴ ላይ አስቀምጬ እኔ ልጅት ወንድነቱን ተፈታተንኩት:: በከፊል ሸክላ በከፊል ጭቃ በሆነች ቤቱ ከዳር እዳር ዘለልኩባት:: አንድ ጠዋት ስነቃ ብዙ ያለፍኳቸው፣ ያልኖርኳቸው መልካም ነገሮች እንዳሉ ሊያሳየኝ ነው መሰለኝ እግዜር አስናቀን አምጥቶ ፊቴ ገተረው:: ገበያ መሃል ጣልያን እድሞ ፒያሳ አሳዶ የተከተለኝ ዕለት ዞር ብዬ ሳየው ጥቁር ረዥም ፊቱ (አንዳንዱ ያልገባው 'ሞጋጋ' የሚለው)፣ ሰማይ የነካ የመሰለው ሎጋ ቁመናው አብረከረከኝ:: የአለባበሱ ጥራት፣ ትላልቅ ዓይኖቹ ውስጥ የሚንቦገቦገው የፈላ ስሜት መረጋጋቴን አበለሻሸው:: በዛው ሳምንት እሁድ ቤተክርስቲያን ስንሄድ ሰራተኛዬን: 'አንድ ወፍ መልዕክት

ከነገረሽ ሳትጨምሪ ሳትቀንሺ ንገሪኝ' አልኳት። ግራ ቢገባትም መታዘዝ ነበረባት። ቀሽም ሰው ደ'ሞ ያልበሰለ አፉ ያፈተልክበታልና......'ስለ ወፉ ለባለቤቴ አትናገሪም' ብዬም ኮስተር አልኩባት።

ታዲያ ባልተቃጠርንበት ቀን ደጀ ሰላም በኩታ ተጠቅሎ(ሁሉአገርሽ ጋ መሄድ ሲገባው) መጥቶ እንዲህ አለኝ፡

«ለመሆኑ ምን ዓይነት ሽቶ ነው የተቀባሽው??»

«ምነው? ኸረ እኔ እቴ......ሽቶ አልወድም» አልኩት፤ «ምን አለኝ አፈ ብስኩቱ?»

«'የሚያምር ጠረን ነው፣ ላብሽ የሎሚ ማይ ነው?'»

ልቤን ደስታ አንተከተካት።

ባሌ ታደሰ እንዲህ አይለኝም። ብሎኝ አያውቅም። ሁሉአገርሽ ይኼን የአስናቀ ምርቃት ትስማ አትስማ እንጃ። እሷ ስለዚህ ዓይነት ነገር ብዙ ታውቃለች። ብትረባም ባትረባም ሳያወድሷት አይተኟት መቼም። ብዙ ወዳጆች እንዳሏትና እንደ ነበሯት በጨዋታ መሃል ነግራኛለች(ዘርዝራ ሳይሆን አለ አይደለ 'ሁሉን ነገር አይቼዋለሁ እባክሽ' ብላ። ከዚህ በላይ ማብራራት ይጠበቅባታል?) እኔም እያየሁ ገምቼአለሁ። እሁድ እሁድ ጠዋት እኔን ቤት ካስገባች በኋላ ተጨማዳ ትወጣና በሚቀጥለው እሁድ ስትመለስ እንደ አዲስ ታጥቦ እንደ ተተኮሰ ካኪ ይሰራታል። እቀናለሁ። ብቀና ምን ያደርጋል? አንዳንዴ የሸረሞጡ የታደሉ ይመስለኛል።

ከአስናቀ ጋር ከዚያ በኋላ በሚስጥር የምንገናኝበት ቦታ እየኼድኩ ሕሊና የሚቆጠቁጥ ጨዋታዬን ጀመርኩ። ብዙ አላስቸገርኩትም። ለምን ብዬ?

ሰራተኛዬ ከአስናቀ ጋር ያንሾካሾክነውን ነገር ለማወቅ ጉጉት አድሮባት አንድ ቀን ያን ሰሞን፡

«ማን ነበር ቤተክርስቲያን መጥቶ ያነጋገረሽ?» ብላኝ ነበር።

«አስናቀ»

«አስናቀን አይመስልም»

«ታዲያ ማነው? ያወቅሽ መስሎኝ? ከአንቺ ጋር አልተነጋገራችሁም?»

«ማን? ምን አነጋገረኝ? እዚህ ስለ መምጣቱ? ምንም አላለኝ። ስለ ሌላ ስለ ሌላ ነገር ነው ያወራኝ»

«አንዳንዱ እኮ ጦር አያቆመውም»

«ምን እቴ ሜቴ?»

«አስናቀ። ካንቺ የተነጋገረ መስሎኛል»

«ኸረ እቴ። እሱ ጉደኛ ነው። አያደርግም አይባልም እና ከአንቺ አውርቶ ጋሼ ታደሰ ጎን ሂዶ ቆመ?»

## ምንም ምንም ምንም አላለኝ

እስናቀ የሚያወራኝ ነገር ሁሉ በሚያምር መልክ ይረብሸኛል:: በግዙፍ ገላው እላዬ ላይ እንደ ጠይም ሰማይ አርፎ ጆሮዬን በጥርሶቹ እየቧጠጠ የሚያማምረውን ነገር ሲለኝ......በትኩሳቱ ሲያነደኝ:: ከታደሰ የበለጠ ሳልወደው አልቀርም:: ካልሆነ ሲጀመር ለምን አስጠጋሁት? ቀድሞ ባለቤቴ ታደሰ ሲያወራኝ ድንገት የተሳሳተ ከመሰለኝ በቸልታና በአክብሮት የማልፈው ሴትዮ እከራከረው ጀምሬአለሁ:: ንቃቴ ጨምሮ ሳይሆን አስናቀ ጋ እንዳልሄድ ባል ሆኖ እዚህ ስለገተረኝ ውስጤ እየተበሳጨ ነው:: ምቀኛ ስለሆነብኝ ነው:: እንደ ገናም በልቤ:

'አላወቅሽ:: ካንተ የበለጠ ስንት ወንድ አለ መሰለህ? ጉራ ትነፋብኛለህ' እለዋለሁ::

በገላ መባለግና በአፍ መባለግ ይገናኛል እንዴ?

ራቁትን ያልለመዱት እንግዳ አልጋ ላይ መውደቅ፣ መሸርሞጥ እንዲህ የሚያሳዝን አንዳንዴም ሰንቅልፍ የሚነሳ ደስታ የሚሰጥ አይመስለኝም ነበር:: አስናቀ ባሌ ቢሆንና ከእሱ ጋር ጠዋትና ማታ አብረን ብንውል በደስታ ፈንድቼ የምሞት፤ በሆዴ ወይም በጀርባዬ በኩል እንደ በሰለ ሙዝ ሸንተረር አውጥቼ የምከፈል ይመስለኛል:: የፍትወቴን ሐጢያት በሁሉ አገርሽ የእያየሁ አላየሁም ከፊል የአቃጣሪነት ድልድይ ላይ፣ በእኔና በአስናቀ ፈጣጣ የድፍረት ባቡር ስሽጋገራት በእርግጥ የሚደበቅ ነገር አለ ማለት አይደለም:: 'ግመል ሰርቆ አጎንብሶ' እንደሚለው ነው ባሌ (የጠበቆች ተረት......ያውም ቆለኛ ከሆኑ):: አስናቀ 'ባልሽን ትተሽ......' 'ታደሰን ባልሽን......'እንኳን አላለኝም:: 'ታደሰን' ነው ያለኝ......'ታደሰን ትተሽ እኔ ልውሰድሽ' ብሎ እርፍ:: ግን በይሉኝታ ቢስነት ልቦቻችን እግር በራስ ሲሆኑ ገና ሰው አልተናገረንም፣ አላወቀብንም ብለን ለመደባበቅ ብንዘል ግብዝነት ይሆናል:: ምንም እንኳን ለሰራተኛዬ ብነግራትም ጠቅላላ በልቤ የቀበርኩትን ሚስጢር ጎርጉሬ አውጥቼ የጆሮዋን ቀዳዳ......ራሴን በሚያጋልጥ አሉባልታ ልሞላው አልፈልግም:: ስለዚህ አንድ እሁድ ጠዋት ጎን ለጎን ተቀምጠን የጠዋት ፀሐይ እየሞቅን ስንተያይ:

«ባለፈው ጊዜ ጠይቀሽኝ ነበር አይደል አስናቀ በጆሮዬ ምን ሹክ እንዳለኝ? እ?»

«ደበቅሽኝ? ወይስ ያለሽ ነገር ነበር?»

«ምንም አላለኝም:: እንደሚወደኝ ነው ያወራልኝ:: የእሱን ዓይኖች ያየሁበት ቀን......»

አባባሌን አልጨረስኩትም:: እሱን ያየሁበት ዕለት 'የተባረከ' ወይስ 'የተረገመ' ይሁን ግልፅ አላደረግሁላትም::

## ትዳሩን ፈቶ ልውሰድሽ አለኝ

የማይደበቅ ነገር ልደብቃት ብጥር ጥቅሙ ምንድነው? ሐሙስ ዕለት አስናቀ መልኬ የማይታወቅበት ቦታ መርጦ (ካለሁበት ሠፈር አለፍ ብሎ ከዐይን

የራቀ ጻገት ላይ) አዲስ ቤት ተከራይቶ እዛ ውስጥ አንዱ ሰፊ ክፍል ያቅበጠበጠኝ ፍትወቴ ጠስ ብሎልኝ አልጋ ላይ እንደተጋደምኩ እሱ በውስጥ ሱሪ ወዲያ ወዲህ እያለ ለምን ቤተክርስቲያን ድረስ መጥቶ እንደዚያ ያናገረውን ምክንያት ስጠይቀው እጁን (የመጻፉ ቀለም ነጭ፣ መጠኑ ደ'ሞ መሰብ የሚያክል) ተደግፎ ልብ በሚያቀልጥ ጎርናና ድምፁ:

«ዕረፍት አጣሁ:: የዚያን ዕለት ጠዋት ስባንን ጎኔ የለሽም:: እጅግ ተበሳጨሁ:: የምሄድበት ጠፋኝ:: በጠዋት ከአልጋዬ ተነስቼ መጣሁና የቁርጡን ነገርኩሽ»

«አሁን ቀስ ብለን ማሰብ አለብን:: የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ነው» አልኩት:: ምን ማለቴ እንደ ሆነ ግን አላውቅም:: መቸኮል ያልነበረብኝ ቀድሞ ሳልገልብለት በፊት ነበር:: ተረቴ አስገረመኝ:: ቸኩዬ ብጨርስም የመተረት መብቴ የተጠበቀ ነው:: ተረቴን የሰማ አይመስለኝም:: ፊቱን ታላላቅ እጆቹ ላይ አስደግፎ የአህያ በመሰሉ ዓይኖቹ አየኝ:: በልቤ እኔም እግዚአቤርዬ ይኼን ታላቅ በአስናቀ ተመስሎ የመጣ ደስታ ፈዕሞ እንዳይከለክለኝ ተማፀንኩት......

«ሰማሽ አንቺ» አልኳት ሰራተኛዬን::

«እ»

«ሚስጢር ልነግርሽ ነው:: እንደ ሌላው ነገር ሁሉ በራስሽ የሚቀር ነው»

«ከራሴ አያልፍም»

«አስናቀ ምን እንዳለኝ ታውቂያለሽ? ተፋቺና እንጋባ»

«ምን?»

«እንጋባ»

«ምን አልሽው?»

«ላስብበት»

«እንዴ! እትዬ ትዳር ውስጥ እኮ ነው ያለሽው:: እንደ ሆቴል ተገብቶ አይወጣ:: በቂ ምክንያት እንኳን ለእቶ ታደሰም ለቤተሰብሽም መስጠት አለባችሁ»

«አስናቀ ራሱን የቻለ ሰው ነው:: እኔም የምፈልገውን የማውቅ ሴት ነኝ:: ብዙ ነገር ሳላይ ነው ትዳር ውስጥ ዘልዬ የገባሁት:: አይመስልሽም? ከታደሰ ጋር ስንት ዓመት እንደወጣን ታውቂያለሽ እንጋባ ከማለቱ በፊት? አንድ ዓመት (ትንሽ ዋሽሁ):: በዚህ ደ'ሞ የቤተሰባችን ሚስጢራዊ ግፊት አለ:: 'በሉ ተጋቡ' አይሉሽም:: እየሽ ከርሞ ካላዋጣ 'የለንበትም' ለማለት፣ ልክ የለመናቸው እንዳለ ሁሉ:: ግን ያደናንቁልሻል:: 'ደስ የሚል ሰው ነው' ይሉሻል:: 'ስክሰስፉል'[49] ነው

49 successful= የሆነለት፣ ሀብት ያለው ወዘተ...(እንግሊዘኛ)(እ)

ይሉኻል:: እኔም ደስ ብሎኝ ነበር:: ገንዘብ ሲቸግረው አላየሁም:: ቆንጆ ቤት አለው:: የምፈልገውን ያደርግልኛል:: ሁሉ ነገር ለትዳር የተቀነባበረ አይመስልም? ግን ዕብደት ይጎለዋል:: በጨለማ መንገድ ዳር መሳም እፈልግ ነበር»

«ምን? አስናቀ ስሞኻል?»

«መሳም ምን አላት? ቤተክርስቲያን ድረስ መጥቶ ባሌ ትይዩ እያዋራኝ ሲቀመጥ ጉብዝና አይደለም? ስንት ወንድ ይፈልገኝ ነበር መሰለሽ:: እሱ ብቻ ነው ደፍሮ 'የስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት ባልደረባ ነኝ' ብሎ የውሸት ፎርም አስሞልቶኝ ከዚያ የሆነውን ታውቂያለሽ:: ድፍረቱ ደስ አይልም?»

«ትልቅ ቁም ነገር አይደለም ይኼ፣ እኔ ይቅር ነው የምለው»

«ለሆነ ነገር ምልክት ነው:: 'አስብበታለሁ' ማለት እኮ ሆነ ማለት አይደለም»

«የሚያሳስብ አይደለም:: እንዲሁ ብትሆኑ ይሻላችኋል:: ይኼ ራሱ አደገኛ ነው»

«ታደሰ ግድ የለውም:: ቢኖረው ኖሮ ይጠረጥር ነበር»

«ለምን ይጠረጥራል? ካመነሽስ? ተይ ተይ የለሁበትም»

ሳቅሁባት:: ሁሉ አገርሽም እኔም ቁንጅናችንን ልጅነታችንን በትክክል ያልተጠቀምንበት ጅሎች ነን:: እኔ ብዙ ፍቅር ሳላገኝበት ራሴን ስቆጥብ፣ እሷ ደ'ሞ ላገኘችው ወዲያና ወዲህ ስትወረውረው፣ እኔ የማያስፈልግ ውድ ነገር ራሴን አድርጌ ስቆጥር፣ እሷ እንደ ርካሽ ነገር ለአላፊ አግዳሚ ስጥታው:: ለእሷ የመዝናናት ነጻነት የሰጣት ለእኔስ ያልሰጠኝ ማነው?

## አይወስድሽም ትዳሩን ፈቶ

(አንድ እሁድ ከሰዓት በኋላ አስናቀ ቤት ሄድኩ:: ከብሎኬት የተሰራ መለስተኛ ቪላ ቤት ውስጥ ነው የሚኖረው:: ቤቱ አሮጌ ቢሆንም ውድ እንደሆነ መገመት አይከብድም:: ሳንኳኳ የከፈተልኝ እሱ ነው:: ያረጀ ሰማያዊ ካናቴራና ያረጀ ሰማያዊ ጂንስ ሱሪ ለብሷል:: ባዶ እግሩን ነው:: እንዲህ ያለ ጫማ እንኳን ቁመቱ እዛ ላይ ነው::

«ታዲያስ ወዳጄ:: እግር እንዴት ጣለሽ?» አለኝ

ቤት ገብተን እንደ ተቀመጥን ያለምንም በዘበዛ:

«ልታገባት ትፈልጋለህ እንዴ?» አልኩት:: ማንን ማለቴ እንደሆነ ገብቶታል::

«አዎ ተግባብተናል»

«ባለ ትዳር ናት»

«ምን ይጠበስ»

«ኸረ ደስ አይልም»

«ለምን? ድንግል እንዳናገባ አዲስ አባ ድንግል መሆኗን ካቆመች ቆየ»

«ፈትሸሃል ሁሉን?»

«ታይተዋል:: ያመለጡ አልተገኙም:: ፋሽን ይመስላል:: ስለዚህ ትራፊ መፈለግ አለብን»

«ጥሩ ልጅ ባስተዋውቅህስ? አብራኝ ያደገች ናት:: ምንም ነገር አታውቅም:: ሳይተላለፉት በፊት:: አብረን ተምረን እኔ ፈተና የመውደቅ ሱስ ሲይዘኝ እሷ አለማያ ኮሌጅ ገብታ ሦስተኛ ዓመት ምናምን ናት:: ቆንጆ ናት:: አንተ ከዚህች ጋር......እውነቴን ነው:: ላንተም ለታደሰም ጥሩ አይደለም:: ሰው ቢሰማ ደስ አይልም:: ካልጠፋ ሴት:: የማስተዋውቅህ ልጅ ከሐረር ለክረምት ትመጣለች ታያታለህ ያኔውኑ ትወዳታለህ:: እመነኝ»

«ከሎሚ ሽታ ልትለያይኝ ነው? ባሏ ከፍሎሻል?»

«ምን ሆንክ? እኔ ላንተ ብቻ ሳይሆን ለማንም የሚጠቅመውን ነው የምነግርህ»

«አንቺ ምን ታገኚያለሽ ከዚህ ምክር?»

«ሰላም»

«በየወሩ ደመወዝ ይከፍልሽ የለ:: ለእሱ ነው?»

«ለማቃጠርና ለመሰለል ሳይሆን ላጅባት ነው:: ሂጂ ያየሁትንና የሰማሁትን ለባሏ ብነግረውስ? እ?»

«እወዳታለሁ» አለኝ አተኩሮ እያየኝ

(ብናገር እንደማልጠቀም ልቤ ያውቃል: ይፋታሉእ!)

«ቢያልፍስ? እኔ 'ወድጄአለሁ' ያልኩበት እልፍ ጊዜ ነበር:: ሳየው አይደለም:: ወንድ ስለውጥ ስለውጥ፣ መለወጥ መለወጥ:: ሌላ ስራ አልነበረኝም ግን......»

«ግን ምን?»

«ግን ብንሞክረውስ? አዎ......ይኸቺን ብትወዳትም ያቺን የበለጠ ልትወዳት ትችል ይሆናል:: ደ'ሞ ሎሚ ሽታ እዚህ ናት፣ ባታገባት ያ ነገር አይቀርብህ ምን አንተ ሂሂሂ......» በአባባሌ አልሳቀም::

ኮስተር ብሎ:

«እናየዋለን»

«ሻይ ልታፈላልኝ አልነበረም?»

«አልነበረም:: ከጠየቅሽ ምን ላድርግ»

«እኔ ደስ ብዬህ አላውቅም?» አልኩት በማሾፍ::

«ቦስሽ[50] ናት ያስደነገጠችኝ:: አሁን እንዴት ነሽ? እዛው ሽመልስ ነው የምትማሪው?»

«መልስልኝ:: ተንኮለኛ ነህ......»

«ቀናሽ? እንዳየኋት እንቅልፍ አልወሰደኝም» አተኩሮ አየኝ......

«ዩንቨርሲቲ ስላልገባሁ ንቀሽኝ ነው? እኛ ወንዶችን እናዝናናለን ወንዶቹ ትተውን ኮሌጅ ይገባሉ......እኛ በዲቃላ ስንወድቅ ኮሌጅ ገብታችሁ ብሩህ ምናምን ትባላላችሁ ሃሃሃ......የማስተዋውቅህን ልጅ ፎቶ አመጣልሃለሁ ከፈለግህ፣ ገና ስታያት ፌንት[51] ታደርጋለህ» ሳቅና ኮስታራነት ደበላልቄ:: እንዳይቀየመኝ::

«ትንሽ እንኳን ከወደድኳት ሉሚን እተውልሻለሁ» አለኝ

«እውነት?»

«እውነት»

«ማልልኝ እስኪ»

«በእያቴ ጋሻና ጦር እምልልሻለሁ»

«ምን?» አልኩ ግራ ገብቶኝ

«በዚህ ጋሻና ጦር» (ግድግዳ ላይ አንድ አሮጌ ጋሻና ሁለት ጣምራ ጦሮች ተያይዘው ተሰቅለው ነበር......እያሾፈ መሰለኝ......ያን አንጋጦ እያየ ቀኝ እጁን ወደ ጣርያው አንስቶ በነዚያ ማለ......)

«በጋሻና በጦር ሲማል አልሰማሁም»

«ምን ጎደለው? እያቴ ይኼን ማይጨው ይዘውት ሄደው ነበር:: ከባድ መሃላ ነው»

«እሺ:: ምን የመሰለች ትኩስ የተማረች ሚስት ታገኛለህ:: ጠባይህን አሳምር ብቻ:: በነገራችን ላይ አሁን እንዳልተገናኘን እንቆጥረዋለን»

ፈገግ ብሎ ራሱን በመስማማት ነቀነቀ::

ያፈላልኝን ሻይ ጠጥቼ ወጣሁ:: እሁድ ሲደርስ የሉሚ ሽታን ዕጣ ማውረድ ፈለግሁ:: በእርግጥ ለሴትዮዋም ይሁን ለልጁ ልዩ ፍቅር የለኝም:: የት አውቃቸውና:: አንዱ የሰፈሬ ልጅ ነው:: ወይም ነበር:: አንደኛዋ በሳምንት አንዴ ወይም ሁለቴ ወይም ሦስቴ የማገኛት ፊቷን ቀን በቀን ማሳየት የምትፈራ ግን ለመሽራሞጥ ጅብና ዓይን ሳያስደነግጣት ከጎረምሳ ጋር የትጻሯን ትራስ የምትጋራ ናት:: ታደሰንም ቢሆን አላውቀውም:: ምናልባት ከቤተክርስቲያን ዘግይተን ስንመጣ ፊቱን ሲታጠብ ውጭ ካላገኘሁት በስተቀር ሳይቀጥረኝ ቀድሞ በመንገድ እንደማያውቀኝ (ጎረቤቱና የሰፈሩ ሰው እንዳልሆንኩ ሁሉ) አፍጥ

---

50 boss= አለቃ(እንግሊዘኛ)(አ)

51 faint= ትማረካለህ/ስመመን ትገባለህ ለማለት(እንግሊዘኛ)(አ)

ጦብኝ ያልፍ የነበረ ሰው ነው:: ለምሳሌ ይኸቺ ሴት ትዳሯን ትታ አስናቀን ብታገባ ስባ ብሬ አፈርድሜ በላች ማለት አይደለም? እንኳን በእኔ ትምህርት ለኮሌጆችም ስራ ማግኘት ከብዶአል:: ታዲያ ጥጋበኞች ባሳከካቸው ቁጥር ዕድሌ የሚበላሻሸው ለምንድነው? ታዲያ እሁድ ሌሊት ከሉሚ ሽታ ጋር ቅዝቃዜን በጋቢያችን ከንብንብ እየተዋጋን፣ እየተሳሳቅን ወደ ቤተክርስቲያን ስንጓዝ:

«በቅርብ ተገናኛታችሁ ነበር ከአስናቀ ጋር?» አልኳት

«አዎ:: ምን እንዳለኝ ታውቂያለሽ? ልውሰድሽ ብሎ አልነበረም? ምን አለኝ መሰለሽ አሁን 'ላስብበት' 'እናስብበት'»

«መጀመሪያውኑ ወንድ ማመን:: መሃላቸውን እኮ ጣል ጣል ነው የሚያደርጓት:: ማፈር የሚሉትን አያውቁም» አልኩ::

«እንደ እሱ እንኳን ሳይሆን በወር ሁሉን እናዘገጃጃለን:: እስከዚያ ድረስ እናስብበት ነው ያለኝ»

«እንዲህ ነዋ የሚጀምሩሽ:: እኔ አውቅልሽ የለ:: ሲርቁሽ ሲፈልጉ ብዙ ምክንያት ይሰጡሻል:: ዘመዶቻቸውን የውሸት የሚገሉ ሁሉ አሉ:: በድንገት ባለትዳር የሚሆኑ አሉ:: በድንገት ልጅ የሚወልዱ አሉ:: በድንገት የመኖሪያ አድራሻቸው ማርስ ይሆናል:: ብቻ ምን አለፋሽ»

«ስለምወደው አምነዋለሁ» አለች ኮስተር ብላ::

በልቤ ሃምሳ ከሃምሳ ነሽ አልኩ:: አስናቀ ፉት ያደረገው መሃላ ትዝ አለኝ:: ልንገራት አልንገራት እያልኩ ሳመነታ ባለቤቷ ታደሰ ከኋላ ደረሰብን)

## ግላ ግላ የበጥባጭ ግላ

(መሃላውን አላመንኩትም:: አለማያ ማለት ምን እንደሆነ አላውቅም ወይስ 'ዓለም'–'ማያ' ነበር የሚባለው? ተስፋ የጣልኩባት ልጅ በድሬ ልጆች ስትበወዝ ኖራ አዲስ አባ ከች አትል(ደ'ሞ 'የድሬ ልጆች ደስ ሲሉ' ትለኛለች):: እንደ ሴት ውሻ አድርጓት:: ኡላ ሆና:: ከአስናቀ ጋር እንዳስተዋወቅኋት ላይና ታች አይታው፣ አጥንታው፣ መዝናው......እኔን ያመንኩባትን ጓደኛዋን እንኳን አላፈረችም......እተቀመጠችበት አቁነጠነጣት:: ዕውነትም የእርሻ ትምህርት ነው ያጠናቀቀችው:: በመጣች በሳምንቱ የሚያመላልሷት ሦስት ሰዎች አየሁ:: ቢሆንም ታዲያ አስናቀ ጠቅላላ መሃላውን ረሳና በአዲሷ ልጅ አንጓጠጠኝ:: ምን ልመልስለት? ምን ልበለው? 'ሕዝብ ጠይቅ' አልኩት:: 'የማውቀው እንዲህ አልነበረም፣ ሕዝብ ሕዝብ ጠይቅ' አልኩት:: 'የአለማያ ውሃ ነው' እያለ ሳቀብኝ:: እስከዛሬ ድረስ የልጅቷ ነገር ይገርመኛል:: በእኔ በራሴ ኑሮ ተስፋ ቆርጬ ምን እንደምታደርግልኝ ሳላውቅም ግን በእሷ መሻሻልና ማደግ ተስፋ አደርግ ነበር:: አንድ ቀን የተበደረችውን ይሁን የገዛችውን (የቱ እንደሆነ አልጠየቅኋትም) መኪና አቆመችልኝና ወደ ከተማው መሃል ሊፍት ሰጥታኝ ስትወስደኝ መመሪያ ፍልስፍናዋን ነገረችኝ:: ጋቢና ጉብታዋ ላይ ተቀምጣ (ቁመቷ መኪናው መሪ

አልደርስ ስላላት ቂጥዋ ስር ትራስ አስቀምጣ ነበር)፡

«ሴት ነኝ አየሽ፡፡ በትምህርት ነፃ አልወጣም፡፡ እዚህች አገር በትምህርት ነፃ አይወጣም፡፡ በትምህርት ብቻ ነፃ የወጣ የለም፡፡ ሕይወት አሁን ነው፡፡ በልጅነት ነው ጨዋታ፡፡ ሴት ሆነሽ ሁለት ነገር፣ ዋና ዋና ነገር ያስፈልግሻል፡፡ ቢቻል ሦስት፡፡ ወሲብ መስጠት፣ ቆንጅና፣ ትምህርት፡፡ በአጭሩ ሽርሙጣ፣ ቆንጆና ምሁር መሆን፡፡ አለበለዚያ የትም አትደርሺም፡፡ ሽርሜነትን ጀማምረሽ እቁመሽዋል፣ ምሁር አይደለሽም፣ ቆንጅናሽ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይጠፋል፡፡ ይጎልሻል፡፡ አንዱን ብቻ ከሆንሽ ይጎልሻል፡፡ ወንዶች ወይም ገገርዎችሽ እንድትሆኚ የሚፈልጉትን መሆን አለብሽ፡፡ ሴት ለማን ተሰራች? ለወንድ፡፡ ቆንጆ.....ሽርሙጣ......ምሁር፡፡ ሦስቱን በአንዴ አጠቃለሽ መያዝ፡፡ እንደ እኔ መኪና መንዳት ትፈልጊያለሽ? ነጠላ ተከናንበሽ ከሡፌር ሉዘሮች[52] ጋር ስትጻሪ ልታረጂ ነው? ነቃ በይ፡፡ ቆንጆ ነሽ፡፡ ሽርሙጣ ነሽ፡፡ በቀላሉ ካናሳ ፖለቲከኛ ጋር አገናኝሻለሁ......ከፈለግሽ፡፡ ይኼ ሁሉ የምታይው ብዙው የማይረባ ሰው ነው፡፡ ይሉኝታ አይያዝሽ፡፡ ኢትዮጵያ ሺት[53] ነገር ሆናለች፡፡ ትጻር ይፈርሳል በየቦታው......እንደ እኔ አይነቶች 'አፍርሱ' የተባልነውን እናፈርሳለን፡፡ ሻል ያለ ፈልጊ......'ጎጆ መውጣት' ምናምን ሲሉ ቃሉ ራሱ አያስቅም? እ? ሂሂሂ 'ቪላ መውጣት' 'መኪና መውጣት' አይሉትም እንዴ?......ሂሂሂሂ......የምትኖሪው አንድ ጊዜ ነው......አስናቀ ምንድነው? የሆነ ባርያ ነገር (አውጥታዋለች እኮ) ወንድ ላሳይሽ? ያለው? የሚያበሉ የሚያጠጡ፣ የሚተኙ፣ የሚያለብሱ፡፡ ማሳደር የሚችሉ፡፡ መኪናቸውን የሚያውሱ፡፡ ሳይቆጥቡ የሚያሰክሩ፡፡ ከፈረንጅ እስከ ተቃጠለ አበሻ አሳይሻለሁ፡፡ የእኔን ልብስ ተዋሺና አንድ ቀን እንውጣ ትምህርት ቤት ደርሶ አለማያ ከመሄዴ በፊት......እያይገሽ......»

'በይ እግዜር ይርዳሽ እቴ' አልኳት በልቤ፡፡ እግዜር የማይረዳው ዓይነት ሰው የለ)

## ከቤቴ በላይ ቁራ ሰፍሮ

እንቅልፍ አጣሁ፡፡ በጠዋት ተነስቼ ምግቤን ሰራርቼ አስናቀ ቤት እሄዳለሁ፡፡ ልክፍቱ እንደሁ አለቀቀኝ፣ መሸ እንግዲህ እምባ ልውጣ[54] አለ ሰውዬው፡፡ ይኼ ታደሰ ማታ ማታ ሳንብብልሽ እያለ ጆሮዬ ላይ ከሚወረውርብኝ ስራ እጦች ከቸከቸኩት ነገር የማስታውሰው ነው፡፡ እተንጣለለ መኝታ ቤቱ ልብሴን አውልቄ እጠብቀዋለሁ፡፡ ጊዜ የለም፡፡ የእሱ ቤት ከሠፈረበት ኮረብታ ወይም ዳገት ላይ ሆኜ የራሴኑ ቤት ማየት እችል ነበር፡፡ የአስናቀን ካፖርት እለብስና ቤቱ በረንዳ ላይ ወጥቼ የባሌ አሮጌ ፔጆው ተንኳታ ግቢያችን ስትገባ አያለሁ፡፡ የራሴን ልብስ ቶሎ ለባብሼ በፍጥነት ቁልቁለቱን እወርዳለሁ፡፡

ታደሰ ልብሱን አወላልቆ ፒጃማ ለብሶ፣ ጋቢ ደርቦ ሳሎን ምግብ ቤት ፊቱን እንደ ተገረመ ሁሉ እጆቹ ላይ አስደግፎ አገኘዋለሁ፡፡

---

52 ያልሆነላቸው( በአባባልዋ ገንዘብ የሌላቸው)(አ)

53 shit= ዐይነ ምድር(እንግሊዘኛ)(አ)

54 መሸ ደሞ አምባ ልውጣ (1951) ፀጋዬ ገብረ መድሕን እሳት ወይ አበባ (አ)

«የት ነበርሽ?» ይለኛል::

«ሁሉአገርሽ ጋ» እለዋለሁ

«እህም:: ጓደኛ ሆናችሁ?»

«አዎ:: ጥሩ ልጅ ናት እኮ» እለዋለሁ

«እም» ይላል

ጅል አይደለም?

ተንደፋድፌ የበሰለ ያልበሰለ አበላዋለሁ:: የሚችለውን በልቶ ይተኛል:: በዚህ እበሽቃለሁ:: ለፍቼ በሰራሁትና በቸልታ በሰራሁት ምግብ መሃል ምንም ልዩነት አለማየቱ:: አንዳንድ ጊዜ የቴሌቭዥን ዜና እያየ እተቀመጠበት ያናውዛል:: እቀሰቅሰዋለሁ:: እየተንገዳገደ ሄዶ ይተኛል:: አንዳንድ ጊዜ አጠገቡ እንዳልሆን የፈለገ፣ የደከመና በማላውቀው ነገር ትዕግስቱ ያለቀ ሰው ይመስላል:: በሌሊቱ ፀጥታ እንቅልፍ አጥቼ ስገላበጥ ከአስናቀ ጋር የምሰራው ብልግና ዝርዝሩ እየታወሰኝ ይቆጨኛል:: ሲነጋ ግን ታደሰን ቁርሱን ዕንቁላል ፍርፍር ወይም የበግ ጥብስ በዳቦ አብልቼ ስራው እሰደውና፣ ራሴን አሰማምሬ፣ እንዳልታወቅም በከንብንቤ ተጋርጄ ወደ አስናቀ ቤት እሄዳለሁ::

ታዲያ አንድ ቀን:

«መረረኝ አስናቀ:: አንደኛውኑ ጠቅልዬ ልግባ» አልኩት

«ታዲያ ምን አለበት:: አንቺ ነሽ የምትወስኚው» አለኝ

የኔ መለሎ፣ የኔ ቁራ፣ የኔ ወንዳ ወንድ::

የዝግባዎች ዝግባ::

○

(ጉድ ፈላ አልኩ:: መጀመሪያ 'ሁሉ አገርሽ ጋ እየኼድኩ ነው' እያለች ስትዋሽ ቆይታ ከዚያ አንደኛውኑ አስናቀ ቤት ጠቅልላ ገባች:: ጠዋት ከቤተክርስቲያን ስንመለስ ነው ውሳኔዋን የነገረችኝ::

«እንዴ ምን መሆንሽ ነው? እንዴ?» ብላት::

«አይ አንቺ ደ'ሞ» አለችኝ::

«ምን ማለት ነው አንቺ ደ'ሞ?» ስላት

«አንቺ ደ'ሞ»

«ትዳር እኮ ጠላ ቤት አይደለም» ስላት

«ተደብሬ እስከመቼ?»

«ደ'ሞ እዚሁ ሠፈርሽ? ራቅ ቢል እንኳን»

«አይ አንቺ ደ'ሞ»

«ነገርሽው?»

«አይ አንቺ ደ'ሞ»

«እንዴ አሁን እኔ ምን ላድርግ?»

«አይ አንቺ ደ'ሞ ሌላ ስራ መፈለግ ነዋ»

«ስራ ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን እሱ ቢጠይቀኝ ምን እላለሁ? ደ'ሞስ ስራው መሬት ላይ እንደ ድንጋይ ('ወይ እንደ አንቺ ልበላት?' እያልኩ እያሰብኩ) ወድቆ አይገኝ:: ከዬት አገኛለሁ?»

«አይ አንቺ ደ'ሞ መፈለግ ነዋ:: ይጠፋል?»

ባሏ ግን አሳዘነኝ::

«ደውለሽ እንኳን ባይሆን ንገሪው» አልኳት

ፈርታለች ግን......

«ምን?»

«እብደት ነው»

«በይ አንቺ ደ'ሞ ፍቅር አላውቅም ነው?» ብላኝ ቁጭ::

ለሁሉ ጊዜ ነበረው::

ዛሬም *ለሁሉ ጊዜ አለው*::

«ለሁሉም ጊዜ አለው» አልኳት

«አይ አንቺ ደ'ሞ» ብላ በሳቅ ፈረሰች)

## የለችም ብሎ ሄዶ በር

(የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ፀሐይ ልትጠልቅ አካባቢ ታጥቦ የደረቀ የራሴን ልብስ ሰብስቤ ቤቴ ፊት ለፊት ሳጥፍ እያለሁ የሎሚሽታ ባል ታደሰ አለሁበት ድረስ ሰተት ብሎ መጣ:: የማውቀውን ስለማውቅ ተደነጋገረኝ::

«ምነው ጋ......ጋሼ ታደሰ ምነው?» አልኩት

«ሎሚ እዚህ የለችም እንዴ?»

«እእእ እዚህ የለችም»

«ሎሚ ሽታ እንደ ነገረችኝ ብዙ ጊዜ እዚህ ናት:: አይደለም እንዴ?»

ነገር ማግተልተል ምን ይሰራል? ቁርጡን ይወቅ አልኩትና:

«ኸረ እዚህ አትመጣም:: መጥታ አታውቅም» አልኩት ተበሳጭቼም::

ደነገጠ:: ከዚያ ረጋ ብሎ:

«ራቴን የሰራች አይመስለኝም:: ሆቴል አልወድም:: ጓዳውን ስለምታውቂ አንቺ......እከፍልሻለሁ......ትንሽ ሽሮ ቢጤ ስሪልኝ»

በማዘን አየሁት:: በማርያም አሳዘነኝ:: አካሄዱ ውስጥ ሁሉ መሸነፍ ነበረበት:: በአንድ ጊዜ፣ በአንድ ቀን ጎበጥ አለ:: ለሁለት የታጠፈ መሰለ:: ስራዬን ጨርሼ ቤቱ ሔጄ......ባይከፍለኝም......እንዴ ብቸገርለት አልጎዳም በሚል ራቱን ሰራሁለት:: ተቀምጠን አብረን ስንበላ:

«ብዙ ቦታ ፈለኳት:: ዘመዶቿ ጋ ሁሉ ደወልኩ:: የትም የለችም:: ግን የምልሽ የሆነ ሚስጥር አላት የምታውቂው? ጥሩ ሽሮ ትሰሪያለሽ......ሽሮ ጥሩ ነው:: ብዙ ፕሮቲን አለው:: አትወፍሪም......የምታውቂው አለ? እወዳታለሁ:: ግን እንዲህ እንደ ምታደርግ አላውቅም ነበር:: የምወደውን አልጠረጥርም»

የማውቀውን ሁሉ መናገር አልፈለግሁም:: ጣጣውን እንዳላበዛበት ነበር::

ነገሩ የተለወጠው መጥፋቷን ለፖሊስ ላስታውቅ ብሎ ከተቀመጠበት ሲነሳ ነው:: በውሃ የረጠበ እጁን በጨርቅ ጠራርጎ::

ያኔ:

«ጋሼ ታደሰ ሌላ ሰው ጋ ሄዳለች» አልኩት

«ምን ማለትሽ ነው?»

«ሌላ ወንድ ጋ»

ከቆመበት ቁጭ አለና:

«ዕውነትሽን ነው?» አለ

«አዎ:: እኔ ጋ መጣሁ ትልህ የነበረው ሁሉ ሌላ ወንድ ጋ እየኼደች ነበር»

«አውቀዋለሁ?»

«አይመስለኝም»

«እዚህ ሠፈር ነው?»

«አዎ:: ሩቅስ አይደለም:: አለፍ ብሎ እዚያ ዳገት ላይ ነው»

በፀጥታ ጠረጴዛውን ሲቆረቁር ቆየና:

«ቤቱ ልሂድ ወይስ ስልክ ልደውልለት?»

«ደውልለት»

«ስልክ ቁጥሩ አለሽ?»

ደነገጥኩ::

«አውቃለሁ አንቺ በጉዳዩ እንደ ሌለሽበት:: አድርጊ ያለችሽን ነገር ታደርጊያለሽ:: እንጀራ ነው:: በልተሽ ማደር የለብሽም? መባለግ ከፈለገች አንቺ

ሊታስቆሚያት አትቺይም:: አይደለም? በስራዬ የዚህ ዓይነት የቤተሰብ ግጭቶች ብዙ ጊዜ ያጋጥሙኛል»

በእፍረት ልሞት::

ትልቅ ሰው ነው ታደሰ::

ትከሻዬን መታ መታ አድርጎ አፅናናኝ::

«ላምጣልህ ቁጥሩን» አልኩና ወደ ቤቴ ሄድኩ)

❍

መምሸት እንደጀመረ አስናቀ ቤት በረንዳ ላይ ሆኜ ታደሰ በፔጆው እየተሳበ ቤቱ ሲገባ እየሁት:: አስናቀ ጎኔ መጥቶ ተቀምጦ ወደ ታች ያያል:: የቀኝ እጁ መዳፍ በውስጥ ልብሴ ስር ጡቴ ላይ እንደ ሙቅ ጎጆ ያርፋል:: ከተከፈተ አፌ የሚወጣው ማንንም የማረከ ሞዛርት ነው:: ታደሰ እቤቱ ገብቶ ምን እንደሚያደርግ በሃሳቤ አወጣለሁ አወርዳለሁ:: ማድቤቴ፣ ያቺ የብረትድስት፣ ጠዋት እሱ ፊቱን ሲታጠብ የምጭራት የክብሪት ሳጥን ድምፅ:: ሳላቋርጥ የምተኛባት ሶፋ:: የመኝታ ቤቴ ትልቅ መስታወት:: አስናቀ አንገቴን ይልሳል:: በጆሮዬ የወንድ ቀረርቶውን ይሰዳል:: ውስጤ የሚፋጅ ሐምሌ ነው:: ምላሱ ቅባት የነካ መቀነት ነው ታጥቄው የማድር:: እንደ ሚወደኝ ይነግረኛል:: የማንሾካሾኩ ግለት ሲገለኝ ነው:: ሁለመናዬ ይከፈታል:: ጠበቃው ባሌ ደንገዝገዝ ባለው ምሽት ያቺ ልጅ ቤት ሲሄድ አየዋለሁ:: ተንከራፎአል:: የደከመው ይመስላል:: የምንኖረው እንዴ ነው:: ነገ ሞት ይመጣ ይሆናል:: የሚሞትበትን የሚያውቅ አለ? የለም:: በጭኖቼ መሃል ግለቴን የሚቀናቀን ቅዝቃዜ ይፈሳል......የአስናቀ አውራጣትና አመልካች ጣት ጡቴን ይቆነጥጣሉ:: በቦዙ ዓይኖቼ (የቦዙ ይመስለኛል) ወደ ቤቴ ሂጄ ተመለስኩ:: ወደ አስናቀም መጥቼ ወደ ቤቴም ሄድኩ:: ተመላለስኩ:: ትዝታና አስናቀ እየነዱኝ:: አስናቀ እየነዳኝ::

......ከዚያ አየኋት ሁሉአገርሽ ወደ ቤቴ ስትሄድ:: እስኪ ለምን ይሆን? አልኩ:: ጨለመ:: መንደሬ ጨለመ:: ትዝታዬንም በረንዳው ላይ ጥዬው የእንጠጠ ትንፋሽ እንደ ወረቀት ገልጠትና ገልቦት እንዲሄድ:: ለአስናቀ እንስሳ ነኝ:: ግማሽ ገላዬ አልጋ ላይ፣ ግማሹ ሜዳ ላይ ሆነብኝ:: ውስጤ ለመጀመሪያ ለሁለት የተከፈለ መሰለኝ:: የማውቀው ያረፍኩበት:: የማላውቀው የተንሳፈፍኩበት:: አስናቀ ደግፎ ቢይዘኝም መረጋጋት ለእኔ አልነበረችም:: መረጋጋት ታደሰ ቤት ቀርታለች:: መረጋጋት እዚያ ናት:: አስናቀ ረብሻ ነው:: ፍስሐ ከላዬ እንደ ሲሚንቶ ፋብሪካ ጢስ የሚነሳ ይመስለኛል......ተንኜ የማልቅ ይመስለኛል:: አስናቀ እንዳይለቀኝ ሆኖ ተጣብቆብኛል......በአልጋው ባሕር ላይ ደረቴ ትራስ እየመታ እግሮቼ የግድግዳ ገደል እየረገጡ......በግማሽ የተጠጣው ማስቲካ ኮኛክ በእጄ መትቼው ሲሚንቶ ወለል ላይ ይሰበራል......ያቺ ልጅ......

ያቺ ሁሉ አገርሽ እኔ ባሌለሁበት በዚህ ደንገዝጋዛ ሰዓት ምን ልታደርግ ቤቴ ትሄዳለች?

## እኔን ያብረኝ ያክንፈኝ

(ታደሰ የነበረበት ሁኔታ አሳዝኖኝ ስራ ከመሄዱ በፊት በጠዋት ቤቱ ሔጄ ሰራተኛ በእርግጥ ይፈልግ እንደሆነ ምግቡን እየተመላለስኩ ልሰራለት፣ ቤቱን ላፀዳለት እንደምችልና ልብሶቹንም ማጠብ ቅር እንደማይለኝ ነገርኩት። ይኼን ውሳኔ ከማድረጌ በፊት ግን ከሚስቱ ጋር የነበረኝ ግኑኝነት በሃሳቤ ተመልሶ እየመጣ በቀጥታም ባይሆን አለ አይደለ ባብሮ አሲያሪነቴ የሚያስጠይቀኝ መስሎኝ አሳስቦኝ ነበር። በመፈፀም ላይ ስለነበረው ነገር ለእሱ አለመንገሬ ትንሽ የወንጀለኛነት ስሜት አሳድሮብኝ እረፍት ነስቶኝ ትንሽ ቆዘምኩ። እየቆየ ግን ሳወጣ ሳወርድ......

'ምን አገባኝ እኔ? አላቃጠርኩ፣ ገፋፍቼ አልወሰድኳት። እሷ ቅር ያላላት እኔ ምስኪንቷ ለምን ልቤ በድብርት ይቆስላል? አንዲት ደሃ ነኝ እንጀራዬ ወዳለበትና እድሌ ወደ መራኝ የማልሄድበት ምክንያት ለምንድነው? 'ወደድኩህ' ብላ በሕግ ያገባችው ባለቤቱ ትታው ስትሄድ እኔ በእሷ ምትክ የምተከዘው ለምንድነው? ሊፈፀም የተቀናበረው ጉዳይ ስህተትም ይሁን ዕውነት ነገር ከእኔ ፍላጎት ውጭ መፈፀሙ ላይቀር ምን አንቀጠቀጠኝ? የሚሆነው ነገር እንዳይሆን የሚመጣውም እንዳይመጣ ሊያደርግ የሚችል ምን ሃይል አለኝና ነው?' አልኩና ቤቱ ሄድኩ። አላማዬን ስነግረው ታደሰ አሰብ አደረገና:

«ሎሚን ብታገኝያት ምን ትያታለሽ?» አለኝ ኮስተር ብሎ። ልዋሸው አልፈለግሁም። ጠቅላላ ምድረ-ሴትን እንዲረግምና ተስፋ እንዲቆርጥ ወይም ለመቁረጥ እንዲቀለው ማድረግ አልፈለግሁም። ወይም ቢያንስ እንዲታዘበኝ።

«ምን እንድላት ትፈልጋለህ?» አልኩት።

«'ይወድሽ ነበር' ብቻ በያት»

«ቀላል ነው። ደወልክላት ግን?»

«በኋላ ሳስበው አያስፈልግም። ምን ያደርግልኛል»

«ለምንድነው 'ይወድሽ ነበር' የምላት?»

«ትቀናለች። እና የሚያስቀናት ነገር ንገሪያት። ሴት ትችልበታለች ስታወራው። ታውቂያለሽ ምን ማለቴ እንደሆነ»

«በቃ?»

«ምግብ እንደምትሰሪልኝ ንገሪያት»

ትክ ብዬ አየሁት።

«እሺ»

«ደመወዝሽ ይጨመራል፣ ልብሴንም ታጥቢያለሽ»

ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ መደርደሪያው ሄደና መፅሐፍ አነሳ:: ትንሽ ከመዳፍ ከፍ ያለች መፅሐፍ:: በቀስታ አገለባበጣትና:

«ይችቺን መፅሐፍ አነብላት ነበር:: ብዙ ጊዜ ማታ ማታ:: የምትሰማኝና የሚገባት ይመስለኝ ነበር:: አይገርምም?» አለ ዞር ብሎ:: ምኑ እንደ ሚገርም አልገባኝም::

ግን አሳዘነኝ::

አቅፎ ባባብለው መልካም ነበር:: ከጉብጠቱ የተቃና አይመስልም:: መፅሐፏን ከቆመበት ወደ አጋጠመው ቦታ ወርውሮ ወደ ውጭ ወጣ:: መኪናው ውስጥ እንደገባ አንቀልቅሎ አስነስቶ እያንቀለቀለ ይዟት ሄደ:: በረረ ልበለው:: ከነፈ እንጂ:: 'ተስፋ የሚሰጥህ ነገር ታች ሠፈር ተዘርግቶ ይጠብቅሃል' የተባለ ይመስላል:: ብነግረው ደስ ይለኝ ነበር:: 'ቀላል ነገር ነው ታደሰ:: ቀላል ነገር ነው:: ታደሰ ከዚህ የመረረ አለ:: አዎ ይችቺ ሐሞት ብትሆንም የባሰ አለ:: የሚያበር የሚያከንፍ ነገር የለውም:: የባሰ መራራ አለ መረጋጋትህን አትልቀቅ' ልለው እፈልጋለሁ:: በመኪናው የጀርባ የመስታወት መስኮት የአንገቱን አደፋፍ አየሁ:: አሳዛነኝ......'እኔን' አልኩ:: እኔን:: እንደ እሱ አሳፋሪ በሆነ መልክ ባይሆንም ጥቂት ጊዜያት የወደድኳቸው ወይም የለመድኳቸው ወንዶች ከድተውኛል:: ግን አልታወኩም:: አንድ ሁለት ቀናት ግን የቆሻሻነት ስሜት ተሰማኝ:: በኋላ በኋላ ራሴው እያደረግሁት እየተደጋገመ ወደ ጨዋታና ወደ ተለመደ ነገር ተለወጠ እንጂ:: እንዲህ ግን አልጎበጥኩም:: ወደ ቤት ውስጥ ተመልሼ ገባሁና የሎሚ ሽታና የታደሰን ቤት ከላይ እስከ ታች ገለባብጬ አጠናሁት:: የገባኝንንና የማውቀውን ነገር ሳዘጋጅ ከመሃል የወረወራትን የግጥም መፅሐፍ ሶፋና ጠረጴዛ መሃል ወድቃ አገኘኋት:: ጠንካራ ነጭ ልባስ ያላት መፅሐፍ ናት:: ልባሷ ላይ 'እሳት ወይ አበባ' የሚል ተፅፎአል:: በግራ በኩል በስተላይ የሻማ ስዕል በቀኝ በኩል በግርጌ ደ'ሞ የአበባ ስዕሎች አሉ:: ገላለጥኩና አየኋት::

ጋሼ ታደሰ ለሎሚ ሽታ ያደርግ እንደነበረው 'አንብብልኝ' ብለው እሺ ብሎ ያነብልኛል?)

○

ከላይ አያለሁ:: በምሽት ሞተሩን አስነስቶ ሲከንፍ:: ሦስተኛ ቀኑ ነው:: እያስጮኸ ሞተር ሲያስነሳ:: ለካስ የእኔ ሱስ ነበረበት:: ደስ ይላል:: የወደደን ራቅ አድርጎ ወደ ሌላ ወደ ወደደ መሸጋገር:: እንዴት ነው ብልግና አይሆንም:: ባል መለወጥ ይባላል:: ለአፍታ እኔ ወደ ነበርኩበት ቀና ብሎ ያየ መሰለኝ:: ያቺ ቀልቃላ ልጅ የት እንዳለሁ ነግራው ይሆናል:: ደስ የሚሉ ዓይኖች ነበሩት:: ታደሰ መልካም ዓይኖች ነበሩት:: ልንተኛ ወይ ሊተኛ ሲል ሶፋው ዙርያ እየተሽከረከረ ስራ ፈቶች የተበተቡትን ግጥም የሚባል ነገር ያነብልኝ ነበር:: የሚያስፈራ:: ገላልጦ እያሳየ የሚያስፈራ፡ ሴት ሳይሆኑ የሴትን ልብ እናውቃለን የሚሉ ገጣሚዎች:: አፍቃሪ መስዬ አሰቃይቼዋለሁ:: ግን ደ'ሞ እኔ እንደ አንድ ግለሰብ የፈለግሁትን መምረጥ የመቻል መብት እንዳለኝ መዘንጋት የለበትም::

ምን አንቀለቀለው ግን? ቢጋጭ ከሆነ ግንብ ጋር? ወይም አህያ ገጭቶ እንደ አህያ ቢሞትስ? ምን ሆንኩ ነው? መጀመሪያ አጠገቡ እያለሁ ወንድ መሆን ነበር:: በሚያስፈልግበት ጊዜ ወንድ አይሆኑም:: በእሷ ምክንያት ሞተ ለማባል ነው? ጤነኛውን ሰውዬ አሳበደችው እንዲባልለት ነው? በእኔ ላይ ሊያስፈርድ? እሷ እንዲህ አድርጋው እንዲህ ሆነ ሊያስኝ? የጠበቃ ተንኮል:: ወይስ ገና ለገና ከዚህ ጉብታ ላይ አይቼው 'እኔን! እኔን! እኔን!' ብዬ ተንደርድሬ እንድመለስለት ነው? ልጅ አደረገኝ? አጠገባቸው ተጋድሞ ያልመተሩት ስጋ በሙሌ ድመት ሲወሰድባቸው የሚነጫነጩ ስንት ውሾች አሉ:: ያቺ ቅማላም ምን ብላው ይሆን? ከዚህ ከቤት በረንዳ ላይ የሰፈሩ የቤት ጣሪያዎች በሙሉ ይታያሉ:: ምንም አያምርም:: ከታች ሆነው ሲገምቱት እንዲህ ቆሻሻ አይመስልም ነበር::

## የዝሆን እሞት መራራ ነው፣ የጎበዝ ልቡ ተራራ ነው

አንድ ማታ የስፖንጁ ጥልቀት ሁለት ስንዝር የሚያክል መከዳዬን ተደግፌ፣ የባለቤቴን የአስናቀን መምጣት ስናፍቅ ያልጠበቅሁት ያህል ዘገየብኝ:: ቴሌቭዥን ከፍቼ ዜና ሳዳምጥ በራሱ ቁልፍ በር ከፍቶ ገባና እንደ በደልኩት ሁሉ በብስጭት አየኝ::

«ምን ሆንክ?» አልኩት

ምንም ሳይናገር አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ:: እጁን እያሻሸ መሬት መሬት እያየ ሳይናገር ጥቂት ቆየ:: ሁኔታው አስፈራኝ፣ ከተጋደምኩበት ቀና አልኩና:

«ምን ሆንክ የእኔ ጌታ ማን አስቀየመብኝ?» አልኩና እጆቼን እንደ ክንፍ ዘርግቼ አቀፍኩት:: አይኖቼንም ጨፍኜ ላብ ላብ የሚል ሰፊ ጠንካራ አንገቱን ሳምኩትና:

«ራት ከበላህ በኋላ ታወራኛለህ» ብዬ ከሶፋው ላይ ተነስቼ ስቆም:

«ለሁለት ወር ፊልድ--መስክ ስራ ሆሳዕና ልሄድ ነው:: ግዴታ ነው» አለኝ::

ከቁሜ ሶፋው ላይ ዘጭ አልኩ::

«ፊልድ? ፊልድ??»

ያለ እሱ አንድ ቀን፣ አንድ ሰዐት መኖር አልችልም፤ የስጋዬም የመንፈሴም ምግብ ነው:: ያለ አስናቀ ቤቱ ይሰፋኛል:: ያለ እሱ አልጋው ይሰፋኛል:: ያለ እሱ ብርዱ ይበዛብኛል

«አብሬህ እሄዳለኋ»

«ምን መሆንሽ ነው?»

«አብሬህ እሄዳለሁ»

«ሴት የምትሄድበት አይደለም:: ከባድ ነው:: የእግር መንገድ አለበት፣

በረሃ አለበት»

«ሴቶች እኩል ናቸው ትሉ የለም እንዴ? ለመሆኑ መቼ ነው የምትሄዱት?»

«ከሳምንት በኋላ:: እኔ ብቻ ነኝ:: ያናደደኝ ይኼ ነው»

«እንዴት ዝም ትላለህ?»

«እሱ አይደለም የሚገርመው? ስራው ሲጀመር የሌላ ሰው ነበር፣ ባላወቅሁት ምክንያት ጠዋት አለቃዬ ጠራኝና ቦታውን ተክተህ ስራ አለኝ»

«አትግባባቸውም ነበር?»

«ምንድነው መግባባት? ስራዬ እኮ አይደለም:: የእኔ ስራ የተሰበሰበ መረጃ እሱን ማጠናቀር ነው:: መደመር፣ መቀነስ፣ ማካፈልና ማባዛት ምናምን»

«ታዲያ እንዴት......» አቋረጠኝ

ከደረት ኪሱ ኤንቬሎፕ አወጣና እተቀመጥኩበት ጭኔ ላይ ጣለው

«ምነው?»

«የሦስት ወር ደመወዜን ሰጥተውኛል:: አንቺ ጋ ይሁን:: የሚሆነው አይታወቅም:: እኔ የቀን አበሌ ይበቃኛል:: ካጠረኝ ከፔቲ ካሽ ገንዘብ እወስዳለሁ......»

ኤንቮሎፑን አገላብጬ አየሁት:: የብር ጠረን ለአፍንጫዬ ይሰማኛል:: እንደ መርካቶ እንደ መርካቶ:: የሚነጅስ አይጠፋም::

## ቸብ ቸብ

ታደሰ እባላለሁ:: የወይዘሮ ሎሚ ሽታ የስማንያ ባሏ ነኝ:: 'ታደሰ' ብላ ስትጠራኝ እናቴ የአባቴን ትንሳኤ ወይም አዲስ መሆን መመዝገቧና መመኘቷ ነበር:: ስም ያቅዳል እንጂ ፈፃሚው ፀባይ ሳይሆን አይቀርም:: የእኔ የሕይወቴ መስመር የተቀየሰው ገና ከእናቴ ማሕፀን ስወጣ ነው:: አባቴ ከጠፋበት የድንቁርና ጎዳና እንዲመለስ ማስተማሪያ ልታደርግበት ስሜን 'ታደሰ' ትበለኝ እንጂ እሱ የተማረም የተመራመረም የሚመራመርም አልነበረም::

*(ቸብ1: ተበዳይ ይበደል ዘንድ)*

እሷ እናቴ ምሥራቅ እንደነገረችኝ አባቴ ፍቅረስላሴን ባገባችው በጥቂት ወራት ውስጥ ተለወጠ:: ሰካራም ሆነ:: ቀስ በቀስም አይደለም:: አንድ ቀን (ጳጉሜ ወር) ማታ ሲመጣ ዘገየባት:: ጠበቀች ጠበቀች:: አድርጎት የማያውቀውን ዘገየባት:: እኩለ ሌሊት ሲደርስ (ከሰአት እላፊ ጥቂት ቀደም ብሎ) ራሱን ሊስት ትንሽ እስኪቀረው ሰክሮ እየተንገዳገደ፣ እየተለፋደደ (እሷ እንዳለችኝ) የአጥር በር ከፍቶ ገባ:: (እሷ በረንዳ ላይ ኩታዋን ለብሳ በርጩማ ላይ ተቀምጣ

እያናወዘች ትጠብቀው ነበር) ከዚያች ቀን በኋላ መስከር አላቆመም:: በተለምዶ እንደ ሚወራውማ በትዳር ጥላ ስር ልጅ ወልዶ መኖር መጥፎ ጠባይ ያርማል፣ ከስህተት ይመልሳል፣ ያረቃል፣ ያረቅቃል ሲባል ነው:: አባቴ ጋ ሲደርሱ ግን እንደነዚህ ዓይነት ልማዳዊ ሕዝበ-አዳም የሚያምንባቸው አባባሎች ቀንጮአቸው እስኪገጠብ በአናታቸው ቆሙ:: ሰካራምነቱ ደ'ሞ ከመቀነስ ይልቅ ቀን በቀን እያየለ፣ እየገዘፈ እሱን ብቻ ሳይሆን እናቴንም እንደ ጥፋት ውሃ ያጥለቀልቃት ጀመር::

የአባቴን መልክና ፀባይ በዝርዝር አላውቅም:: ያው ከሞተ በኋላ፣ ፊት ለፊቷ አስቀምጣኝ የታሪኳን ሒሳብ ስታወራርድ ነው የምትነግረኝ:: የምኖት አየሯን እየጠጣ በአረቄዋ፣ በጅኗና በጠጂ ጉብቱን ዘርፋ በጠራራ ጨለማ ስር ሰባራ መስታወት ላይ የሰቀለችውን የሚወዳት አዲስ አባን በሞት ለቆ ከሄደ በኋላ እናቴ ስታወራኝ......

መሬት መሬት እያየች ዓይኖቿን ጨፈን ጨፈን እያደረገች፣ ዕንባዋ ሊወርድ እንደ መስታወት ሰሌዳ በሽፋሽፍቶቿ መሃል ተኝቶ......

«የአባትህ አንጎል ታውቃለህ፣ ይኼ የጫማ ፈለግ ሳያቋርጥ እንደሚቀበል የቦካ የሐምሌ የጭቃ መንገድ እሱን ነበር......ከእኔ ከምወደው ሚስቱ የበለጠ የጠላ ቤት ወሬ ያመነ......'አጋንንት ነው!' ይላሉ:: 'እንዴት አንድ ሰው በአጭር ጊዜ ሰካራም ይሆናል ያው አጋንንት ካልሆነ?' ይላሉ:: አጋንንት ፍቅርህን የሚሰብር ነው:: ፍቅርህን ከወሬ የበለጠ የሚሰብር ምን አለ? መጠራጠርን እየዘራ፣ አለመግባባትን እያመከረ:: አጋንንት በትክክል ታላላቅ ቂላዋትን የምታሰባስብ ወሬ ናት......

«ከቤት በወጣ ቁጥር ቀድሞ ያላየኋቸው፣ የማቃቸውና የማላቃቸው፣ ያላሰብኳቸው፣ ያላለምኳቸው ወንዶች ከእኔ ጋር ይወጡ እንደ ነበረ ወይም ወዳጃቸው እንደ ነበርኩ ተነገረው::

«'ምስራቅን አገባ? ምስራቅን? እሷ ከግርማ (አባቱ ጓያ የሰበረው)...... ከወራሽ......ከሳሙኤል (የናጠጠ ጉረኛ)......ከሸዋንግዛው፣ ከዳምጤ (በስካር የታወቀ ደራሲ)፣ ከሙሉነህ (ይሄን አላቅም)፣ ከበላይ (የሰካራሞችና የአስቀያሚዎች ቻምፒዮን)፣ ማነው? ጠፋኝ ስሙ......ከእነሱ ጋር ትወጣ አልነበር?' ይሉት ጀመር......

«ይኼው የእናቴን ስጋ ብዙዎቹ ምድር ላይ ይኑሩ የማላውቃቸው ወይ ስማቸው ከዘፈን ምርጫ ዝርዝር ተሰርቆ እንደሆን እንጃ»

ትቀጥላለች:

«ታዲያ አባትህ ደም ስሩ ተግተርትሮ ሊፈነዳ ደርሶ ትልቅ ዕውነት ከሰማይ እንደ ወረደለት ሁሉ 'ታዲያ አውቃለሁ ልትዪ ነው? ማን አየሁ፣ አውቃለሁ ይላል:: አንዴ ጨዋ ነኝ ብለሽ የለ፣ ውሸትሽ ሲወጣ ለምን አትክጂ? ቴሌ ኬክ ቤት ነበር አሉ የምትውይው:: ክፍል ገብተሽ አታውቂም ነበር የሚባለው......ምንሽ ሞኝ ነው? 'ይለኛል

'ማን አለህ?'

'የነገረኝ ነገረኝ'

'ምን ማለት ነው 'የነገረኝ ነገረኝ'? ቡና በወተት እወዳለሁ፣ ኬክ እወዳለሁ፣ ሴት ጓደኞቼን እወዳለሁ......»

'እሱንም ካመንሽ ፍንጭ ነው'

ለምኑ ምን ፍንጭ?

'የባለጌነትሽ'

እንዴት? ኸረ ተወኝ አንተ ሰው! ማን ነገረህ እሺ ንገረኝ

'የነገረ ነገረኝ፣ ዝም ብሎ ሳይሆን ይነግረኛል? ብዙ ቁም ነገረኛ አለ እኮ፣ የሚያይ ሰው አለ፣ ስበደል የሚቆጨ አሉ' ይለኛል::

«ምን ማለት ነው? 'የነገረኝ ነገረኝ'? የአገርህን የወንድ ጅል አየህ? በነገር ተበጣጥሶ ቤቱ ሲገባ፣ ቤቱን በወሬ ወስደውለት ግን ቤት አለኝ ብሎ ይመጣል:: በጭንቅላቱ አፈንድዶ የበቃው:: ይቅርታ ልጄ እንዲህ ለማለቴ:: ምን ማለት ነው የነገረ ነገረኝ? የነገረውን በዕውን ካመነ ለምን ማን እንደ ሆነ አይነግረኝም? የነገረህን አምጣው ዘርዝረው ስለው ራሱን ይነቀንቃል:: ምን ማለት ነው? 'አንተ የማትረባ አምጣው የነገረህን?' ትቶኝ ሊጠጣ ይሄዳል»

አጠገቧ የተቀመጠ ጠርሙስ ዘቅዝቃ ባለ አበባ ብርጭቆ ውስጥ የእግዜር ውሐ ታንቆረቁራለች:: ቁሩሩው የሚማርክ ነገር አለው:: ሰስቱም መኝታ ቤቶቻችን ከጀርባ ስለሆኑ አንዱ ውስጥ ከተቀመጥን ድምፅ ከውጭ ፈፅሞ አይመጣም:: ታዲያ እዚህ ክፍል ውስጥ ከእያንዳንዱ ትንንሽ ከመሰለ ድርጊት የሚወጣው ድምፅ ሁሉ ጥራት አለው:: የዛ ነገር ብቻ ነው:: ተመቻችቼ ወሬዋን ለመስማት እግሮቼን ስዘረጋ የመታሁት የአልጀብራ መፅሐፍ መሬት ወድቆ አየዋለሁ (የመምታቴና የመፅሐፉ አወዳደቅ ያወጡት ድምፅ ማራኪነት ቀላል አልነበረም):: ሳነሳው ቢዳዳኝም ወሬዋን ላቋርጣት አልፈለግሁም::

ግድግዳ ላይ ብርማ የእንጨት ቢጋር ባለው መስታወት ውስጥ አረንጓዴ ቀለም የበዛው የስቅለት ስዕል አለ:: የስቅለቱ ስዕል ለምን አረንጓዴ እንደ በዛበት ባየሁት ቁጥር ይገርመኛል:: እዛ ስዕል ውስጥ ካለው ቁራጭ የመካከለኛው ምስራቅ ሰማይ ላይ ግራና ቀኝ ሁለት ሞላላ ግራጫ ደመናዎች አሉ:: የተሰቀለው ክርስቶስ ቆዳው የነጭ ስንዴ ሊጥ ይመስላል:: በዛ የፀሐይ ቀጠና ውስጥ ቆዳው እንዴት እንዲህ ሊነጣ ይችላል? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ:: ክርስቶስ ፊት ላይ ከአክሊለ ሶኩ ስር ከተለያየ አቅጣጫ ቀጫጫ የደም ዥረቶች ይፈሳሉ:: እነሆ! ሰውዬው::

በእኔና በእናቴ መሃል ከገበያ የተረፈ ከአስር ብር በላይ ገንዘብ ጠረጴዛ ላይ አለ:: በግንባሩ የተደፋው ብር ላይ ሳንቲሞች ተከምረዋል:: በመስኮት የሚገባ ነፋስ ሳንቲም ያልተጫነውን የብሩን አንድ ጎን ያርገበግባል:: እናቴ ከተጋደመችበት ያረጀ ሶፋ ጀርባ፣ የሰው ቁመት እማይደርስበት ከፍታ ላይ

የአባቴ ኮትና ሸሚዝ (እናቴ እንደ ነገረችኝ) እንደ ሚለበሱ ዐይነት--ሸሚዙ ከስር ኮቱ ከላይ ተደራርበው ግድግዳ ላይ ተሰቅለዋል:: በግራ ኮቱ ደረት ኪስ ውስጥ አንድ ቀይ የፕላስቲክ ዕጌሬዳ ተሸጧል:: ከተሰቀለበት ማንም አውርዶት አያውቅም:: ከተሰቀለ ብዙ ጊዜ ቢሆንም ሲቆሽሽ አይቼው አላውቅም:: ከልብሶቹ አይነት አባቴ ዘናጭ እንደ ነበረ መገመት እችላለሁ:: እናቴ ያላረጀ ግን መስመር ማውጣት የጀመረ ግንባሯን ሸብሸባ......

«ነፃነቴ ሰዎች አፍ ውስጥ ነበር አየህ:: ብዙ ሰዎች እሱን የገደልኩ እሱን የገፋሁ ያደርጉኛል:: ለምን እንደ ሆነ አትጠይቀኝ:: ቡና መጠጣትና ኬክ መብላት ስህተት አለው? እዚያ አይደለ ያወቀኝ? የወደድኩት አባትህን ፍቅረስላሴን ብቻ ነበር:: ግን እኔ የምለው እናት ለልጇ ይኼን ማውራት አለባት? ባልረባ ብር ቢራ እየጋበዙ......ከእኔ የበለጠ የሚወዱት መስለው፣ ራሴን በገንዘብ መዝኜ የማላውቀውን ልጅትን ከልቡ አላጣሉትም? ማርያም ላስተምረው ብላ ነው መሰለኝ አንተ ስትወለድ ታዲያ ቁርጥ እሱን:: ያን ጊዜ ለጥቂት ወራት መስከሩን አቆመ:: በደስታ ልቤ ቀጥ ልትል:: ታዲያ ወዳጆቹን እያመጣ አንተን ሲያሳያቸው:

'ምነው ዓይኑ ጋ አንተንም እሷንም አይመስልም?'

'ልጅ በእናቱና በአባቱ ካልወጣ አያቱን ምናምን መምሰሉ አይቀርም'

'አፉ ጋ አንተንም ምስራቅንም አይመስልም:: ሉጫ ፀጉሩን ከየት አመጣው? ዘር እኮ!! የምስራቅ ሉጫ ቢሆንም እንደ እሱ አይደለም:: የእሱ የህንድ ይመስል የለ'

«ቀስ በቀስ መልሰው ወደ ስካር ዓለም ጎተቱት:: ቂልነቱን በዚህ ፈተሹና በኋላ በኋላ የመስሪያ ቤቱ የሒሳብ ሹም አደረጉት:: ከእኔ ማራቂያ ጥበብ ብቻ አልነበረም:: ሊጠቀሙበትም ነበር:: እንደ አህያ ጋለቡት:: አንዳንዶቹ በእሱ ስም ገንዘብ ዘርፈው ከአገር ወጡ:: በኋላ ስሰማ እያሰከሩ የማይሆን ነገር ያስፈርሙት ነበር አሉ:: ያገሬ ወንድ ተስፋ በጠላቱ መገዛት ነው:: ......'ስድ ነበርሽ' ይባላል ካለኝ ማን እንደ ነገረው አይናገርም?

«የአባትህ አንጎል ጭቃ ነበር:: በስካሩ ቀጠለ:: በእኩለ ሌሊት የሚንገዳገድ የማያምር ጅብ ፍጡር ሆነ:: ከሳ:: ጠቆረ:: ራሱን በአልኮል በላ:: ታዲያ አንድ ቀን ከገነት ሆቴል ወረድ ብሎ ቦይ ውስጥ ከቁሙ ወደቀና......ያየ ሲያወራ...... የነበረ......ያው ያሰከሩት ናቸው ሌላ ማን ይሆናል? የተሰበረ ቆሻሻ ጠርሙስ በአንገቱ ገባ:: አለቀስኩ እንጂ ሲሞት:: የእሱ ብቻ ነው ወይስ የወንዱ ሁሉ አንጎል ጭቃ ነው? ልመረምር አልፈለግሁም:: ሳንደሰት ......እሱም በልጅነቱ እኔም ገና በልጅነቴ እንዲሁ ምርር እንዳለን ሁሉ ነገር አለቀ:: የሞተ ሰሞን ለጥቂት ቀናት እነዚያ ጓደኞቹ ፍቅረስላሴ በደረሰበት ነገር 'የለንበትም' ለማለት ነው መሰለኝ 'እንዳትመጡብኝ' ብላቸውም--የሌባ ዐይነ ደረቅ--ሊጠይቁኝ መጥ ተው (ተጠየቅሁ እቴ) ሰው በተሰበሰበበት እንዲህ ማለት አመጡ:

'እንዴ! እንዴ! ፍቅረስላሴ ራሱን የመሰለ ልጅ ወልዶ የለ......' ......ድሮ እንዳላዩት......'ኮፒ በይው:: መፅናናት ነው:: ሰው መሞቱ አይቀር'......ይሉኝ

ጀመር......አየህ?......አየህ የሰው ነገር? አየህ የተንኮል ቴክኒክ?......

«እሱ ያደረሰብኝ በደል ቂም ያስያዘኝ የመሰላቸው አብረውት ሲያጠፋፉት የነበሩት አንዳንዶቹ ሊያባልጉኝ ጠየቁኝ:: አንድ ነበረ እንደ ተቀጠረ፣ ልክ ስራው እንደሆነ ሁሉ እየወሰደ የሚያስክረው:: ከብት አድርጎኝ መሰለኝ 'ላውጣሽ' አለኝ:: ለልጅ ይወራል ይኼ? ለማን ላውራው? ማን ይሰማል? ማን ያምናል?

«የማሳይህ ጎዳናዬን ነው::

«ያ ሰው ልክ የአፍ ድፍረቱን እንደ ጨረሰ......እዚያው ተቀምጦ እያለ በለቅሶ ፈረስኩ:: አለቀስኩ:: አለቀስኩ:: ያፈላሁለትን ሻይ ሳይጠጣ ወጣ:: በልቤ 'ደም ጠጣ' ማለት ጀመርኩ:: ያን ጊዜ፡ 'ደም ጠጣ' ብዬ ጀመርኩና ዛሬ 'ደም ጠጡ' ሆነ:: ብዙዎቹ ከተለያየ አቅጣጫ አደረጉት እንጂ ደም ጠጥተዋል:: 'ያቺ ምስራቅ ጨዋ ሴት ናት' እያለ ሲያወራ ነበር አሉ:: ታዲያ ሲያወራ 'ላባልጋት ጠይቄአት እምቢ ስላለችኝ ነው እንዲህ የምላችሁ' የሚል መሰለህ? ብቻ ሰማሁ ማለቱን:: እውነት ይሁን ውሸት እንጃ:: ምን የሚታመን ነገር አለ ብለህ ነው? አየህ ግን እናት ለልጇ እንዲህ ታወራለች?......መልካም የሚጠጣ ወይ የሚበላ ያዘጋጀች ይመስል? ግን ለማን ላውራው?......»

ጥያቄዋ ለእኔ አልነበረም......

ከተቀመጠችበት ተነስታ ጓዳ ገባች:: በመኝታ ቤት መስኮት መጨለም ወደ ጀመረችው የአዲስአባ ሰማይ አያለሁ:: ነጭ የደመና ብጣሽ ግራጫ ሰማይ ላይ በምስማር እንደ ተመታ ሁሉ ቀጥ ብሏል:: እናቴ ከጓዳ የከሰል ምድጃ ይዛ ወደ ሳሎን አለፈች:: እንድመጣ ጠራችኝ:: ሰማይ ላይ ሳፈጥ ቆየሁ:: ሳሎን ስገባ ከሰል ምድጃው ላይ ጀበና ተቀምጧል:: የምድጃው ፍም ተንገልጧል:: ሶፋ ላይ ስቀመጥ አስራ ሁለት ሲኒዎች የሸፈኑት የእንጨት ረከቦት መጣና ከእግሬ ትንሽ ራቅ ብሎ ተቀመጠ:: ከዛ ጎን ከዕጣን ማንደጃ ላይ እየተከዘ የሚነሳ የመላዕክት ጅራት የመሰለ ጭስ......

❍

ቡናዋ ቀዝቅዞአል:: ቡናዋ ሁሌም እንደ ቀዘቀዘ ነው:: ቡና ታፈላለች፣ ትቀዳለች ግን አትጠጣም:: 'ውይ ይሄ ቡና ማማሩ፣ ሳልቀምስለት በረደ' ትልና እሱን አፍሳ ሌላ ትቀዳለች:: ሶስቱም ደረጃ ሳትጠጣለት ያልቃል:: ከጎረቤታችን ከእትዬ ቀለመወርቅ በተቀር እቤታችን ቡና ለመጠጣት የሚመጣ አልነበረም:: ብዙ ጊዜ ሳገኛቸው አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ ነው:: እናቴ ሞታ ጨርቆስ ስትቀበር ያለቀስነው ሶስት ሰዎች ብቻ ነበርን:: እኔ፣ ነፍስ አባቷና እትዬ ቀለመወርቅ:: ሰአቷን አውልቃ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች:: የሰአቷ የመስታወት ሰሌዳ ጨረር የመሰለ ስንጥቅ አለበት:: የብረት ማሰሪያው በዚያ ፀጥታ የሚያምር፣ ከነውዝ የሚያነቃ ወዳጅ ድምፅ ነበረው:: ሁልጊዜ እማማ ሰአቷን አውልቃ የእንጨት ጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥ የሚፈጠረው ድምፅ ይመስጠኛል:: ዛሬ ዛሬ እኔም የማስራቸው ሰአቶች ያን ድምፅ ለማግኘት ወይም ለመስማት ብዬ የገዛኋቸው ናቸው:: አራት አሉኝ:: ዛሬ ያ ሰአቷ መኝታ ቤቴ ቁምሳጥን ውስጥ በጨርቅ ተጠቅሎ ተቀምጧል......

ግድግዳ ላይ የተሰቀሉት የአባቴ ኮትና ሸሚዝ ንፁሕ ይመስላሉ:: እነሱ ከተሰቀሉበት ስር አጭር ጠረጴዛ አለች:: ከዛ በፊት አይቼአት አላውቅም:: እዚህች አጭር ጠረጴዛ ላይ አባቴ ከዩንቨርሲቲ ሲመረቅ ጋውን ለብሶ የተነሳው ፎቶ አለ:: ፎቶው ማቀፊያ ላይ ጥቁር የአንገት ፎጣ የመሰለ ስስ ጨርቅ ተጥሎአል:: ዛሬ፣ ትናንት፣ ከትናንት ወዲያ የሞተ ይመስላል:: እናቴ ሞልቶ የበረደ ሲኒዋን እያየች ትስላለች:: ሳሏን ስትጨርስ ቀና ብላ አየችኝና:

«እናት ለልጇ አርቲ ቡርቲ ታወራለች?......አርቲ ቡርቲ አይመስለኝም ታደሰ:: ከእኔ በሽታ የብዙ ሰው በሽታ ይታያል መሰለኝ:: አባትህን ሁልጊዜ አስቀው ነበር:: እሱን ማሳቅ ስወድ:: ግን እኔን ነኩኝ፣ ግን እሱን ከእኔ ነጥ ለው እንዴት ሊወዱት እንደሚችሉ ሂሳቡ አልገባውም:: እሱ ያልተነካ መሰለው:: በመሃላችን የገባው ነፋስ ግን የሁለታችንንም ነፃነት ገፈፈ:: እሱን በመውደድ አገኝ የነበረው ነፃነት ጠፋ:: ለስራ ወጥቶ ሲገባ ቀድሚው ከደረስኩ ጊዜው አያልፍልኝም ነበር:: ኮቴውን ስሰማ እተቀመጥኩበት እደነግጥ ነበር:: እቆምኩበት እደነግጥ ነበር:: ዛሬ ድረስ የእርምጃው ዳና እንደ ሙዚቃ እንደ ከበሮ ቃና በጆሮዬ ውስጥ አለ:: ከሦስት ከአራት ሰዎች መሃል የእግሩን አጣጣል መርጬ ማውጣት እችል ነበር:: የሚያስቀና መልክ የሚያስቀና ቁመና ነበረው:: በአልኮል እየፋቁ በሐሰት መረጃ እየተረተሩ እስኪያጠፉት ድረስ:: ያልገባው ሊጥ አባትህ:: የጥርሱ ንጣት ተገፎ የትንባሆ ደለል ሞላው:: የግንባሩ ብርሃን ልክ እንዳንተ የነበረ ነው:: የሐምሌ ሰማይ ሆነ:: ጠረኑ ልጁ ገና የተለቀመ ጥጥ ይመስል ነበር......በየግሮሰሪው እያዞሩ ሰጋቱራና እንግዳ እንግዳ የሚሸት ላብ ቀብተው አመጡት:: መከርኩ:: አስመከርኩት:: በዕንባዬ ለመንኩ:: እምቢ አለ......»

'እምቢ' የምትለው ቃል ከንፈሮቿ ላይ ስትፈነዳ የተፈናጠረ ደቃቃ ምራቅ አፍንጫዬ ላይ ሲያርፍ ተሰማኝ:: አልጠረኩትም:: ዐይኖቼን ጨፈንኩና ረቂቅ ቅዝቃዜውን በቆዳዬ ጠጣሁ:: እናቴን እወዳታለሁ:: 'ልጅን ከወደዱ ከነምንትሱ' ይሉ የለ፣ ለእኔ ደሞ እናትን ሲወዱ......ሊሆንብኝ ነው......

○

ፒያሳ የማውቃት የቡና ቤት ወዳጄ ጋ መሄድ እፈልጋለሁ:: ቋሚ  የሴት ወዳጅ የለኝም:: ካለኝ ቤቴን ማየት አለባት:: ታዲያ እናቴን አጣማ እንድታይብኝ አልፈልግም:: 'የእብድ ልጅ' የማትለኝ ይህቺ የቡና ቤቷ ፀሐይ ብቻ እንደሆነች የፈራው ልቤ ይገባዋል:: ገንዘብ ካገኘሁ ቀን ቀን እንደ ልጃገረድ አቡነ ጴጥሮስ አካባቢ ለምሳ ይገፔያት እሄዳለሁ:: ለፀሐይ ልጅ ነኝ:: ግን እወዳታለሁ:: ቁመቷን እወደዋለሁ:: ልብሷን አውልቃ ጋደም ብላ አንድ እጇን እንትኗ ላይ ጣል አድርጋ ምንም ሳትናገር ስታየኝ እወዳታለሁ:: አተኩራ ስታየኝ ግን እፈራታለሁ:: እንደዛ ስታደርግ እፈራታለሁ:: ስለ እናቴ የምታውቅ ይመስለኛል:: «የእኔ ቆንጆ ምን ላድርግልህ?» ትለኛለች በሚፈስ ድምጽ፣ በሚገል ፈገግታ:: እንደዛ ስትለኝ ጎኗ ጋደም እልና አንገቷን አቅፌ አሸታታለሁ:: እሷም እንደ እናቴ የምትቀባው ኒቪያ ክሬም ነው:: ጠረኗን እንደምወደው እነግራታለሁ::

እናቴ ከገበያ ገብታ የለበሰችውን አውልቃ ዝባዝንኬ የቤት ልብስ

ለብሳለች:: ከዐይኖቿ ድካም እየተነነ ይወጣል:: እውጭ ዝናብ ይጥላል:: ከሰፈራችን ሜዳ ኳስ ሲጠለዝ እሰማለሁ:: ከእናቴ ጋር መንገድ ላይ መታየት አፍር ነበር:: ገና የፊት ጥርሴን ነቅዬ ጣምራ አክስጂን ስስብ፣ የኢያሱ ልጅ 'እብድ ያሳደገው' ብሎ ሰድቦኛል:: ያ አልተረሳኝም:: የስድቡ ሐረግ ግንባሬ ላይ ተለጥፎ እያከረሰሰኝ ሲሳብ ይሰማኛል:: በዚህ የተነሳ ኳስ ከተጫወትኩ ብዙ ዘመኔ ነው:: አሁን አሁን እዚህ ሜዳ የማልሄደው በቂም ይመስለኛል:: የሰፈሬን ልጆች አልፈራቸውም፣ አልጠላቸውም ግን ያደረጉኝን አልረሳም:: ሳልነካቸው ስለነኩኝ መሆን አለበት ያቄምኩት:: ስህተት የለውም:: ጎበዝ ተማሪ ያደረገኝ የኢያሱ ልጅ ስድብና ስድቡን ሲሰሙ ፈገግ ያሉ ጅላንፎዎች መኖራቸው ነው:: እማማ ዕብድ አልነበረችም:: በደረቅ ሌሊት አብዮተኛና ፀረ አብዮተኛ ሲፋናከቱ፣ ከሰፈራችን እስከ ቄራ ባሩድ ሲንጣጣ ሞሳ ዙሪያዬን እንደ ሐረግ ተጠቅላ ፊቴን ጡቶቿ መሃል ደግኜ ሳናውዝ፣ ይኼ ጋሻነት የዕብድ አልነበረም:: ከሁሉ የበለጠ ሰላም የሚነሳኝ ከጋረደችው እናቴ ከፍ ብሎ የሚነሳው ለቅሶዋ ነው:: ገላዋ ይንቀጠቀጣል:: ላቧ ይወርዳል:: በማይገባኝ ምክንያት ማልቀስ እጀምራለሁ:: ዕብድ ማለት በቀጫጫ አጀንዳ ወፍራም ሞት መስራት ነው:: ዕብድ አለ በያይነቱ በየቦታው......በየአደባባዩ......ዕብድ እነዛ ናቸው፣ እብድ እነዛ ነበሩ:: ማልቀስ መጀመሬን ስታይ ቀና አድርጋ ጉንጬን ትስመኛለች:: ከሳመችኝ በኋላ ጉንጯ ሁልጊዜ ጉንጬ ላይ ይቆያል:: ለጥፋ ትይዘኛለች:: ይህቺ ያበደች እናት አልነበረችም:: ልጅ እያለሁ የፈተና ውጤቴ ጥሩ ካልሆነ ከእናቴ እብደት የተጋባብኝ እየመሰለኝ እበሳጭ ነበር:: አስተማሪዬን ማየት እፈራ ነበር('መጀመሪያውኑ ከእብድ ልጅ ምን ይጠበቃል?' የሚሉ እየመሰለኝ):: ግን ጥሩ ማርክ በማምጣቴ በአስተማሪዎቼና በተማሪ ተከበርኩ:: ከሰው በመራቅ ችሎታዬ ስለ ታወቅሁ አኢወማ እንኳን አያስቸግረኝም ነበር:: ታዲያ ከሚያስከብረኝ ነገር ውጭ፣ ሌሎች ፈርተው እንዲርቁኝ ከሚያደርግ ነገር ውጭ ሌላ ነገር አልሰራም:: ሜዳ ዘልቄ የማልሄድበትን ምክንያት እናቴ ታውቃለች:: በረንዳ ላይ ቆሜ ጠባብ ግቢያችንን እያለሁ፣.....

እናቴ ወንበሯ ውስጥ ሆና ታንጎላጃለች:: በጣም የሚያሳዝን ትዕይንት ነው:: ሲያናውዛት ቆዳዋ የበለጠ ይጠወልጋል:: የታች ከንፈሯ ወደቅ ይልና አፏ ከርፈፍ ይላል:: ለነዛ ከንፈሮች ያኔ ኮረዳ እያለች ብዙ ጎረምሳ እንዳለመ ከልጅነቷ ፎቶ ካገኘሁት መረጃ ይገባኛል:: ያን አይቶ ይሄን ሁኔታዋን ያጤነ ልቡ ተነክቶ ቢያለቅስ አይገርመኝም:: ከቆምኩበት ሂጄ ፊቷን ልነካት፣ ቀና ላደርጋት ፈለግሁ:: ጣቶቼ ጫፍ ላይ ጥላሸት ተለድሶ የሚቀር መሰለኝ:: ከአጥሩ በር ጎን ድሮ ልጅ እያለሁ አበባ የነበረበት መደብ አለ:: አሁን ባዶ ነው:: ከእናቴም ከኳስ ሜዳውም ልሸሽ ፈለግሁ:: ወደ ሽርሙጣዬ መሄድ ፈለግሁ:: 'ወደ ምሄድበት ልሂድ' ብዬ ልጠይቃት ዞር ስል ከምታናውዝበት ነቅታ አፏን እየጠረገች ነጠላዋን እያስተካከለች አየችኝና:

«ጣለኝ:: የመርካቶ ፀሐይ......ድሮ የምወደው ቦታ መርካቶ ነበር...... ለልብስ አልነበረም፣ አአህአህአህ......ለግርግሩ:: ዛሬ ዛሬ......:: የት ልትሄድ ነው ቂቅ ያልከው?»

«ፈተና ስላለቀ ከጓደኞቼ ጋር ትንሽ......»

«ጓደኞችህን ምነው አላያቸውም?»

«እዚህ ጨርቆስ ድረስ አይመጡም ከመሃል ከተማ......»

«ከጨርቆስ የበለጠ መሃል ከተማ አለ? የአዲስ አባ ስልጣኔ የሚነሳው ከጨርቆስ ነው:: አዲስ አባ ደሃ ናት፣ ብዙ ሰው መተዳደሪያ ቴክኒክ የሚቀዳው ከጨርቆስ ነው......»

ሳቅሁ:: በጣም ሳቅሁ:: ኮስተር ብላ አየችኝ:: አየኋት::

«አንድ ነገር ልጠይቅህ?» አለች

«ምን?»

«ታፍርብኛለህ?»

«በእንቺ? ምን ማለትሽ ነው?»

«እንዲህ በመሆኔ»

«ምን ሆንሽ?»

«ተው! ተው! ታድዬ ተው! ምን ማለቴ እንደ ሆነ ይገባሃል»

«ለእኔ ምንም አልሆንሽም፣ ትሰሪያለሽ፣ እኔን አስተምረሻል:: አሪፍ እናት ነሽ»

«እሺ ይሁንልህ:: አንድ ቀን እንኳን አላፈርከም? ፍቅረስላሴ ፍቅረስላሴ ስለምል:: በሚዛን አለመውደዴ አስደበኝ:: ምን ላድርግ:: ድክመቴ ነው:: ገመናዬ ነው:: ብታፍርብኝ አይገርመኝም:: ሁላችንም ገመና አለን አየህ:: ንፁሕ ሰው የለም:: የተለያየ ስህተት የሚያሠራ በለስ በልተናል......ሰው ነና:: አባትህ በለሴ ነበር መሰል:: ስትኖር ያጋጥምሃል:: እሱን እንደ ወደድኩ በኋላም ለእሱ ነበርኩ:: ፍቅረስላሴ ሰካራም ቢሆን ልዩ ክፋት አይደለም፡ ከኖሕ ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው:: ታዲያ የሆነ ስህተት ምክንያት ተደርጎ ሰው ማሸሺያ መሆን የለበትም:: ይቅርታ ይደረጋል አይደል:: 'ይቅርታ አደርግልሃለሁ ና' አልኩት:: ልቤን ከፈትኩ:: ራሴን ስህተተኛ አድርጌ ይቅር አልኩት:: ግን እሱ ናቀኝ:: ዲግሪውን እንዴት አገኘው? ለመጨረሻ አልኩና አንድ ዘመዱን መስኮት ገረሱ የሚባል ሰዐሊ ቁም ነገረኛ ለመንኩት እንዲመክረው:: በዝና ሳታውቀው አትቀርም:: ድሮ ልጅ እያለህ ይመጣ ነበር እዚህ:: አሁን ምን እንደ ሆነ አላውቅም ጠፋ፤ የሆነ ድንክ ሰውዬ አንደበቱ ሲያምር:: መማር እንደዛ ነው፡ ወገኑን አገሩ የሚያደርግ፣ አገሩን ወገኑ የሚያደርግ:: መማር ጠቅልሎ ማወቅ ነው:: እዚህች የተቀመጥኩባት ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር፡

'ትወድሃለችና ዝም ብለህ ሕይወቷን አታመሳቅልባት' አለው:: ምን መለሰለት? ይገርማል አባትህ:: ምን አለው መስኮትን? 'ድኩማን' አለው:: መስኮት ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳና ራሱን እየነቀነቀ እንዲህ እንዲህ እየነቀነቀ ውልቅ ብሎ ቀረ ቀረ:: በቃ:: ታዲያ ሁሉ ከሆነ በኋላ እኔ እዚህ ቁጭ

ብዬ 'ዘመድ ነኝ ብሎ ሲቀባጥር ያን ድንክ ልኩን ነገርኩት' እያለ ለጓደኞቹ ጉራ ይነፋል:: ሽማግሌ በመስደቡ ኮራ፣ ዘመዱንም በመስደቡ ኮራ:: ሲነግራቸው ታዲያ 'አይ ፍቅሬ ስትተርቢ እኮ ሌላ ነው፣ አይ አንቺ! እሱ የተጠላ ድንክ አርቲስት ከስዕል በተቀር ምንም የማያውቅ አድር ባይ ነው' እያሉት በሳቅ አወኩ:: አባትህን እያቆላመጡ አነከቱት:: ማቆላመጥ ቋንቋ ብቻ እንደሆነ አልገባውም:: በሉ ውጡልኝ አልኩ:: 'በሉ ውጡልኝ መስኮት እንደ እናንተ አበል ጠጅ ቤት እንደ ትንኝ ተደፍቶ አይውልም ስራ አለበት' አልኳቸው:: አፌዙብኝ:: 'ከዚህ ድንክ ምን አለሽ?' አለኝ አባትህ አህያው:: ፍቅርን የናቀ እንዴት ይቅርታን ይቀበላል? የተያያዘ ነው:: የምትወድህን ዐይኖቿ ውስጥ ታውቃለህ:: በየስፈሩ እየዞርክ መረጃ አትቀበልም:: ሴት ከወደደችህ ሁለመናዋ ላይ ሁሉ ነገር ይፃፋል:: እዛ መንደር አያስኬድም:: አንተስ ከወደድከኝ ለምን ጓደኞችህን አታመጣም? ብልህ የመሰለህን? አንጎል ያለውን መርጠህ? ለምን......?»

«ለምን የማይገባው ሰው አምጥቼ አንቺን እበድላለሁ:: ጥቂት ልጆች አውቃለሁ ግን ለቤተሰቤ ግድ የላቸውም»

«ዱርዬዎች ናቸው?»

«አይደሉም:: በቃ እኔን ነው የሚፈልጉት»

«ፍቅረስላሴ ይሙት በል እስኪ»

«ምስራቅ ትሙት»

ወደ ተቀመጠችበት ሄድኩና እግሯ ስር ቁጢጥ አልኩ:: የጠወለገ ነጭና ቡላ የሆነ ፊቷን ወደ ፊቴ አስጠጋች:: ዐይኖቼ ውስጥ የምትፈልገውን ነገር ፈለገች:: ዐይኖቿ ዕንባ ሲሰበስቡ አያለሁ:: መብለጭለጭ ሲጀምሩ:: ለማልቀስ አፏን ልትጋርድ ስትል እጇን ያዝኳት:: አፏ ሲንቀጠቀጥ እዛ ሳምኳት፣ ከዛ ጉንጯን ሳምኳት፣ ዐይኖቿን ሳምኳቸው፣ ማንም የእናቴን ስም በክፉ እንዲያነሳ አልፈልግም:: አንገቷን ሰበር አድርጋ ወደ መቀመጫዋ መደገፊያ ሸሸት አለች:: እጄ ላይ የቀረ ግራ እጇን ሳምኩት:: ከመሃል ዐይኖቼ እጇ ላይ ቀሩ:: ልጅ እያለሁ የእጆቿ አይበሉባዎች ቀላት ነበራቸው፣ አሁን ጠቁረዋል፣ ቆዳቸው የተሸበሸበ ይመስላል:: ሆዴ ተመሳቀለብኝ:: ዕንባ ወደ አይኖቼ ሊመጣ ያሳክከኛል:: አንገቴን ሰብሬ መሬት መሬት እያየሁ በቶሎ ከግቢ ወጣሁ......

በግማሽ ሰዐት ፒያሳ ደርሻለሁ:: ፍጥነቴ እንደ ሕልም ነበር:: ሁለመናዬ ተቆጥቷል:: ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ግን አላውቅም:: ሩጫ ላይ ነኝ:: አድዋ ሆቴል ገብቼ ገና ወንበር ስቤ እንደተቀመጥኩ ፀሐይ አተኩራ አየችኝና የሚጠጣ ሳትታዘዘኝ እጄን በጨዋታ አስመስላ እየጎተተች አንድ ክፍል አስገባችኝ:: ምንም ሳትናገር በሩን ዘግታ ልብሷን ማውለቅ ጀመረች:: ምንም ሳልናገር ኮቴንና ካናቴራዬን አውልቄ ቀዝቃዛ አንሶላ ላይ በጀርባዬ ተኛሁ:: ዐይኖቼን በእርካታ ከደንኩ:: አጭሩ አልጋ ስላልበቃቸው ሁለቱ እግሮቼ ከቁርጭምጭምታቸው በታች አየር ላይ ናቸው:: የካሊሲዬ ንፅሕና ክፍሉን አበራው (ያው እናቴ ናት እነዛን ያጠበቻቸው):: ጎልቶ የሚጮኽ ሙዚቃና የሰው ጫጫታ ያለንበት ክፍል ድረስ ይሰማል:: ፀሐይ ከቆመችበት አየችኝ:: ሁሌ ራቁቷን ቆማ ወገቧን ይዛ

ዳሌዋን ታሳየኛለች:: ቅርፅዋ የሸርሙጣ አይደለም እላለሁ ለራሴ:: የእፍረቷን ፀጉር እየዳበሰች፣ እየጎተተች በቀዘዘ ፊት:

«ምን ሆነሃል ታድሽ?»

«እንጃ»

«ደህና አትመስልም:: አይዞህ:: ሌላ ቦታ እንሂድ? የማውቃቸው ሰዎች አሉ ክፍል ያከራዩናል:: የሚረብሸን የለም:: አለ አይደለ ብቻችንን እንሆናለን:: ታወራኛለህ:: የሚያስጨንቅህ ካለ ንገረኝ:: እህትህም ልሁን»

አተኩሬ አየኋት:: የአንገቷ አሰባበር ውስጥ ልምምጥ አለ:: ወተት እንደምትለምን ድመት:: ምን እንደምመልስላት አላውቅም:: አልጠበኩም ይሄን ጥያቄ::

«ምንም አያስጨንቀኝም:: ደ'ሞ ገንዘብ የለኝም»

«አበድርሃለሁ» ከት ብላ ሳቀችና:

«ንገረኝ ምን ሆንክ?»

«ናፈቅሽኝ»

«ዋሸኸኝ»

«የዕውነት:: አታውቂም?»

ምን ሆነ ሴቱ? እናቴ ዋሸኸኝ፣ ይህቺ ዋሸኸኝ:: ብስጭቴን ከምራቄ ጋር ዋጥኩ:: ጎምዘዝ ያለ:: የብስጭት ምራቅ ጣዕሙ እንደ አቼቶ ነው:: ከውጭው አለም የጋረደኝን ዳሌዋን እየሳበች በዝምታ ተጠጋችኝና ግንባሬን ስማ እተንጋለልኩበት ከላይ እስከ ታች በስርቅት አየችኝ:: በቀስታ ዐይኖቿን እየከደነች እላዬ ላይ ተቀመጠች:: የተከፈተ አፏ ፈገግ እያለ ፊቷን ሆዴ ላይ ደፋች......እንደ ልጅ ትኮረኩረኝ ጀመር:: በሳቅ ትንፋሼ ቁርጥ እስኪል...... ስትጀምረኝ በኩርኮራ ነው::

○

ቤት እንደ ደረስኩ በካፊያ የረጠበ ጃኬቴን ሳሎን ወረወርኩ:: ደንቤ ነውና እናቴን ሰላም ልላት የተኛችበት ሄድኩ:: ቤታችን በብዙ ቤቶችና አቧራ የለበሱ ዛፎች የተከበበች ስለ ሆነች የሁለታችንም መኝታ ቤቶች ትንሽ የታመገ ቀዝቃዛ ጠረን አላቸው:: እማማ ከሁለቱ አንዱ ክፍል ባዶ ያገኘችው አልጋ ላይ ትተኛለች:: አንድ ሁለት ብዬ ሞቅ ብሎኛል:: ጂን ቶኒክ እወዳለሁ:: ፒያሳ ወጥቼ ሰጎን ሆቴል ደርሼ መምጣቴ ነው:: ውሽማዬ አድራሻዋን ለውጣ እዛ ገብታለች:: ሁለቱም እጆቼ ኒቪያና ሴት ሴት ይሸታሉ፣ አልታጠብኩም:: መጠጣቴን ደ'ሞ ከእናቴ ለመደበቅ ጦር ማስቲካ እያላመጥኩ ነበር:: የተኛችው እኔ አልጋ ላይ ነው:: ሰላም ብዬአት ሳልጠጋት በር አጠገብ መቃን ተደግፌ ቆምኩ:: በግራ እጇ እንድቀርባት ጠራችኝ:: አልኮል ባኗንና አባቴን የነጠቃት መርዝ ነው:: ኢ: ኤስ: ኤል: ሲን በስድስት ኤ በአንድ ቢ ስላለፍኩ ወደ አምስቴ

ስማኛለች:: ይሄ ስድስተኛው እንዳይሆንም እየለፋሁ ነበር::

«አይዞህ አውቃለሁ:: ቢራ ጠጥተሃል:: ፌሽታ እያደረግህ ነው? ይገባኛል:: ቢራ አይገልም የሚገለው ሰው ነው:: የአዲስአባን ሰው ጎርፍ አይወስደውም:: የሚወስደው ቀሽም የከተማ ፕላን ነው:: የዞረበት ጤፍ ብትዘራ እንጀራህ ራሱ የዞረበት ይሆናል:: ና ይልቁን ሳመኝ:: ጉንጭህ ይናፍቀኛል:: እስከዛሬ እናትነቴን አላቃለልክም:: አብረኸኝ አፍረኻል:: ና ሳመኝ» ስለነቃችብኝ በማፈር እየተጎተትኩ ተጠጋኋት:: በግድ ዐይነት ፊቴን ወደ ፊቷ ስባ እምፀ እምፀ እምፀ እምፀ......ጉንጮቼ ምራቋን ለብሰዋል......የአፏ እርጥበት ሲሰማኝ ሁለመናዬ በደስታ ያረገርጋል......ገና ጉንጮቿን ከመልቀቄ......

«ተቆጥቼሃለሁ:: ኮርኩሜሃለሁ:: አንጀቴን ቢበላኝም እንደ ወንድ እጄን አንስቼ ዱላ አንስቼ መትቼሃለሁ:: ከአሁን በኋላ ራስህን ትችላለህ:: ካስከፋሁህ ለአንተ ብዬ ነው:: ይቅርታ አድርግልኝ:: እሺ? የእኔ ስልጆ! አባትህ ክፉ አልነበረም:: ግን ቂል ነበር:: እሱ ከሞተ በኋላ ሰው አላውቅም:: ማወቅም አልፈልግም:: ከቤቴ ስወጣ ወጥመድ ይሸተኛል:: መርገምት በቁና ተሰፍራ እንደ ትኩስ ንፍሮ እየጤሰች የምትጠብቀኝ ይመስለኛል:: ስለዚህ አንተንም ጫጩቴን ባለችኝ ላባ ጋርጄ፣ ረግሜህ፣ ስድቤህ ከጥፋት ያዳንኩህ መስሎኛል:: 'ከሰው ሽሽ' ስልህ ያደናቀፈኝ እንዳያደናቅፍህ ነበር:: ለመሆኑ አባትህን እንደዚያ ያበለሻሹትን ሰዎች መክሰስ እችላለሁ? የእሱ የዋሕነት አይከሰስም? የዋሕነት ወንጀል ሆኖ አይከሰስም? ቂልነት ወንጀል አይሆንም? በመንገድ ላይ ከሚተላለፉት ሰዎች የትኛዎቹ ባሌን አጠፉት? የትኛዎቹ ለብቻዬ እንዳረጅ አደረጉ?......እስኪ ውሃ አምጣልኝ:: ይጠማኛል ለምን እንደሆነ ይጠማኛል»

○

ውሃ ላመጣላት ከማነብበት ተነስቼ እየተነጫነጭኩ እሄዳለሁ:: ሳነብ እናቴም ብትሆን ስታቋርጠኝ አልወድም ነበር:: በተጨማሪም የምማርበት ፋኩልቲ ብዙ ስራ ያሰራናል:: እማማ ብዙ ጊዜ አልጋ ላይ ናት:: የአመት ፈቃዷን ወስዳ አልጋ ላይ ናት:: ሁልጊዜ አልጋ ላይ ናት:: ስለምትረሳ አንዳንዴ ገላዋን እንድትታጠብ የምነግራት እኔ ነኝ:: መታጠቢያ ቤት ንፁሕ ፎጣና ጨርቅ አስገባላታለሁ:: የሰጠኋትን ውሃ አንጋጣ በአንድ ትንፋሽ ትጨልጣለች:: ጉሮሮዋ ሳያቋርጥ ከፍ ዝቅ ይላል:: ብርጭቆውን ጠረጴዛ ላይ ስትመልስ ግንባሯና ፊቷ ላይ ላብ ችፍ ይላል:: ከተማሰ ርጥብ አፈር የወጣ ጓጉንቸር በጣት ወይም በእንጨት ሲጎነትሉት ቆዳው ኩፍ ብሎ አረፋ የመሰለ ነገር እንደ ሚያዝው:: ላቧን በነጠላዋ አብሳ ከተጋደመችበት የለመድኩትን ታንቆረቁርልኛለች......

«የትኛዎቹ የተጀመረው ያማረው የፍቅር ቡቃያ ቡቃያ ብቻ ሆኖ እንዲቀር አደረጉ?[55] ከፍቅረስላሴ በስተቀር ማንንም እንደማልፈልግ እስከሞትም ድረስ አለመፈለጌን ላሳያቸው ምያለሁ:: 'ምስራቅ አለች እንዴ እዚህ አገር?' እንዲሉ እፈልጋለሁ:: በታሪካቸው እንድሠፍር አልፈልግም:: ባረሙት በሰረዙት በደለዙት የውሸት ታሪካቸው ውስጥ 'የሚታዘንልኝ' 'ግራ የገባት' ተብዬ

55 ከወንድዬ አሊ ግጥም ጋር ይገናኛል አውላላው ላይ የካቲት 1980(አ)

መመዝገብ አልፈልግም:: ብትረባም ባትረባም ያንድ ገፅ ያልተበረዘች እሱን የማፍቅር ታሪኬን ይገፍ አፈር እገባለሁ:: ወደ ስራዬ ስሄድና አስቤዛ ልገዛ ካልሆነ ለአስራ ሰባት ዓመታት ከቤት አልወጣሁም:: ቀሩብኝ መሰለህ? ምናቸው ይቀራል? የበሰበሰ ሕብረተሰብ በወሬ ሞተር፣ በወሬ ቤንዚን የሚነቃነቅ፣ በተራ ወሬኞች የሚገዛ፣ ተራ ወሬኞች የሚያሳድሙት ሕዝብ ቢቀር የሚቀርብሽ እርግማን ነው' አልኳት ምስራቅን......»

እናቴ ብዙ ጊዜ ሃይለ ቃል ተናግራኛለች:: ግን ዝርዝሩ ትዝ አይለኝም:: ተናግራኝ ግን አታርቀኝም:: ተናግራኝ ጎትታ ታቅፈኛለች:: ትስመኛለች:: አጥብቃ አቅፋ ትርጉሙ የማይገባኝ ዘፈንና ዜማ እያቀነቀነች ትወዘውዛለች:: እግሮቼ ይደክማሉ:: ዕርግማኗ ሳይሆን ትዝ የሚለኝ እግሮቼ ሲደክሙ ነው:: እንጉሩጉሮዋን እንዳቆመች:

«የእኔ ስልጁ» ትለኛለች::

«እ» ማለት አለብኝ::

«የሴት ልጅ እንዳትባል፣ የዕብድ ልጅ እንዳትባል፣ ጠንክር እ? የእኔ ስልጁ ነህ?»

የማልወደው 'ስልጆ' ስትለኝ ነበር:: ካደግሁ በኋላ ስልጆ ብላ እንዳትጠራኝ ብነግራትም፣ በማላውቀው ምክንያት አንዳንድ ማታ ልታሞካሽኝ በልጅነቴ ቅፅል ትጠራለች::

«ስልጅዬ ራት እንብላ? ርቦኛል:: አንተስ?»

○

እናቴ ራት ለመብላት ተቀምጣለች:: የእናቴ ራት ነው: ሳህኗ ላይ ግማሽ እንጀራ፣ እዛች ግማሽ እንጀራ ላይ እሳት የመሰለ በርበሬው የበዛ ወጥ፣ ከዚህ ጎን በሻይ ማንኪያ ከድስት ቂጥ ተፍቆ የወጣች የመሰለች የአልጫ ክክ፣ ትሪው ቆርቆሮ ላይ ሃኔ የመሰለ በሸንኩርት ብቻ የተሰነገ አረንጓዴ ቃሪያ:: እኔ ካምፓስ ስለምበላ ላስቸግራት አልፈልግም:: እኔ ዛሬ የምበላው ለነገ ለተነገ ወዲያ ይሆናታል:: ቁም ሳጥኔን እየበረበርኩ ዕቃ በሻንጣዬ እከታለሁ:: ከሳጥኑ ጀርባ ሶስት ትላልቅ አልበሞች ተደራርበው አገኘሁ:: አይቼአቸው አላውቅም:: አንዱን አልበም ገና ስከፍተው ያየሁት ስድስት ኪሎ ካምፓስ ፊት ለፊት የቆሙ የአምስት ጎረምሶች ፎቶ ነው:: ወደ እናቴ ወሰድኩና:

«እነማን ናቸው?» አልኳት

«አባትህና ጓደኞቹ.......»

ሁሉም ሙሉ ኮትና ሱሪ ከነክራቫቱ ለብሰዋል:: እጅ ከእጅ፣ እጅ ከትከሻ ተያይዘዋል:: ፎቶአቸውን ሳይ ቆየሁና:

«አባቴን አውቄዋለሁ:: አባትህን በደሉት ያልሽኝ ሰዎች ናቸው?»

«እ» አለች:: 'አዎ' እንደ ማለት

«ሰዎቹ አይመስሉም» አልኳት

«ዩንቨርሲቲ እኮ እባብም ያስተምራል:: አጥፊ ያስተምራል:: ጅልም የበለጠ ጅል እንዲሆን ይማራል ሁለቱ እዚህ የሉም፣ ሁለቱ አሉ:: ተዋቸው»

አልበሙን መመልከት አቆምኩ:: የተቆለፈ በር ያጋጠመኝ መሰለኝ:: ገፍቼ መግባት ፈራሁ:: አባቴ በጣም የሚያምር ጎረምሳ እንደ ነበረ ለእማማ ነገርኳት::

«ምን ይጠቅማል ቢያምሩት?» አለች ቁና ተንፍሳ......

«እማማ ራስሽን ጠብቂ፣ ብትታመሚ ገንዘብ የለንም የምትታከሚበት:: ምን እንከፍላለን? ዩንቨርሲቲ አቋርጬ አንድ ትንሽ ስራ ብይዝስ» ስላት ደንፍታ ከተቀመጠችበት ተነሳች:: በእጇ የያዘቻትን ቁራሽ እንጀራ ከቁሚ ትሪ ላይ በብስጭት ለጠፈቻትና:

«ደካማ ሰው የጠላቱን አጀንዳ የራሱ መስሎት የሚሰራ ነው:: ከመስራትህ በፊት 'የምሰራው ማንን ይጠቅማል' በል:: የአባትህ እንቅፋቶች እሱን ሰካራም አድርገው ሲጥሉት ሴራቸው አንተም ልጅነት ላይ ነው:: አይደል? ሰፋ አድርገው:: ያላሰቡት ሆነ:: ሴራቸው ቤት አስቀመጠህ፣ አሰራህ:: አለፍክ ፈተናህን:: እንቁላላቸውን ጥለው ነበር የሄዱት:: አባትህ ብሩህ ስላልሆነ አልገባውም እንጂ:: አንተ ቆንጆ ነህ:: የገባህ ትመስላለህ:: አገር በአጭር የምትቀረው እንደ አንተ አይነቱ ሲመታ ነው:: ራስህን ስታድን አገርህን ማዳንህም ነው:: ሲያከብሩህ አክብር:: ካላከበሩህ ለምን ትለማመጣለህ? መቼም 'ጂሚ' የተባለ ፈረንጅ ከአውሮፓ አልመጣም አባትህን ሊያጠፋ:: እዚህ ያለ የከረፋ ያገሬ ጅልና ሽረኛ ነው:: አይመስልህም? በመሰረተ ትምህርት ተማሪውና ባስተማሪው መሃል ልዩነት የሌለበት የተረገመ ቦታ ነው:: ግን እነዚያ ያስቃዩኝ የት ሄዱ? የትም:: አየሁ:: የትም:: የት ደረሱ? የትም:: ሂሂሂሂሂሂሂሂሂ:: ውጭ አገር አታለውት የሄዱት እንደሚያኩ እናውቃለን፣ እዚህም አለን አለን የሚሉት ያው አንድ እንጀራ በልተው፣ አንድ እንጀራ አርተው ያድራሉ:: የሚራበውም ሕዝብ ቁጥር ይጨምራል»

ቃሪያውን ብቻውን አነሳችና ለመብላት ወደ አፏ አስጠጋች:: ከተቀመጠችበት ተነሳችና ቃሪያውን ከቁሚ ጥላው ወደ መታጠቢያ ቤት ቸኮል እያለች ሄደች:: ራሴን ነቅንቄ ተከተልኳት......ስገባ ፊት መታጠቢያ ሳህኑ ላይ አቀረቅራለች:: ያስታወከችው ወይ የተፋችው ምራቅ ውሃ መሹለኪያ ብረት ላይ አደይ መስሎ ተለጥፏል......

«ምን ላውራ? የማወራው አስጠላኝ......ምን ላውራ?» አለች

ልደግፋት ወገቧን አቀፍኳት:: የደገፈኝ እጇ እንዳይለቃት ጠበቅ አድርጋ ያዘችኝ:: አፏን ከፍታ እያማጠች ወደ ሳህኑ አጎነበሰች:: ቋቅ ይላታል ግን የወጣ ነገር አልነበረም:: ትንሽ ደቂቃዎች ቆየችና አፏን ተጉመጥምጣ ወጣን::

ላበረታታት ካቀረበችው እንጀራ ትንሽ ቆረስኩና ክክ ወጥ አስነክቼ ጎረስኩ::

«ጥሩ ነው» አልኩ

«አላስኾንም» አለች ፊቷን አጎማዛ......

○

ፊቷ ላይ የመመረር ድባብ አለ። አይኖቿ ቅንድቦቿ ስር የተነፈሱ ኳሶች ይመስላሉ። ከንፈሮቿ ሎሚ እንደ መጠጠች ሁሉ ተሰብስበዋል። የአባቴ ኮትና ሸሚዝ ከተሰቀሉበት ወርደዋል። ለአስቤዛ ትናንት የተውኩላት ገንዘብ ጠረጴዛ ላይ ነው። 'ገበያ ለምን አልሄድሽም?' አላልኳትም። ብርድ ልብሶቿ አልቀዋል። የምትፈልገውን እንድትገዛ ነበር። ሲጀመር የሚያምር አረንጓዴ የነበረው ብርድ ልብሷ ቀለሙ ተለውጦ ጥቁር መሆን ብቻ ሳይሆን ባዘቶ ሆኖአል። ከሞዝቮልድ የገዛሁትን አንሶላ ማታ ከገበያ አምጥቼ ቢፌ ላይ እንዳስቀመጥኩት ነው። ያነሳው የለም። የአባቴ ኮትና ሸሚዝ ከግድግዳ ላይ ወርደው ጠረጴዛ ላይ ተጋድመዋል።

«ማን አወረደው?» አልኩ ወደ ኮቱ እያየሁ

«እኔ ነኝ» አለች። ያፈረች መሰለች። ስታፍር ፊቷ የሆነ ደስ የሚል ነገር አለው። ፊቷ ከቁጣና ጥርሱን ከነከሰ ንግግር ሌላ ምንም ሆኖ አይቼው ስለማላወቅ ይሆናል።

«ለምን አወረድሽው?» አልኳት

«ላራግፍ ስልጅዬ! አመድ ለበሰ እኮ። ጨርቆስ እኮ አቧራ ነው»

ዝም ብዬ ወደ መኝታ ቤቴ አልፌአት ልገባ ስል ጠራችኝ፡

«ትናንት በመንገድ ሳልፍ አንዷ የተናገረችው በጆሮዬ ገብቶ እስከ አሁን ሲከነክነኝ። መሳደቧ እኮ ነው። አንዱን 'አንተ ሂትለር!' አለችው። በአገሬ ክፉ ጠፍቶ ጀርመን አሄዳለሁ? ደደብ ናት። ራሷን ያላወቀች፣ ያልደረሰባት። ሂትለር ምን አደረገኝ? ሂትለር ለእኔ ውብ ነው። ግራዚያኒ ይሻለኛል። እሱስ ምን በደለኝ? ባዕድ አይደሉ እንዴ? አብረውኝ አልበሉ አብረውኝ አልጠጡ። አብረውኝ ባንዲራ ይዘው አልተንጠለጠሉ። እንጀራ ከቆሎ ሕብስት ከአንባሻ ሽሮ ከክክ አልተሻሙኝ። ሂትለር ብሎ ነገር። እነዚህ ጀርሞች፣ እነዚህ መርዞች ቆመህ በወገንህ መሳቂያ ያደርጉሃል። ለምን ትስቃላችሁ? ብትል አይገባቸውም፡ አህያ ምን ይገባዋል? አህያን ብትገለብጠው፣ ብትጠብሰው፣ ብታለብሰው፣ ብታስተምረው፣ ብታበጥረውና ብታሰክረው ያው አህያ ነው። ለምን ይስቃሉ? እጠይቃለሁ። አህዮች ሆይ ለምን ትስቃላችሁ? ትዳሬ ፍቅሬ በመፍረሱ? አየህ! እኔ ላይ የሠፈረው ጀርም እስኪይዛቸው ነው። እሱ እንዲደርስባቸው እፀልያለሁ፣ ቢገባቸው። ቤቴን እያፈረሱ ያልገባኝ መስሏቸው አፍጥጠው 'ቤቱ እንየው' ብለው ይመጡና ስለ ዲሞክራሲ ጥሩነት፣ ስለ መንግሥቱ ሃይለማርያም መጥፎነት ያወሩኛል። ማነህ አንተ? እላለሁ። ማነህ አንተ? ማነህ አንተስ? መለኪያዬ ረቂቅ አይደለም አየህ። ከባድ ነው ማን። ቤቴን እያፈረሱ ንጉሥ ያማሉ። አወናካሪዎች። ሌላም ስራ አልነበራቸውም። ማወናከር። አንዳንዴ ሳጠባህ ውትቴ ከደረቴ ሲፈስ ይመርህ ነበር? ትንሽ አልጎመዘዘህም? ይመስለኛል ነበር የእኔን

ኅምዛዛነት የምትጠባ። ይሄን ሳስታውስ አንጀቴ ስፍስፍ ይልብኛል። ጡቴ ያለ እማአስጥል[56] መሮ የነበረ ይመስለኛል። ነክቶሃል አንተንም። አይገርመኝም ብሩህነቱን በመጥፎነቱ የሚለካ የዛገ ተልካሻ ትውልድ በረሃብ ተያይዞ ቢያልቅ። ውሸቴን አይደለም። በእኔ አንድ ባል የቀኑ ሌላ ሃብት ቢኖረኝማ ምን ያደርጉኛል? 'እሳት ነህ አንተ' 'እሱ ፍቅረስላሴ ሆሆ እሳት እኮ ነው' ይባባላሉ። አፈር ድሜ እሳት። ከረፈፍ አንኅለ ቢስ ሁሉ። እንዲሁ በተራብ አገር ለትንሽ ምቾት ሲባላና ሲያባላ እንደ ማንም እየበላና እየኮሰ ይሞታል። እንደ ማንም አልቀናውም እንደ ተባለ ዜጋ ጥቁር አፈርና ነጭ ድንጋይ ይለብሳል። ይኼ ልጄ ታደሰ ቀላል አይደለም። በዚህች በእኔ የሕይወት ቀዳዳ ብትገባ አገርህን ታገኛታለህ። ከባድ ፍልስፍና የለውም ልጄ። እሱ ከገባህ ሁሉ ይገባሃል። ተጠንቀቅ......»

ቁና ቁና እየተነፈሰች ከተቀመጠችበት ተነሳች። እንደምትታጠብ ሁሉ ፊቷን ላገች። አፏ ዳርና ዳር የምራቅ ቆበር አለ። የምታደርገው ስለ ጠፋት አካባቢዋን አየች። ጎኔ መጥታ ተቀመጠችና እጄን ያዘችኝ።

«ይሄ የአፍሪካ ቀንድ ጅል ይሄ አንኮ፣ በእኔ እበልጥ በእኔ እበልጥ እየተገፋፈጠ የሚጠፋ ነው። አንዳንዴ ከደም ሳይሆን ከንፍጥ የተሰሩ ይመስለኛል። እየህ ብትበጣቸው ቀይ ደም ሳይሆን ሞራ የመሰለ ንፍጥ ነው የሚወጣቸው። ከዚህ የበለጠ ሊሆኑ አይችሉም። ላም ሳር ሊግጥ ውሻ ቆሞ ሊሸና እነዚህ ደ'ሞ እያበላሹ እንዲጠፉ የተሰሩ የታሪክ አንከሊሶች ናቸው። ታዲያ ፖለቲካ ያወሩኛል መጥተው። ደርግ ምንትሴ፣ መንግሥቱ ቀባጥሴ። ቂልሽን ፈልጊ። ሞቴን በኩራት እጠብቃለሁ። ግልግል ከነሱ። 'ሞተች' አይባልም 'ተገላገለች' ነው። ቢቻል ሬሳዬ እዚህች እነሱ የቆሙባት መሬት ውስጥ ባይሆን። የሆነ ብቻ ሩቅ ቦታ ብቀበር፣ ለቅሶም ባይደርሱ እወዳለሁ። 'ቀብሬ እንዳትደርሱ' የሚል ደብዳቤ አሁን ብፅፍ ደስ ይለኛል፡ ምክንያቱም እኔ ቲያትር መስሪያ ፕሮፕ[57] አልሆንም። በሕልሜም በዕውኔም ወደዚህ ዓይነት መማረር የምመጣ አልመሰለኝም ነበር። እንዲህ ዐይነት ሕይወት ምድር ላይ ያለ አይመስለኝም ነበር። ቀሚሴን ገልበው በመራራ ሕይወት ቂጤን ቸብ አደረጉት......ሂሂሂ የሚያቃጥል ዐይነት። እስከ አሁን እንደ እሳት የሚያቃጥለኝ ቸብ......ቆሞም ሞቶም......ቆሞም ሞቶም......»

ፊቴን አልፎ አልፎ እየዳበሰች......አንዳንዴ እጄን (የቀኝ ወይም የግራውን) እጆቿ መሃል አስቀምጣ ፍትህ ከዚያ እንደሚፈልቅላት ሁሉ እያሸች፣ ከሻሸዋ እስር ያመለጡትን የሽበት ዘለላዎች ቦታቸው ለመመለስ እየሰበሰበች፣ በአመልካች ጣቷና በአውራ ጣቷ አፍንጫዋን እየመዘለገች፣ እየተናፈጠች......ጣቶቿ ላይ የተጣበቁትን የንፍጥ ሐረጎች ያገኘችው ነገር ላይ እየሞዠቀች......ዓይኖቿም ፈጠውና በዕንባ ሰሌዳ ታውረው......የተጠበሰ የመሰለ የፊቷ ቆዳ በሚያሳዝንና በሚያስፈራ መልክ ወዝዞ......

---

56 የናትን ጡት የሚያስጥል መራራ ቅጠል(አ)

57 መድረክ ላይ የሚቀመጥ የተዋንያን መገልገያ ዕቃ። ጠቃሚ ባይሆን እንኳን የተዋናዩን ገፀ-ባሕርይ የሚያብራራ ደጋፊ ቁስ። ለብቻው ራሱን ያልሆነ ነገር።

*(ቻብ2፡ ከመ ሃሙራቢ)*

ከአምስት ዓመት የዩንቨርሲቲ ትምህርት በኋላ በሕግ ትምህርት የኤል ኤል ቢ ዲግሪዬን በማዕረግ አግኝቼ ተመርቄ ስወጣ የየቀኑ ኑሮአችንን የሚያውገረግሩ ማሕበራዊ ችግሮችን በቀላሉ የምፈታ መስሎኝ ነበር:: በከፍተኛው ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ ሆኜ ስሰራ 'ወንጀል' እና 'ምስክርነት' ስለ ተባሉት ጉዳዮች ብዙ ፈተሸኩ:: ተከሳሾችን 'ተረጋገጠ' በተባለ የምስክርነት ጦር አገላብጬ ወጋሁ:: ባዘገመ ሂደት የተረዳሁትና የተገለፀልኝ አስፈሪ ሁኔታ ቢኖር ከዕውነት ቀድሞ መተማመን/እምነት መኖሩ ነበር:: እንዴት ከተጨበጠ 'ሳይንሳዊ' መረጃ የበለጠ ሰዎች መተማመንን ያምኑታል? ለምን ብሎ ውሸትንም ሆነ ዕውነትን በመተማመን ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ብቻ ደጋግፈን እንቀበላቸዋለን? በስራዬ ጉዞ የተገነዘብኩት ነገር፣ *ዕውነት* በቀላሉ እጃችን መዳፍ ውስጥ መጥታ ተደላድላ አለማረፏን ነው:: ተንጋለው የሚያናውዙ ስነፎች ጭን ላይ እንደ ድመት ተስባ መጥታ አለመቀመጧን ነው:: 'ዕውነት የታካቾች አይደለችም' የሚባለው ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? በምስክርነት መረጃ ተመርቼ እስር ቤት የከተትኳቸው አንዳንድ 'ወንጀለኛ' የተሰኙ ሰዎች በኋላ በኋላ በእርግጥ ወንጀለኛ መሆናቸውን ተጠራጠርኩ:: ከዚህ በመነሳት የአባቴና የእናቴ የአለመግባባት መነሻና ይሄም አለመግባባት ያደረሰው ጉዳት ቀላል ጉዳይ ሊሆን ይችላል ብዬ ገመትኩ:: በመጀመሪያ መተማመንን ከመረጃነት ክልል አወጣሁት:: የእናቴን እሮሮ ተጠራጠርኩ:: አሳዛኝ ማሳመኛ ለቅሶዋን በጥያቄ አጠርኩት፣ ከርቀትም ይዘቱን በጥያቄ እየጎነታተልኩ መልስ ለማግኘት ጣርኩ::

እናቴ፡ 'ያጣሉን ሰዎች ዕቅዳቸው ከፍቅረስላሴ እጅ ወጥቼ ማንም የሚሻማበት የልጅነት ቁንጅናዬን ማንም አልጋ ላይ እንድጥል፣ እንድባልግ ነበር:: ያ አይሆንም:: እነሱ እሱን ትቼ አግድም በሚስጥር ወዳዘጋጁልኝ ወንዶች እንድሄድ ነበር:: እቅዳቸው በመሳካቱ ከሚደሰቱ ብቻዬን እሞታታለሁ' ስትል እልኋ ቢሆንስ? እልኋ ነው እንጂ አባቴ ገና ሲጀመር ከልቡ አምኖ እንደ መጨረሻ ፍቅረኛው እንዳልተቀበላት ጠርጥራ እንደሆንስ? ከእሷ ይልቅ ምናልባት አባቴ የልኳንዳ ቤት ሥጋ፣ ቢራ፣ ጠጅና የጠጅ ቤት እምቡቲቶ (ገንዘቡ ሲያልቅ ሰፈራችን ያለ ዝነኛዋ አቦል ጠጅ ቤት ይሄዳል) መውደዱ አስከፍቷት ከሆነስ? ልቧን የሰበረውና ከርካፋ ያደረጋት ያ ያልነገረችኝ ዕውነት ነው ብል ከትክክለኛነት ብዙ የምርቅ አልመሰለኝም::

እናትነቷን አምኜ ወይም በሌላ ጨዋ ባልሆነ አባባል እናትነቷ 'ደልሎኝ' እሷ ያለችኝን ባለማመኔና በመጠርጠሬ የደረስኩበት፣ ግን እሷ ደፍራ ያልነገረችኝ በትንሹም ቅር ያሰኘኝ ዕውነት ይሄ ሳይሆን አልቀረም አልኩ:: ሙሉ በሙሉ ቢዋደዱ ደስተኛ ነበርኩ:: እሱ ቢወዳትም እዛ የመውደዱ ዕምብርት ውስጥ ገና ከመጀመሪያው ልብ ያላላት ቢልም/ወይም የናቃት እሷም ያላየቻት የመጠራጠር ዕንቁላል ነበረች--'ወዳጆቹ' በተባሉት ሰዎች ቀላል 'ወንዴ' አሉባልታ እስከትደቀል:: ተደቅላ ወጥታ ጆፌ ሆና ክንፏን እያማታች የሁላችንንም ሕይወት እስከትበጠብጥ:: እናቴ 'መጥፎ' ያለቻቸው ሰዎች ያደረጉት ነገር ቢኖር አባቴ

ውስጥ ያለውን እንከሳነት ተጠቅመው ጠልፈው መጣል ነው:: ላጋነውና አባቴን ጠልፎ የጣለው አባቴ ራሱ ሊሆን ይችላል:: የእሱ መበላሸት ምናልባት 'ወዳጆቹ' የተባሉትን ሰዎች እንደ ኳስ ጨዋታ አዝናንቷቸው ይሆናል:: ምናልባትም በእርግጥ መቶ በመቶ እናትና አባቴ የተፋቀሩ መስሏቸው በቅናት ወላጆቼ ላይ የዘሩባቸው ክርክሬሻ ይሆናል:: የሁለቱም ውድቀታቸው መነሻ ያልተሟላ ፍቅር የነበረ ከሆነስ? አስገራሚው ጉዳይ እናቴ ሁኔታው ውስጥ እያለች በቂ መረጃዎችን ሰብስባ አባቴ እንደሚወዳት ወይ እንደማይወዳት ማረጋገጥ ስትችል አረጋግጣም የሚበጃትን ማድረግ ሲገባት ቸል ግን አለች:: 'ፍቅር ዕውር ነው' ይባል የለ:: ግን ሁለቱም ለምን በስህተት አይጠረጠሩም? አባቴ እናቴን ተሳስቶ እንዳገባት ሲረዳ በብስጭት ጠጪ መሆኑ ትክክለኛ የባሕርይ ለውጥ ምርጫ ነበረ? እሷስ ለመመደብ የሚያስቸግር አፍቃሪና እግረኛነት የተመሳቀሉባት ልጃገረድ ከነበረችስ? እናም ይኼ ፀባይዋ አባቴን ሞዛዛ ተጠራጣሪ ካደረገውስ?

ዕውነት የሚባለው ነገር ከምናየው፣ ከማናየው፣ ከምናምንበትና ከማናምንበት የተቀመመ መሆኑን መረዳት የሚያስፈራራ፣ በትንሹም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር አለው:: አይደለ? በማንፈልገው 'ተበዳይነታችን' ውስጥ ባናወራውም የራሳችን ተሳትፎ ይኖርበታል:: ምንም ብንክድ አወዳደቃችን ውስጥ የኛ ሃሳብ በማይታይ መልክ አፍሮ ተቀምጦአል ('እዚህ ምን አደርጋለሁ?' እያለ):: ሌሎች ድርጊት ውስጥ ያለው ማጥፊያ ሴራ በእኛ የታበየ የቂሎች ሳቅና ድጋፍ የታጀበ መሆኑን እንስተዋለን:: እና ይሄ አጠራጣሪ 'የራስ ቦታ' ትክክለኛውን መልስ እንዳያገኙ ወላጆቼን አስሮ ይዟቸው እንደ ነበርስ?

እናቴ ዕድሜዋ፣ (ልጅ እንኳን ነበረች) ብሶቷና መገለሏ አዳክመዋት ስለደረስኩበት ዕውነት (ቢያንስ እኔ እንደ መሰለኝ) ቀድሞ ልጅ እያለሁ ብዙ ነገር ሳልረዳ የነገረችኝን የአመፃ ኡኡታዎቿን ቅር እንዳይላትና ስሜቷን እንዳልጎዳው በማለት ጥርጣሬዬንና ጥያቄዎችን አንስቼባት ተከራክሬአት አላውቅም:: ቁጭቷና ተስፋ መቁረጧ ከደም ስሯ ጋር ተገንብቶ ነበር:: ሕይወቷ ነበር::

እንድ ቀን የተጠራጣሪነት አቋሜን የለወጠው ሁኔታ ተፈፀመ::

የጥብቅና ስራዬን በጀመርኩ በሦስተኛው ዓመት ላይ አንድ ማታ ከስራ ስገባ አልጋዋ ላይ፣ ጋቢዋን እስከ ትከሻዋ ደርባ የአባቴን ፎቶግራፍ አቅፋ ለዘለዓለም እንቀላፍታ አገኘኋት:: የገፅዋ ደም፣ ስጋና ስብ በቀስም የተመጠጠ ይመስላል:: ይሄም ሆኖ ወዝ ነበራት:: ወደ ፊቷ ስጠጋ የኒቪያ ቅባት ሽተተኝ:: ስትደበር የምገዛላት የልብወለድ መፃሕፍት ሁልጊዜ እንደ ሚሆነው ከመደርደሪያቸው ወርደው ገፃቸው ተከፋፍቶ ግራና ቀኝ፣ ላይና ታች፣ ከፊሎቹ አልጋ ላይ፣ ከፊሎቹ መሬት ላይ ተበታትነዋል:: ፊት ለፊቴ ጠረጴዛ ላይ እሷና አባቴ በሙሽርነታቸው ጊዜ ተቃቅፈው እየሳቁ የተነሱት እጅግ የሚያምር በተስፋ የተሞላ ፎቶ አለ:: ያልተጠናቀቀው ዕንቡጥ ያ ነበር:: የቬሎዋ ንጣት፣ የክረቫቱ ንጣት፣ የጥርሶቻቸው ንጣት፣ የሱፉ ጥቁረት፣ የፀጉራቸው ጥቁረት፣ እሷ ደ'ሞ ከሆነ ነገር እንደምትሸሽ ሁሉ ደረቱን ተጠግታው ትስቃለች:: እንዲህ አልጋ ላይ እንደማያት የምታልቅ አትመስልም:: ለመጀመሪያ ጊዜ

ያን ቀን (የጨቅላነቴ ጊዜ ሳይቆጠር) ቀርቤ ያቀፉኝን፣ ያጎረሱኝን ጣቶቿን አየኋቸው:: ቀርቤ ነካኋቸው:: የጣቶቿ ጫፎች በታይፒስትነቷ ሰበብ እንደ ድንጋይ ከራራ ነበሩ:: ወዝ አልነበራቸውም፣ ፊቷ ሞታም ያዘነ ይመስላል (ሁሌ ያዘነ ፊት እንደነበራት ትዝ አለኝ)፣ ወደ ጎን ወደ መሬት የምታይ ይመስላል (መሞቷ ያሳፈራት ዐይነት)፣ ግራ እጇ ከጋቢው ወጥቶ አየር ላይ አምላክን እንደሚለማመጥ የገረጣ መዳፉን ወደ ሰማይ አድርጎ:: የደረበችውን ጋቢ ከላይዋ ሳነሳ ከስር የሙሽራነቷን ቬሎ ቀሚስና ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ አይ የነበረውን የአባቴን ኮትና ሸሚዝ እንደለበሰች አየሁ:: ሁሉንም በስርዐት ለብሳለች:: ነጭና ጥቁር አዝሙድ ፀጉሯን ታጥባ ተጎንጉናለች:: ጉንጉኗን ሳምኩት፣ ከግንባሯ ከፍ ብዬ:: እንዲህ ተጠንቅቃ አታውቅም:: ወጣት መሰለች:: በእነዚህ የውሰት ጨርቆችና (አንዱ ከራሷ፣ ሌላው ከፍቅረኛዋ ልጅነት) የሙት ፀጥታዋ ውስጥ እናቴ ቆራጥ መሆንዋን አየሁ:: ከዚህ የበለጠ ስር ነቀል ነገር አለ? ፈራኋት:: ሬሳዋን ሳየው ከሌላ ጊዜ የበለጠ ደስተኛና የተዝናናች መሰለችኝ:: ለአፍታ በዝርዝር አቅዳ ራሷን ያጠፋች መሰለኝ:: ጭንቅላቴን ደረቷ ላይ አድርጌ ልቤ እስኪችል አለቀስኩ:: ሞትን በሚገርም መልክ ጣፋጭ የሚያደርጉ ሽረኞች ምን ያህል የሚገርሙ ናቸው?

ይሄ ሁሉ ነገር በእርግጥ ልቤን መታው:: ከዛ አዲስ ጎዳና የከፈተልኝን የመጀመሪያ ጥያቄዬን ጠየቅሁ:: እንዲህ: ምናልባትም ልክ እንደ ጣቶቿ ምግብ አብስለውና የኪቦርድ ፊደል ጠቅጥቀው እንዳሳደጉኝ እንደነሱ እሷም ልብ ውስጥ እስከዛን ጊዜ ድረስ ያላየሁት፣ ያልገባኝ፣ ያልተረዳሁት፣ ተጠየቅ የጋረደኝ፣ ነገር ነበር እንዴ?

አሟሟቷ እንደተበደለች ነገረኝ:: ባትሞት ኖሮስ? አንድን ዕውነት ለመረዳት፣ ለማመን በሞት ጎዳና ማለፍ አስፈላጊ ነው? ሳትሞት ዕውነተኛነቷን ማረጋገጥ እንዴት ተሳነኝ? እማማ ብቻዋን እንደ ነበረች ገባኝ:: የምሰማት እኔ ብቻ ከነበርኩና እየሰማኋት ካላመንኳት፣ ከዛ የበለጠ ብቸኝነት አለ? እንድደርስላት አልነበረ ልፋቷ:: ይሄ ሲመነዘር፣ በድፍረት ቢመነዘር እማማን ብቸኛ አድርጌ እንደ ገደልኳት አያስቆጥረኝም? ፎቶዋን እየዳበስኩ እንድትምረኝ እለምናለሁ:: እዛች የመቃብሯ ድንጋይ ውስጥ ፎቶዋ ተቀብሮ ሳይ አንዳንዴ የአዲስአባ እናቶች በሙሉ እንደ እሷ እየተከዱ ሳይታመኑ የሞቱ ይመስለኛል::

አባትና እናቴ በጋራ ስለኖሩበትና ይሸሹት ስለነበረ ስህተታቸው ስጠቅስና 'መከራከሪያዎቼን' ስናገር፣ እነዚህ መከራከሪያዎቼ የራሴ ስህተቶች እንደሆኑ ተገነዘብኩ:: ማረጋገጫዬ የት ነበር? ግምቶቼን በስሜት ተናገርኳቸውና፣ በሕግ ጠቢብነቴ፣ በተጠየቅ፣ በጥያቄና በተጠራጣሪነት አጀብኳቸውና ምን ይሁን? ትክክለኛነቴ በመረጃ እርዳታ ተገልፆ ነበር? ልጇ ሆንኩና የሞተችበትን ምክንያት በትክክል አውቃለሁ ማለትስ ነው? እንደ ገጣሚው ደበበስ ከዘመኗ ተኳርፋ[58] ብል ፍፁም ትክክል ነው? ከመሞቷ በፊት ያለኝ እሷን የምጠራጠርባቸው መረጃዎች ምን ያህል አስተማማኝ ናቸው? ሌላውን ሳይሆን ራሴን በድፍረት ተጠራጠርኩ......እንግዳ አድራሻ ነበር......

---

58 ለምን ሞተ ቢሉ (1968)
'ለምን ሞተ ቢሉ/ ንገሩ ለሁሉ/ ሳትደብቁ ከቶ/ ከዘመን ተኳርፎ/ ከዘመን ተጣልቶ' ደበበ ሰይፉ የብርሃን ፍቅር ቅፅ 2

ይኼ ሁሉ ገጠመኝ (የእናቴና የሁሉ ነገር) ሕይወት በተወሰኑ የስሜት ሕዋሳት መዝጋቢነት መረዳት የምትከብድ[59] የተሰራችባቸው እያንዳንዷ ነጠላ ነገሮችና ጉዳዮች ተቀርበው መታየትና መጠናት ያለባቸው መሆኑን ተረዳሁ:: ይሄ ከባድ ነው:: ማንም ስለጠንኩ የሚል የሰው ልጅ በየትም አለም ያደረገው አይመስለኝም:: ቢያንስ ወደ ጠቅላላ ዕውነት የሚያቀርብ እርካታ ፍለጋ ወደ ግጥም ንባብና ወደ በሰለ ኪነት ማጋደል የጀመርኩት ከዚያ በኋላ ነው:: ከያኒ ሳይሆን ኪነት ማድነቅ የጀመርኩት:: ይኼም እንኳን በሚስጢር ነበር:: ይኼ ሚስጥርነት አንደኛው ግንዛቤዬ ነበር:: ግጥም ልውደድ ብል ግራ ጉዳይ አይደለም:: ብዙ የሚወዱ ሰዎች አሉ፣ ግን ለምን በሚስጢር ወደድኩ?

---

59 አራተኛ አመት እያለሁ ረዳት ፕሮፌሰር ሰላም ነህ ሙሉዬ የተባሉ አስተማሪያችን ከከርቸሌ እስር ቤት ተለቀው እንደወጡ አንድ ኮርስ ላይ እንድንወያይበት ያቀረቡት የጥናት ወረቀት ላይ ያለው ሃሳብ ትዝ ብሎኝ፣ ወረቀቱን እቤት ያለኝ የትምህርት ቤት ፋይሌ ውስጥ ፈልጌ አገኘሁትና አንድ ሁለቴ አነበብኩት:: የጥናት ወረቀቱ 'ፍፁም መረጃ አለ?(Total information)፣ ከእስር ቤት ወደ ሕግ ቤት' የሚባል ባለ ሃያ ዘጠኝ ገፅ የግል ታሪካቸውን ያካተተ በከፊል የራሳቸውን ልምድ ለመመርመር ያቀረቡት ዘገባ ነው:: በመጀመሪያ ጥቂት ገፆች ላይ ስለ ሃሳባዊነት(subjectivism)፣ ስለ ኪነታዊ ዕውቀት፣ ስለ ካንት፣ ስለ አፍላጦን፣ ስለ መረጃ (evidence) ስለማረጋገጥ ጥቅንጥቆች(problems of verification) ወዘተ ሲያስነብቡን ቆይተው ከዚህ የሚከተለውን እየቆየ ራሴንም ወደ ተጠራጣሪዎች ሰልፍ የከተተኝን ሃሳብ ያስቀምጣሉ:
«......ስለ አሽራውያን ሰምታችኋል? ስለዚህ ነገር የሰማሁት እስር ቤት ነው:: አሽራውያን የተባለው ቃል የተፈጠረው በሰዐሊው መስከት ገረሱ ነው:: የተፈጠረበት ጊዜ ከአብዮቱ በፊት ነው:: ያን ጊዜ ተፈጥሮ እስከዛሬ ይኼን ቃል ያላወቅንበት ምክንያት ብዙ ነው:: ይኼን በዚህ አጭር ወረቀት ውስጥ ለማብራራት ጊዜ አይኖረኝም:: ግን ስለ አሽራ ትርጉሙን ከተናገርኩ የመልሱ ቦታ ብዙ የሚርቅ አይሆንም:: መስኩት ሲጀምር የአብስትራክት ኤክስፕረሺንዝም ተከታይ ሰዐሊ ነበር:: ለምን እንዲህ እንደሆነ አነበብኩት መፅሐፉ ውስጥ አይነግረንም:: (መስከት ገረሱ የሰውር ጉንዳኖች ሰልፍ፡ ስለ ስዕልና ስለ ማሕበራዊ ዕውነታ ጥቂት ማስታወሻዎች 1967):: በእሱ አባባል በአንድ የግል ልምዱ በመቀስቀስ ('ግል' የምትለዋ ቃል አስፈላጊ ናት እዚህ) ተነካናኪነት ወደ ሚለው አመለካከት ተሰማርቷል:: ተነካናኪ በእሱ አባባል ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጣውን መረጃ በመጠቀም ዕውነታን በስዕል ማቅረብ ማለት ነው:: ('ከየትኛውም አቅጣጫ' አስፈላጊ ቃል ነው):: የእሱ ተጻራሪዎች (በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዐሊዎች ሊሆኑ ነው፣ ብዙ ደራሲዎችም ይሆናሉ) እሱ አሽራውያን የሚላቸው የሚሰሩት ግን አንድን ክስተት እንድንረዳው ከሚያደርጉን አስር የመረጃ ቅንጣቶች መሃል እንዲመቻቸው አድርገው (የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የተጠየቅ አገልግሎት የሚሰጣቸውን) አንዱን ብቻ መርጠው በማውጣት የአስተሳሰብ ስርዐት ለማዋቀር የሚጥሩ ናቸው::(አንድ ሲል ከአንድ በላይና ከአስር ያነሰ ማለቱ ነው) ይሄ በስታቲስቲካል ሳይንስስ (statistical sciences) ሳምፕል(sample) ወይም 'ናሙና' የሚሉት አይደለም:: መስከት የሚያነሳው ሆን ተብሎ አስሩ መረጃ ('ሆን ተብሎ' አስፈላጊ ቃል ነው) እንዳለ እያወቅን አንዱን ብቻ እንደ ታላቅ ወካይ ጉዳይ አንስተን ስንሚዘዝ ነው ይላል:: አንድ ነገር ብዙ ነገሮችን አይገልፅም:: ጥረት ይኖራል ግን አይገልፅም:: እንዲህ ማድረግ ግን በመስከት አባባል አሽራዊነት ነው:: ይሄን አባባሉን ከያኒዎች እንዴት እንደተቀበሉት እንርሳና (እንዳለም የሚያውቁ ዛሬ ያሉ አይመስለኝም) መከራከሪያ ሃሳቡን መጀመሪያ ከስነዕውቀት ጋር፣ ቀጥለን ከወንጀል ምርመራ ከዚያም በተከታታይ ከቅጣትና ከምስክርነት ጋር አሽራዊነትና ተነካናኪነት ምን ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል፣ ካላቸውም ከነዚህ ግኑኝነቶች ምን ጉዳትና ጥቅም እንደምናተርፍ እናያለን.......' ሰላም ነህ ሙሉ (ረ.ፕሮፌሰር) ፍፁም መረጃ አለ? ከእስር ቤት ወደ ሕግ ቤት Department paper የሕግ ፋኩልቲ 1984

ሁድርስቶች በደራሲ ይፃፋሉ።

ሉይኼ/ይኸቺ ደራሲ ሕብረተሰባችን ውስጥ ነው ያለው/ያለችው።

በፖለቲካ፣ በኃሳ፣ በዕውቀት፣ በጉራና በ'እኔ እበልጣለሁ' የተከፋፈለ ኅታታ እናቴ እንዳለችኝ 'ነገረኛ ሕብረተሰብ' ውስጥ አንድን ደራሲ ከማን ጋር እንደ ቦደነ ሳያውቀ (ቦድኖ አልቦድኖ እንደሆነ በመጀመሪያ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው) በግልፅ በአደባባይ ማቆላመጥ ጠላትን ሊያበዛው ይችላል። እሳት ወይ አበባን ለሰው አድንቄ ብናገር በዚህ አቋሜ ማን ይቀጣኛል? የደበበ ሰይፉን ግጥሞች አድንቄ ብናገር እነማን ያሴሩብኛል? በዐሉ ግርማን ባቆላምጥ ማን ይቆራርጠኛል? ባለቀ ሬድዮ ባትሪ ድንጋይ የተጣሉ፣ ተጣልተውም የተጋደሉ በዚህም መነሾ ፍርድ ቤት የቀረቡ እንዳሉ አውቃለሁ። በአለቀ ባትሪ የተጣሉና የተጋደሉ በሌላ ነገር ያቅታቸዋል? ብዙ አይቼአለሁ። ብዙ የታወቁና የተማሩ ባልረባ ጉዳይ ላይ ከጀርባ ቡድን ይዘው ሲካሰሱና ሲባሉ አይቼአለሁ......በማር ጠብታ ውስጥ ስለ ሰጠሙ ሕዝቦችም አንብቤአለሁ[60]።

አንዳንዴ እናቴን ሳልጠግባት በተለይ እሷ እንዳለችኝ ተጨዋችነቷን ሳላየው፣ ከአንጀቷ ተንተክትካ ስትስቅ ሳላዳምጣት (ትዝ ይለኛል ደ'ሞ አንዳንዴ ባልገባኝ ምክንያት ወይም ቢገባኝም ያስቃል ብዬ ባልገመትኩት ነገር ፍርፍር ብላ ስትስቅ......ረዥም ፊቷ ተስተካክለው በበቀሉ ነጭ ጥርሶቿ ሲከፈት...... ይሄን ሕዋችን ላይ የተዘረጋውን ወተትማ መንገድ ለወር አጥግባ ማስተናገድ የምትችል ይመስለኝ ነበር። አንዳንዴ እያነበብኩ ወይ እየበላሁ ሳለሁ በዝምታ አተኩራ አይታ ፊቴን ዳብሳ እንደ ቁጣ ኅተት አድርጋ አፌን የምትስመኝ። ከንፈሮቿ ሁልጊዜ እንደ ስኳር የሚጣፍጡኝ እንደ ቡና የሚሸቱኝ ነበሩ። ዛሬ ዛሬ እንኳን ከዛ ትንሽ ከመሰለ ግን ረቂቅ ድርጊቷ ተዋርዶ እንደመጣ ውርስ የምጠጣው ስኳር የበዛባት ጥቁር ቡና ነው) ከዚህች አለም ማለፏ ይቆጨኛል።

○

ቆሜም ተኝቼም በትክክል የተደሰተች እናቴን ሳላያት ከዚህ ምድር ያገለሉና የቀነሱ ('መግደል' ማለት ሰውን ከምድር ላይ መቀነስ ማለት ነው)

---

60 ከደራሲ ከበደ ሚካኤል መፅሐፍ ከዕውቀት ብልጭታ)። በዚህ በከበደ ሚካኤል የምክር መፅሐፍ ውስጥ የሰፈረ አንድ ታሪክ አለ። ታሪኩ እንዲህ ነው፡ አንድ አዳኝ ውሻውን አስከትሎ ለአደን ይወጣል። ይቀናውና የገደል ማር አግኝቶ እሱን ቆርጦ ይመጣል። ውሻውን እንዳስከተለ ማሩን ሊሸጥ ገበያ ይወጣል። ገበያ ማር ነጋዴ ጋ ሄዶ ዋጋ ሲከራከር ከተሸከመው ማር አንዲት ጠብታ መሬት ትወድቃለች። ይህቺን ጠብታ ያየች አንዲት ወፍ ልትቀስም በራ መጥታ መሬት ከማረፏ የማር ነጋዴው ድመት ዘላ ቀጨም ታደርጋታለች። ድመቷን ያየው የአዳኙ ውሻ በተራው እመር ይልና ድመቷን ይቀረጥፋል። የድመቷን መቀርጠፍ ያየው የማር ነጋዴ በመበሳጨት ጠመንጃውን ይመዝና የአዳኙን ውሻ ተኩሶ ይገለዋል። አዳኙ በውሻው መገደል ተናዶ ጠመንጃውን አቀባብሎ ነጋዴውን እንካ ቅመስ ይለዋል። ነጋዴው ይሞታል። ነጋዴው መሞቱን ያዩ የነጋዴው ዘመዶች ተጠራርተው መጡና አዳኙን ተኩሰ ገጠሙ። የዚህ መታኮስ ወሬ አዳኙ አገር ደጋ ያኔውኑ ይሰማና ዘመዶቹ ታጥቀው ገበያው ወዳለበት ከተማ ወርደው ነጋዴው ዘመዶች ላይ ይተኩሳሉ። በዚህ ዓይነት የሁለት አገር ሰዎች ትልቅ ጦርነት ይጀምራሉ።

ሰዎች ያለመቀጣታቸው ያበሽቀኛል፣ ያሳስበኛል:: አንዳንዴ በወንጀለኛ መቅጫ የሰፈሩ ግን በመረጃ ማረጋገጥ የማይቻሉ በደሎች ሰዎች ላይ በሴራ ይሰራሉ:: መረጃው ከተገኘ ደ'ሞ ተስተካካይ ያልሆነ ነገር ለተበዳዮች ይፈረዳል:: በዚህ በኩል ሕጋችን ፍርደ-ገምድል ነው:: አስገራሚነቱ ብዙዎቻችን ሳንከራከር በዚህ ስህተት ማመናችን ነው:: የመቅጣት ቲዮሪ[61] አንደኛው ረድፍ እንደ ኢማኑኤል ካንት ሬትሪቡቲቭዝም (retributivism) ነው:: ይኼም አጥፊውን በጥፋቱ ልክና ዓይነት ቅጣ ማድረግ አስፈላጊ መሆን እንዳለበት የሚጠቁም ነው::[62] እዚህ በጨርቆስ ከተማ ደንብ ደ'ሞ 'ቅጣ ሲያደርጉህ መልሰህ ቅጣ አድርግ' (ቅጣን በቅጣ) ይባላል:: ይሄ በላቲን ሌክስ ታሊኦኒስ ወይም በቀጥታ ትርጉሙ የብድር በምድር ሕግ ይባላል፣ በዕብራይስጥ ደ'ሞ ሚዳ ከነገድ ሚዳ ይባላል:: ኦሪት ዘፀዓት 'ነፍስ በነፍስ፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር፣ መቃጠል በመቃጠል፣ ቁስል በቁስል፣ ግርፋት በግርፋት ይከፈል'[63] ወይም ኦሪት ዘዳግም 'ነፍስ በነፍስ፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር ይመለሳል' የሚሉት ነው[64]:: ይኼን ብድር ለምድር መቅጣቀጣ አዲስ ኪዳን አንዱ የቀኝ ጉንጭህን ቢመታህ የግራውን አዙረህ ስጥ ብሎ ይሽረዋል:: አንዳንዴ ስለ ጥንታዊው የባቢሎኑ ንጉሥ ሐሙራቢ[65] ሳስብ በአጠቃላይ አገሩን ያስተዳድርበት የነበረው ሕግና የፍርዱ ቀጥተኛነት ዝባዝንኬ ባለማብዛቱ ይመስጠኛል:: በአሁን ዘመን የሌላ ሰው ዓይን ያጠፋ ወንጀለኛ ሰው በገንዘብና በእስር ቅጣቱን ይቀበላል::

ለመሆኑ ዐይንና ገንዘብ የሚለዋወጡበትን ሂሳብ ማን ይሰራዋል? ከአንድ ጤነኛ ዐይን የማገኘው ደስታ ምን ያህል ብር ያወጣል? ትክክል ልውውጥ መሆኑን በምን እንለካለን? በየአገሩ ብቻ ሳይሆን በየዳኛው ዓይነት የተለያየ ፍርድ አይኖርም? ሐሙራቢ 'ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ' ብሎ ሲወስን እጅግ ትክክለኛ ፍትህ ይመስላል:: ሆን ብሎ አንድ ዓይኔን ያጠፋ በገንዘብ ቢቀጣ ቀጥሎ ዕውር መሆኔን ተመኝቶ የቀረችዋን ዓይኔን 'ገንዘብ ከፍዬ ማጥፋት እችላለሁ' ብሎ እንዲያስብ አያደርገውም? እናቴ ምሥራቅ ሙያዬ ዳኝነት የሆነ ልጇ ቆሜ እየሄድኩ ተበድላ ያለ ፍትሕ ስትሞት አየሁ አይደል?

ሌላው ብዙ ጊዜ የሚዘነጋው ነገር በመረጃ መልክ በአሃዝም ይሁን በስሜት ሕዋሳት ሊያዙ የማይችሉ ወንጀሎች መሰራታቸው ነው:: ምስክሮች፣

61 Theory of punishment(አ)

62 The critic of practical reason ॥ ክሪቲክ ኦፍ ፕራክቲካል ሪዝን(1788)(ኢማኑኤል ካንት)(አ)

63 ኦሪት ዘፀአት 21: 22-25(አ)

64 ኦሪት ዘዳግም 19:21(አ)

65 የባቢሎን ንጉስ 1810–1750 ከክል በፊት የኖረ:: 282 የሚደርሱ ሕጎች ያወጣ(አ) በ1915 ኤም ኤል ደብሊው ኪንግ የተረጎመው የሐሙራቢ ሕግ ውስጥ ያሉ ስስቱ ከዶች የሚገልፁት ይሄንኑ ነው: 196ኛ ኮድ/ሕግ(አንድ ሰው የሌላውን ሰው ዐይን ቢያጠፋ የራሱም ዐይን ትጠፋለች)፣ 197ኛ ኮድ/ሕግ(አንድ ሰው የሌላውን ሰው ወርች ቢሰብር የራሱም እንዲሰበር ይሆናል)፣ 200ኛ ኮድ/ሕግ(አንድ ሰው የሌላውን ሰው ጥርስ ቢያወልቅ የራሱም ጥርስ እንዲወልቅ ይሆናል)

መተማመኖች እዚህ ዐይነት ሁኔታ ላይ ሲደርሱ ትርጉም ያጣሉ:: ማለት ሕግ እንደ ራዳር ቢሆን ከዛ ራዳር ስር ጨለማ ጨለማውን ብዙ ወንጀሎች ይሰራሉ:: አባቴ ለምን እንደ ሞተ ሲያወሩ የማያቁት ሰዎች ሁሉ አፋቸውን ሳይዛቸው: 'ሚስቱ ስታበሳጨው መጠጣት ጀመረ፣ ከዛ ብዙ ሳይቆይ አልኮል ገደለው' ይላሉ:: የመረጃ መውገርገር የሚያሳየን የአባቴ አጥፊዎች ያላቸው ማህበራዊ መረብ ሰፊ እንደ ነበረ ብቻ አይደለም:: የአባቴን አሟሟት ከስሩ ለመመለስ ጥረት እናድርግ ቢባል የምንጠቀምበትን መረጃ ለማግኘት እጅግ አዳጋች ብቻ ሳይሆን አስተማማኝም እንዳልሆነም ነው:: የአባቴና የእናቴ ታሪክ እንደ ቫይረስ በሚያደርጋቸው የፈጠራ መረጃዎች ተበርዟል:: እንዲህ ነው: ወንጀል ከመሰራቱ በፊት የነበረው ኩነት ታሪክ ይባላል:: ኩነቶቹ የተገነቡበት መረጃዎች የተውገረገሩ ናቸው:: ለራዳሩ የሚታዩት እነዚህ ወንካላዎቹ ናቸው:: ለራዳሩ የሚታየው እነዚህ ወንካላ መረጃዎች ለስነው የሰሩት ውግርግር ታሪኩ ነው:: ታሪክ ያውገረገረም ተጠያቂ ነው:: መረጃዎችን ለማውገርገርና ታሪክን አሳስቶ ለማቅረብ (የግለሰብ እንኳን ቢሆን) ትልቅ የተደራጀ ስራ ይጠይቃል:: ይሄ የሚያሳየው የእነዚህ ወንጀሎች መሰረታዊ ፀባይ በብዙ ዓይነት ሰዎች ተሳትፎ በተለያየ መጠንና ስልት መሰራታቸው ነው::

ግን እንዲህ ዐይነት ከራዳር ስር ሰው ማሳደድ ተደጋጋሚ ከሆነ፣ በእኔ ግምት ብዙ የተማረሩ ዜጎች በመፍጠር ቤተሰብን ብቻ ሳይሆን አገርንም ማፍረስ የሚቻል ይመስለኛል:: እንደው ለመሆኑ የእናቴና የአባቴ ፍቅር በዚህ ዓይነት ዘዴ መፈራረሱ አገር አይጎዳም? እናቴ 'በእኔ የሕይወት ቀዳዳ ብትገባ አገርህን ታገኛታለህ' ስትል ይሄን ማለቷ ነበር እንዴ? አገር መናድና ሰላም ማደፍረስ የሚፈልጉ ሰዎች ተደራጅተው በዚህ ዓይነት ስልት ብዙ ግለሰቦችን ካለሙት ግብ እንዳይደርሱ አድርገው ማበሳጨት አይችሉም? የእነዚህ ግለሰቦችስ መበሳጨት ለአገሪቷ እድገት የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ አያስናክለውም? መንፈሳቸውንስ አደፍርሶ ተስፋ አያስቆርጣቸውም? ለሁላችንስ ያስቡ የነበሩትን ሰዎች የተማረሩ ግለኞች አያደርጋቸውም? 'ያገባናል' የሚሉትን ሰዎች 'ምን አገባኝ' እንዲሉ አያደርጋቸውም? ይሄ ባይሆን በምሬት 'የመጣው ይምጣ' ብለው ከሁሉ ለመራቅ ከአገር ሊሰደዱ አይችሉም? መሰደዳቸውንስ አንዳንድ ፖለቲከኞች (ራሳቸው አባራሪዎቹም ሊሆኑ ይችላሉ) 'ዲሞክራሲ በመጥፋቱ ነው' ብለው በመንግስት ሊያመሃኙ አይችሉም? እንበል እንዲህ ዓይነቱ የማስተጓጎል ኪነት ቢቀናበርና ለረዥም ጊዜ ቢሰራበት ብዙ ግለሰቦችን የግል ችግር በመሰለ ነገር ነጥሎ በማውጣት አፍዞና አደንዝዞ የአገር ሕልውናን ማውገርገር አይቻልም? ብሎስ አገርን ከካርታ ላይ በቀላሉ በራሳቸው በዜጎቹ ምሬት መሰረዝ ሊፈፀም አይችልም? በየቀኑ የምናያቸው አልባሌ የመሰሉት ቅናትና ምቀኝነት (የኤቲክስ[66] ፈላስፎች ማስተር ኢሞሽንስ[67] ይሏቸዋል) ረቀቅ ባለ ስልት ስማቸው ግን ሳይጠራ በሆነ ቁም ነገር በመሰለ የፖለቲካ አጀንዳ ስር ቢዋቀሩስ? ቢዘገይም አገር ማጥፊያ ሞተር እንዲሆኑ ቢቀመሩስ? እናቴ እየተራገመች መሞቷ ምናልባት ምንም ማድረግ ካለመቻሏ ጋር የተያያዘ ሆኖ ይሆን? ውድ ፍትህ ካልተገኘ በርካሽ

66 ethics

67 master emotions=ቀንደኛ ስሜቶች(እንግሊዘኛ)(አ)

አቅመ ቢስ እርግማኗና ፍልስፍናዋ ለመገላገል?

እናትና አባቴን ያለያዩ ቤተሰቤን ያፈረሱ (ያለ እህት ያለ ወንድም ያስቀሩ) ወደፊት እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳያደርጉ ቢያንስ ለመቀጣጫ አጥፊዎቹን ስካራም በማድረግ፣ ከሚስቶቻቸው ጋር በማጣላት፣ ከልጆቻቸው በማሸሸ ፍርድ መስጠት አይቻልም? ልክ አባቴ እንዳረፈ ወደ ጠላለፉት ሰዎች፣ ዳኞችና ፖሊሶችን ልኮ በማስገደድ ወደ አደባባይ አውጥቶ ሕዝብ እየታዘበ፣ እንደ አባቴ ሰባራ ጠርሙስ ላይ ራሳቸውን ጥለው እንዲሞቱ ማድረግ ቢቻል ኖሮ እንደማለት::

እናቴን አንድ ጊዜ ከማለፏ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ (ምናልባት አንድ አመት በፊት) ፍቅረስላሴ ከሕይወቷ በመቀነሱ ምን እንደ ቀረባት ለማወቅ (ወንድ ቢጠፋ ወንድ ሞልቶ በሚል ግንዛቤ):

«አባዬን ስታፈቅሪ አብረሽው ምን ማድረግ ትፈልጊ ነበር? ምን ትመኚ ነበር?» ብዬ ስጠይቃት:

«ኡሀኡሀኡሀአሁአሁ......ይሄ ሳል ሲጋራ የማጤስ አስመሰለኝ አይደል?... ቀላል ነበር:: በጣም ቀላል:: አንድ የምወዳት ነጭ ቀሚስ ነበረችኝ፤ እሷን ለብሼ ከኬክ ቤት(ብርቅ ነበር ያን ጊዜ) እሱ ሲወጣ እኔ ልገባ ስል ከጓደኞቼ ጋር ሦስት ነበርን ልክ በሩ ጋ ሳየው......እዚህ ልቤን መታኝ......የማላመልጠው ነበር:: ያኔውኑ ጓደኞቼ እንኳን አስጠሉኝ:: ሌላ ሰው አስጠላኝ:: ልቤ ግብት አለ:: ያን ቀን ማታ ቤቴ ገብቼ ሙሉ ምሽት ሳስበው ነበር:: አልጋዬ ላይ በጀርባዬ ተኝቼ ፈዝዤአለሁ፣ ዝም ብዬአለሁ:: ባሌ ይሆንና የማስበው ምን ነበር መሰለህ? አንዲት ትንሽ ቤት ትኖረናለች፣ ትልቅ አይደለችም......ሦስት ክፍል......በቃ:: ጀርባዋ በፀሐይ መጥለቂያ ይሆናል:: እኔ በዛች ነጭ ቀሚሴ እሱ የሚያምር ክንድ ነበረው በካናቴራ እንሆንና ጎን ለጎን ተቃቅፈን......እ...... ተቃቅፈን ኡኡአአአሁአሁአሁ......ተቃቅፈን አብረን ፀሐይ ስትጠልቅ ማየት...... ለአንድ ቀን አይደለም......በቃ ቁጭ ብለን ለዘላለም:: መወለድህ ትዝ የሚልህ ስታፈቅር ነው:: በጣም ሲከፋህም ትዝ የሚልህ መወለድህ ነው:: የመጀመሪያው እንዳትሞት፣ የሁለተኛው ቶሎ ለመገላገል:: አንድ ነገር በሕይወቴ አድርጌአለሁ:: እርግጠኛ ነኝ:: ባይረባም አንድ ሰው ወድጄ ነበር:: አቤት አዲስ አባን እንዳ ወደድኳት! መሬቷን በርከክ ብዬ መሳም ነው የቀረኝ:: ሃብት አልፈለኩም:: እሱ አብሮኝ ካለ ምን እንደምበላ ትዝ ብሎኝ አያውቅም፤ ይኼው አላህ ምስክሬ ነው:: እሱን ለማስደነቅ ሹመትና ዶክተርነት ሌላ ምናምን አልነበረም:: ሺህ ዶክተር ብትሆን የሚያያይዝህ ፍቅር ከሌለ ሜዳ ላይ የምትቀሩት አንተ፣ መድሃኒት፣ ገንዘብና ጀርም ናችሁ:: እሱን እሱን ስል ሁሉ ነገር አለቀ:: ለባሌ ዳንስ ትምህርት ሃንጋሪ መሄድ እችል ነበር:: አልሄድኩም:: ቂል ነኝ? እዚሁ ከእሱ ጋር......ኡኡኡ......እጅ ለእጅ ሆነን በቃ ሽበት በሽበት መሆን ማንንም አይጎዳም:: ይጎዳል? ኡኡኡኡህ?»

እንዲህ ብላ የበረደ ቡናዋን አንስታ በዝምታ አየችኝ:: ግንባሯ የበለዘ ይመስላል:: የከንፈሮቿ ክብደት ግን ሁሌም የማይረግፍ ግርማ አለው:: አይኗ እንደ ቡችላ አይኖች ትልቅና ለስላሳ ናቸው:: በፍርሃት ይቀለጨለጫሉ::

ከመንገድ በተከፈተ የሳሎን በር እየሾለከ የድሮ ዘፈን ወደ ተቀመጥንበት ተረጋግቶ ይመጣል:: ዞር አለች:: አይኖቿን ወደ በር ወርውራ ከንፈሮቿን መጠጠች:: ፀጉሯ ፊቷ ዙርያ ባልተበጠረ ግድ የለሽ ስልት ተንዠርግጓል......ገፅዋ ላይ ብዙ ጥላ እንደ ጥቁር ደም ይፈሳል......

እነሆ! እንስቲቱ!

* * * * *

በቀዝቃዛ ገለልተኛነቴ(ይኼም በእናቴ ተፅዕኖ የተፈጠረ) ጥቂት ዓመታትን በብቅ ጥልቅ ብቸኝነት እንዳሳለፍኩ አንድ ሰሞን የስራ ባልደረባዬ ወንድም በመኪና አደጋ ሞቶ ለቅሶ ስደርስ ዛሬ ትታኝ ከሄደችው ከባለቤቴ ከሎሚሽታ ጋር ተዋወቅን:: ፍቅር የመሰለ ነገር ወይም የዕውነት ፍቅር ያዘኝ:: እርግጠኛ ግን አልነበርኩም:: ሁለመናዬን ግን አልሰጠኋትም:: ሁለመናዬን ጠቅልዬ እንዳልሰጠሁ የማውቀው እኔ ብቻ ነበርኩ:: የምትፈልገውን ሁሉ ሳላንገራገር አደርግላታለሁ:: 'ስራ መሄድ አስጠላኝ' ስትለኝ ሁሉ ግራ ነገር ቢሆንም የቤት እመቤት እንድትሆን ፈቀድኩላት:: አብዛኛውን ጊዜ በምንኖርበት አለም መውደዳችን የሚገመገመው ለሴቶቻችን በምናደርገው ስጦታና ቦርሳቸው ውስጥ በምንጠቀጥቀው የገንዘብ ብዛት በመሆኑ የልቦናዬን ትክክለኛ ስፍራ ሊያጠና የተገፋፋ ሰው አልነበረም:: ግን ጥያቄዋና ፍላጎቷ እየሰፋና እየበዛ መጥቶ አንዲት ቀን እንኳን ማዕድ ላይ "በስመአብ" ብላ የማታውቀው ሎሚ 'ቤተክርስቲያን እስማለሁና አጃቢ ቅጠርልኝ' አለችኝ:: አልተከራከርኳትም:: ግን ውስጤ አድፍጦ የተቀመጠው የጥርጣሬ አውሬ የሚበላው እንዳገኘ ሁሉ እያዛጋ ተነሳ::

አንዲት የማርያም ፈረስ የተባለች ተንቀሳቃሽ ከወዳጇ ጋር ሩካቤ ካደረገች በኋላ ዞር ብላ ጭንቅላቱን ከአንገቱ ላይ ቆርጣ ትበላዋለች:: ግን ወንዴው የማርያም ፈረስ ያለው ይሄ በእንስቷ የተበላው አንጎል/ጭንቅላት ብቻ አይደለም:: ወንዴ የማርያም ፈረስ በጠቅላላ ገላው ሁለትና ከሁለት በላይ አንጎሎች አሉት:: አንደኛው ጭንቅላቱ ውስጥ ያለው ነው:: በአካል ግዝፈት የምትበልጠው ሴቷ አንዱን አንጎል ቀርጥፋ ከበላችው በኋላ አይሞትም:: ሌላ አንጎሉን በመጠቀም በሕይወት መኖሩን ይቀጥላል:: ይሄ ለእኔ ሁኔታ ልዋጭ ሊሆን ይችላል::

የሎሚሽታን ተንኮል ሳይ የጠበቃነት ሁለተኛው ደመ-ነፍሴ መከላከያ ድርጊቱን ማቀናበር ጀመረ:: 'አጃቢ ቅጠርልኝ' ካለች በኋላ ከስራ እየቀረሁ ባልጠረጠረችኝ ጊዜና ቦታ ሰለልኳት:: ከማን ጋር እንደ ዋለች አየሁ:: ተረጋግቼ፣ ሳልበሳጭ፣ የተበለጥኩ ወይም የተታለልኩ ሳይመስለኝ ስትወጣና ስትወርድ አየኋት:: እያንዳንዷን ገጠመኝ ማስታወሻዬ ውስጥ በዝርዝር አሠፈርኩ:: ማን እንደ ሆነች አጠናኋት:: ከሕግ ራዳር ስር በሕቡዕ የሚሰራውን በሕቡዕ ማጥናት ስለ ሚያስፈልግም ነው:: ትክክለኛ ፍትሕ እንዳይኖር ከሚያደርጉት እንቅፋቶች ዋነኛው የትክክለኛ መረጃ አለመገኘት ነው:: አሰስኳት:: የምትረግጠውን ረገጥኩ::

ባለፈችበት አለፍኩ......

ምን ጎድሎባታል?

ምንም::[68]

ስለምን እኔን ትታ በጎዳና ላይ ተጠቃቅሳ ሲመሽ ሲመሽ እየተበለሻሸች መጣች?

አላውቅም::

የማውቀው ነገር በሁለታችን መሃል ያለው ግኙኝነት እንደ ቆመ ነበር:: እኔ ቤተክርስቲያን አንድ ቀን አብሬአት ሄጄ ራቅ ብዬ ስቆም አስናቀ የተባለው ጎረምሳ ወዳጇ አጠገቧ ሴት መስሎ መጥቶ (ብልጥ መሆኑ ነው? ጠበቃ በመሆኔ ከእሱ የበለጡ ዱርዬ ወንጀለኞች በየፍርድ ቤቱ እንዳየሁ አይገባውም?) ሲቆም እኔጋም ተጠግቶ ሲያሾፍብኝ ምን የሚያስቅ አለው?

እኔ ብዋረድ ለእሷ የሚተርፋት ቁም ነገር ምንድነው?[69] ግን የመራቅ ድርጊቷን ባልገባት ግን በረቀቀ መንገድ ራሴ እየደገፍኩ እልህ ሁሉ ገብታ ፈጥና እንድትሄድልኝ ገፋፋኋት:: የድሮ ፀባዬን አለወጥኩም ማለት አልገባኝም ማለቴ ይመስላት ነበር:: አስናቀ ከተባለው ሰውዬ ቤት ደርሳ ስትመለስ እንዳልገባው አቅፌ ደባብሼ ግን ከገላዬ እየተቃለድኩ አግልዬአት......ስራ ያደከመኝ መሰዬ:: ራቀች:: እሷም ራቀች:: በመጨረሻ በዚያው ቀረች......

አስቤ በስሜት ተገፋፍቼ ልበ-ሸርሙጣ ሳገባና የሚጎዳኝ ውዥንብር ሕይወቴ ውስጥ ሳስገባ ሐላፊነቱም የሎሚ ነበር:: እኔ በደካማነቴ በፍቺ ውስጥ ማለፍ ነበረብኝ:: አንዱ ቅጣቴ ነው:: በደስታ እቀበለዋለሁ:: ለጥቂት ቀናትም ወይም ወራት ለእኔ ብቻ ከመሰለችኝ ሴት ጋር በመተኛት በሽታ ሰብስቤም ይሆናል:: ሁለተኛው ጥፋቴ ይሆናል:: ይኼንንም ቅጣት ሳልከራከር እቀበላለሁ:: ግን እሷስ? ግን እሷ ከባሕርይዋ ጋር ተከታትሎ የሚመጣ ቅጣት እንዳለ ካልተረዳች የማያባራ ጥፋት ልታደርስ አይደለ? አርጅታ ፍላቷ በርዶ በወንዶች ተንቃ የሚችላት የምትችለው አንዱ ጅል ላይ እስካልተለጠፈች? በቀል አይደለም:: ትንሽ ሐሙራቢያዊ ቢሆን ነው::

---

68 አንዳንድ ሴቶች ባላቸውን ለምን እንደሚያታልሉ ሲጠየቁ: 'በወሲብ አልተስማማንም' ይላሉ:: እንዲህ የሚመልሱበት ምክንያቱ በሕግ ይሄ ነገር ለፍተሻ እንደማይቀርብ ስለሚያውቁ ነው:: ወሲብን በተመለከተ እስከተጠራጠርኳት ድረስ ሎሚ ሽታ በእኔ ያልተደሰተችበት ጊዜ እንዳልነበረ በየቀኑ አረጋግጬአለሁ:: ይሄ ችሎታዬንና በተፈጥሮ የታደልኩ መሆኔን ሰፊና የተለያየ ልምድ ያካበተችው ሸርሙጣዋ ወዳጄ ፀሐይ በእስር ጣቷ መፈረም ትችላለች::

69 *ፈሰሰ ወይ ፍቅሩ*
*ተረሳ ትዳሩ*
*የካብትሽ በካብቴ*
*በቃ ቁም ነገሩ?*
(እንደተባለው ነው)
(ደበበ ሰይፉ <u>ሔዋን ብቻ ለአዳም</u> የብርሃን ፍቅር ቅፅ 2 / 1982)

አዲሱ 'አስናቀ' የተባለ 'ባሏ' ስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት እንደሚሰራ ደረስኩበት:: አለቃውም አብሮኝ የተማረ የጠበቃ ጓደኛዬ ታላቅ ወንድም ነበር:: ከእሱ ጋር ተነጋገርንና በስልጣኑ ትንሽ እንዲባልግ ጠይቄው ለሦስት ወይም እንደ ሁኔታው ለስድስት ወር አስናቀ ክፍለ ሐገር ለስራ ተመድቦ እንዲሄድ አደረግሁ:: ቀላል ቀሚሷን ገለብ አድርጌ የምትኮራበት፣ ወንድ ይጀነጅናል የምትለው ቂጧ ላይ ከራዳር ስር የሰጠኋት ቸብታ ነበር:: በሁለት ሳምንት ውስጥ ሎሚሽታ ትሰራለች ብዬ የጠበቅኋትን ነገሮች ማድረግ ጀመረች::

እናቴ ወደ መራችኝ ሁሉን የመጥላት ጎዳና፣ ጓዜን ጠቅልዬ አልሸመጠጥ ኩም:: አሁን በሰላም በተረጋጋ መልክ ጎዳናውን ለሚታመን ፍቅር ራሴን ለመስጠት በእይኖቼ እዳብሳለሁ:: ትንሽ አብጣ የታመመች ነፍሴን ከፀሐይ ጋር በጂን ቶኒክ (ወሲቧ ለዘላለም ይኑር)፣ ወይም በግጥም እፅናናለሁ (ሁሉ አገርሽ እያነበበችልኝ)::

## እቴ ሜቴ ሎሚ ሽታ

አንድ ቀን ታደስ በማስታወሻ ላይ ዘርዝሮ የፃፈልኝን ራትና ምሳ ማዘጋጀቴን አጠናቅቄ (ቀይ ሽሮ ወጥ፣ ምንም ምንም ማለቴ ሽንኩርት ቅቤ ዘይት የሌለበት የበግ ጥብስ፣ ከነጥብቆው የተቀቀለ ድንች፣ በቅቤ የታሸ የጤፍ ጨጨብሳ፣ የሚታጠቡ ሁለት ሸሚዞች፣ የሚተኮስ አንድ የካኪ ሱሪ ወዘተ......) ለማረፍ ሶፋው ላይ ተቀመጥኩ:: በአንድ እጄ መፅሐፍ ይገኤለሁ:: የአንድ ግጥም ሁለት መስመሮች ካነበብኩ በኋላ......

*ፀሐይዋ ስትወጣ......*
*በድቅድቅ ጨለማ......*[70]

መፅሐፉን ወደ ጎን ወርውሬ ሁልጊዜ እንደማደርገው በጀርባዬ ተጋደምኩና ያሳለፍኳቸውን የጥቂት ዘመናት ይዘት እያወጣሁና እያወረድኩ፣ ሲቆጨኝ ራሴን እየሰደብኩ፣ ስደሰት ደ'ሞ ለራሴ እንደ ዕብድ ፈገግ እያልኩ ስዝናና ስልክ ተደወለ::

አንስቼ «ሃሎ» ስል ማን አጋጠመኝ?

......ሎሚ ሽታ!!

ለረዥም ጊዜ ስለባሏ(በትክክል ምን እንደምለው ስለማላውቅ ነው? ውሽማ? ባል? ውባል[71]?) ስለ አስናቀ መልካም መልካሙን ስታወራኝ ቆየችና በተማረረ ድምፅ:

«ሁሉዬ ነሽ? (ተቆላመጥኩ) ምን እያደረግሽ ነው? እዚያ ቤት እንደ ምትኖሪ ጠርጥሬአለሁ» ቆጣ ብላ በስተመጨረሻ ሁለቱ ቃላት ላይ:: ሳዳምጣት ቆየሁና ልቤ ከመቆሟ በፊት......

---

70 ከደበበ ሰይፉ ከ ላንቺ ለጨለማይቱ (1964) የተቀነጨበ(የብርሃን ፍቅር ቅፅ1)(አ)

71 ውባል: የባል ሚና የሚጫወት ውሽማ:: የጨርቆስ ክፍለ ከተማ ቃል::(አ)

«ምነው?» አልኳት ረጋ ብዬ ልክ የቤቱ እማ ወራ እንደ ሆንኩ ሁሉ......

ትንሽ ዝምታ ነበር:: የአፏ ቁጣ ለራሷ ጆሮ ተሰማት?

«እንዴ ያወራሽኝ ያቺ አለማያ ትማራለች ምናምን ያልሽኝ ጓደኛሽን ታስተዋውቂኛለሽ?»

አላማዋ አልጠፋኝም:: ነበርኩበት ዱሮ......ይኸቺ ዓይነት ትውውቅ ውስጥ::

«ደስ ካለሽ አስተዋውቅሻለሁ:: ግን ያስተዋዋቂ ይከፈለኛል» አልኩ ሳቅ ብዬ:: ፌዝ አስመስዬ::

«ምነው እስከዚህ?» አለች ትንሽ ለመሳቅ እየጣረች::

በፍጥነት አሰብኩ:: መጀመሪያ አስተዋውቄ ማያያዝ አለብኝ:: ሽርክናቸው ጦፍ ሲል 'ለአስናቀ ልነግርብሽ ነው' እላታለሁ:: በዚህ ቴክኒክ ጥሩ ገንዘብ አላጣም:: ጅል ይኑር እንዲኖረን እያልኩ::

«ውይ ቀላል አይደለም እንዴ? እንዳንቺ የነፃነት ስሜት ያላት ልጅ ናት:: ጣጣ ፈንጣጣ አትወድም» አልኳት::

('ጣጣ ፈንጣጣ' ደስ የሚሉ ቃላት አይደሉ? ቢበራዩ ከውስጣቸው አንድ ፍሬ ነገር ጠብ አይልም እኮ......ጣጣ......)

«ሂጂ?! ደስ ሲል:: ቤተክርስቲያን ለምን አብረን አንሄድም? እከፍልሻለሁ»

ተገኘቶ ነው:: ከፈለገችው ተላቃ ወደፈለገችው ትጣበቅ:: ምን አገባት ሁሉ አገርሽ? 'መስሎሻል' አልኩ በልቤ:: ገና ብዙ ቁም ነገር ባልተጠራቀመባት አንጎሌ ብር እየደመርኩ::

*ግንቦት 1987 ሆላንድ*

# በለስ[72]

ዛፏ......

ያረፈደ ጠዋት ነው:: ገነት ላይ ሌሊት የወረደው ጉም ግን ገና አልተነሳም:: እየተጥመለመለ አድራሻው ወደ ማይታወቅ አቅጣጫ የሚሰርበውን የግዮንን ወንዝ ተከትሎ ጥቁር አረንጓዴው ደን ላይ የተዘረጋው አመልማሎ የመሰለ ጉም ላይሰደድ፣ ላይተን፣ የትም ላይሄድ የማለ ይመስላል:: የወንዙ መነሻ በታላላቅ የሾላ፣ የዝግባና የጽድ ዛፎች በስፋት ተከቦአል:: ግራና ቀኙን በደማቅ ቅጥልጣይ የተሸፈኑ ደርባባ ኩረብታዎችና ተራራዎች አሉ:: ትልቁ ደብር ላይ ወጥቶ ለተመለከተ በስተግራ በኩል የግዮን ወንዝ በዝምታ የሚገባበትን ስፋቱን በዓይን መመተር የሚከብድ ትልቁን የፃናን ሐይቅ ያያል:: ወንዙ ወደ ሐይቁ ከሚገባበት ስፍራ ጀምሮ የዐይን እግር እስከሚደርስበት እርቀት የሐይቁን ደርዝ ከፈፍ ያቀፈው ጭጋግ የተተበተበባቸው የአረንጓዴ ተራሮች ሰልፍ ነው:: እያረፈደ ሲሄድ ወንዙን ተከትሎ ከሚወርደው በአየር ላይ ከተንጠለጠለው ሰፊ የጉም ጎዳና ብዙው ተኖ ረፋድ ላይ የሚቀረው እየተጥመለመለ የሚወርደውን ግዮንን የሙጥኝ ያለ እንደ ሰንቁ የሚፈልቅ ካፊያ ተደግፎ የሚያልፈው ቀጭን የጥጥ መቀነት ነው:: ከርቀት ደ'ሞ በሁሉም አቅጣጫ መልኩ የማይለይ አጎበር የወደቀበት የመሰለ ለመሰወር የሚያሽቃብጥ አድማስ አለ:: ሰማዩ ላይ መልካቸው የተለያየ፣ የሚያማምሩ እንግዳ ወፎች ወዲያ ወዲህ ይበሩበታል:: እነዚህም የክንፋቸው ስፋት የሚያደናግር፣ የላባቸው የቀለም ሕብር የሚያፈዝ ነው::

---

72 ይኼ ልብወለድ 'የጤፍ እንጀራ ፍርፍር' ሴማ ሆኖ ከተሰሩ በአንድ ጥራዝ ሊታተሙ ታቅደው ከነበረ አንድ ረዥም ልብወለድ፣ ሦስት አጫጭር ታሪኮችና አንድ ኖቬላ ተነጥሎ በዚህ መድብል የቀረበ ነው::(ደ)

ከግዮን ወንዝ መነሻ ብዙም ሳይርቅ ቀጭን ጢስ ወደ ሰማይ ይነሳል። ይኼን ጢስ አየር ላይ ከተዘረጋው ጉም የሚለየው የአረጋጉ ፍጥነትና ዕድሜ ነው። እያረፈደ፣ ፀሐይ እያቀናች ስትሔድ ወንዙን የሚከተል የሚመስለው ጉም ይተንና እየተቻኰለ ከመሬት የሚያርገው ይሄ ስስ ወተትማ ጢስ ብቻ ይቀራል። አንዳንድ ቀን ከሰማይ መሃል ወደ ምድር ወተት የሚንዠረዠር ይመስላል። ጢሱ የሚነሳበት ስፍራ በአረንጓዴ፣ በቢጫ፣ በሐምራዊ፣ በቀይ፣ በሌሎችም ቀለማት ሕብር ውስጥ የተነከረ ነው። ጠቅላላ የደኑ ላይና ታች በወፎችና በአራዊት ቅዳሴ አብዶአል። ከነዚህ ሁሉ መሳጭ ተክሎችና እነሁላይ የተፈጥሮ ጣዕመ ዜማዎች ዘልቃ የምትታይ የሐመልማልና የቀለም ድምብል የመሰለች፣ የቅጠሎቿና የፍሬዎቿ ሕብረት ዐይንና ልብ የሚስብ ዛፍ አለች። ከሌሎቹ መለየቷን ለማሳየት ዐይነት ሳይሆን አይቀርም ዙሪያዋን በአትክልተኛ የተከረከመ የመሰለ ሪም አለ። ዛፏ ከላይ እስከታች ዐይን በሚማርኩ እና ጠረናቸው በሚመስጥ ፍሬዎች ከአመት ከአመት ትሸፋናለች። ከዚህች ዛፍ ፍሬዎች ግን ማንም በፍፁም ለቅሞ እንዳይበላ እግዜር በተባለ በዋናው ሐላፊ ተከልክሏል። ምድርና ሰማዩን የሞሉት አዕዋፋትና እንስሳት እንኳን በላይም ሆነ በታች በዛፏ አጠገብ ሲያልፉ ወይም ከሥሯ ከሚነሳው የሞቀ ውሐ ለመታጠብ ሲመጡና ሲሄዱ እንዳላዩአት ሁሉ ሆነው ነው። እላይዋ ላይ ቢያርፉ እንኳን ከውስጣቸው ፍሬውን ወግተው ወይም ነክሰው ጣዕሙን እንዲያዩ የሚገፋቸው ስሜት ወይም ጉጉት ከውስጥ እንደሚባለው ከውስጥ አልተፈጠረላቸውም።

ዛፏ ተካይ አላት። ተንከባካቢ አላት። የሚበላት ግን የለም። እርጅና የሌላት፣ ወጣትነት የሌላት አንድ ቀን ብቅ ባለችበት መልኳ ለረዥም ጊዜ የቆየች ናት። እዚህ ዛፏ የተተከለችበት አካባቢ እንደ አሸን ከፈሉት እንስሳትና አራዊት ሌላ ሁለት የሰው ፍጡራን ይኖራሉ። አንድ ሴትና አንድ ወንድ። ሴቷ ሔዋን። ወንዱ አዳም ይባላሉ። እዚህ ላለው ተፈጥሮ የበላይ ገዢዎች ሲሆኑ ከቁጥጥራቸው ውጭ እንድትሆን ሰፊ መብት የተሰጣት ብቸኛ ተክል ዛፏ ብቻ ናት። የበለስ ዛፍ ይሏታል። ብዙ ብዙ ዘመን አልፏል። ደፍሮ ሊበላት ቀርቶ ደፍሮ የነካት አልነበረም።

## ሔዋን......

ሔዋን ከእንቅልፏ ስትባንን አዳም እጉኗ የለም። በዚህ ሰሞን በተለይ ለሁለት ጠዋቶችና ለሁለት ምሽቶች ሊገልፁት በማይችሉበት ምክንያት ይጠፋፋሉ። ያው አጋጣሚ መሆን አለበት። ከተኛችበት ሣር ላይ ፊቷን እያበሰች፣ በተለይም ዐይኖቿን እየጠራረገች ተቀመጠችና ዙሪያዋን አየች። የለመደችው የንጋት ፀጥታ። ዙሪያዋን አጭር እንግጫና እንደ ላሁጫ ፀጉር የተለጠሰ ለስላሳ ሳር የለበሰ ሜዳ ነው። ትናንት ሲመሽ ከአንድ ነብር ጋር እዚህ ድረስ እየተጫወተች እንደመጣችና እሷ እዚሁ ተዳክማ ለማናወዝ ስታርፍ ነብሩ ሜዳውን ዘልቆ አንድ ትልቅ ዛፍ ላይ እንደወጣ ትዝ አላት። ሁልጊዜ ወደዚህ ስትመጣ የሚያጋጥማት ነብር ነው። ቀና ብላ ወደ ዛፉ አየች። ማንም የለም። በገነት ውስጥ በተፈለገው አቅጣጫ ያለምንም ችግር መመላለስ እንደምትችል ታውቃለች። የሎስ ተሳፍራ መብረር፣ በድብ፣ በጅብ፣ በአንበሶች፣ በአውራሪስ፣

በጎሽ ጀርባ ላይ መጋለብ፡፡ እያንባቀቀች ከተቀመጠችበት ለመነሳት ስትሞክር አልሆነላትም፡፡ እግሮቿን ቁርጥማት እንደያዛቸው ታወቃት፡፡ ገላዋን የሸፈነው ፀጉር በጤዛ ረጥቦአል፡፡ በዚህ ዐይነት ፀሐያማና ሞቃት ወር ያውም ሙሉ ጨረቃ በወጣችበት ሌሊት ብርድ ለምን ደጋግሞ እንደሚመታት ግራ የሚያጋባ ሀሳብ ውስጥ ከቷታል፡፡ ሁልጊዜ ባልታወቀ ምክንያት ጨፌ ጨፌውን እየመረጠች ማደርያ መምረጥዋ እንደሆነ ፈጥና አልተረዳችም፡፡ የሆነ እንስሳ ጀርባ ላይ ተቀምጣ ወደ ሙቅ ውሐው ኩሬ ለመሔድ ሊረዷት የሚችሉትን እንስሳት ስም ጠራች፡፡ የደረሰላት አልነበረም፡፡ እንስሶቹ አንዳንዴ ትዕዛዟን የመቀበል ግዴታ ቢኖርባቸው እንኳን ባልተረጋገጠ ምክንያት ወይ አይሰሙም ወይ እዚያ አካባቢ የሉም ወይ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ናቸው፡፡ ወይ በሚስጢር እግዜር እንዳይታዘዟቸው ነግሯቸው ይሆናል፡፡ ማን ያውቃል የዚያን ረቂቅ ጌታ ስራ፡፡

ቢቸግራት አዳምን ጠራችው፡፡ ጉሮሮዋ እስኪቆስል እስኪደክማት በጩኸት ጠራችው፡፡ ምናልባት አዳም ፀሐይ ለመሞቅ የማዮንን ወንዝ ተሻግሮ በምዕራብ በኩል ወደ ዛና ሐይቅ ሔዶ ይሆናል፡፡ የዚህ ሱስ አለበት፡፡ የትም ይዋል የትም ይደር ሁልጊዜ በመጀመሪያ ከሔዋን ጋር የተያዩበት ስፍራ ሄዶ በሆዱ ሳር ላይ ተኝቶ ቁርሱን አውጥ እየበላ ፀሐይ ይሞቃል፡፡ በሆዱ ተንበልብሎ ካልጠፋ መብል በባዶ ሆዱ በጠዋት አውጥ እየለቀመ ይበላል፡፡ ጨዋታ ሲያሰኘው ኮፍያ የመሰለ ቅርፊት የጫኑ ግዙፍ ቀንድ አውጣ ፈልጐ አግኝቶ ከእሱ ጋር ጎን ለጎን ሆኖ ሜዳ ለሜዳ ሲንከራተት ይውላል፡፡ ጓደኛው ሔዋን አበላሉን ይሁን አጨዋወቱን አትወደውም፡፡ የሚስማሙበት ጠዋት ቢኖር ጥሬ የጣያስ እንቁላል በልተው በፀጉራቸው ውስጥ የሚተራመሱትን የሚጎዱ ወይ የማይጎዱ ተባዮች እየለቀሙ ፀሐይ አብረው ሲሞቁ ነው፡፡

ሔዋን በቀስታ ቆመችና በብርድ የተቆራመተ አንድ እግሯን ለማሟሟቅ አራገፈች፡፡ ለማራገፍ ሞከረች፡፡ አንድ እግር እንኳን ለማራገፍ፣ ራሱ የሚራገፈው እግር መጠነኛ የጤነኛነት ደረጃ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ መሬት ላይ ተመልሳ ተቀምጣ ለአጭር ጊዜ ገላዋ ላይ የተኛውን ፀጉሯን ያበሰበሰውን ጤዛ መጥረግና እግሮቿን ማሻሸት ጀመረች፡፡ በሰማይ የሚበሩት ትናንሽ ወፎች ናቸው፡፡ ሲነጋ ሁልጊዜም እንዲህ ነው፡፡ እንደዚህ ጎሕ ሲቀድ የሚታዩት በራሪዎች ውብ ይሁኑ እንጂ መጠናቸው ትንሽ ነው፡፡ ታዲያ አዳም ወደ አለበት ተሸክሞ የሚወስዳት ፍጡር ፍለጋ ሰማዩን ለዕርዳታ ብትማትር የሚረባ ትልቅ ወፍ አላገኘችም፡፡ ገላዋን የሸፈነው በእርጥበት የተንጀላጀለው ፀጉር እንዲህ በቀላሉ የሚደርቅ አልመሰላትም፡፡ በተለይ ከብብቶቿና ከእግሮቿ መሐል እንደ ጅራት የወረደውን ዻሕማ ደጋግማ አልባውና ልጋው ቅዝቃዜውንና እርጥበቱን አልተወም፡፡ እንዲህ ሆና ማርፈዷ ነው፡፡ ዙሪያዋን ግን ሜዳው ላይ ተኝቶ የነበረው አመዳይ እየለቀቀ በልጣጣ ልግልግ አረንጓዴ ሣሮች እየታዩ ነው፡፡

**ጋንጩር......**

ታላቅነት ከታዛዥነት እንደማይበቅል ቀድሞ በማወቁ ነው ከዕሕረ አርያም በመብረቅ ተመቶ የወረደው፡፡ በሚረባ መሳሪያ አይደለም፡፡ በመብረቅ፡፡ ብርሐን መፍራቱ መታወቁ ነው ያስጠቃው፡፡ የውስጥ አዋቂ ነገር፡፡ የሚያምንበት ነገር

ግን በተፈለገ አቅጣጫ እሱ ከእግዜር አለማነሱ ነው። ነፋሳትን ያዛል። ውሐትን ያዛል። እሳት መኖሪያ ቤቱ ነው። በዚህ ምድር ላይ ሊገዛ የማይችልበት ቦታ የለም። እንዲህም በመሆኑ ነው በምቀኝነት ተገፍቶ የወጣው። በዚህ ስልት መዋረዱ ብቻ ሳይሆን ይባስ ብሎ እግዜር ከሁሉ ሥራው የሚኮራባቸው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ፍጡራንን በአምሳሉ ሰርቶ እዚህ የደን ጓዳ መደበቁና ከእሱ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ ማድረጉ ሰይጣንን ያበሽቀዋል። ሰይጣን ጠላቱ እግዜር ፍፁም ዓለም ፈጥሮ እንደማያውቅ ከረዥም ጊዜ የኑሮ ልምዱ ይረዳል። እነዚህም 'ሰው' የተባሉ ፍጡራን ፍፁም አለመሆናቸው ከሌሎች መላዕክት የበለጠ ይገባዋል። ሲጀመር የእግዜር ጓደኛው አገልጋዩና አማካሪው አልነበር? የጊዳ አዋቂ ነው። እግዜር እኒህ አዳምና ሔዋንን የማይጎልበት አትክልት ቦታ ውስጥ አስቀምጦ ጥያቄ የማይጠይቁ፣ የማያጉረመርሙ፣ ተቃራኒ ጉን የሌላቸውና የማይጋጭባቸው እንስሳት አስተኔዎች ፈጥሮ ፍፁም የሚታዘዝለት አለም አቀናብሮ ከልሏል። ይኼ ፍርሐት ነው። ሰይጣን ከቀድሞ ልምዱ እግዜር የረቀቀ ፈሪ እንደሆነ ያውቃል። ሰይጣንን ያስጨነቀው የእግዜር ፈሪ መሆንና ስልጣን መውደድ ሳይሆን የእግዜር ቀንደኛ ፍጡራን የተባሉት ሁለት ሰዎች ጉዳይ ነው። በእሱ ግምት እነዚህ ፍጡራን እግዜር በጨካኝነቱ የደበቀባቸውን የሚጣፍጥ ብዙ እውነት የማየት ዕድል አላገኙም። ለአሉባልታ ለአሉባልታውማ ፍፁም ሆነው ነው የተፈጠሩት። ከገነት ውጭ ባለው ዓለም ላይ ያሉ ኒፊሊሞችና የሰው ልጆች እንደሚያወሩት የግዮን ወንዝ መነሻ ላይ ሁለት በደስታ የሚኖሩ ፍጡራን እንዳሉ ነው። ተረቱ እንደዚያ ነው። እግዜር ያሰራጨው አሉባልታ የሚለው ይኼንን ነው። ሠይጣን ማንኛዋንም ዓይነት ተረት ሲሰማ ተረቷ ከየት እንደሆነች፣ የማን እንደሆነች ብዙም ሳይጨነቅ በቀላሉ ያውቃታል። ሲጀመር እግዜር ሰማይና ምድርን በቃሉ በሰይጣን አባባል 'በወሬ' ሲፈጥር እዛ ቀዝቃዛ ጨለማ ውስጥ ለሳምንታት የኪሩቤልን ዕጣን እያሸተተ አብሮት ሲንሳፈፍ አልነበር። ሠይጣን አቋርጦ በመጣው ሁለት ሰፊ አገር ላይ የሚነገረው ምድርና ሰማይን በገነባ አምላክ ምስል ሁለት ሰዎች መሰራታቸውን ነው። እነዚህም ሁለት ፍጡራን ከስህተት የተገለሉ፣ በደስታ የሚኖሩ ታዛገሮች መሆናቸው የሰይጣንን አንጀት አቃጥሎታል። እግዜር በምድር ላይ ስልጣኑ ገና ያልጠና መሆኑን ወደ ፊት ይኼን ችሎታውን እንደ ምሳሌ እየጠቀሰ ጉራ የሚነፋበት ድርጊቱ ይሆናል።

እግዜር ግን ማዘዝና ጌታ መሆን ቢወድም ተመርጦ እንዲወደድ ይፈልጋል። ለፈጠራቸው ሰዎች ምርጫ ሊሰጣቸው ይፈልጋል። ለተመልካች አምባገነን ቢመስልም የሚሰጠው ነፃነት ውስጥ የመምረጥ ፈተና መደባለቅ ይወዳል። ሠይጣን በራሱ አይቶታል። ይኼ ድክመት አለበት። መግዛት ብቻ ሳይሆን አስጨንቆ የመግዛት ድክመት አለበት። በዚህች በተወሳሰበች ምድር ላይ እንደ መምረጥ አስቸጋሪ ነገር አለ? ሠይጣን በዚህች በመልአክ በምትጠበቅ (የእሱን መላዕክት ፈርቶአቸው አያውቅም) የአትክልት ቦታ 'የበለስ ዛፍ' የምትባል ተክል እንዳለች ሰምቷል። እነዚያ ምስኪን ፍጡሮችም ከዚህች ዛፍ የሚበቅለውን ፍሬ ማየት እንጂ መብላት እንደማይፈቀድላቸው አረጋግጦአል። ሁሉን ነገር ሰጥቶ የዚህቺን አንድ ዛፍ ፍሬ መከልከል ምን ይባላል? የሰይጣን

የመጀመሪያ ጥያቄ ይኸቺ ነበረች......ለምን? ደብቆ ከፈጠራቸው በኋላ ስለዛፏ መኖር ሰዎቹ ካልተናገሩ ወሬውን ማን ወደ ውጭ አወጣው? መቼም ዐይን ከሌለ የሚታይ ነገር አይሠራም:: ሆድ ከሌለ የሚበላ ነገር አይፈጠርም:: ስለዚህ ሰይጣን በዚህ ፍፁም በሆነች ገነት ውስጥ አንድ የጐደለ ነገር እንዳለ ገባው:: የጐደለውን ነገር ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም:: እግዜር 'ፍጡሮቼ በእኔ አምሳል የተቀናበሩ ፍፁም ናቸው' ብሎ ጉራ ቢነፋም ነጭ ወሬ እንጂ ፍፁም እንዳልሆኑ ከበለስ ዛፍ እዚያች ገነት ውስጥ መተከል በቂ ግንዛቤ ማግኘት ችሏል:: ሰይጣንን ብልህ ያደረገውና በሰማይ ቤት ያስጠላው ከቃል[73] ይልቅ ድርጊት! የድርጊት ያለህ! ማለቱ ነው:: በቀላል አማርኛ ሆድ ሰርቶ፣ የሚበላ ፍሬ አበጅቶ፣ እነዚህን ጎን ለጎን አድርጎ፣ 'አትብሉ' ማለት ያ ፈተና ነው:: ወሬውስ በራሱ በአምላክ የተበተነው በተዘዋዋሪ እነዚህን ሰዎች የሚፈትን ከይሲ ፍለጋ ሊሆን አይችልም?

ሠይጣን በውስጠ ወይራ የተጋበዘ መሰለው:: ታዲያ ካልሆነ ሰዎቹን እንደ ፈጠራቸውና እዛው እንደ ዘጋባቸው በሰላም አይቀመጡም? የሚያምር ፍሬ አስቀምጦ 'አትብሉ' ብሎ ማለት እንደ ፈተና ነው:: ታዲያ እነዚህን የፈረደባቸውን ሁለት ሰዎች እግዜር ምን ሊፈትን ነው?

## ያቺ ዛር......

አ! እስታርቴ አ! ዛር! አ! ሶፍያ! ውብ ሶፍያ:: ተጊዥ፣ ሒያጅ፣ ሰጤ ዛር ሶፍያ:: ሠይጣንን እስከ አሁን የሚያበሽቀው እሷን ማጣቱ ነው:: ለአዳም ከሔዋን በፊት መጀመሪያ ለሚስትነት ወይም ለደባልነት የተመደበችለት ሴት ዛሯ ሶፍያ ነበረች:: የገነትን እድሞ የረበሸች:: የሰበረች:: ሰይጣን እንኳን ቢፈልግ ዳግመኛ በመብረቅ መጠለዙን ፈራ እንጂ እሷ ዛሬ ብትኖር በረዥም ፀጉሯ ውስጥ ወይ ገላዋ ላይ ባለ የተገኘ ቀዳዳ ተደብቆ መግባት ይችል ነበር:: ለጉጉት:: ለወሬ ጉጉት:: ገነት አምራው አይደለም:: አውሬ፣ ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ፣ ቅጠላቅጠልና ውሐ ፈሰሰበትና አንድ ቦታ ለሰይጣን ልዩ አይሆንም:: ልዩ የሆነበት በመታጠሩ ነው:: የገነት የአትክልት ቦታ በአራት አቅጣጫ በመላዕክት መጠበቁ ነው ያጓጓው:: ታች ከሐይቁ የደቡብ ጫፍ ከሚፈሰው የጢስ ፏፏቴ ላይ ሲያሻው ጢስ መስሎ፣ ሲያሻው ቀስተ ዳመና መስሎ፣ ሲያሻው በውሐ የታጠበ አለት መስሎ፣ የብርሐን ሰይፉን ሲፈልግ ሰውሮ ሲፈልግ በገሐድ እያንተገተገ የሚጠብቅ መልአክ አለ:: ሠይጣን ከሩቅ ሆኖ እያየ ይኼ ሁሉ የጥበቃ ጉድ እሱን ለማራቅ እንደሆነ ይገባዋል:: እዛ የቆመውን መልአክ ሰይጣን ድሮ ያውቀዋል:: ዕርሐ አርያም ለእግዚያብሔር ዙፋን አዳልቶ በእሱም ቦታ ተተክቶ ለመሾም ሲዋጋ የፍልሚያ ጥበቡ ያስቸግረው ነበር:: ክንፉን

---

73 ፊሊሞዎች አንድ ዘፈን አላቸው:: ይሄን ዘፈን ታዲያ በወደቀ ግንድ ብቻ አጅበው እሱን እየደበደቡ ይዘፍኑታል:: በእነሱ ባህል 'ግጥም' የሚባለው አንድ ትርጉም ብቻ የሚያስተላልፍ መንታ መስመሮች ያሉትና የኋልዮሽም የሚደግሙት ሲሆን ነው:

*ላሂ!ሆ!ቃልማ ቃል ነው......ላሂ!ሆ!*

*ሆ!ላሂ!ነው ቃል ቃልማ......ሆ!ላሂ!*

ሰይጣን 'የኪነት ቅንጣቱ ያልገባቸው የማይገባቸው እጅግ ደካማ ፍጡራን' ይላቸዋል:: ፊሊሞዎች ምንም እንኳን መዝፈን ባይችሉም በጥቅሻ የጊዜ እርዝመት ውቅያኖስ ማቋረጥ የሚችል በአየር ላይ የሚቀዝፍ ሰረገላ ወይም ጥየራ ነበራቸው::

ተመቶ ወደ ምድር ከመውደቁ በፊት ቆስሎ ሲንፏቀቅ ግን ሰይጣን የዚህና መሰሎቹ መላዕክት ጆሮዎች እስኪደነቁሩ ትኩር አድርጎ እያየው «ባርያ!» ብሎ ጮሆበታል:: ይኼ መልአክ ይኸቺን ስድብ ይረሳል? ቢረሳ እንዲህ እንቅልፍ አጥቶ እየተሰወረና እየተከሰተ ለምን ይጠብቃል? ዕድሜ ልኩን የእርሻ ቦታ ለመጠበቅ የማለ ከባሪያ ሌላ ምን ሊባል ነው? አልረሳም::

ሶፍያ አዳምን ጠዋት እንደተኛ ትታው ከገነት ወጥታ ዞራ ዞራ ትመለስ ነበር:: በኋላ በኋላ አላባሬ ያላትን የወሲብ ፍላጐቷን ራሷ ቦርቡራ ነው ያገኘችው:: ከሰይጣን ጋር ምድር ውላ፣ ከፈሊሞዎች ጋር ተዳርታ ተዳክማና ዝላ አጠገቡ መጥታ ስትወድቅ በመገረም ያያታል:: አዳም አልገባውም:: አዳም የማይወደው ድምፅዋን ነበር:: ድምፅዋ የቆቅ ነበር:: በኩባክኛዋ መሃል በረዓይትና በሰው ልጆች ቋንቋ የተበከለ ግዕዝዋን ስትናገር አዳም እተኛበት ይሰቀጥጠዋል:: ነውዝ ባሳሰረው አፉም: «የእኔ እመቤት ምነው ቋንቋሽን ባታበለሻሺው:: አልገባኝም እኮ:: ልተኛበት:: ስተኛ ካየሽኝ ሌላ ቦታ ሒደሽ ተኚ:: እሺ? እሺ የእኔ እመቤት?» ድምፅዋን ስለማይወደው ማዋራቱን ችላ ቢላትም እተጋደመበት ንጭንጭዋን ያዳምጣል:: ትናገራለች እንደ ኩባክ: «ምነ ምነ እኔ ስመጣ ነው እንቅልፍ የሚይዝህ? እ? ደካማ:: ወንድነትህ ይኼ ነው? ለምን ከዚህ ወጣ አትልም? እ? ሚስቱ ሆኜ አታዋሪኝ ይለኛል? ከማን ጋር ላውራ? እ? ጉድ ሲያረፍድ ይመጣል!» አዳም ተዝናንቶ ለመተኛት ይጥራል:: እንዲቀናም በየቦታው ስላጋጠሟት «ወንዳድት» ያለማፈር በዝርዝር ልታወራው ትሻለች:: አዳም ጅሉ:: በትክክል ጅልነቱ እንኳን ሳይሆን ወሲብ ምን እንደሆነ በጥልቅ አለማወቁ ነው:: «የት ጠፋሽ?» ብሎ ሲጠይቃት ጠልቆ ሊረዳው በማይችል ኩርማን ቅኔ: «ወጣ ብዬ አለምን አየሁ» ትለዋለች:: አዳም የነገሩን ክብደት የተረዳው እጅግ ከርሞ ነው:: በሁለት ስዎችና ቁጥራቸውንና ዝርያቸውን በሚያውቃቸው ራሱ ስም ባወጣላቸው መልካም እንስሳት ተሞልታ የነበረችው ገነት ከወገባቸው በላይ ሰው፣ ከወገባቸው በታች ፈረስ፣ ቀንድ ያላቸው ሰዎች፣ ጅራት ያላቸው ሴቶች፣ የሰው ፀጉር ያላቸው ዋኖሶች፣ የሰው እግር ያላቸው አሞሮች፣ የእንቁራሪት ቆዳ ያላቸው ሰባዊ እንስቶች ይመላለሱባት ጀመር::

የእግዜር ችሎታውና ድክመቱ ትዕግስቱ ነው:: ትዕግስት ያበዛል:: ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን ብቻ ያበዛዋል:: ሶፍያ ስትሳሳት በዝምታ እያየ ስህተቷን ይቆጥራል:: ወይም ምናልባት እንደሚወራለት ያህል ወደ ፊት የሚመጣውን ነገር አያውቅም:: ገማች ነው:: የፈጠረው ፍጡር ወደ ፊት ምን እንደሚመስል፣ ወይም ወደ ምን/ማን እንደሚለወጥ አጥርቶ መገመት አይችልም:: በሰማይና በምድር የሚወራለት አሉባልታ ግን ዛሬንና ነገን ይፈጥራል እየተባለ ነው:: ሰይጣን እግዜር ስለወደፊቱ የሚያውቀው ነገር አንድ በጣም ብልህ የሆነ ሰው ከሚያውቀው የተለየ እንዳልሆነ ይጠረጥራል:: አብሮት ኖሮ አይቶታል:: ለምን ስለ ሰይጣን ስለራሱ መሸፈት ቀድሞ አልተረዳም? ወይስ ደም የማፍሰስ ፍላጎት ከአልፋው አድሮበት ነው? ትዝ ይለዋል ሰይጣን በመጀመሪያው የአመፅ ጦርነት ዕለት ከሰባተኛው ሰማይ ወደ ምድር የመላዕክት ደም እንደ ዝናብ ለአርባ ቀናት እንደወረደ:: እዚህ ያስደርስ ነበር? ቢሳሳት 'ድክመቱን አውቄ ያደረኩት ነው' ብሎ ለማስወራት መፈለጉ ካልሆነ ለሌላ ለምን ተአምር ነው?

ይኼም ይሆንለታል፡፡

አዳምን ሊታጫውተው የተፈጠረችለት ሶፊያ ሰላም የምትነሳው ብቻ ሳትሆን......ገነት ውስጥ ያሉትን ፍጡራን አሃዝ ወደ ሰማይ ያነሳች ሆነች፡፡ ገነት በሚያስፈራሩ ዐይነት ፍጡራን እየተሞላች ስለሄደች አዳም ራሱ በምሽት መመላለስ ፈራ፡፡ ቢሰላችና ቢማረር ደጋግሞ ለእግዜር አቤቱታውን አቀረበ፡፡ ጮኸ፡፡ ግን የሰው ልጆች አባታችን ነው እናከብረው በሚል 'ጮኸ' ይሉታል እንጂ፡፡ ትክክሉ ቋንቋ እንኳን ማቃጠር ነው፡፡ ለማያውቃቸውና ላልወለዳቸው እግዜርም ላልመደበለት ፍጡራን (የዲቃላ መንተፍ የተጀመረው ከዚያ ዘመን ሳይሆን ይቀራል?) እንጀራ አባት ሆኖ ማገልገል የሚወድ ማነው? አዳም እንደ ፈጣሪው ትዕግስት ስላለው ብቻ የሶፊያን ረባሽ ሴሰኛነት ችሎ ቆየ፡፡ እስከዛሬ ብትኖር ኖሮ ገነትን ከነዲቃላ ልጆቿ ለመውረስ ብዙ ጊዜ ይወስድባት እንዳልነበር ሰይጣን ያውቃል፡፡ ቢያንስ ገነትን ከውጭ ባይቻል ከውስጥ በሶፍያ የሴሰኛነት ባሕርይ ተከለሎ በመግባት አዳም የማይወዳቸውን ፍጡራን ቁጥር በማብዛት ከገነት ጌታነቱ ተማሮ እንዲወጣ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡ ይኼ የመጀመሪያው ዲሞግራፊክ ሳይንስ[74] ሳይሆን ይቀር ነበር? እስመርሮ እስመርሮ በሴረኞችና በደደቦች የእሐዝ ብልጫ መልካሞችን አርፈው ከተቀመጡበት ማባረር? እግዜር አንድ ሳንካ ትዕግስተኛ መሆኑ ሲሆን ትልቁ ብልሐቱ ደ'ሞ ትዕግስቱ መቼ እንደሚያልቅ ግልፅ አለማድረጉ ነው፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ሶፊያ ከፊሊሞዎች ጋር ስትዳራ ውላ ወደ ገነት ስትመለስ መልአኩ እንዳትገባ ከለከላት፡፡ የእግዜር ንፁሕ እርሻ የባለጌዎች ማረፊያ አይደለም አላት፡፡ ከገነት ምስራቅ ደጃፍ የዓባይ ፏፏቴው ስር ተቀምጣ የለቅሶ ቲያጥሮን ስትሠራ የወለደቻቸው ልጆች ሁሉ በእሳትና በመብረቅ እየተገረፉ የቻሉበት በሰማይ እየበረሩ ያልቻሉበት በምድር እየተንኳተቱና እየሮጡ ከገነት እንዲወጡ ተደረገ፡፡ የሚገርመውና የሚያሳዝነው ሶፍያን በየቦታው ከተወዳጀት ከገነት ውጪ ከነበሩት እንስሳት ጀምሮ እስከ ፊሊሞዎች ድረስ የሚያስጠጋት አንድ ፍጡር እንኳን አላገኘችም፡፡ ሲጀመር ዓላማቸው ገነትን ማፍረስ እንጂ የሶፍያ ውበት ማርኳቸው አልነበረም፡፡ ከሶፍያ የበለጡ ውብ እንስቶች እነሱ ጋ እንደ አሸዋ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም እግዜር ትዕግስቱ አልቆ ቁጣ ከጀመረው የት እንደሚያባራ ስለማያውቁ ሁሉ ፈሩ፡፡ የተንከላቸው ስር ገብቶት ግን እግዜር ትንሽ ቅጣት እንኳን በላያቸው አለመስንዘሩ ብዙውን በፍርሐት ደስታ አንቀጥቅጧል፡፡ የሥራ ውጤታቸውና ሐይላቸው ምድር ላይ ከሚታይ ታላላቆች የተለየ እግዜርን የተምታታበት ገፀ ባሕርይ የሚያደርገው ይኼ ነው፡፡ እግዜር አዳምን ይወደዋል፡፡ ከማንም ይወደዋል፡፡ እንደሚባለው ከምርጥ አፈር የገነባው እሱን ነው፡፡ በጠባዩ የተረጋጋና ትዕዛዝ ተከታይ በመሆኑ የፈለገውን ያገኛል፡፡ ታዲያ ሶፍያና ልጆቿን ከገነት አሳዶ ካስወጣ በኋላ አዳም በሰላም እንደተኛ ከትንሽ ጎን አጥንቱ በቀላል ቀዶ ጥገና ያማረች የእሱን ትዕዛዝ የምትሰማ ፍላጎቱን የምትከተል ሌላ ሴት ጓደኛ ሔዋን የተባለችውን ሰራለት፡፡

መፍጠር የትም አለም ላይ ፍፁም ሆኖ አያውቅም፡፡ ዛሬ ፍፁም የሆነ

74 ስነሕዝብ(አ)

ነገር ነገ ፍፁም አይሆንም:: አንድን ፍጡር በራሱ አምሳል ከፈጠረና ይህቺ አምሳሉ ደ'ሞ በተልከሰከሰ ሴሰኛነት ልታሳብደው ከደረሰች ሁለት ነገር ሊኖር ነው:: አንድ: ሲጀመር አፈጣጠሩ ፍጹም አልነበረም:: ሁለት: ፈጣሪው አሁን በፈጠረበት ሰዓትና ደቂቃ ፍፁም ነገር ቢያደርግም ወደ ፊት ስለሚመጣው ለውጥ ገና ያልተረዳቸው ነገሮች እንዳሉ ያሳያል:: ሰማይ ቤት በወንዶች የተሞላ ነው:: እግዜር ስለ ወንዶች ያውቃል:: ለአዳም ሴት ሲሰራለት ግን ፀባይዋ ምን መሆን እንደሚችል መገመት አልቻለም:: ሰላ ሰላ የሚያሰኝ የደሟን ትኩሳት ቀንሶባታል፣ ውበቷን ቀንሶባታል፣ የአካሏን ቅርፅ አበላሽቶባታል:: ገነትን ሰብራ ብትወጣም የሚነካት የወንድ ፍጡር አይኖርም:: ታዲያ አጎዶ፣ ሽፋፋ፣ ጭገራምና የማትማርክ መርገም በራሱ በአዳም 'ሔዋን' ተብላ የተሰየመች ሴት ገነት መሐል ማምጣቱ ሳይሆን ሰይጣንን የገረመው ከዚህም ጋር አብሮ 'የዕውቀት ዛፍ' የተባለች ተክል ከዛፎች ሁሉ የምታምር ዛፍ፣ ከፍሬዎች ሁሉ የምታምር ፍሬ የምታበቅል ሁለቱንም ሰዎች መፈተኛ ሆና የዚያኑ ዕለት እዚያ አትክልት ስፍራ ውስጥ መተከሏ ነው::

## ሦስት ብልጠቶች......

አዲስ ሴት ገነት ውስጥ ገብታ ሁሉ ነገር የተለወጠ ቢመስልም እንኳን ያ መልአክ የጅል ጥበቃውን አላቆመም:: ሠይጣን ገነትን ከሩቅ እያየ ዕቅድ የመሰሉ ነገሮችን ማሰላሰል ጀመረ:: በመጀመሪያ አዳምን ማታለል፣ መሸወድ እንደማይችል ተረዳ:: አዳም ብልጥ ስለሆነ አይደለም:: ተስማምቶታል:: ይበላል፣ ይጠጣል፣ ከእንስሳት ጋር ይላፋል እናም ይተኛል:: ከዚህ አርቆ አያስብም:: ተከራካሪም አይደለም:: ሴቷን ግን አትክልቱ ቦታ ውስጥ ያለ ትልቅ ዲብ ላይ ወጥታ ቢያንስ በቀን አንዴ ከገነት ውጭ ያለው ስፍራ ምን እንደ ሆነ ለማየት ስትጥር አይቷታል:: ማጫወቻ፣ ማዋሪያ አረፍ ማሸኮርመሚያ ዕድሉ አልነበረውም:: አስቀያሚ ብትሆንም ገነትን ማፍረሻ መሣሪያ በቂ ትሆናለች::

መልአኩንም ማራቅ ቀላል ይሆን ይሆናል:: መልአኩ ከገነት በር ለሰከንድ እንኳን ትኩረቱ ፈርሶ በሀሳብ ይሁን በአካል ገለል ቢልለት የፈጠ ዘር መስሎ ሾልኮ መግባት ይችላል:: ትንሽ ቀዳዳ ነው የሚፈልገው:: ከፏፏቴው በታች እጅግ ቆንጆ የሰው ልጆች ይኖራሉ:: እነሱም በፊት በፊት በውበታቸው የተማረኩ ሁለት መቶ የሚደርሱ መላዕክት ወንዶች እነዚህን በሩካቤ ስለፈቀዱና ስላወቁ በእግዜር ተረግመው እንደሌላው ፍጡር እዚሁ ምድር ላይ እያደኑና ያደኑትን እየበሉ አሉ:: ሠይጣን ከእነዚህ ቆንጃጅት በተለይ እንደ አባታቸው ክንፍ ያላቸውን ያውቃል:: ከራሙኤል፣ ከዳንኤልና ከአሳኤል ሴት ልጆች ዘር አለው:: ከእነዚህ ሴቶች ጥቂቶቹን (የራሱም ወዳጆች የነበሩትም ቢሆኑ ምን አለበት) የነጠሩ መልከ መልካሞችን ከምስራቁ የገነት በር ከፏፏቴው ጉም ስር ወንዙ ያልሞላ ዕለት ያው ባማረ የበጋ ጎሕ ራቁታቸውን መጥተው እንዲዋኙ ማድረግ ይችላል:: የኔፊሊም ጎበዛዝት ሴቶቻቸውን ለዚህ ስራ ይለቁለታል:: ይኼ መቸም ሰይጣን ራሱ ቁማር እንደሆነ ያውቃል:: ማዘለቁ አጠራጣሪ እንደሆነም ጉበቱ ድረስ ይሰማዋል:: እነዚህ አሁን ያሉት የገነት መላዕክት ብልጣ ብልጥ ባይሆኑም ስነስርዓታቸው ጠንካራ ነው:: ከተባሉትና ከታዘዙት

ውጭ ውሃ የሚቀዱ አይመስልም::

በራሱ ሕሊና የሚመራ ብልህ ነኝ ባይ በቀላሉ ይታለላል:: ተታሎም፣ ያንን መታለሉን በመጠቀም ስህተት ውስጥ ከቶ እንዲደናገጥ ማድረግ አደናግጦም ማጋለጥ አጋልጦም በስህተቱ መሳቅና ሌላው እንዲስቅበት ማድረግ ይቻላል:: ይኼ ከተጠናቀቀ በኋላ በፍርሃትና በዝቅጠኛነት ስሜት ተውጦ ሊላቀቀው የማይችል የባርነት ደይን ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል:: ማምለጥ ዕድል እስኪሆን:: እነዚህ መላዕክትን ግን የሚያያይዛቸው ሰፊ በዓይን የማያዩት በእጅ የማይዳስሱት የእግዜር የመንፈስ ስርዐት ነው...... ይሄ ስርዓት ሰይጣን ሊገባው በማይችል ውስብስብ ቁልፍ የታተመ ነው:: ቅንነት ይባላል:: ይኼን ስርዓት ሰይጣን መፍታት ይከብደዋል::

ማንም ነገር ወይም ፍጡር በሕይወቱ ተመሳሳይ የሆነ ውበት ውስጥ አይሆንም:: ይለዋወጣል:: የገነት ውበት ግን ከስሞ አያውቅም:: ውበት ተወዳጅ ተፈላጊ ነገር ቢሆንም ይሰለቻል......በየቀኑ ደጋግመን የምናየው ውብ ነገር ሲቆይ ይሰለቸንና መኖሩን እንዘነጋለን:: በተጨማሪም እንደዚያ ዓይነት ልቅ-ውበት የትም ቦታ መቼም ጊዜ የነበረና የሚኖር ደንብ ይመስለናል:: የገነቷ ዛፍ በክረምት ዳመናና ጭጋግ በበዛበት ጊዜ ቀለሚና ቁንጅናዋ ሐጋይና ጥቢ ሲሆን ከሚከስተው ውበቷ የተለየ አይደለም:: የእግዜር አንዱ ድክመት ይኼ ደንብ እንዲለመድ ማድረጉ ነው:: የቅጠሉቿና የአራዊቶቿ ብቻ ሳይሆን እዚያች ገነት ውስጥ ያሉ ሁለት ሰዎች ውበት እንደ ተወለዱበት ቀን አዲስ ነው:: ፍፁምነት በራሱ እማንም ፍጡር አእምሮ ሰርጎ ከገባ ጥያቄ ይቀሰቅሳል::

ሰይጣን ገነትን የማፍረስ አላማው ቀን ባለፈ ቁጥር እንቅልፍ እየነሳው ሄደ:: ምን ማድረግ እንዳለበት ነጋ ጠባ ሲያስብ አንዳንድ መደምደሚያዎች ላይ ደረሰ:: በመጀመሪያ ራሱ በአካል ሾልኮ መግባት አለበት:: ግን ይሄን ለማድረግ ትንሽ ሴራ፣ ትንሽ ብልጠትና አንዳንድ ተባባሪዎች ያስፈልጋሉ::

ገነት ውስጥ ከሚኖሩት ራሳቸውን ከዚያ ቦታ ለመንቀል ያለፈቃዳቸው እንዲሳተፉ ከሚደረጉት ከሔዋን፣ ከአዳምና ከዛፏ በተጨማሪ ከገነት ውጪ አስራ ሦስት የኔፊሊም ቆነጃጅትና ያለወቅቱ እንዲመጣ በሰይጣን የታዘዘ ፀሐይና ጭጋግ የተንከሉ ንጥረ ነገሮች ነበሩ:: የዘበኛውን መልአክ ፀባይ ለመፈተሽ ለወር ያህል እሱ ከሚቆምበት ፏፏቴ ፊት ለፊት ማራኪ ባለክንፍ ቆነጃጅትን ደርድሮ እየዋኙ እየቀለዱ እንዲወዳጁት ለማድረግ ቢጥር አልሆነለትም:: የእግዜር ቤተ-መንግስት ከከሐዲ የጠራ ይመስላል:: እነዚያ ሴቶች ያልሳቡትና ሌላ ሌላ ነገር ያላሳሰቡት መልአክ ወይ የተሰለበ ወይ ልብና አእምሮውን ሰማይ ቤት ትቶ የመጣ ነው:: ሠይጣን በዚህ ጥበብ የፈለገው አልሆነለትም:: ይባስ ብሎ መልአኩ ከሴቶቹ ራቅ ብሎ ተንኰል እንዳለበት የገባው ዐይነት ሰይፉን ሰማይ ላይ ሰቅሎ፣ ብርሐኑን በሺህ አቅጣጫ ፍንትው አድርጐ በጋለ ፊጠጣ የሚጠብቅ ሆነ:: ለአማላይነት የተደረደሩት ሴቶች ሠይጣን እንዳቃቂላቸው ሁሉ ተከፉ:: አጉረመረሙ:: ከፊሎቹ ሠይጣንን 'የማይሆን ነገር ታስራናለህ' ብለው ፀጉራቸውን እንኳን ለማዳረቅ ትንሽ ወዲያ ወዲህ ሳይንጠራዘዙ እንደ ጢስ በሚበነው የግዮን ውሐ የሉመሉሙ ክንፎቻቸውን እያራገቡ ወደ ታች ወደ በረሀው እየተንጋጉ

ወረዱ:: የተቀሩት አልማረክ ያላቸውን መልአክ ለማብሸቅ የማይወደውን ዐይነት ፉጨት ሲያፏጩ የተበሳጨው መልአክ ከአድማስ አድማስ የሚደርስ ወርቅማ መለከቱን ነፍቶ አደንቁሮ አባረራቸው:: ታዲያ ወደ ገነት ሰርጎ ለመግባት እንኳን ሰናፍጭ፣ ሩሕ ማሾለኪያ ቀዳዳ አልተገኘም:: ሰይጣን የጠባቂ መልአክ ብርሃንዓይን እንዳያርፍበት ከሩቅ ተራራ ጀርባ ተቀምጦ አዳምና ሔዋንን የመቅረብና የማሳሳት እቅዱ ሲፈረስ ታየው::

እግዜር በልማዱ ፍጡሮችን ሲሰራ ሁለት የማይተዋቸው ብቆታዎች አሉት:: ውበትና ብልሐት:: የፈጠረው ነገር ውብ ወይም ብልህ መሆን አለበት:: ውብነቱ እንዳይፈተሽ፣ ብልሕነታቸው እንዳይጠረጠር አንፃራዊነትን ያጠፋል:: ሔዋን ለአዳም እጅግ ውብ ናት:: ከገነት ቢወጣና ከሰው ልጆች አንዷን ሴት ቢያይ ሔዋን ከዝንጀሮ ያልተለየች ነሁላላ ፍጡር እንደሆነች ይገባው ነበር:: እንኳን ከሰው ልጆች ገነት ውስጥ ካሉ ብዙ እንስሳት በውበቷ የምትበልጥ አይደለችም:: እግዜር ይሔን ያውቃል:: አዳም ግን አያውቅም:: እንዳያውቅ ተወስኖበታል:: ምናልባት ለአዳም የአንድ ቀን ፈቃድ ተሰጥቶት ለዕረፍት ከገነት ቢወጣ ተመልሶ መምጣቱ አጠራጣሪ ነው:: ታዲያ ይሔ እስር ግቡ ምንድን ነው? መቼም አንድ ሴራ ሲሴር ቀደም ቀደም ብሎ የሚወራው የሚሴራው ግብ ሁሉን የሚጠቅም ቅዱስ ነገር እንደሆነ ተደርጎ ነው:: ሠይጣን ታዲያ 'እስር' ብሎ የሰየመውን የእነ አዳምን የየቀን ሕልውና ሌላ የሚከስበት የጣመ፣ የሚጥም ወይ የሚጥም የሚመስል **ተስፋ** ማዘጋጀት አለበት:: ያላዩት አገር እንዲናፍቃቸው:: የእግዜር ፍፁምነት ለተስፋ ቦታ አይሰጥም:: በፍፁምነት መሃል 'ጊዜ' ተጠቃላ ተኝታለች:: እዛ ውስጥ ትናንት፣ ዛሬና ነገ ተዋህደው ያለንጭንጭ ተቀምጠዋል::

ሰውን የመሰለ የፍጡሮችን ሁሉ የበላይ (መቼም ተብሏልና) በአጥር አጥሮ በመልአክ ወታደር ማንም እንዳይገባና እንዳይወጣ አድርጎ ዐይነት ዕቅድ መጨረሻው ምንድነው? ያሰኛል:: አንድ ነገር መጨረሻ ያስፈልገዋል:: እሱ ሲያልቅ አዲስ ነገር መምጣት አለበት:: የሠይጣን ዓላማ ለውጥ የማምጣት ተስፋ የመዘርጋት ነው:: ሔዋንና አዳምን ተስፋ መስጠትና ከሆነም ከእስር ማስወጣት፣ ካስወጣቸው በኋላም ቢከፋም ቢለማም እንዳያንገራግሩና እንዳይሸፍቱ እንደገና ሌላ ተስፋ መስጠት:: እሱ ሲሰለቻቸውና የተጠበቀው ካልሆነ ሌላ ተስፋ መስጠት ወዘተ......ተስፋው ትክክል ይሁን አይሁን አጋጣሚዎች የሚፈቱት ነው:: ምናለበት ሰይጣንም እንደ እግዜር ትንሽ ነገር ቢያዞር:: እግዜር በለስን እንደተከለ እሱስ ሰይጣን የተስፋ ጥርጣሬን ቢተክል? ታዲያ ስራው እንዲሳካ ገነት ውስጥ የሚገባ......የተስፋ መልዕክት የሚያስራጭ......የለውጥ ሐዋርያ ያስፈልጋል::

የገነት አጥር በመልአኩ ሠይፍ የታጠረ፣ በአይኖቹም ነጋ ጠባ የሚሰለል ቢሆንም ይሄ ቁጥጥሩ በፍፁም ደፍኖታል ማለት አይደለም:: ገነት ውስጥ ልዩ ዛፍ ተተክላለች የሚለው ወሬ በየአለሙ መሰራጨቱ ራሱ ገነት ሙሉ በሙሉ እንዳልተለሰነች ምስክር አይደለ እንዴ? ምንም እንኳን በገነት መዝገብ ያልተመዘገቡ ባዕዳን የመግባት መብት ባይኖራቸውም የ'ዛ ነዋሪ እንስሳት

ጥቂቶች ያውም ከስንት ሺህ አንድ እየወጡ ሲገቡ ይታያሉ። ምናልባትም በሰይጣን ግምት ብልጠት አለን የሚሉ፣ መታፈኑ የሰለቻቸው እንስሳት የተለየ አየር፣ የተለየ ምግብ፣ የተለየ ፍቅር ፍለጋ እየተሠረቁ መውጣታቸው ይሆናል። ከእነዚህም ሲበዛ የተሰላቸች የመሰለች፣ ቢያንስ ጨረቃ በተለወጠች ዕለት በተለይ ሊንጋ አካባቢ ከገነት ወጥታ ስትዝናና የምታረፍድ እባብ የምትባል እንስሳ አለች።

እግዜር ገነትን ለማስጌጥ የሰበሰባቸው ነፍሳትና ተክሎች ውበታቸው ሁሉ የሚያፈዝ ነው። ደረጃ ግን አላቸው። በጣም ከሚያምረው ወደ ማያምረው። በጣም ጠንካራ ከሆነው፣ በጣም ደካማ ወደ ሆነው። በጣም ግዙፍ ከሆነው ረቂቅ እስከሆነው። እንዲጋጣሚ ሆኖ ሳይሆን አይቀርም ሲመሽና የፈጠረውን ሲያጤን 'አስቀያሚ' የሆኑት በሁለት አቅጣጫ እንዳይጐዱ በማለት ለእነዚህ 'አስቀያሚያን' ብልሐት የሚባል ነገር ፈጥሮላቸዋል። እሱ ፈጣሪ ሰርቶ ሰርቶ፣ ይሠራ ይሠራና ምናቡ ይደክማል መሰል አንዳንድ ነገር ያበላሻል። ከእነዚያ አስቀያሚያን ብልጥ ከሆኑት እንስሳት አንደኛዋ እባብ ናት። ብልጥነቷ ደ'ሞ ቂም ልቧ ውስጥ እንድትዘራ ዕድል ሰጥቷታል። በእግዜር ላይ ቂም አላት። ገነት ውስጥ ብልጥ መሆንና አለመሆን ጥቅም የለውም። ብልጥ ከሌላው የበለጠ ለመብላት፣ ለመጠጣት ቢያገለግል፣ ይኼ ደ'ሞ አስፈላጊነቱ የመብልና የመጠጥ እጥረት ባለበት ቦታ ነው። እንደ ገነት ያለ ምቹ ሥፍራ ግን ሁሉ የፈለገውን ስለሚያገኝ ብልጥ መሆን በፍጹም ቦታ የለውም። እንደ አህያ አይነት ደደብና፣ እንደ እባብ ዐይነቷ ጮሌ እኩል እንዲደሰቱ ይጠበቃል። እኩልም ናቸው።

ታዲያ ቦታው እኩልነት ያለበት ቢመስልም በረቀቀ መልክ ስሙ የማይጠራ የተንሰራፋ ተዋረድ አለ። አንዱ ማስረጃ የእባብ ችግር ነው። እባብን አስቀያሚ በመሆኗ ገነት ውስጥ ከጉዳይ የሚጥፋት የለም። ይኼ እኩልነት ነው? አዳምና ሔዋን ያልዳበሱት አብረው ያልተኙት ያላጫወቱት እንስሳ ገነት ውስጥ የለም። እሷን ግን ለሰላምታ እንኳን ዞር ብለው አይተዋት ወይም አጢነዋት አያውቁም። ከገላዋ ክፍሎች የሚያምሩት በውብ ቀያቴ ላባ የተሸፈኑት አራት እግሮቿና ለጥ ያለው ለስላሳ ቀስተዳመና የመሰለው ባለቀለም ሰፊ ሆዷ ናቸው። እግዜር ደ'ሞ ላባዎቹን እግሮቿ ስር፣ ሕብረ ቀለሟን ሆዷ ላይ ስላደረጋቸው ሥራ ፈቶ አጐንብሶ የሚያይላት፣ ዐይቶም 'ይኸቺ እባብ ለካስ ቆንጆ ናት' የሚላት አይኖርም።

እባብ የአዳምንና የሔዋንን ስሜት ለመፈተሽ አንዳንድ ቀን መተላለፊያ መንገዳቸው መሐል በጀርባዋ ተንጋላ የሚያማምሩ እግሮቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ ስትጠብቃቸው እንዲህ እያዩአት እንዲህ አተኩረው እያዩአት 'ከየት መጣ?' ብለዋት ያልፋሉ። ይኼ ቸለልታ ያበሽቃታል። አትነክሳቸው ነገር። አትጮህባቸው ነገር፣ አትለማመጣቸው ነገር......

ከመዘ.[75] አንድ ጠዋት ሰይጣን ገነትን የመስበር ሴራውን እያውጠነጠነ ከግቢ ውጪ ሲያንዣብብ አንድ እግረ መልካም ጀርባውን የተላጨ የመሰለ

75 እንዲሁ(ግዕዝ)

እንስሳ ከገነት ግቢ እየዘለለ ሲወጣ አየ:: እንዲህ የውጭው አለም ከሚቀናባት ከዚያች እየቧረቀ የሚወጣ እንስሳ አይቶ አያውቅም:: ከሚወጡት ብዙዎቹ ሹክክ ብለው ወጥተው በፍርሐት ገልመጥ ገልመጥ ብለው መሬትና ሰማይ አነፍንፈው፣ ቅጠል ነካክሰው፣ ፍሬ ቆረጣጥመው በመጡበት ሹክክ ብለው ይመለሳሉ እንጂ:: እባብ ግን የጠዋቱ ቀዝቃዛ ሳር ላይ እንዳበጃጀችው አልጋ ተንከባላ ጀርባዋን በዛፍ በግንድና በመሬት ዲብ አ'ካ......ጣዕሙን በምን እንደወደደችው አይታወቅም መረሬ ጭቃ የተደባለቀበት ውሐ ጠጥታ (ሰይጣን በስጨት ያለ ጊዜ ይኼን መገሸር ይወዳል) ሁለመናዋን አቆሽሻ በሆነ በተወሰነ ሰዐት ላይ መዝገብ እንደሚጠራ ሁሉ ተመለሰች:: ስትመለስ ግን እየፈነጠዘች አልነበረም:: የመመለሷ ድርጊት ውስጥ እሷ ልትሰይመው ያልቻለች ግዴታ የተገነባባት ይመስላል:: ለምን ግን? ሠይጣን ለመመለስ የፈለገው ጥያቄ ይኼንን ነው:: ለምን? ካልወደደች ለምን ገነት ተመልሳ ትገባለች?

ሆድ::

የእግዜር አንደኛው ሌላ ችሎታ መፍጠሩ ሳይሆን እነዚህን የሚራቡ ማድረጉ ነው:: ረሐብ በተገኘው ነገር እንደሚገታ ቢታወቅም--ሆድ የገባ ምንም ይደግፋልና......ገነት ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ግን እውጭ ከወጡና እዛ ከከረሙ በረሐብ የሚያልቁ ይመስላቸዋል:: ከፊል ዕውነትነት አለው:: የገነት ምግብና ኑሮ ጣዕም አለው:: የሆድ ጣዕም አለው:: ደህንነት አለው:: የነብር አራስ ከቡችሎቿ ጋር የፍየል ግልገል ሰባስባ ጡት የምታጠባበት አይደል......በመጠኑ ስለዚህ ነገር የተረዳችው እባብ ብትሆንም የገነት ምቹነት ትዝታ እየሆነ ይጠራታል:: የእግዜር መስተ-ምግብ ድግምትም ይሆናል::

ይኼ የእባብ ባሕርይ ለሰይጣን ቀዳዳ ሰጠው:: በእርግጥ ከግቢው በሚወጡ ሌሎች (ከእባብ በስተቀር) እንስሳት ተመስሎ በእነሱ አድሮ ገነት ሊገባ ይችላል:: አእምሮአቸው፣ ልሳናቸውና አኗኗራቸው ውስጥ ግን ደቃቃ ሽፍትነት እንኳን ስለሌለች ሊጠቀምባቸው አይችልም:: የሚወረስ አእምሮ ቢያንስ ክፍት ቦታ መስጠት አለበት ለተቃራኒ አስተያየት ማስፈርያ:: መልአኩን ሸውዶ በሆነ ቀዳዳ ገነት ውስጥ ሊገባ ካልቻለ......ሌሎች እንስሳትን በደደብነታቸው ወይ በድክመታቸው ሽንቁር ገብቶ ማድረግ የሚፈልገውን ቢያስደርጋቸውስ? ቢያንስ ቢሞክርስ? በዚህ ምክንያት ለዚህ ዋና የሰይጣን ሴራ የመጀመሪያዋም የመጨረሻዋም እጩ እባብ ሆነች::

**መሳፈር......**

ሠይጣን ሺህ ፈረሶች ለጉሞ ያውም እሳት የሚተፉ በገነት ሰማይ ላይ ሲያቋርጥ እንደ ወለል ከስሩ የተነጠፈውን የእግዜርን መንፈስ ጥሶ ታች መውረድ ስለማይችል ጠባቂው መልአክ ቀና ብሎ እያየ ብዙ ጊዜ 'ጉረኛ' እያለ ይሰድበዋል:: ውርደቱ ሆኖ አላወራውም እንጂ:: እባብን ተሳፍሮ ቢገባ ግን ከመልአኩ ስድብ ያመልጣል፣ የመንፈስ ቅዱስንም ግድግዳ ይሰብራል:: የእግዜር ዝብርቅ ጠባይም ይጠቅመዋል:: አለምን አርቅቆ የፈጠረ ሁሉን ነገር ማዘዝ፣ ማፍረስ፣ መስራት የሚችል እንዲህ እንዲህ ዐይነቱን ትንንሽ ድክመት መዘንጋቱ

ምን ይባላል? ምናልባት ሰማይና ምድርን የሠራቸው ባጠቃላይ ለዝርዝሮቹ ሳይጨነቅ ይሆናል። ምድርን 'በውሐ ተሞይ' ሲላት ትሞላለች። ውሐዎች ግን በየራሳቸው ፍላጐትና ምርጫ ከፈለጉ ባሕር፣ ከፈለጉ ሐይቅ፣ ከፈለጉ ምንጭ ወዘተ......ይሆናሉ። ለእሱ እንዲህ የሚለብሱት ወይም የሚወስዱት ግላዊ ቅርፅ ግድ አይሰጠውም። የውሐ ጉዳይ የውሐ ጉዳይ ነው። እግዜር ዝርዝር ውስጥ አይገባም። ምናልባትም በእያንዳንዱ ፍጡር ውስጥ ሲያስፈልግ የሚጠቀምባት 'ግለኛ' ነፍስ አስቀምጦ ይሆናል። አዳምን የመሰሉ ይዘንጉታል። 'ፈዛዛ' የሚባሉት ይኼኔ ይሆናል። እባብን የመሰሉ ይጠቀሙበታል። 'ብልጥ' የሚባሉት ይኼኔ ይሆናል።

......እባብ ከገነት እድሞ ወጥታ በጀርባዋ ተኝታ ሆዷንና የሚያማምሩ እግሮቿን በፀሐይ ስታሞቅ ሰይጣን ከላይ ሆኖ እያንገዋበበ ያያት ጀመር። ከእግሮቿ ላባ ውበት ይኼን ያህል አስቀያሚ አልመሰለችውም። እንደውም ከገነት ውጭ የሚኖሩ አንዳንድ ነፍሳትና እንስሳት ቢያዩአት የእግሮቿን ቅርጽና ውበት ያደንቁላታል። እባብ የዚህ የውጪው አገር አድናቆት ስቧት አያውቅም። አይሰማትም። ከሆነ ከሆነ እባብ መደነቅ የምትፈልገው ተመርጠው ገነት በገቡ እንስሳት ብቻ ነው። ሌላው ያልተመረጠው እኮ ገና ሲጀመርም ፋርሽ የሆነ ነው። በዚህ ዐይነት ለስለስ ብሎ በሚወርድ የጠዋት የፀሐይ ብርሐን ስር እባቧ ሙቀቱ ሰመመን አስገብቷት ገላዋ እየላላ በእርካታ አፏን ከፈተች። እንቅልፍም እንደወሰዳት ሆነች። የእባብን ከንፈር የሚያይ የለም እንጂ የሚያምሩ ከንፈሮች ነበሯት። የእባብ የአፏ ቅርፅና የከናፍርቶቿ ቀለም ብቻ ሳይሆን፣ በጠዋት የፀሐይ ውጋጋን ውስጥ እየተንቦገቦገች ታች ከንፈሯ ላይ የተዘለሰችው ምላሷ ዐይንና ልብ የሚስብ ውበት ነበራት። ይኼ በጅምላ በማየት አንዳንድ መልካም ነገሮችን ስቶ ማለፍ የፍጡራንና የፈጣሪ ስህተት ሳይሆን አይቀርም......

ሠይጣን በአየር ላይ እየተንሳፈፈ የእባቢቱን አእምሮ ብቻ ሳይሆን ልሳኗንም መቆጣጠር እንዳለበት ተገነዘበ። አእምሮ ያለ ልሳን ምን ይጠቅማል? የሚቀጥለው የእባቢቱ ወደ ገነት ጉዞ የእግዚአብሔርን ልጆች የሕይወት መንገድ የሚለውጥ መሆን አለበት። ይኼ መለወጥ የሚወለደው በዲስኩር ነው። ከሚያምር ቃል። ከሚያምር ድምፅ።

በቃል የተሰራውን ዓለም በቃል ማፍረስ።

እባቢቱ አፏን ከመክደኗ በፊት ሠይጣን መላ ገላውን ወደ አየር፣ ወደ ነፋስ ቀስት ለወጠና ተወርውሮ ውስጧ ገባ። እንደ ከባድ ቀዝቃዛ ንፋስ። ብዙ ዓይነት ምላሶች አይቷል......ሠይጣን የዚያች ዐይነት ውብ ምላስ ግን አይቶ አያውቅም። የቅርፅዋ ሞላላነት፣ የጫፏ አሹዋሹዋል። በተጨማሪ ምላሷ ላይ ግራ ቀኝ አግድም ሕብር ያለው ቀለም የተሰመረባት ነች። እዚህ መልአኩ የሚቀመጥ በት ፏፏቴ ላይ የሚዘረጋው ቀስተ ዳመና ጠቦ ምላስ ቢሆን እንደማለት ነው። ከዚህ በሕብር ከተሰራ የምላሷ ቀለም የሚያምር ከተከፈተው አፏ ርቆ የማይኼድ እዚያው ከውጭ እንደተቃጠለ አየር የሚውለበለብ ሺህ ቀለማት የተሰበጣጠሩበት የሕብረ ቀለም ውጋገን አለ። የሚነካ የሚመስል......በጣት ቢነኩት የሚፈርስ የሚመስል። የሚያረጥብ የሚሞቅ የሚመስል። እነዚህ ውብ

ከንፈሮች የሆነ ችሎታ እንዳላቸው ከአፈጣጠራቸው ልዩ ትንቢት ይሰጣሉ። እባብ ይኸቺን ምላሷን አንዘላዝላ በገነት እርሻ ውስጥ ብትዞር በውበት ደረጃ የሚሰጣትን ተዋረድ ወደ እነ ገነት ወፍ ማስጠጋት ትችል ነበር። ገነት ውስጥ ግን የተመዘገበ ሕግ ባይኖርም ምላስ ማውጣት ከስርዐት ውጪ ነው። ቢፈቀድ እንኳን ማን ትዝ ብሎት የምላሱን ውበት ለማሳየት በየድንቹና በየካሮቱ መስከ መሐል አንጀልጅሎ ይዞራል? ደፍሮ እንዲህ እንኳን ለማድረግ በትንሹም ቢሆን ስለራስ ማወቅ ያስፈልጋል። ቢያንስ መስታወት፣ ቢበዛ ደ'ሞ ውበትን ዐይቶ የሚመክር ወዳጅ ያስፈልጋል። እባብ ገነት ውስጥ ወይም ከገነት ውጭ ወዳጅ አልነበራትም። የገነቶቹ የሸኚት ክፉ ስለሆነች ሳይሆን የሚያስፈራ ጀርባ፣ የሚያስቀይም የጀርባ ቆዳ ስላላት ነበር። ከገነት ውጭ ደሞ ያሉትን እሷ በትዕቢቷ አትቀርባቸውም። በገነት ምደባ አስቀያሚ ብትሆንም ከዚያ ውጭ ካሉት ፍጡራን ጋር ለወሬም ይሁን ለሌላ እንደ እሷ ዓይነት ምርጥ ቢቀላቀል 'ጨዋነት' እንዳልሆነ ይገባታል። ታዲያ ሰይጣን የእባብን ልሳን ፍለጋ ብቻ ሳይሆን በምላሷ ውበትም ስለተማረከ እባብን ሊሠፍርባት ቆረጠ። ተወርውሮ በአፏ ሲገባ ግን እውስጥዋ በመጠኑ እንግዳ አለም አጋጠመው......

ሠይጣን የገመተው ስተት ብዬ ገብቼ ያኔውኑ እግሮቼን ዘርግቼ ጅራቴን አጥፌ ተረጋግቼ ጥፍሬን እየላስኩ እቀመጣለሁ ብሎ ነበር። በአፏ ገና እንደገባ እባቢቱ ከነበረችበት ሰመመን አቲትዋ እንደ ወደቀ ሁሉ በድንጋጤ ባና ተነሳች። መደንገጥ አልነበረባትም። ብዙ ጊዜ እግዜር ይሁን ሰይጣን ሰው ይሁን እንስሳ የሚያዩት ሊያዩት የፈለጉትን ነገር ነው። ሠይጣን እባብን ተከፍታለች ብሎ ከጠበቃት በኋላ ተወርውሮ ሲገባ የጠበቀው ስልቅጥ እንድታደርገው፣ ስልቅጥ አድርጋ ሆዷ አመቻችታ እንድትከተው፣ ይኼም ጥሚት ምላሷን በእርካታ እንድታጣጥም እና በሚወደው የሚፋጅ ግሳት እንድታስተናግደው ነበር። ከዚያ በኋላ ደ'ሞ ባለው የገላዋ ስርዐት ውስጥ ከበላችው ምግብ ጋር ተደባልቆ በደም ሥሯ ገብቶ አእምሮዋ ውስጥ መስፈር ነበር ሃሳቡ። ምንም እንኳን እባብ የገነት ነገር እያስከፋት አጥር እየሰበረች ብትወጣም ያለፍላጐቷ ሆዷ ዘሎ የሚገባ ነገር አጋጥሟት አያውቅም። ከገነት ውስጥ ኑሮዋ የሚያስከፋት ዋናው ነገር ያለፍላጐቷ አንዳንድ ነገር እንድታደርግ መገደዷ አይደለ? በድንጋጤና በመገረም ተፈናጥራ ከተኛችበት መነሳት ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ ወድቃ በመንፈራፈር፣ ዛፍና ቅጠል በመቧጠጥ ሆዷ ውስጥ የገባውን እንግዳ ቁስ፣ እንግዳ አየር ለማስወጣት እየቋቋች ያልተሳካ ሙከራ አደረገች። ሠይጣንን ያጋጠመው ተከላካይነት ቢገርመውም ጨጊራዋን በጥፍሩ ጨምድዶ ይዞ እየሳቀ መጨረሻዋን ለማየት ተዘጋጀ። እባብ ተፈራግጣ ተፈራግጣ ቢቸግራት ፍርሐት፣ ግራ መጋባትና ድካም አባሯት ገነት እድሞ እየሮጠች ገባች። ሰይጣን 'ላያመልጡ ይፈራገጡ' አለና የድምፁ ሞገድ በአፏ እስኪወጣ በሳቅ ፈረሰ።

እባብ ገነት ስትገባ ሰይጣን ሆዷ ውስጥ እጁን ተደግፎ ጋደም እንዳለ የአትክልቱ ስፍራ መዓዛ ይሸተዋል። ትልቅ ደስታ ተሰማው። በሆዱ ተንበለበለና ፊቱን በጉሮሮዋ አቅጣጫ አደረገ። በአፏ ቀዳዳ የሚገባው ሕብረ ቀለም ያለው ብርሐን ብልጭ ድርግም እያለ ይታየዋል። ፈርጠም ብሎ ዓይኖቹን ከድና አፍንጫውን እንደ ወናፍ እያንቃነቀ ስትሮጥ በሚከፈተውና በሚዘጋው የእባቧ

አፍ እንደ ጎርፍ የሚገባውን መልካም ጠረን ምንም ሳያስቀር መምጠጥ ጀመረ:: ሆዷ ውስጥ ግን ብዙ መቆየት አልፈለገም.....ሆዷ ቅርናታም፣ አስቀያሚና የሚፋጅ ነው:: ፍጡራን ቆዳና ላባ እየተያዩ እርስ በእርሳቸው ከሚንቀለጳጰሱ እውስጥ ገብተው የሆድ እቃ ቢፈታተሹ የእግዜርን የፈጠራ ችሎታ ለማጣጣል ቀላል መረጃ ያገኙ ነበር::

ሰይጣን በትዕግስት ከጠበቀ በኋላ እባብ ያጋጠማት ነገር እያስገረማት የዛፍ ጥላ ፈልጋ አረፍ ስትል ገላዋ ውስጥ የሚያደርገውን ጉዞ ጀመረ:: በደም ስሯ ውስጥ ከደም ተቀላቅሎ መፍሰስ ጀመረ:: ትንሽ ግራ የሚያጋባ ስፍራ ነው:: የፈሊሞ ሴቶችን፣ የሰው ልጆች ሴቶችንና ያበሸቁት ባሎቻቸውን አልፎ አልፎ ከመሳፈር በስተቀር የእንስሳ ገላ ውስጥ ገብቶ የጋለበበት ጊዜ አልነበረም:: ብዙ ጊዜ ሰይጣን የሚሳፈረው መቀናቀን ሲገጥመው ነው:: ታዲያ የደም ስሯ አዘረጋግና የብልቶቿ አቀማመጥ ግራ አጋብቶት ብዙ ጊዜ መንገድ እየጠፋው ተጨነቀ:: የተወሳሰበ ሥራ እንደሆነ ይገባዋል:: ለሰይጣን ግን እግዜር ሐይለኛ እንጂ ውስብስብ ሆኖበት አያውቅም:: እንዳይምታታበት ብዙ ጊዜ ፍጡራንን በሚወራረስ መልክ እንደሰራቸው ይገባዋል:: አንዱ የአንዱ እንስሳ የማይረባ ኩረጃ ይመስላል:: አይቀርምና ግን ቢረዝምበትም፣ ቢደክመውም እባብ አንጎል ከጥቂት ቆይታ በኋላ ደረሰ:: እንደዚያ በመረጃ ጥቅጥቅ ያለ የብልት ዝርያ አጋጥሞት አያውቅም:: በምስሎችና በቀላል አመልማሎ በመሰሉ ሐሳቦች የተሞላ ጭንቅላት ነበር:: የአንጎሏን በር ከፍቶ ሲገባ በላዩ ላይ እንደ ጐርፍ ተንደው ሊያፍኑት ደረሱ:: ብዙዎቹ ግን የመብልና የመብላት ሐሳቦች ናቸው:: የአእምሮዋ ክፍሎች ጠቅላላ ወይ በምግብ ምስል ታጭቀው የተሞሉ፣ ወይ አዲስ መሞላት የተጀመሩ ናቸው:: የእባቢቱ ዕውቀት ሆድ ነው:: የብርቱካን፣ ሎሚ፣ ዝንጅብል፣ ባቄላ፣ አናናስ፣ ሮማን፣ እንኮይ.....እና ሌሎችም እሱ አይቷቸው የማያውቅ እንግዳ የፍራፍሬና የቅጠላ ቅጠል ምስሎች ናቸው......በመጨረሻ ከነዚህ ሁሉ ትርምስምስ የሀሳብ ምስሎች መሐል የበለስ ዛፍ ብቅ አለች:: የዝናብ ጊዜ ምስሏ፣ የፀሐይ ጊዜ ምስሏ:: ሺህ ምስሏ:: ከዚያ የአዳምና የሔዋን ምስል:: ሔዋን ስትሮጥ ምስል:: አዳም ተኝቶ ምስል:: የዛፏ፣ የአዳምና የሔዋን ምስል:: ብዙ ጊዜ ምስሎቹ ከሰማይ ላይ ሆነው የተሣሉ ናቸው:: እባቢቱ ዛፍ ላይ ወጥታ ይሆናል ብዙ ጊዜ የምታያቸው:: ሰይጣን ገና ዛፏን ሲያያት የበለስ ተክል መሆኗን መረዳት አልተሳነውም:: እንደተቀመጠ ዙሪያውን የሚንሳፈፉትን ምስሎቿን በጣቱ እየነካና እያፈረሰ ፈገግ አለ:: አንጎሏ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ የሚሠፍርበት ቦታ ፈልጐ ፈልጐ ተስፋ ቢቆርጥ አረፍ ብሎ መተከዝ ጀመረ:: ትክዛው ግን የሴራ ነው:: አንዱን ክፍል ከምግብ አፅድቶ ሊጠቀምበት ፈለገ:: ይኼ ግን አይሰራም:: ከመጀመሪያው እባቧን መሳፈር የፈለገው ጭንቅላቷ ውስጥ ለክህደት የሚሆን የተመቻቸ ባዶ ቦታ ይጠብቀኛል ብሎ ነበር:: አንጎል ውስጥ ለክሕደት የተከለሉ ቦታዎች ብዙ ጊዜ ወለላቸው በቂንጥ የተለሰነ፣ ግድግዳቸው ግራጫ የተቀባ ጣራቸው ደምና የደም ውጋጋን የማያስገባ ነው::

የጅማት፣ የንፍጥና የልፋጭ ግድግዳ ተደግፎ እግሮቹን ዘርግቶ ሲያስብ ፊት ለፊቱ ማየት በሚያዳግት በቀስታ የሚርገበገብ ስስ የሞራ ግድግዳ አየ:: በመጀመሪያ የዐይኖቹ ግድፌት መስሎት ነበር:: ዐይኖቹ ገድፈው አያውቁም::

ቢሆን ቢሆን አይኖቹ አስተካክለው ያዩትን ነገር አእምሮው በተንኮል ዕውቀቱ አጣሞ ይተረጉማቸዋል እንጂ፣ ዐይኖቹ በፍፁም ተሳስተው አያውቁም:: ከሕዋሳቶቹ የሰላ ክፍል ቢኖረው ዐይኖቹ ናቸው:: ሰሜን ዋልታ ተቀምጦ ደቡብ ዋልታ መቀላወጥ ጨዋታ ነው አያሰኝም:: ደቡብ ዋልታ ተቀምጦ ሰሜን ዋልታ ላይ የሚንደባለሉትን የሞርስ ጂሞች እንደ እጁ ጣቶች ይቆጥራል...... ይሄ እንደ እግዚአብሔር አቅም ነው:: ከዚያ እንደገና የተገረመ እጁን ዘርግቶ በአመልካች ጣቱ ይሔን የጅማት ዐይነ-ርግብ በቀስታ ነካ ነካ አደረገው:: ተንደለ:: ሰይጣን ስለ ፍጡራን ብዙ ዕውቀት ቢኖረውም እንዲህ የተለየ ነገር ሲያጋጥመው ደነገጠ:: የመጀመሪያው ነው:: የዚህ ዐይነት የአእምሮ አከፋፈል አይቶ አያውቅም......እስከ ዛሬ ያጋጠመው አከፋፈል ግልፅ ነው:: ከክፍል ክፍል ሲሄድ ገና ከደጃፋቸው ለምን ማጠራቀሚያ እንደሆኑ የሚለይ ምልክት ነበራቸው:: ከተጋደመበት ተነሳና ጣቶቹ ላይ የተጣበቀውን ልፋጭ አራግፎ የተቀደደውን ጅማት ግራና ቀኝ እየከፈተ ጭንቅላቱን በቀስታ ወደ ውስጥ ሰደድ አደረገ:: ግድግዳዋና ጠፈሯ ግራጫ የሆኑ ክፍል ናት:: የምን ቦታ እንደሆነች አወቀ:: ግራጫ ቀለም ያላቸው ክፍሎች የጥርጣሬ ክፍሎች ናቸው:: ይቺንን ማንም አጋንንት ያውቃል:: አልፈነጠዘም:: *የገነት እንስሳት ቀስ በቀስ እየተለወጡ ነው እንዴ? ሕይወታቸው እየሰለቻቸው በልቦናቸው ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል እንዴ? ወይስ ለመደፈር፣ ለመደፈር እንድትችል እግዚአብሔር ይቺን እባብ መርጦ የዚህ ዐይነት ክፍል ሰራላት? እግዜር ገነትን የማፍረስ የረጅም ጊዜ አላማ ነበረው እንዴ?* ሠይጣን እዚህች ግራጫ ክፍል ተቀምጦ ሺህ ጥያቄዎች እስኪደክመው አወጣና አወረደ:: አወረደና አወጣ:: በመጨረሻ ምን አገባኝ! እንደማለት እጁን አወናጨፈና ገነትን ማፍረሻ አጭር እቅዱን በአራት ተራ ቁጥር አሰላስሎ አስቀመጠ::

1: *እባብ ከውስጧ የሚያስተላለፍላትን ትዕዛዙን ትቀበል አትቀበል እንደሆነ ጥቂት ፈተናዎች መስጠት*
2: *የበለስ ዛፍ ላይ መሳፈር*
3: *የሔዋንንና የአዳምን የቀን ውሎ ሳያሰልሱ መከታተል*
4: *ሔዋን ወይም አዳም ፍሬውን እንድትበላ/እንዲበላ መጐትጐት::*

እነዚህ አጠቃላይ ንድፎች ሲሆኑ በየራሳቸው አስቸጋሪ ረቂቅ የሆኑ ንዑስ እቅዶች ያዝላሉ:: በተለይ አራተኛው ጅምላ ንድፍ በሰው ልጅ ታሪክ የሚነገርለት ወይ ከማበሳጨቱ የተነሳ ከነጭራሹ ለመረሳት የሚፈለግ ጉዳይ የሠፈረበት ነው:: (አንዳንድ ፈላስፎች ግን የሚደነቅ ገድል ነው ቢሉም)

ብዙ ሳይቆይ ሰይጣን ይህቺን ግራጫ ክፍል እንደ ግሉ የምድር ለምድር ቤት ቆጥሯት ውስጧ መሮጥ፣ መብረር፣ መንፈላሰስ መንጋለል፣ ማናወዝና ማንዛረጥ ጀመረ::

## ማን ናት?......

እባቢት የአእምሮዋ ሁኔታ ሲለዋወጥ ይሰማታል:: የሆነ ነገር በትንንሹ

ይኮረኩራታል......በትክክለኛውና በለመደችው ነገር ውስጥ ሁሉ......ስህተት ነገር ያለ ይመስላታል። ለምንድነው ያ አመልማሎ ዳመና ወደ ሰሜን የሚጓዘው? ፀሐይዋ ዙሪያ ያለው ቀስተ ዳመና ምን ልሁን ብሎ እዛ ሄደ?......ቀለማት ስንት ናቸው? ዛፎቹ ወደ ላይ ለምን ያድጋሉ? ከበለስ ዛፍ ላይ እንዲህ ያወጣኝ ዐይነምድር ለምን ወደ ታች ሄዶ ወደቀ? ይህቺን የምታምር ዕንቁራሪት ከዕንቁላሎቿ ላይ ገፍፌ እንዲህ ብበላት ምን ይጎልባታል? ጥያቄዎቹ እንደ ደም በገላዋ እየተሰራጩ ቀድሞ ከውስጧ የነበሩትን ክፍት ቦታዎች የደፈኑ መሰላት......ለመሆኑ ክፍት ቦታ ነበር? ይህ የተሰማትና ስህተት የመሰላት ነገር ግን ምሉእ መሆኗ ነው። ከጥቂት ሰአታት በፊት ምሉእ አልነበረችም። ጥያቄዋና ድርጊቷን የሚያያይዝላት ነገር አልነበረም። ይኼን ድፍረት ሰራው። የጐደላት ድፍረት ነበር።

እሷ ሰይጣን መሆኑን አታውቅም እንጂ ከተሳፈራት ጀምሮ ቀድሞ በማትሔድበት ጐዳና ላይ፣ ቀድሞ ደፍራ በማታልፍበት ጥሻ ውስጥ መተላለፍ፣ መራመድና መዝናናት ጀምራለች። የገረማትና ድፍረቷ የተለየ ችሎታ እንደ ሰጣት የተረዳችው፣ ሌሎች እንስሳት እየተገላመጡ እሷን ሲያዩዋት ነው። በኤሊ አቅም እንኳን፣ እንደ አሸን ከሚርመሰመሱት አንዷ፣ ድንጋይዋን እየጎተተች 'ከየት መጣች?' ብላ ለከበቧት መሰሎቿ ሹክ አለች።.....በገነት ውስጥ በግልፅ ካልተመዘገቡት እርግማኖች አንዱ ሐሜት ነው። ትናንት አይተው በናቋት ትንንሽ እዚህ ግቡ የማይባሉ እንስሳት (ድንጋይ ተሸካሚ ኤሊ፣ ቅርናታም ጥርኝ፣ በጠጣም ፍየል፣ ፎከታም ውሻ፣ ትሎችና ትላትሎች ወዘተ......)እፍ 'አስቀያሚ' ተብላ እንዳልተገለለች ሁሉ ዛሬ ያውም በአጭር ጊዜ ከገነት ወጥታ በገባችበት አፍታ በብዙዎቹ አንደበት 'ማናት?' መባል ተጀመረ። ለአባብ ይሔ ነገር አልጣማትም። ፍጥነቱ ብቻ ሳይሆን የመገረማቸው፣ የስያሜአቸውና የጥያቄአቸው መመሳሰል የጠበቀችውን ያህል የፍስሐ ስሜት አልሰጣትም። 'ማናት?' ተብሎ የሚነሳው ጥያቄ ቀድሞውኑ መልስ ይሰጥበታል። 'ያቺ አስቀያሚዋ የነበረችው እባብ እኮ ናት' መባሉ አይቀርም። አስከፊ ነው። ጥያቄውን አስከፊ የሚያደርገው ተከትሎት የሚመጣው መልሱ አስከፊ ስለሚሆን ነው። ገነት ከታሪክ ውጭ ተንሳፋ ያለች ብትመስልም ድሮዋ እየተቆፈረ (ሃላፊ ጊዜ) የፍጡራን አፍረት ተመልሶ እንደ አዲስ ደረታቸው ላይ ይፃፋል፣ ይታረሳል፣ እንዲያብብም ሆኖ ይዘራል። እንዲያፈራም ይፀለይለታል። ይኼን እዛ ውስጥ የሚርመሰመሰው ቂላዋት ፍጡር ሁሉ ባይናገረውም በሆዱ ያውቃል። የሐሜት ቀለምና ይዘት በቅዱስ መንፈስ ትዕዛዝ እንኳን አይፋቅም። ቢለወጡም የማይለወጥ ነገር አለ። እሥረኛን ግን ከየቀኑ ትንንሽ የሐሜት ጨዋታ ሌላ ምንስ ሊያዝናናው ይችላል? ይኼ የተመሳቀለ ሐሜትን ፈርቶ የመሸሽና ደፍሮ ለመታየት የመፈለግ ስሜቶች እባብን በእጅጉ አደናገሯት። መታየት በሚቃረነው የመሸሽ ስሜት ይታገዳል። መሸሽ መታየት በመፈለግ ስሜት ይታገዳል። ሠይጣን ጨለማ ጓዳው ተቀምጦ ይኼ ዐይነት የወልዋላ ስሜት መልዕክት ገና በትክክልና በጥልቀ ካልገሰሰው የእባቧ የሃሳብ ጓዳ ሲደርሰው ውሳኔውን ሰጠ። ሁለቱ ስሜቶች አንድ ላይ ሊሆኑ አይችሉም እንዴ? ማን ከለከለ? ለዚህም ድርጊት ቦታው ተዘጋጅቷል። የግጭት ስሜት ሲተረሽ 'የምናባቱን' ስሜት ይፈጥራል። ይኼ ስሜት በበቂ የጥፋት

ጨረር ከተመታ የማያፍር ምፀት ይሆናል፣ ምፀት ደሞ የሰይጣን አገር ነው......
የምፀት አገር ዋና ከተማው ሰይጣን የሚንፈላሰስበት ምፀት ራሱ ነው:: ተቃራኒ ስሜቶች ተቺ አስተሳሰብ ሲጎንጉኑ ከሁለቱ አንዱ በነሲብ ይመረጥና ውጤቱ በዕድልና በአጋጣሚ ድግምቶች የተገዛ የቁማር ኪነት ይሆናል:: ይኼን መዝለቅ አለበት:: ሁለቱን አስማምቶና አጣልቶ መብቀል አለበት:: የተለያየ ተቃራኒ ሳይሆን የተጋመደ ተቃራኒ መሆን አለበት:: አሸብራቂ አያዎ::

እባቢት በሰይጣን ትዕዛዝ እየተገፋች ገነት ማዕከል የተቀመጠችው የበለስ ዛፍ ዘንድ ሔደች:: ምሽት ተቃርቦአል:: በመጀመሪያ ያደረገችው ነገር ቢኖር በዛፉ ላይ እየዳኸች ወጥታ ቅርንጫፎች መሐል መስፈር ነው:: ታቹን ከወንዙ ዳር ስድስት ቡራቆች በሰልፍ ተደርድረው ውሐ ይጠጣሉ:: ቡራቅ ውሐ ሲጠጣ የትም ይሰማል:: የነሱ ዘመዶች የሆኑት አህዮችና ፈረሶች በዚህ ኳኳታም ፀባዩ 'እናፍርበታለን' የሚሉት ፍጡር ነገር ነው:: ውሐውን በጥማት እየጮሁ እንደሚጠጡትም ብዙ ሳይቆይ ይጠግቡና ስፋታቸው የሚያስደነግጥ ነጫጭ ክንፎቻቸውን ዘርግተው እያናፉ ከዛፎች በላይ ይነሳሉ:: በዚህ የሰከረ አነሳስ መሃል የሚያራግፉት ላባ የወንዙን ጠለል እንደ ቢሶስ ይሸፍነዋል:: በአህዮችና በፈረሶች ላይ የሚስቁት ይሄኔ ነው::

እባቢት ዛፉ ላይ ስትወጣና ስትጋደም ከፍተኛ ደስታ ተሰማት:: አድርጋው አታውቅም:: ሌሎች በውበታቸው የሚኩራሩ ነፍሳት በለስ ዛፍ ላይ እየወጡና እየወረዱ ሲላፉ ለእሷ ለአስቀያሚዋ የማይገባ ቦታ እየመሰላት በማፈር ትሸሽ ነበር:: ታዲያ እሷንም ይሁን ሌሎችንም እንስሳት እንዲገርማቸው አድርጋ ዝንትንት ብላ አንዱ የበለስ ቅርንጫፍ ላይ ተጋደመች:: የመጀመሪያው የድፍረት ጠበል ነው:: ይኼ ጠበል ራሱን እየጠጣ ዐይነት የሚያድግ አስካሪ ቅመምነት ነበረው:: ችግኙም የራሱን የእርካታ ጠበል እየጠባ ዐይን እስኪሞላ ይንዠረገጋል:: ድፍረት ሲሰፋ ደ'ሞ ትዕቢት ይወልዳል:: ይሄ ደ'ሞ ሰፊ ጥያቄ ለመቀስቀሻ መሰረት ይሆናል:: ጥቅሻ፣ ቅጥጥብ የነበረችው ነገር አስደንጋጭ ትኩረት ትሆናለች:: ሠይጣን ከዚህች ትንሽ የእባብ ድርጊት የገባው ነገር ቢኖር ገነት የቆመችበት መሰረት ይኼን ያህል ጠንካራ አለመሆኑ ነው:: በእሷና በሌሎች እንስሳት መሐል በቀላል የአካል ልዩነት ('የውበት' ልዩነት) ሽብልቅ ሊገባ እንደቻለ ሁሉ፣ በእነዚህ አዳምና ሔዋን በሚባሉ ሁለት ሰዎች መሐልና በፈጠራቸው ጌታቸው መሐል አለመተማመንን መሻጥ እንደሚቻል ነው:: ሽብልቋ በለስ፣ መዶሻው የእባብ ልሳን ነው:: ይኼ እውነት ወይም ዕውነት የመሰለ ነገር አስደንቋት እባብ ለራሷ ፈገግ አለች:: ለመሆኑ እሷ የምታስበውን ሌሎች እንስሳት ያስባሉ? አለማሰባቸው የበላይነት ስሜት ሰጣት:: ግን እሷ አሰበችውና ምኑ የበላይነት ይሆናል? እንዲህ ማሰብን የበላጭነት ቦታ የሰጠው ማነው? እንደ ዞረባት ሁሉ ዓይኖቿን ስትጨፍን አእምሮዋ ውስጥና በሰራ ገላዋ ደም ስር የሆነ የሚጣፍጥ ነገር ሲፈስ ተሰማት:: ሰይጣን የከመከመላት ሀሳብ ልዩ ፍላጎት በልቦና ያነግሳል—ዐይን ጨፍነው የሚያዳምጡት 'ዝም ያለ' ሙዚቃ ነው......አድርጋ የማታውቀውን ለመጀመሪያ ጊዜ በለስ ዛፍ ላይ በኩራት የተሞላ እንቅልፍ ተኛች......ከላይ እስከታች የቆዳዋ ጠለል ልትገልፀው በማትችል የሚጣፍጥ ፍትወት ይነዳል......

**አካም!......**

......ሔዋን የሙቅ ውሐው ኩሬ ውስጥ እንደደረሰች ዘላ ገባች:: የምትወደው ዐይነት አወኛኘት ነው:: ዘላ መግባት ትወዳለች:: ምድር ስትለቅ አይደለም:: ስውነቷ ውሐውን ሲመታውም አይደለም:: መሐል ላይ ስትሆን:: በአየር ውስጥ ስታልፍ:: አሞራ የሆነች ሲመስላት፣ ገላዋ ሲቀላት:: ውሐ ውስጥ ገብታ ብቅ ስትል ያየችው ሁለት ነገሮች ነው:: ውሐው በመጮሁ ተደናግጠው ከየዛፉ በድንጋጤ በርግገው ሰማዩን ጢም አድርገው የሸፈኑትን ወፎችና በሚያምር ነጭ የፀሐይ ብርሃን ውስጥ የሚያባብል ነገር ሆና የቆመችዋን የበለስ ዛፍ:: የወፎቹን ነገር ለምዳለች:: የበለስ ዛፏ ውበት ግን ሆኖ በማያውቅ መልክ ልቧን ወሰደው:: የእግሮቿን ቁርጥማት ረስታ ውሐ ከዐይኖቿ ላይ በሁለት እጆቿ እየላገች ፈዛ ማየት ጀመረች::

ሰይጣንን መቀመቅ እንዲገባ ካደረጉት ጠባዮቹ አንዱ እንቅልፉ ነው:: ስንፍናው አይደለም:: ዕንቅልፍን ራሷን ይወዳታል:: እግዜርን ጠላቱ አድርጐ ቢቆጥረውም ዕንቅልፍ የሚባል ነገር በመፈልሰፉ ያደንቀዋል:: ቀኑን ሙሉ ባልለመደው የእባብ ደም ስር ሲመላለስና፣ ዕርጥብና ጨጋጋ በሆነች ጠባብ አንጎሏ ውስጥ ታስሮ መዋሉ አዳክሞት ተጣጥፎ ተኝቶ ነበር:: ድካሙ ዕንቅልፍ ጠራ:: ዕንቅልፍን ደ'ሞ ይወዳታል:: ሔዋን ባጋጣሚ ከከፍታ ቦታ ዘላ ውሐውን በገላዋ ስትመታው እባቢት ከዕንቅልፏ ባትባንን ኖሮ (የእሱን ይሁን የእሷን ዕንቅልፍ ተኝታ) ለዛሬ ጠዋት ያዘጋጀው የሴራ ገመድ ሳይሰራበት ይበጠስ ነበር::

ሔዋን ጥቂት እንደቆየች ከዛፉ ውስጥ የሚንኮሻኮሽ ነገር ሰማች:: ለማየት ድምፁን የሚፈጥረው ነገርና ፍጡር ምን እንደሆነ ለመረዳት ወዲያ ወዲህ አየች:: ከዚያ ካልጠበቀችበት አቅጣጫ ባልጠበቀችበት ጊዜ ከዛፉ ላይ:

«አካም!» አለ......የሚያምር እኩያ የሌለው ውብ የሆነ ድምፅ::

ሰላምታውን ልትመልስ ሔዋን ዙሪያ ገባዋን አየች:: በቅርቧ ማንም የለም:: በውሃ የተጠመቀ ፊቷን እያለበች ከዝላይዋ ያገኘችውን ደስታ ስታጣጥም:

«የምታምር ዛፍ ናት አይደል?» አለ ያው የሴት ይሁን የወንድ የሚያምታታ ውብ ድምፅ

«ማነው?» አለች ሔዋን

«እኔ ነኝ......በድምፅ እንኳን አታውቂኝም?» አለ እባብ::

«ኸረ እኔ እንጃ»

«ይገርማል በጣም ይገርማል»

«ምኑ ይገርማል?» አለች ሔዋን

«እኔን አለማወቅሽ» አለች እባብ::

«ሳላይህ እንዴት አውቅሃለሁ?» አለች ሔዋን

«በድምፄ:: በአንደበቴ:: ዝናዬን አልሰማሽም?»

«አልሰማሁም»

«ይኼ እኮ ነው የኛ ነገር»

«የማን ነገር?»

«እዚህ ገነት የምንኖር»

«ምን ጐደለ?»

«ምን ይጐላል እሱማ:: መምነሽነሽ ነው እንጂ:: ከአንድ ነገር በስተቀር» አላት::

«ምንም የጐደለ ነገር የለም» አለችው::

«ልጠይቅሽ:: የዚህ እርሻ ጌታ አላት:: ማነው?»

«እኔና አዳም ነን ጠባቂዎቹ»

«እም......እም:: በነገራችን ላይ በገነት ውስጥ ካየኋቸው ፍጡራን እንዳንቺ የሚያምር አላየሁም ብልሽ ታምኛለሽ?» አለቻት እባብ::

«ምን?»

«ማማር»

«ራሴን አይቼው አላውቅም:: አምራለሁ?» አለች ሔዋን::

«የጐደለው ሌላው ይኼ ነው:: አሁን ሳወራሽ እንኳን ሦስት የጎደሉ ነገሮች አጋጥመውኛል:: ልብ ካልሽ»

«ምን?» አለችው::

«አንደኛ የገነትና የዚህ ዛፍ ጠባቂ ሆነሽ እኔን አታውቂኝም:: በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ ማንንም እንስሳ ብትጠይቂ ስለ እኔ የማያውቅ የለም:: ሁለተኛ አንቺ ውብ እንደሆንሽ አታውቂም:: በጣም በጣም ውብ:: ሦስተኛ ሐላፊነት በተሰጠሽ ቦታ የፈለግሽውን ማድረግ አትችይም:: ስህተቱ ለምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ዐይኖችሽ አልተገለጡም»

«ዐይኖችሽ አልተገለጡም?»

«አዎ......አያዩም......»

«ያያሉ»

«ያያሉ ግን አያዩም:: የእኔ ያያሉ»

«ለምን ያንተ ያያሉ?»

«ጥሩ ጥያቄ ነው:: ይኸቺ የተቀመጥኩባትን ዛፍ ታያታለሽ?»

«አዎ»

«አታዪአትም! ከዛፎች ፍሬ ላይ የሚወርደውን ወለላ ታዪአለሽ? የቅጠሎቹን ወዝና ውበት ታዪአለሽ? አንዲት ቀን እንኳን ነሸጥ አድርጎን የፈጣሪያችንን ጥበብ ለማመስገን ስጦታውን ለማክበር ከዚህች ፍሬ ምሳሌ ወስደን ውስጡን ሰብረን አይተናል? ምርጥ ክብርትነቷን፣ ፍጡርነቷን፣ ረቂቅነቷን፣ ውበቷን፣ ምርቃትነቷን ተጠግተሽ አይተሽ አታውቂም። አንድ ነገር ከተከለከላችሁ በኋላ ዞር ብላችሁ አታዩትም። የመከልከል ትርጉሙን አለማወቅ ይሉሻል ይሄ ነው። አለማየት የሚባለውም ይኼ ነው። ለመሆኑ ይኸቺ ዛፍ ውብ አይደለችም?»

«ጌታዬ በጥበቡ የፈጠራት ውብ ናት»

«ጌታሽ የፈጠረውን ነገር ማመስገን የለብሽም?»

«አዎ አመሰግናለሁ፣ አደንቃለሁ፣ ይኼንንም ጠዋት ማታ ለእሱ በፀሎቴ አሰማለሁ»

«ውሸት ነው። ገነት ውስጥ ያለውን ሁሉን ነገር በመንካት ስታመሰግኚ ይቺቺን ዛፍ ግን አንድም ቀን አልነካሻትም። ሳትነኪያት ማመስገን አትችይም። ሳይነካ ማመስገን የሚችለው ማነው? የተባለውን አልሰማሽም?»

«ስላልታዘዝኩ አልነካም»

«አትንኪ አልተባልሽም። የተባልሽው አትብይ ነው»

«እኮ ያው ነው»

«ተይ የእኔ ቆንጆ......ተይ ተይ። አስተውለሽ ተናገሪ። መብላትና መንካት አንድ ነው? ምን ዓይነት ግዕዝ ያለበት ቦታ ነን እግዚአብሔር ሆይ»

«አይደለም ግን ይቀርባል»

«እሺ አድርጌ የማላደርገውን ላዋራሽ። ውሐ ጠምቶኛል ልበል። በጣም ጠምቶኛል ልበል። ውሐ ከመጠጣት ይልቅ ምላሴን ብቻ አውጥቼ......ልክ እንደዚህ ውሐውን በምላሴ ጫፍ ነክቼ ብመለሰው ጠጣሁ ይባላል?» አላት። ምላሱን በረዥሙ አውጥቶ ውበቱን እንድታይለት አድርጐ ወደ ውሐው ጠለል እየሰደደ። ከዛም በቀስታ ለአመል ወራውሬ በመሰለች የምላሱ ጫፍ የውሃውን ጠለል ጠፋው......የውሃ ደቃቅ ኳሶች ከኩሬው ጠለል ላይ ተፈናጥረው ተነሱና ያለ ድምፅ ሕብረ ቀለም እንዳለው ርችት ፈነዱ......

«ምላስህ በጣም ያምራል» አለችው ሔዋን በፈዘዘ ድምፅ።

«ስለ እኔ ምላስ እናቁምና ጥያቄዬን መልሽልኝ»

«ምላስህ እንዲህ ያማረ ከሆነ እግዜር መርጦ የሰራህ ነህ ማለት ነው»

«ጥያቄዬን መልሽልኝ ሔዋን!» ስለ ምላሱ እንዲወራለት ያልፈለገ ዓይነ አፋር መስሎ......

«ስሜን ማን ነገረህ?»

«የእመቤቴን ስም?......ጥያቄዬን። በፈጣሪሽ!»

«ምንድን ነበር ያልከኝ?»

«በምላሴ ውሐውን ብነካው ጠጣሁ ይባላል?»

«በፍፁም»

«እሺ እንበል እጅሽን እንደምላስ እንውሰደው። የዚህችን ዛፍ ፍሬ እንደ ውሐው እንመስላት። አሁን እንዲህ በጫወታ ለጫወታ የዚህችን ዛፍ ፍሬ በጣቶችሽ ብትነኪያቸው በላሽ ይባላል?»

«አይባልም»

ከመሐል ሔዋን መልስ እንደሰጠች ውሐው አጠገብ ከተንጠለጠሉት ፍሬዎች አንዱ ተበጥሶ ሔዋን እምትዋኝበት የሞቀ ኩሬ ውስጥ ወደቀ። እንደምታውቃቸው ብዙ ፍራፍሬዎች ወደ ታች እንደመስመጥ በቀስታ እየተንሳፈፈና እየተንከባለለ ሔዋን በቆመችበት አቅጣጫ መጣ። መንገድ ልትለቅለት ፈቀቅ ፈቀቅ አለች።

«ደካማ ነሽ» አለ እባብ

«እኔን ነው!?»

«አዎ። የፍሬዋ ነገር ማርኮሻል። ተማርከሽ ታያለሽ። ውሐው ውስጥ አወዳደቋ ወድቃም የምትንከባለልበት ሁኔታ ገርሞሻል። የልብሽን ግን መስራት የፈራሽ ነሽ። በአጭሩ ውሽታም ነሽ። ቢያንስ ንኪው እስኪ። ቀስ ብለሽ ንኪው። መንካት መብላት አይደለም ተባብለናል። በዚህ ተስማምተናል። በአጠገብሽ ሲያልፍ ንኪው» አለ እባቡ።

ሔዋን ግራ በመጋባት የተደበቀው ፍጡር የተወሸቀበትን ቁጥቋጦ አተኩራ ስታይ ቆየች። ከመሐል የእባቡ የሚያምር ምላስ ውልብ አለና ሦስት የሚያማምሩ የበሰለ ፍሬዎች በውሐው ላይ እየተንሳፈፉ በእሷ አቅጣጫ መጡ። ውሐ ውስጥ ሲያርፉ የወለዷቸው ቦጭታዎች ግን ሌሎች ፍሬዎች ሲወድቁ የሚያወጡትን አይነት ድምፆች አልነበሩም። ስልት ባለው መንገድ በተቃኘ ድህንፃ ላይ የሚጋፉ ነፋስ ሲተም ዐይነት። በለዘብታም ጥፍራቸው የተከረከመ አለንጋ ጣቶች በፍቅር ይዘው ሲከረክሩት ዐይነት። ይሔ ድምፅ ከውሐው አወራረድ ጋር ከተክሎች የቅጠል ንቅናቄና ሿሿታ ጋር ልብ ይወስዳል። ፍሬዎቹ ፊትና ኋላ ሆነው እየተከታተሉ በሔዋን አቅጣጫ መጡ። የመጀመሪያውን ፍሬ ትኩር አድርጋ እያየችው አልፏት ሔደ። ሁለተኛውን ለመንካት ፈለገችና የሰደደችውን እጇን በፍርሐት ቶሎ መለስ አደረገችው። ሦስተኛው ፍሬ እንደ ቀደሙት ሁለቱ እየተገለባበጠ እየተንሳፈፈ አልፏት እንደ መሄድ አለና የቆመ መሰለ። የሚያምር በወዝ ጨፍ ያለ ቆዳውን እያሳየ «እቆመበት» ነጥብ ላይ ፈልሰስ ማለቱን ቀጠለ። ከውሐው ስር የሆነ እጅ ተደብቆ ይኼም እጅ በፍሬዋ እንቁልልጭ የሚጫወት ይመስላል። ሔዋን እጇን ሰዳ ፍሬውን ያዘች። ከፍሬው ሆድ ውስጥ አናሳ ንቅናቄ የሰማች መሰላት፣ እንደ ትንኝ ልብ ምት። በድንጋጤ በለሷን ለቃ እጇን ስትመልስ ጣቶቿን ወደ አፏ ወደ ከንፈሮቿ ወሰደች።

የፍሬውን የጣዕም አስማት ያወቀችው ይኼን ጊዜ ነው:: ሰውነቷ የሞቀ፣ ደሟ አዲስ ሐይል ያገኘ፣ ከውስጥ በሁለመናዋ ተሰምቷት የማያውቅ ፍስሐዊ ስሜት የፈነዳ መሰላት:: የዚህ ተስተካካይ ዐይነት ጣዕም፣ ጠረን ያለው ፍሬ ወይም ምግብ ከዚያ በፊት ቀምሳ እንደማታውቅ ተረዳች:: ይኼም መረዳቷ አሳፈራት፣ አስፈራት:: እግዜር ይኼን ለምን እንዳይበሉ እንደ ከለከላቸው እያሰበች በመገረም አተኮረች:: ከመሐል ሌላ አንድ ፍሬ ከበለሷ ዛፍ ላይ ሰው በጥሶ እንደ ጣለው ሁሉ ኩሬው ውስጥ ወደቀ:: በሔዋንም አቅጣጫ በውሐው ላይ በፍጥነት እየጋለበ መጣ:: ይኼን ፍሬ ሔዋን በስስት አነሳቸው:: ላፍታም ሳትግደረደር ገመጠችው:: የፍሬው መረቅና ቅርፊት ገና ጥርሶቿን ሲነካ እየቀለጠ በጉሮሮዋ ወረደ:: እንደ ሰከረች ነገር ሆነች:: ዓይኖቿ በሕብረት፣ በዝግታ ተጨፈኑ:: ፊቷን ወደ ሰማይ አንስታ አፏን በመማረክ ከፈተች:: በአፏ ግራና ቀኝ ከተከፈተው ፍሬ የወጣው የሚያጥበረብር፣ በቀስታ የሚሳብ መረቅ ነበር......በዚህ ሰፊና ጥልቅ ዕርካታ መሃል......መጀመሪያ የገመጠችውን ውጣ ዓይኖቿን እንደ ጨፈነች ቁና ቁና እየተነፈሰች ውሃ ውስጥ በቀስታ ቁጢጥ አለች:: ሁለተኛ ልትገምጥ ስትል ገላዋ እንደ ደነገጠ ሁሉ ተሰበሰበ:: የጨፈነቻቸው ዐይኖቿን ስትገልጥ ነፋስ በሰራ አካላቷ ውስጥ የነፈሰ ገላዋንም የቀለላት መሰላት:: ሠይጣን ወደ ኩሬው ጠለል የሰደደውን ምላስ ወደ እባቧ አፍ ውስጥ ሰብስቦ ፈገግ እያለ ያያል:: ሔዋን የምትበላውን ፍሬ አጋምሳ የነበረችበት ኩሬ ውሃ ውስጥ ቆመች:: ዝቅ ብላ ስታይ በተገነዘበችው ነገር ደነገጠች:: ፍሬውን ወርውራ ከውሐው ውስጥ በሩጫ ወጣች::

«የት ነው የምትሔጂው? አላለቀም» አላት እባብ::

«ምን ሆንኩ:: ምን ሆንኩ?» አለች::

«ምን ትሆኛለሽ?» አላት እባብ በማኪያኪያስ

«ይልቁን እራቁትሽን ሆነሽ ማየት አልፈልግምና ውሐ ውስጥ ገብተሽ ማድረግ የሚገባሽን ነገር ልንገርሽ»

«ምን ሆንኩ?»

«ራቁትሽን ሆነሻል»

«ምንድነው ራቁት መሆን?»

«በቀላሉ ሲተረጐም ከጥቂት ጊዜ በፊት ገላሽን ሸፍኖት የነበረው ፀጉር ረግፎ–ጡቶችስ ሲታዩ፣ አባለዘርሽ ሲታይ፣ ቂጥሽ ሲታይ ማለት ነው:: የሚያሳፍር የለውም:: የሚያሳፍረው ብቻሽን እንደዚህ መሆንሽ ነው»

«እያየሽኝ ነው?» አለችው::

«ምናለበት:: አትጐጂም:: በጣም የሚያምር ገላ ነው ያለሽ:: ይኼን የመሰለ ገላ በጭገር መሸፈን ወንጀል አይደለም? የምትጐጂው መቼ እንደሆነ ታውቂያለሽ?» ሔዋን አልሰማችውም:: በረዥሙ ያደገ ፃር መሐል በሁለት እጆቿ ጭንቅላቷን ይዛ ቁጭ አለች:: የምታስብ፣ የምትተክዝ ወይም ከባድ ራስ ምታት የያዛት ትመስላለች:: ውስጧ ሀሳብ ይርመስመሳል......በፊት የማታውቀው

መኖሩን ያልተረዳችው መስየም የማትችለው ስሜት ፍሬዋን በመቅመሷ የተገደደ ዓይነት ከተደበቀበት ተገፍትሮ እንደወጣ ያህል ይሰማታል:: ከውስጥ ከልቧ እስከዛሬ መኖሯን ያላወቀቻት ትንሽ በር ሲጢጢ ብላ ተከፈተች:: ምን ማድረግ እንደሚገባት አታውቅም::

ሰይጣን ሔዋንን ድርብ ስህተተኛ ሊያደርጋት ፈለገ:: ወደ ረግረጉ መስመጥ ከጀመረች ለምን ቀስ ብሎ ወደ'ዛው ወደ ምትወርድበት አይገፋትም?

«የምትጎጂው ብቻሽን ስትሆኚ ነው......ብቻሽን ራቁትሽን መሆን ይጐዳሻል» አላት እባብ ቀስ ብሎ::

«ይጐዳኛል? ምን አደርጋለሁ ግን?»

«ከፋሽ?»

«አልከፋኝም:: ደስ የሚል ነገር አለው:: ግን ያስፈራል»

«አላልኩም:: አላልኩም:: ብቸኝነት:: ተቻኩለሽ ብቻሽን በላሽው፣ ተይ ልልሽ ነበር (ሊላት አላሰበም):: ለዚህም ነው:: እመኚኝና የምታስቢውን ንገሪኝ:: ልንረዳዳ እንችላለን:: ዕውቀት መሐይምነትን ይፈጥራል:: መሐይምነት በዕውቀት ይጠፋል:: እንደገና ያሸነፈው ዕውቀት በመሐይምነት ይጠፋል:: እንዲህ እንዲህ ነው አየሽ:: የሚያልቅ ነገር የለም:: ይመስላል ግን የለም:: ከዚህ ነው ደስታ የሚገኘው:: ወደ ዋናው ነገር ልመልስሽና እንዲህ ሆነሽ ብቻሽን መኖር የለብሽም:: ከዚህ ደስታሽ ለጊደኛሽ ለአዳም አካፍይው:: አይመስልሽም? እኔ ብሆን እንደዚህ ነበር የማደርገው:: ደስ ያሰኘኝን ነገር ከጊደኛዬ ጋር እካፈለዋለሁ:: አይደለም?»

«እያሰብኩ ነበር:: ግን እንዴት......?»

«መላ አይጠፋም:: አዳም ከበላ በኋላ አንድ ላይ ስትሆኑ ከምታገኙት ደስታ ትንሽ ባስተዋውቅሽ እወዳለሁ»

«ምን ደስታ ይኖራል ሌላ? እንደዚህ የሚያስፈራ እንዲሆን አልፈልግም»

«እስክትለምጂው ነው:: የፍሬዋ ቅመምና ጣፋጭነት ለምላስ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ሰውነትን ነው የሚሰማው:: አይደለም እንዴ? ይኼን እንኳን አልነግርሽም:: ከነዚህ የሰውነት ክፍሎች እግሮችሽ መሐል አሁን ድረስ ፀጉር ተሸፍኖ ያለው የገላሽ ክፍል አንዱ ነው:: ይኼ የገላሽ ክፍል ከማንኛውም የሰውነትሽ ክፍል የበለጠ ፍሥሐ የሚፈልቅበት ነው:: ፍሬዋን ከመብላትሽ በፊት ይሰጥሽ የነበረው አገልግሎት አንድ ብቻ ነበር:: ከአሁን በኋላ ሁለትና ሦስት አገልግሎት አለው:: እስኪ ዳብሺና እይው»

«እ......እ......ፈራሁ:: እምቢ»

«አትፍሪ......እሱን እንዲነኩልሽ የምትለምኝበት፣ የምትለማመጭበት ጊዜ ይኖራል:: ካፈርሽ ተይው:: ነገር ግን አዳም ሲመጣና ፍሬዋን ከበላ በኋላ ለእሱም ቢሆን ለአንቺ የጠቆምኩሽን የአካላታችሁን ቦታ ብትፈታተሹ ጥሩ ነው:: ደስታ እዚያ ውስጥ ነው......»

«ለመሆኑ......» አቋረጠችው «አዳም መብላት አለበት?»

«ብቻሽንማ አይሆንም:: ብቻሽን በፍፁም አይሆንም:: እሱን አይደለ የምነግርሽ»

«ምን ላድርግ?»

«እኔ ይኼን መምከር ይከብደኛል:: እንደ አንቺ ብሩህ አይደለሁም:: የቀረውን ለአንቺ ትቼዋለሁ:: መላ ፈልጊ ራስሽ:: መላ አታጪም»

## እቱ መላ ምቺ......

ሠይጣን ሔዋንን ፍሬ እንድትበላ ካደረጋት በኋላ የነገሩን መጨረሻ ሳያይ ተነስቶ ከገነት መውጣት አልፈለገም:: በዚህ ጉጉቱ እተንጠለጠለበት ዛፍ ላይ እንደ ተጋደመ ቀጥሎ የሚሆነውን መጠርጠር ጀመረ:: ከዛፉ ላይ ሆኖ ያያታል:: ፀጉሩ የረገፈ ቀይ ዳማ ቆዳዋን ትዳብሳለች:: እጅግ ገርሟታል:: ውበቷ ደ'ሞ ከገነት ውጭ ካሉት ፈሊሞዎችና የሰው ልጅ ሴቶች የሚበልጥ ነው:: ሰይጣንን የእግዜር ሐያልነት አስቀናው:: የዚህ ዐይነት ዳሌዎች፣ እንዲህ ዐይነት ጡቶች፣ እንዲህ አይነት ዐይኖች የሚፈጥር እግዚአብሔር ችሎታው ከፍተኛ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው:: ሔዋን ገላዋን ፈትሻ ፈትሻ የሙቅ ውሐውን ኩሬ በቀስታ እያቋረጠች መጣችና ከበለስ ዛፍ ፍሬ አንድ ለቅማ ወሰደች:: እባብ ይኸቺን አምስተኛ ፍሬ ለአዳም የምትሰጥ መሆኗን ገምቶ ድምፁን ዝቅ አድርጐ ሳቀ:: ሔዋን ፍሬውን በአንድ እጇ ይዛ በሣሩ ሜዳ ውስጥ መሮጥ ጀመረች:: ከመሐል ቆመችና ወደ ላይ አንጋጣ ወደ ተከፈተው ሳንቼር ወደ መሰለው ሰማይና ወደ ከበባት የጠቆረ ሐመልማል እሪታዋን ለቀቀችው:: ኡኡኡ ኡኡኡኡኡ ኡኡኡኡኡ ኡኡ ኡኡኡኡ ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ እባቡ ግራ ገብቶት ከተቀመጠበት የበለሷ ዛፍ ዝቅተኛ ቅርንጫፍ እንደ ሽሽት በቀስታ ወደ ላይ ወጣ:: የዚህ ዓይነት ድምፅ የትም ሰምቶ አያውቅም:: ሔዋን እንደገና ኡኡታዋን ለቀቀችው:: የዚህ አይነት ጩኸት በገነት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሰማቱ በየአቅጣጫው ያሉ አውሬዎች ነፍሳትና በራሪ ነገሮች ተደነባበሩ:: ለሔዋን ለራሷ ይኼ ዓይነት ድምፅ ከእሷ የወጣ አልመሰላትም:: ድምፁ ለዘመናት ውስጧ ተቀምጦ እየበሰለ፣ እያደባ የሚወጣበትን ቀን ሲጠብቅ የኖረ ይመስላል:: መጀመሪያ ከጉሮሮዋ ሲወለድ የሆነ ጥርጣሬ ነበረው:: እንደ ሳል ነበር:: ቀኔ ዛሬ ይሆን እያለ እያሰበ፣ ልውጣ አልውጣ እያለ እየሰላሰለ:: የሔዋን ሩጫና በጡንቻዎቿ የሚፈሰው የድንጋጤና የፍርሃት ስሜቶች እንደ አበረታቱት ዐይነት ተፈትልኮ ሲወጣ ሔዋን ቆማ አፏን ይዛ ያፈለቀችውን የድምፅ ትዝታ አተኩራ አሰላሰለች:: ምክንያቱም 'ኡኡኡ!!!' ብላ አታውቅም:: እውስጧ ይኼ አጃቢ ድምፅ እንዳለ ይገባታል፣ ግን እንዲህ ቀላል ተርታ ረቂቅነት ያሌለው ነገር አልመሰላትም:: በለስን የመብላትን ያክል ስህተት ሰርቶ እንዴት ይሄን ዓይነት መናኛ ድምፅ ለማጀቢያ ታወጣለች? አንጀቷን የሚበላ የልጅ ልጆቿን የሚያሳጣ ስህተት ሰርታ ያን ስህተት የሚያጅበው ድምፅ ኡኡኡ!!! ብቻ ይሆናል? እዚህ ካሉ የወፎች ዘፈን ምናለበት አንዱን[76] እንኳን ብትሰራው?......

76 ሰይጣን ገነትን ካፈረሰ በኋላ አዳምና ሄዋን የልጅነት ሕይወታቸውን ሲነጋ ሲነጋ

የዚያ አይነት እንግዳ ድምፅ እዚያ አካባቢ መስማቱ አዳምን ግራ ስላጋባው ሁልጊዜ ከሚተኛበት ከግዮን ወንዝ መውጫ ከከሰላ ዳር እየሮጠ ሲመጣ ታየ:: እባቢቱ/ሰይጣን የሔዋን ተንኮል ገብቷት ከት ብላ ሳቀች::

አዳም እየሮጠ ሲመጣ ሔዋንን ሣር መሐል ቆማ ስትጮህ አገኛት:: በቀኝ እጇ ከኋላዋ ፍሬ ደብቃ ይዛለች:: አዳም ይኼን አላየም::

«ማነሽ አንቺ? እ? ሔዋን?» አላት::

«ሔዋን እኮ ነኝ አዳምዬ» አለችው::

«የእኔ ሔዋን? ፀጉርሽን ምን አደረግሽው?»

«የሚያቃጥል ውሐ ውስጥ ገብቼ እንዲህ ሆኜ ወጣሁ......እንደሱ አትየኝ ያሳፍረኛል»

«ተላልጠሽ የለ እንዴ:: የዚህ ዓይነት መጥፎ ውሃ አለ እንዴ?» በዝምታ ለረዥም ጊዜ በመገረምና በተመስጦ አያትና:

«ምን የሚያሳፍር ነገር አለው......ይሁና......ምናለበት» አለ ቀጥሎ

«እንዴት 'ይሁን' ትለኛለህ? አውሬ መስዬ»

«ግድየለም ነይ:: ሔዋን እንደ ሆንሽ አልጠፋኝም:: የሌላው ገላሽ ፀጉር ጠፉ እንጂ አታሳስችም:: እኔ ቦታ ሔደን ቁርስ እንበላለን፣ አልበላሽም አይደለ? ያ ውሐ ያለበትን ቦታ ታሳይኛለሽ፣ ሌላ ጊዜ እኔም እንዲህ እንዳልሆን»

«እዚያ አንተ ቦታ መሔድ አልፈልግም»

«የት እንሒድ......?»

«እወዲያ ዋርካው ጋ» አለችው ከበለስ ዛፍ ጀርባ ወደ ቆመው ሰማይ ጠቀስ የአጋም ዛፍ እያሳየችው::

«እሺ እንሒድ......»

«ቁርሴን በልቻለሁ:: አንተም ብላ» አለችና ፍሬውን በጨረፍታ አሳየችው::

«የሚያምር ፍሬ ነው በእግዚአብሔር» አለ ውልብታ ብቻ ዓይቶ::

«በጣም ነው የሚጣፍጠው:: ብዙ ነገር አለ ጌታችን ሰርቷቸው እኛ

---

በትኩስ አእምሮአቸው እያስታውሱ እንዲበሳጩ፣ በዘፈንና በግጥም የታጀበ ዜማ ለዋኖሶች አስተምሮ ነበር:: ዛሬ ዛሬ የተለየ ነገር ተባለ እንጂ ቀድሞ እንዲህ ነበር:

*'ኩኩ መለኮቴ*
*ኩኩ መለኮቴ*
*ሔዋን በበላችው*
*በእባብ ለከከችው*
*አዳም በገመጠው*
*በሴት አላከከው*
*ኩኩ መለኮቴ*
*ኩኩ መለኮቴ'*

ያላገኘናቸው:: እንካ ብላ» ሊቀበላት እጁን ዘረጋ::

«አልሰጥም እምቢ:: ከእጄ ላይ ግመጥ» አለች ፍሬዋን ወደ ጀርባዋ ደብቃ::

«ምነው በእግዚአብሔር?» አፉን ከፈተ:: ፍሬውን አስገባችለትና ገመጠ:: በአፉ ዳርና ዳር ምራቅ ወጣ:: ወዝ ወጣ:: ቅባት ፈሰሰ:: 'ይጣፍጣል' ብሎ ለመናገር አፉን ሲከፍት......የሆነ ነገር ትዝ ብሎት ደነገጠ:: ሔዋንን ትኩር ብሎ አያት::

«ከየት አገኘሽው?»

«ከዚያ» አለችው ወደ በለስ ዛፍ ጠቁማ:: ይለይለት ዐይነት:: ቶሎ ያልተገነዘበችው አሁን የገባት ሁለት ነገሮች ነበሩ:: ማሰብ እንደ ምትችልና ይሄንንም ሃሳቧን ከማንም መደበቅ እንደ ምትችል ነው:: ቋንቋ ሆድ ውስጥ፣ የሆነ ሌላ የገላ ክፍል ውስጥ ታስሮ መቀመጥ እንደሚችል መረዳቷ የሆነ የእርካታ ስሜት ሰጣት::

የዋጠውን ለመትፋት ቢስልና ደረቱን ቢመታ መንገድ የጀመረው በለስ በራሱ ቅባት እያዳለጠ ወደ ሆዱ ወረደ:: ያኔውኑ አዳምን የሸፈኑት ፀጉሮች ከገላው ላይ ከስራቸው እየተነቀሉ ነፋስ ውስጥ እንደ እፉዬ መብነን ጀመሩ:: አዳም የሆነው ሁሉ ነገር ገብቶት መሬት ላይ ወድቆ ማልቅስ ሲጀምር፣ ሔዋን አዲስ ፀጉር የለሽ ትከሻውን አቅፋ ራሷን ራሱ ላይ አስደግፋ እንደ ማዘንና እንደ ይቅርታ ዓይኖቿን ጨፈነች::

ያሰበችውን ተንኮል አዳም መገመት አለመቻሉ ከባድ ዕውቀት ሆነባት:: ዓይኖቿን ጨፍና ተባይ የሚርመሰመስበት ፀጉሩን ተደግፋ የደረሰችበት አንድ እውነት እንደ ድሮው በጠረን፣ በስሜት፣ በወዝ የውስጥ ፍላጎታቸውን መናበብ እንዳቆሙ ነው:: እንደዛ ተደግፋው የጋራ ስቃያቸውን ሲሰቃዩ፣ በብርድ ሲንዘረዘሩ፣ በፍርሃት ሲርበደበዱ የእሱን አታውቅም እንጂ እሷ ስም ልትሰጠው ያዳገታት ጥ/ትልቅ ብቸኝነት ተሰማት......

ሰይጣን ይሄ ሁሉ ውበት እንዲህ በቀላሉ በቲያትር ሲፈርስ ማየቱ አሳዘነው:: ዕውነት በቲያትር ሲፈርስ:: ይኼ አስገርሞት ትንሽም አሳዝኖት እንደ ደከመው ሁሉ እያሰበ እዛው እባብ አንጎል ውስጥ መቆየት ፈለገ:: ከተጋደመበት መነሳት አልፈለገም:: ሰይጣንን ያስገረመው ነገር ቢኖር ሁሉ እንዲህ በቀላሉ ማለቁ ነበር:: ፊት ለፊቱ ያጋጠመችውን አንድ የበለስ ፍሬ በእባብ ምላስ በትከዛ ይልሳል፣ ምላሱን በቀስታ እያወጣ የፍሬዋን ሙቅ ከብነት በምላሱ ይዳብሳል፣ በምላሱም ቀላል ግፊት ፍሬዋ ቆዳ ላይ የሚያገኘውን ቅባት የመሰለ አውላ ያጣጥማል፣ በተቀደደም ቅርፊቷ በኩል በቀጭኑ የሚወጣውን ቃናው የሚጥም ወተት የመሰለ ጢስ እያየ ይገረማል:: *እንዴት ይጣፍጣል? እንዴት ብርድና ሙቀትን ሳይጣሉ አቀናበረ? ምን ዐይነት ብልሀነት ነው? ግን ግን ግን......እንዴት ሁሉ ነገር በቀላል ፈረሰ? እንዴት?*

## መንገዱ ጨርቅ አይደለም......

እባብ በለስ ዛፍ ላይ እንደተኛች ነው:: ሠይጣን ከአዕምሮዋ ወጥቶ መሔድ አልፈለገም:: በዐይኖቹ ባላጋራው እግዚአብሔር ክብሬ አርፎበታል የሚለውን ቦታ ሲናድ ማየት ጓጓ:: አንድን ነገር እንዲፈርስ ማሴር ብቻ ሳይሆን ስራውም መጠናቀቁን መመልከት የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ:: በመጀመሪያ አድራጊ፣ ከዚያ ተመልካች የመሆን:: የዚህ ነገር አስደናቂ ጐኑ የእግዜር፣ የፈጣሪ ከገነት መጥፋት ነው:: ሰይጣን በሽሩ እንደሚያጠፋት ግምት ካለውና ካወቀ አውቆም መከላከል አለመሞከሩ አብሮ ሴረኛ ያደርገዋል:: መፍጠር እኰ ራሱ ማሴር ነው:: በአለም ላይ ካሉ ፍጡራን ሳይበላ የማያድር አለ? ሁሉ በመልኩና በፀባዩ ቢለያይ የሚያራብሸው አንድ 'ሆድ' የሚባል ነገር አለው አይደለ:: ታዲያ እግዜር በፈጠረው በዚህ 'ሆድ' በተባለ ቀላል ዕቃ ገነትን የሚያህል የፈጠራ ዕንቁ ስትፈርስ ማየት ደግ ነገር ነው ብሎ የሚያምን ይኖራል?

የሰይጣን ያልጠገበች የአጥፊነቱ ወስፋት ገና እየተወራጨች ናት:: ታዲያ የገነት መፍረሻ ጊዜ መጀመሩን ለማስታወቅ ሳይሆን አይቀርም ከላይ እስከታች ነጐድጓድ ተሰማና መብረቅ ታየና ከአድማስ አድማስ ምድርን ከድኖ የሚጥመለመል ከመሐሉ ብርሐን የሚፈልቅበት የሚያምርና የሚያስፈራ ሰማዩን የሚያምስ ዳመናና ጉም መጣ:: ብዙም ጊዜ ሳይወስድበት ይኼ ነገር እየተግበሰበሰ መጥቶ እበለሷ ዛፍ ትይዩ ሲደርስ ቆመ:: በመልካም ጊዜና በደንቡ ከዛ ዳመና ስር ዐይን የሚያጠናግር ነጭ የብርሃን ጎርፍ መውጣት ነበረበት..... ሰይጣን እግዜርን እንዲህ ጮማጎ አይቶት አያውቅም:: አዳምና ሔዋን እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ መሬት ወድቀው ከእግዜር ለመሸሽ በዛፍ ተከልለው ፊቶቻቸውን ደፉ:: እንደ እሳት የሚንተገተግ መዳብ የመሰለ አንድ እጅ ከጉሙ መሐል ወጥቶ ወደ አዳምና ወደ እነ ሔዋን እያመለከተ......

«ምን ጉድሎባችሁ ከዚያች ዛፍ በላችሁ?» የሚል ድምፅ መጣ:: ሠይጣን የሚያውቀው ድምፅ ነው:: ትናንት የሰማው ዐይነት የሚያውቀው ድምፅ ነው:: የድሮ ጌታው:: እባቧ አንጉል ውስጥ ሆኖ ያዳምጣል::

አዳም ቁጭ ብሎ አንገቱን ሰብሮ ፊቱን ደፍቶ በፍርሐት እየተንቀጠቀጠ፡

«ይኸቺ ሴትህ አሳሳተችኝ» አለው::

ሰይጣን ይኼን ሲሰማ እባብ አንጉል ውስጥ በጀርባው እንደተኛ አፉን ወደ ግራጫው የሞራ ጣሪያ ሰቅሎ እግዜር እንዳይሰማው ከት ብሎ ሳቀ:: የእግዜርን የጆሮ ችሎታ ያውቃል:: የትኛው ከፍታ እንደሚሰማው፣ የትኛው 'አደነቆረኝ' እንደሚል፣ ለጆሮው የትኛው እንደማይደርስ ያውቃል:: አዳም ፍሬውን በላ...... የመጀመሪያ ሐጢያቱ ትዕዛዝ ማፍረሱ:: ሁለተኛው ሐጢያቱ......ማሳበቁ:: ከበላ በላ ነው:: ከእርግማኑ ከቀመሰ ቀመሰ ነው:: 'ሴቲቷ' ቅባጥሴ ምን አመጣው? እግዜር ይሔ ሁለተኛው የአዳም ሐጢያት አልታየውም:: እግዜር የቻልተኛነት ይሁን አብዝቶ የመታገስ በሽታ አለበት:: ፈጣን እግዚአብሔር ቢሆን የአዳምን ሐጢያት ሁለት ሊያደርገው ይችል ነበር:: ምናልባት ያን ጊዜ በሐጢያት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበችው አንድ ብቻ ስለሆነች ይሆናል......ሲሰለጠን! ሲከርም ያ ማነው እንጨት ተመርኩዞ በረሐ አቋረጠ የተባለው ሙሴ ምንትሴ

አስር እስኪሚያደርጋቸው። ያን ጊዜ አምላክ ሥራ አዳክሞታል መሰል ብዙም ንግግር ሳያበዛ ቅጣቱን መስጠት ጀመረ። እርግማኑን በተናገረ ቁጥር የገነት አረንጓዴነትና ውበት እየጠፋ የአዳምንና የሔዋንን ገላ የሸፈናቸው የቀረው ደቃቃ ፀጉር እየረገፈ አየሩን የማይመች፣ የሚያስፈራ ቅር ቅር የሚያሰኝ ነገር ሰረፀበት። ሔዋንን ሲረግም እንዲህ አላት:

«ማሕፀንሽን እረግመዋለሁ፣ ምጥሽን አበዛዋለሁ»

«ለባልሽ ታዘዢው፣ እንደተመኘሽው»

አዳምን ደ'ሞ:

«ስራ ልፋ፣ ወዝህን ድፋ» አለና ረገመው።

እግዜር ግን ያልገባው ከሁሉ ከሁሉ የባሰ ሳያውቀው ፍርሐትን መፍጠሩ ነው። የእርግማኑ ቢጋር እያሰፋ ከገነትና ከሰዎቹ አልፎ እባብን ጨመረ። ያ መከረኛ መብረቅ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ እባቧ የተጋደመችበትን የበለስ ዛፍ መታው። እዚያ ገነት ያሉ ፍጡራን ሁሉ እሳት አይተው አያውቁም። ዛፏ ስትቃጠል እባቧ በፍርሐትና በድንጋጤ ዘላ ወረደች። እባብ ዘላ ካረፈችበት መሬት እንደ ለመደችው መነሳት አልቻለችም። ያለ እግር እንደሆነች ገባት፣ እሱ ብቻ ሳይሆን ያ የሚያምር ምላሷ ጠፍቶ በምትኩ የተሸነተረ እሾክ ነገር ተጎልጉሎ ወጣ። ከወደቀችበት ሆና ለእግዚአብሔር ለመጮህ ስትፈልግ ያ የሚያምር ድምፅ ከየት ይምጣ። ለደቂቃዎች የእባቧ አንጐል በፍርሃትና በጥያቄዎች ተሞላ። አስቀያሚነት እንደ ዕርግማን ይሰጣል ማለት ነው? እርግማኑ እንደተጠናቀቀ ያ እጅ ያ ጉም ያ ውበት ያ ግርማ እየተሳበ ወደ ኋላ ሲሄድ እኔም አይቅርብኝ ዐይነት ገነት መግቢያ ቆሞ የነበረው መልአክ ሠይፉን እያወዛወዘ አዳምና ሔዋንን መቃጠል ከጀመረችው ገነት ያባርር ጀመር። ሠይጣን እባብ አንጎል/ እእምሮ ውስጥ እየተንደባለለ ከግድግዳ ግድግዳ እየተጋጨ ሊገባው ያልቻለውን ከቁጥጥሩ ውጭ ፈጥኖ የመጣውን ለውጥ በብስጭት ይገመግማል። ከእርግማን ቀጥሎ ማዋረድ። ማዋረድን ምን አመጣው? ማዋረድ ስንቅ መሆኑ ነው? ወይስ እርግማን የሚጠናቀቀው ውርደት ሲለጠፍበት ነው? ወይስ የእርግማን ሆድቃ የመርገምት ይዘት ጭምብል ለብሳ ተቀምጣለች? የምትገርመው የመጨረሻዋ ዕርግማን ናት። እግዜር እጁን ጉያው ሰብስቦ ከነዳመናው በማይታወቅ በማይታይ ሰማያዊ ጉድጓድ ሲመጠጥ እኔም አይቅርብኝ ባይው ገብርኤል ይሁን አንድ መልአክ እያጉረመረመ መስማት በሚያዳግት አደንቋሪ ከፍተኛ ድምፅ:

«አዳም ራስሽን ይቀጠቅጣል አንቺም ሰኰናውን ትነክሻለሽ» ብሎ እባብን ረገማት። ሰው የእባብን ራስ ቀጠቀጠና ምን ይጠቀማል? እሷስ ሰኰናውን ነክሳ ደም ሥሩ ውስጥ መርዝ ረጭታ ምን ይጠቅማታል? የማጣላት ደቃቃ ዘር መነስነስ ራሱ ዕርግማን ቢሆን ነው እንጂ። ፈጣሪ፣ ረጋሚ፣ አባራሪ፣ አተናኳሽ። እግዜር ሁሉን ይችልበታል ቢባል ይሔ ምሳሌ ነው። ታዲያ ገብርኤል ወይም የሆነ አንድ መልአክ እንደ ነጭ አሞራ ክንፉን እያራገፈ ወደ ሰማይ ሲወጣ ሳቀ። የሚያስቅ ነገር የለውም። ሠይጣን እርግማን ባጠበበው የእባብ እራስ ውስጥ ተጋድሞ በነገሩ በመጠኑ አዘነ። 'ከፈጠራቸው ሰዎች ስደተኛ የሚሰራ አምላክ ትልቅ ደካማነቱ ነው' አለ። ቢበሽቅ ቢናደድ የእባቧ ጨለማ አንጎል ውስጥ ጥርሱን ነክሶ መልአኩ አልሰማውም እንጂ 'እናትክን' አለ። የገረመው

የሰማይ ቤት የሰው ሐይል ጥራት እያጣ መሔዱ ነው:: ያሉት፣ የሚያጋጥሙት መላዕክት ሁሉ እንኩል ሳይሆን ጥሬ ጉልበት ነው ያላቸው:: ሰይጣን መላዕክትን ሲመራ አሽከሮቹ ጮሌ እንደ ነበሩ ትዝ ይለዋል:: እነኚህ ያሁኖቹ ካልሆነላቸው ይማታሉ:: ያልገባቸው ነገር ከመማታት ወዲህ፣ መማታት ከመድረስ በፊት ግን ብዙ ነገር እንደ አለ ነው:: ብዙ ብዙ ነገር አለ::

እባብ በገላዋ መለወጥ አፍራ መረገሟ ገብቷት እየተሽሎከለከች በሳር ውስጥና በአፋፍ ላይ በደረቷ ስትሮጥ አንጐሏ ውስጥ ለውጥ ተነሣ:: ሠይጣን እውስጥ ሲገባ በጭንቅላቷ ውስጥ እንደ ጭስ ይንሳፈፉ የነበሩ የተለያዩ የገነት የምግብ ዐይነቶች እየተሰወሩ ቦታቸውን ሣር፣ የማይረባ አረም፣ ጠረኑ የማያምር የአሸዋና የአፈር ብናኝ ሞላው:: ስራውም ስላለቀ፣ እባብን መጋለብ ስለሰለቸው፣ ቦታውም መመቸት ስላቆመ እባቧ አንድ ገደል አጠገብ ስትደርስ ሰይጣን እንደ አየር ሆኖ ከገላዋ ተመንጥቆ ወጣ::

**አዲስ ጌታ......**

ሰይጣን ሐላፊነት እንዳለበት ያውቃል:: በምድር ላይ እግዜር ፈጥሯት የነበረችው ገነት የተባለች አንድ ግዛት ፈርሳ በእጁ ሆናለች:: ነዋሪዎቹ የእሱ ናቸው:: የእሱ አገልጋዮች ባይሆኑም የእሱ ለማድረግ በጣም በጣም ሰፊ ዕድል አለው:: አዳምና ሔዋን ሮጠው የተደበቁበትን ቦታ መፈለግ ጀመረ:: ፈሪ ሆነዋል:: ሰይጣን እራሱን ግርማ ሞገስ ወዳለው ቁመናው ወዳ'ማረ ነጭ በነጭ ወደለበሰ ሽማግሌ ለውጦ መጣራት ጀመረ:

«አዳም!» «ሔዋን!» «አዳም!» «ሔዋን!»

የሚመልስለት አላገኘም:: መልስ ያልበቀለበት ያ የመጀመሪያ ፀጥታ በቅርታ እንደተኛች ትንሽ ልቧም በቅርታ እንደምትመታ የግልገል ልብ ድምፀት ነበረው:: ዞር ዞር ቢል ወይ እቆመበት ቢያሽት እነ አዳምን በአንድ ጊዜ እንደሚያገኛቸው ያውቃል:: ግን የእሱን ጥሪ ሰምተው ከልባቸው 'አቤት!' እንዲሉት ነው የፈለገው:: በዚህ በተረበሸበትና ባልተረጋጋ ሁኔታ ፍርሃት ስላጥለቀለቃቸው ማንንም አምነው 'አቤት' ሊሉ ግን አይችሉም:: ሰይጣንን የሚመልስለት ሲያጣ ተስፋ በመቁረጥ ለአመል ዞር ዞር ብሎ ጥቅጥቅ ያለ ቁጥቋጦ መሃል አዳምና ሔዋን ተቃቅፈው ዐይኖቻቸው በፍርሐት ፈጠው እየራዱ አገኛቸው::

«ሰማህ አዳም ሴትህን ይዘህ ከዚህ ቁጥቋጦ ውጣ የማነጋግርህ ነገር አለኝ» አለው:: ሠይጣን የዚያ አይነት የደነገጠ የፍጡር ፊት አይቶ አያውቅም:: የፈራ፣ የተጨነቀ፣ የተጠበበ፣ ምን ሆንኩ? ምን አደረኩ? የት ልሒድ? የሚል ፊት:: መናገር የማይፈልግ፣ መነቃነቅ የማይፈልግ፣ መተሣሠሩንም የፈራ፣ መፍራቱንም የፈራ የሰው ፊት:: ፍርሐት ለሰው ልጅ የራሱን የሆነ ብቸኛ ገፅ እንደ ሚፈጥርለት ለመጀመሪያ ጊዜ ተረዳ:: ለእሱ ለሰይጣን ይህ አዲስ ዕውቀት ነበር::

«ማነህ አንተ?» አለ አዳም እየተንተባተበ

«እንግዳ ተቀባይ» ሰይጣን ራሱ ያልጠበቀው መልስ ነበር የመጣለት

«ምን ዓይነት እንግዳ ተቀባይ?»

«ምን ዓይነት? ምን ዓይነት ናችሁ? የተሰደደ የተጎዳ መጠለያ የሌለው ናችሁ:: መሰደድ አታውቁም:: ዛሬ መጀመሪያችሁ ነው:: ይኼ የገባችሁበት ዓለም እጅግ እንግዳ ነው:: ምክር ካላገኛችሁ ትጎዳላችሁ:: በመንገድ ሳልፍ ሰይፍ የያዘ ሃይለኛ ፍጡር ሲያባርራችሁ አየሁ:: በግንባራችሁም ስትደፉ አየሁ:: ስትጮሁ ሰማሁ:: ልረዳችሁ መጣሁ:: ስማችሁን የሰማሁት ያ ዳመና የመሰለ አስፈሪ ነገር ሲመጣ ጀምሮ ስለነበርኩ ነው:: የሚገርም ስም ነው ያላችሁ:: የሚገርም ነው»

«ራቁታችንን ነን:: ማንም ሊያየን አንፈልግም» አለ አዳም እየራደ

«ማን እንደሆንኩ በሙሉ መናገር አያስፈልገኝም:: በመጠኑ እንዲህ እንድትሆኑ አስተዋፅዖ አድርጌአለሁ......ነገር ግን አልተዋችሁም:: አደጋ ውስጥ ጥዬ አልተዋችሁም» አለ:: እየተንጠራራ ዙሪያውን ተንዘርፎው ከበቀሉ የኮባ ቅጠሎች በብዛት ዘንጥፎ ወደ እነ አዳም ወረወረና:

«ልበሱት» አላቸው:: በመጀመሪያ አዳም ቀጥሎ ሔዋን ገላቸውን በሰጣቸው ቅጠሎች ጋርደው ከተደበቁበት ወጡ::

«ለምን እንድንወጣ አደረከን? ምን ይጠቅምሃል?» አለ አዳም በመዶረር

ሔዋን ሰይጣንን አተኩራ እየችውና:

«እስኪ ምላስህ?» አለችው

«ምን?»

«እስኪ ምላስህ?»

«ተይ:: 'እባብ ይላስህ' ልትይኝ ነው? ይሄውልሽ ካስደሰተሽ» አለና ምላሱን አሳያት

«ፍሬውን ስበላ የነበረው ፍጡር ምላሱ የአንተ ዓይነት አይደለም እስታውሳለሁ አንተ ገነት አልነበርክም»

«ይሁን አልነበርኩም፡ ይልቁን ተከተሉኝ» አላቸውና ሰይጣን ከከበባቸው አስፈሪ ጫካ እየመራ አወጣቸው:: ከሩቅ ከሰማይ በወረደ እሳት የምትቃጠለው ገነት ቀልታ ትታያለች:: አዳም ቀና ብሎ አየ:: ምን እንደሆነ አልገባውም:: ሠይጣን እየሳቀ በጣቱ ወደ ገነት ጠቆመውና:

«ገነታችሁን እግዚአብሔር እያቃጠላት እያጠፋት እንደሆነ እይ» አለው::

«ጥፋተኞች ነን» አለ አዳም በከሰሰ ድምፅ:: ለአፍታ ቀና ብሎ ከሰማዩ ጋር የተቀላቀለውን ጢስ እያየ የሚያስብ መሰለና አንገቱን ደፋ:: የክዳቱን ውጤት እንዲያይና በዚህም እንዲጨነቅ ለማድረግ ሰይጣን ደጋግሞ ቢያመላክተውም ለማየት ፈቃደኛ አልሆነም:: ሔዋን የሚሰማት ብታጣም ወደ ጢሱ አያሳየች:

«ያ ምንድነው?» እያለች ትጠይቃለች:: ሠይጣን የሰማት ቀይቶ ነው::

ከሰማትም በኋላ ሊመልስላት አልፈለገም። ገነትን ማፍረሻ መሳሪያ አድርጎ ተጠቅሞባታል። መሣሪያውና አገልጋዩ በመሆኗ ሳይሆን አይቀርም ትንሽ ንቋታል። በተራው መያዝ ወይም ማንበርከክ የሚፈልገው አዳምን ነው። ሔዋን ከስህተቷ ብትማርስ? ከስህተቷ ተምራ ወዳጅነቱ እንዲጠረጠር የሚያደርግ ነገር ብትጠይቅስ? ('ከገነት ያስወጣሽን ጨካኝ ሆነህ፣ ካንተ ጥሩ እንዴት ይጠበቃል? 'ብትለው) ወደ አዳም መዞር ነበረበት። የእሱ የአገልግሎት ጊዜ ይመጣ ይሆናል።

አንድ ሸለቆ ቦታ ሲደርሱ ሰይጣን ሴትዮዋና ሰውዬው ተቀምጠው እንዲጠብቁት ነገረና ድቅድቅ ያለ ዱር ገባ። ሲመለስ ሦስት በራሪዎችና በጉያው ብዙ ደረቅ እንጨት አቅፎ ይዟል። አዳምና ሔዋንን ሳያናግር እንጨቶቹን ደራረበና ከጉያው ሁለት የባልጩት ድንጋዮች አወጣ።

«እዩ» ብሎ አዘዛቸው።

ባልና ሚስቱ ወደ ተከመረው እንጨት እየተንፏቀቁ ተጠጉ። ሰይጣን በስብሰው የኮቸሩ ቅጠሎች ሰበሰበ። ባልጩቱን ደጋግሞ አጋጨና እሳት ሰርቶ አቀጣጠለ። አዳምና ሔዋን እሳቱንና ጭሱን ሲያዩ በፍርሃት ወደ ኋላ አፈገፈጉ።

«ስሙ እናንተ ይኼ 'እሳት' ይባላል። እሳቱ ሲነድ የሚወጣው ነጭ ነገር 'ጭስ' ይባላል። ቅድም ገነት የተቃጠለችው በዚህ ነው፣ ያያችሁት ያ ከገነት የሚትጎለጎለው ነጭ ነገር ከዚህ በዛ እንጂ 'ጭስ' ይባላል። እሳቱ ለብዙ ነገር ይጠቅማል። እሱን ቆይታችሁ ታውቁታላችሁ። ይኼ እሳትና የገነት እሳት አ? በጣም ይለያያሉ። ያ የእግዜር ሐብት ይሔ ግን የእናንተ ነው። አሁን ስለራበን እነዚህን ዶሮዎች ጠብሰን እንበላለን። የማደርገውን በጥንቃቄ እዩ። ሌላ ጊዜ እንገናኝ ይሆናል። እንገናኝም ይሆናል» አለና ግራና ቀኝ ባላ ባልቾ እንጨቶች ተከለ። የዶሮዎቹን ላባ ነጨና በባልጩት ሆዳቸውን ቀዶ የውስጥ ዕቃቸውን አወጣ። አዳምና ሔዋን እንደ ልጅ ተገርመው ያዩታል። ከዚያ ዘንግ በውስጣቸው አሳለፈና ሦስቱንም እሳቱ እንዲመታቸው አድርጎ ባላዎቹ መሃል አንጠለጠላቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጥብሱ ጠረን አዳምና ሔዋንን እንደ ሰካራም አደረጋቸው። የሚቦረቡራቸውን ረሐብ ለማስታገስ ዶሮዎቹን ለመቧጠጥ ከተቀመጡበት ሲነሱ ሰይጣን እየተቆጣ ቢከለክላቸውም ሊያዳምጡት ፈቃድና ልቡና አልነበራቸውም። የመጀመሪያው ቅጣት ሔዋን ላይ መጣ። እሳቱ ጠብሷት መሬት ላይ እየተንከባለለች መጮህ ጀመረች። ሠይጣን ሁኔታቸውን እያየ እተቀመጠበት በሳቅ ፈረሰ። አዳም ተቆጣ። በሚስቱ መጐዳት ተቆጣ።

«ስሙ እናንተ የምታውቁት ስለ ገነት ነው። ፈጣሪያችሁ ስደተኛ አድርጓችኋል። ለስደተኛ አዝናለሁ። ከምታውቁት ዓለም ወደ ማታውቁት ዓለም ነው የመጣችሁት። የጉልበተኛ ደካማ ያጠቃውን ስደተኛ የሚያደርግ ነው። በአካል የሚያሽሽ ነው። አይደለም? በረሃብ ብትሞቱስ? ጥሩ አይደለም። ስለራሳችሁ አታውቁም። ስሚ ሔዋን መነፋረቅሽን አቁሚና አንድ ነገር ልጠይቅሽ? ገላሽን ለምን ሸፈንሽ?»

ሔዋን እንደመመለስ በእሳቱ የተጠበሰ እጇን እያርገበገበች ወደ ባሏ

በማፈር ጠጋ ብላ ተቀመጠች::

«ስለአፈርሽ......ሌላ ምክንያት የለውም:: ለምን አፈርሽ? ማፈር ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? እህቴ ሆይ ማፈር በራስ አለመደሰት ማለት ነው:: በራስ ላለመደሰት የማታምኚው ሰው መኖር አለበት:: ማለት ሌላው የሚያይሽ ዐይን የማታምኚው መሆን አለበት:: እኔን አታምኚኝም የሚገርመውም አዳምንም አታምኚውም:: ምንድነው አለማመን? እሱን አሁን ለመግለፅ ከባድ ነው:: ብችልበትም አይገባሽም:: በቀላሉ በሚገባሽ ልግለፅልሽ:: አሁን በማድረግ ላይ ያለሽውን ማፈርና መሸፋፈን ለምን የምታደርጊው ይመስልሻል? ጡት ሰላለሽ:: እግሮችሽ መሐል በፀጉር የተሸፈነ የሆነ ነገርም አለ:: አዳምስ ለምን ታፍራለህ?»

«ሐጢያቴ:: ትዕዛዝ አለማክበሬ» አለው

«ወሬኛ:: ወግ ትችልበታለህ:: እሱን አላልኩህም:: ገላህን ለምን በቅጠል ሸፈንከው? ኮባ ስወረውርልህ ቀልበህ ታችህን አይደለ የጋረድክበት:: ለምን አናትህን አልጋረድክበትም?»

ዝም አለ::

«እግሮችህ መሐል ምርጥ የስጋ ቁራጭ አለ:: እሱ ያሳፍርሃል:: ማፈር አይገባችሁም:: ከገነት ስትወጡ የተሰጣችሁ ሽልማት ነው:: ዶሮው እስኪበስል ድረስ እንዴት እንደምትገለገሉበት አሳያችኋለሁ ..........................................

...............................................................................................................

...............................................................................................................

...............................................................................................................

..................ከዚህ በኋላ አንቺም ትፀንሺያለሽ:: ልጅ ትወልጂያለሽ:: ጌታችሁ ከገነት ሲያባርራችሁ «ምጥሽን አከብደዋለሁ» ሲል ነበር:: ምን ማለቱ እንደሆነ ለራሴም አይገባኝም:: እግዚአብሔራችሁ ምነው ያልተፈተነ አዳዲስ ተንኰል የሚፈጥረው?»

«እንደሱ አትበለው» አለ አዳም በቁጣ::

«ምን ልበለው?»

«ትእዛዝ ስላፈረስን መቀጣት አለብን»

«ታዲያ ይሔ ሁሉ ምነው አዳም? ከገነት ተባረራችሁ፣ ሞትን ተሰጣችሁ፣ ወሲብ ሰጣችሁ......እሱም ጣፍጦ እንዳያልቅ ልጅ ሰጣችሁ:: ልጅ ሲሰጣችሁ ምጥ በተባለ መንገድ:: ግን ምጥ ሲከብድ ምን እንደ ሚመስል ራሴ አላውቀውም:: አይገርምም? ይኼ ሁሉ ፋይድ ለምንድነው? ገና ለገና አንዲት ፍሬ ተቀመሰችና ምን ይጠበስ?»

«አንድ ፍሬ መሆኑ አይደለም:: ትዕዛዝ ትዕዛዝ ነው:: ቅጣቱ ይገባናል» አለ አዳም::

«ምን አደረግነው እስከዚህ?» አለች ሔዋን ምጥ ምን እንደሆነ እንደምታውቅ ሁሉ::

«እኔም ያልኩት ይሔን ነው» አለ ሠይጣን::

«አሁን አንድ ፍሬ በላንና ምን ይሁን ነው?» አለች ሔዋን::

አዳም በቁጣ ከተቀመጠበት ተነሣ:: ሊማታ የፈለገ ይመስላል:: ግራና ቀኝ እቆመበት ተወራጨ:: ሠይጣን ተገርሞ ያየዋል:: ግጭቱ ካቀደው ወሰን እንዳያልፍ በመፍራት ሠይጣን የጠበሳቸውን ዶሮዎች ከተሰቀሉበት እንጨት ላይ አወረደና እንዲመገቡ ጠራቸው:: መሬት ላይ ቁጭ ብለው እያንዳንዳቸው አንዳንድ ዶሮ ይዘው እየነጩ መብላት ጀመሩ:: አይነጋገሩም:: ስለሚበሉት እንግዳ ምግብም ማውራት አልፈለጉም::

ሰይጣን ቆቅ ይወዳል:: ይሄ የትም የተወራለት ነው:: ስጋ እየነጨ ቆቅ እንዴት እንደሚወድና ቆቅ እንዴት እንደሚያዝ ለአዳምና ለሔዋን ያወራቸዋል:: ድንጋይና ዱላ በጣም ጠቃሚ መሣሪያዎች እንደሆኑና በተለይ እሳትን ከተቆጣጠሩ አደገኛ አውሬዎች ለመግደልና ለማስፈራራት እንደሚረዱ ያወራቸዋል::

ሞት ወደ በዛበት ዓለም እንደመጡ ነው የሚነግራቸው:: አሁን የገቡት ሕይወትና ሞት የመጨረሻውን ግጭት የሚያደርጉበት ቦታ እንደሆነ ያብራራላቸዋል:: ዶሮዎቻቸውን በልተው እንደጨረሱ ሠይጣን ይጠይቃቸዋል:: አዳም እንዲህ እንዲህ አይነት የሚጣፍጥ ሥጋ በልቶ እንደማያውቅ ሲናገር ሔዋን ተጨቃጭቃ አቋረጠችው::

«እኔ ከቀመስኩት ምግብ ሁሉ እንደበለስ የሚጣፍጥ የለም» አለች:: አዳም ተነጫነጨ:: ሠይጣን መሳቅ ጀመረ:: ሔዋን እየተንተባተበች ሲጠቃለል እንዲህ የመሰለ ነገር ስለ በለስ ፍሬ አወራች:

«የበለስ ፍሬ በመጣፈጧ ብቻ ሳይሆን በአሰራሯም ከማንኛውም አይነት ፍሬ የተለየች ናት......ፍሬዋን ከላይ የሸፈናት ወፍራም ቀይ ሥጋ ነገር ከውስጡ የሚያስገርምና የሚጣፍጥ ልብ ነው የደበቀው......ፍሬው ሲገመጥ ከውስጥ ሙቀት ይወጣል:: ውስጡ የሚሞቅና ጢስ የሚያወጣ ፍሬ በምድር ላይ አለ? ገነትም ዘንድ ሌላ ሁለተኛ አልበቀለ......ውስጡ በመሞቁ ብቻ ሳይሆን በመለስለሱም ተወዳዳሪ አልነበረውም......ይኼ ውስጡ ያለው ነገር በዐይንም ሲታይ ማንም የሚያደንቀው ውብት ነበረው»

ይኼን ዕውነት ሰይጣን መስማት አልፈለገም:: እናም መሳቁን አቁሞ የእግዜርን ፈጠራ የሚያጣጥል ነገር አወራ:

«ስሙ የእግዜር የፈጠራ ችሎታ የማዳቀል ችሎታ ነው:: እስከ ዛሬ አልገባችሁም:: ይኸቺ አሁን የበላናት አውሬ ዶሮ ትባላለች:: እሷን የሚመስሉ ብዙ አዕዋፋት አሉ:: ማየት ትችላላችሁ:: የሚበሩ የማይበሩ:: እግዜር ይህችን ዶሮ የምትበር አድርጐ ይሰራትና ስሟን ቆቅ ይለዋል:: በኤሊና በቀንድ አውጣ መሐል ብዙ ልዩነት አለ? ፍየል የሚባል እንስሳ አለ:: በግ የሚባል እንስሳ አለ:: ልዩነታቸው አንደኛው ላት አለው፣ አንዱ የለውም:: እነዚህን እንስሳት በየቦታው ታዩዋቸዋላችሁ:: የበለስ ፍሬን አሰራር አውቃለሁ:: ሽፋኑ፣ ቅርፊቱ የሾላ ፍሬ

ነው:: እሱን ታዩታላችሁ ከውስጡ ግን እህል ነው:: እግዜር የሾላ ፍሬና እህል ወስዶ ነው የደባለቃቸው:: ያገናኛቸው:: ችሎታው እሱ ነው:: በወሬ ስሰማው ልዩ ጉድ መስሎኝ ነበር:: ኒፊሊሞች እንደ እሱ ሊሰሩ ሞክረው አልቻሉብትም:: ገርጃጃ፣ ቀልበ ቢሶች:: እነሱ ባይሰሩትም የበሰስ ፍሬ ልዩ ሚስጢር አይደለም:: ትኩስ መሆኑና መሞቁ ትንሽ በሰላ አእምሮ ቢመረመር ይታወቃል:: ትኩስነቱ እሳት ስላለበት ነው:: ይሔ የጠበስንበት እሳት ነው:: እግዜር እሳትን እንደ ቅመም የበሰለ ፍሬ ውስጥ ከእህሉ ጋር ቀላቅሎ አስገባ:: አያስገርምም:: ካለው ነገር ነው የሚሰራው......»

እጁን በንቀት አመናጨቀ::

«አንተ ትሰራዋለህ?» አለ አዳም

«ለምን?» አለ ሰይጣን በሽቆ

«የእግዜርን ስራ ናቅኸው ግን አንተ ትሰራዋለህ?» አለው::

«ምን ላደርግበት? ሾላ ፍሬ ሞልቷል፣ እህል ሞልቷል:: እሳቱም ይሔውና......ምን ያደርግልኛል? ፈተና ልሰጥበት? እንደ እናንተ ያሉ መውጫና መግቢያ የጠፋቸው ፍጡራን ልፈትሽበት? ደካማ መርዳት እንጂ ማባረር ፀባዬ አይደለም:: ከጌታችሁ ጋር ያልተግባባነው ለዚህ ነው:: ተንኮል አላውቅም:: በፈተና ስም አላስቸግርም:: 'ፍጡራኔ' እያልኩ በአፌ እያቆለጳጰስኩ በማይረባ ፈተና የፈጠርኳቸውን፣ የሚወዱኝን አላበለሻሽም:: እስከ አሁን ተንኮል አልሰራሁባችሁም:: እግዜር ቢሆን እስከ አሁን ስንት ሕግና ትእዛዝ ያስተላልፋል:: እኔ ነፃነት ነው የሰጣኋችሁ:: 'በለስ' 'በለስ' ትላለህ ምን ጠቀመችህ? ወጥመድ ሆና እንደዚህ የተንከራፈፈ ስደተኛ አደረገችህ እንጂ......አሁን ምን እናደርጋለን መሰላችሁ......የሾላ ዛፍ አሳያችኋለሁ»

«እሱ አይደለም......ዋናው ውስጡ ያለው ነው የሚጣፍጠው» አለች ሔዋን::

«ሚስትህ ትሻላለች» አለው ለአዳም ሰይጣን::

«በምን?»

«ያለችበትን ችግር ታውቃለች:: ገብቷታል:: እኔ አሁን ብሔድ ምን ትበላላችሁ?»

«ዶሮ» አለ አዳም

«እኔን አመስግነኝ ስላሳየሁህ:: ዶሮ መያዝ መልመድ አለብህ መጀመሪያ:: የመጨረሻ አታላይ እንስሳ ዶሮ ናት:: አውቃታለሁ:: መያዝ ከባድ ነው:: ያዝኩ ስትል ትበራለች:: ያዝኩ ስትል ትበራለች:: ችለህበት በበትርህ መተህ ብትገላት እሚሟሟቷ ያሳዝንህና ባልበላኋት ትላለህ:: አታላይ ነገር ናት:: አታላይ አልወድም:: ፍጥረቴም አታላይ አይደለም:: እመኑኝ:: ዶሮን አውቃታለሁ:: አታላይ ቢኖር እንኳን የምወደው አታላይ ጥፋቱን የሚያርመውን ነው......እንደ እኔ» ሣቅ አለና ቀጠለ:

«እኔ ላሳያችሁ እፈልጋለሁ:: ገነት ውስጥ የነበረው ነገር ሁሉ የሚበላውም የሚጠጣውም እዚህ አለ:: ለመበላት መልካም ያልሆኑ መርዛማ ነገሮችም አሉ:: እነሱንም አሳያችኋለሁ:: ከዚያ የሚያምር ቦታ ለምን እንደወጣችሁ ነው ያልገባኝ......» አለ ኩስተር ብሎ::

«እሷ:: እሷ አሳስታኝ»

«አሁን ምን ጉደለብን?» አለች ሔዋን::

«ምን ጉደለብን? ዕፍረቱስ፣ ውርደቱስ» አዳም ተመናጨቀ::

«ትዝ ይላችኋል የገነት ኑሮ......?» አለ ሰይጣን

«ለምን አይለንም?» አለች ሔዋን «በተለይ በለሷ:: በልቼ አለመጨረሴ ይቆጨኛል» አለች ከት ከት ብላ:: አዳም የምትነክሰው ይመስል ሸሸት ብሎ አያት::

«ቆንጆ ፈልቃ ሚስት አለህ» አለው ሰይጣን

«ምን?»

«እርሳው:: በነገራችን ላይ የማሳያችሁን ከማሳየቴ በፊት አንድ ጥ ያቄ ልጠይቃችሁ:: በጣም ከባድ ዝናብ ቢጥል፣ የሚበላችሁ፣ የሚገላችሁ አውሬ ቢመጣባችሁ ምን ታደርጋላችሁ? ለመሆኑ ከባድ ብርድ ቢኖር ምን ታደርጋላችሁ?»

አልመለሱለትም እየተያዩ ዝም አሉ:: በመጀመሪያ የ'መበላት' ትርጉም አልገባቸውም:: ሁለተኛ 'አውሬ' የሚለው ቃል እንግዳ ሆነባቸው::

«አልገባችሁም እ? መበላት ማለት አንተ ይሄን ዶሮ እንደ በላኸው አንተን ደሞ የሚበላህ አለ ማለት ነው......አምላካችሁ የሰራው ጉድ ነው ምን ታፈጡብኛላችሁ:: ገነት የነበሩት እንስሳት ገነት ከፈረሰ በኋላ አውሬ ሆነዋል:: ስለዚህ ከመመርመራችሁ በፊት ገና ለገና ገነት እናውቀዋለን ብላችሁ አትመኑት፣ እሱ ረስቶአችኋል:: ግን መመርመር ጊዜ ስለሚወስድ የሚሆነውን አሳያችኋለሁ::

«ቤት ትሰራላችሁ:: ተከተሉኝ» አለና ከተቀመጠበት ተነሳ:: የአካል ንቅናቄው የሽማግሌ አይመስልም:: ኋላ ኋላውን እየሮጡ ተከተሉት:: የአዳምና የሔዋን እግሮች የተሣሠሩ ይመስላሉ:: ሠይጣን ቁጥቋጦ እየገላለጠ ትንሽ ከሔደ በኋላ አንድ ፍርኩታ ፊት ለፊት ቆመ:: አዳምና ሔዋን እጅ ለእጅ ተያይዘው ከኋላው ቆሙ::

«ይሔ ዋሻ ይባላል:: እንደ ማየው ከሆነ በተፈጥሮ የተሰራ ነው:: ግን በቂ ጥልቀት የለውም:: እናንተ የምታደርጉት ነገር ምንድነው......ትልቅ እንጨት ትወስዱና ጫፉን በዚህ ባልጩት አሹላችሁ......እንደዚህ...... አፈሩን በዛ እየናዳችሁ ወደ ውስጥ ማጉድጉድ ነው:: ይኼ ብቻ አይበቃም:: እዚያ ያነደድኩት አይነት እሳት አለ እና እሱን የመሰለ ማታ ማታ ዋሻው መግቢያችሁ ጋ ታነዳላችሁ:: አውሬዎች እሳት ይፈራሉ:: ማስጠንቀቂያ ልንገራችሁ እንዳትረሱ

እሳቱ መጥፋት የለበትም:: እሳት ሲጠፉና ሳይጠፉ ምን እንደሚመስል ላሳያችሁ እፈልጋለሁ:: ያልኳችሁን ሁሉ ካደረጋችሁ ዋሻ መሆኑ ይቀርና ቤት ይሆናል:: ተከተሉኝ......»

ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን ብዙ ነገሮችን ካሳያቸውና ካስተማራቸው በኋላ ሾላ ያለበት ኮረብታ ላይ ወሰዳቸው:: አንድ ያማረባት የተንዠረገገች ሾላ ዛፍ መርጦ ከስሯ ቆመ:: ቀና ብሎ የዛፏን በምቾት መንዠርፈፍ በመደነቅ አየ:: እዚህ ጥላዋ ስር ለእፍታ ማረፍ ተመኘ:: ግን በእግዜር ስራ መመሰጡን ለነዚህ ሰዎች ማሳየት አልፈለገም:: በዛፏ ክንዶች ላይ የተንዠረገጉት ቢጫና ቀይ ፍሬዎች የሚማርክ መአዛ ያወጣሉ......ወደ ሩቅ የሚያይ መስሎ ከዛ መአዛ አንድ ሁለቴ ስቦ ሰፊ ሳንባውን ሞላ:: «አሁን የቆምነው የሾላ ዛፏ ስር ነው» አለና ስለ ሾላ ዛፏ ብዙ ከማውራቱ በፊት፣ ከቆመበት ኮረብታ ስር የተዘረጋውን እጅግ የሚያምር መልካምድር በመፍዘዝ አየ:: ለምን ዛሬ እንደ ማረከው ግራ ገብቶታል:: የሚያውቀው መልካምድር ነው:: ሌላ ተጋሪ ስለመጣበት ይሆን?

«ከዚህ በታች የምታዩት አገር በሙሉ የእናንተ ነው:: ልዩነቱ እንዲገባችሁ ነው:: ገነት የእናንተ አልነበረችም:: እናንተ የገነት፣ ገነት ደ'ሞ የእግዚአብሔር ነበረች:: ቢሆንማ ኖሮ እንዲህ አትሆኑም ነበር:: አሁን ይሔ ሁሉ በውስጡ ያለው በራሪ፣ ተንቀሳቃሽ፣ ተክሉ ሁሉ የእናንተ የሁለታችሁ ብቻ ነው:: የእናንተ:: ይገባችኋል? እሱን ትጠብቃላችሁ:: እውስጡ ያለውን ማልማት፣ ማጥፋት የራሳችሁ መብት ነው......»

ንግግሩን አቁሞ ተቃጥላ ጥቁር ጠባሳ የመሰለችውን ገነት በዝምታ አየ:: አካባቢው ውበት እንደጐደለበት ገባው::

«ውበት ይረግፋል ደንብ ነው» አለ ድምፁን ዝቅ አድርጐ:: አዳምና ሔዋን አልሰሙትም::

«ወደ ሾላው፣ ስለ ሾላው ልጨርስ......የሚያምር ዛፍ ነው:: ግርማ ያለው ይመስላል:: ፍሬዋን አይታችኋት እንደሆነ ትንሽ ናት:: ፍሬዎቹን ስታዩ ዛፉ ገልጃጃ አይመስላችሁም? ዛፉ የቂልነትና የብልጠት ድብልቅ ነው» አንዷት ፍሬ ወስዶ ግራ እጁ መዳፍ መሐል አስቀመጣትና:

«ይችቺ ፍሬ ብታፈርጧት ወተት ይወጣታል:: ወተቱ አይጠጣም:: በተረት ምን እንደሚባል ልንገራችሁ......ይቅር:: ወደ ፊት ትሰሙት ይሆናል:: እናንተው ራሳችሁ ተረት ትፈጥሩ ይሆናል:: ደካሞች ተረት መፍጠር ይችላሉ:: አንድ ነገር መለወጥ ሲከብዳቸው በተረት ያባብሉታል:: ወደ ሾላዋ እንመለስ:: እዩማ......»

ሾላዋን ለሁለት ከፈላት:: ጠረኗ ከነፋስ ጋር ዙሪያቸውን ፈሰሰ:: ሔዋን ከእጁ ነጠቀችው:: ሰይጣን ሳቀ::

«ሔዋን ሰማሽ? መጡኑ አነስ እንጂ ያንን በለስ አይመስልም?» አላት:: ሳትመልስለት ፍሬውን ነከሰችው:: ጥርሶቿ ሽው ብለው ገቡ:: የሾላው ከፊል አፏ ውስጥ ከፊሉ እጇ ላይ ቀረ:: ማላመጥ አቁማ የፍሬውን ውስጥ አየችው::

ከዛ ውስጥ እየተትመሰመሱ የሚወጡትን ትንኞች በመገረም ታያለች። ሊታባርራቸው እጇን አርገበገበች። ማላመጧን ጀመረች። ፊቷ ላይ ቅሬታ ሰፈረ። አልወደደችውም።

«አትከፊ» አለ ሰይጣን። ግማሹን ግማጭ ሾላ ከእጇ ተቀብሎ። ሔዋን በከፊል ያላመጠችውን ከአፏ አውጥታ ጣለችው።

«ይኼ ዶሮ ቀብትቶሽ ነው እንጂ የሚጠላ ፍሬ አይደለም። ያበሸቀሽ ውስጡ ያለው ትኩስ ተፈጥሮ አለመኖሩ ነው። ትንኞቹም ይሆናሉ። በለስ ለምን ትኩስ እንደ ሆነ ቀጥዬ አሳያችኋለሁ። ከማሳየቴ በፊት ግን ቃል ትገቡልኛላችሁ። ዕውቀት ይሸጣል እኮ። መሸቀያው መስመር ነው የሚለዋወጠው እግዜር ገነትን ይሰጣችሁና እናንተም መታዘዝን ትሰጣላችሁ። እኔም ሳላፍር ምንም ወዳጆቼ ብትሆኑ......ሃ!......ሃ!......ለእኔ የምትሰሩልኝ ነገር ይኖራል። ቀላል ነው። ፈቃደኛ ናችሁ?»

አዳምና ሔዋን ተያዩ። ግራ እንደተጋቡ ያስታውቃል።

«ግራ አትጋቡ። ቀደም ብዬ ስለገባችሁ አሰራር ነግሬአችሁ አሳይቼአችሁ ነበር። አንተ ወንድ እሷ ሴት ናችሁ። ቅድም እንዳሳየኋችሁ እናንተ ስትተዋወቁ......ጨዋ ልሁንና ሴቷ ትፀንሳለች፣ ልጅ ትወልዳለች። ከዘጠኝ ወር በኋላ። ጊዜውን እርግጠኛ አይደለሁም። በአጭር ጊዜ ግን ቀጥራችሁ ይበዛል። እኔ የምፈልገው የመጀመሪያ ልጃችሁን እንድትሰጡኝ ነው......» አለ።

ሔዋን ዘለል ዘለል እያለች፡

«እሺ እሺ» አለች። አዳም ሔዋንን ወደ ጐን ገፋ አድርጐ

«ለመሆኑ ልጅ ምንድነው?» አለው።

«ሃ ሃ......አታውቅም? አታውቅም?» አለ ሠይጣን ላልጠበቀው ጥያቄ አእምሮው ውስጥ መልስ እየፈለገ።

«አላውቀውም»

«ምን? ልጅ......አየህ ልጅ ምን ልበልህ?......ትንሽ ሰው ነው። እንዳንተ፣ እንደ እኔ ይሆንና ትንሽ ነው። እንደ እሷ ትሆንና ትንሽ ናት። ሴት ልትሆን ወንድ ሊሆን ይችላል። ብዙ ጊዜ ይንጫንጫሉ። ነጭናጫ እወዳለሁ። ነጭናጫ ነገሮች ደስ ይሉኛል። ለምን እንደሆነ አላውቅም። ብዙ ትወልዳለች ሴትህ፤ እኔ የምፈልገው የመጀመሪያውን ነው። ሴት ብትሆንም፣ ወንድ ቢሆንም። እንስማማለን?»

ሔዋንና አዳም ተያዩ። ዝም አሉ።

«ተስማማን?» አለ ሰይጣን።

አዳም ሔዋንን አየና ፍላጎቷን አጢኖ በአወንታ ራሱን ነቀነቀ። እሱ ፊት ለፊት......ሁለቱ ከኋላ ከኋላ እየተከተሉት ኩረብታውን ትቶ ወደ ሜዳ ወረደ። ብዙ ተጉዘው አንድ አምባ ላይ ደረሱ። አምባው ላይ እንደ ወጡ ታች ታቹን

ፊት ለፊታቸው በአረንጓዴ የውሐ ማዕበል የተጥለቀለቀ የመሰለ እጅግ ሰፊ ሜዳ አዩ:: ሦስቱም ፊዘው ያን ሲመለከቱ ቆይተው ሠይጣን ሣል ሣለና እጁን ወደ ሜዳው ዘርግቶ:

«ይኼ የምታዩት ሜዳ ላይ የበቀለው ዛሬ ጠዋት የበላችሁት የበለስ ልብ የተሰራበት ነው»

«ሣር አይደለም?» አለ አዳም::

«ይመስላል......ስሙ ጤፍ ይባላል......አያምርም?......ኑ ላሳያችሁ......»

○

ሠይጣን ተሰናብቶአቸው ከሔደ ሰላሳ ዓመታት አለፉ:: እሱ 'ተሰናብቼ ሔድኩ' ብሎ ቢናገር እንኳን በየጊዜው እየመጣ በሕቡዕ ረቂቅነቱ አዳምና ሔዋንን ያጤናል:: ሰይጣን ራሱ የሚወደው ስራ ማባት ነው:: አባ መውጣት ነው:: ቀድሞ በመፈጠሩ ያገኘው ጥቅሙ ነው:: ሰው ላይ ጌትነት ያጎናፀፈው ሕቡዕ መሆኑና መስለል መቻሉ ነው:: ሲያሰኘው ከሚሰራቸው ተንኮሎቹ የተፈጥሮን ለውጥ ዕጣና ዕድል አስመስሎ ለደካማ ክሱት ፍጡራን ማምጣቱ ነው:: በግሉ ከሔዋንና ከአዳም ጋር ቂም እንደሌለው ያውቃል:: ቂሙ ከእግዚአብሔር ጋር ነው:: ይኼን ቂሙን ደ'ሞ በየኼደበት አይናገረውም:: የእግዚአብሔርን ስራ ሲቀናቀን እጅ ከፍንጅ ቢያዝ በጥላቻ ሳይሆን ፍትህ እንዲሟላ ያደረገው ጥረት እንዲመስልለት ነው:: ፍጡራንስ ገነኑ አልገነኑ ሙለሉ አልሙለሉ ምን ምርጫና ዕድልስ አላቸው ለበላይ ሐያላን አይኖቻቸውን ከድነው ከመገዛት የበለጠ? የሰይጣን ቂሙና በቀሉ በየቀኑ እንዳበበ ነው:: የዚህ ዋናው ምክንያት ደ'ሞ ብዙ ጊዜ ሳያቋርጥ በእግዜር መበለጡ ነው::

እነ አዳም ከገነት ሲወጡ የተሰጣቸው ወይም የተሸለሙት ለመሰናበቻ ይዘዋቸው የወጡት ዝነኛ እርግማኖች የመሞት ፍርድና ለጊዜው አስደስቶ የሚጠፋ የወሲብ ስሜቶች ነበሩ:: ይኼ የተመረጠላቸው ሞት ግን ቂል ቢጤ ነው:: ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣላ ያገኘው ስሙ ከብዶ 'ሞት' ተባለ እንጂ አሰራሩ ግን ቀላል ነው:: ደንቃራነቱ መርቀቅ ያጥረዋል:: አዳምና ዘሮቹ ኖረው ኖረው አርጅተው ይሞታሉ:: ቀለም የለውም:: ዝንጉርጉርነት የለውም:: አይወሳሰብም:: ሞት የሚመጣበት ቀን ባለመታወቁ ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ ያለ የአምባገነን ፀባይ ቢለግሰውም ብቅ የሚለው ከርሞ ነው:: ታዲያ ሰይጣን የዚህን ሞት ዕርቀት ቅርብ እናም ማንም ሊረዳውና ማንም ሊረበሽበት የሚችል ጉድ ሊያደርገው ይፈልጋል:: ብቅ ባለ ቁጥር ታዲያ የሚወዱትና የሚወዳቸው በሞት በመወሰዱ የሰው ልጆች እግዜርን እንዲያማርሩ ይፈልጋል:: በእዚህ የእግዜር ትልቅ ፈጠራ ጀርባ ላይ አንድ የጠባሳ ሥረት ሊለጥፍ ይፈልጋል:: እግዜር በፈጠረው አጠቃላይ የሞት ድባብ ስር ሠይጣን የራሱን ትንሽ አውሬ ማስቀመጥና ሰዎችን የተርበደበዱ ማድረግ አለበት:: መሰወር የፈለገው ለዚህ ነው:: ሰይጣን ሊታይ በማይችል መልክ በርኖሱን ለብሶ ተሟሙቆ ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣል:: ሰይጣን በፈጠራው ብዙ ጊዜ አዲስነት ያጥረዋል:: ይሔን ያውቃል:: እግዜር ምንም ቢያዳቅል ትልልቅ ተፈጥሮ ይሰራል:: የሚጊዝበት

ጉዳና ነው:: አዳምና ሔዋንን የመጀመሪያ ልጃቸውን እንዲሰጡት ሲያግባባቸውና ቃል ሲያስገባቸው በትክክል ይሔን አስቦ አልነበረም:: ደመነፍሱ ግን በእግዜር የእርግማን ሀሳብ ውስጥ የጉደለ ነገር እንዳለ ነገረው:: እርግማኑ ልሙጥ፣ አጠቃላይና ነጠላነት የሚያጥረው መሆኑን የተገነዘበውም በደመነፍሱ ነው:: ድንጋይ ሰው ቢቃጣበት አናቱን ለመሸፈን እንደሚያጉነብሰው፣ እጁንም ጭንቅላቱ ዙሪያ እንደሚሰበስብ......

እንዲሁ......

○

ከሰላሳ አመታት በኋላ ሰይጣን ተመልሶ ሲመጣ ያረጀ እንዲመስል ፀጉሩን የውሸት አሽብቶ ግንባሩም ላይ መጠነኛ የቆዳ መስመሮች ሰርቶ...... መሳጭ አእሩግነትን ተከናንቦ ነው:: አንድ ቀን አዳምና ሔዋን የሚኖሩበት ቦታ ሲከሰት ከሰጣቸው ዋሻ ገና እንደ አልወጡ አየ:: ከዋሻው ዙርያ ቀድሞ ልብ ያላለው ረገርኝ ርም የዝግባ ዛፎች ያሉበት ደን አለ:: ከደኑ ካካቴ ይፈነዳል:: በስተቀኝ በኩል የበግ በዓታና የላም እንቧታ ይሰማል:: በስተግራ ትንሽ ወንዝ ይፈሳል:: ሺህ ይብራ ሰማይና መሬቱን ሞልቶታል፣ ቆቅ ይንካካል፣ የወንዙንም አንድ ፈረድ ተከትሎ የደረቀ ሰንዳፋ ነው:: ከዋሻው ወረድ ብሎ ቀድሞ ልብ ያላለው ቅዝቃዜው የሚሰማ ፃማ አለ:: ከዋሻው በስተላይ የተራራው ዳገት በዞጲ ዛፍ ተሸፍኖአል:: አንበሶች ከዚህ ሲያገሱ ይሰማል:: ከዋሻው አጠገብ የሚያልፈውን ወንዝ ታኮ ብዙ ቁራዎች የፈሰሱበት የደረሰና ያልደረሰ ቋሳ ተዘርግቶአል:: ወንዙ ላይ የራዛ ክቢ ወተት መስሎ ተኝቷል:: የርኤም መንጋ እያላዘነ ከወንዙ ወዲያ ያልፋል:: ከዋሻው በስተግራ ዝርግ ጥቁር ድንጋይ ላይ አንዲት ነጭ ውሻ ተጋድማ ለቁጥር የሚያዳግቱ ቡችሎች ታጠባለች:: ውሻዋ አጠገብ ሃያ የሚደርሱ ዳንግሌ በጎች ተጋድመው በፀጥታ ያመነዥካሉ:: ዋሻው መግቢያ ከፍ ብሎ ያለ ዛፍ የአፈርና የሳር ዳገት ላይ ተለጥፈው የሚያናውዙ ሺህ ድምቢጦች አሉ:: ወንዙ ዳር ከበቀለ ደንበቆና ሙጃ የከብት ሆዋ ይሰማል::

አዳምና ሔዋን ሊጋ ምሽት ውስጥ እሳት አንድደው ሲሞቁ አገኛቸው:: ሰይጣን ቆሞ ካለበት ከሩቅ ሰፊ ሐይቅ መሃል የጉም ቆብ የደፋች ትንሽ የመሬት ቁራጭ ያያል:: ሃና መሃል የተኮፈሰው የዳጋ ደሴት ነው:: እዛ የምትኖር ከመቶ አመት በፊት የሚያውቃት የፌሊሞ ውብ ነበረች:: ዐይኖቹን ወደ ዋሻው መለሰ:: አዳም አስጨናቂ የወገጥ አመታት ያሳለፈ አይመስልም፣ ገና ልጅ ነው:: ያማረ ጠይም ቸብቸቦው ራቁቱን ነው:: ትልቅ ሱፋል አገልድሞአል:: ሚስቱ ሄዋንም ቁርበት ላይ ተጋድማ ተጠብሰው የጠቆሩ እንጉዳዮች ከኮባ ቅጠል ላይ እየለቀመች ትበላለች:: እሷም እንደ ባሏ ቀይ ሱፋል አገልድማለች:: የአዳም ጢም እንደ ቆሸሸ ሐረግ ደረቱ ላይ ተንዘርፎአል:: ሔዋን የተከዘች ትመስላለች:: ሰይጣን ከሰላሳ ዓመታት በፊት ያየው የሔዋን ቀልቃላነቷ የበረደ ይመስላል:: አገዳደሟ ዘንፋላነት አለበት፣ የእንጉዳይ አለቃቀሟ እርጋታ አለበት:: የዋሻውን በር ጋርደው ሦስቱም ልጆቻቸው ኩል ውሐ፣ አቤልና ቃየል የበሰበሰ ዛፍ ጉራጅ ላይ ጎን ለጎን ተደርድረው ተቀምጠዋል:: ዋሻው ፊት ለፊት ሳሩ የተገጠበ ሪም ላይ የእንስሳት ቀንድና አጥንት ተከምሯል:: ሰይጣን ከፍ ባለ ድምፅ ሠላምታ

ሠጥቶ ወደ ዋሻው አፍ ሲቀርብ አዳምና ሔዋን አይተውት ከመቅጽበት የገቡለት ቃል ትዝ ብሏቸው አሉበት ፈዘው ቀሩ:: ሔዋን ከተጋደመችበት ተነስታ አዳም ጎን ተቀመጠችና ጥቁር ባሕር የሚወርድበት የመሰለ እናቷን አዳም ትከሻ ላይ ጣል አድርጋ ሰይጣንን ሳይሆን የሚንቀለቀለውን እሳት አተኩራ ማየት ጀመረች::

«ጤና ይስጥልኝ ሔዋን:: ጤና ይስጥልኝ አዳም ደኽና ናችሁ ለመሆኑ?» አለ ሰይጣን እየሳቀና ወደ ከበቡት እሳት እየተጠጋ::

የሚንቀለቀለው እሳት አምስቱም ፊት ላይ ጥላና ብርሐን እያዘባረቀ ይጥላል:: መልስ አልሰጡትም:: ገና የሚስቅ ገጹ ላይ ዐይኖቻቸው ሲያርፉ አዳምና ሔዋን መናገር እንደሚችሉ ረሱ::

«ተቀመጥ አይባልም?» አላቸው ሰይጣን ጥርሶቹን እንደገሸለጠ:: አቤል ድምፁን ከፍ አድርጐ:

«ጠጋ በልና እሳት ሙቅ:: ጊዜው ይበርዳል» አለ:: ጎኑ መሬት ላይ የወደቀ ግንድ ባይኖቹ እያሳየው::

ሠይጣን በፈገግታ አየው::

«ጥሩ ኅበዛዝት አድርሳችኋል......መኩራት አለባችሁ» አለና የአቤልን ግብዣ የናቀ ዓይነት ሄዶ ቃየል ጎን ተቀመጠ::

«የተረሳ መስሎን ነበር» አለ አዳም በመጨነቅ በመጠበብ::

«ምኑ?» አለ ሰይጣን ነገር እንዳልገባው::

አዳምና ሔዋን ተያዩ:: ሰይጣን ከት ብሎ ሳቀ፣ መገረማቸውን ለማደፍረስ::

«ለመሆኑ አዳም ያ ያሳየኋችሁን ሣር ምን አደረጋችሁት?» አላቸው:: መናገር የፈለጉ አይመስሉም::

«ለምን መጣህ?» አለ አዳም ጥያቄውን ሳይመልስለት::

«ተው ተው ተው አዳም ቃል ተገባብተናል:: ከ30 ዓመታት በፊት:: ቃል የገባችሁልኝን መቼም ትፈፅሙልኛላችሁ ብዬ እገምታለሁ:: እናንተ የእግዜር ሰዎች ናችሁ:: ሌላ ሌላው ተንኮለኛ አለ ቃሉን አጥፌ:: እናንተ ይኼ ይኼ ዓይነት ፀባይ ሲያልፍ የማይነካችሁ የእግዚአብሔር ፍጡራን ናችሁ»

«አንችልም» አለ አዳም

«እሱ እንኳን አይሆንም:: ቃል ቃል ነው:: ነገሩን አነሳሁ እንጂ:: ቃልን መጠበቅ መሸነፍ አይደለም......በነገራችን ላይ የሚበላ የሚጠጣ የላችሁም? ከሩቅ አገር ነው የመጣሁት:: እንግዳ መቀበል አታውቁም......እ? አዳም ተለውጠሃል:: በጣም ተለውጣችኋል»

«ምንም አታገኝም:: አታለኸናል:: እያውቁም የዋህ ናቸው ብለህ አታለኸናል......ያ ጥሩ አይደለም:: ልጆቼን እግዚአብሔር ይጠብቅልኛል:: አዎ እሱ ይጠብቅልኛል» አለ አዳም በብስጭት ጭቃና አመድ ባቆሸሸው እመልካች

ጣቱ ወደ ሰማይ እየጠቆመ:: ሔዋን ከተቀመጠችበት በዝምታ ተነስታ ወደ ዋሻው ጀርባ ገባች:: ወደ ውስጥም ሳትዘልቅ በአጐዛና በቆዳ ተጠቅላ እየተንቀጠቀጠች ሁሉን ታያለች::

«አሁን በእግዚአብሔር ማመን ጀመራችሁ? ጥንት ነበር አስቦ......» አቋረጠና ሌላ ጉዳይ ማውራት ቀጠለ......

«በል አዳም እሱን አትበለኝ:: ሰዎች ቃል ከተግባቡ እግዜር አያገባውም:: እግዜር አያድንም:: በሰዎች ያለ ቃል በሰዎች ነው:: ተግባባን? በየትም በየትም መውሰዴ አይቀርም» አለ ሠይጣን ጢሙን እየላገ የለበጣ ተኰሳትሮ:: ቃየል ነገሩ ግራ ስለገባው እናትና አባቱ ከሰይጣኑ ጋር የሚያወሩትን ካዳመጠ በኋላ:

«ምን ትፈልጋለህ እንግዳ?» አለ ትንሽ በቁጣ

«ጉዳዬ ከአባትህ ጋር ነው:: የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ነህ?»

«አዎ......ምነው?» አለ ቃየል ኩስተር ብሎ::

«አሃ......አሃ......አባትና እናትህን ልትከላከል ነው?»

«በሰላም የምንኖር ሰዎች ነን......አንረብሽም እንዲረብሹንም አንፈልግም»

«ኸረ?» አለ ሰይጣን በከፊል ማሾፍ::

«አዎ» አለ አቤል ከመሐል

«አይመስለኝም:: ለማኸኝ አንተ የበኩር ልጅ......ለመሆኑ ከኩል ውሐ ጋር ከተኛህ ስንት ጊዜህ ነው? ሁለት ወር? ሴትህ ከታናሽ ወንድምህ ጋር እንደምትተኛ ታውቃለህ? አንተ እርሻ ቦታህ ከአፈር ጋር ስትታገል እሱ ጠቦት ይዞ እየመጣ......የአንተን ስንዴ ዳቦ እየበሉ ሲጠግቡ ተደብቀው የሚሰሩትን አይተሃል?»

«በቃ በቃ» አለ አዳም በቁጣ እየተቁነጠነጠ::

«ተው ተው አዳም:: ተው:: ቶሎ ቁጣ ቁጣ ይልሃል:: ቁጣ ብልሀነት ከሌለው ምን ያደርጋል? የአዳም ቁጣ ግራ ነው:: አዳም ይቆጣል ይታለላል ይቆጣል ይታለላል:: የማያልፍለት:: ምን እንደሚባል ታውቃለህ? ተተርቶብሃል......«የአዳም ቁጣ» ተብሎ:: ምን ማለት እንደ ሆነ ታውቃለህ? ሳያቋርጡ መቆጣትና መታለል:: ዘሮችህ እንደዛ ይሆኑ ይሆን? ትልቁ ልጅህም ያንተን ሳይወርስ አይቀርም:: ለማንኛውም ቃል ከተገባ መሆኑ አይቀርም:: ቃልህን ልሰማ መጣሁ እንጂ......»

«ጥሩ አልነበረም የሠራኸው ስራ» አለችው......ሔዋን ወደ አዳም ጎን ተጠግታ ራሱን እየዳበሰች::

«እሱን ጨርሰነዋል»

«አላለቀም» አለ አዳም ከተቀመጠበት ተነስቶ በእግሩ የሚቀጣጠል ትልቅ የጉቶ እንጨት እየመታ:: ፍም በየቦታው ተበታተነ:: ልጆቹ ከተቀመጡበት ተደናግጠው ተነሱ:: አላስተዋሉም በሰይጣን አቅጣጫ የተፈናጠሩት ቀለምዒዖች

ጤዛ ሆነው ሲወድቁ::

«ምንድነው የሚፈልገው?» አለ ቃየል::

«ሊወስድህ ይፈልጋል» አለ አዳም::

«ውሸት:: ውሸት» አለ ሰይጣን ከተቀመጠበት ተነስቶ::

«ውሸት:: ቃላችን፣ ንግግራችን ነው የሚወስድህ:: ከ30 ዓመታት በፊት ከአባትህ ጋር የመጀመሪያ ልጁን ሊሰጠኝ ተዋውለን ነበር:: ዛሬ ቃሉን ሊክድ ዳር ዳር ይላል:: አንተን የመሰለ ጉረምሳ በውሽታም አባት የሚያድግ አይመስለኝም ነበር......ይሆናል ለካ!......ሃሃ!!......አይ አለማወቅ:: አይ አይ አለመብሰሌ» ቃየልና አዳምን እያቀያየረ አያቸው::

ቃየልና አዳም ተያዩ:: ቃየል ፊቱን መለሰ:: ፀጥታ ነገሰ:: እሳቱ እየተንጣጣ ይቀጣጠላል::

«ቃየል ስማህ ልጄ ልጅ መውለድ ምን እንደሚመስል አላውቅም ነበር:: እኔም እናትህም»

ቃየል ፊቱን መልሶ አባቱን በቁጣ እየውና:

«ለዚህ ነው እኔን የምታሸሹኝ:: ለዚህ ነው ለእኔ ከባድ ሥራ የምትሰጡኝ ......ሥራ ቦታዬ ስውል ከኩልውሒ ጋር አሼሼ ገዳሜ ልትሉ? በልባችሁ ከዕለታት አንድ ቀን ትቻችሁ እንደምሄድ ታውቁ ነበር ማለት ነው? እኔ ላይ የተደረገውን ሴራ ታውቁ ነበር? 'እስቀያሚ' እያላችሁ የምታሸሹኝ ለካስ ሌላ ጉድ አቀናብራችሁልኝ ነው:: አንተስ አቤል ታውቅ ነበር አይደለም?......»

«በፍፁም! በፍፁም ጋሼ»

«እሱም እንደ አንተ መስማቱ ነው» አለች ሔዋን

«ውሸት:: ለምን አምናችኋለሁ? እስከአሁን ከኖርኩት ውጣ ውረድ እንደማትወዱኝ መገመት እችላለሁ:: ለካስ አባት በድብቅ አዘጋጅታችሁልኛል:: ነገሩ ሲታወቅና ቀኑ ሲደርስ ያለፈቃዳችሁ ያደረጋችሁት ታስመስላላችሁ»

«ኸረ ቃየል በእግዚአብሔር......በእግዚአብሔር......» አለች ሔዋን::

«ምን በእግዚአብሔር ትይኛለሽ......ይልቁን ለዚህ ለእንግዳው ለአባቴ የሚበላ፣ የሚጠጣ አምጭለት:: አታስመስሉ:: የተከፋችሁ አታስመስሉ:: በይ የሚጠጣ አምጪለት:: የማርሰው እኔ:: እህሉ የእኔ» ቃየል ከተቀመጠበት ተነስቶ ተንቆራጠጠ::

«ተው እንጂ ቃየል:: ተው እንጂ ሥነስርዐት ያስፈልጋል»

«ሥነስርዐት? የምን ሥነስርዐት? በምንድነው የሸጥከኝ ለመሆኑ? የምን ውል ነው እንስማው» አለ ቃየል::

ሰይጣን ተረጋግቶ የሁሉን ፊት እየለዋወጠ ደስታውን አንጀቱ ደብቆ የሁሉን ፊት እየለዋወጠ ያያል:: አለመተማመናቸውን አየ:: አለመተማመን

የሞት መጀመሪያ ነው:: አለመተማመን ያ ረዥም ጎዳና ነው ሞት ተረጋግቶ የሚጓዝበት:: ያቺ ጎዳና ናት ግጭት ተፀንሶ የሚወለድባት:: ቂም የሚያብብባት:: ይቅርታ የሚሰወርባት:: ሰይጣን ያያል ዓይኖቹ ስር የሚፈልገው ስርዓት እየተገነባ ሲንገረገግ::

አዳም በእፍረት አንገቱን ሰበረ:: ሰይጣን ረጋ ብሎ ከ30 ዓመታት በፊት የሆነውንና ከወላጆቹ ጋር የተዋዋሉትን ጉዳይ እየደመረና እየቀነሰ በሚመቸው መልክ ባጭሩ ለቃየል አወራው:: ቃየል እንደ ወፈፌ ሆነ:: አንድ ጊዜ ወደ ዋሻው እየተራመደ አንድ ጊዜ የዛፍ ግንድ እየደበደበ፡

«ለሆድ ሸጣችሁኝ:: ለሆድ?»

«ስማ ቃየል እንደዛ አይደለም:: ለሆድ አይደለም» አለ ሰይጣን::

«በል ዝም በል፣ አሁን ራስህ እያልከኝ? ለምን ተሰጠሁ ሊባል ነው? ለምን ተሰጠሁ ልትለው ነው?»

«ከዚያ በላይ ነው:: ቅድም እንዳወራሁት አባትና እናትህን ከገነት ያስወጣቸው ሆድ አይደለም:: ጉጉት ነው:: አንተን ለእኔ ያዋዋላቸው እንዲሸልሙኝ ያደረጋቸው ጉጉት ነው:: አታቅለው:: ሆድ በተገኘው ይሞላል:: ጉጉት ግን ያን የፈለከውን ካላገኘህ አይበርድም:: የሰው ልጆች ድክመትና ጥንካሬ ነው:: ከቀናህ ጥንካሬ ይሆናል:: ካልቀናህ ድክመት ይሆናል:: ይልቁን መነጫነጩን መነታረኩን እናቁምና ከሩቅ መንገድ የመጣሁ ሽማግሌ ነኝ እህል ውሐ በሉኝ»

«ግን......ግን ይሔ ጉጉት ፈጠረ የተባለውን ጉድ ባየው እወዳለሁ:: የት አለ?» አለ ቃየል::

«እኔም ባየው እወዳለሁ» አለ ሰይጣን

«ምን?» አለ ቃየል

«ባየው እወዳለሁ?» አዳም ግራ ተጋብቶ ሠይጣን ላይ አፈጠጠ::

«ምን ታየኛለህ?» አለው ሰይጣን ከተቀመጠበት ተነስቶ

«ለምን አላይህም? አታውቅምና ነው? ውሸታም ሰው ነህ»

«ቆይ ቆይ:: እኔ አልዋሸም:: እግዜር እናንተን ሲፈጥር በአምሳሉ ነው:: ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? እንደ እሱም መስራት ትችላላችሁ ማለት ነው:: በራሳችሁም አምሳል ፍጡር መፍጠር ትችላላችሁ ማለት እኮ ነው:: እየውማ ትልቁ ልጅህን:: ያን ጊዜ ካልረሳችሁት እግዜር ነገሮች ሲፈጥር አዳቅሎ ነው ብዬአችኋለሁ:: ይደባልቃል የነጠረ አይደለም ብዬአችኋለሁ:: ሰብሉን አሳየኋችሁ:: እኔ በተቻለኝ አቅም እንዴት እንደሚፈለፈል፣ እንዴት እንደሚዘራ አሳየኋችሁ:: ከዚያ በኋላ በለሷን መፍጠር የራሳችሁ ጉዳይ ነው:: 30 ዓመቶች ሙሉ ስታርሱ የበለሷን ልብ አልሰራንም እንዳትሉኝ......ሃ......» አለ ሰይጣን::

«የምን እርሻ ነው?» አለ ቃየል::

«አልገባህም:: የተሸጥክበትን ዕቃ ራስህ ስታዘጋጀው ነበር» አለ ሰይጣን::

«ምን ማለቱ ነው ይኼ ሽማግሌ?» አለ ቃየል

«ቀስ ቀስ» አለ ሰይጣን የቃየል አባባል ያስደነገጠው መስሎ::

«ትልቅ ሴራ ነው የተሰራብኝ ማለት ነው:: አሳዩኝ እስኪ:: በገብስ ሸጥ ከኝ......በሽምብራ? በምስር? በበቆሎ?» አለ ቃየል

«ኸ ኸ......በጤፍ» አለ ሰይጣን ድምፁን ዝቅ አድርጎ ፊቱን ወደ መሬት ደፍቶ ልክ ሚስጢር እንደ ሚናገር::

«ምን? በጤፍ?» አለ ቃየል ደንግጦ:: አዳምና ሔዋን ፊታቸውን ወደ መሬት ደፉ::

«በጤፍ......ምነው? ምናለበት?» አለ ሰይጣን ቀና ብሎ የውሸቱን ፊቱን ኮስተር አድርጎ::

«በጤፍ!......ጉድ!» አለና ቃየል በተስፋ መቁረጥ ከቆመበት መሬት ላይ ቁጭ እያለ::

«እንየዋ» አለ ሠይጣን ወደ ሔዋን እያየ:: ከሚነደው እሳት ነበልባሉ የሚንቀለቀል ጉልጥምት ይዛ ወደ ዋሻው ጀርባ ገባች:: የምትሰራውን ለማየት እስከ ደጃፉ ድረስ ተከተላት:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጠፍጣፋ ሸክላ ላይ የተከመረ ነጭ የጤፍ እንጀራ ይዛ ተመለሰች::

«አይዞህ ቃየል እኔ ስወስድህ ነፃ ሰው ትሆናለህ:: እኔ ስወስድህ ልብህ ይረካል:: አሁን ይኸቺን ነገር እንቋደሳት» አለ:: ሔዋን ፊቱ ጥላለት የሔደችውን ሠፊ ቀራፎ እያየ:: መመልከቻና እህሉን ማጥኛ በቂ ብርሐን ለማግኘት ጠፍጣፋውን የሸክላ ሰሐን ከዋሻው ጥላ ስር ይዞት ወጣ::

«እም......እም......ሲያዩት ያምራል......ለመሆኑ ይኼ የፈጠራ ሥራችሁን ስሙን ማን አላችሁት?» አለ እየሳቀ ቀና ብሎ:: የእንጀራውን ጉብታ ነካካና ከላዩ ጣል የተደረገውን ሐር የመሰለ ቁራጭ አንስቶ ከስር የተወሸለውን ነገር በዓይኖቹ አጠና:: ከቁራሹ እንኩሮ ስር በበርበሬ የደመቀ ለጋ ቅቤ ውስጥ የተነከረ ትንሽ የፍርፍር ክምር አየ:: ከቆመበት ዛፍ ስር እጁ መሐል ካስቀመጠው ሸክላ ሰሐን ላይ ጢስ ሲነሳ አየ:: ወደ አፍንጫው ወስዶ በቀስታ አሸተተው:: ቀና ብሎ ወደ ዋሻው አየ:: ሁሉም አፍጠው ይታዘቡታል:: በይሉኝታ ከእንጀራው ቆርሶ ከፍርፍሩ ክምር በአውራ ጣቱ ንዶ በእንጀራ ጠቀለለና ጎረሰ:: የገባው ነገር በዚያች አፍታ የበላው ምግብ በፍፁም እንደ በለስ ልብ እንዳልሆነ ነው:: ቅርፁ የበለስን ልብ ይመስላል እንጂ የገመተውን ያህል አለማማሩ ነው:: አለመጣፈጡ ነው:: ለመናገር አፉን ሲከፍት:

«ዝም ብለህ ብላ» አለ አዳም::

«እዩ......ይኼማ ጥሩ አይደለም:: የሚያሳፍር የለውም:: እንዴት ቢሰራ

ብትነግሩኝም ሚስቴን ላስተምራት እችላለሁ:: ክፋት የለውም:: ባትነግሩኝ ምን ይለውጣል? መስማቴ አይቀር:: ወሬ ከነፋስ ቀድሞ ይጓዝ የለ:: ወሬ እንደሚባለው ከዕርግማን ይፈጥናል»

«ከምትወደው ወሬህ ስማው:: ብላና ይውጣልህ» አለች ሂዋን እየተመናጨቀች::

«ማወቁ አይቀርም:: ያቀያይመናል እንጂ.»

«ያቀያይመናል? ተቀያይመናል እንጂ.:: በቅቶናል» አለ አዳም::

«አይ አዳም:: ከአምላክህ ተቀያይመህ:: ከእኔ ተቀያይመህ:: ወዳጅ የሚያስፈልግበት ምድር ላይ ነህ ያለኸው:: እስኪ የሚስትህን መረቅ ልቅመስ:: በነገራችን ላይ ሔዋን እያማረባት ነው:: ወላድነት ያሳምራል መሰለኝ:: ወይስ አርግዘሻል?......እስኪ ልቅመሰው ይኼን እህል......»

«ቶሎ በልተህ ጥፋ» አለች ሔዋን ዋሻው በር ላይ እንደቆመች:: ዘንግታ በእጇ የያዘችውን ጉልጥምት ወደ እሳቱ ውስጥ እየወረወረች::

«ቀስ ሴቲቱ......ቀስ......'ሴቷ' ነበር የሚልሽ ፈጣሪሽ......ምን እንዲህ የሚያበሳጭ ነገር አለ......በጣም የሚጣፍጥ እህል ነው» ዐይኖቹን ጨፍኖ ማላመጥ ቀጠለ:: ጣዕሙን እየፈተሸ እየመሰለ በጣዕሙ የተመሰጠ እየመሰለ.........

«በምን ተሠራ? ቅመም ለመዳችሁ? ትንሽ ያቃጥላል......ማቃጠሉ ነው ዋናው......ቅቤም ለመዳችሁ? ጎበዞች ናችሁ:: ብሩህ ናችሁ:: ዕውነትም የእግዚአብሔር ምስል ናችሁ:: ኩልውሐ ስለ ዕርግዝናሽ......ልጠይቅሽ?»

«ምን አገባህ ደ'ሞ ሌላ ልጅ ፈለግህ?» አለ አዳም

«ይቅርታ ልጅ በላ አይደለሁም:: ነጋዴ ነኝ:: አንዳንዴም ፈላስፋ ነኝ...... ስለ ዕርግዝናሽ:: ከአቤል ነው ያረገዝሽው አይደለም? እ?» አለ:: ሌላ ጉርሻ አፉ እያስገባ:: እያላመጠ በማሾፍ ፈገግታ ሔዋንን፣ አዳምንና አቤልን፣ ቃየልን ኩልውሐን እያቀያየረ እያየ::

«አላረገዝኩም» አለች ኩልውሐ::

«አትዋሺ......አትዋሺ ያስታውቃል:: ሆድሽ ገፍቶአል» አላት::

ቃየል የተቀመጡትን ቤተሰቦቹን እያቀያየረ ተመለከተና መሬት በጥፊ መታ::

«ምን አበሳጨህ?» አለ ሰይጣን ነገር እንዳልቀሰቀሰ::

«ምን ይደረጋል......ማንን ልመን?» አለ ቃየል በብስጭት

«ስለምኑ?» አለ ሰይጣን እንደ ደንቆሮ::

«በጤፍ ሸጡኝ......እንደገና እንደገና......»

«ምነው መናገር ፈራህ......» አለ እንዳልገባው:: ቃየል ወደ ኩልውሐ ተጠግቶ አጉዛዋን ገልጣ ሆዷን እንድታሳየው ጠየቃት:: እምቢ አለችው::

«እህትህን እንዴት ያን ዐይነት ነገር እንግዳ ፊት ትጠይቃለህ?» አለ አዳም ከተቀመጠበት በቁጣ ተነስቶ።

«ቢሆንም ዕውነት የተገኘበት ቦታ መውጣት አለበት» አለ ቃየል በመናደድ።

«'መኑ ነይጠበብ እምአዳም ወስህተ በብዕሲት[77] የተባለውን አልሰማህም? ታሪካቸውን አባትና እናትህ አልነገሩህም እንዴ? ይወራል በአገሩ...... ያልሰማ የለም። ይኼ እኮ ቀላል ነው ልጄ። ሐጢያት ከአሁን በኋላ ደንብ ነው ሃሃሃ» አለ ሰይጣን እንደ ብርሃን የፈገገ ጥርስ እያሳያቸው። ቃየል ገላመጠው።

«ቆይ ቆይ የማልወደው ነገር ሰው ሲጣላና ሲጎዳ ማየት ነው። ያጣላችሁን ነገር ለምን በግልፅ አትናገሩትም?» አለ ሰይጣን አሁንም እንዳልገባው።

«ምን አገባህ?......ጥፋ አንተ ሽማግሌ» አለ ቃየል።

«እሔዳለሁ። እሔዳለሁ። ቢያንስ የዚህን ስም ንገሩኝ። የምበላውን ነገር ስም ንገሩኝ» አለ ወደ ማዕዱ በረጠበ እጁ እያመለከተ።

«ጤፍ እንጀራ ፍርፍር ይባላል» አለ ቃየል በንዴት።

«ጥሩ። በጣም ጥሩ። እንጀራ ፍርፍር። ልንገራችሁ? የመጨረሻ እርካሽ ነገር፣ የመጨረሻ ውድ ነገር በእንጀራ ፍርፍር መሸጥ መለወጥ ነው። እኔ ግን ጥሩ እቃ የለወጥኩ አይመስለኝም» እጁ ላይ የተለወሰውን ቅባት በልብሱ ጠረገ።

«ምን ታወራለህ። ሒድልን። ተወን በሰላም» አለ አዳም። ሰይጣን ከተቀመጠበት ተነሳና ልብሱን አራገፈ። ለመናገር እንደፈለገ ሁሉ ሳሉን ሳለ። አዳምን ሔዋንንና ልጆቹን በየተራ ገላመጠ።

«የሚገርመኝ......እንደ እናንተ ያሉ ደካሞች እንዴት ይኸቺን ዓለም አሸንፈው መኖር እንደሚችሉ ነው። የሚገርመኝ ካልጠፉ የተባ ፍጡር አምላካችሁ እናንተን መፍጠሩ ነው። ዕውነት ዕውነት እላችኋለሁ አልቻለበትም። እዚህ አባትና እናት ልጃቸውን በፍርፍር የለወጡ። እዚህ መሸጡን ያላወቀ አስቀያሚ ቂል፣ እሱን እዚህ በከባድ ሥራ ጠምደው መልከ መልካም ብለው ያሉት ታናሽ ወንድሙ ሴቲቱን በሚስጢር እንዲያስረግዝ የሚያደርጉ እናትና አባት። እዚህ የማይረባ እረኛ ወንድሙን ለሴት የከዳ። ይኼ ነው......ይኼ ይኼ...... (በእጁ እያሳየ) ቤተሰብ ነው ተባዝቶ አለምን የሚሞላው? ለማንኛውም ቃየልን ወስጄዋለሁ። እኔ የምወስድበት መንገድ አለ። አብሮኝ በአካል አይሔድም። ግን እወስደዋለሁ። ለእናንተም፣ ለሌላም ራስ ምታት አደርገዋለሁ። ትንሽ ከእናንተ እሱ ይሻላል። መሸፈት ይችላል። የእናቱ ጥቂት ደም አለበት። በሉ ብዙ አወራሁ። ደኅና እደሩ......ሃሃ» አለና ወደ ደኑ በቀስታ እየተራመደ ገባ። ከኋላው ሔዋን ትጮሃለች፡

«ያንሳህ እቴ!......የሚያነሳ ያንሳህ!......ጅቡ ይብላህ!» እያለች። ሠይጣን ከእነሱ ዐይን ከተሰወረ በኋላ እየሳቀ በወንዝ ላይ ይራመዳል......ጨርቁን ገፎ ወደ ሰማይ ለመብረር ይነሳል።

---

77 ከአዳም ማን ጥበበኛ ይሆናል እሱም በሴት ተሳሳተ(ግዕዝ)

**ኡኡታ......**

ሰይጣን አካላዊነቱን ትቶ እረቂቅ መሆን ሲጀምርና ከወንዙ ጠለል ላይ እንደ ድኝ ላቦት ወደ ላይ ሲነሳ ከታች ከመሬት እነ አዳም ከሰፈሩበት አቅጣጫ ጩኸት ሰማ:: ኡኡታ:: ከገነት ውጭ ምድር ላይ የተሰማች የመጀመሪያዋ ቁቁታ:: እንደ አዝማች ይኸቺ ኡኡታ እንደ አንጊ ይኸቺ ጩኸት በሕይወት ዘፈን ውስጥ በሕይወት አገዳ ላይ በብርቱ የምትገባ ናት:: ከአጀማመሯ በተለይ የሴት መሆኗ ኡኡታዋን ውብ፣ አስቀያሚ፣ አስደንጋጭ፣ አስገራሚ፣ ዕንግዳ፣ ያደርጋታል:: ሴቷ የኡኡታ ልምድ ያላት አትመስልም:: በአዳኝ እንደ ቆሰለ እንስሳ ቡታው ተራራ ጫካ ሞልቶ......ምሽጉም በመፍረሱ የሚበሳጭ...... የሚሸሸው አደጋ ግን አፍንጫው ሥር ተተግኖ እየሸተተው......ቅጠሉ እሽንጡ ተቸንክሮ ዛቢያው ነፋስ ውስጥ እንደሚወዛወዝ አፎቄ......

ቁስል እየሰራ፣ ያልነበረ ቁስል እያበጀ::

የእርግጠኛነትን መጥፋት የሰው ልጅ ዐይን ሥር ያስቀመጠች ጩኸት......

ጅምላ ሞት የግል ስትሆን......ዝርዝር ሲወጣላት......

ሠይጣን ያቀደው እንደሰራለት አወቀ::

ከሚበርበት ሰማይ ወደ ታች ሲመለከት ቃየልን ሲሮጥ አየው:: የለበሰው ቆዳና አጐዛ ከላዩ ይወድቃል:: በአናቱ ላይ የሰካው የሳር ቆብ ብቻ ሲቀር እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ አፍረቱን ጥሎ እንዳበደ ሁሉ በእርሻ መሐል ይሮጣል:: የሰራው ስራ ጨካኝ ግን ቀላል ነበር:: ሔዋን ኮረብታ ደርዝ ላይ ቆማ ሁለቱንም ክንዶቿን ፊት ለፊት ዘርግታ እዬዬዋን ትለቃለች:: የመጀመሪያው የለቅሶ ግጥም ከኮቸሩ ከንፈሮቿ በምሽት ነፋስ ይጠለፋል:: የሰው ልጅ የመጀመሪያው የለቅሶ ግጥም እንዲህ እንዲህ የመሰለው:

**በኩሬ ኮበለለ!**
**ወንድሙን ቀተለ!**
**በኩሬ ኮበለለ!**
**አቢቹን ገደለ!**

ጎፈሬዋን ነፋስ ወደ ጀርባዋ ይገፋዋል፡ አዳምም ትከሻዋ ላይ እጁን አስቀምጦ መሬት መሬት እያየ ገላው በለቅሶ ይርገፈገፋል:: ያገለደመው ለምድ ወገቡን ለቆ ወርዶ መሬት ላይ ተሰብስቧል፣ ራቁቱን ነው:: በዝምታ ተኝተው የነበሩ ውሾች በድንጋጤ ተበታትነው ያላዝናሉ፣ ቡችሎች ተረብሸው መሬት ላይ ወዲያ ወዲህ እየተንከባለሉና እየተርመጠመጡ ያለቅሳሉ፣ የደነበረ የጎሽ መንጋ ሙጃና ፊላ እየጣሰ ይሮጣል፣ ከውሃው ያልገባ ሞርስ ወደ ሰማይ አንጋጦ ያጓራል፣ ዋሻውን ከከበቡት የዝግባና የዞፒ ደኖች ውስጥ ያሉ እንስሳት በመበርገግ አያሌ ዋዋታ አወጡ:: ኩልውሐ በፍርሐት ዋሻው ደጃፍ ላይ እየተንቀጠቀጠች ቆማለች:: ድንጋጤ አስቷት በእግሮቿ ላይ ሽንት ይወርዳል:: ምን ማድረግ እንደሚገባት አታውቅም:: አዳምና ሔዋን ከቆሙበት ዳገት ወርደው አቤል ደም

ፈሶት ወደ ወደቀበት ነጭ አረንዛ መሬት ቀረቡ:: ሁለቱም ሲያነሱት አጎነበሱ፣ ነፍስ የሌለው የአቤል ገላ አዳም ክንድ ላይ እንደ ትኩስ ጤፍ እንጀራ ተዘለሰ:: «ልጄ ልጄን ገደለው! አቤልን ገደለው! ምን ሆንክ!? ምን ነካህ ቃየልዬ!? በኩሬ ኮበለለ! ወንድሙን ቀተለ! በኩሬ ኮበለለ! አቢቹን ገደለ!» ትላለች ሔዋን::

እንዲህ ሲሆን ሰይጣን አዳምን ቀርቦ አላየውም:: ልቦናው ቃየልን እመንጠቁ ላይ ነበር:: በዚህ ምኞቱ ሰክሮ ቸለል ሲል አዳምን ልብ ብሎ አላየውም:: አዳም ሚስቱን ወደ ደረቱ ሲያስጠጋት አላየውም:: አዳም ሔዋንን ወደ ደረቱ አስጠግቶ እቅፎ ሲያዝን አላየውም:: ሔዋን እዬዬዋን ስትለቅ አዳም አዝኖ ከዐይኖቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕንባ ሲወጣ አላየም:: አዳም ወደ ሔዋን ተጠግቶ ዓይኖቿን ሲስማቸው ሰይጣን አላየም፣ ግንባሯን እየሳመ ሲያባብላት አላጤነም:: ሰይጣን ምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ «መሳም» ሲፈጠር አላየም:: በመሳም የታጀበ ርህራሄ ሲፈጠር አላስተዋለም:: አዳም ሚስቱን ሲስማት የዕንባን ጨው ጨው ማለት ለመጀመሪያ እንደተረዳ ሰይጣን አላጤነም:: የሰይጣን ዓይኖች ያተኮሩት ያለ ዓላማ በሚከንፉት የቃየል እግሮች ላይ ነበር:: እነዚህን እግሮች የት ወስዶ እንደሚያሳርፋቸው እያሰላሰለ ነበር......:

ወደ ታች ዝቋላ ወይስ የድሮ ወዳጄ ቤት ያች ድራተኛ ወዳለችበት ዳጋ?

ሠይጣን እየሳቀ......

እንደ ጥቁር አሞራ እየዋኘ ሰማይ ጨለማ ውስጥ ገባ::

ግን......

አዳምን አላየውም:: አዳም ሔዋንን እያባበለ እየሳመ ሲያፅናናት......

ባዶ ሳርና ቅጠል የሞላው እቀዘቀዘ አገር ላይ የሰው ልጅ ርህራሄነትን ሲያምጥ ሰይጣን አላየም::

*ሰኔ 1987 ሆላንድ*

# ለድልህ

## ስለ መናፍቅ

ካሌብ ጥቃትን በቀላሉ ተቀብሎ መዋጥ ብቻ ሳይሆን ይሔ የመዋጡ ድርጊት አንጀቱ ውስጥ (ከእንብርቱ ትንሽ ዝቅ ብሎ) አልፎ አልፎ የሚቀሰቅስበትን አጓጉል የበቀል ቁጣ ያለ ችግር መግታት ይችላል:: ሆደ ሰፊ የሚባለው ነው ('ሆደ ቦርቃቃ' እንደ ማለት):: ማንም ሰው ሊያጠቃው የሚወረውርበትን የመጉዳትና የሁከት ዳረጎቶች፣ ያያቸውን ያላየ፣ የሰማቸውን ያልሰማ መስሎ 'ጨዋ' እንደሚባሉት አንገቱን ሰብሮ በደበዘዘ ፈገግታ ይቀበላል:: የማያምርና የሚጎዳውን ውጤቱንም የቸልታ ሰፍነግ እንደ ባሕር የተዘረጋበት ሆዱ ውስጥ ያበርደዋል:: አንዳንድ ጊዜ ይኼን ደካማ ልማዱን አጠራረቡ መበላሸት በጀመረው አእምሮው ያላምጣል (መደነዝ የጀመረው ይኼ ዓይነት 'የመቻል' ስራ ስለበዛበት ይመስለዋል):: ልማዱ ያበሽቀዋል:: እንደ እግሩ፣ እጁ፣ አፉ፣ ሌሎች ብልቶቹና ልብ ምቱ ይኼ ባሕርይ አብሮት የተፈጠረ ይመስለዋል:: ገና ወጣት ነው ግን በረባ ባልረባው ጉዳይ ሁሉ የማንንም ቅንዳሻም የትችትና የዕርፈት እሳት በአንድ ጆሮው እያስገባ በሌላው አመዱን እየተፋ እንዳልተነካ ሁሉ በቲያትራዊ ቸልታ ከማለፍ በስተቀር፣ ከተወሸቀበት ድንጋዩ ወጥቶ የሚያዋክቡትን መስደብና መቀናቀን ያልቻለ ኤሊ ነው::

አንዳንድ ጊዜ ሲማረር አስከፊ የሆኑ፣ እንኳን ሰው ይቅርና የድንጋይ አድባር አውጋር የሚያቀልጡ አባባሎች የጥርሶቹን ስልፍ አልፈው መፈንከት የሚገባውን ሰው ፈንክተው፣ የሚያነዱትን አንድደው ራሳቸውን ማጥፋት ይፈልጋሉ:: በዚህ የመልስ ድርጊት ሕይወቱ ምሉዕ እንዲሆን ይፈልጋል...... ግን በቸለልተኛ ትዕግስቱ ይገላቸዋል:: አንዳንዴ በልቦናው ሰውን ከማክበርና የሰውን ስሜት ከመጠበቅ ወጥቶ (ቢያከብሯቸውና ስሜታቸውን ቢጠብቁላቸው

የማይገባቸው አእላፍ ዓይነት ሰዎች አሉ) የለከፉትን መልሶ መልከፍ የግል ደንቡ ማድረግ እንዳለበት ያምናል:: ስርቶት ግን አያውቅም:: ይኼ በሚገርም መልክ ኑሮውን ያልተሟላ እንዳደረገበት ይገባዋል (ትንሽ እንኳን ክፉ መሆን መልካም እንደሆነ ሁሉ):: ሴት ጓደኛው ሰብለ ይሔን የመታገስና ችላ የማለት ፀባዩን ስለምታውቅ ከአገኘችው ጀምሮ እስክትለየው ድረስ በትንንሹ ጉዳይ ትወጋጋዋለች፣ ትነካካዋለች:: ይኼ ድርጊቷ ትክክል እንዳልሆነ ቢያውቅም አልፎ አልፎ ቢያማርረውም፣ ስለሚወዳት ብቻ ችላ ይላታል......

## ስለ ሰብለ

ሰብለን ይወዳታል:: ሰብለን የሚወዳት ስታወራ ነው:: ሰብለን የሚወዳት ስትስመው ነው:: ሰብለን የሚወዳት አንዳንድ ጊዜ ደንግጣ በሆነ አጋጣሚ (ውሸቷንም ሊሆን ይችላል) ክንዱን ይዛ ጐኑ ጥብቅ ስትል ነው:: ሰብለ በሁለት እግሮቿ ወገቡን ቆልፋ 'ካሌብዬ!' ስትለው (ከንፈሮቿ 'ብ' ን ለመስራት ከተነካኩበት ተላቀው ተከታይዋን ሆሄ 'ዬ'ን ስትጠራ አፏ የሚሰራው ቀርፋፋ አከፋፈት) እንደዛ ሲሆንም ይወዳታል:: ሰብለን የሚወዳት ስለቤተሰቦቿ ፈጣጥራም ዕውነቷንም ስታወራው ነው:: ሰብለ ወጥ የነካካቸው የሚያማምሩ ጣቶቿን ድንቡሽ ከንፈሮቿ መሃል ሰክታ ስትጠባቸው (ዘገበአ ዘወጥአ) እንደዛ ሲያያት ይወዳታል:: ሰብለን የሚወዳት የከንፈር ቀለሟ ቡናማ ስለሆነ ነው:: ሰብለን ሁልጊዜ የሜንተል ጠረን ስለሚከባት ይወዳታል ('አባትሽ ቤታቸውን የሰሩት ባሕር ዛፍ ላይ ነው እንዴ?' ሊላት ይዳዳዋል አንዳንዴ):: ሰብለን የሚወዳት ፊቷን ዘንበል አድርጋ ጆሮዋ ላይ የወደቀውን የፀጉር ሰበዝ በቁሌታም ደንብ ዞር ስታደርግ ነው:: ሰብለ ግን ከምንም ከምንም ከማንኛውም አርዕስት የበለጠ 'ስለዚያን ጊዜው' ማውራት ትወዳለች: ዳቦ በሙዝ ስለበሉበት፣ ዳቦ ቆሎ ስለከተከቱበት እስር ቤት፣ ነጋ ጠባ በስጋት እየተያዩ ሕይወት መነፈግን ስለፈሩበት ዘመን፣ እዛ ስላወቋቸው አብረው ታሳሪዎች፣ በዚህ ሁሉ ሰበብ ስለ ተጫናት ቸልተኛነትና 'አንተ ብቻ ቀረኸኝ' እንቶ ፈንቶ......

እሱ ደ'ሞ ታሪክ ያደክመዋል:: 'ያኔ የታሰርን ጊዜ' ምናምን የሚባል ነገር ሰልችቶታል፣ 'አታውቀውም እንዴ እሱን ከፍተኛ እስር ቤት አብሮን ነበረ' ምናምን ከሚባል ነገር መራቅ ይወዳል......እሷና እሱ እዚያው ከሚያደርጉት ግኑኝነት ውጭ ሌላው ሌላ ሆኖአል:: ስለተዋወቁበት የከፍተኛ ሃያ እስር ቤት፣ ስለዚያም የሦስት ወራት የስጋት ጊዜ አያወራም:: ሕዋሳቶቹ የከተቡትን ነገሮች ሁሉ በልቦናው ሰብስቦ እንደያዘ ቢያውቅም ለዛሬ የሚበቃ ወሬ የሚሆን አይመስለውም:: እሱ ስለማንም (ስለ አሰረውና ከመታሰሩ በፊት ስላገለገለው ድርጅት) ስለ ምንም (ስለ እስሩና አብሮት ስለሚመጣው የስነ ልቡና ጭንቀት) አያወራም:: ዛሬ ፍቅር መስጠት የማይችሉ፣ ዛሬን በመልካም በሚጥም መንገድ ማጠናቀቅ የከበዳቸው ጉድለታቸውን ለማሟላት ወደ ኋላ ስለሚሸሹ 'የነበር ወሬ' ይወዳሉ ብሎም አይደለም:: ፍልስፍና የለውም:: በአጭሩ 'ያኔ የታሰርን ጊዜ' ብሎ ትዝታ ማውራት አይሻም::

ከዚህ ዓለም በሞት ሊሰረዝ የደረሰ የመሰለው ጊዜ ውስጥ ነው ሰብለን ያገኛት:: እና ደ'ሞ የዚህ ይሉኝታ አለበት:: ልክ እሷ እንዳዳነችው ሁሉ::

ባታድነውም ብቻ የስነ ልቦና ድጋፍ ነበራት......ፍርሃትና ስጋት ሲወጥረው ጨለማና ፀጥታን ተገን አድርጎ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን እየረገመ ጋቢ ድንኳን ስር ሰብለ ሴትነት ውስጥ ፈንድቶአል......ከተፈታ ጀምሮ ግን እንደ ተለወጠ ሰብለ አልተረዳችም:: እሱ እዚህ ነው:: እዚህ መሆን ይፈልጋል...... እሷ እዛ ናት ታሪኳን ተለማምጣ ያለች፣ አዲስ ዕውቀቷን ሁሉ በዚያ መነፅር የምታይ......ለሚያወራው ነገር ሁሉ ማወዳደሪያዋ ትናንት ነው:: አማሮታል......

መልካምም ሆነ ክፉ ባለፈ ጊዜ ሱስ መያዝ አይወድም:: አሳጥሮ ይቀበላል:: ያለፈው ዘመን ለእሱ ሰብለን ሰጦታል ደ'ሞም ሌላ ነፍጎታል......በቃ:: አንዳንድ የማያመልጡት ነገር አለ፡ ታሪክ የሰጠውን ሰንበር--እሱ ላይ እያፈጠጠ ማርጀት አይፈልግም፡ የአለፈው ዘመን ቅጥረኛ መሆን አይፈልግም:: ሰብለ እንደ ተለወጠ ግን አልተረዳችም:: ምክንያቱም አልነገራትም:: 'ያኔ......' ብላ ማውራት ስትጀምር አእምሮውን ወደ አጋጠመው አቅጣጫ ለስደት ይለቃል፣ እያያት አይሰማትም......ጭንቅላቱን በምትለው እንደተስማማ ሁሉ እየነቀነቀ አያናግራትም......

......ለቀጠሮው የዘገየው ምሳውን ሳይበላ ለመምጣት ስላልፈለገ እንደሆነ ከነገራት ምሳውን ማን እንደሰራለት አይነግራትም:: በተለይ እንጀራ ተጋግሮ ቃተኛ ካልበላ ቅር ይለዋል:: ስለበላው ቃተኛ አይነግራትም (ቢነግራት፡ 'እኛ ከትፎ እንፈልጋለን ደርግ ቃተኛ ያበላናል' ትለዋለች):: ቃተኛ እንደሚወድ አይነግራትም:: መንገሩ አሳፍሮት አይደለም፤ ከእናቱ ከቀለመወርቅ የጤፍ እንጀራ ቃተኛ የሚስተካከል ምን 'ፉድ'[78] አለ? በደንብ ዕንቅልፍ እንዳልተኛ ሲነግራት ('ዘመኑ የሚያስተኛ አይደለም እኮ' ትለዋለች) እናቱ ቅዝተኛ ስለሆነች ዕንቅልፍ አልወስድ ሲላት በሌሊት ተነስታ መብራት እያበራች ምግብ እየሠራች ዕቃ እያነካካች እንደምትረብሸው አይነግራትም (ቢላት፡ ደርግ 'እናቶቻችንንም ነጀሰብን' ትለዋለች):: ያለፈው ነገር በትክክል አያረካውም:: በትንሽ፣ ተርታ በሆነች ግን ለምለም ነፍሱን ባጠፋችው የጡጦ ለግላጊዎች ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ እስር የተከተተው በሙሉ ችሎታውና በሙሉ ልቡ በመሳተፉ ነበር:: ታዲያ ታስሮ ሲፈታ የተረዳው አንድ እውነት ድርጊቱና ዕውቀቱ ተመጣጣኝ ያልነበሩ መሆናቸው ነው:: ከዕውቀቱ ይልቅ ተሳታፊነቱ ከባድ ነበር:: (ኢንተለጀንስ[79] ሲሰራ እንዲሰልለው የታዘዘው ሰው የት ሆቴል እንደሚበላ፣ የት ቡና እንደሚጠጣ፣ ምን ዓይነት ኬክ እንደሚወድ፣ ስንት ደቂቃ እየበላ እንደሚቆይ፣ ከየትኛዋ ሴት ጓደኛው ጋር በብዛት እንደሚውል፣ የቁን ቦታ እንደሚያዘወትር በመሰለሉ፤ ይኼም መረጃ ተቀናብሮ ተልኮ በቦክሰኛ ኬክ መርዝ ተሰጥቶት እንደ ሞተ ሰምቶአል፤ ያውም በጣም በኋላ) ዛሬ ምሳውን ምን እንደበላ ሲጠየቅ ለመናገር ደስተኛ አይደለም:: 'የተገኘውን በላሁ' ሲል መናገር ተሰላችቶ አይደለም:: የተረዳው ነገር፣ አፉን አውጥቶ ለማንም ባይናገረውም ትንንሽ የራሱ ዕውቀቶች፣ ለራሱ ብቻ የሚሆኑ፣ ከማንም የማይጋራቸው እዚህ ደረቱ ስር ማስቀረት እንደሚያስፈልገው ነው:: ትንንሽ ልምዶች ይሁኑ ትልልቅ የራሱ ብቻ ናቸውና ከሰው ዕይታና ጆሮ መደበቅ እንዳለባቸው ነው:: አንዳንድ

78 food= ምግብ(እንግሊዘኛ)(አ)

79 ስለላ

ዕውቀት እንደዛ ነው......

ትናንት ብዙ ገንዘብ ኖሮት ዛሬ ግን 'የለኝም' ሲላት ምክንያቱን እንዲህ ነው ብሎ አይነግራትም:: እህቱ ታማ ለሆስፒታል ያለውን ገንዘብ በሙሉ በመክፈሉ እንደሆነ አይነግራትም (ቢላት: 'ደርግ ከእስር ቤት የተረፈውን ወጣት በበሽታ እየጨረሰው ነው' ትለዋለች)::

ዛሬ ገንዘብ ይዞ አይታው በበኑጋታው:

'ካሌብዬ ሐብል ግዛልኝ' (ሌላም ነገር ሊሆን ይችላል) ስትለው

'የለኝም' ሲላት ምክንያቱን እንዲህ ነው ብሎ ዘርዝሮ አይነግራትም::

'ይኼኔ ያቺ ማናት......እሷ ብትሆን......' ትለዋለች:

'ያቺ' 'እሷ' ከእስር ቤት በፊት የሚያውቃት የመጀመሪያ ወዳጁ ከዐሰል[80] የተፈለፈለች የምትመስል አደሬ ልጅ ናት:: ወደ መርካቶ የቅመምና የቅራቅንበ ሱቋ ስትንዝ ከኋላዋ ወለላ እየተንጠባጠበ የሚቀር፣ የሐረር ነጋዴና የድሬዳዋ ተማሪ አረንጓዴ ምላሱን ጎልጉሎ የሚከተላት ዱብራ:: ያቺን የመሰለች ልጅ ይተዋታል ብላ ስለማታምን ለማወዳደሪያና ለማስደንገጫ ሰብለ ስሟን በአፏ ነክሳ ይዛለች......ሲበዛባትና ሲመቻት ልትተፋበት:: ግን ስሟን አትነግረውም:: አንደኛ ስሟ ያምራል ከ 'ሰብለ' ያምራል:: እንደገና ቅናት አለች--በምትንቀጠቀጥ ፈገግታ በጥማም ጃፓኒ ሹራቧ ከጡቶቿ ስር ከካሌብም ከማንም የምትደብቃት:: ለእሱ ግን የሐሊብ መቅረት ታሪኩ ቀላል ነው:: አባቷ 'የትም ለማይደርስ ፍቅር አትልፋ ክርስቲያን ነህ አንተ' ብለውት ነው:: ፊት ለፊት በማዘን ነው የነገሩት:: ፊት ለፊት 'ና ልጄ ተቀመጥ......ተቀመጥ' ብለው 'ይኸቺን ሳንቡሳ እየበላህ፣ በሻይ ትጣፍጣለች' እያሉ፣ ሰንደልና ዕጣን የሚሸት ቀኝ እጃቸውን ትከሻው ላይ ጣል አድርገው፣ 'ሐሊብን እርሳት' ያሉት:: በአደናጋሪ መልክ አባቷን በግልፅነታቸው ይወዳቸዋል::

እስር ቤት ብርድ ልብስ የጋረደው ሲሚንቶ ላይ ተጋድሞ ሐሊብ በሕልሙ ስንቴ ነው ለጎኑ ሙቀት ያመጣችለት......በእስኪቷም ላንቃ በልታው የሄደች......

......ሰብለ ስትነዘንዘው ከሸውሻዋነቷ፣ ከእሾህ አፏ ሊገላገል ሲሰደድ ሚስት ሊያደርጋት አይቻል እንጂ ወደ ሐሊብ ነው:: በድብቅ መርካቶ ሱቋ ሄዶ በዝምታ አቅፎ ፊቱን አንገቷ ስር ቀብሮ ወደ ውስጥ የሚተክዘው[81] ሐሊብ ደረት

---

80 ማር

81 በጎዳና ዕውቀት ሁለት ዓይነት ትክዛዎች አሉ ይባላል:: የሚያስጠማና የማያስጠማ:: የሚያስጠማው 'ወደ ውጭ' ነው፣ በለቅሶና በእዬዬ የሚከሰተው:: የማያስጠማው 'ወደ ውስጥ' ነው:: ይኼም እንዲህ ነው:......ሐሊብ ታቅፈውና ዓይኖቿን ጨፍና አንገቱ ላይ ተዘልሳ 'አባቴ እንዳይመጣብን' እያለች ጀርባውን እየዳበሰች አቅፋው ዝም ትላለች:: 'ለምን መጣህ?' ብላ ብትጠይቀውም አይነግራትም:: ስለዚህ አትጠይቀውም:: እስኪደክማት ወይ ለቋት እስኪቀመጥ ወይ እንግዳ እስከሚረብሻቸው አቅፋው ትቆያለች:: ይኼ ወደ ውስጥ ነው:: ሁለመናውን ሲተነፍስ ስትሰማው ሞላ አንጀቷ በስቃይ ትላወሳለች:: ማሕፀኗ ይነዳል:: በድብቅ የሆነ ዱር ሄዳ ምኑም ባይገባትም ሺህ ልጆች ብትወልድለት ትፈልጋለች...... በጨዋታ በጨዋታ ዛሬ 'በልጅነቴ' ብላ ስትል ሀሊብ ደምቆ ትዝ የሚላት ከሥለቱ

ላይ ነው......እዛም ነው እሷና እሱ ብቻ እንዲሰሙት የሚያማምሩ ፍሬ የሌላቸው ነገራት እያትመሰመሰ የሚነግራት እያድበሰበሰች የምትነግረው......'ሐሊብዬ' 'የእኔ ዓይናማ' ቢከለከልም ሌላ ጉዳይ ስልምልምታ ከከፈተው አፏ በተጸከሙ ከንፈሮቹ፣ ብርታትን እንደ ዘምዘም ይመጣል......

......ያልጠፋ የፍቅርዋን ናርዶስ ይታጠናል......

የአዲስ አባን ሶብይ ምን ትዛዛት ያቆሙታል?

ቆስሎና ተዳክሞ ያረፈባት ናት ሰብለ:: ለእሱ የይሉኝታ ጋሪ የምትነዳ የአንድ ቀውጢ ዘመን ፍጡር መሆኗ ነው......

ይኼን ያው እንደ ሌላ ልምዱ ለሰብለ አይነግራትም::

«ኸረ ሐሊብ ጓደኛዬ ናት:: ዘመዶቼ ናቸው ቤተሰቦቿ፣ ይልቁን እሁድ እንገናኝ እዛ ቦታ እንሄዳለን» ይላታል

«ተው እባክህ ካሌብ እስከዚህ ቂል አደረከኝ»

(መባል የማይገባውን ትላለች)

እንግዲህ እንዲህ የምትለው አርብ ዕለት ማታ ነው......

## ቅዳሜ ከሰዐት በኋላ

ካሌብ መኖሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ከቤቱ ፊት ለፊት ሳሩ ያለቀ መሬት መሃል በእርጅና ጥቁር የሆነ ኩርሲ ላይ ተቀምጧል:: ፊት ለፊቱ ያለው የኮረኮንች መሬት ላይ የስሌን አንሶላ ተዘርግቶ ቃሪያ ተሰጥቶበታል::

«ቃሪያውን እይልኝ የሠፈር ዶሮ እንዳይጭረው» ብላው እናቱ ቀለመወርቅ ፀሐይ እንዳይጎዳት ከራሷ በላይ ባለ አበባ የቀጭኔ ዣንጥላ ፏ አድርጋ መርካቶ ከሄደች ቆየች:: እህቱ ኮረሪማ ጋቢ ተከናንባ ፊት ለፊት በረንዳ ላይ ሽራ አልጋ ዘርግታ ከወፍ በሽታዋ እያገገመች ጋደም ብላለች:: ፊት ለፊቷም ትንሽ የእንጨት ጠረጴዛ ላይ ውሐ በፕላስቲክ ኩባያ ተቀምጦላት አልፎ አልፎ ያን እያነሳች በትጋት ትመጣለች:: እሱ በግራ እጁ የደራሲ ገጻም ማርታን *የጠፋ ቀለበት* የተሰኘ ልብ ወለድ ባመልካች ጣቱ አልቦ ይዟል::

«እንዴት ነው?» አላት እህቱን ምናልባት ለስድስተኛ ጊዜ

«ትንሽ ተሽሎኛል»

ከዚያ ትንሽ ያነብና ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ተጋደመችበት ሔዶ ከነጋቢዋ አቅፎ ሳም ሳም አድርጌ፡ 'አይዞሽ' ሊላት ይዳዳዋል:: ግን ከተቀመጠበት መነሳት አልፈለገም:: እሷም ደ'ሞ መንከባከብ ሲበዛባት ትነጫነጭ ይሆናል:: ከዚያ እሱም እሷም ከሚመቻቸው ዕርቀት 'ታዲያስ' ይላታል:: በተሰላቸ

---

ሸብሮች ተርፎ በአገር አማን ቀን በመላጣ እናቱ ሱቋ ደፍ ላይ መጥቶ ሲቆም የሆነችውን ነው:: እዛ ከስቶ ሌላ ሰው መስሎ የቆመው እሱ መሆኑን እንዳወቀች ምንም ሳትናገር እተቀመጠችበት ሻልዋን እንደ ተከናነበች በለቅሶ ተርገፈገፈች:: አስራ ስድስት አልሞላትም ያኔ::

መልከ እሷም 'ትንሽ ተሽሎኛል ደህና ነኝ አሁን':: ከዚያ ስለ ሐሊብ ያስባል:: በአእምሮው ውስጥ ይኼን ቅብብሎሽ ሲሰራ ነፍሱ ትረጋጋለች፣ እንደሚጣፍጥ ሕልም ያረካዋል:: የሰብለን ከንፈር የሐሊብን ሚስጢራዊነት......ከዚያ የሰብለን እግሮች (አወይ ጥንካሬ፣ ወፌላላ ያላደከመው)......የሐሊብን ቡናማ ሐር (እሱን ለብሶ ስለ ጀጎል ማለም)......ከዚያ የሰብለ ምላስ (መለፍለፍ ሲወድ በተለይ ደርግን መስደብ)......ከዚያ እንደ ስኳር ኳስ የሚነክሱትን የሐሊብ በረዶማ ጥርሶች (በርጫ አድርጊኝ)......የሰብለ ወገብ (እንደ ቀንድ ዋንጫ ሰንደቅ)......የሐሊብ ዳሌ(ድንገት እንዲያ በልጅነታቸው ሲተማተሙ እንደ አፈር ሐውልት ቢፈርሱስ?)......የሐሊብ የቅመም ሱቅ......የገዳምን መፅሐፍ በአመልካች ጣቱ እንዳለበ......እሷን ቀይ ዳማ ሐሊብን ሲሸጡ የተንጠለጠሉ የቅመማ ቅመም ብልቃጦች፣ ዣንጥላዎች፣ ቅሎች፣ ኮሮጆዎች፣ ቀሚሶች፣ ሱቲዎቿና ላክስ ሳሙናዎች፣ ሰንደሎችና የወይራ እንጨቶች መሐል መጀመሪያ የሳማት('ታዲያስ!')......አረንጓዴውን ሰሌዳ የስትራክቸር አስተማሪው በፎርሙላ ሞልቶ እሱን ትኩር አድርጎ ካየ በኋላ...... ወደ ተማሪዎቹ ዞር ብሎ 'ከሴት ጓደኛዬ ያምራል' ብሎ ያለው *ሃሃሃ*...... የእህቱ ዓይኖች......('ታዲያስ!') እዛ ጋ ድልህና አፍርንጅ መስሪያ ቃሪያ...... *እናቴ ቀለመወርቅ በየሳምንቱ ለምን መርካቶ?* የሐሊብ እርጥብ ከንፈሮች...... የልጃገረድነቷን ጀጎል ያፈረሰበት የሸበላ ዕድሜአቸው ሰንበት......በተከፈተ መስኮት የወርቅ መረባ የመሰለ ሰማይ ሲያዩ......ለአንድ ሰዐት ተቃቅፈው ሳይነቃነቁ ቀኝ ለግራ እጅ ተያይዘው ነበር......አባቷ ሱቃቸው መስስ ብለው ሲገቡ......ሐረር ተሰዳ የላከችለት ፎቶ......*ልባችንን የሚያቆስለው ብዛቱ*...... ምን ነበር ከፎቶው ጀርባ? በሰማያዊ ጭቃ ቀለም በርክርክ ሊወድቁ በሚቃጡ ሆሄያት: 'ብሞትም አልረሳህ የእኔ አይናማ'......ፎቶውን ከፎቶ ስር ከሌላ ፎቶ ስር ደ'ሞ ከሌላ ፎቶ ስር ፍቅር እንደ መቅበር......ማንም እንዳያየው......

*ምነው ዘገየች እማማ*......(ታዲያስ!)

መፅሐፍ ያለበበት ጣቱ መንታ ሰንበር እያወጣ......

ታሪክ ሐይለኛ ነው::

ይዘቱንም ይሁን የይዘቱን ሐይለኛነት አይናገረውም::

«ምን ታስባለህ?» አለች እህቱ

«እ......እዚህ ልብ ወለድ ውስጥ ስለአለችው ባለታሪክ» ዋሻት::

«ደራሲው ገዳም እኮ እዚህ ሰፈር ያለው ነው»

«ማን ነገረሽ?......እንዴ? ይሄ የማርታ ባለቤት? አትይኝም?»

«አዎ»

«እም......»

«ምነው?»

«ምንም:: ደራሲ መሆኑን አላውቅም ነበር:: ደ'ሞ የአባቱ ስም ማርታ ነው እንዴ?»

«የሚስቱን ስም ነዋ! የብዕር ስም ዐይነት......»

«አባቱ እንዳይገሉት»

«ሂሂሂ......አንተ ሲቪል ኤንጂኒየሪንግ ምናምን በል አርቱን ለእኔ ተወው......»

«ጉረኛ......»

«ሂሂሂ......ሁሁሁ»

ከተጋደመችበት እያማጠች ቀና ብላ ውሐ ጠጣች:: ዓይኖቿን ጨፍና የሚያስብ መሰለች:: የሕመሟን ቁርጠት ይሁን ውጋት እያዳመጠች እንደሆነ ይገባዋል::

ተነስቶ እህቱን ሊያቅፋት ፈለገ:: ተነስቶ አቅፎ ያላባቸው ቅንድቦቿን ሊስም ፈለገ:: ያውቃል ከራሱ የበለጠ እንደሚወዳት:: አንድ እህት ብቻ ናት፤ ወንድሙም ናት:: የሁለት ዓመት ታናሹ ብትሆንም ከባዕዳን ለከፋ እንደ ነብር ተከላክላዋለች:: ትናንት ጠዋት ሆስፒታል ተኝታ እስከ አንገቷ ብርድ ልብሷን አልብሷት ፊቷን እያየ ዓይኖቹ ዕንባ እንዳቀረሩ ለሦስት ሰዓቶች ያህል አልጋዋ ጎን ሳይነቃነቅ ስለ ልጅነቷ እያሰበ ቆሞአል:: ይኼን ለማንም አይነግርም:: በንፁህ ነጭ ጨርቅ ቋጥሮ አደረቱ የሆነ ጉድጓድ፣ የሆነ የልቡ ጉረቤት እሷን ለመውደዱ ምስክር ከሆኑ ሌሎች ድርጊቶች ጋር ደብቆ ያስቀምጠዋል::

ከገዳም ጋር በእድሜ ብዙ ቢራራቁም......ሲገናኙ እንደ ወዳጅ ይተራረባሉ.....ከተመቻቸውም ይገባበዛሉ......በዕድሜ ቢበልጠውም 'ይፎግረው' ነበር:: ሠፈር ከሕፃናት ልጆቹ ጋር ሲሮጥ የሚውል ደስተኛ የመሰለ ነበር:: መሿለኪያ አንድ ጊዜ ሴት ልጁን ገመድ ዝላይ መንገድ ዳር ሲያስተምር አይቶታል......ጊዜ አግኝቶ እንዴት ፃፈ?......ገዳምን ሌላ የማያውቀው ሰው አድርጉት ነበር......ለምን ታዲያ አንድ ጊዜ ራስ ሆቴል ሲያገኘው ስላሳተመው መፅሐፍ አልነገረውም?

እንደ ገዳም ለድርሰት ባይደርሱም መረጃዎች እንዳሉት ያውቃል፣ ግን ሰብሰቧቸው አያውቅም:: ድርሰት እንዲሆኑ መረጃዎች መከፋፈል፣ መፈረጅ አለባቸው:: እሱ አእምሮ እልፍኝ ውስጥ ግን እነዚህ መረጃዎች በትንንሽ የስሜት ቀረጢቶች ታስረው በየቦታው ተበትነዋል......

......ያቺ ቋጠሮ የሐሊብ ዓይኖች ናቸው......አከዳደናቸው አስማታዊ ዓይነት ተንቀራፈው:: (ሐረር ስትሄድ እንዴት ነው ያለቀሱት? ሌላ ሌላ ነገር ረስቶ ስለ ልቅሶዋ ብቻ ሊፅፍ ይችላል?)

......ከንፈሮቿና ከንፈሮቹ ሲከደኑ የሚሆኑት:: (ከመሃላቸው ያለው የስኳር ሙጫ ሠራዊት ልቡን አስሮት የለ! የጥንት ፊውዳል ነገስታት ባላመኑበት ስልት ያለያየውን ባህል ሳይጠቅስ ስለ ሀሊብ ሊፅፍ ይችላል?)

......ያ ቋጠሮ የጠራ ያዲስ አባ ሰማይ ነው፣ ሰማዩ እንዲህ ለምን ጠራ? ጥያቄ:: ወደር የሌላት ስብቅል ከተማዩ:: (ያለፈበትን መከራ ብቻ

ሳይሆን ስለፈጠረው መከራ ሳይጠቅስ ስለ አዲስ አባ መፃፍ ይችላል? የገደለም የተገደለም ሁሉ የእግዜር ፍጡር አይደል?)

......ያቺ ቋጠሮ 'ለምንድነው ሰብለ የምትነዘንዘኝ?' ናት:: (እየነዘነዘችው ሳለ እየነዘነዘችው አዳምና ሔዋን ሲሆኑ ግን ሁልጊዜ ለምንድነው ጥርሶቿ አንገቱን እየነከሱ የሚያቆስሉት?)

......ያቺ ቋጠሮ......ባዶ ናት:: ምን ሊያስቀምጥባት ነበር? (መርሳት አይፈቀድለትም:: ከረሳ መፃፍ የለበትም:: ያስገደለው ሰውዬ ሚስት ማማሯ እንዳያመልጣቸው ከአንድ ፖፖላሬ ከሚኖር ጎረምሳ ሽርካቸው ጋር አስተዋወቋት:: ከባሏ ገዳይ ሳታውቅ ልጅ ወልዳ አሁን አንዳንዴ ሜክሲኮ አደባባይ ያያታል:: የውሸት ወዳጅ ሆኖ ያስወለዳት ጎረምሳ የበቀል ስሜት ይኑራት አይኑራት ከሰለላት በኋላ ተዋት:: ቢፅፍ ይሄን መከሰት ይፈቀድለታል?)

......ያ ቋጠሮ እስር ቤት ነው:: በቀይ ሽብር ኩርኩም የደቃው:: ኮሚኒስት ነኝ ብሎ በመሰል ኮሚኒስት የተቀጣበት:: እሱ ቋጠሮ ዙሪያ የተዘጋ ዚፕ ነው— መዳቡ የሚያበራ (የተሰራበትን ብቻ ሳይሆን የሰራባቸውን መቼ ነው የሚፅፈው? ለምን ይፈራል?)::

......እዛ ጋ ያለች ቋጠሮ የሞራ መረብ የተደገፈች 'ምን ባደርጋት ይሻላል ሰብለን?' ናት ከስሯ ማጭድ የመሰለ የጥያቄ ምልክት እያንቀላፋ:: ነፋስ ደ'ሞ አለ አእምሮው ውስጥ......ቀዝቃዛ ነፋስ......ሁሉን ሸፋፍኖ እንደ ብሉኬት አድርቆ የያዘ::

## ቀልሽ/ቀልዬ

እናቱ ቀለመወርቅ ልጅ እግር ሳይዳ ናት:: ምናልባት አርባ አምስት ቢሆናት ግን ወጣት የምትመስል:: ጥቁረቱ የጠራ፣ ሽበት ጠብ ያላለበት ባለስድስት ረድፍ ጉንጉን አላት:: ክንዷ ትልቅና ቀይ ነው:: ፊቷ ከፀሐይ ይሁን ከኑሮዋ ይዘት በመጠኑ ጠቆር ብሏል:: አፍንጫዋ ጫፍ ላይ ጥቁር ላስቲክ የመሰለ ማድያት አለ:: አቋቋመ መልካም ገና እንዲህ ሲያይዋት የምታስደንግጥ ሙሉ ሴት ናት:: ከመርካቶ እንደ መጣች የገዛችውን አስቤዛ ቤት ውስጥ ወርውራ ሴት ልጇን አፏ ላይ ስማ የወንድ ልጇን እናት ዳበስ ዳበስ አድርጋ ወደ አቀደችው ስራዋ ተመለሰች:: የተሰጣውን ቃሪያ አገላብጣ ከመሐል ያመለጣት አንዳንዱን እያነሳች ቀነጣጠሰች:: በዝምታ እቤት ገብታ ሙቀጫ ከነዘነዘናው አምጥታ ስጠው ጉን አስቀመጠች:: እናቱን ሳርማ መሬት ላይ አስተካክላ ለማቆም ትንሽ ለፋችና ቀና ብላ ወንድ ልጇን እንዳላለቀ የእጅ ስራ በዓይነ ውሃዋ አገላብጣ አየችው:: ፈገግ ብሎ አያት:: ሰብለ አንድ ቀን ስለ እናትና አባቷ የልጅነት ፍቅር ያወራችው ትንሽ ነገር ትዝ አለው::......ዛሬ ከፊሉን ረስቶታል:: አንዳንዴ እናቱን ስለ ወጣትነት ጊዜ ፍቅሯ በዝርዝር ለመጠየቅ ያስብና ይረሳዋል:: ይዘነጋዋል:: ወይም ከመሐል የመጠየቅ ፍላጎቱን የሚቃረን ሀሳብ በአእምሮው ይነግሳል:: አሁን 'ተደብሯልና' ሊሞክር ፈለገ፡

«ስሚ እማማ ከአባባ ጋር እንዴት ተዋወቃችሁ?» ፈገግ ብሎ

ደዌዋ ያደከማት የመሰለችው ኮረሪማ ዓይኖቿን በቀስታ ከፈተች......ዞር ብላ አየችው:: ከንፈሮቿ ላይ የመገረም ፈገግታ አለ::

«ት/ቤት......ምነው?» አለች ቀለመ ወርቅ

«ለማወቅ......ትንሽ ብትነግሪኝ ደስ ይለኛል»

«ምን ያደርግልሃል?» መውቀሟን አቁማ አየችው......

«እንዴት? ምናለበት ብጠይቅሽ? ባውቅ»

«ልምድ ለመቅሰም» አለች እህቴ በማሾፍ

«እንዴት? የእኔ ልምድ ለአንተ ይሆናል?» አለች እናት

«ምናለበት?»

«የሴት ልምድ ለሴት ነው»

«ልምድ ፆታ አለው?» አለች እህቴ

«የሴት ልምድ አለ፣ የወንድ ልምድ አለ»

«እሱ የያዝከው መፅሐፍ ወላጆቻችሁን ጠይቁ ይላል?» አለች እህቴ በማሾፍ::

«አንቺ ዝም ብለሽ ስሚ፣ ታመሻል»

እህቴ ለመሣቅ ሞከረች::

«የት ነበር የምትማሩት?»

«እሱንም አታውቅም? ቀ.ኃ.ሥ»

«አንድ ክፍል?» እህቴ

«ጉበዝ ተማሪ ነበር?» እሱ

«አንድ ክፍል:: እኔ ጎበዝ ነበርኩ ከእሱ:: ደስ የሚል ቀጫጫ ነበር:: አካሔዱ ራሱ ሌላ ነበር፡ ጆን ዌይን ምናምን እንደሚባሉት ካው ቦዮች እ?» ዘነዘናዋን መሬት በቀስታ አጋድማ እንደ ባሏ የወጣትነቱ ጊዜ ለመራመድ እየሞከረች:: ሴት ልጇ ሳቀች::

«ረዥም፣ ቀይ፣ ቆንጆ ሰልካካ ነው:: ፀጉሩ ከርዳዳ ነው:: እና ያን ጊዜ ከርዳዳ ፀጉር ለመክፈል በመቀስ ወይ በምላጭ ተላጭተህ ቦይ ታበጃለህ......ባለ ቦይ ነበር»

«ምን አስጨነቃችሁ? እስከዚህ»

«ጊዜው ነዋ ምናባቱ» አለች እህቴ

«በጣም አፍረው ነበር:: በልቤ አላፍረውም፣ ግን አፍራለሁ፣ እሽኰረ መማለሁ ሂሂሂ......» ዘነዘናዋን ከጣለችበት አነሳችው::

«ዛሬም አለ እሱስ»

«አለ ዛሬ? እንጃ:: ይሽኰረመማሉ ግን ቶሎ ይሰጡሃል ሃሃሃሃሃ»

«እማማ!!!» አለች ልጅቷ በመቆጣት

«የዘመኑን ባሕል ነው የምነግራችሁ......ቃላቴን ማረም ባለመቻሌ ይቅርታ.....»

ልጅቷ በጀርባዋ ከተንጋለለችበት ቀና ብላ ውሐዋን ተጐነጨች::

«ያን ጊዜ መሽኮርመም በሽ በሽ ነው:: በአብዛኛው ከውስጥ የመጣ ማፈር ነው:: መልካም ኪነት ማለት ነው:: አሁን ያለው መሽኰርመም እንደሚመስለኝ ቴክኒክ ነው:: መሳብያ ወጥመድ ነው:: የውሸት ዕርቀት የመፍጠር ዓይነት...... ምን ልበልህ......»

«እና አስቸገረሽዋላ!»

«በመጠኑ:: ግን አንጀቱ አልነበረኝም:: ክፍል ሲገባ ደብተሩን ዴስክ ላይ አጣጣሉ::(ባዶ እጇን እንደ ቲያትር አየር ውስጥ እየወነጨፈች ፈገግ አለች) ከዛ እንደቆመ በመጀነን ከዳር እስከዳር ሁላችንንም ያያል:: እና ስንጋባ ሰለሞን ሚዜው ነበር:: ሰለሞን የሚባል ልጅ ነበር:: አሁን ከቀይ ሽብር አምልጦ አሜሪካ ነው የሚኖረው......'ታዲያስ ሰሌዋ ጠፋህዋ' ይላል:: ሰለሞን ደ'ሞ 'አርፈህ ተቀመጥ......ጋረድከን......ቀውላላ' ይለዋል:: ጣቱን እያወዛወዘ ከንፈሩን ነክሶ ይቀመጣል:: ልፊአቸው ደ'ሞ እይይይ ይበጠብጠናል:: ከተላፉ ክፍሉን ዘበራርቀው የማይጮህባቸው የለም:: ሁሉ ይጮህባቸዋል:: ጨዋታ በጣም ይወድ ነበር:: ከሁሉ የሚስቡኝ ጥርሶቹ ነበሩ:: በቆሎ የሚመስሉ ጥርሶች ነበሩት:: ታዲያ ተላፍቶም ይሁን ተላክፎ ብቻ ያላየ መስሎ በጎን አይቶኝ ይቀመጣል»

«እንቺስ?»

«ውድድ አድርጌዋለሁ ግን 'አታስበላም' ነው የሚባለው? እንተዋወቃለን ......በዓይን አየህ......ትንሽ መከጃጀል አለ:: ሁለታችንም ይገባናል»

«እሱም ዓይነ አፋር ነበር እ?»

«ሌሎች ጋ ክፍል ውስጥ ደረቅ ነው:: እኔ ጋ ሲደርስ ይለወጣል:: ይኼንንም አውቃለሁ:: አዎ ያኔ ብዙ ነገር ያስፈራል:: ያን ጊዜ ይኼ ዓይነት ነገር ከተጀመረ ትምህርታችን የሚበላሽ ይመስለናል:: ቤተሰባችንን እንፈራለን:: አስተማሪን እንፈራለን:: ራሱ የክፍላችንን ተማሪ እናፍራለን:: ትምህርት ቤት መማሪያ ብቻ ይመስለናል አየህ:: ዛሬ የተለየ ነው:: አብዮቱ ይመስለኛል ድርቅናን ከመንቃት ጋ ያስተካከለው:: ምንም የአለም ፖለቲካ የማይገባው ሁሉ መንግስት ግልበጣ ሴራና ትግል ላይ በድርቅናና በ'ትችልበታለህ' በመሳተፉ አሪፍ የሆነ መሰለው፣ እናም ፈጣጣነት ማሕበራዊ ሆነ:: ማለት መንግስት መቃወም የቻልክ ደረቅ እንዴት አንዲት ቆንጆ መልከፍ ያቅትሃል አይነት መሰለኝ:: ዛሬ ግን መጀመሪያ ትገባበዛላችሁ:: ከዚያ ከሆነ ትማራላችሁ:: የእኛ ጊዜ ትንሽ ኰስተር ያልን ነበርን፣ በኋላ እስኪበላሽ:: ታዲያ ይኼ የመግደርደርና የመፍራት ግጭት ያሰቃየናል:: ግን የሆነ ዓይነት ዕውቀት ይወጣዋል:: የምትወደውን ልጅ ሰርቀህ ማየት እንዴት ደስ እንደሚል:: የሚያም ጣፋጭነት ነበረው......ያው

በኋላ ቀስ በቀስ ተዋወቅን:: እሱ የሚኖረው ዘነበ ወርቅ ት/ቤት አካባቢ ነበር:: እኔ የምኖረው ሺህ ሰማንያ አካባቢ ነበር:: ብቻ......»

«ማን አነጋገረ መጀመሪያ?»

«ቲያትር አብረን ሰራን:: የሼክስፒርን ሮሚዮና ዡልየት:: እኔ የዡልየትን ደንገጡር እሱ ደ'ሞ ማንን ነበር......በቲያትር ውስጥ ተነጋገርን:: ተረበኛ ገደለን:: ሮሚዮና ዡልዬትን እንሰራለን ብለው ሮሚዮና ዡልዬትን ሆነው መጡ እያሉ......ሂ ሂ ሂ......እናደድ ነበር እንዲህ ሲሉኝ»

«አሁንም እንደዚያው ነው እኮ»

«አሁንም የለም ማለቴ አይደለም:: ግን እንደ ማየውና እንደ ምሰማው ከሆነ......ተወው:: ገንዘብ አለው ከመሃሉ......ሁልጊዜ መጋበዝ አለብህ:: ግን አየህ ማህበራዊ እሴትና ግላዊ እሴት አለ:: ሁለቱ ይጋጫሉ:: ከወንድ የሚጠበቅ ነገር አለ አሉ:: መጋበዝ፣ ጌጥ መግዛት፣ ምናምን የመሰለ:: ያን ጊዜ ብዙ ሴቶች የለንም ክፍል ውስጥ:: ወንዶች ይሻሙብናል:: 'እሷ ግልፅ አድርጋለች' እባል ነበር:: እንዲህ ሲሉ ሳፍር:: እኔ አባታችሁን 'ጋብዘኝ' ብዬው አላውቅም:: አፍራለሁ:: በፍፁም እሱን ነበር የምፈልገው:: የሆነ ነገር ግዛልኝ ብዬው አስቸግሬው አላውቅም:: መሐላችን ዕቃና ገንዘብ እንዲገባብን እንዲያደፈርሰው አልፈልግም:: እስከዛሬ እንደዚሁ ነው»

«ሁለቱስ አይሆንም?»

«መጥፎ አይደለም ግን ሀሳብ አለዋ:: አየህ......ይመስለኛል ልግዛላት አልግዛላት ሀሳብ ነው:: የገዛሁላትን ትወደዋለች? አትወደውም ይሆን? አንዳንዴ ትዝ ይለኛል ዳቦ ቆሎ ቤት ከተሰራ እወስድለት ነበር:: ስወስድለት ግን ለክፍሉ ሁሉ የወሰድኩ እንዲመስል አድርጌ ነበር ሂሂሂ......:: ግን ብዙው ለእሱ ነው:: እና በኪሱ ዳቦ ቆሎዬን ከቶ ከሩቅ ከጓደኞቹ ጋ እያወራ በስሜት ሲበላ ሳይ እንዴት ደስ እንደሚለኝ:: አብረህ ማጥናት፣ እሱ ሲከፋ መከፋት፣ ስሙ ሲጠራ መደንገጥ፣ ፈተና ሲከብደው መጨነቅ፣ ሲሳሳት ትንሽ አጣፍጠን እንዲያምር አድርገን መቆጣት ግብታዊ ነው የሚባለው?......ለሴት ልጅ ያ ዘመን ከባድ ነበር:: እናቴን ቤት ውስጥ እረዳለሁ:: ትልቁ ወንድሜ ሚቹ ፍቅረሥላሴ ልብሱን አያጥብም ነበር እኔ አጥብለታለሁ......የማጥኛ ጊዜህን ሁሉ ይሻማሃል:: አንዳንዴ አባታችሁን ብቻ የማስብበት ጊዜ ነበር:: ያ ያስፈራሃል:: አባታችሁ ችግሬ ይገባዋል:: ከሰዓት በኋላ እንደ አሁኑ ሺፍት አልነበረም:: በምሳ ሰዓት ልጆች ምሳ ለመብላት ሲወጡ አንዱ ክፍል ወደ ኋላ ቀርተን የምንሰራውን እንሰራለን:: አስር ሰዓት ላይ ደ'ሞ......ትምህርት የሚያልቀው በዛ አካባቢ ነበር ቤቴ ከመሄዴ በፊት ትምህርት እንዳለቀ ወደ ኋላ ቀርተን ያልሰራነው ቤት ሥራ ካለን አብረን እንሰራለን:: የምናወራው ካለ እናወራለን»

«አሃ!! ማዘር»

«ሌላ ነገር የለም......»

«ታዲያ......ይደብራላ......ሃሃሃ»

«እንደ አመለካከትህ ነው:: ድሮ ካልኩለስ ሰርተን ስለ ሴክስ፣ ስለ ወሲብ ስለገባችን ምንም አናውቅም:: ዛሬ አራት መደብ ሳትጨርሱ ስለ ሴክስ ስለ ፔሬድ[82] ታውቃላችሁ:: ግን ደ'ሞ በአባለዘር በሽታ ትታመማላችሁ:: የዞረባችሁ ናችሁ:: የአትኩሮት ጉዳይ ይመስለኛል:: ደስታ የሚሰጥህ ሕልም ምንድነው? በሕልምህ ትደሰታለህ ወይ?......አየህ? ፍቅር የግል ቢሆን......ያ የግል ሕልም የተስተካከለ ነው?»

«እኔ የምለው ዲግሪ አለሽ ግን እዚህ በርበሬ ትወቅጪያለሽ ለምን ትክክለኛ ስራ በተማርሽበት አትሰሪም ነበር?»

«ይኼ ትክክለኛ አይደለም እንዴ? ልጆቼን ማሳደግ ትክክል አይደለም? እናንተን ማን ያሳድግ? በላይ በላዩ ወለድኩ......ሁሁ ያስቆጠርኩህ እኔ ነኝ፡ ኤቢሲዲህንም::......ስርቼአለሁ በተማርኩበት ግን አላስደሰተኝም:: ከማጀት ወደ አደባባይ ሲሉ እኔ ገልብጬ ከአደባባይ ወደ ማድቤት ሂሂ......»

እዚህ ላይ ለአፍታ መናገሯን አቆመች:: መቀጠል አልፈለገችም:: ወይም የአቀማጠሟን ስልትና የጨዋታዋን ይዘት ለመለወጥ እንዳሰበች ሁሉ::

«ልጆቼን ለገረድ......ሰራተኛ ነው የሚባለው ዛሬ?......ለሰራተኛ አልሰጥም:: አንድ ወር ትቼአችሁ ስሔድ ስራ ቦታዬ ላይ ሳለቅስ እውላለሁ:: ጡቴ በወተት ሞልቶ ሽንት ቤት እየገባሁ ፊት መታጠቢያ ላይ እሱን ሳፈስ ሳልብ እውላለሁ......ልጅ እያለህ ታሳዝን ነበር:: አሁን ጉራዳ ሆንክ እንጂ» የውሽቷን ሳቅ አለች......

የሆነ የቅደም ተከተል ስህተት ላለማረም ወይም ዝርዝር ለመሸሽ እየጣረች ነበር::

ፀጥታ::

አፉን ከፍቶ ሊውጣት የሚቁነጠነጥ ፀጥታ:: ይኼን እንደ መጅ የሚከብድ ፀጥታ በጎሪጥ ታየዋለች 'ሞኝህን ፈልግ ዓይነት' 'ተወኝ ገብቶኛል' ዓይነት:: ቃሪያ እየዘገነች በዝምታ ሙቀጫ ውስጥ ትከታለች:: ሙቀጫው ሲሞላ በፈገግታ በሚሰባበሩ ዓይኖቿ ካሌብን እያየች በቀስታ ቃሪያውን መሸክሸክ ጀመረች:: አሁን ልጇ መናገር ወይ መጠየቅ ቢያቆም ትወዳለች:: ወደ ምትሸሸው አንዳንድ ነገር......በጥያቄ እየጐተተ፣ በቀስታ እየነዳ በልጅነቱ ቅንነት ወደ ማትፈልገው የቁጭት ኩሬ ዳር እንዲወስዳት አልፈለገችም:: መረሳት የሚገባቸው ነገሮች አሉ:: በፍፁም መረሳት የሚገባቸው ነገሮች::

«ጓደኛዬ ሰብለ ምን ትመስልሻለች?»

ተንፈስ አለች:: ጥያቄው ከእሷ ስለራቀ::

ቀና ብላ አየችው፤ መናገር ፈልጋ ግን ራሷን ለማገት እንደምትጥር ያስታውቃል::

«ንገሪኝ»

---

82 period = የወር አበባ(እንግሊዘኛ)(አ)

«አንተ አብረሃት የምትውለው ያላወቅሃትን እኔ......»

«አንዳንድ ጊዜ መውደድ ከብዙ ግድፈት ይጋርደናል:: እናውቃለን አንድ ቀን ዘሎ እስኪገጨን እንደምንጠብቅ»

«ይኼንንም ካወቅህ!......ብልህ ነህ»

«ምን አልሽ?»

«ይኼንንም ካወቅህ......» መውቀጧን አቆመችና እየሳቀች አየችው:: ምን አሳቃት ዓይነት አያት

«እንደበተ ርቱዕ ናት?» አለችው

«ምን ማለትሽ ነው? መጥፎ ነው?»

«በዚህ ዕድሜዋ እንደበተ ርቱዕ ከሆነች የምታውቃቸው ነገሮች ጥቂት ናቸው ማለት ነው:: ስለዚህ እነሱኑ ደጋግማ ታወራለች:: ትውስታዎቿ በማነሳቸው፣ መረጃው በመጥበቡ መሽምደድ ትችላለህ ማለት ነው:: ይኸቺን በመቀመር ብሩህ ከመሰሉህ ሞላጫ ናቸው»

«መናገር መጥፎ ነው? ሰብለን እኩ ሞላጫ ነች እያልሻት ነው......»

«እንደበተ ርቱዕ መሆኗን አሁን ከአንተ መስማቴ ነው:: ብዙ አነጋግሬአት አላውቅም:: ትሸሸኛለች»

«ለምን ትሸሺሻለች?»

«ሴት ለሴት ይተዋወቃል»

«ለምን አትነግሪኝም ነበር?»

«አንተ ከተስማማችህ እኔ ምኔ ናት»

«አቀላጥፋ ስለምትናገር ብቻ ትጠራጠሪያታለሽ? ደ'ሞ የእኔ ችግር ያንቺ ችግር አይደለም እንዴ? እኔ ብደበር......»

«ትዝ ይልሃል ፖለቲካ ገብተህ ለነበረ ጊዜ ገና በልጅነትህ? አቀላጥፎ ተናጋሪ ነበርክ:: ብሩሕ ትመስል ነበር ግን ምንም አታውቅም:: ዛሬ የተሻለ ታውቃለህ፣ የተሻለ ይገባሃል ግን ትንተባተባለህ:: ብዙ ተፎካካሪ ሃሳቦች አእምሮህ ውስጥ ስላሉ ትክክለኛውን ለመምረጥ ጊዜ ስለሚወስድብህ ይሆናል»

«እንደዛ አስቤው አላውቅም» እንደ መተከዝ አለ:: ስለ ዱሮው ማሰብ አይፈልግም::

«የመናገር ችሎታ ውስጡ ብዙ ነገሮች አሉበት:: አንደኛው ስሜትህን መቆጣጠር ትችላለህ:: እንደ አክተር ነህ አየህ:: ስለዚህ ውሸት ወይም ዕውነት ትንገርህ አታውቅም......»

አባባሏ ሳበው፣ ይኼን ሰብለ ላይ ታዝቧል:: ችላ ብሎ አልፎታል እንጂ ......የምታምር ልጅ ስትዋሽ ምን ታደርጋለህ? እጇን እጅህ ላይ አስቀመጣ

ትናንት ያወቀችውን ዛሬ ብትረሳ፣ ዛሬ ያወቀችውን ነገ እንደምትረሳ ብትጠረጥር:: መርጠ ረሺ ማቆላመጥ ይደባልቅበትና ይሸውዳል:: እሱም ያደርገዋል:: ከመዋደድ ሥር እንደ ላስቲክ ስስ የሆነች፣ ግን ነጋ ጠባ በተለያዩ ገጠመኞች እየተፈተሸች የማትጠፋ ቅጥፈት አለች:: ሁሉ ያውቃታል:: ተራ ትመስላለች ግን በእነሱና በፍፁምነት መሐል ያለች ግድግዳ......ራስን የሚያስት ወሲብ እንኳን የማይበሳት:: ከቀናትና ከሰነባበተች እንደ ባልጩት የምትከር......

«ታዲያ......»

«በባልና ሚስት መሐል ስለሚፈጠሩ ብዙ አለመግባባቶች አይቼአለሁ:: ችላ የተባሉ ትንንሽ ነገሮች በጊዜ ዕርዝመት ያብጣሉ ወይም ልፍስፍስ የመሰሉን እየቆዩ ከባድ ይሆናሉ:: ዛሬ ትክክል የመሰለህ ነገር ነገ አይመስልህም:: የውሸቶችም ዓይነት ዓይነት አላቸው:: ከስማና የመሰሉት ሲጠራቀሙ ትልቅ ይሆናሉ:: ወይም ትልቁን ነገር ለመዋሸት መለማመጃ ይሆናሉ:: ወይ መፈተሻ..... ይነቃል? ወይስ አይነቃም? መፈተሻ ይሆናሉ:: እየህ እየነካካህ ተነቅቶብህ ወይ አልተነቃብህ እንደሆነ የምትመረምርባቸው:: ታቆላምጥሃለች?»

«አዎ......ታዲያስ»

«ማቆላመጥ መቼ ጀመረችህ?»

«እንጃ ምናልባት እስር ቤት ወይ ከተፈታን በኋላ እንጃ፣ አንቺ ትዝ ይልሻል? አንቺን ፋዘር[83] መቼ ነው 'ቀልዬ' ያለሽ?»

«ሂሂ......አሁን ትዝ አይለኝም......ሂሂ......ለመሆኑ አንዴ ታስርህ ከእኔ የበለጠ ትጠይቅህ የነበረችው የመርካቶ ልጅ አለች?»

«ሀሊብን? ምነው?»

«ሀሊብ ነው ስሟ? የት ጠፋች?»

«ተተካቻ!......ማዘር ሳይገባሽ ነው?» አለች እህቱ በፍጥነት

«ዝም በይ አንቺ የማታውቂውን»

«ለምን አላውቅም?......ፎቶዋን ሁሉ እኮ አ-ይ-ቼ-አ-ለ-ሁ» አለች እህቱ እየሳቀች

«ምናባቷን ዕቃዬ ውስጥ......»

«አያሳፍርም......»

ወደ እህቱ ሄዶ እንደ ጨዋታ ክንዷን ያዘና እንደ መቆንጠጥ ያዛት::

«አፈር ስሆን......አፈር ስሆን......»

ትቷት ወደ ነበረበት ተመለሰ:: ከሀሊብ መለያየቱ የእሱ ጥፋት ባይሆንም ለእናቱ ሊነግራት አልፈለገም:: የግሉ ውድቀት ይመስለዋል......መስለም ነበረበት:: ከሀሊብ ጋር ጀጎል ገብቶ......

---

83 አባቴ ለማለት(እንግሊዘኛ)(አ)

«ተወው አትንገረኝ ከቀረ ቀረ ነው......» ሊያብራራላት አልፈለገም:: ምን ይጠቅማል? ከአቆሙበት ለመቀጠል ቸኮለ:: ሁለቱም የሚሸሿቸው ነገሮች እንዳሉ አያውቁም:: ዘመን ራሱ የፍቅር እንቅፋት ሊሆን ይችላል::

ሲጠየቅ: 'መቼ?' ሲባል......

'በዚያ በእንቅፋት ዘመን'......

'በዚያ 'በሉ እንያችሁ፣ ተጣሉ፣ በርቱ ተኮራረፉ' በተባልንበት ዘመን'......

'ያ ዘመን......' የሚባል......

«እና ይሄ ያልሽው ማቆላመጥ......»

ምን ይበል?

«ቶሎ ላቆላምጥህ ካለችህ፣ ሳታውቅህ እንደሚያውቅ ሁሉ ከካበችህ ሽሽ»

«ትዝ አይለኝም......ለምን?»

«ቶሎ ማቆላመጥ ሽፋን ነው:: ምን ያስቆላምጣል?»

«መቼ እንዳቆላመጠችኝ ትዝ አይለኝም ግን ከ90 በመቶ ፍቅር ይልቅ ትንሽ ውሸት እንዴት ይከብዳል?»

«መጀመሪያ ፍቅር አለ ወይ? ብለህ ጠይቅ:: ካለ ውሸት የለም:: ውሸት ካለ እ......ፍቅር....እንጃ......»

እዛ የሚከብድ ፀጥታ ውስጥ ሳታስበው ገብታ ቆመች:: በተወሰኑ እሷ ብቻ በሚገባት አባባሎች የሚፈጠረው ማዕከሉ የወየበ፣ ገዋ ያነቀ፣ ከጠቆረ ሽጥ ሐተታና ኑዛዜን ሰንቅሮ 'እሙኝ' እያለ የሚያስፈራራ፣ ልትሸሸው የምትጥረው ትዝታዋ......

አይሰወር ነገር......

ከተኛበት ነጋሲ ዓይኖቹን ገልጦ አያት:: እሱም እንደማይነገር እሷም እንደማትናግረው ያውቃል:: ሁለት አስርታት የተኛ ነው:: አንገቷን ወደ ተከስከሰው በርበሬ ተከላ ዕንባዋ እንዲመጣ ጠበቀች......ዛሬ ቢያንስ ማመሃኛ አላት......

### ፀጥታ ነጋሲ......

ይኼ አብዛኛው የምንኖርበት አለም ፀጥታ ነው:: ያልተነገረለት ነው:: ሆሄ፣ ቃል፣ አንቀፅ፣ ምዕራፎች፣ ቅጻሴና ዘፈን፣ እንጉርጉሮና ምንትስ አልተነዳበትም የሚባል:: ምድር ላይ ከተሰሩና ከተደረጉ ከታሰቡና ከታለሙ ነገሮች የተመዘገበው ስንቱ ነው? የአዳም የመጀመሪያ ሳቁ ተመዝግቧል? የመጀመሪያው የአዳም ወይ የሔዋን እንጉርጉሮ ይታወሳል? የሐጢያት መጀመሪያ የተባለችው በለስ የተበላችበትን ጊዜ፣ ሰዐትና ደቂቃ የሚያውቅ አለ?......

ሙሴ ቀይ ባሕርን ሊሻገር ሲል ያን ያህል የውሐ ብዛት አይቶ ስለማያውቅ

ሸንቱን ደጋግሞ በመሸናቱ የተበሳጨው ወንድሙ ኢያሱ 'ይኼ ተብታባ ምን ሆነ? መንገዱን ገና ሳናጋምስ ፊኛውን ታመመ እንዴ?' ብሎ መናገሩን ማን መዘገበ? ሙሴ ይኼን ሰምቶ ያዙኝ ልቀቁኝ 'ይኼን ምላሳም ካልደበደብኩ' ማለቱስ?......

......ናምሩድ አፉን የፈታበት ቋንቋ ምን ነበር? ሰለሞን ንግሥት ሳባን አፈር ምድር እንሰት ኮባ ስር የደበቀቻትን ድንግልና እንደ ተራ የሊባኖስ በለስ አልጋው ላይ ስትጥልለት ድንቁርናዋና ልጅነቷ አስገርሞት እየሳማት: 'የእኔ ጅል ያን ሁሉ የተንዝሽው ለዚህ ነው?' ማለቱን ክብረ ነገሥት መዝግቦታል? ሳባስ እብራይስጥ ባለማወቋ እንደተተረበች ሳይገባት መሞቷን እናውቃለን? ሳባ ገላዋን ስትታጠብ አንድ ታይጋና የተባለ ጉብል ቁጥቋጦ ውስጥ ተደብቆ የንግሥቲትን እፍረት በማየቱና ያየውንም በአክሱም ከተማ እየዞረ 'ንግሥት ጭናቸው ላይ ንቅሳት አለ፣ ደ'ሞ ገና አልጨጎኑም' እያለ በማውራቱ ዐይኖቹ እንዲወጡ ሆነው በዕውርነት አልተቀጣም? ይሄን የሚያውቅ አለ? በዚህም ሰበብ ከርሞ ልጁ ሲሞት ቀብር ላይ የመጀመሪያው *ተሰለብ ሰለሞን*[84] ሙሾ አልወረደም?......

......ፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ በስደት ዘመኑ ዋሻ ተደብቆ ማልቀሱና መናፈጡ በየትኛው ድርሳን ሰፍሯል? ነገረኛ ጳጳስ አባሮት ከኢንፍራንዝ አገው ምድር ከአገው ምድር ዳሞት ሲሮጥ ሰላሳ ሰባት ጊዜ በአፍጢሙ መውደቁ ተመዝግቧል? ሰላሳ ሰባት ጊዜ፡፡ ለመሆኑ ተማሪው ወልደ ሕይወትስ ይኼን አስታውሶ ፅፎለታል? ኸረ ዛሬ 'ሙሉ' ስለሚባል ደብተራ የሚያውቅ አለ? በልብነድንግል ጊዜ ወደ አዋሽ የሚሄድ መልዕክተኛ አጅብ ተብሎ መልዕክተኛው ሰው ቀረጢት ውስጥ በአጋጣሚ የቤተክርስቲያን ዝርዝሮች ያሉበት የሚስጢር ካርታ (ስዕል) አግኝቶ ይኼን ለማጋለጥ ወደ እንጦጦ ሲያመራ በአቡኑ ሕቡዕ ወታደሮች መገደሉ? ይኼ ካርታ ለቱርኮች እንደተላከ ከአቡኑና ከእሱ ሌላ ማን ያውቅ ነበር?......

---

84 *'ተሰለብ ሰለሞን'* በንግሥት ሳባ ጊዜ በመታወር ለተቀጣው ልጅ እናቱ ያወረደችለት ሙሾ ስም ነበር፡፡ (በድሮ ጊዜ ሙሾዎች በሴማ በሴማ ይመደቡ ነበር፡፡ እንደ ድርሰትና እንደ ግጥም አርዕስት ወይም ስም ይወጣላቸው ነበር) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባለስልጣኖች በሃሙራቢ አራማዊ ሕግ መሰረት 'ሕግ አፈረስ' የተባለ በሞት ከቀጡ በሟቹ ቀብር ላይ የሚወርደው ሙሾ ሁሉ መጠሪያ ስሙ 'ተሰለብ ሰለሞን' ተባለ፡፡ ('ተሰለብ ሰለሞን' ሲጀመር ትርጉሙ የንግሥታችንን ድንግልና ጠቢቡ ሰለሞን በማታለል ከወሰደ አጥፍቷልና እሱስ ለምን ብልቱን በመሰለብ አይቀጣም ለማለት ይመስላል) ሴትዮዋ ለልጁ ያወረደችው ሙሾ በከፊል ይሄንን ይመስል ነበር:
*የጤፍ ዳሊጋ ብበርቅ......ቆረሁት እጄን*
*ቆንጆ ኢጋጥሞኝ ብስቅ......ቆረሁት አፌን*
*የሰው ድካ ብዘል......ሰበሩት እግሬን*
*ተንተክትኬ ብስቅ......ናዱብኝ ቅንቄን*
*አስታርቶን እንዳይይ......ልጄን አወሩት*
*ተሰለብ ሰለሞን......ከተሃል ንግሥት*
ግጥሙ የተገኘው ታሪክና አፈ ታሪክ ከተባለው የፀሐይ አታክልት መፅሐፍ ነው፡፡ (1964) አአ አርቦሽ ማተሚያ ቤት፡፡

......ታላቁ ራስ አሊ የመጀመሪያ ሚስታቸውን በጥፊ ሲመቱ እልፍኝ ውስጥ ማን ነበር? በዚህ ሰበብ ከልጅቷ አባት ጋር ግብግብ ገጥመው የፊት ጥርሳቸው አንዱ የላይኛው በቆመጥ እንደ ረገፈ የት ተመዝግቧል?......

......ሚኒሊክ ልጅ እያሉ ደሴ ገበያ ማታ ለጋ ጨረቃ የወጣች ዕለት ዓይተዋት ስለ ወደዷት የአፋር ልጃገረድ እሳቸው ለማን ነግረዋል? አንዱ አሉባልታ ሰምቶ የሙዚቃውን ባቲ[85]*(ሽረ ባቲ ባቲ/ ባቲ ገንደልዩ......)* ቅኝት የፈጠሩት ሚኒሊክ ናቸው ቢለን ምን ልንል ነው?......

......በዚህች በኮተቤ ገጠርና በዚያች በሰማይዋ ፀሐይ መሃል ምን አለ? በዚህች በኮከበ ፅባሕ ዳገት መሃልና ባራት ኪሎ ስንት ነገር አለ ካርታ፣ የሰው ትውስታና የብርሃንና ሰላም ጋዜጠኛ ያልያዘው? ጋሼ? ሰማሽ እቴ? ብዙው ጉዳይ አልተመዘገበም::......

......እተጌ መነን ለስደት ሎንዶን ሲገቡ በትካዜ 'አንቺ ሆዬው ለእኔ'ን ማንጎራጎራቸውን ማን ተናገረ? ቤታቸው ሲገቡ ተፈሪ ጢማቸውን በቀስታ እየላጉ 'መነንዬ ሰማሁሽ፣ በእዝጌር በባህታ ይገፍሻለሁ እዛ መናፈሻው ጋ አትዝፈኚ ፈረንጅ ይሰማል፣ 'ይህቺ ባርያ አበደች' ይሉሻል' ሲሉአቸው መነን 'አንተ አላበዛኸውም' ብለው አኩርፈው መኝታ ቤት ገብተው ለአንድ ሳምንት በራሳቸው ላይ እንደ ዘጉ ተመዝግቧል? ኃይለሥላሴ ታላቁን ንግግር የዓለም ማህበር ላይ ተናግረው ሲያበቁ መልካም መልስ በማጣታቸው ከረዳታቸው ከነሎሬንዞ ትዕዛዝ እንኳን ተደብቀው ለማንም ሳይታዩ መታጠቢያ ቤት ገብተው ማልቀሳቸው ተፅፎአል?......

......ልዕልት ተናኘወርቅ ታላቋ ብሪታንያ በጣልያን ወረራ ዘመን በስደት ላይ እያለች ባዝ ጎዳና ላይ በትህትና የተዋወቃትን ዲላን ቶማስ[86] የተባለ የዌልሽ ጉብል መውደዷን ብላቴን ጌታ ሂሩይ አውቀው፣ ብላታም ተበሳጭተው ሰው ባሌለበት ጠርተው ቤት ዘግተው 'ጉግሳን የመሰለ የመኳንንት ልጅ እያለ ምኑም ከማይታወቅ አረመኔ ጋ ምን ልትሰሪ? ብትችይ ሱባዔ ነበር፣ ባልወልድሽም እቀጣሻለሁ' ብለው የትልቋን ልዕልታችንን ጭን እንደ ሕፃን ልጅ ጭን አልመዘለጉትም? እያለቀሰች ለመነን ለእናቷ ብትናገር 'ደግ አደረገ ልቤን አራሰልኝ...... ከሞላ የአገርሽ ወንድ እነ ባልቻ አሉ እና ማንናቸው እነ አርአያ አሉ......ያ ደ'ሞ ልጄ ስንቱ ስንቱ አበበም አለ ምን የመሰለ ሎጋ ደ'ሞ ነጫጭባ ምን አሰኘሽ ልጄ?' አላሏትም? ይሄን ማን ሰምቶ ነበር? ማን ያውቅ ነበር? ተናኘ የመጀመሪያ ሴት ልጇን ባዝ ከተማ ስትወልድ ጋሼ ሎሬንዞና አዛዥ ወርቅነህ ድንገት ዲቃላ ከተወለደ 'አስፈላጊው እንዲፈፀም' ተብለው በተጠንቀቅ ሲጠብቁ እንደ ነበር ማን ያውቃል? እተጌ 'እንደ አገራችን ዓይነት ፍል ውሃ እዚህ እኮ አለ:: ነይ ታጠቢ' ተብለው ሲሄዱ እዛም ደርሰው ሲጠይቁ 'ጥንት የሮሜ ሰዎች የታጠቡበት ነው' ቢሉአቸው 'እምቢ የፋሽሽት ነገር አልፈልግም ተናኘ ነይ ውሃ አፍሽልኝ'[87] ብለው በችኮላ አልወጡም? ሲወጡስ በር ላይ ያገኛቸው

---

85 በወረሞ አፍ ለጋ ጨረቃ ማለት ነው(አ)

86 በታላቋ ብሪታንያ ስዋንሲ ዌልስ እአአ በ1914 ተወልዶ በ1953 ያረፈ ገጣሚ(አ)

87 'እኚህ ሴትዮ አገራቸው ይኼ ዓይነት መታጠቢያ መቼ ሰሩና ነው የሚኩራሩት?' ብለው

አንድ አእሩግ ፈረንጅ ወደ አንገታቸው ንቅሳት እያሳየ አልሳቀምና......'ንቅሳቴን ከጠላህ ዘርህ አገሬን ለምን ወሰደ?' አላሉትም? (እሱ ግድ ባይሰጠውም) እነሱ ሳያዩ ዲላን ቶማስ ጉልበቱ ደካማ ቢሆንም ተሳዳቢውን ቢራ ቤት ድረስ ተከትሎ ሂዶ ሊደበድበው አልሞከረም? ስለዚህ ገጠመኝ እንደ ፃፈ ማን ያውቃል?[88]......

......አቶ ቃልኪዳን ታች ሠፈር ያለው የሙዚቃና የቪዲዮ ካሴት ነጋዴ ሲሞት እንደ ሞተ ማን አወቀ? መሞቱን አውቆ ከቀበረው ስንቱ ነው በትክክል በምን ምክንያት እንደ ሞተ የአወቀ? ዛሬ ከሃያ ዓመታት በኋላ አቶ ቃል ኪዳንን የሚያስታውስ አለ? ያቺ እንጀራ ጋጋሪ ሴት ልጇ ፅንስ አስወርዳ ብትታመምባት ሰፈሩ ከሚያወራባት ውርደት ለመደበቅ ብላ ገጠር ከተማ ልካት እዛ ብትሞትባት፣ ከዚህ ዓለም ማለፏን ለማን ነገረች? አሁን ድረስ 'ልጄ በሕይወት አለች' ብላ ታወራ የለም? ያ የልጅቷን አለመኖር የሞላውን ልብወለድና ቀናሽ ፀጥታ እያሽካካን እንኖረው የለ? የልጅቷ እናት የጋገሩትን እንጀራ ያልበላ የሠፈር ሰርገኛስ ነበረ?......

......ያ ይሄ ፀጥ ያለ ሕዋ ነው:: ሕዋው ድንቁርና ነው:: የታቀደም ያልታቀደም::......

......እህቴ ሆይ! ሃሙስ በተባለ ቀን ዕድሜሽ ሁለት ወር እያለ እናትሽ ጡጦ ስትነጥቅሽ ምን እንዳልሽ፣ አንቺም እናትሽም ትዝ ይላቸዋል?......

---

አቶ አበበ ረታ እተጌን ለተናኘ አምተዋቸዋል ይባላል::(የሎሬንዞ ትዕዛዝ የቃል ማስታወሻ)

88 አንዳንድ ሰዎች እኤአ በ 1934 የታተመው *18 ግጥሞች* የተባለው የመጀመሪያው የግጥም መፅሐፉ የተናኘ ወርቅ መኝታ ቤት ውስጥ የግል መፅሐፍት መደርደሪያቸው ላይ እንደ ነበር 'አየን' የሚሉ ይናገራሉ:: እና ከመፅሐፉ ልባስ ስር በእንግሊዘኛ ግልፅ በሆነ አፃፃፍ በፍቅር የተጠራ የተናኘ ስምና ማንም የሚያውቀው የዲላን ፊርማ ነበር:: በተጨማሪም ስለ ዲላን ካጠኑና ከሚያጠኑ ሐያሲያን
......If I were tickled by the rub of love........./I would not fear the gallows nor the axe/ Nor the crossed sticks of war...የተባሉት ስንኞች ቶማስ ለተናኘወርቅ ሲል መደባደቡን/ ከሰው መጋጨቱን የሚገልፁ እንደሆነ የሚያውቁ ስንት ናቸው? ከሰላሳ ዓመታት በፊት በንጉሠነገሥት ኃይለሥላሴ ፅ/ቤት አንድ እንግዳ ፋይል ውስጥ የሸቶው መዐዛ ያልጠፋ ልዕልቲቷ ለአቶ ቶማስ በአማርኛ የፃፈችው ደብዳቤ ተገኝቶአል:: ደብዳቤው ሳይላክ ይቅር፣ ወይ ራሳቸው ልዕልቲቷ እንደማስታወሻ ለራሳቸው ይፃፉት፣ ወይ በንጉሡ የስለላ ድርጅት ተለቅሞ እዚያ ይግባ፣ ወይ ከተላከ በኋላ በእንግሊዝ የስለላ ድርጅት ለንጉሱ ይመለስ የተረጋገጠ ነገር የለም:: ግጥሙ ይሄ ነበር፣

*'ስዘነጋ እላለሁኝ......ልቤ ጠፍቶብኝ ወድቆ*
*የባዝ የደንጋይ ምንገድ ላይ......በቶማስ ሌባው ተሰርቆ::*
*ወረቀት የሚመስል ሶብይ......ጠጉረ መልካም ወድጄ*
*አልሆን አለ መገናኘት......እዚህ ጦቢያ ተወልጄ::*
*የእኔም አገር ታላቅ ናት......የአንተም አገር ታላቅ*
*ግን ሁለታችን ተለያየን......አንዲት ቀን እንኳን ሳንስቅ::*
*ቅዱስ መፅሐፍ አንጀበኛ......የማይሆን ነገር ቢያስተምርም*
*ቶማስ ይወዲታል እስተሞቱ......ይህቺን ዛላ አይጠረጥርም::*
*ሁሉ ነገር በልብ ነው......እንዛለን በዚች አገር*
*በጡፍህ ውስጥ የእኛን ጉዳይ......አምልጦህ እንኳን አትናገር::*
*ይህቺንም ለራሴ ነው......ተደብቄ የማስበት*
*ማንም ቀልቃላ ደብተራ......ታሪክ ናት ብሎ እንዳይጥፋት'*
(የተፃፈበት ቀን አልተገለፀም:: ምናልባት 1950 ዎቹ ውስጥ ነው)

......ገጣሚውና ጸሐፊ ተውኔቱ ዮፍታሄ ንጉሴ አልጋው ላይ በሆዱ ተንበልብሎ (ገና ከየካ አስቀድሶ የእግር መንገዱ አድክሞት ኩታውን እንኳን ሳይጥል) እንደተኛ ከማጅራቱ ሊያንቁት ስለመጡት በአራት ጣቶቻቸው ላይ የወርቅ ቀለበት ያጠለቁ እጆች ያወራው ማነው? ......ዮሐንስ አድማሱን ሊያጠፋ ተቀጥሮ አስመራ ፔንሲዮን ስላረፈው ቀጭን ወጣት አናርኪስት ኮማንዶ ዛሬ የሚያውቅ ማነው? ይሄም መልከመልካም ሰልካካ ልጅ ሐያሲውንና ባለቅኔውን ሊገድለው ሲል 'ወደ ጌታህ ልልክህ ነው?' ብሎ መናገሩን ማን ሰማ? ምን ማለቱስ ነበር?......

......ኮሎኔል መንግስቱ ከኬንያው መሪ ጋር ተገናኝቶ 'ሰላም ወዳድ አይደለህም' ብለው አራፕ ሞይ ሲናገሩት 'የቀረኝ ነገር ሚስቴን ውብ አንቺን ለኢሳያስ መዳር ነው' ብሎ መልሶላቸው የኬንያውን የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር አላሳቀም? ማን ይሄን በጋዜጣ ዘገበው?......

......ታላቁ አብዮት ይዘንጉታል እንጂ መርሳትን የመቀናቀን ነው:: ታላቁ አብዮት ይናቃል እንጂ ሰፌ አባባሎችን፣ አጠቃላይ መደምደሚያዎችን ዘንግቶ ወደ ረቂቆቹ መውረድ ይሆን? ጀግንነት ትንንሽ የመሰሉ ነገሮችን የማስታወስ፣ የመርሳትንም ተራራ ማፍረስ ይሆን? ያን ያን ታሪክ ማድረግ ይሆን አዋቂነት?......

## ታሪክ ነጋሲ......

እንኮዬ ቀለመወርቅ በውዴታም በግዴታም የተፈጠረችበትን የኖረችበትን ሕዋ መምሰል አለባት:: ምኗ ከማን ይለያል? የታሪክ ስልባቦት ቢገፈፍ ከስሩ ያረፉ በራሳቸው ምዳቤ የደመቀ የግል ሕይወት ያላቸው ጥቂት ናቸው:: ካሉ-እነሱ ዕውነተኛ ጀግኖች ናቸው:: እነዚህ ከሺሆች ጋር ሺህ መስለው በጉልቤና በጫጫታ ጀግና ነን የሚሉትን ሳይሆን ይሄ የእያንዳንዱ ሰው ልፋት የሠፈረበት የተፀነሰበት:: ይሄ ይሄ ዓይነቱ ልፋት ግን በቡድን ስልጣናት ይሰረዛል:: ደቃቃ ዕውነቶች እንደ አደገኛ ተቆጥረው በጅምላ ትረካ ታጥረውና ተጠፍጥፈው ዝርዝሮች ወደሚጣሉበት ገደል ተወርውረው እንዲሰወሩ ይደረጋል:: አንዳንዴ እነዚህ ደቃቃ የተጨቆኑ ዕውነቶች ቀን ጠብቀው፣ ተደቅድቀው ከተዳፈኑበት ድቡሽት ላይ ይወጣሉ፣ ባልተጠበቀ ሰዓት የጋረዳቸውን ጅምላ ትረካ ጥሰው አረንዛ ፈንቅለው መኖራቸው እዚህ ዓይናችን ስር ይመጣል......

## ፊታውራሪ ዳዊትና እመቤቴ ሆይ ቀልሽ

አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ቀለመወርቅ ስድስት ኪሎ ከሚገኘው የዩንቨርሲቲ ካምፓስ ዋናው መፃሕፍት ቤት ስትወጣ ከፊት ለፊት ብዙ ተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ኮረኮንች ላይ ተሰብስበው ታያለች:: ጊዜው የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ ብዙ አመታት በፊት፣ ሚያዚያ ወር ውስጥ:: ሚያዚያን አትረሳም:: መዘዘኛ:: ወደ ሰላሣ የሚደርሱ ተማሪዎች ጀርባቸውን ለእሷ ሰጥተው ከፍ ያለ መደብ ላይ ቆሞ የሚናገር ሰው ያዳምጣሉ:: ተናጋሪው ኮከበ ፅባሕ ስትማር የምታውቀው ዳዊት ገ/ኢየሱስ ነው:: እዚያ እያለ የሁለት ዓመት ሲኒየሯ ነበር::

እዚያ እያለም 'ረባሽ' ወይም 'ሪቮ' ከሚባሉት ተማሪዎች አንደኛው ነበር:: ከርዳዳ ከማጅራቱ የተቆጣጠረ አፍሮ መሆን የጀመረ ፀጉሩን አቁሞ በስሜት ያወራል:: ከወደ ግንባሩ ሚዶ የበተናቸው ጥቂት ፀጉሮች በምሽቱ ነፋስ እንደ ረገበ አጥር ወደ ኋላ እየተገፋ ፊቱን ረዥም ያስመስሉታል:: ይኼ ሊያስቃት ነበር:: ከዚያ እያወራ እያለ እሷን ሲያያት ንግግሩን ለአፍታ አቆመ:: ረቂቅ እሷ ብቻ የተገነዘበቻት የመሰለች አፍታ ነበረች:: ቅፅበታዊ የንግግር አገታቱ ትኩረቷን ሳበው:: ዓረፍተነገር ሳይጨርስ መቆሙ:

«በትክክል ይሄን ፋሺ......»

ምናልባት አድማጮቹ የንግግሩን ለሰኮንዶች መቋረጥ ልብ ካሉ የሚተረጉሙት ሊናገረው የፈለገውን ግን የጠፋውን ለመሰብሰብ እንደሚያስብ አድርገው ነበር:: *(ፋሺን? ፋሺሽት?)* ይሔ ፀጥታው ትንሽ አስደንቋታል...... ንግግሩን ገትቶ፣ ከቆመበት ከፍታ ሳይወርድ ዓይኖቹ ያተኮሩት፣ ተማርከው ያፈጠጡት የእሷ የውበት ትዕይንት ላይ ነበር:: ባሏ ሲጀመር እንዲህ አተኩሮ አይቷት አያውቅም:: እያደባ፣ እያሰለሰ በዓይኑ ቂጥ እየመዘናት፣ እየተንተባተበ፣ እየተልፈሰፈሰ ነው......እንዲህ እንደ ዳዊት ሌላ የሚወደውን ነገርና በዐይኖቻቸው ሺፋሺፍት እየሳሱ የሚያደንቁትን ሰዎች ዘንግቶ አይደለም:: ዳዊት በትኩረቱ እንደ ዲጅኖ ወረደባት:: እግሮቿ ተንቀጠቀጡ:: አዲስ ነገርም ሆኖባት በማፈር ፊቷን ዞር አደረገች:: ወደ መሬት ዓይኖቿን ደፋች:: (*«በትክክል ይኼን ፋሺሽታዊ ፊውዳላዊ መንግሥት......»)* አንገቷን ሰበር እያደረገች ልጥፍ ቡናማ ቆዳ ጫማዋ ላይ ስንት ደቂቃ በማፈር ደጋግማ አፈጠጠች? በዚህ የመቅለስለስ በር ነው ዳዊት መፈክሩን ይዞ የገባው::

ዳዊት የታወቀ ታስሮ የተፈታ 'ሪቮ'[89] ነው:: (በተማሪ 'ትግል' ታስሮ መፈታት ራሱ 'ችሎታ' ነው፤ በምን ሂሳብ እንደሆነ ባይታወቅም) ዝናው በኋላ ከመጡት ከነመኩንን ይበልጣል፤ ከነጥላሁን ከነዋለልኝ ይስተካከላል:: የተናገረው ነገር ብዙው መሬት ቢወድቅም፣ በትክክል ማን ዝነኛ እንዳደረገው እንዴት ዝነኛ እንደሆነ ባይታወቅም......የዝነኛነት ስሙን ብቻ ተጠቅሞ፣ አራግፎ ጠርጐ የፈለገውን የሃሳብ ቂጣ ለተማሪ ያበላል:: ይኼ የፖለቲካ ማሕበራዊ ልምዱና ያለትችት የተደነቀ ስሙ ብዙ አይነት ዝርያ ካላቸው ሴቶች ጋር አገናኝቶታል:: እንደ ማርታ ደፋር የሆኑ በግራ እጃቸው በንብ፣ በከንፈሮቻቸው ፖለቲካ፣ በቀኝ እጃቸው ደ'ሞ ቀሚስ የሚገልቡ አስቀያሚ ሪቮ ልጃገረዶች እግሮች መሃል ገብቶ ወጥቷል...... እንደ ማአ ብብት እንደ ሮዛ ሉክዘንበርግ ዐይን አር የሚሸቱ......ወይም ቅን ሴቶች......የእናቱ አፍሮና አንደበቱ የሳባቸው፣ ወይ በዝነኛ ወንድ ደረት ስር ተደርምሰው መሞትን የሚሹ......ከራሳቸው፣ ከአገራቸው ወይ ከንጉሡ ነገስት ኃይለሥላሤ የተጣሉ......

ከሁሉም የሴት ዐይነት የሰበሰበው ተሰብስቦም የጠለለ ልምድ አለው...... ይኼ ልምድ ቁንጅናና በተለይ ዝርያ እንዲለይ ያደርገዋል::

ፊታቸውን ብቻ በመሰለል በቀላሉ ተገፍተው የሚንጋለሉትን ያውቃል:: በአንደበቱ የተወጠሩት እነ ማን እንደ ሆኑና መቼ መርገብ እንዳለባቸው

---

89 revolutionary (ሪቮሉሽናሪ) የሚለው ቃል ሲያጥር/ አብዮተኛ/(አ)

ያውቃል......

ዝና የሚያቀልጣቸውን የሴት ዐይኖች ገና ሲያያቸው ያውቃቸዋል......

ሲዝናናባቸው የሚደሰቱ፣ 'ዳዊት አርጎኛል' ብለው ሽንት ቤት በር ላይ ከመፃፍ የማይመለሱትን ገና ሰላም ሲላቸው ያውቃቸዋል......

በዚህ ሁሉ አልፎ ግንባሩን ሳያጥፍና ሳይጠራጠር ብዙው ሴት 'ጅል' ነው ብሎ ያምናል:: አንዱ ምክንያቱ እሱ እንደ ሚለው በአጠቃላይ ስቱደንት ቦዲ (student body[90]) የተባለው አንድ ትልቅ በረት የጅሎች መሰባሰቢያ መሆኑ ነው:: ለዳዊት ሴቶቹ የዚህ ትልቅ አካል ንዑስ ስብስብ (subset[91]) ናቸው:: በአዋጅ ያልተጠቀሰ ፊላጭ ቆራጭ ነው:: አመለካከትህ ተወናከረ የሚሉትን፣ ስህተትህን ልጥቀስ፣ ልመዝግብ የሚሉትን ይቀጣል:: የነዚህን ዐይነት ሰዎች ስም ያጠፋል፣ በካምፓስ መኖርን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል:: አልተመዘገበም እንጂ የዩንቨርሲቲው አስተዳደር 'ረባሽ ናቸው' ብሎ ካባረራቸው ተማሪዎች የበለጠ እሱና ሽርኮቹ ከካምፓስ አማረው ያስወጡት ተማሪ ቁጥሩ ይበዛል:: ያን ካልቻለ የሕብረተሰቡን ዓይነ አፋርነት ተጠቅሞ በራሱ ይሉኝታ ያፈዘዋል:: ነቅተናል ቢሉ የሚሉት ቢብስ 'ይሉኝታም አያውቅ?' ነው (ያውም በየዶርማቸው በሹክሹክታ):: አበሻ የሚፈራው ዐይነአውጣና ይሉኝታ ነው:: ዳዊትን ከተቹትና ካሙት በኋላ ተመልሶ መጥቶ ግን እንደ ናዳ ይወርድባቸዋል፤ ለፍላጎቱ ይንበረከካሉ:: ተማሪውን ከትምህርቱ እያለያየ ቤቱ የሚያስገባው፣ እያስገባ የሚያስወጣው በሃሳቡ ረቂቅነት አልነበረም::[92] በአደገበት ይሉኝታ እየተጫወተበት ነው:: ተማሪዎች በተደጋጋሚ እየተንጋጉ እሱና መሰሎቹ ለሚሰሩት ተንኮል ሲገዙና ውድ የትምህርት ጊዜአቸውን ሊያፈርስባቸው ነገር/ፖለቲካ ሲጠመጥም ቆመው ይከራከሩታል (ሌላ አገር ቢሆን ይደበድቡታል):: ከዚህ ሁሉ ተነስቶ–

---

90 የተማሪው ክፍል/አካል(አ)

91 (ንዑስ ክፍል):: ዳዊት የሴት ቲየሪ ሙሉ ዕውቀት የለውም፤ ግን እንጀባ አለው፣ ጥራዝ ይነጥቃል:: ትርጉም የሚያቀናብርበት የራሱ ስልት አለው:: ተጠየቁን ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይ እንዳሻው ያወጣዋል ያወርደዋል:: ፊልፍሎ ልወቅ የሚል ተመራማሪ የለበትም:: ምሳሌ:-

| | |
|---|---|
| (1)<br>አልማዝ የተማሪው አካል ናት<br>አልማዝ ቂል ናት<br>የተማሪው አካል ቂል ነው | (2)<br>የተማሪው አካል ቂል ነው<br>አልማዝ የተማሪው አካል ናት<br>አልማዝ ቂል ናት |

በተራ የማህበራዊ ግኑኙነት ብልጣ ብልጥነት አገር ማንቀጥቀጥ መቻል ማን ይጠላል? እንዴት ነጠላዎቹ ጂሞቹን ያክላሉ? ጂሞችስ እንዴት ነጠላዎቹን ያክላሉ? ብሎ የሚጠይቀው የለም:: ምክንያቱም ይኼ ስሌቱ በልቦናው የደበቀው የራሱ ምስጢር ነው::

92 ግጭትን ወደ ጀብድ ለውጦ የኪነትነት ቀለም ይሰጠዋል:: ፖለቲካ ለእሱ ዕውቀትን ተከትሎ የሚመጣ ሳይሆን የፈጠራ ስራ ነው:: ያለችህን ዕውቀት ተጠቅመህ እንዴት እንደ ምትተነትን አይደለም:: ያለው አማራጭ ያለችህን ዕውቀት ተጠቅመህ በሚያምር ቋንቋ የሚያንጫጫ የድርጊት ኪነት እንዲኖር የመልፋት ነው:: ሲያልቅ ሰዎች ዕውነት ከኪነት ይምታታባቸዋል:: ጀብደኛ አርቲስቱ ፖለቲከኛ ይመስላቸዋል::

ከወጣቶቿ፣ ከዩንቨርስቲው ተማሪ ቂልነት ተነስቶ አገሪቷን ይንቃል:: ዛሬም ብቻ ሳይሆን ወደፊትም እንደማይከዱት ያውቃል:: ጅልነታቸው እንደማይለወጥ፣ እንደማይሰረዝ፣ እንደማይጠፋ ከአሁን ፀባያቸው ይገምታል:: እና ሁልጊዜ ልፍስፍስ ሃሳቡን 'ወደ ፊት ታሪክ እንዳይታዘበን' በሚል ሐረግ ያስረዋል:: ዛሬ ጡጦ እንደሚጠቡ ሁሉ የሚሸውዳቸው ወጣቶች አርጅተውም ጡጦ መጥ ባታቸውን እንደሚቀጥሉ ይገባዋል:: ወደ ፊትም ሽበት ከከበበው አፋቸው፣ ከደኸየ ምላሳቸው ፍሬ የማያወጣ ቃል እያዝረበረቡ የእሱን ታሪክ አዳንቀው ይዕፉሊታል::[93]

---

93 አንዳንድ ሰዎች በመጠኑ በአደባባይ ረብሸውታል፡ በተለይ አብዮት ፈንድቶ ሶሻሊስቶች መደራጀት ጀምረው እርስ በእርስ መተራረብ፣ በጋዜጣና በሬድዮ መናከስ በጀመሩ ጊዜ:: አንደኛው ትችት የተቃጣበት ለአጭር ጊዜ ተከታዮች አፍርቶ ግን አባሉቹን በፍጥነት ያጣው የተነካናኪ ኪነጥበብ ወይም ስዕል አሳሳል ዘይቤ መስራች መስኮት ገረሱ *በአንድ ሐፍታ መፅሔት* ያደረገው ቃለ መጠይቅ ነው::

<u>አአ፡</u> በሌላ መፅሔት ላይ የተማሪ ንቅናቄ አጥላልተሃል ይባላል:: ታዋቂ የሆኑ እንደ ዳዊት ገ/ ኢየሱስ ያሉ ሪቮሉሽናሪስ እንደተቹህ አንብቤአለሁ::

<u>መገ፡</u> ትችታቸውን አንብቤአለሁ:: ጥልቀት የለውም:: ስድብ ነው:: ስም ይለጥፉብሃል:: ኮምፕራዶር፣ አቀባባይ፣ አቃጣሪ አርቲስት፣ እበላ ባይ ወዘተ ይሉሃል:: ደስ የሚል ነው:: ለሐይለስላሴም ይሁን አሁን ለመጡት ደርግ ለተባሉት ወታደሮች ባቃጥር ለአገሬ ነው:: ለማላውቀው ለሌኒን አይደለም:: ማነው ሌኒን? ማነው ያ መላጣ? ማነው ትሮትስኪ? እሱስ ቢሆን ለምን ከነመነፅሩ ሲአል አይወርድም? ያስተማሩኝን ንጉስ ሙቱ ብዬ አልሰድብም:: ከተንከባከበኝ ልጅነቴ አልጣላም:: ያ ዕውነት ነው:: ብቸኩል የምንከሰው ቀንድ ነው:: የሚያቻኩሉን ቀንዱን እኛ እንድንበላ ስጋውን እነሱ እንዲበሉ ነው:: ስጋውን ማን እንደሚወስደው ዛሬ ሳይሆን ከርሞ ከርሞ ይታያል:: አልፎሬጥም:: ሁሉ ነገር በሰላም እንዲያልፍ እፈልጋለሁ:: ማንም ወገኔ አታሎም ይሁን ተታሎ እንዲሞት አልፈልግም:: አራት አምስት ሺህ አመት እዚችው ቦታ የኖርን የምንተዋወቅ ነን:: ዳዊት ጨቅላ ነው:: ዳዊት ከብልጥ በላይ አይደለም:: ያ ተራ የስንዝሮ ብልጠቱን ብሩህነት ይሉለታል:: ብሩህ የዘመኑን ሳይንስ ከአገሩ ጋር አገናዝቦ የሚሰራ አንጎል ያለው ነው:: በከሰል ኢንዱስትሪ ቆሽሸው የነበሩ አውሮፓና ቅዱስ ፒትርስበርግ ሳንባቸውን የደፈኑባቸው ነጮች የሚያወሩትን ኮፒ አድርጌ አይደለም:: የጠራ አየር ያላት አገሬን በባዕድ አልነጅሳትም:: መልካም ነገር ከባዕድ እወስዳለሁ:: ስዕሎቼ የዚያ ምስክር ናቸው:: ግን 90 በመቶ ገና ሀሁ ያልቆጠረ ሕዝብ ኮሚኒስት ሁን ብዬ አልሰብከም:: ከሌላ አገር መፈክር ወስዶ ስለ ጮኸ ድፍረቱ ተደንቆ እንደ ሆነ ረጋ ካላልን ትርጉም የለሽ ይሆናል:: ዳዊት ቢታሰርና ቢሞት አላዝንም:: አቤ ጉበኛ ቢታመም ጉንፋን ቢይዘው አዝናለሁ:: ምክንያቱም አቤ የጠራ ብሄረተኛ ነው:: አናርኪስቶችና ኮሚኒስቶች ቀድመው የሚያጠፉት እሱን ነው:: ስለዚህ ደደቦች አያስፈሩኝም:: ግን የጥፋት ዘመን ከማምጣታቸው በፊት ጠማማነታቸውን ቢቀንሱ ደግ ነው::

<u>አአ፡</u> ስዕልህ ከባድ የባዕድ ተፅዕኖ አለበት ይባላል:: ተነካናኪ ጉራ ነው የሚሉ አሉ::

<u>መስ፡</u> በባህሌ ላይ ሂስ አድርጌ ከተነሳሁ አዲስ ነኝ:: አሰያየሜ አዲስ ነው:: ያ ማለት በባዕዳን ይሄን የመሰለ የባህል እርምጃ አልተደረገም ማለት አይደለም:: አገሬን በልቤ ያደረግሁ ኮስሞፖሊታን ነኝ:: ማለት ከአለም ተፅዕኖ ማምለጥ አልችልም:: ዘሉ ያለ ማብራሪያና ያለ ደንበኛ ሒስ ግን የነምሳውን ጉስታቭ ክሊምት ትመስላለህ ቢሉኝ ፖለቲካ ነው የማደርገው:: በኪነቱ በብሄረተኛነቱ ስትበረታባቸው በስም ማጥፋት ይመጣሉ:: ስለ ኪነት ሃባ የማያውቀው ዳዊት ገ/ኢየሱስ ሲዘባርቅ ነበር:: ኪነትን የሚወዳት ለእሱ ቡድን ስታቃጥር ነው:: ኪነት ለማዳላት አትነሳም:: መረጃዎቹ ወደ እዛ ከወሰዱ ምን ማድረግ ይቻላል? አገር ልጆች አሏት በተጨማሪም አገር የእንግዴ ልጆች አሏት:: ዳዊት የእንግዴ ልጅ ነው:: ያልተመቸው ታሪክ ሲያነጥስ ተስፈንጥሮ የሚወጣው ንፍጡ ነው:: እሱ ዳዊትና መሰሉቹ ናቸው:: አፍንጫችን ውስጥ ስለ ነበረ ክብር እንስጠውም:: አገርህን

ቀለመወርቅ በዳዊት ንግግር ተመስጣለች:: ከዳዊት ሰፊ አፍ የሚለቀቁት የባዘቱ፣ የበለዙ፣ ያረጁ ያፈጁ ቃላትና ሃሳቦች ቢሆኑም ወፍራም ድምፁ ውስጥ ለስላሳ ሐርማ ውበት አላቸው:: ከዚህም በላይ እተሰበሰቡ ሰዎች መሃል ስለሚነገሩ ሳይሆን አይቀርም የሆነ ያልተጠበቀ ሐይል ያገኛሉ:: ከጐበዝ ተማሪዎች ብትመደብም፣ ቀለመወርቅን እንደ ልዩ ጉድ የሚመስጣት እንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር:: ከዳዊት አፍም ፈረንጅኛ ቃላት እንደ ሸኖ ሰንደዶ ተረጋግተው ሲመዘዙ......እና ማራኪ ጉራማይሌው......:

«ኦብጀክቲቨ ሪያሊቲውን[94] እናጢን......»

«ኤክስፕሊሲቲሊ ኦር ኢምፕሊሲቲሊ[95] ስትራግሉ[96] ይቀጥላል......»

ምክንያቱን ያን ጊዜ አልተረዳችም እንጂ ለስብሰባው ፍላጐቱ ሳይኖራት እስኪበተን ድረስ ስታዳምጥ ነበር:: ፖለቲካው ሳይሆን ዳዊትና ያሚያቀናብረው ስፔክታክሉ[97] ስቧት:: አልገባትም እንጂ በየዋህነቷ......ያኔ የስፔክታክሉ ጉልህ ቦታ ውስጥ ናት:: የሆነ ነገር......'ምን አደርጋለሁ እዚህ?' ዓይነት ስሜት ተሰምቷታል......ግን የዳዊት የጓን አስተያየቱ ደ'ሞ አቁሞአታል:: እንግዳ አይነት ይሉኝታ: 'ተማርኮ አይቶኝ እንዴት ንግግሩን ሳይጨርስ እሄድበታለሁ?'......

የመጀመሪያ ስህተቷ ነበር......

ስብሰባው ተበትኖ መንገዷን ስትቀጥል ኰቴ ከኋላዋ ሰማች:: ዞር ብላ እንኳን ሳታይ ማን እንደ ሆነ በትክክል ገመተች:: ቆማ የጠበቀችውም ለዚህ እንደሆነ ገባት:: ራሷን ታዘበች:: ራሷን ትንሽ ጠላች::

«ሠላም አውቅሻለሁ መሰለኝ» አላትና ዳዊት እንደ ጨዋታ በትከሻው በትንሹ ገፍቶ እንደ ውሻ ታከካት:: ማንን ሊፈራ::

«አንድ ጊዜ አይቼሻለሁ......(አመልካች ጣቱን ቀስሮ፣ ባዶ አየር ላይ

---

መውደድ አለብህ መጀመሪያ:: ምሁር ስለሆንክ አዳምጡኝ ከማለትህ በፊት:: ስለሆንክም ሁሌ ትክክል ነህ ማለት አይደለም:: የሰራተኛ አምባገነንነት የሰራተኛ አምባገነንነት እያሉ ይጮኻሉ:: በሁሉ በኩል ደ'ሞ ዶክተሮች ናቸው:: ማታለል ከዚህ የበለጠ አለ? ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የኪነት ሃብት ብዙ ዘናጭ ነገር መስራት ትችላለህ:: እችላለሁ:: ክሊምትን የማደንቀው ሰዐሊ መሆኑን በአንዳንድ ቦታ ተናግሬአለሁ:: ቢሆንም ተፅዕኖ ፍለጋ እሱ ጋ አልሄድም:: እኔ ወደድኩት ማለት የአገሬ ሰዎች ብዙዎች ወደውታል ማለት አይደለም:: ራሴን ማወቅ አለብኝ:: መስኮት መስኮት ነው:: ራሱን ያላወቀ ከያኒ ብዙ ይጎለዋል:: ጭቁን ጭቁን ጭቆና ጭቆና ስላልክ የአገሪቷ ችግር ገባህ ማለትም አይደለም:: በአብሮ አደግህ አገር አጥፊ በቀላሉ ልትጠመዘዝ ብሎም ልትበተን ትችላለህ:: ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ከሆንክ የቀረው ቶሎ ይገባሃል:: የዳዊት ትልቁ ችግር እንደ ብዙው ወጣት በቀላሉ እህያ ስለ አልሆንኩለት ነው:: ሱሚ ነው:: በነገራችን ላይ ድንክነቴን ስድብ ማድረጉና ለከርከር ማምጣቱ እኔን አሳፍሮ አደባባይ እንዳልወጣ ለማድረግ ከሆነ አይሆንለትም:: ምክንያቱም ከድንክነቴ ጋር ብዙ ዐመታት ኖሬአለሁ:: እኔ ድንክነቴን እንደ ማውቀው እሱ አገሩን አያውቅም:: ሂሂሂ::

94 objective reality= ነባራዊ ሁኔታ(አ)

95 implicitly or explicitly= ግልፅም አይሁን ይሁን ትግሉ ይቀጥላል(አ)

96 struggle= ትግል(አ)

97 spectacle= ትዕይንት (እንግሊዝኛ)(አ)

አተኩሮ) የሕግ ተማሪ ነሽ አይደል? ኩከበ ፅባሕ ነበርሽ እ?» አልመለሰችለትም:: አብራው ጎኑ መሔድ እንደ ገና ደ'ሞ መሸሽ ፈለገች:: ከስብሰባው የተበተኑ ተማሪዎች አተኩረው ሲያዩአት:: ቀሽምነትና ትልቅነት ተሰባጥረው ተሰማት::

«ዳዊት እባላለሁ» ሊጨብጣት ቀኝ እጁን ዘረጋ:: ቆመችና ለአፍታ ቀና ብላ አይታው፣ ያይኖቹን ትልቅነት መሃላቸው ያለውን ቡናማ ኳስ ያንንም የከበበውን የሚያስፈራ የሚውጣት የመሰላትን ንጣት ለሰከንዶች አጥንታ ጨበጠችው (እጅ ነው ጣውላ?):: ከግቢው እስኪወጡ ሁሉን ነገር ነገረችው:: ስሟን፣ አስተማሪዎቿን፣ የጥናት ፅሑፏን እየሠራች እንደሆነ ወዘተ......ለዚያ ቀን በመንገድ ላይ ተለያዩ:: ባለትዳር መሆኗን አልነገረችውም......:: እንዲመጣላት በር መክፈቷ ይሆናል:: እንደ ካቡት ይኼ ባለስንጥቅ ቀሚስ እንደሚሉት:: በውልብታ ዛልን በማሳየት ለፍትወት የመጥራት:: እዛ ያልተገለጠው፣ ፀሐይ ያልደረሰበት ግን ነፋስ እሚተላለፍበት ጨለማ ሞቅ ያለ የሩካቤ ተስፋ እንዳለ የሚጠቁም::

ይኼ ሁለተኛ ስህተቷ ነበር......

እቤት ባሏ ሲራክ ከሥራ ገብቶ ገላውን ሲታጠብ ደረሰች:: ዳዊትን ለመርሳት የጀመረችውን ልፋቷን፣ በመተታጠብ ጉልበት ለመስጠት ተከትላው ገባች:: ሁለቱም የሻወር ውሐ እየወረደባቸው በሎጋ ቁመናው ሥር ጠልሎ ፀጉሯን ሲያጥባት፣ ዳዊት አንገቷ ግድግዳ ላይ በሙቅ እንደ ተለጠፈ አይናማ ሰው ስዕል አልሔድም ብሎ ታየዋለች......እጆቿም በደመነፍስ በሳሙናና በውሃ ዳጥ ውስጥ፣ አድርጋ የማታውቀውን የባሏን ገላ ረስታ......

«እሺ'ኝ እንጂ ቀልዬ! ምን ሆንሽ?» እያላት......

በበነጋታው መፃሕፍት ቤት ዳዊትን አገኘችው......

ከማጥኛ ቦታ አመራረጧ ራሷ ሰርታው ራሷ ያልገባት ዓይነት ሴራ ነበረው:: ከውጭ ከተቀመጠችበት ምንም ያህል ሳይርቅ የሰው መተላለፊያ መንገድ ነው:: ቀኝ እግሯን ብትዘረጋ በተከፈተ መስኮት እስከ ጉልበቷ ድረስ ወደ ውጭ ማውጣት ትችላለች:: በመንገድ የሚሔድና የሚመጣ ተቀምጣ ስታነብ ሊያያት ይችላል:: እዛች የተቀመጠችው ምናልባት ዳዊት ካምፓስ ካለ በዚህም መንገድ ካለፈ እንዲያስተውላት ፈልጋ እንደሆነ የገባት ከግማሽ ሰዐት በኋላ እሱ ራሱ ፊት ለፊቷ መጥቶ ጉብ ሲል ነው:: ዳዊትን የከበበው የትንባሆ ጠረን፣ ቀይ ሪቮሉሽንና የሆነ የሚጋፋ መምቻ ወንዳወንድነት ነው:: የዓይኖቹ ትላልቅነትና ለስላሳነት እያባበላት (እንዴት ትልቅና ለስላሳ ሆኑ?)......ሊያነብ የነበረውን መፅሐፍ እንዳልፈለገው ሁሉ ወደ ግራው ራቅ አድርጎ ገፋው:: በውሰት ቅብብል የተሻሸ ሽሮማ ቀለም ያለው what is to be done?[98] የተባለ መፅሐፍ ነው:: ከመፅሐፉ የታች ቀኝ ጠርዝ በኩል የመላጣ ሰው የቻርኮል ስዕል አለ:: ሲራክ ጉኗ ተቀምጦ እሷን ለማዋራት የወሰደበት ጊዜ ስድስት ወር ነበር:: ያውም እያፈረ......ተማሪ አስተማሪ የተገኘው ተመልካች 'ምን ይለናል?' እያለ::

98 ምን መደረግ አለበት? (ሩሲያዊው ኮሚኒስት ቪላድሚር እሊች ሌኒን የፃፈው መፅሐፍ)

የዳዊት ቅልጥፍናና ፍጥነት ሳባት። የአይኖቹም ትልቅነትና ቡናማነት......

«ማረፍ አያስፈልግም እንዴ?» አላት ወደ ጎን ገፋ ያደረገውን መፅሐፍ ስታጤን አይቶ።

«ገና አንድ ሰዓት መቀመጤ ነው»

«ፔፐር እኮ መጀመሪያ አስበሽ መጨረስ አለብሽ ለመፃፍ ከመጀመርሽ በፊት......እ»

«እሱን የጨርስኩ ይመስለኛል......ደሞ እንደዛ ማሰብ አያቆምም......አሁን ማቴርያል መሰብሰብ አለብኝ። ኬዝስ[99] ምናምን ......»

«ማረፍ ከፈለግሽ፣ ቡና ምናምን እንጠጣ»

«ምናልባት ከአንድ ከሁለት ሰዓት በኋላ» ለመግደርደር ነበር። ቢገባውም ያላወቀ መሰለ። እንዳልተንሰፈሰፈች እንዳልተንገበገበች ከራሷ ስሜት ጋር እያሴረ። እንደፈለገች ቢያውቅም......

ሲራክን ያውቀዋል ቢያንስ በዓይን። እንደተጋቡ ግን አያውቅም። ቢጋቡስ? ማን ግድ አለው? ራሷን ካልጠበቀች ልቧ ከተከፈለ? ለእሱ ለዳዊት የትምህርት ጊዜአቸውን ብቻ ሳይሆን ባልተተቸና ባልተሰላ ጉብዝናው ለጭንግፍ አዋቂነቱና ለጥራዝ ነጠቅነቱ ተማሪ ወዳጁን ይገብራል......ሴቶች ጭኖቻቸውን ይከፍታሉ......

«ጥሩ እዛ ነኝ። መጥቼ አወስድሻለሁ» እንዴት የተረጋጋ ነበር። 'ሪቮነት' በታሪክ ማሕደር ብቻ ሳይሆን (ታሪክ ይኼን አይደርሳም) ሴቶች ማሕፀንም ውስጥ ይጣፋል። እዛ ማሕደር ውስጥ የረጠበው ትኩስ ግድግዳ ላይ ምርቃትና እርግማን በኖራ ካፊያ ይመዘገባል። አንድ ሪኙም አፍታ ባሏን፣ አንድ አጭር አፍታ ደ'ሞ ካገናቻቸው ወሬት ያለፉ የሚያውቋትን፣ ስለ እሷና ስለ ሲራክ መዋደድ የሚመሰክሩትን፣ በድንገት እዚህ ከዳዊት ጋር ተቀምጣ ቢያንስ በአፍ ስትተሻሽ ቢያዩዋት የሚሏትን......፡

*«ቃልዬ! ተማምለን ነበር እንዳንከዳዳ......»*[100]

*«ሴት!»*

*«ሴትን ማመን»*

*«አይ የሴት ነገር»*

*«እሷም እንደዚህ?»*

*«አይ! ይ ይ»*

*«ኤድያ እቴ! ሴትን ማመን»......*

የመሳሰለ ነገር ሲሏት፣ ከዚያ ትዳሯ......ትዳሯ ደ'ሞ ራሱን የቻለ ካፖርት

---

99 ምሳሌዎች(እ)

100 ባልዋ ምናልባት ከዘፈን ግጥም ላይ የሚበጥሰው......

የደረበ፣ ሽበት የፈሰሰበት አእሩግ፣ የከሰረ ወይ የተበደለ የሰው ፍጡር ተመስሎ ሊተቻት ዘንጉንና ጭራውን እያነሳ......ከዛ ደ'ሞ ዳዊት ወፍራም ግርማ ያለው ድምፁ፣ ማራኪ ጉራማይሌው፣ በራስ የመተማመን ቂንጡ......የሚያማምሩ ዓይኖቹ.....

......ከዛ የመንገዱ ነገር......

መንገድ ላይ ያሉ ሰዎች......መፅሐፍት ደረቱ ላይ አቅፎ የያዘ አንዱ ሁለመናዋን አተኩሮ አይቶ (ከደረቷ እስከ እግሮቿ) ጠቀሳት:: ፊቷን አዞረች:: ቀና ብላ ደ'ሞ ዙሪያ ገባዋን ታያለች:: እወዲያ የኢትዮጵያ ስብስብ ፅሑፎች ያሉበት ቦታ ተደፍቶ የሚያጠና የተማሪ መአት:: ያው አነ ዳዊት 'ትምህርት አቁመን እንሂድ' እስኪሉት:: እምቢ ካለም 'ሳቦ' ብለው አዋክበው ወደ መጣበት እናቱ ጉያ በሴራቸው እስኪከቱት:: እንደ ልጅ እስኪያደርጉት:: ኢንሳይክሎፔድያዎችና ሌሎች *ሬፈረንስ ማቴርያልሾ*[01] ያሉባቸው መደርደሪያዎች መሃል ዳዊትን ከጀርባው አየችው ተደፍቶ ሌኒንን ሲመጥ:: ፊቷን መለሰች:: ድንገት ቢያያት ስለ እሱ መምጣት የጓጓች እንዳይመስል:: እዚህ ብዙ ወንዶች አሉ:: ግን ባኗን ለምን እንደ መረጠች ታስባለች:: እዚህ መአት ወጣቶች አሉ ለአጭር ጊዜ ብትንጉራደድ እንደ ቂል አፋቸውን ከፍተው የሚያጠኗት የሚያነቧት፣ ከጭኖቿ መሃል የሚነሳውን ጠረን አነፍንፈው አፋቸውን ሰቅለው እንደ ከልቢ የሚያላዝኑ......ይህቺ ቀይ ዳማ ከሪቮሉሽን ያማረች (መች ይሆን የሴትነት አቅሟን በገጭ ገው ዘርፈው በርካሽ የሚተጏት?):: እንዴት በስድስት ዓመታት ውስጥ አንድ ወንድ ብቻ ታውቃለች? ምን መርምራ ምን አወዳድራ ነው (ዋናው ማወዳደር አይደል) ሲራክን የመረጠችው? ይኼ ሁሉ ነገር በአእምሮዋ ሲወጣ ሲወርድ፣ በንባቧ ብዙ እንዳልሔደች፣ የፃፈችውም ትኩረት እንደሚጎለው፣ የእንግሊዘኛዋ ሰዋሰውም የተበላሸ መሆኑን አየች::

በራሷ ትኩረት ማጣት በመማረር ከተቀመጠችበት ስትነሳ ዳዊትን ወደ እሷ ጠረጴዛ ሲመጣ አየችው:: የዳዊት 'ሊጋብዝሽ' ንዝንዝ ጥልቀት ሳባት:: ሰዐቷን አየች:: ሰዐት እንዲህ አክብሮ ከመጣ አስቧት ነው:: ባያስባት ጊዜ ይስት አልነበር:: መሃላቸው በትንንሽ ሲኒዎች ጥቁር ቡና እየጤሰ......ማባበያ አፉ የበሰለ ትኩሳት ብቻ ሳይሆን የብዙ አውቃለሁ ሞገድም ነበረበት......ልቧ ውስጥ ሪቮሉሽን እንደሚያስነሳ......

ግራ የገባው የመሰለ ሳቂ--ከጥርጣሬ ከፍርሐት የፈለቀ--ፊቷ ላይ እየፈሰስ:: ያን ቀን ቡና ከጠጡ በኋላ ግኑኝነታቸው አላቆመም::

ካምፓስ ባለች ቁጥር ይገናኛሉ......

የድርጊቷ ክብደትና ስፋት የሚሰማትና የሚታወቃት ፀጥታ ቦታ ተቀምጣ ዓይኖቿን ስትጨፍን ነው:: በተለይ ማታ ሲራክ በድካም እያፋሸከ ሠንገሮ ቁመናውን እየጎተተ ወደ አልጋው ሲሔድ 'ክላሲካል ሙዚቃ ልስማ' ብላ አሳባ ሳሎን ሶፋ ላይ እግሮቿን ዘርግታ ተዝናንታ ስትቀመጥ፣ ባልጠበቀችው ፍጥነት ጀርባዋ ገና የሶፋውን መደገፊያ ሲነካ በጥልቅ ማሰብ የምትጀምረው ግን ስለ ዳዊት ነው:: የሆነ ብሎን የሚፈታታ፣ ሞተሯን የሚያውገረግር ካቻ

ቢቴ ነገር ወደ ውስጥዋ እንደ ወረወረ ይገባታል:: በአፏ እየቀረባት ሊነካት ግን ያልደፈረ:: ሁለመናዋ ከውስጥ እየላላ ሲሄድ......ጨዋታ መሃል ከማጅራቷ ዝቅ ብሎ እጁን መጋፊያዎቿ መሃል ጣል ሲያደርግ......ስፋቱና ክብደቱ እግሯ ድረስ ይሰማታል:: በማይገባት ምክንያት ዐይኖቿን ጨፍና ሸርተት ብላ ኮቱን ለብሳ ጎኑ መመስግ ትፈልጋለች:: አልፈረሰችም እንጂ ተሰነጣጥቃ በቋፍ ናት:: አደጋው ትንሽ ይገባታል:: ከባሏ ጋር የመጀመሪያ ዓመት ላይ ይኼን ዓይነት ስሜት አሳልፋለች:: 'መቼ ነው የሚነካኝ?' (ብርቅነቱም):: አደጋው እየገባት ከውስጧ እያማጠች ትተነፍሳለች:: ጭር ባለ ማታ ቀይ ዳማ ጡቶቿ ጋቢዋና ውስጥ ልብሷ ስር ይነዳሉ......ጭኖቿ መጋጠሚያ ያልባታል:: የስራ አካላቷን ይኮረኩራታል:: ከዘጋቻቸው ዓይኖቿ ወዲያ የዳዊት ሰፋፊ ደፋር እጆች ከላይዋ እንደ ክንፍ አርብበው......

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ከሲራክ ጋር ለምሣ እንደተቀመጡ 'እየጻፍኩት ነው' የምትለውን የጥናት ወረቀት በአጋጣሚ ጠረጴዛ ላይ አግኝቶ ማንበብ ጀመረና የሚበላውን አቁሞ:

«ምን ሆንሽ? መሠረታዊ ቴስስሽን[102] እየሳትሽ ነው:: ትኩረት የለሽም ወይስ ንባብሽን አስተጓጉልሽ?» አላት:: ምንም አልመለሰችለትም:: በልቧ 'ምን ይነጨንጨኛል' አለች:: በልቧ ደብቃ ተችታው አታውቅም:: እውስጧ ያለው ሃሳብ ደስታና ቀልድ (አዝና አታውቅም) ሁልጊዜ በሙሉ እውጭ ነበር:: ከጐሉ እስከ ደበዘዙ አእምሮዋ ጨለማ ውስጥ የሚመላለሱት ሃሳቦች በሙሉ እሱ እንዲያያቸው ሙዳይዋ ውስጥ ነበሩ:: እና ሙዳይዋ ክፍት ነበር፣ ባሏ ያሻው ቀን እየገባ ይወጣል:: በእነዚህ ሁለት ቃላት ('ምን' እና 'ይነጨንጨኛል') ትዳራቸው ውስጥ ለሚገባው አንቀጥቃጭ ሽብር በር እንደከፈተች ያወቀችው በኋላ ነው::

አንድ አርብ ዕለት ከሰዓት በኋላ የፈራችው ግን የጠበቀችው ነገር ሁሉ ተደረገ:: ስድስት ኪሎ ከአሜሪካን ኢምባሲ ከፍ ብሎ ያለ አንድ ሆቴል ዳዊት ይዟት ገባ:: አልቤርጉ ገብታ አታውቅም:: ተቀምጣ አልጋው ዳር ትከሻዋን አቅፏት፣ እጇን እየሳማት፣ ቅንጧን እየሳማት......*እቴ ወይኔ ልዋል፣ እቴ ወይኔ ልዋል፣ በሹርባሽ መሃል*......ሊያባብላት......ሊያረግባት እሽሟን ፈር በፈር በአመልካች ጣቶቹ እያከከላት......በራስ ጥላቻና ልታቆመው ባልቻለችው ቁሌት መሃል ልትተረተር......

ዳዊት ፀጉሩን ተቆርጦአል:: ሰልከክ ያለ ፊቱ ወንዳ ወንድ መስሏል:: ጉልህ ዓይኖቹ የፈጠጡ መስለዋል......ከሚግበሰበስ ፀጉሯ መሃል ፈልፍሎ አውጥቶ ጆሮዋን ሳማት:: አንገቷን ሳማት:: እንደ ላባ የሚለሰልሱ ጡቶቿን በአፉ አንገላታቸው:: የአዝማሪ ማሲንቆ እና ቀጫጫ የወንድ ድምፅ(የወንድ ድምፅ እንዲህ ይሰንናል?) ከሆቴሉ ጀርባ ካለ ጠላ ቤት እየተንቀለቀለ ሲመጣ እየሰማች......*እቴ ወይኔ ልዋል፣ እቴ ወይኔ ልዋል፣ በሹርባሽ መሃል*......

የሆነች አርባ ሻማ አምፖል......የተዝረከረከ ኮርኒስ መሐል የሸረሪት ድር ከቧት የተንጠለጠለች......(ዓይኖቿንም ከድና): *ያ የእኔ አንጐል ነፀብራቅ ነው:: ያ የሸረሪት ድር የአንጀቴ ትብትብ ነው......ጠቅላላ ይሔ ያጋጠመውን ወንድ*

---

102 መነሻ ሃሳብ(አ)

*የሚሰበስብ ማሕፀኔ ነው......*

ፍርሃት የተበተበው ገላዋ አልተፈታታም።

የዚያን የኮረዳነቷ ዕለት የብር አምባር ሰበረልዎ ምሽት......ባሏ ሲራክ ደረት ላይ አብራው እንደተወለደች ቆዳው ተለጥፋ አንገቱን አላባራ ባላት ስስት እየመጠጠች......ታስታውሳለች መሃላውን......*ምን ነበር? ምን ነበር በትክክል ሲራክዬ ያለው?* ዘመድና ጎረቤት ከውጭ እየጨፈረ......ፊቷን በማፈር በረዶ የመሰለ አንሶላ ላይ ለጥፋ......ሲራክ የለበሱትን አንሶላና ብርድልብስ ገፎ እያያት፡ ከማጅራቷ እስከ ቂጧ እያያት፡ የጀርባዋን ቅንፍ (መሆን አለበት)፣ ሽኩርኩር ቂጦቿን (መሆን አለበት)፣ የእግሮቿን አወራረድ (መሆን አለበት)፣ የባቶቿን እብጠት(መሆን አለበት፤ ሌላ ምን ያያል?)......'እወድሻለሁ' ያላት...... ያኔም እንዲህ እንደ አሁኑ ትንቀጠቀጥ ነበር። ምን ያመሳስለዋል? ጭኖቿ ይንቀጠቀጡ ነበር። ምን ያገናኘዋል?

ዳዊት እንደ ሩብ ሰማይ ከጊኒ ሠላጤ ዶፍ አዝሎ እንደ መጣ ዳመና ከላይዋ ይንሳፈፋል......እምቢታ ግን ከአፏ አይወጣም። እዚህ ግቢ ውስጥ የሚያውቃት ሰው ቢኖርስ? ባሏን የሚያውቅ ቢኖርስ? ዳዊት ወደ ትራሱ ሲገፋት እንደ እንጨት ከራ ነበር። ኮቱን ሲያወልቅ ሱሪውንና ጫማውን ሲያወልቅ......እጆቿን ደረቷ ላይ አመሳቅላ......አታየውም......ግድግዳ ላይ ሁለት ጣቶቹን አውጥቶ የሚያሳይ ክርስቶስ አለ......ደረቱም መሃል በእሳት የተቀጣጠለ ልብ......

ዳዊት ደንዳና ሰውነቱን እየጐተተ የቀረውን ልብሱን ሲያወልቅ ማየት አልፈለገችም። ቀሚሷን ገልቦ በቀስታ የውስጥ ሱሪዋን እየጐተተ ሲያወጣ እጆቿን ደረቷ ላይ እንዳጣመረች አልተነቃነቀችም። እግሮቿን ግራና ቀኝ ሲከፍት ግራ እግሯ ለብቻው ሲንዘረዘር አስተዋለች (ለምን ለብቻው?)። እግሮቿ መሃል ሲንበረከክ አይታው ወደ ማታውቀው ባዶ ፊቷን አዞረች። ዓይኖቿ ዕንባ አቅርረዋል። ዳዊት በሐይልና በፍጥነት ወደ ዳሌው ሳባት......

ግን እንዲህ ሲሆን የማትረሳት አፍታ ነበረች እንደ ቁራጭ የቀለጠ ፊልም አንጎሏ ላይ ታትማ የምትውለበለብ......እሷ ብቻ የምታውቃት......አንጎሏ ግራጫ ላይ እንደ ጠባሳ የተቀመጠች......እንዲህ ዳዊት በሰፊ እጆቹ ወገቧን ግራና ቀኝ አንቆ ወደ እሱ ሲስባት እጅግ ለአመል እሷ ብቻ የምታውቃት ዐይነት። ዳዊት እንኳን በልምዱ ያልጠረጠረውና መዝኖ ያልደረሰበት ረቂቅ ዕርጋታ ዳሌዋ ዙሪያ ነበር።......የሰከንድ ሽራፊ......። ዳዊት ውስጧ እንዲያርፍ የፈለገችበት አፍታ......ሲስባት እንዲቀለው እንዳይቸገር ዳሌዋን ለአመል ከአልጋው ያነሳችለት......እናም በእፍረት ሊፈርስ የነበረ ግራ ዐይኗ አሙልቆ የዳዊትን ዘንግ ያየበት አፍታ......

ማታ ቤቷ እስክትደርስ ድረስ ኩፍ ብላ ነበር። በዚህ ኩፍታ ሥር ግን ያልጠበቀችውን ዓይነት የወሲብ ደስታ አግኝታለች። የሚገርማት ይኼ ነበር። *እንደ ባሌ ሳልወደው ግን መተኛቱን ለምን ወደድኩት?*......የአጥር በሯን ከፍታ እንደገባች ሲራክ ሳያያት በሬት ጨለማ ውስጥ በልፊያ የተልቆሰቆሰ የመሰላትን

ቀሚሷንና ሌላ ልብሷን፣ ኩፍፍታዋንና ቅሬታዋን አረመች:: ቤት ስትገባ ሲራክ የረገበ ሶፋ ውስጥ ተቀምጦ ተኮሳትሮ አገኘችው::

«ምነው?» ዓይነት በአይኖቿ ጠቀሰችው

«ለምንድነው እንዲህ የምታመሺው?»

«እየሰራሁ ነዋ! ፔፐሬ እኩ ነው!»

«ሁለት ወር አለፈ ግን ምንም የለም»

«ምን ማለትህ ነው? ዝም ብሎ ይመጣል? እስኪ ልረፍ ደክሞኛል»

እልፋው መታጠቢያ ቤት ገባች:: እንደዚያን ቀን ታጥባ አታውቅም:: የዳዊትን የፀጉር ቅባት ጠረኑ ለብሰው ብታጥበው አልለቅ ብሏታል:: ግንባሯና የሆነ ራቁቷ ላይ ስራዋ የተዓፈም ይመስላታል:: ለስላሳ ጀርባዋም በዳዊት ጥፍር ኬንትሮስ የተቦረቦረበት:: በራሷ እፍራ ከባሷ ጎን አልተኛችም:: አልፎ አልፎ በፍርሐት ትንዘፈዘፋለች:: እኩለ ሌሊት ሶፋው አልመች ብሏት አልጋ ላይ ስትወጣ በእንቅልፍ ልቧ እንኳን ደንግጣ ነበር:: ሲራክ ጎን ተኝታ ቀን የሆነውን እያሰበች አንዳንድ ጊዜ ድምፅዋን አጥፍታ የመገረም ሳቅ ትፈትላለች::

*ሆን ቢቃ? እንደዚህ ፈጥኖ?......እንደዚህ ማፍጠ?*

ያን ማታ እንቅልፍ አልወሰዳትም......

ለሌሎች አይታይም እንጂ ዳዊት ሁለመናዋ ላይ በማይታይ ቀለም ተፅፎ አለ:: ጊዜዎች መጡ በፀጥታ ተቀምጣ የዳዊት የኮት ጠረን ሲናፍቃት የሆነ የሳውንደረ ኬሚካል መአዛው......ያንን እንደ ካፖርት አልብሶ አልቤርጎ ሲያስገባት......እየሳቀ እዛ ብብቱ ስር ሆና የንቃ ወንድነቱን እያየች (በምኔው?) ሲስቅ ያኮረኮረው የቦርጩ ንቅናቄ ፊቷን ሲያሻት......የተወጣጠረ እንገቱ ትዝ ይላታል ጅማቶቹ ጣት መስለው እዛም ፊቷን ቀብራ በፍትወት እየነደደች......ሲራክ እዛ ወንበር ላይ ከራት በኋላ ተቀምጦ እሷ እዚህ ሶፋ ላይ ጋደም ብላ እሱ ስለ መስሪያ ቤቱ 'አቶ ግርማ' ስለ ሚባል ድሮ ስለሚያስቃት ሰው ሲያወራ......እሷ በልቧ የዳዊት ግርማን ታስባለች፡ ተማሪ ደረጃ ላይ ክርክር ገጥሞ......ስርዐት በድቦ፣ አለም ተችቶ፣ እስቆ ሲሄድ......አልጋ ዳር ራቁቱን ጭገራም ደረቱን እንደ ታርዛን እየደበደበ ስትስቅለት......ባሏ ያወራል ስለ ግርማ......እሷ አጎንብሳ ስትስቅ እግሮቿ በናፍቆት በእሱ በዳዊት ናፍቆት ለፍትወት እየረገቡ......ስለ ግርማ ሲራክ እያወራ እያለ......

ትሬንታ ኳትሮ በአጠገቧ ሲያልፍ እሱ ዳዊት ነው......እያንጋራ

ቅዳሜና እሁድ ጭንቅላቷ በናፍቆት ይነዳል......

ሰኞ በጠዋት ባሏ ለስራ ሲሄድ እሷ ካምፓስ ዳዊት ከመኝታው ሳይወጣ...... ካጠበው ወር የሞላው እንሶላ ትንባሆና ረሻት የሚሸት......ማቃተቷ እንደተባለው እዛ ቤተ መንግስት ድረስ......

ታዲያ በእርግጥ ያለች መስላት......ለመጀመሪያ ጊዜ ምድር ላይ ያለች

መሰላት:: ከአንድ መንግስት ከሚፈራው ልጅ ጋር እየወጣች ነው:: ተማሪ የሚያደንቀው ነው:: ማርክሲስት ባትሆንም ከስር ነቀል ትተኛለች:: ቅር የሚላት ግን ሕዝብ አላወቀላትም:: ሁሉ ነገር አካሄዷን ለወጠው:: በቀስታ ግራና ቀኝ ይዋልል የነበረው የቀሚሷ ጓላ በፍጥነት መቅዘፍ ጀመረ:: አንዳንዴ ሁለት ሰዎች ማለት ሁለት ሴቶች የሆነች ይመስላታል:: ገላዋን በቁም መስታወት ውስጥ ስታይ መልካም ቅርፅዋ......ሾጤነቷ......በእፍኝ የሚያዙ እንደ ላባ የለሰለሱ ጡቶቿ......ምንተፍረቷን የከበበው የሚፈልቀው የዞማ ደሴት ከነ ልሳኑ.....የአንገቷ አተካከልና የጉንጮቿ ስርጉድ.....*'ሲራክ የተማበቀብኝ ለዚህ ውበት ይሆን?'* አለች:: ሎጋ፣ ዠርጋዳ የነበረው ባሷ የዳዊት ቀልጣፋነት ሲጠጋው ቀርፋፋ ገልጃጃ ሆነባት:: ያሻትን ወንድ ዳዊት ባሳያት ውበቷ ማሰገድ እንደምትችል ገባት:: ይኼ ለስላሳ ቆዳ ብዙ ሻካራ ወንዶችን ማቅለጥ እንደሚችል ተረዳች:: ታድያ ለምንድነው ዳዊት አንዲት ቀን እንኳን ያለ እሷ ማሳለፍ የሚከብደው? ለምንድነው በወሲብ ሰዴቻው የሆቴል ሕንፃ ሊንድ የሚደርሰው?

እየተፍነከነከች ያገኘችውን እጇ የገባውን መፅሐፍ ይዛ ከቤት ትወጣለች:: ......*መሂድ መሂድ አለኝ መንከልከል መንከልከል......ያ የማይጠፋ አዝማሪ::* እየተፍነከነከች (ቀሚሷን ሁሉ አሳጥራ ፀሐይ ደርሶባቸው የማያውቁ ጭኖቿ፣ የሚላሱ የማር ዘንጐች መስለው መፃሕፍት ቤት ትቀመጣለች)......ወይ በችኩላ እርምጃ ወደ ወንዶች ዶርም[103]......*ባገርህ ጎዳና በዚያ በሸርተቴ፣ እጥፍ ዘርጋ እያለ መጣልህ አንጀቴ*......አዝማሪውን ትሰማለች ወይስ ሽክላ ነው? እንዴት ቀላል ነው?......ከካምፓስ ሁለተኛ መግቢያ በስተግራ ቤተክርስቲያኑ ሳትደርስ ጥላ ስር ደብተር ጭኗ ላይ ዘርግታ......*አይጠቀለልም ቀን እንደ መጫኛ፣ ጠበበኝ ጨነቀኝ እኔ አንተን ማግኛ*.....አዝማሪው ከአየሩ ጋር የትም አለ:: ዳዊት የዕንቁላል አስኳል ውጦ ይመጣል......*መምጣቴ መች ቀረ ልቤ አጥር ዘሎ፣ ካረፈብኝ ወዲህ የልብህ አሉሉ::* ባልገባት ምክንያት እሱን ከቀመሰች በኋላ ገላዋ ውስጥ ያለው ሚስጢር አንጓት::

ሦስት ወሮች ሙሉ እንዲህ ሆነ::

ሲራክን ማሳረፊያ፣ መመልከቻ ቦታ አልነበራትም::

ውስጧ ጠርጋ ያዘጋጀችው እሱን የሚሰበስበው መከዳ ላይ ዳዊት በግዙፍ ገላው ተንዠርጎ የተቀመጠ ይመስላታል......

ዳዊት ሁልጊዜ ወደ ቤቱ ለመሄድ (እሱ ቀድሞ ይወጣል) ተጠናቆ ከአልጋ ተነስቶ ልብሱን እየለበሰ ወደ ታች ሲያያት......ከጎደፈ አንሶላ መሃል ልጦ ያወጣት እሾኳ ረግፎ ያለቀች አብሾንካ[104]......

ተገላልጣ ተዘበራርቃ ተነባ የወደቀች መፅሐፍ......

ምዕራፍ ዜሮ......

---

103 dormitory(dorm)= መኝታ ቤቶች ያሉበት ሕንፃ(እንግሊዘኛ)(አ)

104 ቁልቋል(ኦሮምኛ)(አ)

ቢገልጥ ቢገልጣት......ቢፅፍ ቢፅፋት ማሕፀኗ የማይጠግብ ስበት ነው......

## ማስታወሻዎች

ከሦስት ወሮች በኋላ......

በትክክል ከሦስት ወሮች በኋላ ዳዊት ጠፋ።

ብትጠብቅ ጠፋ። ብታይ በየቦታው ብትቀላውጥ፣ ታስሮ ይሆን እንዴ ምናምን እያለች አግድም ስትጠይቅ ስታስጠይቅ፣ ገላዋ እየናፈቀው..... እያቁነጠነጣት......

እንቅልፍ እየነሳት......

ጠፋ።

አስገራሚ ግን ቀላል ማሕበራዊ ሳይንስ ነበር......እሷ ያልገባት።

እንደተሸወደች የተረዳችው አንድ ሌሊት እንቅልፍ ሲጥላት ሲል ነው...... (ሌሊት ሌሊት አእምሮ በጥራት ያስባል መሰል)

ጧ ብላ ነቃች።

ጧ......

ዓይኖቿ ሁለቱም እስከ መጨረሻቸው ተበርግደው ነበር......

ከአፏ 'እንዴ?' የሚል ቃል ሊወጣ ሲፈራገጥ። ከአልጋ ተነስታ ሳሎን በውስጥ ልብስ ወዲያ ወዲህ ትላለች። ወይም ጠረጴዛውን ከከበቡት ወንበሮች አንዱን ስባ ሳታነብ ጭንቅላቷን እጆቿ ላይ አስደግፋ መፅሐፏ ላይ አፍጣ ትቀመጣለች። ማመንም ይከብዳታል። (ዳዊት ስልችታው ባይተዋት ሒያጅነቷን ምን ያቆመው እንደ ነበር አይገባትም) እንደ ንግሥት የሚያያትን፣ እንደምትሰበር ሁሉ እየሳሳ የሚነካካት ሲራክን ትታ ማንም እርጥበቱን አድርቆባት የወረወራት ፎጣ (የትም ወድቆ በሚገኝ የአዝማሪ ግጥም እየፎገራት) እንደሆነች መገንዘቧ ቆጠቆጣት።

ለገባው፣ ለጠረጠረ ከውታዋ ገፅታዋ ላይ እንደ ድርሰት ይነበባል። መዓት ዓይነት የራስን መጥላት ቁንጦች ውስጧን ወረሯት። ጠቅላላ ከጅምሩ ዳዊት ያደረገው ነገር ቲያትር መሆኑ ገባት።

ሲራክ እዛ ስድስት ሜትሮች ያህል ብቻ ርቆ ከተኛበት በእንቅልፍ ልቡ ከአልጋ እየተጉተተ ወጥቶ ፊት ለፊቷ ቆሞ ምን እንደሚረብሻት ይጠይቃታል። ይጠይቃትና 'ወረቀቱን መፃፍ ከአስጨነቀሽ አብረን እንሰራዋለን አታስቢ' ይላታል። ከዛ በርከክ ብሎ ፊት ፊቷን እያየ ቅንድቦቿን በጣቶቹ በፍቅር ስሜት እያበጠረ ሲነካት ማስታወክ ትፈልጋለች።

ዳዊት ስለ ምትፅፈው ወረቀቷ ጉዳይ ስታነሳበት......ስሟን አቆላምጦ፣ ችሎታዋን አደናንቆ (ችሎታ ይኑራት አይኑራት እንዴት እንዳወቀ እንኳን አልጠየቀችውም)፡

«በፊውዳል ህብረተሰብ ወይም በክላስ ሶሳይቲ ጀስቲስ[105] ሊኖር አይችልም:: ሪቮሉሽን ብቻ ነው ለተበደሉት ፍትሕ መስጠት የሚችለው:: ይኼ ሕገ መንግሥት ገለመሌ የሚባል ገገ. የሚገለገልበት መሣሪያ ነው» ይላታል:: ባሏ እንጀራ በወጥ ጠቅልሎ በአፏ ስፋት መጥኖ (ዳዊት ሊያደርገው አይችልም) ሊያጉርሳት ሲያነሳ አይኖቹ ውስጥ የምታየውን የዋሕነት ውንጀላ ታደርገዋለች:: አብራው እየበላች ትን እንዲላት ትፈልጋለች:: በቁጭት ሳይሆን በትንታ ሞቶች እንዲባልላት......በመዲናዋ ተረት ውስጥ መልካም ስሟ ተጠብቆ እንዲኖር::

አንድ ቀን ዞሮ እንደተኛ ጀርባው ላይ ተለጥፋ ሆዱንና ደረቱን እየዳበሰች ማጅራቱ ላይ አለቀሰች::

«ምነው ቀልሽ?»

«አረገዝኩ መሰለኝ»

«እ?» በጀርባው ተገለበጠና ትኩር ብሎ አያት::

«ታዲያ......ኤ......ነይ የእኔ እመቤት»

«የምንኖረው በኪራይ ቤት ነው:: እኔ መመረቅ አለብኝ....»[106] ወዘተ......

በዚህ አባባሏ ከዕውነቱ ባትርቅም ሐጢያቷን ሊያከብደው እንደሚችል የገባት በኋላ ነው:: ያረገዘችው የዳዊት ከሆነስ? ዳዊት ደልዳላ፣ ዘለግ ያለ ጠይም፣ ወንዳ ወንድ:: ባሏ ቀጫጫ፣ ዘለግ ያለ ቀይ.....

ቀኗ ደርሶ እንደ ተገላገለች ተስገብግባ ያየችው ልጇ ጨቅላ ፊቱ ዳዊትን እንደሚመስል ነበር:: በልቅሶ ፈረሰች:: ባሏ በተሰማት ደስታ ሐያልነት ያለቀሰች መሰለው:: አዋላጅና አጃቢ ነርሶቹም::

«አዎ......የመጀመሪያ ልጅ ያስለቅሳል......አየህ......እ......» ብለው ተስማሙ:: ጆሮዋም ውስጥ እንዲህ ዓይነት የማትፈልገው የወሬ እሾህ በቀስታ ሲሰገሰግ ትሰማለች:

«ደስ የሚሉ ወጣት ባልና ሚስት አይደሉም? መታደል እቴ:: እሱ ጠበቃ፣ እሷም ጠበቃ ልትሆን ነው አሉ»

«ወይ መባረክ:: ልጁ ቅላቱ ቁጭ አባቱን ነው እኮ» (አይ ቁጭ!)

«ያቺ የማትሮኗ ቀልቃላ ፀሐፊ ይኼን ዳኛ ስታየው እንዴት እንዳደረጋት አየሽ? እንዲህ እንዲህ አደረጋት:: እሱ ዞር ብሎ ሊያያት ነው? አሳፈረልኝ»

ቀለመወርቅ ልጇን ጡት ስታጠባ ፊቷ ባዶ አየር ላይ ያተኩራል:: በነሲብ ፊቱን ሳታይ ጡት ታጎርሰውና ሰው (ባሏ ወይም ሰራተኛዋ) ሳያይዋት እስከትረካ ድረስ ታለቅሳለች:: አይኖቿ ነጋ ጠባ እንዳበጡ ነው:: ሌሊት እንቅልፍ እንደ ጣላት የሆነ ነገር ልጁን ሰርቆ ቢወስደው ወይም እንደ ውሐ ቀስ በቀስ እየተነነ ቢያልቅ ትወዳለች:: ይኼ ካልሆነም እሷ በሕይወት መኖሯ ቢያቆም ትመኛለች:: ትልቅ ጥፋት እንደሆነ ታውቃለች:: ከጥፋት ልዩ መሆኑ ደ'ሞ የሚሰረዝ

---

105 class= ክላስ (መደብ) /society= ሶሰይቲ(ሕብረተሰብ) /justice= ጀስቲስ(ፍትሕ)(እ)

106 ለመጋባት ብለው እሱ ትምህርቱን አቁሞ ስራ ይዞ ነበር::

የሚደለዝ ጥፋት አለመሆኑ ነው::

ጭኗ ላይ ይጠባል ይጫወታል ያለቅሳል:: እዚህ ነው::

የበቀል ስሜት ተነሳባትና ('በቀል'[107] ነው ማለቷ ራሱ ግራ አጋብቷታል) ከሁለት አመቶች በኋላ የማትረብሻት ሴት ልጅ ወለደች:: 'ታደልኩ' አላት ሲራክ:: 'ኮረሪማ' አለቻት ስሟን......የትዳር ወጧን ብታጣፍጥላት:: ቆይቶ ስራ ይዛ ልጆቹ እያደጉ እያሉ......እነ ዳዊት የሚፈልጉት የለውጥ አብዮት ፈነዳ:: የእነ ዳዊት:: የትም የማያደርሱት እሽኮለሌ እንደሆነ ውስጧ ይገባታል:: ለዳዊትና ለመሰሎቻቸው ቀለመወርቅ የመጀመሪያ አገራቸው ነበረች በዱርዬነታቸው የሰቀሏት:: ተረጋግቶ እልቧ የተቀመጠውን ፍቅር በድለላ፣ በቅጥፈት ጎነታትለው ያፈረጡ:: የትም ሳያደርሱ ውስጥዋ ሰምጠው እንደ ተምች የሚቆረጥም ነገር የከተቧት:: ከሁሉ፣ (በተለይ ጭር ባለ ቀን፣ በጨለመ ፀጥታ ጋደም ብላ ስታስብ......) ከሁሉ ከሁሉ ያቺ የመጀመሪያ ቀን ከዳዊት ጋር ሲተኙ በመግደርደር መሃል ያደረገችው ፈቃድ አሰጣጧ ይቆጫታል......ያቺ የሰከንድ ቅዳጅ......ዳዊት ሲስባት በቀስታ ዳሌዋን እንዲቀለው ያቀበለችው......በተከደነው ግራ ዐይኗ አጮልቃ ያየችው አፍረቱ.......ያ ምስል እስከ ዛሬ አለ......ያ ምስል አብሯት ከባሏ ጋር ይተኛል......በቅዝቷ እየመጣ እንደ ከባድ ጉም ያርፍባታል......ያ ሰርጎ ገብ ምስል እንደ እመቦቲቶ ስጋ ሕይወቷ ዳቦዎች መሃል በራሱ ፈቃድ ብቅ እያለ ይመሰጋል......

ያበሳጫታል......

ለምን!? ለምን? ለምን? ሁሌ ለምን? ለምን?

አንዳንዴ ባሏ ሲራክ ያደገ ወንድ ልጁን ትኩር ብሎ ያየውና:

«ቀልሽዬ እኔን አይመስልም ይኼ ጠጣ:: ከዘመዶችሽ አንዱን ምናልባት» ይላታል::

አያት ድረስ ይዘመታል::

አላርፍ ያለ ማሕፀን......

አላርፍ ያለ ደንቆሮ ማሕፀን......

አላርፍ ያለ ደንቆሮ ማሕፀን ዲቃላ ቆንጥጦ ይመጣል......

አንድ ሰሞን......ሁሉ......የተረሳ የመሰለው ነገር ሁሉ......በልጇ የዳዊትን መሰል አሳሳቅ ይቀሰቅስና ወይ በዓይኖቹ አገላለጥ ይነቃቃና.....በእስፐሮ ልታባርረው የማትችል ራስ ምታት ጠቅላላ አናቷን ቆልፎ ይይዘዋል:: ሁለመናዋ ይደከመዋል፣ አንጎሏ ማሰብ ያቆማል:: መናገር ትጠላለች::

ይሄን ሁሉ የሚያከብደው ሲራክ ለእሷ ያለው ፍቅርና ስሜት አለመለወጡ ነው:: ይሄ ይገርማታል፣ ይሄ ያሳፍራታል:: ፊቷን ሲዳብሳት የገፅዋን ብልቶች እየነጠለ እየነካ እየሳመ ሲያቆላምጣት.....ጢሙ አንገቷን ሲዳስሳት......በእንሶላ

107 በዚህ የቃል አመራረጥዋ ለራሷ 'ሁለትነትን' የሰጠች መሰሏታል(ወንጀል ሰሪና ወንጀል የተሰራባት)

ስር ዘንበል ያሉ ያጠቡ ጡቶቿን ዕድሜአቸው በመግፋቱ ሳይንቃቸው በለሆሳስ እያገላበጠ ሲስማቸው፣ ሲጨብጣቸው፣ ሲለቃቸው የከረረ ጫፋቸውን እንደ ዘቢብ ሲመጥ፣ በረዣዥም አጥንታም እጆቹ የስብ መቀነት የለበሰ ወገቧን አቅፎ እግሮቿን ግራና ቀኝ እንደ ልጅነቱ በሰከረ ስሜት ሲከፍት......ማልቀስ ትፈልጋለች:: ሲያቆላምጣት እንኳን የምታውቃቸው የለመደቻቸው ቃላት ያስፈሯታል:: ልቧ በእሱ ፍቅር ገና ረግረግ በነበረ ሰሞን......እንደ ቄጤማ ያረጋት ጊዜ፣ አዲስ የጫጉላ አንሶላ ላይ ቆዳቸው የነደደ ሰሞን......ከአፉ ቃሎቹ ሲወጡ ውበቱ እኩያ አልነበረውም......እንደ ክታብ ፅሑፍ ሴትነቷ ወደ ገነት ይተረተር ነበር......ባይነጋ ትወድ ነበር::

ያ ሁሉ፣ ያ በማማሩ የሚያሳዝነው ነገር ሁሉ፣ ዕውነተኛ ባልሆነ ወሬኛ፣ ፈጣን ባልሆነ ቀልቃላ ተበላሸ:: ሲራክ 'ቀልሽ' 'ቀልዬ' እንዳይላት ትፈልጋለች:: 'ቀለሃ' ማለትም ይመስላታል--ያላትን ባሩድ ጀርባው ላይ አርከፍክፋ......

ገና ገላዎቻቸው ሲነካኩ በልቧ «ጌታዬ ጌታዬ አታቆላምጠኝ» ትላለች:: ተከናንበው የጠራቸው የቁልምጫ ስሞቿ ዛሬ ድረስ ጭኖቿ ላይ ተጣብቀው ጠባሳ የሰጧት ይመስላታል፤ ደረቷ ውስጥ ቃር ሆነው የገቡ፤ ወደ ሆዷም ቁርጠት መስለው፤ ደ'ሞ ብታጥባቸው የማይሄዱ በደረቅ ሌሊት እንደ አልቂት እየተሳቡ ከጡቶቿ ስር ደም የሚመጡ የአንሶላና የብርድልብስ ብናኝ ሆነው፤ ጠረጴዛው ላይ ጨርቅ ለብሰው የፈሰሰ ውሃ መስለው ክርኗ ላይ እከክ መስለው ሊወጡ:: የየዋሕ የማይሞት አፍቃሪ ትኩረቱ ስቧት አንገቱን አቅፋ (ዓይኖቹ ዓይኖቿን እንዳያዩና ምናልባትም ሙሴው ዳዊት ብሌኗ ውስጥ ለዘላለም የሚቆይ ፎቶ ግራፉን ትቶ ሂዶ እንደሆነ እንዳያይባት) የቤታቸው ነጭ ጠፈር ላይ አፍጣ የባሏን የፍቅር ግርፊያ በማይጠግብ ስሜት ትቀበላለች:: ያላበው ጀርባውን እየዳበሰች የትም እንዳይኼድባት ታባብለዋለች:: 'ፍቅርህ ገደለኝ' ትለዋለች:: መኝታ ቤታቸውን በልቅሶ 'በአትተወኝ' 'በአንድ ነገር አድርገኝ' በአሳፋሪ የወሲብ ቃላት ትሞላዋለች......ይሔ ሁሉ ግን የተጠቀጠቀባትን እረንቋ አጥቦ አያወጣላትም:: በአጭር ጊዜ ለከሰመ ወሲብ ለዓመታት እንዲዘልቅ የተመኘችው ትዳሯን እንደለወጠች ይገባታል::

ተርጓሚ የለውም እንጂ ይኼ ሁሉ ታሪክ አፍንጫዋ ስረሰር ላይ ማድያት ሆኖ ተፅፏል:: እንደ ሃይሮግሊፊክስ፤ እንደ ኩኒፎርም ቢነበብ ማድያቱ ድርሳኗ ነው......

ሲራክ አተኩሮ ያያትና እንዳንዴ፡

«ቀልዬ ፊትሽ ጥርት ብሎ አምሮ አፍንጫሽ ላይ ያለው ማድያት አይገርምም? ዝም ብሎ የተለጠፈ ይመስላል» ይላታል

«የደም መደፍረስ ነው:: ውሃ አልጠጣ:: ውሃ ብጠጣ እኮ......»

ከአንድ ውሸት ቀጥሎ የሚመጣው የውሸት ሰልፍ ያስገርማታል:: ውሸቶች ዝርያቸው አንድ ነው እንዴ? የወሲብ ይሁኑ የሌላ......ቅጥፈቶች ተጠራርተው ይሰበሰባሉ?

ንስሐዋን ስፋትና ጥልቀት ለመስጠት ኮሌጅ በሰለጠነችበት ትምህርት የያዘችውን ስራዋን አቁማ ጠቅላላ ገረዱ መሆን ፈለገች:: ውሳኔዋን ለሲራክ ስትነግረው ጥቂት ቀናት ተከራከረና ደስታዋን ላለማበላሸት ሲል ብቻ እሺታውን ሰጣት:: ከጠዋት እስከ ማታ ትዳሯን ያቆመች የወጣላት የቤት እመቤት ሆነች:: ወገቧን ታጥቃ ልጆቿን ስታበላ፣ ስታጠጣ፣ ስታጣጥብ፣ ስታለብስ፣ ስታስተምር፣ ስትቆጣ፣ ስታጫውት......ንስሐ እንደ ገባች በዚህም ምህረት እንደ ወረደላት ቆጠረችው.........

......ዛሬ ቅዳሜ በርበሬ ስትቀነጥስና ስትወቅጥ አእምሮዋ ውስጥ ያለው ዳዊት በጮሌነቱ፣ እሷ በደካማነቷ የተዉት ዲቃላ ወይም የልጅ ቁስል ወይም በማድያት የተሳለ ማንም የማያነበው ማስታወሻ ሳይሆን በራሷ ስርዓት የከሸነችው፣ ምላስ ላይ ሲያርፍ ጣዕሙ የሚያስክር ድልህ ነው:: ሠፈረተኛና ዘመድ ጠያቂ ሁሉ አበክሮ የሚያነሳው የቅመማ ጥበብዋን ነው:: ባለቤቷ ሲራክ በራሷ ተነሳስታ የፈጠረችውን እስከ ዛሬ በከተማው ተስተካካይ ያልተገኘለትን ሾላፍ[108] የተባለ ምግብ በሳምንት አንዴ ካልበላ ቢያንጫንጨው አይገርምም:: ባለ

108 ሾላፍ(ሾላ ፍርፍር)

(ለፀደይ መፅሔት የተላከ ከሰባት ገፅ ዕሑፍ ላይ ተቀንሶ የወጣ:: በመፅሔቱ መታተም መቆም ምክንያት ሳይወጣ የቀረ:: የፅሑፉ ባለቤት ቀለመወርቅ ፈይሳ)

'ኢትዮጵያ እንደ አገር ብዙ ተገጥሞላታል:: ስፋት ያላቸው መልካምድሮቿ ተገልፀዋል አባይ፣ አዋሽ፣ ዳሽን፣ የኢሊባቡር ደኖች ወዘተ......:: ግን ስለ ሾላ ዛፍ ተገጥሟል? ፖለቲከኞቻችንና ከያኒዎቻችን ዝርዝር ይፈራሉ:: ይመስለኛል:: በጥንት ጊዜ ሮም ታላቋ ካርቴጅን ለሾላ ፍሬ ብላ ወራለች:: ጦረኛው ጄኔራል ካቶ ከጋቢው ስር ሾላ አውጥቶ (ዝርያው ከእኛ አገር ይለያል) ለተሰበሰበው የሮም ሴኔት እያሳየ: «ካርቴጅን የምፈልጋት ለዚህ ነው» ብሎ እንደተናገረ ተመዝግቧል:: እኔ ስለ ሾላ ሳወራ እንደ ማንኛውም ሰው በአእምሮዬ የሚመጣው ልጅነቴ፣ ደንና ባላገር ነው:: የአዲስ አበባ ከተማ አይደለም:: ሾላ ሲነሳ ሁላችንም በትውስታ ወደ መጣንበት ገጠር እንመለሳለን:: የሾላ ነገር ሲነሳ በትውስታ ዕውቀት ውስጥ በየቦታው ነን፣ የተበታተንን ነን:: ይሄ የስነ ልቡና ክፍተት ነው:: ይሄ ደካማነት ነው(......) አዲስ አበባ ቅኝ ገዢዎች የሰሯት ከተማ አልነበረችም:: አጀማመሯ አገርኛ ነበር(......)ከጥንት ጀምሮ ሾላ በተለያዩ አገሮች ለምግብነት ይውል ነበር:: በእነዚህ አገሮች ዛሬም እንደዛ ነው:: እኛ ሾላን ከጥንት ጀምሮ እናውቃለን:: አዲስ አባን የሰሯት መኳንንቶች ሾላን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: በአብዛኛው ከተማዋን የሰራት የአማርኛና የኦሮምኛ ተናጋሪ የገበሬ ሰራዊት ባህሉ ውስጥ የሾላ ዛፍ አድባር ናት:: ከመበላት አልፋ በሃይማኖት የእምነት ባህል ውስጥ ተዋቅራለች:: የማንቦት ልደታ ዋናው ክሱት ምሳሌ ናት:: ጥያቄዬ ሌሎች አገሮች እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቀው እንዳንዶቹም ከሃይማኖት አላቀው አለም ንግድ ውስጥ አስገብተው ሲከብሩበት እኛ ለምን አላደረግነውም የሚል ነው:: ይሄ ውስብስብ ጎዳና የሚወስድ ጥያቄ ነው በተሟላ እንመልሰው ብል:: ያውም አቅሙ ካለኝ:: በዚህ የሐይማኖት ጠቢባን፣ የታሪክ ጠቢባን፣ የማህበራዊ ሳይንስ ጠቢባን እንዲረዱኝ እጠይቃለሁ:: ግን ሊያስኬድ የሚችል አጭር መልስ ልስጥ:: ለምን ዘመናዊ ሁኔታ ውስጥ ሾላን አላስገባናትም ነበር? መልሱ ማንነታችንን ስለረሳን ነው(......) አንድ ቀን ጋዜጣ ላይ አፋር ሽለቆ ሃዳር የተባለ አካባቢ (በኋላ ድንቅነሽ የተገኘችበት) አርኪዮሎጂስቶች 12 ሺህ አመት ዕድሜ ያለው የሾላ ፍሬ አገኙ የሚል አነበብኩ:: ይሄ በሬድዮና በጋዜጣ ከማንም የተጋራሁት አጋጣሚ ነው በልቦናዬ የሾላን ነገር የቀሰቀሰብኝ:: በበነጋታው ዜናው ጋዜጣ ላይ ከወጣ በኋላ ነው ጉዳዩ የቀልድ አጃቢ ሆኖ እየተሳቀ የተረሳው:: ዛሬ ስለዚህ ግኝት የሚያውቅ የለም:: እኔ ግን ሾላን ማጥናት ጀመርኩ(......) በአገራችን ብዙ ዐይነት የሾላ ዛፎች አሉ(......)የሳበችኝ ሆለታ ከተማ መግቢያ በስተምስራቅ የተወለድኩባት መንደር ውስጥ ከልጅነቴ ጊዜ ጀምሮ የማውቃት ሾላ ናት:: ወደ እዛ ሄድኩ:: አንዳንድ ነገሮች ለማወቅ ከመጀመሪያው መምጣት ስለ ነበረብኝ ነው(......) ይህቺ ዛፍ በሳይንስ **ፊከስ ሳይካሞረስ** (ficus syacamorus)ትባላለች:: ያተኮርኩት በዚህ

ጠጅ ቤቷ እትዬ አቦል ያን ዳገት እየተጎተቱ ወደ እሷ ቤት ሲወጡ ለሌላም አይደለ ትኩስ ጤፍ እንጀራ በድልህ ሊበሉ ነው:: ያለፈው አመት የሁዳዴ ጦም የሱፍ ፍትፍት የተላከላቸው አቦል ከትንሿ እህታቸው ከበረካ ጋር በልተውት ዛሬ ድረስ ሁለቱም የሱፉንና የቀልሽን ስም ያነሳሉ:: በረካ ኩሩ ብትሆንም ቀለመ ወርቅ ቤት ድረስ ሄዳ፡

«ባለቤቴ መስኮት ሱፍ ይወዳል ግን እንዳንቺ ያማረ መስራት አልችልም አባክሽ እህቴ ልውሰድለት መፈትፈቻ ስጪኝ፣ እናም እልበትሽን እንዴት እንደምትሰሪው አሳዪኝ» ስትላት የሚገርመው አይኖርም:: ፍትፍቱን በልቶ ልቡ የጠፋው ባለቤቷ አርቲስት መስኮት ገረሱ ብድር ሊመልስ ቀለመወርቅን በትልቁ ስዕል ስሏት አዲስ አባ ማዘጋጃ ቤት ሕንፃው ፊት ለፊት ሰቅሏት ነበር:: (የስዕሉ አርዕስት *እመቤት ውሻግራ*[109] የሚል ነው:: የኪነጥበብ ሐያሲውና

---

ስም በምትጠራው ያሳደገችኝ ሾላ ላይ ነው(......) በትክክል የሾላ ፍሬ የአበቦች ስብስብ ነው:: ማለት እውጭ በዐይን እየታዩ ማበብ የነበረባቸው አበቦች ይታጠፉና በራሳቸው ላይ ይከደናሉ:: ሾላ ፍሬ ከፍተን እውስጥ ስናይ የምናያቸው ደቃቃ ጥቋቁር ነገሮች አበቦች ናቸው:: አበቦቹ ታጥፈው ፍሬ ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ አይከደኑም፤ በሳይንስ ኦስቲኦል (ostiole)የተባለች ደቃቃ ቀዳዳ ይተዋሉ:: ድቀላ የሚካሄደው በዚህች ቀዳዳ በሚገቡ በተለምዶ ቁጫጭ ብለን በምንጠራቸው በጣም ትንንሽ ተርቦች ነው(......)አሰራሩ ቀላል ነው:: ለብቻው ሾላን የመብላት ልማድ እንዲኖር ሳይሆን በየቀኑ የተለመደው ምግባችን ውስጥ እንዴት ማዋቀር የምንችልበትን መንገድ ነው የፈለግሁት:: 'ሾላፍ' ማለት በመልካም በርበሬና ቅቤ የተሰራ ፍርፍር ውስጥ በርጥብ ስጋ ወይም በቋንጣ ፋንታ ሾላ የሚገባበት ነው:: እሷንም ለመስራት(እንደ እንስት ነው የምጠራት) ከዚህ በታች ያሉትን ነገሮች እናድርግ፡

1/ለአንድ እንጀራ ቢያንስ አስር የሾላ ፍሬዎች ያስፈልጉናል

2/የበሰሉ የሾላ ፍሬዎች መርጠን እንወስዳለን (ቢጫ ወይም ቀይ)

3/እንከፍላቸውና የውስጣቸውን ጥቁር እንገፋለን:: የምንከፍላቸው ለአራት ወይም ለሁለት ነው::

4/የተቆራረጡትንና የተገፈፉትን ሾላዎች ፀሐይ ላይ እናሰጣለን:: ኮቸሮ እስኪሆኑ ይደርቃሉ(sundried shola)

5/ከደረቁ በኋላ ለብቻቸው በሚበቃ ቅቤ ወይም ዘይት ይጠበሳሉ::

6/እነዚህ የተጠበሱት ፍርፍር ወጥ ውስጥ ገብተው በመጠኑ ወጡ እንዲመዘምዛቸው ይደረጋል:: (ከአምስት እስከ አስር ደቂቃ) ሟሙተውና ተልቆስቁሰው እንዳይጠፉ መጠንቀቅ አለብን::

ይሄ ከደረሰ በኋላ በእንጀራ ይፈተፈታል:: ሾላፍ ይባላል:: የሾላ ፍርፍር ማለት ነው:: ባለቤቴ ይሄን ከቀመሰ በኋላ ቋንጣ ፍርፍር የሚባል ቀምሶ አያውቅም(......) ለእርሻ የሚሆን መሬት ያስፈልገናል:: የመሬት አዋጅ ከታወጀ ገና ሳምንት ስላለፈው ይሄ አዋጅ ለእኔ እቅድ ምን ያህል ጆሮ እንደሚሰጥ አላወቅም(......)ሃሳቤ ትልቅ የፍራፍሬ ኢንዱስትሪ ለመቋቋም አይደለም:: የሾላን ነገር አንድ ግብ ለማድረስ ብቻ ነው(......) የሾላ ዛፍ እህቴም እናቴም ናት:: ወደ ተሰደድኩበት ወደ ከተማ እመጣታለሁ:: ባለው ነገር ላይ አልተረባረብኩም::

109 (......)የመጀመሪያ አርዕስቱ 'እመቤቴ ሆይ እገሊት' ነበር:: 'እገሊት' ያልኩት የሴትዮዋን ስም ለመተካት ነበር:: ሴትዮዋ ስሟ እንዲወጣ ፈቃደኛ አልነበረችም:: የመልኳ በደንብ አለመታየት ከእሷ የተሰጠኝ ሃሳብ ነው:: ለምን መሸሸግ እንደፈለገች ስጠይቃት ምን ማለቷ እንደሆነ ባይገባኝም 'ለሁላችንም ይበጃል ብዬ ነው' አለችኝ:: (ከመስኮት ገረሱ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ)
አለማየሁ ሌንጮ(አርታኢ) <u>ከባህላዊና ዘመናዊ የኢትዮጵያ ያሳሳል ፋናዎች፡ እስር ቃለ መጠይቆች</u> አአ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት 1970:: ገፅ 34፡

የቀልድ ወግ ፀሐፊው ሙሉነህ ልኡል ስዕሉን በሚመለከት ሰፊ ዘገባ አቅርቦ ነበር[110]) ያ ሙያዋ ተፈጥሮ ውስጥ፣ ሕይወቷ ውስጥ እንደ አየር ይፈሳል::

---

110 «ስአሊ መስኮት ከብዙ ጊዜ በኋላ ከአደባባይ ጠፍቶ ሲመለስ ለየት ባሉ ስዕሎች ብቻ መሆኑ ሳይሆን በተሟላ ስሜት ነው:: ሁለተኛው መደብ ስዕሉ ***እንደኛ 18*** የተባለው ***እመቤት ውኸግራ*** (10ሜ በ 5ሜ) የተባለ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን ማራኪ ስዕል አለበት:: እመቤት ውኸግራ በስጋ፣ በነፍስ ያለች የመሰለች ቤት አዲስ አባ መሃል ቁጭ ያደርግልናል:: ስሟና ትክክለኛ መልኳ ባይታዩንም መኖሪያዋ ጨርቆስ አካባቢ ነው ተብለናል:: መሃከለኛ ዕድሜ አላት:: ሁለት ልጆች አሏት:: ስዕሉ ላይ ቡና አፍልታ ተቀምጣ ፈገግ ብላ ሲኒዎቿን ታያለች:: አስራ ሁለት ሲኒዎች አሉ:: ሁላችንም ለመጠራታችን ይሄ ቁጥር ምልክት ነው:: ሁላችን የአገራችን ሐዋርያ አይደለን እንዴ? ከሞያሌ እስከ ራስ ካሳር፣ ከጅቡቲ እስከ ካርቱም ያለ ሀባሻ ሁሉ ገና አዲስ የፈላ ቡና እንዲጠጣ ተጋብዟል:: እዚህ ብፌ ደላጋር ተቀምጨ ቀና ብዬ ወደ ቸርችል ጎዳና ሳይ ምንም ያህል ብርቅም ስርኔን የሚሰማው አምሮ የተቆላ የይርጋ ጨፌ ቡና መዓዛ ነው:: ሴትዮዋ በጥባጭ አትፈልግም:: በሰላም የምትጠጣ ናት:: ካልሆነ......:: ካልሆነ ከጀርባዋ ግድግዳ ተደግፎ የቆመ አርጌ ጠመንጃ አለ:: ውኸግራው እሱ ነው:: ውኸግራ አንፃራዊ ጥንታዊነት አለው......ተልካሻ ዘመናዊነትን ያልሰለጠነ በመሰለ ፍሬ በሚሰጥ የባሕል ቆራጥነት መቀናቀን ማለት ይመስለኛል......ሴቶቻችን ቡና መቅዳት የጀመሩት ከማንም ቀድመው ነው፣ መጠጫ የሰሩትም ከማንም ቀድመው ነው:: ይሄን ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የቡና ስርዐት የሚያበላሽ በአርጌ ውኸግራ ይቀጣል:: ይሄ ዲያሌክቲክ ነው:: የነጠረ ሰላም የለም:: አርፈህ ቡና ለመጠጣት ከፈለግህ ውኸግራህን ከጎን አስቀምጥ ማለት ነው:: መስኮት ገረሱ ይሄን ያስብ አያስብ አላውቅም:: ኪነታዊ ስራ ሳይ ማህበራዊው ጻራ ይመጣብኛል:: ሰላም ያለትጥቅ የለም:: አሳዛኝ ነው:: ግን አለም እንደዛ ነው:: ከሴትዮዋ ጀርባ ያለው ግድግዳ ላይ መስታወት የመሰለ ነገር አለ:: እዚህ መስታወት ውስጥ ተራሮች፣ የሰው ምስሎችና የሚፈሱ ሰማያዊ ወንዞች አያለሁ:: የተዝናናች የመሰለችው ይህቺ ሴትዮ ብዙ ሃላፊነት ያለባት ትመስላለች:: ይሄም አልረበሻትም:: ወደ ላይ በተዘረጋ ግራ እጇ መሃል የሾላ ፍሬ ይዛለች......ይሄን ብሉና ቡናውን ጠጡ የምትል ይመስላል......ስዕል ነውና እስከ ዘላለም አንበላውም......እሱን ካልበላን ቡናውን አንጠጣም በዚህ መስኮት ፈተና ሰጥቶናል.....ለምን የሾላው ፍሬ ቀለም የጡቶቿን መሰለ? የአዲስ አባን ኗሪ የመሰጠው በተለይ ወንዶችን የሴትዮዋ መልክ ነው:: ፊቷ ባይታይም ጡቶቿ ግን የዕውነት ያሉ ይመስላሉ:: ቆሞ የማያያት የለም:: ስዕሉን ሳይ በሁለመናዋ ተመኘኋት:: ቡና ለመቅዳት ያነሳችው ክንዷና ፀጉሯ ማርኮኛል:: ከሁሉ የሳቡኝ ግን እንደ ሌሎቹ ኢጆሌ ሻገር የጡቶቿ ትልቅነትና(በማካፈያቸው ውስጥ ጨረቃ ተደብቃለችን?) እነሱን የጋረደው ሸማ ንጣት ነው(ለመሆኑ በምን ቢታጠብ ነው እንደዛ የነጣው?):: ልጅ ብሆን ተመኘሁ:: ልጅ ሆኜ ከነዛ መጥባት ተመኘሁ:: ከዚያች ሴት ጡት የጠቡ የተመረቁ ናቸው:: ያቺ ሴት ጡቷን ይዛ የረገመችው የበቃው ነው:: ይህቺን ሴት አይቶ ሰው ሞትን ቢሸሽ አይገርመኝም (እንደ ደራሲ ስብሐት ያዲስ አባ ተረቶች ገፀባሕርያት እንደ እጋፋሪ እንደሻውና እንደ ልጃቸው አላዛር):: ሴቶቻችንን መስኮት በአዲሱ ስራዎቹ ወደ ሕሊናችን አምጥቷቸዋል:: የዛሬዋ ልዩ ናት:: ልዩ የሚያደርጋት የጠራ ቡና ከፈለግሽ ተኳኳዪ፣ የጠራ ቡና ከፈለግሽ ሐብታም እግቢ፣ ወዘተ ዐይነት መልዕክት የለውም:: የጠራ ቡና ከፈለግሽ ውኸግራሽን አትርሺ ነው:: ለምን የአዲስ አባ ሃያሲያን መስኮትን ጦረኛ እንዳሉት እዚህ እናውቃለን:: ግን ጦረኛነት አይደለም:: እሱ እንዳለው ጠንቃቃነት ነው:: ከቸልተኛነት እንድንወጣ ሊነግረን ነው:: ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ተራራዎቹንና ተራራዎቹ ላይ የሰፈሩትን ወገኖች እንድናስታውስ ሲነግረን ነው:: መጀመሪያ ላይ ያልገባኝ ነገር ከስዕሉ በስተግራ የሚታየው የግራ እግር ጫማ ጫፍ ነበር:: መስኮት የሴትዮዋ ትልቅ ልጅ የግራ እግር ጫማ እንደ ሆነ ነው የነገረን:: ለምን ገባ? አይነግረንም:: ግን የጫማው ምስል ሲያደናቅፈኝ ይቆይና በመጨረሻ ደጋግሜ ሳየው ከጠቅላላው ስዕል ጋር በስምረት ሲፈስ ይሰማኛል:: (ዐይንና ምቾትን ሳያቋርጥ ያደናቅፋል ያሉኝ አሉ) መስኮትን 'ወንድሜ ሆይ እንኳን ተመለስክልን እንለዋለን'» (ሙሉነህ ልዑል <u>ፈጣን ቀኖች: አንዳንድ ኪነታዊ ግንዛቤዎች</u> 1974 እአ

ትልቅ ልጁ ሲቪል ኢንጅነሪንግ ሦስተኛ አመት ተማሪ ነው። ሴት ልጁ ኮሪሪማ የሳይኮሎጂ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነች። ቀልዬ ጉልበቷን የመነዘረችው በዚህ ነው። ልጆቿ ሌሎች ድልሆቿ ናቸው። ጊዜአቸው ደርሶ በተራቸው ወደ ዓለም ይወጣሉ። ከእሷ ጉያ ሾልከው እወዲያ የጥላቻ፣ የፍቅርና ያለመተማመን ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ሲጨንቃቸው ሲጠባቸው ይጠይቋታል............

## ቃሪያና ድልህ

እና ልጁ እየፈራ እየተባ ጠየቃት......

«ከአባቴ ጋር ብቻ ነው የወጣሽው? ሌላ ፍቅረኛ አልነበረሽም?»

ቶሎ አልመለሰችለትም። ሰንባ ያቀረሩ ዐይኖቿ እንዲታዩባት አልፈለገችም። ሊፈነዳ ያኮበኮበ ለቅሶዋን እንደምንም እየዋጠች ስራ እንደ በዛባት ሁሉ ከፍ ዝቅ አለች፣ መሬት ላይ ተንበርክካ ቃሪያውን አመሰች። የሙቀጫውን ከንፈር ጠራረገች። ቤት ገብታ ወጣች። ዘነዘናዋን ይዛ ብስጭቷ ጠስ ብሎላት እንደ ቆመች፣ በሁኔታዋ ግራ የተጋባው ልጇን የበለጠ ዳዊትን ከሚያስመስለው ያደገ ፀጉሩ ጋር በሙሉ አይኖቿ ልታየው አልፈለገችም። እጆቿ ለአመል ተንቀጠቀጡ። ጀማሪ ብትሆን ኖሮ ዘነዘናው ጣቶቼን አፍዝዟቸው ነው ትል ነበር።

«በብዙ ወንዶች መፈለግ ሴትን ደስ ይላታል። የሁላችን ችግር ሙሉ በሙሉ የሚፈልገን ማን እንደ ሆነ አለማወቃችን ነው......»

«እናስ?»

«ተወኝ......»

«ሰብለ ጥሩ ልጅ ትመስልሻለች?» መልሶ አመጣባት። ችግር እንዳለበት ጠረጠረች።

«አንተ ነህ የምታውቀው። እኔ አብሬአት አልውል። ትወዳታለህ?»

«ይታወቃል?»

«አዎ። ልብህን ካዳመጥክ። ልብህን አትያዘው። ችግሩ አየህ በሌላ ሰው ጆሮ ስታዳምጥ ነው። ሌላ ወንድ ከወደዳት የሆነ ነገር ቢኖራት ነው ብለህ መውደድ። እንደዚህ የመሳሰለ። የግል ባሕልህን እይ። የስሜት ፖለቲካ ነው። እዚህ ደረትህ ሥር አዳምጥ (ጡቷን በቡጢ ገጨች)። አትሳሳትም»

«ከአባባ ጋር ብቻ ነበርሽ?»

«ሲራክን የሚሆን የለም። አባታችሁ the best[111] ነው። የእኔ ስለሆነ አይደለም። መልካምነት ደካማነት ይመስለኝ ነበር......» ከመሃል አተኩራ አየችውና ስለሚቆጫት ነገር ልታወራቸው ፈለገች። ሁሉንም ልትዘከዝክ። እንደዚህ እንደ ቃሪያ ወቅጦ ያደቀቃትን። አልደፈረችም። ሌላ ጉዳይ ቀጠለች፡

---

ቁርጡሜ ማተሚያ ቤት)

111 አቻ የሌለው/እጅግ በጣም ጥሩ(አ)

«ባደርገው የማልረሳው ቁጭት ይሆናል:: እርግማን ይሆንብኛል:: ዝም ብሎ ባል አልነበረም እሱ:: ብዙ ነገር ነበር:: ብዙ ነበር የእኔ ጌታ:: ምንም አያድርግብኝ እግዜር» አለችው:: የአነጋገሯን ጥብቀት ሰምቶ አተኩሮ አያት::

«ታድለሻል ማዘር»

ከት ብላ ሳቀች......አቋረጣት:

«ከመሃል ፍላጐት አይለወጥም? ልብ አይለወጥም?»

«ምናልባት የዚያ ዓይነት ሰዎች ይኖራሉ» ዕንባዋ ሊመጣ ይኮረኩራታል:: በራሷ አባባል እንደ ተነካች ዓይነት:: መውቀጧን ቀጠለች:: ሴቷ ልጅ ካናወዘችበት ባንና ተነሳችና ግራ እንደገባው ሁሉ ዙሪያ ገባዋን አየች::

ምናልባት በሕልሟ ሌላ ልዩ ቦታ ነበረች:: ሙቀጫ ያሌለበት ፀሐይና የሚለበልብ ቃሪያ ያሌለበት......

«የእኔ እመቤት......ውሐ አምጣላት እስኪ»

ልጁ ያኔውኑ ከተቀመጠበት ተነሣ......

እናት አካሄዱን አየች......ለስንት ሺህኛ ጊዜ::

«ሰብለ ትንሽ ትነዘንዘኛለች» አለ:: ወደ ቤት ሊገባ ሊያልፋት ሲል ፊቱ ላይ ጭንቀት እንደ አለ አየች::

«ንገራት»

«ልቤ እሺ አይለኝም:: ላስከፋት አልፈልግም:: ነገ ለምሣሌ እንገናኝ ተባብለን ነበር:: መሄድ አልፈለግሁም......አለ አይደለ እኔ እንጃ......»

«የማትወደውን ነገር ስታደርግ ከደረስክባት ንገራት:: ውስጥህ አትያዘው»

ሰብለን ይወዳታል:: ግን ልቡ እስኪጠፋ አይደለም:: እናቱን አተኩሮ አያትና ጥርሱን ሳያሳይ ፈገግ አለ:: ግራ ጉንጯ ላይ ሳማትና አለፋት:: አካሄዱ እንደ ዳዊት ነው:: በረንዳው ላይ ዘሎ ወጣ:: ጭንቅላቱን ዘንበል አደራረጉም......ጠይምነቱና አጥንቱም የዳዊት ነው::

«ነፍስህ የእኔ ናት ልጄ.....የእኔ ድልህ» አለች ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ለራሷ ብቻ እንዲሰማት:: ለምትወቅጠው በርበሬ የምታጉተመትም ይመስላል......

......ሰብለን ትቷት እንዲሄድ ለልጇ ልትነግረው ዳዳች:: በምክር ይሆናል? እንዴት ቋንቋ ልብን ይገራል? ሃሣብ እንዴት ፍቅርን ይገራል? የልምድ ሐያልነት ነው......የሚያረቀው......የሚያበስለው......

ቃሪያው ተከስክሶ አልቆ ለወፍጮ ቤት ዝግጁ ነው::

—— // ——

*በጋ 1987 ሆላንድ*

# ሁለት ተኩል የውስጥ ሱሪዎች ለአዲስአባ

## ውልታዎች

የልዑል መኰንን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት[112] እዛ' የጥቁር እንጀራ ግንፍልፍል እመሰለው መርካቶ ክፈፍ ላይ ነው የተሰየመው:: ከትምህርት ቤቱ ዋና መግቢያ በኩል ያለው ሰፊ አስፋልት ወደ መሳለሚያና አቡነ ጴጥሮስ ይዘልቃል:: በስተሰሜን በኩል በደረቅ ቂጣና በባይተዋርነት የተፈነከተ ጠላ የሚደማ የደሐ ወገን ሠፈር ነው:: በስተምዕራብ የክፍለሐገር አውቶቡስ ማቆሚያ ነው......በምስራቅ በኩል ጠርዙ በሰው ዐይነ ምድር የተዘመዘመ ጠባብ የኮረኮንች መንገድ አለ ወደ አባ ኮራን ሠፈር የሚያዘልቅ:: እዚህ አስፋልት መሃል ቢቆሙ ግንባርዎ ቀና ሲል የሚላተመው ከዘመን አመጣሽ ቆርቆሮ ቤቶች፣ ከዘመን አመጣሽ ሙዚቃ ቤቶች፣ ከዘመን አመጣሽ ጎተራዎች፣ ከዘመን አመጣሽ ቡና ቤቶች፣ ከዘመን አመጣሽ ፎቶ ቤቶች፣ ከዘመን አመጣሽ ሻይ ቤቶችና ከድንቅነሽ[113] ጊዜ ጀምሮ ከነበረው የእንጦጦ ተራራ ሰንሰለት ጋር ነው......የምንተነፍሰው አየር እንደ ልዩ ወጥ ያደርገዋል: ውስጡ በርበሬ፣ ሽሮ፣ የሉካንዳ ስጋና አጥንት፣ ሽንኩርት፣ ቅመማ ቅመም፣ ቤንዚንና የሚሞቅ ብረት ጠረን ያለበት (እንደ ኢያሱ ዓይነት ቀልደኞች 'ብረት ቦዘና' ይሉታል)......ሴላም የማልረዳው::

እዚህ ልዑል መኰንን ከመምጣቴ በፊት መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የተማርኩት ባልቻ አባ ነፍሶ ነበር—እዛው ልደታ እሳቸው ያቋቋሙት ሠፈር:: ከዛ ስምንተኛ እንማር የነበርነው ልጆች ሚኒስትሪ ወስደን ካለፍን በኋላ አብዛኛዎቹ

112 ዛሬ አዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ የሚባለው(አ)

113 በፈረንጅ ስያሜ ሉሲ:: አፋር መሬት የተገኘችው የጥንተ ሰው አፅም በፓሊኦአንትሮፖሎጂ ምደባ አስትራሎፒቲከስ አፋረንሲስ የምትባለው::(አ)

የሰፈሬ ልጆች ማርታ አላናን ጨምሮ ሌላ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲመደቡ፣ እኔና በደንብ የማላውቃቸው ጥቂቶች ደ'ሞ ልዑል መኰንን አጠቃላይ ገባን (በዕድል ይሁን በዘመድ አላስታውስም)። ከጓደኞቼ ከእንዳለ ኮሮጆ፣ ከሃና ሞሲሳ (ጎረምሶች በፈረንሳዩ ንጉሥ ሉዊ አስራ አራተኛ ሚስት ስም 'ማሪያ አንቶይኔት'[114] ብለው የቀፀሏት ቆንጆ)፣ ከለምለም ትግሬዋና ከለምለም ሠንጋ ተራ፣ ከዮናታን(አጭር በመሆኑ 'ናፖሊዎን' ተብሎ ቅፅል ስም የተሰጠው) እናም ከአየለ ጋና መዝሙሮች መለየቱን አልወደድኩም ነበር።

ልዑል መኰንን ሁለተኛ ደረጃ ከገባሁ በኋላ ባልቻ ትምህርት ቤቴ ስትናፍቀኝ አልፎ አልፎ በዚያ በልደታ በኩል እሄዳለሁ—በ'ቶቡስ የማልፍ ከኾነ እንኳን ወርጄ። ታዲያ ከግቢው ውጭ ቆሜ የረገበ ሽቦ አጥሩን ተደግፌ ተማሪ የሌለበትን ግቢ አያለሁ:

ቀይ አቧራ የሸፈነውን ሜዳ......

(ቅዳሜና እሁድ የታጠቡት ንፁሕ ሸራ ጫማዎቻችን ሰኞ ሰኞ እዚህ ላይ በሚያበሳጭ መልክ ያድፋሉ። ነጫጭ የዩኒፎርም ሱሪዎቻችን ቀይ-ቡላ ይሆናሉ)

በአርጅና የቆሸሹና የተቦረቦሩ የሕንፃውን የእንጨት ግድግዳዎች......

(ከብርድ፣ ከነፋስ፣ ከሐሩርና ከድንቁርና የጋረዱን)

ትምህርት ቤቱ ሲከፈት ጀምሮ ያዘመሙ የሚመስሉትን የእግር ኳስ ሜዳውን የጎል እንጨቶች......

(መሰረታቸው በምስጥ ጥርስ የቀጠነ)

የተገጣጠበ መሬት ላይ በአንፃር ተራርቀው የተተከሉ የቅርጫት ኳስ የብረት ቀለበት የሚሰቀልባቸውን ትላልቅ የባሕር ዛፍ አጣናዎች......

(ኳሱን ማንጠር እንደ ከበደኝ ነው የወጣሁት)

ከወዲያ ድሮ ተቀምጠን ምሳ እንበላበት የነበረው ሳር የተሸፈነው ጉብታ ዛሬ ተመልጦ በኮረት የተወረረውን......

ከዛም ጀርባ በረዣዥም ዛፎች የተጋረደው የምስጢር ድባብ የነበረው ቢልዲንግ ኮሌጅ[115]......

ብዙ ጊዜ ከቤ[116] ዘቡሌው—ከወንዶች ሽንት ቤት ፊት ለፊት የዛገ የውሃ ገንዳ ምሰሶ ተደግፎ የሚቆምበትን ቦታ......

(ያ ለካፌ ብዙ ውሃ ከጠጣን እየመጣ 'በቃህ' ብሎ በካልቾ የሚመታን—ግን

---

114 ይህቺ ፈረንጅ ቆንጆ ትሁን አትሁን ጎረምሶቹ ማረጋገጫ አልነበራቸውም። ግን ሁላችን በልጅቷ ሃናነት ሳይሆን በማሪያነቷ ተማርከናል። በዚያን ጊዜ ስለ ፈረንሳይ አብዮት እንማር ነበር(ምን አገባን?)።

115 የሕንፃ ኮሌጅ(አ)

116 እሱን ማብሸቂያ ዘፈን ነበረን። ከግጥሞቹም አንዱ ትዝ ይለኛል:
*'ጻቦ በውሐ በጣም ጠግቤ*
*ሽንቴ መጣብኝ ተፋልኝ ከቤ'*

ምን አገባው ነበር?)

ዳርማር ጫማ ፋብሪካን......

(ቆሻሻ ብለው የጣሉትን ብጥቅጣቂ ቆዳ እየለቀምን ቀበቶ እንዳልሰራን)፡ ከዚህም ጐን ያሉትን የሠላጣ፣ የድቡልቡል ጎመን፣ የካሮት የቆስጣ እርሻ ቦታ መደቦቻችን.....)

በስተደቡብ ያለው ጥቁርና ነጭ የተቀባ(ጉሬዛው) የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሕንፃ......

(ከጀርባው ዳገት ነበር፣ እላዩ ከቆሙ እስከ ቶሎሳ ሠፈር የሚያሳይ፡ ከስር ደ'ሞ ሚስጥረኛ ሸጥ ነበር ወሰናችን ላይ እባብና ሌላ አውሬ ፈርተን የማንጠጋው፣ የሽቦ አጥሩን ደፍረን ያላለፍነው......ከእዛም ዳገት ቁምጣችንን አውርደን ከግቢያችን ወደ ጉሬዛው......የሸናንበትን እርቀት ስናወዳድር......)

በነዚህ ሁሉ ውልታ ተቆንጥጬ ዕንባዬ በመንታ ዐይኖቼ ተከትሮ ሊረግፍ ይቃጣዋል:: የኾነ ምትሐት ነበረው:: ከጠዋት እስከ ማታ (ከምንደበርባቸው[117] አንዳንድ ቀኖች በስተቀር) ጨዋታ፣ ቀልድ፣ ትምህርት ብቻ ነበር:: ባልቻ ት/ቤትን ወጥረው፣ ወጥረው እስከ አስራ ሁለተኛ ቢከፍቱባት እንዴት ያለች ውብ ቦታ ትሆን ነበር? ገናናነትም ነበረባት:: በእርሻ ውድድር የአዲስአባን ከተማ እንዳሸነፈች ነው:: በጅምናስቲክ አዲስ አባን እንዳሸነፈች ነው:: በእግር ኳስ አዲስ አባን እንዳሸነፈች ነው:: ስንታየሁ ሣህሌ ባልቻ ነው:: ጂምናስቶቹ ብርሃኑና በዛብህ ባልቻ ናቸው:: የእግር ኳስ አርቲስቱ ግርማ ባልቻ ነው:: አየለ ጋና ባልቻ ነው:: ግብረገብና ሲቪክስ ያስተምረኝ የነበረው ብርሃኔ ጃርሶ ባልቻ ነው:: ባልቻ ምናልባት ዘመኑን ነበረች......ምናልባት የዘመኑ ልቡና ነበረች......

**(ስለ ምንድነው ስለባልቻ እባ ነፍሶ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትዝታ የማወራው? ስለ ምንድነው ለዚያ ዘመን ውልታዎቼ ስፌ ቦታ[118] የሰጠሁት? ጀግና ስለማፈቅር ነው? ምናልባት:: ለስልቦች ስለማዝን ነው? ከቴም:: ሕይወቴ አራት ዋና ዋና ጎዳናዎች ነበሩት:: አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ የተማርኩባቸው ት/ቤቶች፣ በጤፍ አጥግቦ ያጎለመሰኝ ጎጃሜው የባሕር ዳር ቴክኒክ ኮሌጅ'ና ስራ ይገፍ የእኔንና የማርታ አላናን አራት ልጆች እንዳሳድግ ብዙ ሳይጨቃጨቀኝ ያሰራኝ የመንግስት መስሪያ ቤት:: ከእነዚህ አልወጣሁም:: ወርደ-ስፌ ጊዜ ግን ጠባብና ጥልቅ ልምድ ነበር--የጥልቅነቱን ነገር እንጃ እንጂ:: እነዚህ አራት 'ቦታዎች' ወይም 'ጎዳናዎች' የኖርኩባቸው ናቸው:: ስለ አንዱ ሳወራ አንዳንዴ ሳላውቀውም ሆነ አውቄ ስለሌላው ማውራት እጀምራለሁ:: ይሄ 'መፍረክረክ' የበለጠ ይጠቅም እንደኾነ እንጂ የሚጎዳ አይመስለኝም:: ጥልቀቱንና ስፋቱን ባልተረዱት ፖለቲካ ነፍሳቸው ከጠፋና ሕልማቸው ከተዳፈነ አንዳንድ የዕድሜ እኩያዎቼ ጋር**

---

117 'ድብርት' የተባለው ቃል ያን ጊዜ አይታወቅም ነበር

118 ስፌ ነው እንዴ? ሁለት ገፅ 'ስፌ?' ይባላል

አነፃፅረው ጉዞዬ ብዙ ጀብዱ የሌለው 'ምስኪን' እንደ ኾነ ሁሉ ሊነግሩኝ የሚፈልጉ 'አራዳ ነን' ባዮች ይኖራሉ:: ያልገባኝን አድርጊ አላውቅም:: ለምሳሌ ማርታ ሚስቴ የሆነችው አውቄአት ነው:: ያገባኋት ባልቻ ለመማር ሰባተኛ ክፍል ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ ስለ እሷ በቂ መረጃ ሰብስቤ ነው:: በቂ ጥናት አድርጌ ነው:: (ገና ስወዳት ልጅነቷን ለማግለል......አየለ ጋና ካስተማሩኝ ጅምናስቲክ ጥቂቶቹን፣ ከስንታየሁ ሳህሌ አክሮባቶች ቀላል የሆኑትን ሁለቱን ባር ሜዳ ላይ ወስጄ አሳይቼአታለሁ:: በዚህም ተማርካለች) (ልኡል መኮንንም ስማር ዘጠነኛ ክፍል ጎኔ የምትቀመጠውን የፀሐይ ለገሰን ጠይም ውበት አየሁ:: ማርታዬንም ከእሷ አወዳደርኩ፣ በዚህም ጠይሞች የሚጋሩት ረቂቅነት ገባኝ) ከሁሉ ከሁሉ ደ'ሞ የበለጠ አፍቅሬአት ነው:: ከቤቷ ተነስታ አቶቡስ ማቆሚያው እስክትደርስ ቂጥዋን ምን ያህል ጊዜ ግራና ቀኝ እንደምታወዛውዘው ቆጥሬአለሁ:: ሳታዋኝ እንዳለሁም ሳልነግራት ከኋላዋ ተከትዬ:: ያን አስገራሚ የጎረምሶችን ፊት የጠፋ አረማመድ ስቆጥር ጊዜዬን በከንቱ ያበላሸሁና ልቦናዬ የተሰረቀ መሰሏቸው የሳቁብኝ በኋላ ፖለቲከኛ የሆኑ 'የነቁ' ወዳጆቼ ነበሩ:: ፖለቲከኛ ለምን እንደሆኑ፣ እንዴት እንደሆኑ፣ ምን እንደሚያውቁ፣ በዝርዝር ምን እንደሰሩ አሁን ስጠይቃቸው የሚናገሩት ነገር ባዶ ሊሆን ምንም አይቀረው...... ከዚህ ዓረፍተ ነገር ቀጥሎ እንዳለው ቦታ[119]

[redacted]

ለመሆኑ ማርቲ ስንት ጊዜ አወዛወዘችው ያን ነገሯን?

ሁለት መቶ አርባ ሰባት ጊዜ:: አንድ!—ግራ:: ሁለት!—ቀኝ:: እንዲያ እንዲያ እያለ::

አቶቡሱ ውስጥ ከእሷ ጋር አብረን ቆመን ስለ 'ሁለት መቶ አርባ ሰባት' ስነግራት ግንባሯን የአቶቡስ ምሰሶ ላይ አስደግፋ አፏን ባንድ እጇ ጋርዳ በሳቅ ፈረሰች:: እንዲህ ስትስቅና ልቧ ሲሰለብ እጇን ወገቧ ዙሪያ ጠምጥሜ በሳቅ የሚነሳና የሚወድቅ የሚንቀጠቀጥ ሆዷን አዳመጥኩ፣ ማጅራቷም ላይ ልቤን የሰበረውን ውበቷን አየሁ—ወዝ[120] ያዝለፈለፈው ሳሁሜ ፀጉር በአከርካሪዋ

119 ይሄን ጨለማ ቦታ አንድ አርታኢ ወዳጄ 'የብረት ዲሲፕሊን በለው' ብሎኛል::

120 'ማጅራቷ ላይ ያለውን ፀጉር የጠቀለለው ወዟ ነው ወይስ ላቧ?' ብለው በቡድን ተከፋፍለው የተከራከሩ፣ የተጣሉ፣ የተደባደቡና የተታኮሱ ጎረምሶች አልነበሩም:: ወጣቶች አንድ ሰሞን በ 'ቸ' ና በ 'ሸ' ሆሄያት ልዩነት የፖለቲካ ፍትጊያ ያደረጉበት ጊዜ ነበር:: ያን ሰሞን ከማርታ ጋር የተለያዩ ቦታዎች ጊዜው ጥሩ አይደለም እያሉ ቢያስፈራሩንም፣ እፈዘዙ የመንግስት ሆቴሎች ሄደን ኬክና ቡና ጠጥተናል:: ግንት፣ ራስ ግሬል፣ ሸበሌ ያለንን ሳንቲም ለቃቅመን የምንውልባቸው ቦታዎች ነበሩ:: እዚህ በፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፍና የማይሳተፈው ይሰበሰባል:: ከሰው ለመምሰል ብዬ አፌን አምልጦት ፖለቲካ ለመናገር ከጀመርኩ ማርታ አጠገቤ ካለች እንዳቆም ምልክት ትሰጠኛለች:: ወይም 'ምነው ችሹ ሆንሽ እንዴ?' ብላ ትተርበኛለች:: ወይም 'ልጃችን መተሻተሽ ሊጀምር ነው' ብላ ታሽሙዋጥጠኛለች:: ከመስኮት ገረሱ የቀዳችው ቃል ነበር:: ሰዐሊው ወይም

**ወርዶ:: እደግመዋለሁ: በወዝ የተነከረ ላሁጫ ፀጉር በአከርካሪዋ ወርዶ፤ እስከ አከርካሪዋ ወርዶ:: ጥቂት አሻራዎች:: በእነዚህ አራት የዕድሜዬ ፈርጣታዎች ውስጥ ማርታ አብራኝ ነበረች:: ታዲያ በዚህ በዚህ ስሌት ላይና ታቹ የእኔ ሕይወት ከተገናኘ ማን ምን አገባው ከፈለኩበት ጀምሬ እፈለኩበት ብደመድም?)**

ታዲያ ልዑል መኮንን ስገባ ቀልጣፋ አሦች የሚዋኙበት ሰፊ እንግዳ ባሕር የወደቅሁ መሰለኝ:: ተማሪዎቹ ትላልቆች ናቸው:: ደብተርና መፅሐፍ ያለ ቦርሳ ወይም ያለቀረጢት የሚሸከሙ ጢም ያላቸው ብዙ ተማሪዎች በየክፍሉ አሉ:: ታዲያ እነዚህ ልጆች (ልበል እንጂ) በሚያስፈልገውና በማያስፈልገው ጉዳይ እየጮኹ የሚናገሩ ይመስለኛል:: የትምህርቱ ብዛት ደ'ሞ ያስፈራል:: አሥር ዓይነት ትምህርት ነው የምንማረው:: ሳይንስ ሲባል ባይሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዝክስና ጀኔራል ሳይንስ፡ ሒሳብ ጂኦሜትሪና አልጀብራ አለው:: ፈረንሳይኛም እንማራለን:: ይታያችሁ ፈረንሳይኛ ስንማር:: ደስ አይልም? በዚያ ላይ የመፅሐፎቹ ብዛት:: ፈራሁ:: አስተማሪዎቹ ያስፈራሉ—ያረጁ ናቸው:: የፈረንጅ አስተማሪዎች ይበዛሉ፡ ሕንድ፣ ሲሎን[121]—ደ'ሞ አንድ አሜሪካዊ አለ—እንግሊዘኛው በደንብ የማይሰማ፡ ሲናገር የሚኰናኰን:: 'እከሌ እንግሊዘኛ ሲያወራ እንደ አሜሪካ ነው' የሚባለው እንደዚህ ሰውዬ ሲያደርገው ነው እንዴ? እል ነበር:: ሕንዶቹ የሚያስተምሩኝ ጉዳይ ላይ ሳይሆን የአለባበሳቸውና የፀጉራቸው እንግዳነት ላይ ሳፈጥ እውላለሁ:: የአገጩን ጢም የሚጐነጉን አለ:: እጀ ጠባብ (ቀሚስ) የሚለብስ አለ:: የሴቶቹ ሕንድ አስተማሪዎች ጉርድ ካናቴራዎች (ቾሊ) ብብታቸው ጋ ሁልጊዜ በላብ መጠየሙ ለእኔ ትዕይንት ነበር:: እነዚህን ሴቶች አባቴ ቢያገኛቸው፡

«ብይ አሁን ወለቅ አድርጊና እጠቢያት፣ ውሃ እናትሽን ገኋል?» የመጀመሪያዎቹን ሁለት ወሮች ወይም ሦስት ወሮች ዞሮብኝ ነበር:: ከባልቻ ትምህርት ቤት ይገፔ የመጣሁት አስተማሪን ማክበርና ቀድሞ ክፍል የመግባት

---

ስዕል ጣይው መስኮት ገረሱ በዚያን ጊዜ የሚሰራውን ፖለቲካ ስሙን 'መቸሻቸሸ' ብሎት ነበር:: 'ቸ' ና 'ሸ' በተባሉ ሆሄያት እንደሚጋጩ ዐይነት:: የግራኞች «የቀጨ ልፊያ» ይለዋል አንዳንዴ:: አንድ ተመሳሳይ ሃሳብ አስልፈው ግን እርስ በርስ የሚደባደቡትን ቡድኖች የሚጠራብት ነው:: ግለሰቦችን ደግሞ 'ችሹዎች' ይላቸዋል::
'.......ሲቷም ወንዱም 'ችሹ' ይባላሉ:: ችሹዎች አሳዛኝ፣ አስቂኝ ፍጡራን ናቸው:: ዕውቀትን ሳይሆን ሴራና ስም ማጥፋትን ንቃትና ስማርትነት የሚያደርጉ ናቸው:: መረጃ ማሰባሰቢያ ስልታቸው ሕቡዕና ስለላ ነው:: ሳይንሳዊ አይደለም:: ምክንያቱም ትክክለኛው በግልፅ፣ ምስክር ዐይን ስር በመረጃ የቆመ ሳይንስ ለቀጣፊ ምላሳቸው ይከብዳቸዋል'
'......የሃሳብ ጥራትና ተጨባጭ ልዩነት ሲጠፋ ጅሎች በተራ ሆሄ ይጣላሉ:: እጃቸው ላይ የሚቀረው ሊደነቁበት የሚፈልጉት ተራ ሞት ነው:: ይሄን ከርካሳ ነገር 'ትግል' እንድንልላቸውና እንደ መልካም ነገር በታሪክ እንድንመዘግብላቸው ይፈልጋሉ:: ሱሚ ነው:: በሚያቀጣችሁ በዚያው በፈንታችሁ ቀጥሉ'
'......ቢያውቁም ባያውቁም ለኢትዮጵያ ከባድ መቃብር በመቆፈር ላይ ናቸው:: የምንገባበት ግን ሁላችን ነን:: ኩቴም ስር ነቀል! አይ መቸሻቸሸ:: (መስኮት ገረሱ የዕውር ጉንዳኖች ሰልፍ፡ ስለ ስዕልና ስለ ማሕበራዊ ዕውነታ ጥቂት ማስታወሻዎች 121 ገፆች ቦሌ ማተሚያ 1967 እአ)

121 ዛሬ ሲሪላንካ የምትባለው አገር(እ)

የመሰሉት ጨዋነትና ስነስርዓት የሚያሳዩ ልምዶቼ ከተለያየ አቅጣጫ ትርጉም የሌላቸው ሆኑ:: ከክፍሌ ተማሪዎች አንዳንዶቹ ወሰን የለሽ ቀልደኞች ነበሩ::

ማንም ሳይጠይቀው:

«እስኪ አንዴ ዝም በሉ አስተማሪ እስኪመጣ የምነግራችሁ ጆክ[122] አለ» ብሎ ድርቅ የሚል ብልግና አውሪ አለ::

የምማርበትን ክፍል ተማሪ እንደፈለገ የሚያሽከረክረው አንድ ኢያሱ የሚባል ዘግዛጋ፣ ጢማም፣ በፈንጣጣ የተበላ የመሰለ እንጀራ ፊት ያለው ልጅ/ ሰውዬ ነው:: ኢያሱ የማይሰራው ተንኮልና ኩሸት የለም:: አስተማሪ ከሚያዘው ትዕዛዝ ይልቅ ኢያሱ የሚያዘው በተማሪዎቹ ተደማጭነት አለው:: ኢያሱ በዘመኑ መዋዕለ ነገሥት ያልሠፈረ ንጉሠ ነገሥት ሐይለ ሥላሴን የሚያስንቅ አምባገነን ነበር:: ተማሪ የኢያሱን የመጨረሻ አላማ ባያውቅም ከበሬታውንና አድማውን በዳሰሳ ይከተላል:: ለምሳሌ:

«ምን ይመስላችኋል ይህቺ ቀርፋፋ የሕንድ አስተማሪ አታስጠላችሁም?»

ከእሱ የተማከሩት ጓደኞቹ:

«አዎ» ይላሉ::

«ምን እንሰራለን እዚህ:: ሜዳ እንውጣና ኳስ እንጫወት» ይላል::

« እሺ !!» «እሺ!! » «እሺ!! »

«እሺ!! » «እሺ!! »

«እሺ!!» «እሺ!!» «እሺ!! »

ይላል ተማሪው::

«አንድ ሰው እዚህ ክፍል ይገኝና ወዮለት እኔን አያድርገኝ:: ሁላችንም ኳስ ሜዳ! ቀለሜዋዎች ወደ ላይብረሪ[123]:: ላይብረሪ የሚፈልግ ላይብረሪ ተግባባን አይደለም?»

« አዎ» «አዎ» «አዎ»

«አዎ» «አዎ»

«አዎ» «አዎ» «አዎ»

(ላይብረሪያችን ተከፍቶ አያውቅም:: የዚህም ተቋም አላፊ ወፍራም ረዥም ቀስስተኛ ሰው ነው:: የመስራት ፍላጎት ያለው አይመስልም) በዚህና በዚያ ቢል ኢያሱ ሊያዘው ያልቻለው ልጅ ታረቀኝ ኀበና ብቻ ነበር::[124]

---

122 (joke)= ቀልድ(እንግሊዘኛ)

123 (library) መፃሕፍት ቤት(እንግሊዘኛ)

124 እንውጣ ሲባል ክፍል ውስጥ ዴስኩ ላይ ተጣብቆ የሚቀረው ታረቀኝ ኀበና ብቻ ነበር:: ታረቀኝ አንገቱ ቀጫጫ፣ ቁመቱ አጭር፣ እናቱ በአፍሮው ሰበብ ሳይሆን አይቀርም ትልቅ ነበር:: ክፍል ሲገባ ሁልጊዜ ትንሽ፣ ጥቁር፣ የምትንሳፈፍ ጎጆ ቤት ቀድማው የገባች ይመስላል:: ከክፍል እንውጣ እየተባለ እያለ ከኢያሱ ወይ ከደሳለኝ ወይ ከሽመልስ

ትምህርትን በዚህ ዓይነት ብቻ ሳይሆን በተለያየ መልክ ማቆም ቀላል ነበር:: የተማሪ የፖለቲካ ገጭ ገው ይመጣና–የት እንደ ተወሰነ ባናውቅም ባይታወቅም–ቦይኮት (boycott)[125] የሚባል ነገር እናድርግ ይባልና በእነ ኢያሱ የሚተዳደረው ተማሪ ክፍል መግባት ያለመፈለግ ብልግናው፣ ሞልፋጣነቱና ደለቀቅነቱ ቁም ነገር መስሎ ቁጭ ይላል:: ትክክል ነገር ይሆናል::

**(የሁሉ ነገር ሽል አለው አይደል? ዕንቁላል ምናምን? ስለ 'ተማሪ ንቅናቄ' ሲወራና ስለ መነሻው ሲጠቀስ ከትውስታዬ ሐይቅ እየዋኘ የሚነሳው እነዚህ የድርጊት ቀለሞች የፈሉበት ባለጌ ማሕፀን ነው......)**

በግሌ ኢያሱን አልወደውም ነበር:: ቢያስቀኝም፣ ቢቃለደኝም፣ ቢኮምከኝም:: ምክንያቱም ለምን እንደሚቃለደኝ፣ ለምን ሊያስቀኝ እንደሚጥር፣ ለምን ሊኮምከኝ እንደሚለፋ ሙሉ በሙሉ ስለማይገባኝ ነው:

**(ትምህርት ቤት በተማሪ ሲዘጋ ጊዜ ነበረኝ ብዙ ከማርታ**

---

ወይ ከአንድ የእነሱ አቸፍቻፊ ጋር ከተያየ ከንፈሮቹ ላይ ትንሽ ፈገግታ እያሳየ ቀኝ እጁን ዴስኩ ጉያ ሰዶ መፅሐፍ ያወጣል:: የተዘጋጀ ይመስላል:: አንድ ቀን ከዴስኩ ስር መዞ ያወጣው 'ስንክሳር' የተባለ ትልቅ መፅሐፍ ነበር:: ኢያሱ ሁላችን እንድንሰማ በሳቅ እየተንተከተከተ ድምፁን ከፍ አደርጎ:
«ታረቀኝ የሚያነበውን እዩ፣ ሰበታ ገብቶ ከብት ሊያረባ ነው:: ስለ ሳር ያነባል:: ሹፌ!! ስሚ ተሬ! መጀመሪያ ላሚን ግዢ ስለ ሳር ከማሰብሽ በፊት ሃሃሃ!!!»
ኢያሱ ሲቀልድ ማሳቅ መቻሉን ከተጠራጠረ አጠገቡ ያለውን ሰው በክርኑ እየጎሰመ ይለምናል:: የታረቀኝ እምቢተኛነት ሲደጋገምባቸው ዴስኩ መቀመጫው ላይ ውሃ ያፈሱበታል፣ ሳያይ ተቀምጦበት በርግጎ ሲጮህ እነ ኢያሱ በሳቅ ይፈርሳሉ:: ሁሉ ተማሪ በኮፒ ሳቅ ይከተላቸዋል:: የኢያሱ ትልቁ ችሎታ ጥፋቱንና ተንኮሉን ሁሉ ጨዋታ ማስመሰል መቻሉ ነው::
አንድ ቀን እንደ ተለመደው በእረፍት ሰዓት ላይ በትምህርት ቤት ድምፅ ማጉያ ከዩኒት ሊደፉ ቢሮ ከሁለተኛው ፎቅ ግጥም ወይም ድርሰት ይነበባል:: ብዙ ተማሪ ሕንፃዎች መሃል ሆኖ በተመስጦ ያዳምጣል:: ግጥሙ እንዳለቀ ውብሸት ወርቅአለማሁ የተባለው ደራሲ በመጽሔት ላይ ያወጣው አጭር ታሪክ ደስ በሚል፣ እንደ ማር በሚጥም፣ ለስላሳ፣ ወፍራም ድምፅ ለሃያ ደቂቃ ያህል ተነበበ...... ከሕንፃው ቀረብ ብዬ ቆሜ ስለነበር በቢሮው የመስታወት መስኮት አንባቢው ማን እንደሆነ አየሁ:: ባልገባኝ ምክንያት ደነገጥኩ:: ከእረፍት ወደ ክፍል እንደ ተመለስን ታረቀኝን እንዲመጣ በጉጉት ጠበቅሁ:: ታረቀኝን ማየት ጓጓሁ......አፍሮውን አስቀድሞ በተለመደ በማውቀው አረማመዱ መሬት መሬት እያየ መማሪያ ክፍል ገባ:: ገፁ ላይ የሚያምር ድርሰት ያነበበና ብዙ ሰዎችን በድምፁ የማረከ አይመስልም:: ሐራምቤ ሸሚዝ ለብሶ ነበር:: ሐራምቤ ሸሚዝ አልወድም:: የተዝረከረከ፣ የተደፋ ቀለም ይመስለኛል:: እዚህ ሃራምቤ ሸሚዝ ላይ በአማርኛ በትልቁ፣ ከዛ ስር ደ'ሞ በእንግሊዘኛ ***[illegible]***'የሚል ፅሑፍ ነበር:: ***[illegible]*** ትርጉሙን አላውቅም:: ለዘላለም ባላውቅ ግድ አልነበረኝም:: ድርሰቱን ሲያነብ ሳየውና ስሰማው የደነገጥኩበት ምክንያት የመንፈስ ቅናት እንደሆነ ገባኝ:: በየትኛውም አቅጣጫ ይሄን የቅናት ስሜት አላውቀውም ነበር:: በዚህ ድርጊቱ ታረቀኝ ከሁላችን የበለጠ እንደ ሆነ ገባኝ:: በጥቂት አጋጣሚዎችም(ያንን ቀን ጨምሮ) ኢያሱ ታረቀኝን ሲያየው እንዳላየው ሁሉ ዓይኖቹን ሲመልስ አየሁት:: ማንም ሳይገባው ኢያሱ ታረቀኝን እንደ ሚፈራው ገባኝ:: በነኢያሱ እንደ ከብት ከሚነዱት አንዱ ነበርኩ:: ከተማሪ ረብሻ ተገልሎ የሁላችንን የእረኛ ትርምስ የናቀው የታረቀኝ ወንዳታነት ዛሬ ድረስ ትዝ ይለኛል::

125 ማቆም፣ ትቶ መሄድ (ትምህርት አለመማር)

**አላና ጋር ለመላፋት፣ ለማጥናት አንዳንድ የዚህ ዐይነት ልቦለዶችን ለማንበብ። ቆይቶም በቦይኮት ሰፈሬ ውስጥ በተከደከድኩበት ዘመን ነው የጎረምሳ ከንፈሮቼ በማርታ ከንፈሮች የሰለጠኑት። ለዚህም እነ ኢያሱን አንድ ሰሞን አመስግኜአለሁ። በዛች የሁለተኛ ደረጃ የቦይኮት ዘመን ባልቻ አባ ነፍሶ ሰማር እነ አየለ ጋናና እነ ብርሃኔ ቾርሶ ያስተማሩኝን የጠራ የመማር ስነስርዓት አደፍርሼአለሁ)**

እሱን ብቻ ሳይሆን የሒሳብ አስተማሪያችንን ነመራንም አልወደውም። ጓደኛዬ ቀርፋፋው፣ ጎታታውና እንስልጁ (ክፍል ውስጥ አስተማሪ እያለ ሁሉ የእውነት ያናውዛል) በሱፍቃድ ግን ይወደዋል—በተለይ ጆሜትሪ ሲያስተምረን። ነመራን ገና ሳየው ነው የቁጥር ጉዳይ የዞረብኝ። ጓደኛዬ 'በደንብ ስማው' ይለኛል። እኔ ደ'ሞ በደንብ አልሰማም። ምክንያቱም እዚያ አካባቢ ሁሉ ነገር የሚዞር ነው—ከፊል ግራ ተጋብቼአለሁ። ዋናው የአስተማሪዎች አለመከበር ነው። ተማሪዎቹ ቡድን አቋቁመው የፈለጋቸውን ባልት ይሰራሉ።

ቀስ በቀስ ግን  መለወጥ ጀመርኩ።

**(«ከዶሮ ጋር የዋለች ድመት ቅንቅን መሰብሰብ ለምዷ መጣች»
ወይስ**

**«ከዶሮ ጋር የዋለች ድመት ዕንቁላል መጣል ለምዷ መጣች»
ወይስ**

**«ከድመት ጋር የዋለች ዶሮ የአይጥ ቋንጣ ለምዷ መጣች»)**

ቀድሞ ለመማር፣ ለማወቅ እጥር የነበርኩት ልጅ የማልወደው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሲደርስና 'ትተነው እንውጣ' ሲሉ ደስ ይለኝ ጀመር። ሒሳብን በዚህ መልክ እሸውዳት ጀመር። ብቻዬን 'ፎርፌ የመስጠት' አቅም ስለሌለኝ—የእነ ኢያሱንና የጓደኞቹን ሽፍትነት መጠቀም ተመቸኝ። የምጠላው አንዱ ቃል 'ቀለሜዋ' ኾነ። እኔ የምፈልገውን ትምህርት ፎርፌ እንስጥ ሲሉ ግን እናደዳለሁ።

የኢያሱ ቡድን ከጠላ ግን ሁሉ ጠላ ማለት ነው። 'ት/ቤት ዘግተን እንውጣ' ሲባል ረባሽ የተማሪ መሪዎች ግንኙነት የሚያደርጉት ከኢያሱና ከጓደኞቹ ጋር ነው......የተቀረነው ቢዘቀዝቁን የምንዘቀዘቅ ቢያቆሙን የምንቆም ቀላል አቶክቷኪዎች ነበርን።

## ከአከሱም ስንሸሽ

ባልቻ መለስተኛ ሰማር እስከ አጥንቴ ማዕከል (መቅኒ) ድረስ የሰረገው ግብረገብ የተባለው ነገር ሁሉ ቀስ በቀስ በልዑል መኮንን ትኩሳት እየተቀጣ መቅለጥ ጀመረ። ከአለፈው የቀረኝ የሁሉ ነገር አጠቃላይ ውልታ 'ና ማርቲ አላና ብቻ የነበሩ ይመስለኛል......የተኖሩ ተረቶች ከሰዎች ግንባር ላይ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ይፋቃሉ ቢኗችሁ ይሂውና......

ብዙዎች የሚጠሉት የታሪክ አስተማሪያችንን ነበር። የሚፈሩት ብል

ይሻላል:: አስተማሪው ከሌሎች አስተማሪዎች ሁሉ ሽማግሌ ነው:: ሽበት የተበተነበት ሁልጊዜ ወደ ኋላ የሚለጥሰው ከግንባሩ እስከ ማጅራቱ እያብረቀረቀ ደረጃ እየሰራ የተኛ ፀጉር አለው:: የሚናገረው እንግሊዘኛ ስለሚከብደን ተቀምጠን የምናየው አነጋገሩን፣ አለባበሱንና የፀጉር አበጣጠሩን ነው:: ሙሉ ሱፍ ኰትና ሱሪዎች፣ በረዶ የመሰሉ ሸሚዞች፣ የወይን ቀለም ያላቸው የሹራብ ሰደርያዎችና ሁልጊዜ ተመሳሳይ ቀለምና ጥራት ያላቸው ባለሰንበር ከረቫቶች ይለብሳል:: ብላክቦርድ ላይ ሙሉ ጉዳይ ወይም ሙሉ መልዕክት ፅፎ አያውቅም:: ቆሞ ወረቀት እየገለጠ ያነብልናል:: አልፎ አልፎ ከባድ ከባድ ቃላቶችንና ስሞችን ከሥራቸው እያሰመረ ይከትባል—ብላክቦርዱ መሃል፣ ብላክቦርዱ ጥግ—በተዘባረቀ መልክ:: አንዳንድ ቀንም ደብተራችን ውስጥ እንድንፅፍ በቃሉ ያነብልናል::

ይሄ ሰውዬ ገና አንድ ሳምንት እንዳስተማረን የሕይወት ታሪኩ በ'አራዳ ነን' ባይ ልጆች ተጠንቶ መጣ:: ለዕረፍት ጊዜ ታሪኩን የነገረን ከኢያሱ ጐን አንድ ዴስክ ላይ የሚቀመጥ ገዛኸኝ የተባለ መልከ መልካም ልጅ ነው:: ሴቶች ከዚህ ልጅ ኋላ ኋላ እንደሮጡ ናቸው፡ እንዲህ እያሉት፡ ገዛ፣ ገዚሽ፣ ገዝዬ፣ ግዛቸው—የማይጠሩበት ቁልምጥ የለም:: ክፍላችን ውስጥ ያሉትን ጥቂት ሴቶች እንዳቀፈ፣ እንደኰረኰረ ነው::

ሲነግረን፡

«ስለዚያ ሞዛዛ የታሪክ አስተማሪ የሰማሁትን አንድ ልበላችሁ:: እዛ ጋ፣ ሽመልስ አዳምጥ—ወሬኛ! አሁን እኮ ቁም ነገር ነው የማወራው» አለ ገዛኸኝ

«ምንድነው ተናገሩ:: ጥርስህን ተነቀስክ?» አለ ሽመልስ

«ምን አገባህ:: ገጣጣ አይነቀስም»

«እናትህ ናት የነቀሰችህ»

«ዝምበል:: ዝጋ:: አለበለዚያ ነገርኩሽ»

«ይልቁን አውራን ምን ኾነ»

«አንተ ዝም በል—ስማ ትኩስ ወሬ እንዳያመልጥህ»

«ውሸት ነው አትስሙት»

«እዚጋ ስሙኝ—ነጋ የታሪክ አስተማሪያችን አማኑኤል ደርሶ መልስ ናት[126] ሲባል ሰምተናል:: የምትረባሱ ካላችሁ እብድ የሚሰራውን ስለማያውቅ......»

«ሰምተናል!»

«ሰምተሃል?»

«ታዲያስ! ከእኛ ምን ያመልጠናል:: አንድ አመት አማኑኤል ነበር...... ዩኒቨርስቲ ያስተምር ነበር አሉ» አለ ሽመልስ ከተቀመጠበት ሳይነሳ እየጮኸ::

126 እብድ እንደ ማለት:: ይሄ አባባል በዚያን ጊዜ ተወዳጅ ከነበረው ከብርሃኑ ዘሪሁን ልብወለድ መፅሐፍ አርዕስት ከ 'አማኑኤል ደርሶ መልስ' የተወሰደና በከተማ ትውፊት ውስጥ የተዋቀረ ነው:: አማኑኤል ሆስፒታል በአዲስ አባባ ከተማ ኮልፌ ወረዳ የሚገኝ የአእምሮ በሽተኞች ሃኪም ቤት ነው::

«ዝምበል......ልጨርስበት......»

ስለ ነጋ ሙርነት ከታወቀ በኋላ ምንም አያደርገንም በሚል አንዳንድ ተማሪዎች እየዘገዩ ክፍል መግባት ጀመሩ:: በተለይ ገዛኸኝ:: ነጋ የሚያስተምሩን ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ነው:: አሜሪካዊው የፒስ ኮርፕ ሰውዬ ስለ ግሪክና ስለ ሮም ታሪክ:: ፈረንጅ ስለፈረንጅ:: አበሻው ስለአበሻ:: ፈረንጁ ሒፒ የሚባሉትን ይመስላል:: አበሻው ዕብድ ነው ተብሏል:: (ታሪክ የሚያስተምሩን ሁለት የዞረባቸው ሰዎች ነበሩ ብል ኖሮ ይፈረድብኛል?) ነጋ ሲያስተምሩ ከባድ ናቸው-ብአድማጭና በእሳቸው መሐል ውጥረት መፍጠር ይችላሉ......ይሔ ይስበኛል:: ደ'ሞ የኢትዮጵያን ታሪክ በእንግሊዘኛ መማር ለልጅነቴ ደስ የሚል ነገር ነበረው:: አንድ ቀን ለሩብ ሰዓት ያህል እንዳስተማሩ ገዛኸኝ አንኳኩቶ ገባ:: ነጋ ዞር ብለው ባያዩትም፣ በጆሮአቸው እንደሚከተሉት ግን ይታወቃል:: ከኋላቸው ቀስ እያለ አልፎ ወደ መቀመጫው ሔደ::

ሲቀመጥ:

«ለምን ዘገየህ? ኸ» አሉት:: ፊታቸው ላይ ምንም ዓይነት ስሜት የለም::

«የምመጣባት ባስ[127] መንገድ ላይ ተሰብራ ነው»

«ይሰበር አይሰበር አናውቅም፤ ግን ክፍል ዘግይቶ ሲገባ ታዲያ 'ይቅርታ ቲቸር' አይባልም? እኔን ብቻ ሳይሆን ክፍሉንም ይቅርታ መጠየቅ አለብህ:: ሁለተኛ እንዳይደግምህ:: ምን ላይ ነው የቆምነው? we were talking about the ancient known greatness of Ethiopia—the Axumite empire......»

ክፍሉ የበለጠ ፀጥ አለ:: ሲናገሩ ከቆሙበት አልተነቃነቁም:: አንድ እጃቸው ሊገልጡት የነበረውን ወረቀት አልለቀቀም:: ተማሪው በማይታይ የፍርሐት ገመድ በሕብረት ተወጥሮ የታሠረ መሰለ (እንዲህ በአንድ ሰው የአንድ ጊዜ ቁጣ የሚንቦቀቦቁ አልመሰለኝም):: ገዛኸኝ ራሱን ከእነ ኢያሱ ጋር የክፍሉ መሪ አድርጐ ስለሚቆጥር አስተማሪው ፊት መፍራትና ማፈር አልፈለገም መሰለኝ የአቶ ነጋን ቁጣ ወደ ጨዋታ፣ ወደ ቀልድ ሊለውጥ ሳቅ ሳቅ አለ:: ሊገልጡ የጀመሩትን የገፅ ወረቀት እንደያዙ:

«ምን ያስቅሃል?» አሉት:: አሁን ቁጣቸው ፊታቸው ላይ እየተንቦገቦገ::

«አይ......እ......»

«ጥርሳም:: አማረልኝ ነው? ምን እንደ ቤት ያንበላጥጥሃል?–እንደወንጻ ገረድ ይሠራሃል:: ጥርስህን ከምትነቀስ እንብብ:: እኔ እንደ አንተ ዐይነቱ መቀለጃ አይደለሁም:: የፌዝና የተንኰል ልጆች ናቸው እዚህ የወረወሩኝ:: ከአንተ አይነቱ ጋር......የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩንቨርስቲ የሚያንሰኝ ሰው ነኝ......ደግሞ ትስቃለህ?» እንዲህ ተናግረው አለቀቁትም:: ቀጥ ብለው እንደቆሙ በግራ እጃቸው የያዙትን ቾክ በፍጥነትና በብስጭት ወረወሩት–እንዴት እንዳነጣጠሩ–ፊቱ ላይ መቱት:: ገዛኸኝ እንደዚያ ሲደነግጥ አላየሁትም:: ገዛኸኝ እንደዚያ ደንግጦ አያውቅም:: ክፍሉ የበለጠ ፀጥ አለ:: የቅንድቤን እንዲት ፀጉር ነቅዬ ወደ

127 አቶቡስ(እንግሊዘኛ)(አ)

ወለሉ ብጥላት የምታወጣው ድምፅ አባ ኮራን ሠፈር ይሰማል......አስተማሪው ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ወረቀታቸውን ገልጠው:

«the pride of axum fell in the hands of a jewish queen called Judith, Gudit or Isatua......» ብለው ቀጠሉ::

ትምህርቱ አልቆ ቲቸር ነጋ ከወጡ በኋላ ኢያሱ ተማሪው ፊት ለፊት ቆሞ እንደ አስተማሪው ተመስሎ ቲያትር ለመስራት ሙከራ ላይ እያለ የአማርኛ አስተማሪያችን ገባ:: እየሳቀ:: አፉን ጠመም አድርጎ ይስቃል:: በተጫዋችነቱ ሁሉ ይወደዋል:: ብዙ ጊዜ ከሰዓት በኋላ ስለሚያስተምር ክፍሉ ይሸታል:: ክፍሉ መሽተት ጀምሯል:: ጥቃቱ በአፍንጫው ስለሚሰማው እየሳቀ በሌላ ነገር እያስመሰለ እሱ በሚቆምበት በኩል ያለውን መስኮት ከፈተ:: እኔን ጨምሮ የክፍሉ ሦስት አራተኛ ተማሪ በሽራ ጫማ ይመጣል—ወይ በቻይና ወይ በባለአዞ:: የእኔ ባለአዞ ናት::

የዚህ ሰውዬ ሰዋሰውና ይሄ ጠረን ሲደባለቁ.......

የኢያሱን ትከሻ ይዞ:

«ጉዳዩ ምንድነው?» አለ::

«ትንሽ ከገዛኸኝ ጋር ቁም ነገር ይዘን ነው»

ብዙ ሳይቆይ ያ የሚያስለች ሰዋሰው ተጀመረ:: ሰዋሰው ሲያስተምረን ያስጠላኛል:: ቅኔ፣ ተረትና ምሳሌ፣ ስለድርሰት አፃፃፍ ሲያስተምረን ግን አስተማሪ ይመስለኛል:: ስለተሻጋሪ ግስ፣ ስለማይሻገር ግስ፣ ቦዝ አንቀፅ፣ አዕማድ—የፀና፣ ድኩም የኾነ ሲል—ዕንቅልፌ ይመጣል......ሦስት ነገር ለምርጫ ቢቀርቡልኝ: መስቀል፣ ተቃጥሎ መሞትና ሰዋሰው:: መጨረሻ የምመርጠው ሰዋሰው ነው:: ዛሬ ደ'ሞ 'ዘርፍ አያያዥ' ስለተባለ ነገር ወይ በሽታ ማውራት ጀመረ:: ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ዘርፍ፣ ዘርፍ አያያዥ:: እንዲህ ማስተማር ሲያምረው ሰውዬው 'ሆኅተ ጥበብ ዘ ስነፅሑፍ' የሚባል መፅሐፍ በእጁ ያንጠለጥላል::

የዚህ ሰውዬ ሰዋሰውና ያ ጠረን ሲደባለቁ.......

ማስተማሩን ጨርሶ ከመሔዱ በፊት ሁለት ሁለት ከባድ ቃላቶች እላያችን ላይ ወርውሮ መሄድ ደ'ሞ ልማዱ ነው::

የዛን ዕለቱ *'ሐብ ሐብ'* (የመሬት መንቀጥቀጥ)እና *'በጢሐ'* (ዱባ) ነበሩ::

በመደነቅና በመገረም የልጅነትና የጉርምስና አይኖቻችን ሲፈጡ ስቆ ይወጣል:: ሁሌ ስቆ ይወጣል:: ታዲያ የዚያን ቀን ዞር አለና:

«የታሪክ አስተማሪያችሁን አትንኩት ቀልድ አያውቅም:: ያቺ የፈረንሳይ አስተማሪ ደ'ሞ ሽርኩ ናት:: ትጠብቀዋለች» ብሎ እንደ ለመደው በጎን እየሳቀ ወጣ......(በምኔው ነጋ እንደ ተለከፈ ሰማ? የአማርኛ አስተማሪያችን ይሄን ካለን በኋላ ወሬው የተጓዘበት ፍጥነት ለረዥም ጊዜ ሲገርመኝ ነበር)

ቅደም ተከተሉ ዞሮብኝ ነበር......ማለት:

ኢያሱ ታሪክ መማር ይጥላ ወይ የታሪክ አስተማሪያችንን ይጥላ ወይ ታሪክ ስለጠላ የታሪክ አስተማሪያችንን ይጥላ ወይ የታሪክ አስተማሪያችንን ጠልቶ ታሪክ ይጥላ ግራ እንደ ገባኝ አስራ አንደኛ ክፍል ስንደርስ ተለያየን......

የእኔ ታሪኬ ስነሥርዐት ነበር:: እሱን ከመሰል ተማሪዎች ጋር በጋርዮሽ አድማ ብረት ቦዘና ውስጥ እየተንፈራፈረ እየተወራጨ "ኸረ አድኑኝ!' እያለ ገና ሳይሞት መርካቶ አስፋልት ዳር ሬንጅ ቆፍረን አፈር እፍ ብለን ገና ሲምቧች እያለ ቀብረነዋል......

ያ ሰሞን የአንድ ትውልድ ስነስርዓት የማበላሸት ተራ ውልታ ብቻ ሆኖ ሊያልፍ ይችላል.....

## የዘበናይ ግማሽ

አንድ እሁድ ዕለት አባቴ 'እቴ ዘበናይ' የሚላቸውን ትልቅ አክስቱን ለመጠየቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ስድስት ኪሎ ይዞኝ ሄደ:: ከዚያ አካባቢ ያደነቅሁት ቦታ የየካቲት አሥራ ሁለት ሐውልትና አደባባይን ብቻ ነበር:: የዩንቨርስቲው ግቢ ትንሽ ደን ስለበዛው አልመሰጠኝም:: 'ዩንቨርስቲ' ሲባል አእምሮዬ ውስጥ የተሳለው ፎቅ በፎቅ የኾነ ቦታ ነበር::

የአባቴ አክስት ቤት በጣም ትልቅ ነው:: ግቢው ትልቅ ነው፣ ሴትዮዋንም በኋላ ሳያቸው እሳቸውም ትልቅ ነበሩ:: ቤቱ ፊት ለፊት ሰማይ ጠቀስ የኩባ ደን አለ በአጠገቡ ሳልፍ እንደ ብዙ አሞራ ክንፎች እየተርገፈገፈ ያደነቆረኝ:: የበረንዳው እርዝመት ከጣውላና ከሲሚንቶ የተሰራ ግልገል ሜዳ ነው:: በረንዳው ላይ ሁለት የሳጠራ ወንበሮች አሉ......በኋላ እንደ ተነገረኝ የቆርኬ አጐዛ የለበሱ:: ቤቱ ውስጥ አምስት የሦፋ መቀመጫዎች አሉ......አንዱ ረዥም አልጋ የሚያክል:: ለዕድፍ መከላከያ ወይም ለኪነት አላውቅም ሁሉም ሙሉ በሙሉ ርካሽ ባለ አበባ ጨርቅ ለብሰዋል:: የአባቴ አክስት አንገታቸው በንቅሳት የጠቆረ፣ (በዚህ ዐይነት:መጠመጠመጠመጠ መጠመጠመጠመጠ)፣ ፊታቸው ወፍራም ክብ ነው:: ከአባቴ ጋር ሲነጋገሩ ወደ አስር ጊዜ ያህል በሚቿ ንግሥት በእቴጌ መነን ማሉ፣ እንደ ገና አስር ጊዜ እኚሁ ንግሥት በሚወዷት ማርያም ማሉ:: ገና ቤት ውስጥ እንደ ገባን እኔ እምሄድበት ልዑል መኰንን ት/ቤት ከሚማር ልጃቸው ጋር አስተዋወቁኝ:: እንደ እኔ ዘጠነኛ ክፍል ነው:: በአይን አውቀዋለሁ:: ስንገናኝና ወላጆቻችን ከበውን ስንጨባበጥ ከዚያ በፊት በደንብ እንደምንተዋወቅ ሁሉ ወይም ልክ ለወራት ተለያይተን የተገናኘን ጓደኛሞች ዐይነት 'እንደምን አለህ' 'እንደምን አለህ' ተባባልን::

አልፎ አልፎ ስለ አስተማሪዎችና ስለትምህርት ስናወራ ቆይተን ዝም ተባባልን:: የእሱን አላውቅም እንጂ እኔ ተደናብሬ፣ የማወራው ጠፍቶኝ ነው:: ልጁ ሲናገር የተረጋጋ ነው:: አይንተባተብም:: የሚናገረው ቶሎ ቶሎ ይመጣለታል:: አንደበተ መልካም የሚባሉት ዐይነት:: ስሙን የሰማሁት እናቱ ደጋግመው ሲጠሩት ነው:: 'አልዬ' ሲሉት 'አለማየሁዬ' ሲሉት:: ሴትዮዋ እቴ ዘበናይ ደጋግመው ስለ አርሲ መሬታቸው ያወራሉ::

«......ጥር ላይ ናና አንድ ሁለት ኩንታል ጤፍ ውሰድ» አሉት አባቴን

«ኧረ እባክሽ መጠያየቃችን ይበልጣል......ገና ስንገናኝ እንዲህ አትበይኝ»

«ምን አለበት ጉቦ እኮ ነው:: አንተ ሰው አታይ:: አያ......ያለፈው ጊዜ ከደብረወርቅ መጥቶ ስለእናትህ ብቻዋን መኾን አወራኝ:: እኔ ገብቶኛል ለምን እንደማትሔድ:: አልሞላልህ ብሎ እንደኾነ አውቃለሁ:: እኔ እህትህ ነኝ:: ዘር ቆጠራ ኾኖ ነው አክስትህ የሆንኩት:: ሙት......ምን ትስቃለህ? እንደ ታላቅ እህትህ ስማኝ ደ'ሞ......አንተ መጥፎ ሰው ኾነህ ወይም ሰንፈህ አይደለም የደኸየኸው:: የመንግስት ሥራ ያዋጣኛል ብለህ ገባህ:: አልቀናህም:: ደ'ሞ እ...... አሁን እኔን ስማኝ ይልቁን ብንረዳዳ አይጐዳም:: በዚህ ኑሮ፣ በመንግስት ገንዘብ እኔ እራሴ እንዴት እንደምትኖር ያሳስበኛል:: አዛኝ እንኳን እሱ እራሱ አለ የበላዩ:: እኔ እንደ እህትህ ነኝ:: ጤፉ ገበያ ቢወጣ ሰላሳና አርባ ብር ነው[128] ለአንተ ለወንድሜ ትንሽም ብትሆን ታሣርፍሃለች፤ ጥር ላይ ና እኔ ምን የመሰለ ጤፍ በጆንያ ቋጭ አድርጌ እጠብቅሃለሁ»

«አላስቸግርሽም......እሱ ክርስቶስ አለ»

«አይ ይኼ መልስህ የሚጥምም አይደል......ሌላ ምክንያት ይሻላል...... በፊት ያን ጠጅ ቤቱን ውሰድና ጠጅ ቤት ይሁንህ ብልህ ቤንጤ ሆነህ እምቢ ብለህ......ያልተለመደ ነገር......አንድ ራስ መኮንን ድልድይ አጠገብ ትኖር ለነበረች......ውቤ በረሃ እንዲያ ወደ ታች ወረድ ብሎ ለምትኖር አንድ 'አቦል' ለምትባል ወዳጄ ሸጥኩላት:: ታድያልህ አሁን የአገሩ ወታደርና ቦሊስ ከአራተኛ፣ ከጎፋ፣ ከቦሊስ ሆስቢታል እየተጠራራ እየመጣ አሁን ልጄ ቢጠሯት አትሰማም:: ዲታ ሆናለች:: ከየት እንዳገኘህ ይሄን ሃይማኖት ተባለቅኔው አገር ተጎጃም መጥተህ ጉድ ያሰኛል:: ማሩን የፈጠረው እዝጌር፣ ጌሾውን የፈጠረው እዝጌር፣ ጠጅን ቢያስብ አይደል:: አንተ ዘለህ መነኩሴ አይሉህ ምን ተእግዜር ስራ መሸሽ:: ጠጣ ያለህ አለ? አትብላ ያለው......ያቺ ሚስትህ ይብላኝላት:: ስማኝማ ብዙ ብዙ ነገር አለ እህ ብለው ካዩት ካዳመጡት ማለቴ ነው...... የአባቴ ዘመዶች ወለጋ ነው ያሉት በደረሶ በኩል ነው የሚሄደው የራስ ጎበና ዳጬ የትልቁ ልጅ ሚስት የላቀች ዘመዶች እኮ የአባቴ ሚስት ዘመዶች ናቸው......በጣልያን ጊዜ ከጎሐ ፅዮን ሸሽተው ወለጋ ገብተው ነበር:: አሁን እዛ ልጠይቃቸው ስሄድ በአዲስ አባ ዞሬ ነው:: ወለጋን የሚያህል አገር ጎጃምን የሚያህል አገር እንግዲህ ቤንጤ ከሚያደርጉት አገሩን ዋና ዋናውን ድልድዩን ስራ አያስተምሩም? እንደው ሳስብ ነው......የተማርኩ አይደለሁም......የፈረንጅም አፍ አልችል......ግን እንደው የሚረባ ሌላ ነገር ጠፋ? ድልድይ ድልድይ መስራቱን ኩባንያውንም መቼም ፈረንጅ ያውቅበታል ያን ያን:: እኛ ወሬ ነው ወሬ ነው:: ለምን መሰለህ አይወዱንም:: እኛ ደ'ሞ እንከፍ ልጆች ነው ያሉን...... ንጉሡ እየቀለቡ የሚያስተምሩት ባለ ኮሌጁ ሁሉ ድንጋይ ሲወረውር ይውላል፤ ድንጋይ ተሚወረውር የሚወረውረውን ሰብስቦ ሕንጣ አይሰራም:: እንከፍ እኮ እንከፍ ሆኖ አይመጣም፤ ስልት ስልት ብልጠት አለው:: ጥሩ የሚሰራ አስመስለህ ነው እየህ የጅል ስራ የምታሰራው:: ቢሞትም ቂል ምን ይጎዳል

---

128 ይሄ የጤፍ ዋጋ ትክክል ነው(አ)

ብለህ......ለእናቱም አይሆን......ወንድሜ አሁን እንደው ለቃቅመህ በየፋብሪካው ብትሾማቸው ፋፋና ባስታ ነው የሚሰሩት:: አሁን እንደው ይሄ 'መሬት ላራሹ' ሲል መዘዝ አድርገህ አንድ ጋሻ ብትሰጠው አፉን ያዝ:: ከአስቀያሚ ሚስቱ ከአሮጊቷ አፋተህ እንዲቷን ጠይም ቆንጆ እንካ ብትለው እኮ......የለም በቃ:: እውነት የለም:: ዙፋን ላይ ብታስቀምጠው አይችልበትም ሲተፋ የሚያድር ሆዳም ይሆናል:: እኩል ለመሆን ሲጥሩ አይቻልም:: ሲጥሩ አሁን ሰው ይሄን ጣት እኩል ሁን ብለው እኩል ይሆናል? ለማድረግ አይቻል:: ሲፈጠር አይደል፣ እኩል ይሁን ታልክ መቁረጥ አለብህ እሱ እኩልነት አይባልም ቁምጥና ሌብሮሲ ይባላል» አለማየሁ አፉን በእጁ ጋርዶ ይስቃል::

«ምን ያስቃል? የሚያስቅ የለውም:: ንጉስ ደግ ነው፣ ንጉስ መጠን ያውቃል:: ንጉስ ከኛ ጋር ተቀምጦ ይብላ አይባልም፣ አሁን የፈረንጅ ብሬዝዳንት በሴቼንቶ ይሄዳል? በስድስት ቁጥር አውቶቡስ ይሳፈራል? የእኛ ንጉስ ምን በወጣቸው:: አምስት መኪና አላቸው አስር መኪና አላቸው:: ንጉሥ መታማቱ እኮ ነው:: ታምቶ ተሞቷል:: ታዲያ ምን ይጠበስ? የፈረንጅ ንጉሥ ዝተት ይለብሳል? አሁን እዚህ ኮሌጅ የሚሳደበው ኡሪ ያወቀ የመሰለው እንደው ንጉሥ ቢሆን ልብሱን ሰንጋ ተራ ያሰፋ መሰለህ? አይ ቂሌ:: ብዙ ሰው አይቼአለሁ:: እዝጌር ከመረጣቸው የማንም ልጋጉን ያልቆረጠ......እውነት......ሰላማዊ ሰልፍ ተሰልፈው አብቅተው እዛ ለጥቀህ ብትወጣ የተሰለፉበት መንገድ አያራመድም...... በቃ ልጋግና ለሐጭ ነው......ገና አፋቸውን መሰብሰብ አልቻሉም......ሂሂሂ ዕውነት......መልካምና ደግ ለመለየት ኮሌጅ አያስፈልግም፤ ባቡርና አሮቢላን ለመስራት ብቻ ነው ዩንበርሲቲ የሚባል::......ድንጋይ ውርወራውን ትተው ለአገራቸው የሚጠቅም ነገር በሰሩ......የአንተ ጠጅ ቤት አልፈልግም ማለት ድንጋይ ውርወራ ይመስላል......ትንሽ ሰርተህ ትተህ ሌላ ይሻላል የምትለውን ንግድ ብትጀምርስ? ብቻ እሱ ካላለው......»

ልጁ ፊቱን ላለማሳየት እየጣረ ይስቃል:: አባቴ ፊቱን እንደ እንጨት አድርቆ ይሰማቸዋል::

«ምን ያስቅሃል? ትምህርት ቤት ሲረበሽ ትወዳለህ......ሰነፍ:: ለሰነፍ የተሰራ ተንኮል......ጥርስህን እንዳልለው:: ለእኔማ ለሱቁ ጥሩ ነው:: ትሰራልኛለህ...... አንተ በራስህ የትም አትደርስም እንጂ በትንንሽ ረብሻ አሰልጥነው አሰልጥ ነው ዙፋን የሚወስዱ ዕለት ጠብቀው ይገሉሃል......መጫወቻ፣ የማይገባው መጫወቻ፣ የት የት ሄድኩ አባተ?......ልጅህን ተጠንቀቅ ያማረበት መስሎት ገና በልጅነቱ......» ልጁ ፊቱን መራራ አደረገ ......

ወዲያ ወዲህ እያሉም ከዚህም ከዚያም ከጓዳም ለሰስ አድርገውም እየጮኹም ያወራሉ:: ትችታቸው ቀልድ ይመስላል:: ቀልዳቸው ትችት ይመስላል::

«ሰማህ ልጄ--ብድልህ ትበላለህ?» አባቴን 'ደሃ ነህ' እያሉ ሲዶክኩት ቆይተው ወደ እኔ ተሳቡ::

«ግድ የለም እበላለሁ»

«'ግድ የለም' አይደለም......ወጥ አልሠራንም፣ እስከንሰራ በድልህ ቁርስ ቢጤ ቀማምሳችሁ ጠብቁ»

ሴትዬዋ ብዙ አልተመቹኝም:: ወይም ንግግሬ ትክክል አይደለም::

«እሺ እበላለሁ»

«'እሺ' አይደለም»

«እበላለሁ»

አለማየሁ እራሱን ያካል:: ግማሽ የመዳከም ሣቅ በአፉ ሰርቶ:: ለሚገነፍለው ቁጣቸው መልስ መስጠት አቁሜ በዝምታ የሚያወሩትን በአወንታ ራሴን እየነቀነቅሁ መስማት ጀመርኩ:: ብዙም ሳይቆይ በትሪ ላይ ሁለት እንጀራ ተዘርግቶ፣ እዚያ ላይም ትንሽ ነጭ የሸክላ ሣህን ተቀምጣ፣ ሣህኗም መሐል ላይ ቡጢዬን የሚያክል የጠበቀ ድልህ:: ይኼ ዝግጅት አራታችን መሃል አጭር ጠረጴዛ ላይ መጥቶ አረፈ::

«ብሉ! ብሉ!......ጠላ ትጠጣለህ?» አሉ ሴትዬዋ ወደ እኔ እያዩ::

«አልጠጣም»

«ጎረምሳ እኮ ነህ አንተ ለትዳር ደርሰሃል......ብቸና ቢሆን እንድረው ነበር:: ጠላ አልጠጣም ይላል?»

«ራሴን ያመኛል»

«የእኔ ጠላ ራስ አይነካም:: ሰውነት ነው የሚኾነው:: ትከሻ ነው የሚኾነው»

«ተይ ያመዋል ደ'ሞ ፀሐይ ነው»

«ፀሐይ ሲወርድ ይሔዳል......ምን ያስቸኩላል፣ ከአለማየሁ ጋር እየተጫወቱ ይቆያል አንተስ ምን አስቸኩለህ? ማንን ትድራለህ?»

ለመከራከር ጊዜ አይሰጡም:: ካላስመረጡኝ ለምን ጠየቁኝ? ብዙ ጊዜ የጠቀለሉትን ጉርሻ ማዕድ ላይ እንደ ሚጢጢ ሐውልት አቁመው ወደ ጓዳ እየገቡ ከጓዳ እየወጡ ነው የሚናገሩት:: ለአፍታ ዮዲት ጉዲት መሰሉኝ...... እኛም የቦካንና የፈዘዝን የአክሱም ደብተራዎች::

«ጠጣላት:: እሷ አትለቅህም» አለ አባቴ::

እንደሚባለው ጎጃሜዎች አይለቁም......

አለማየሁ አይናገርም:: በዝምታ ያዳምጣል:: የመጀመሪያውን የሚያቃጥል ጉርሻዬን እንደዋጥኩ......እቴ ዘበናይ በረኸም ብርጭቆ ጠቆር ያለ ጠላ አምጥተው ፊቴ አስቀመጡ::

«በል ጠጣ፣ ዘመድ ቤት ሔዶ የተገኘው ነው የሚቀመሰው:: አንተዬ ሰነስርዐት አስተምረው እንጂ»

ጠላውን እንደጠላት በጐን እየዋለሁ:: ብዙም ሳይቆይ የተገነዘብኩት ነገር

ከአንድ ሣህን ላይ ቁጢጥ ያለ ድልህ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተሻምቶ መብላት መከበዱን ነው:: በመጀመሪያ ተራ መጠበቅ አለብኝ:: የአራታችንም ያሞጠሞጡ እጆች እንጀራ ቆንጥጠው በርበሬ ለመተምተም ሲያንገብቡ የድልሁ ክብ ቢጋር ሁላችንንም ማስተናገድ የሚችል ስፋት እንዳሌለው ይከሰትልናል:: እጅ ለእጅ እንኮራኮማለን:: ወይም እንነካካለን:: ጉርሻ ሲያነሱ መነካካት ወራሪ ያስመስላል:: ቀጥሎ በተለያየ ደረጃ አብሬአቸው ከምበላቸው ሰዎች ጋር እንግዳ ነኝ:: ሁለቱ የሚያስፈሩኝ አዛውንቶች ናቸው:: ሶስተኛው እኩያዬ ቢሆንም ያወቅሁት ዛሬ ነው፣ ሲበላ ደ'ሞ አስገራሚ በሆነ መልክ ይንቀራፈፋል:: የአንድን ሰው የአበላል ፍጥነት ማወቅ ወይም ከፍጥነቱ መላመድ ተራ ጠብቆ ለመብላት ያመቻል:: ይኼን 'የጉርሻ ሳይንስ'[129] ይነግረናል:: አብሮ መብላት ትልቅ የድርድር ምንድነው የሚባለው? የዲፕሎማሲ? አዎ የዲፕሎማሲ ችሎታ ይጠይቃል::

አባቴን እንደ እንግዳ ባልቆጥረውም አብሬው ከበላሁ ዘመን የለኝም-- የአሁኑን የአበላል ስልቱን የማውቀው (የአበላል ስልት በየጊዜው ይለዋወጣል ሲባል እሰማለሁ)[130] ከሩቅ ተመልካች ሆኜ እንጂ አየተሻማሁ ፈትሼ አይደለም::

---

129 'የጓደኛ ወይም የወዳጅ ሌላ ተመሳሳይ ቃሉ ባልንጀራ ነው:: ቃሉ መነሻ ትርጉም አለው:: አንደኛው ባልንጀራ (በአለ እንጀራ)የእንጀራ ባለቤት የእንጀራ ጌታ ሲሆን፡ ሁለተኛው እኩያ፣ ባልደረባ፣ አቻ፣ አብሮ አደግ ጓደኛ፣ _እንጀራ አቋራሽ_ ማለት ነው::(_ዐዲስ መዝገበ ቃላት_ ደስታ ተክለ ወልድ):: እንጀራ አቋራሽ የሚለው ቃል የጉርሻ ፍልስፍናን የሚገልፅ ይመስለኛል:: ባለ እንጀራ ወይም እንጀራ ያለው ማለት ብቻ ሳይሆን (ሁለቱን ትርጉሞች ብናሰባጥራቸውና በትርጉም ብናደነድናቸው) የሚያጎርስ ማለት ሊሆን አይችልም? ለማጉረስ እንጀራ የያዘ ወይም ያለው ማለት ሊሆን አይችልም?' ከነቢዩ ጎበና (ናቢ) _ከአራት ሺህ ዓመት በላይ የምግብ ባህል :ሲሳዩና እንቅፋቱ_ 1963 ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት:: (መግቢያ) ገፅ 6::
'አንድ ጉርሻ እነዚህ የሚከተሉት ንጥረ ነገሮች ያስፈልጉታል፡ እንጀራ፣ የሚጠቀስ ወጥ/ማስፈራሪያ፣ ጤነኛ ክንድ፣ መጠቅለል የሚችሉ ጣቶች፣ ከአንድ በላይ በላተኛ፣ የሚያማምሩ መለማመጫ ቃላት (በሞቴ፣ አፈር ስሆን)፣ ማስፈራሪያ ቃላት(ምናባቱንስና! ይህቺን ብላና አልመጣብህም) ወዘተ:: ጉርሻ አለማዊ ስጋ ወደሙ ነው፣ በግለሰቦች መሃል ያለ ቁርባን ነው፡ ቃል ኪዳን ነው (በእጄ በልተህ እንዲህ አታድርገኝ):: ጉርሻ ሁለት አቅጣጫ አለው፡ ወደ ራሲ የምወስደው ጉርሻና ለሌላ የምሰጠው ጉርሻ:: ቃሉ ባለቤትና ተሳቢን ደምሮ የያዘ ሃይል ነው:: ድርጊት ውስጥ ሲፈታታ የተወሳሰበ ይሆናል:: ከጉርሻ ጋር የተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦች አሉ፡ ፍጥነት፣ መተሳሰብ፣ መተዋወቅ፣ የዕድሜ ትልቅና ትንሽነት፣ የስልጣን ተዋረድ......ወዘተ) _'ናቢ፡ ዝኒ ከማሁ::_ ምዕራፍ 2፡ የጉርሻ ዓይነቶች::

130 የጉርሻ ፊኔሚኖሎጂ (The phenomenology of Gursha)ምዕራፍ 4:: '......የጉርሻችን መጠን፣ ቅርፅና ይዘት በግል ሕይወታችን ውስጥ ከሚያጋጥመን ደስታና ጭንቀት ጋር ይለዋወጣል:: እንጀራን ለመብላት ቀላል ቢመስልም የተወሳሰበ የጣት ንቅናቄ ኪነትና ጤንነት ይጠይቃል:: አንዳንድ ጣቶቻቸው የታመሙና ርሂ ያበላሻቸው ሰዎች እንጀራ መጠቅለል ባለመቻላቸው የስነ ልቡና ችግር እንደ ደረሰባቸው ይናገራሉ:: ይሄን በሚመለከት አስተያየታቸውን የጠየቅኋቸው የፍቼ ከተማ ኗሪ የሆኑ ግርማ ደንበባ የተባሉ አንድ አዛውንት እንዲህ አሉኝ፡ 'ለምለም እንጀራ ቆርሼ ከበላሁ ሁለት ዓመት ሆነኝ:: ጠዋት ማታ የሚናፍቀኝ ምንም ሳይጎልብኝ የጎደለብኝ የሚመስለኝ የሚሞቅ የበግ ቅቅል ውስጥ ለምለም ጤፍ እንጀራ ነክሬ መብላት ስላልቻልኩ ነው:: መረቅ ጭኔ ላይ ሲንጠባጠብና ሱሪዬን በቢጫ ወይ በቀይ ቀለሙ ሲያቆሽሸው ማየት ይናፍቀኛል:: በፍጥነት በማርጀት ላይ ያለሁት ያን በማጣቴ ሳይሆን አይቀርም:: ዛሬ ባለቤቴ 'ላጉርስህ' ስትለኝ ልቤ አይደርስም:: እኔ በልጅነቴ እሰራው የነበረው አይነት ልቁስቁስ ነው ጉርሻዋ:: እንደ ጉርምስና ጊዜዬ መጉረስ እፈልጋለሁ:: ያን ጊዜ ሐይለኛ ልጅ ነበርኩ:: በሚድል

እዚህ የተሰበሰቡትን ሰዎች ሁሉ ፀባይ አላውቅም:: በስተቀኝ ጎኔ የተቀመጠው አለማየሁ መፍራቴንና ማፈሬን አይቶ ሊያበረታታኝ መሰለኝ አልፎ አልፎ 'ብላ' እያለ ይገፋፋኛል:: ደጋግሜ እሱን የማየው ግን በቀኝ እጁ የጠላ ብርጭቆውን ብቻ ሲያነሳ ነው::

«እኔ የምለው ልጅህ አይርቀውም ልዑል መኮንን ድረስ እየሄደ ሲማር--አይርቅህም?» አሉ እኔ ላይ አተኩረው::

«ይርቀኛል»

«በምን ትሔዳለህ?»

«በአቶቡስ:: ትንሽ እንኳን ቀረብ ቢል በእግሩ እልከው ነበር» አለ አባቴ፣ ጥያቄውን ከመመለሴ በፊት ፈጠን ብሎ::

«ልጅህን በአቶቡስ ልከህ ታስተምራለህ? እንዴት ጉበዝ ነህ? አለማየሁን እኔ አንዳንዴ ሲረፍድ ነው በአቶቡስ የምልከው--አንተም አበዛኸው:: ልጅ ነው ምናለ በእግሩ ቢሞክር፣ ይጠነክራል»: (በልባቸው ምናልባት 'ምን እየበሉ ነው ልጁን በአውቶቡስ የሚልኩት?' ይሉ ይሆናል ሴትዮዋ)

አለማየሁ እኔን አየኝ:: ድልህ ባልነካው ግራ እጁ የብርጭቆውን ጠላ አንስቼ ተጎነጨሁ:: ይመራል:: የሚመር ወፍራም ጠላ::

---

ዌይት/በመካከለኛ ክብደት/ የጠቅላይ ግዛቴ የቦክስ ሻምፒዮን ነበርኩ:: ተለቅ፣ ጠበቅ ያለ፣ የልቃቂት ቅርፅ ያለው፣ መሰረቱ ሰፋ ብሎ የተረጋጋ፣ የጠመጠመው እንጀራ ቢጎነታትሉት እንኳን የማይተረተር፣ በውስጡ እንደ መኖሪያ ቤት ሳሎን(ቀይ ወጥ)፣ መኝታ ቤት(ክትፎ)፣ ጓዳ(አልጫ)፣ በመጨረሻ ሁሉንም ሰፍቼ የምይዝበት ወደ ንጣት የሚወስደው ሚጥሚጣ ያለው ጉርሻ እሰራ ነበር:: ይሄን ከእጄ የሚነጥቀኝ አልነበረም:: ይሄ ጉርሻ አገሬ ነበር:: ሰጎርሰው አፌ በስርዐት ግን በስፋት ይከፈታል: አፌ ማሕፀን ነው:: ይሄ ከአገሬ አፈር፣ ከአገሬ ነፋስና ውሃ ጋር የማደርገው ሁሌ በችለሳ አዳሜ የሚያልፈው ሩካቤ ነው:: ያን ጉርሻ ስነክሰው ለጥርሶቼ የሚሰማኝ ደረጃ ነበር:: ይይዘኛል፣ ይለቀኛል:: አላምጬው ስውጠው ሆዴ ውስጥ እህል እንዳለ ይታወቀኛል:: የዚያን ዘመን ጉርሻ ተመልሶ አይመጣም:: የጎጃም ገበሬ ሳይደክም እኔ በርሂ ደከምኩ::' <u>ናቢ: ዝኒ ከማሁ</u>:: ምዕራፍ 4: ዜጎችና ጉርሻ::

'......ጉርሻ እንደ ሰው ልጅ ፀባይ በዝግመተ ለውጥ ሒደት ውስጥ ያልፋል፣ ይለወጣልም:: በችኩልነት ዘመን የተውሸከሸከ ችኩል ጉርሻ እየተሰራ ይበላል:: በኮስታራነት ዘመን ዳረጎቶች እንደ እብነ ወሰን ጠንካሮች ናቸው:: በልፍስፍሶች ዘመን ጠቅልለው ቢተዉት ራሱን ችሎ ማሰድ መሃል የሚቆም 'ተጠቀለልኩ' ባይ ጉርሻ ይጠፋል፣ ይሄም ያልፍና ራስን ማጣጣል ይመጣና ቀጥሎ ጉርሻ ይናቃል:: የዳቦ ጉርሻ ኪነት የለውም:: የመጠን ንጥር ብቻ ነው ስፍራው:: የጤፍ እንጀራ የዳቦዎች ከፍተኛ ደረጃ ነው:: ከእርሻ ቦታ እስከ እዳሪ ያለው ጠቅላላ ሕይወቱና ጠቅላላ ጉዞው በፍልስፍና መቀመር አለበት:: ያ ካልገባህ ስለ አገሬ እሰባለሁ ማለቱ ውሸት ነው:: ስለዚህ ከተለያየ አቅጣጫ መዝነን ካየነው ሊጠና የሚገባው ጉርሻ የእንጀራ ብቻ ነው:: እየዞርኩ የሰዎችን ጉርሻ በመብላት የሰው ፀባይ መንገር እችላለሁ፣ ብልህነቱ ካለኝም የዘመኑን ፀባይ በትንሹም ቢሆን ማብራራት እችላለሁ......» <u>ናቢ ምዕራፍ 6: ዝኒ ከማሁ</u>::

'......ጋቢና ነጠላ ልንሰራበት ያዘጋጀነው ልቃቂት ጉርሻ መምሰሉ፣ ነጠላና ጋቢ እንጀራ መምሰላቸው፣ በተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሌላም የቀሳውስት ጥምጥም ልቃቂት መምሰሉ፣ የአገር ባህል ልብስ ለብሰው ወዲያ ወዲህ የሚሉ ኩሩ ሴቶች ጉርሻ መምሰላቸው...... በዚህም ሁሉ የጉርሻ ቅርጥ መያዛቸው......ተራ ገጠመኝ ነው?' <u>ናቢ ምዕራፍ 6 ዝኒ ከማሁ</u>

«ጨርቆስ እሩቅ ነው……ደ'ሞ ዳገት ነው፣ ገና አልበረታም» አለ አባቴ ፈገግ ብሎ እያየኝ……

«የተክለሃይማኖት ጉብታ……ስታየው ከባድ ይመስላል እንድ ፍሬ ልጅ ነው በደቂቃ ይወጣታል:: ስንት ይሆናል ዕድሜው?» አሉ እቴ ዘበናይ:

«አሁን ነሐሴ አሥራ አምስተኛውን ጨርሶ አሥራ ስድስተኛውን ያዘ»

«አሥራ አምስት?»

«አዎ……ያንቺው ስንት ነው?……ስንት ነህ አንተ?»

«ኸረ እኔ እንጃ አስራ አምስት……ይሆንሃል አንተ?»

«አሥራ ስድስት» አለ አለማየሁ

«ተው አትዋሽ አስራ ስድስት አይሞላህም»

«ከሦስት ወር በኋላ አሥራ ሰባት እገባለሁ» አባሰባቸው

«ይሔ የእኔው ታላቅ አይመስልም?» አለ አባቴ::

«እውነት አርጅቷል……የወለድከው ልጅ አለ የምታስብለት?» አሉ ሴትዮዋ በትኩረት እያዩኝ:: ፊት ለፊቴ ርብርብ ቦርጫቸው እንደ ባለ እርከን ገደል ቁጭ ብሏል:: አንዳንዴ ነቅነቅ ሲሉ ውሃ እንደተሞላ ፊኛ ሊዋልል ይጥራል:: የሣህኗ ድልህ በእንጀራ ተጠራርጋ ከአንድ ጐን (ከአባቴ ጐን) ብጉር የምታክል ነገር ቀርታለች:: መጥገባችን ሳይሆን ይሉኝታችን ወስኗት::

«ምሣህን የት ትበላለህ?» አሉ:: እሳቸው እኔን እያዩ ሲጠይቁ የሚመልሰው አባቴ ነው:: ለሰላምታ ነው የመጣሁት ወይስ በዘመድ ልስለል ነው?

«ምሣውን ይዞ ይሔዳል»

«ይኼ ጥጋበኛ 'አልሸከምም……ተሸክሜ አልሔድም' ብሎ አስቸግሮኛል» አሉ ዘበናይ::

«የእኔውም ቢቸግረው ነው እየጮኸን ይዞ የሚሔደው»

«አለማየሁ ሻይ ቤት ኬክ ለምዶ ሸፈተ–ከሰኞ ጀምሮ ወጥሮ ይዞ ይሔዳል»

(ምን ማለት ነው 'ወጥሮ?' እስከዛሬ ያልገባኝ ቃል፣ ስሜቱ ቢገባኝም:: ምንድነው የሚወጥረው? የምሳ ሰሃኑን?)

«በእግሬ እየሔድኩ ምሳ እንዴት እሸከማለሁ» አለ አለማየሁ::

«ዝምበል……ሰው ፊት ይከራከረኛል? እኔ ነኝ እናት አንተ?! የሚለኝን ትሰማዋለህ?……ይህቺ ምንድን ናት የቀረችው? አትበሉም?……አንቺ.!……ወጡ እንዴት ነው!? ድስቱን ጣድሽው!? በል አለማየሁ ይህቺን ጥረጋት……»

አሁንም አሁንም ይጣራሉ፣ አሁንም አሁንም 'አንቺ! እንቺ!' ግን የምትጠራዋን ልጅ አላየኋትም::

«እዚህ ቅርብ ለምን አታስገቢውም? የእኔን ይኼ አመት ይለፍ እንጂ

ደህና ከሆን እዛው ሽመልስ አመጣዋለሁ፤ በእግሩ ይሄዳል……»

«አድርገህ ተገላገል፣ ልጁም አይድከም:: የእኔው እዛ አንዳንዴ ሐብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ጋ ሱቅ አለችኝ አይደል ከትምህርት ቤት ሲወጣ በዛው እዛ ጎራ ብሎ ያግዛል……ብሏት እንጂ ለምን ነው የምትተዋት……አለማየሁ ብላት»

ትልቅ ቀይ ነጥብ የመሰለችው ድልህ ላይ አፍጠው::

አለማየሁ ሁሉን ነገር እንዳልፈለገ ፊቱ ላይ ይነበባል:: በእግር ትምህርት ቤት መሄዱን፣ ምሳ መሸከሙን፣ የምትጠረገዋን ድልህ በልቶ መነሳቱን:: መከራከር፣ እምቢ ማለት የሚችልም አልኾነም:: ሦስቱንም አልቻለም:: በቀስታ እጆቹን ከደበቀበት አውጥቶ ዘረጋ:: በጣቶቹ መሃል መሃል እስከ ቁርጭምጭምታቸው ድረስ በእከክ ነጭ ነው:: ሲያሳምጥ እንጂ እንጀራ ሲቆርስ ወይም ጉርሻውን ሲጠቀልል እንዳላየሁት ትዝ አለኝ:: አስደናቂ ችሎታ ነበር:: ልቤ የት ነበር ግን እንዲያ ሲሸውደኝ? እከኩ እንዳይታይበት እንደ አዳኝ እያደባ ይበላ እንደ ነበር ገባኝ:: አባቴ ቶሎ ዐይኖቹን ከልጁ እጅ ላይ ዞር አደረገ:: እኔም ለመሸሽ ስል ብቻ ያስመረረኝን ያሰደበኝን ጠላ ለመጠጣት ብርጭቆዬን አነሳሁ……

ሣህኗ ንፁህ ኾነች:: የእንጀራ ዐይኖች ድልሁን ጠርገው ሲወስዱ የፈጠሯቸው ቀጫጫ የድልህ መስመሮች ካልሆኑ ያጎጠጎጠ ፈጣጣ ቀይ ቀለም የለም:: እጄን ለመታጠብ ሀሳብ ሳቀርብ ሴትዮዋ የድልህ ምልክት የሌለበት ደረቅ እንጀራ በያዘ እጃቸው ወደ አንድ ኮሪዶር እያሳዩ:

«ያን ተከትለህ ውጭ……ከቤቱ ውጭ ቦንባ አለልህ እዛ ታጠብ» አሉኝ::

ከጀርባ ሰፊ ሾጣጣ ቢጫና ቀይ የኾነ ሳር የበቀለበት አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ወና መሬትና ረዥም በብሎኬት የተሰራ የአገልግሎት ቤት አለ:: ከእዚያ ከማድ ቤቱ የሽር ጉድ ኮቴ ይሰማኛል:: ልሰይመው የማልችል የምግብ ጠረን አፍንጫዬን እንደ ሰራዊት ይወረዋል:: ምንድነው? እያልኩ ባነፈንፍም ያልገባኝ:: የሰርቪሱ ቤትና ሳርማ ሜዳው ከሚገናኙበት ቦታ ትልቅ የብቅል ስጦ አለ:: እሱን ወደ ቀኝ ትቼ ካለፍኩ በኋላ ሜዳው መሃል ከመድረሴ በፊት በደመቀ አረንጓዴ ሳር የተከበበች ቧንቧ አየሁ:: አጠገቧ ውሐ ያበሰበሳት ሳሙና የተሸከመች ትንሽ የእንጨት ጠረጴዛ አለች:: እዛም ሄጄ እጄን እየታጠብኩ ሳለሁ ከኋላዬ ኮሽታ ሰማሁ:: ወደ 'ዚህ አልፌ ስመጣ ማንም ስላልነበረ ደንግጬ ዞር አልኩ:: አክስቴ ጀርባቸውን ወደ እኔ አዙረው፣ የዘረጉት ስጦ የተስተካከለ ፀሐይ እንዲያገኘው ለመንበልበል ጥቂት እስኪቀራቸው ድረስ ሳር መሬት ላይ ተንበርክከውና ተወጥረው እጃቸውን እንደ አካፋ አድርገው ብቅል ያገላብጣሉ:: በዚህ ወቅት ባለአበባ ቀሚሳቸው ወደ መቀመጫቸው ተሰብስቦ በሕልሜም ይሁን በ'ውኔ አጋጥሞኝ የማያውቅ ልዩ የኾነ በቃላት ዘርዝሮ መግለፅ የሚከብድ አስገራሚ የውስጥ ሱሪ አየሁ::

**(ታላላቆችን ማክበር ባህሌ ነው:: በዕድሜ ከእኔ ያረጁ ሰዎች የሚናገሩትን በጥሞና አዳምጣለሁ:: ይሄ ጴንጤው አባቴ፣ ጨርቆስ ሲጋጅ እናቴ፣ መሰል አዛውንትና የባልቻው ብርሃኑ ጃርሶ**

**ያስተማሩኝ ዕውቀት ነው። እስከ ዛሬም ያልጣልኩት ልምዱ ነው። በዕድሜ ከፍ ያሉትን ሰዎች ሁልጊዜ 'ጋሼ' ብዬ እጠራቸዋለሁ። ያረካኛል። ዛሬ ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያምን ፊት ለፊት ባገኛቸው አልዋሽም እንደሌላው ሰው አድር ባይ ለመሆን ወይም ለመጣበስ ወይም ስርጎ ገብ ከሆንኩም የምፈራቸው ለመምሰል «ፕሬዝዳንት መንግስቱ፣ የመከላከያ ምናምን ወዘተ......» ሳይሆን «ጋሼ መንግሥቱ» ብዬ ነበር የምጠራቸው። ታዲያ ስለ አክስቴ በማወራብት ጊዜ ሴትዮዋን በማክበር ብቻ ስለዚህ—በከፊል እንኳን ስላየሁት የውስጥ ሱሪ ሰፋ አድርጌ ከማብራራት ተቆጥቤአለሁ። ይሄ ድርጊቴ ከደራሲነቴ /ከመፃፍ/ ጋር የተደበለውን ቅንነቴን ሊያበላሽ እንደሚችል ብገምትም የፈለገው ይምጣ ብዬ ቀጥዬበታለሁ። በዚህ አቋሜም ማንም ሃያሲ ነኝ ባይ ቢተርበኝ፣ ቢያንቋሽሽኝ ልፋቴን በደስታ እቀበለዋለሁ። ያስፈራኝ ጉዳይ (ፊሪ አልባልና) የገለፃ ዝርዝር ውስጥ ከገባሁ የዘመኑን የሰለጠነ አንባቢ በማሳቅ ትጉኋን አክስቴን እንዳላጣጥላት፣ ከዚህም ተያይዞ እናቶቻችንን በአጠቃላይ እንዳላኪያኪስ ነው። ይሄን ለመፃፍ ስነሳ ግን ዕውነት ዕውነቷን እጠቅሳለሁ በሚል በመሆኑ ራሴ ውስጥ አሳዛኝ ግጭት መፈጠሩ አልቀረም። በትንሹም ቢሆን የልፋቴን ውጤት ጤነኛ ለማድረግ በከፊል ስላየሁት ስለዚህ ዕቃ/የውስጥ ሱሪ/ ጥቂት መግለጫ ቃላት ልወርውር። ነጭና ነጭ የመሰለ ቀለም አለው(የቀሚሳቸው ጥላ ስላረፈበት ቀለሙን በቅጡ ለመለየት አስቸጋሪ ነበር)። እግር ማስገቢያ ቱቦዎቹ ግለቂያ ላይ ስንዝር የሚያክል ስፋት ያለው ኪሮሽ ስራ የተጠለፈ ዘርፍ ዙሪያውን አለ። ቁመቱ ከጉልበታቸው ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ይቆማል)**

እጄን ታጥቤ ቀድሞ ወደ ነበርኩበት ሳሎን ክፍል ከተመለስኩ በኋላ የአባቴ አክስት ብቅል ከሚያስጣጡበት መጥተው ስለ ጠላ ሳይሆን ስለልጃቸው ሲያስቡ እንደቆዩ ሁሉ ኮስተር ብለው:

«አለማየሁ ሰማህ? ከነገ ጀምሮ ምሳህን ውሰድ—ከወንድምህ ጋር አብረህ ትበላለህ። ምናለበት ከወንድም 'ና ከጓደኛ ጋር ተማሪ ሁሉ ተሰባስቦ ቢበላ ምን አለበት?» ለጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃሳብ ያቀረቡ ይመስላል።

«ኸረ ልክ ነሽ እሱስ» አለ አባቴ

(ለጤፉም እየተጣበሰ ይሆናል)......

ከአለማየሁ ጋር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምሳችንን አብረን እንድንበላ ቢወሰንም ደስተኛ አልነበርኩም። የእኔ ክፍል 9ዲ የእሱ 9ሲ ነው። ጎረቤት ነን። በምሣ ሰዐት 'ጠፋህብኝ' ብዬ ማምለጥ አልችልም። ጥሩ ምግብ እንኳን ያመጣ ነበር። የእኔ ምግብ ወይ ሽሮ፣ ወይ ክክ ነው። አልፎ አልፎ ጉረቤት ወይ የሠፈር ሰው የላሜን በሽታ ሐኪም አላገኘውምና ልትሞትብኝ ነው ብሎ አባቴን ለእርዳታ ጠርቶት ቅርጫ ካልገባን በተቀር ስጋ አላመጣም (ጨርቆስ አካባቢ ብዙ ጊዜ ምስማርና ላስቲክ እየበሉ የሚታመሙ ከብቶች አሉ። ከብት ለማርቢያ

ባይመችም የሚጥረው ሰው ግን ብዙ ነው):: አለማየሁ የፈለኩትን ምግብ ባመጣ ግድ የለውም......እኔ ደ'ሞ የእጁን እከክ እያየሁ ምኑም አልበላልህ አለኝ:: ብዙ ጊዜ ምሳ ሰዓት እንዳይደርስ እመኛለሁ:: ትምህርት ቤት ቢረበሽ እመኛለሁ:: ለሁለት ሰዓቶች ሞቼ–የምሣ ሰዓት ካለፈ በኋላ ብነሳ እወዳለሁ:: ት/ቤቱ ውስጥ ብዙ ጊዜ ውሐ አይመጣም:: በዚህ ምክንያት እጅን መታጠብ ይከብዳል:: አባቴ ደ'ሞ–አልገባው ይሆን?–ስለ ልጁ ጤንነት ይጠይቀኝና ዝም ይላል::

«የእቴ ዘበናይ ልጅ ደህና ነው?»

«ደህና ነው»

ከዛ ዝም::

«እንደዛ ያለ ትልቅ ልጅ ያደረሰች አይመስለኝም ነበር»

(ትልቅ እከክ ሊል ይሆን?)

«ዕድሜዋም እኮ ትልቅ ነው እኗ......እምም የእኔ ትልቅ ሳትሆን ትቀራለች?»

(ከጭላሎ ብርድ ቢያመልጡ ከፋቸው?)

እኔ የአባቴ ጭቅጭቅ፣ ነገር ምልልስ፣ የአንድ ወገን ንትርክ፣ እና የመሳሰለ እንዳያጋጥመኝ ፈርቼ ዝም እላለሁ:: ይሄ መልስ እንደሚጠብቀኝ አውቃለሁ:

'ኮርተህ ነው'......

ከአለማየሁ ጋር ስንበላ የምሳ ቦታ የምመርጠው እኔ ነኝ......ብዙ ጊዜ ሜዳ ላይ መብላት እወዳለሁ:: ሜዳ ላይ ዐይኖቼን የሚስቡ ነገሮች አያለሁ:: የክፍላችንን አንድ ተማሪ አይና ስለእሱ አወራለሁ......ኳስ ሲጫወቱ አያለሁ...... ዘሎ ለመግባትም ይቀርበኛል:: መማሪያ ክፍል ውስጥ የምንበላ ከሆነ ግን ብዙ ጊዜ የምሳ ሰሐኑን ማየት አለብኝ ይሄም ምርጫ ሳላቋርጥ ያከከ እጁን እንዳይ ያስገድደኛል::

ከአለማየሁ ጋር ስበላ በማይገባኝ ምክንያት ትዝ የሚለኝ የእናቱ የውስጥ ሱሪ ነው:: ማሰብ እፍራለሁ......ግን በአይነ ሕሊናዬ እንደ ዜፔሊን ጥየራ በስድስት ኪሎ ሰማይ ላይ እየተንሳፈፈ ሲመጣ አየዋለሁ......መርካቶ ላይ ጥላሞቱን ይጥላል......ሕዝብ ወደ ላይ እያንጋጠጠ ያጨበጭባል......ወደ ቢሾፍቱ እየተንሳፈፈ ያልፋል......የአየር ሐይል ፋንቶም ጀቶች ደብድበው እስኪጥሉት...... ስድ ዕላሎቴ ሳቁን እንዳያመጣው ቶሎ ዐይኖቼን ስገልጥ የማየው ጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ሁለት አጥቆች ያህል የተተከሉትን፣ ተተክለው የሚፈተፍቱትን እከክ የፈሰሰባቸውን የአለማየሁን ቀኝ እጅ ጣቶች ነው፣ አመድ የመሰለ የዘመዴ የእምባር መዋያ ነው......

አንዳንዴ የማስበው ሐጢያቴ ገብቶት እናቱን እየተበቀለ ይመስለኛል......

ይኼን ሁሉ ለማንም አላወራም:: ለማንም አልናገርም:: አብራኝ ጎኔ ለምትቀመጥ በሌላ ነገር ለማምናት ፎለፎል የክፍል ጓደኛዬ ለፀሐይ ለገሰ

እንኳን ልነግራት አልፈለኩም:: እሷ የምታውቀው ሰው አለማየሁ ክፍል ውስጥ ቢኖርስ? እሷ የምታውቀው ሰው አለማየሁን ቢያውቀውስ? የፀባይዋ ማዕከል መሳቅ ነውና ሌላው ሁሉ ቀርቶ ብትስቅብኝስ? ይህቺ ቀላል የመሰለች ሁኔታ የትምህርት ቤት ሕይወቴን ኩምጣጣ አደረገችው:: ቶሎ ትዕግስቴ የሚያልቅ፣ ቶሎ የምሳደብ፣ ሁሉን ነገር በንጀሳ የምተረጉም፣ ዕድሌን ረጋሚ ሆንኩ:: ግራ ነው:: የማንፈልገውን ነገር አድርጉ ሲሉን ከባድ ተዕሶኖ እንዳለው የገባኝ ያኔ ነው:: ባልናገረውም በልቦናዬ ሲንሸራሸር የሚውለው የዚያን ጊዜ መፈክሬ:

«ማንንም ሰው ደስ የማይለውን ነገር/ጉዳይ አታስደርገው!!»

አንዳንድ ጥቅሶች ዘመንን ይገልፃሉ::

## ቦንዡ[131] አንድ ሰማያዊ

የፈረንሳይ አስተማሪያችን የማስተማሪያ ፕሮግራሟ ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ላይ ነው:: ስሟ ላ ሻፔል ይባላል:: ንክ ነው የተባለው የታሪክ አስተማሪያችን የጋሼ ነጋ 'ገርል ፍሬንድ'[132] ናት ይላሉ:: ግን ይገርመኛል ምክንያቱም እሷ በጣም ወጣት የምትመስል እሱ መሸበት የጀመረ በመሆኑ ነው:: ለፀሐይ ለጌ/ለገሰ ይሄ ነገር ግራ እንደ ገባኝ ስነግራት በመሽኮርመም አፏን ይዛ በሳቅ ትሞታለች:: ቆንጆ በመሆኗ የተለያያ ዕድሜ ያላቸው ፈላጊዎች ስለነበራት ይሄ ትዝ ብሏት ይሆናል:: ከሰዓት በኋላ ደ'ሞ ብዙ ጊዜ ኮስተር ያለ ትምህርት የለም:: አስተማሪው የውጭ አገር ሰው ከኾነ (ብዙ ጊዜም ነው) ኢያሱ ክፍሉን ወክዬ አንድ ነገር ልናገር ይፈቀድልኝ ብሎ አስተማሪውን ይጠይቅና የትምህርቱን አቅጣጫ ያስለውጣል:: በተለይ ሕንዶቹ ላይ ተንኮሉ በደንብ ይሠራል::

«As you know sir we can not go India. We love India from what we heard (ልክ ነው እንግሊዘኛዬ አይደለም?!) we like you tell us a story about India (ምንድነው እሱ ተረት?!) Fairy tale, proverbs you know!»

አስተማሪው ደስ ብሎት ማስተማሩን ትቶ ከተመደበለት ፔሬድ ዘልቆ የሚያልፍ ተረት ያመጣል:: ተረቱ ይጣፍጣል:: ከትምህርቱ የበለጠ ይጥማል:: መዋሸት አይቻልም:: እንዲያውም የሚያስተምሩን አንዳንዴ በፍፁም አይገባኝም:: ወይም አያስደስተኝም::

ታዲያስ ይሔ ጥበቡ ፈረንሳይኛ አስተማሪ ላይ ስለ አልሰራለት መሰለኝ ሌላ ሌላ ማጠፋፊያ ነገር መቀመር ጀመረ:: ከመምጣቷ አምስት ደቂቃ በፊት ተማሪዎች ፊት ለፊት ቆሞ:

«ከላ ቻፔል የሚማርካችሁ ነገር ምንድነው?» አለ

ገዛኸኝ:

«እግሯ» አለ::

«ትክክል–ሌላስ? እስኪ እዛ ጋ 'እግሯ' የምትሉ እጃችሁን አውጡ»

---

131 መልካም ቀን(ፈረንሳይኛ) የሰላምታ ቃል ነው::

132 girl friend= የሴት ወዳጅ(እንግሊዘኛ)(አ)

ብዙ ልጆች እጃቸውን አወጡ::

«እኔ ደ'ሞ ምኗ ደስ እንደሚለኝ ታውቃላችሁ?»

«ምን?»

«ሙታንታዋ»

«ባለጌ»

ክፍሉ በሳቅ ፈረሰ

«የት አየኸው?»

«ትናንት ማታ»

«መስቀል ተራራ ነበርክ እንዴ?»

«የት ይሔዳል ይሔ--ጎንደር ጠጅ ቤት ከገርሉ ጋር ነበር ያመሸው:: አሰፉ ደህና ናት? ስንት በቆልት በሰናፍጭ ከመሰሎቻችሁ ጋር በላችሁ በመተባበር? የበቆልት ካውንስል ሳታቋቁሙ አትቀሩም»

አሃ አሃ ሆ ሂ ሂ ሆ አሃ አሃ

«ቆይ ዝም በሉ አንድ ሃሳብ አለኝ»

«ተናገራ»

«ሙታንታዋን ማየት»

«አይተኸው የለ አንተ»

«እኔ ያየሁት ትናንት ነው»

«ምን አይነት ነው?» አለች ፀሐይ በመሽኮርመምና በማፈር::

«ፀሐይ እረፊ! ይሔ የቤት ጉዳይ አይደለም:: የልዑል መኰንን ሴቶች ጠግበዋል»

«በየቀኑ ነው የምትለዋውጠው» አለ ሽመልስ

«ነገረችህ?» አለ ኢያሱ

«እንዳንተ መሰለችህ ፈረንጅ እኰ ናት:: አንተ አሁን የለበስከውን ሙታንታ ሚኒሊክ ሲሞቱ አያትህ ያደረጉት ነው:: ጎበዝ አያት መሬት ያወርሳል የአንተ አያት አሮጌ ሙታንታ ያወርሱሃል:: በአያት ያልታደላችሁ ብትኖሩ አንተና የእንጠጠ መዝሩጥ[133] ናችሁ:: ማታ አጥበሽ ጠዋት ነው የምትለብሺው አይደለም?......አልደርቅ ሲለው የጋለ ብረት ምጣድ ላይ ይጠብሰዋል:: የመሳለሚያ ልጆች ሰማችሁ በጣም በጠዋት ጬኸት ከሰማችሁ የኢያሱ ሙታንታ እሳት በዝቶበት ሲጮኽ ነው»

«ማብሸቅሽ ነው:: ወሬኛ! ያንተን አጎዛ ማን አየ:: ሰማ በሱፈቃድ

133 በተረት ውስጥ ያለ የጅብ ልጅ:: ሯጭ ለማለት ነው::(አ)

ሌላ ትንሽ ልጅ ፈልጉ......ገዳሙ......ና! ና!» እንደ ጠራኝ ያኔውኑ ሄድኩ:: ምክንያቱም ምሳዬን ክክ በእክክ ነው የበላሁትና ተበሳጭቼአለሁ......

«እዚያ ከበሱፊቃድ ጋር ትቀመጫለሽ:: አትፍሪ»

ኢያሱን ፊት ለፊት ቀርቤ በጥራት ያየሁት ያን ዕለት ነው:: በጣም ትልቅ አፍንጫ አለው:: ወደ ኋላ መንጋጋው አንድ ጥርሱ የቆሸሸች ወርቅ ናት፣ ስሊጥ ምናምን ተለጥፎባታል[134] ጥርሶቹ ንፅሕናቸው በጣም አጠያያቂ ነበር:: አንዳንዶቹ ለምን ተገልለው እንዲያ እንደ ተበደሉ አላውቅም እንጂ የቆሸሹ ትናንሽ ከፋይ ጫማዎች ያስታውሳሉ:: ምላሱም ቡላል ግራጫ ነው:: ቀርቦ እንደ አንድ ሁሌ እንደምንላፋ አንጋራ የማደርገውን ሲያብራራልኝ የፊቱ ስርዝመትና ስፋት የሚውጠኝ መሰለኝ::

«እዚህ ትሆኚና የላ ቻፔልን ሙታንታ አይተሽ ምን ዐይነት ቀለም እንደኾነ ትነግሪኛለሽ»

«እንዴት?»

«ፊትህን ዴስኩ ላይ እንዲህ አድርግ--አስተኛው:: ምን ታየኛለህ?--አዎ እንደዚ'»

«እንዴ? ብታየኝስ?»

«ምን ታይሃለች? አታስበላአ! ብላክ ቦርድ ያየሽ ምሰይ......»

ተማሪዎች በሙሉ «እይ» የተባልኩትን እንዳይ የኢያሱን ሴራ ደግፈው መጮህ ጀመሩ:: «እሺ» ብዬው ስለ ነገሩ ሳሰላስል ላ ቻፔል ክፍል ገባች:: ኢያሱ ያኔውኑ ወደ እኔ ዞር ብሎ «በርቺ ገዳሙ» አለና ጠቀሰኝ:: ከዚያ ዞር ብሎ ምንም እንዳላደረገ ሁሉ እየሳቀ ከሁላችን ከፍ ባለና ጎልቶ በሚሰማ ድምፅ:

«ቦንዡ ማዳም! ምናባታችሁን በደንብ እዩ......»

ሙታንታዋ ከታየ ማየት የሚጠላ የለም:: ግን ሁኔታው አይመችም:: አንደኛ ፊት ለፊት ነኝ፣ ሁለተኛ እንቅልፍ እንቅልፍ ይለኛል:: በተጨማሪ ሙታንታ የማየት ስሜት የለኝም:: ግን ከዚህ ያለመፈለግ ጀርባ እንደ ጉም የሞላኝ የየቀኑ ብስጭቴ አለ::

---

134 ኢያሱ ጥርስ ላይ ያየሁት ስሊጥ የእናቴን አባት አገር አሩሲን/አርሲን ያስታውሰኛል:: ያን ጊዜ በአገሪቷ የሰሊጥና የቦሎቄ እርሻ ንግድ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር:: ኢያሱ ክራንቻ ላይ ያየሁት ስሊጥ አንዳንዴ በጂኦግራፊ ስለ ትሮፒካል ፎሬስትና ስለ ትሮፒካል ሃይላንድ ፎሬስት ወይም ስለ ካሽ ክሮፕ ሳጠና ሳልፈልገውና ሳላቅደው ራሱን እንደ ቻለ አንድ መልካምድር ውል ይለኛል:: ያ ብቸኛ ስሊጥ (ወይም የመሰለ ነገር) እንደ አንድ ድክር የቅዝቃዜ ወግ ከዓይኔ ሕሊናዬ ረግረግ እየተንገዳገደ ይወጣል:: ይኼንን ስዕፍ እንኳን የኢያሱ መልክ ደብዝዞ ቢታየኝም ያ ጥርስና ያቺ ብቸኛ ቀዳዳ የመሰለች ስሊጥ ቦግ ብለው ይታወሱኛል:: ያኔም እሱን ት/ቤት ግቢ በየቦታውና በየጊዜው ሳየው(ሜዳ፣ ሳይብሬሪ ደረጃ ላይ፣ በጠራራ ፀሐይ ወዘተ......) ይገርመኝ ነበር:: መገረሜ መነሻ አለው:: ኢያሱ ከምሳ በሁዋላ ሁልጊዜ ከአፉ የማይለየው ትልቅ የሐረር መፋቂያ ነበረው:: ታዲያ 'ያ ስሊጥ ከዚህ የጥርስ መፋቂያ እንዴት አመለጠ?' እላለሁ:: አራት ዓመታት እዛ ተምሬ የማስታውሳቸው መቶ ገፅ የማይሞሉ ፍሬ ያሌላቸው ደካማ ትዝታዎች ናቸው:: ከነዚህም አንዱ ይኼ ቂጡ ስር ስሊጥ የለጠፈ የኢያሱ ቤዥ ጥርስ ነው::

ላ ቻፔል የአበሻ ስማችን ስለከበዳት ለሁላችንም የፈረንሳይኛ ስም አውጥታልናለች። የእኔ 'አሂ/ሔንሪ' ነው የፀሐይ 'ኒኮል' ነው የበሱፈቃድ አይያዝም–የኢያሱም አይያዝም። ለእሷ ካልኾነ ብዙው ለእኛ አይያዝም። ጥያቄ ስትጠይቀን የፈረንሳይኛ ስማችንን ጠርታ ነው። የፈረንሳይኛ ስማቸው የየቀኑ መጠሪያ ኾኖ የቀሩ ተማሪዎች አሉ። ፊት ለፊቴ የምትቀመጠው ቅድስት ስሟ ሻንታል' ኾኖአል። ዘመዶቿ እንደዚያ ሳይጠሯት አይቀሩም። እንዲያ ስትጠራ ትወዳለች። ስሟ እየሳባት ሳይሆን አይቀርም ፈረንሳይኛ ጉበዝ ናት።

«ቦንዡ» አለች ላ ቻፔል እንደገባች። አካሔዷ ያለ ልማዷ ቀሰስ ያለ ነበር። መአት ቂጥዋ ከኋላዋ እንደ ክብ ወንበር ይከተላታል።

«በሱፍቃድ እንግዲህ በርቱ» አለ ኢያሱ። ላ ቻፔል ትክ ብላ አየችው፡

«ኬስክ ቱ ዲ?» (ምን ተናገርክ?)

«አይ እነዚህ ሕፃናትን በደንብ አዳምጡ ነው የምለው» አለ በአማርኛ። ክፍሉ በሳቅ ፈነዳ። ላ ቻፔል ተበሳጭታ እኔና በሱፍቃድ ከተቀመጥንበት ዴስክ ፊት ለፊት ወንበር ስባ ተቀመጠች። እንዲህ በቅርብ ሳያት የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው። ራቅ ስል ቄንጠኛ ነገሯ ብቻ ይታየኛል። የምታምር ይመስለኝ ነበር። ስቀርባት ዕድሜዋ ትልቅ ኾነብኝ–ፊቷ ጠቃ ጠቆ የሞላው ነው–ፀጉር መብቀያ ቀዳዶች ዐይነት፣ ጥርሶቿ የበለዙ ናቸው። አንድ እግሯን አንስታ ሌላ እግሯ ላይ አስቀምጣ ማውራት ቀጠለች። ጭኗ ለስላሳ ነጭ ነው። ጭን የተደረበበት ከስር ያለው የሌላ ጭኗ ዛል እስከማየው ድረስ ሁለቴ ይከተፋል–ከዚያ በስተመጨረሻ ስማይ የመሰለ ሙታንታ ይታያል። በአጭር ቀሚስ የተጠቀለሉት እነዚያ ታላላቅ ጭኖች ልዩ ሚስጢር ነበራቸው። ጭንቅላቴ ውስጥ ብራ የበጋ ሰማይና ትኩስ የላም ወተት ተደበላልቀው ይፈሳሉ። የምታወራውን መስማት ትቼ ጭኖቿና ሙታንታዋ አእምሮዬ ውስጥ የፈጠሩብኝን የደስታ ስሜት እንደ ከረሜላ እጠባለሁ። በዚህ መሐል ጨከን ያለ እጅ የተንዠረገገ አፍሮ ፀጉሬን ያዘኝ። ያኔ የፈረንሳይኛ ስሜን ሰማሁ። 'አሂ!!!'። ቀና ስል ቲማቲም የመሰለው የላ ቻፔል ፊት። የኾነ ረዥም ቁጡ ንግግር በፈረንሳይኛ ጮኸች። ትርጉሙ ባይገባቸውም የክፍሌ ልጆች አላማዋን ስለተረዱ በሣቅ ጦሽ አሉ። ፀጉሬን ለቃ ወደ በር ሮጠች፣ ተመለሰች፣ ፊቷ ደም መሰለ። የከሰአቱ ፀሐይ አዳክሟት ያንቀላፋ የመሰለው ቁመናዋ ነፍስ ዘራ።

«ሲያምርባት» አለ ሽመልስ።

እንደገና አፍሮ ፀጉሬን ይዛ ድሮ ወደ ምቀመጥበት ወንበሬ እየጐተተች መለሰችኝ። የጭኖቿ ውበት እንጎሌ ዙሪያ እንደጉም አርፏል። የቂጧን መጉመጥመጥ፣ መንዘርዘርና መዝለል የማየው ድምፁ እንደማይሰማ የቴሌቭዥን ትዕይንት ነው።

እንደተቀመጥኩና እንደተረጋጋሁ የድርጊቴ ተፅዕኖ ተገለፀልኝ። ፀሐይ እየሳቀች፣ እየተሽኰረመመች ጎኔን ስትጉስመኝ ኢያሱና አርቦሾቹ በእኔ መጠቀማቸውን ብጠላም–ያየሁት ነገር ከመስዋዕትነቱ ጋር እንደሚመጣጠን ተረዳሁ።

ላ ቻፔል ንጭንጯንና ማስተማሯን ጨርሳ ገና እንደ ወጣች:

«የሙታንታዋ ቀለም ምን አይነት ነው?» አለኝ ኢያሱ

«በሱፌቃድ አይቿል» አልኩት

«ማን እኔ? ሒድ--እኔ ራሴ ፈርቼ አላየሁም»

«አላየንም እንዳትሉኝ? ቁንጮህን ጎትታ ያነሳችህ ለምንድነው?»

«እሷን መሰላት እንጂ አላየሁም» አልኩት::

«ፕላናችንን አበላሹ፣ እነዚህ አይረቡም» አለ ኢያሱ::

ለእረፍት ከክፍል ልንወጣ ስንል ከታረቀኝ ጋር በር ላይ ተገጣጠምን::

«የውስጥ ሱሪውን ቀለም ማወቅ ትፈልጋለህ?» አልኩት

«አልፈልግም:: የሴትዮዋን የግል ነፃነት ነው የተጋፋኸው» አለኝ

ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም:: የግል ነፃነት ትጋፋለህ ቀባጢሶ:: መራበሽ እንጂ ፍልስፍና አይገባኝም:: አላፈርኩም:: ቀጠልኩ:

«ልጠይቅህ አንድ ነገር? (እሺ እስኪለኝ አልጠበቅሁም) ሐራምቤ ሸሚዝህ ላይ የፃፍከው ምንድነው?»

«እም......ተነካናኪ?»

«እ......»

«አንድ ሰዐሊ የፈጠረው ቃል ነው:: በምትችለው አቅም ለአገርህ መልካም ነገር ለመስራት መሳተፍ ማለት ነው:: አገርህን በተመለከተ ስለ ሁሉ ነገር ለማወቅ መጣር ማለት ነው:: አንድ ነገር ብዙ ጎን አለው ብሎ ማመን ማለት ነው:: ስዕል ትወዳለህ?»

«አይ......»

«ስነፅሑፍስ?»

«እወዳለሁ መሰለኝ»

«ከምትወደው መነሳት አለብህ የተነካናኪ ትርጉም እንዲገባህ:: ከማወቅና ከማድረግ ነው የሚመነጨው:: ዕውቀትና ማድረግ የእነሱንም ሚዛን መጠበቅ ነው»

ምን ይላል ዐይነት አተኩሬ አየሁት:: ምን እንዳለ ሳይገባኝ አልፎኝ ሄደ::

ማታ ተኝቼ የተነጋገርነውን ሳስብ የምትፈልገውን መጀመሪያ ዕወቅ ያለ መሰለኝ:: የምፈልገው ምንድነው አልኩ ለራሴ?

'የምትፈልገውን ማወቅ' ብሎ ነገርስ?

ትምህርቱ ያደክማል:: ስራዬ ስለኾነ አጠናለሁ እንጂ:: ከአሥር አስተማሪዎች--ሦስቱ ቢሆኑ ነው የሚማርኩኝ:: ላ ቻፔልን እንደዚያ ካደረግኋት

በኋላ 'ረባሽ' ነው በሚል ግምት በተቆጣጣሪ ዐይን ታየኝ ጀመር። የፈረንሳይ አምባሳደር ሊመልሱት የማይችሉትን ከባድ ፈረንሳይኛ ጥያቄ በፈረንሳይኛ ልትጠይቀኝ የተነሳሳችው ከዚያ በኋላ ነው። ሳልወድ በግድ የፈረንሳይኛዬን ነገር በደንብ መከታተል ጀመርኩ። ብዙ ጊዜ ድንቅ በኾነው ሳያስጠነቅቅ በሚመጣው ድንገተኛ እርፍናዬ ትገረማለች። እኔም በጭኖቿ ውበትና በውስጥ ሱሪዋ ንፁሕ ስማያዊነት እንደተገረምኩ።

## ማርቲና እኔ

ቅዳሜና እሁድ ትልቅ ግለ-ደስታ የምጠብቅበት ጊዜ ቢሆንም፣ ልብሶቼን በማጠብና በመሳሰሉ ጉዳዮች–ወር ከገባ ደ'ሞ የዕድር ገንዘብ ለመክፈል ከቤቴ ራቅ ብዬ በመሳክ......እንደዚህ ትንንሽ በመሰሉ ነገሮች ተጳከሜ አንዲት ፌሽታ ነገር እንኳን ሳላደርግ ስንበቶቹ ያልፋሉ።

አንድ ቀን ወደ ቤት የሚመጣው የቧንቧ ውሐ መስመር ስለተቋረጠ እነ ማርታ አሳና ቤት ሔደህ ልብስ እጠብ ተባልኩ። ሣፋ አንጠልጥዬ፣ የማጥ በውን ጨርቅ በአንሶላ ጠቅልዬ ጀርባዬ ላይ አዘልኩና ሔድኩ። የእኔን የራሴን ልብስ ለማጠብ አንድ ሰዐት አይወስድብኝም። ቢበዛ ሁለት ሱሪ፣ ቢበዛ አንድ ሙታንታ፣ ቢበዛ ሁለት ጃኬቶች፣ ቢበዛ ሁለት ሸሚዞች፣ ቢበዛ ሁለት ጥንድ ካልሲዎች እና ቢበዛ ሁለት አንሶላዎች ነበሩ የማጥባቸው። የራሴን ልብሶች ለማጠብ ስነሳ እናትና አባቴ–'እግረ መንገድህን ይህቺን እጠባት' ብለው በድሉ ሕንፃን የሚያክል የጨርቅ ክምር ጎኔ ይጥሉልኛል።

እመረቅበት ይሆናል እንጂ'ህ፡

'ተባረክ፣ እደግ'

ተባርኬም እንደኾነ ሲደርስ አይቼው አላውቅም። ዕደግ ተብዬ እንደኾነ፣ ባይመርቁኝም ማደጌ የሚቀር አይመስለኝም......ለማደጉ ለማደጉ–ቢያንስ ለምልክትነት የእጅ ጣቶቼ ጥፍሮች እንደ ሙጃ እንደ ተመዘዙ ነው።

ጊዜው ከጠዋቱ አራት ሰዓት ትንሽ ቢያልፍ ነው። ሠፈሩ አስፋልት ላይ፣ ብዙ ሰውና መኪና በማይመላለስበትም የኩረኩንች መንገድ ላይ በቅዳሜ የመዝናናት ተስፋ የተጠመዱ ጎረምሶችና ሕጻናት ፈሰዋል። ሜዳዋ ጠርዝ ላይ ካለች አንድ ዛፍ ስር መቦኮተ የተባለ አንድ የስፈራችን ድንክ ልጁን ጭኑ ላይ አስቀምጦ ጨዋታ ያያል......በቀኝ እጁ የልጁን እናት ያካል......ትልቁ ሜዳና አካባቢው በጎረምሶች ጎርናና ድምፅ ሙሉ ነው። የማርታ ቤት ከዚህ ሁሉ የቅዳሜና እሁድ ፌሽታ ጎን ነው የቆመው። እሷ ቤት ግቢ ሆኜ የሚጠለዝ ኳስና እየጮኸ የሚሳደብ ጎል ኪፐር እሰማለሁ። እነ ማርታ ቤት ግቢ እናቷና እሷ ልብስ ሲያጥቡ ደረስኩ።

እናቷ:

«ደህና አደርክ?» አሉኝ።

«ደህና» አልኳቸው። ማርታ አይታኝ ፈገግ አለች።

«ውሐ ቆመባችሁ አሁንም?» አሉ።

«አዎ»

አጠገባቸው ሳፋውንና የተሸከምኩትን ጨርቅ አስቀመጥኩ። ከልብሴ ቋጠሮ በጀርባና በሆዱ በኩል 777 የሚል ቁጥር የተፃፈበት ትልቅ፣ ጠርዙ ስለት ያለው አዲስ ሳሙና አወጣሁ። ከማርታ ባሊ ውሐ ወስጄ ሳፋው ላይ ደፋሁ– ውሐው ይበርዳል። በመጀመሪያ ወፍራም ባለ ገበር የከፋይ ጃኬቴን አስገባሁ። ይሄ ልብስ ውሐ ጠጥቶ እስኪረሰርስ ጊዜ ይወስዳል።

«ይሄን ሁሉ አንተ ብቻ ልታጥብ ነው?» አሉኝ እናቷ ወደ ከመርኩት ጨርቅ አይተው።

«አዎ»

«ኸረ ተባረክ። እናትህ ታድለዋል–እኚህ የኔ ሴቶች እንኳን ተለምነው ነው የሚያጥቡት። በጭቅጭቅ። በጭቅጭቅ ራሴ ዞሮ ነው»

(ማርታ ሁለት እህቶችና ዜሮ ወንድሞች አሏት)

ሳልወድ እንደማጥብ አያውቁም። ዝም አልኩ። ማርታ እያጠበች እናቷ ምርቃት ላይ በማሾፍ ፈገግ ትላለች።

/አላጥብም፣ ደስ አይለኝም/ ብል......

መሰረቱ ጠንካራ የሆነ እኔ ልቀናቀነው የማልችል በልምድ የተፈተሸ መከራከሪያ ያቀርባሉ፡

(ምን ስትሰራ ልትውል ነው? ያው መከረኛ ትምህርት ነው? ሁልቀን ደብተር፣ ደብተር ምን ይሰራል......የጉልበት ሥራ ጥሩ ነው)

ይቀጥላሉ፡

/ካጠብኩ በኋላ እጆቼ ሲደርቁ አልወድም/

(ቅባት ተቀባዋ)

/ካጠብኩ የራሴን ልብስ ብቻ ማጠብ አለብኝ/

(አልጠገብክም?)

/ትምህርቱ አስጠልቶኛል። ሌላ ሌላ መፅሐፍ ማንበብ እፈልጋለሁ/

(ዋናው ልብ ነው ብታነበው ምን ይሰራል?)

/ስፖርት ራሱን የቻለ ውጤት ያለው የጉልበት ሥራ ነው። ለመላው ሰውነት ገንቢነት አለው። ልብስ ማጠብ ለአንድ የአካል ክፍል ግንባታ ብቻ የሚረዳ ነው። ለክንድ ምናምን/

(ግርማ ቸሩን እንጠይቃለን)

/ብዙ ጊዜ አጉንብሰው ልብስ ሲያጥቡ የሚውሉ ሰዎች ሸፋፋ የሚሆኑ ይመስለኛል......./

(የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተፅፎአል?)

እኔና ማርታ በፀጥታ ስናጥብ ቆየን። ጠይም ክንዶቿ (እንደ ት/ቤት ጓደኛዬ እንደ ፀሐይ ጉንጮች የለሰለሱ) እስከ ክርኖቻቸው በሳሙና አረፋ ተሸፍነዋል። አልፎ አልፎ ግንባሯን በእጇ አይበሉባ ታካለች--ወይም ላብ ትጠርጋለች። የአይኗ አከዳደን ያናወዘ ያስመስላታል። ቀሚሷን ወደ ጉያዋ ሰብስባለች......ስራ ጠምዷት ልብ አትልም እንጂ ጠይም ጭኖቿ በስፋት ተጋልጠዋል። ጥላ ውስጥ ስለተቀመጠች ሙሉ ግርማቸውም ኾነ የውበታቸው ገፅ አልተከፈተም......አንዳንዴ ጭኖቿ መሃል አሳንብሼ የአንድ ጭኗን ለስላሳ ቦታ በመርፌ ብወጋው ደም ሳይሆን የማር ወለላ የሚያኾ ካልሆነም የአበባ አውላ የሚያንዠረዥር ይመስለኝ ነበር......

እያጠብኩ እያለሁ የማርታ እንደዛ በከፊል መጋለጥ ፈረንሳይ አስተማሪዬ ላይ ያደረኩትን ኩሸት አስታወሰኝ። ስሜቷ ምን እንደሚሆን ለማወቅ ልነግራት ፈለግሁ።

«ስሚ ማርታ!»

«ምነው?» አለችና ቀና አለች።

«ምን እያሰብሽ ነው?»

«ምንም»

«አንድ ነገር ልንገርሽ?»

«ምንድነው?»

«ትምህርት ቤት አንድ ጊዜ ያደረኩትን?»

«ምን አደረክ?»

ለትንሽ ጊዜ ዝም አልኩ። አንገራገርኩ።

«ተናገር እንጂ!--ለምን መጀመሪያ ልንገርሽ አልክ?»

«የፈረንሳይኛ አስተማሪያችን......» በሙሉ ታሪኩን ነገርኳት።

«አንተ ባለጌ ኾነሃል!» አለች። ቆጣ ብላ። ስትቆጣ ማሚት ትሆናለች፣ ታባባለች።

«ይሔ ብልግና ነው?»

«ታዲያስ። ደንበኛ ዱርዬነት አይደለ!»

«ሰው አስገድዶኝ ነው ያየሁት--እኔ የውስጥ ሱሪዬን ቢያዩ ግድ የለኝም»

«አንተ ወንድ ነሃ!!» ጮክ አለች።

«ወንድና ሴት አለው እንዴ?» መቀለዴ ነበር

«እንጃ» ቁጣዋ አልበረደም

«ቆይ እሺ. አንቺ አሳይኝ ብልሽ አታሳይኝም?»

«ሒድ እዛ!» ወደ ኋላዋ አየች:: እናቷ አካባቢያችን መኖራቸውን ለመፈተሽ:: የሰሙን መሰላት:: በዝምታ ማጠባችንን ቀጠልን......ከሜዳው አንዳንዴ የሚነረት ኳስ ድምፅ ይመጣል......ወደ ሰማይ አንጋጠው ኳስ የሚጠብቁ ልጆች አስባለሁ......ፀሐይ ከፍ ስላለች የጨረሯ ተዳፋት ማርታ የተቀመጠችበት ቦታ ደርሷል:: ብርሐን ወደ ጉያዋ በገባ ቁጥር በስሱ የተቆላ ወዛም ቡና የመሰለ ቆዳ ይታያል::

«ምን ታያለህ?»

«ምንድነው የማየው?»

«አዎ......ሙት ስድ ኾነሃል!»

«ሙታንታ ካደረግሽ ምን አያለሁ»

በቀሚሷ ጭኖቿን ለመጋረድ ሞከረች::

«ለምን በውል አናደርገውም?» አልኳት

«የምን ውል?»

«እኔ ልብስሽን አጥባለሁ፣ አንቺ ሙታንታሽን ታሳይኛለሽ»

ዝም ብላ አየችኝና:

«ውሸት:: በኋላ እምቢ ልትል ነው:: እምቢ:: አንተን አላምንህም»

«ለምን? እኔ ዋሽቼሽ አውቃለሁ?»

«አልፈልግም......እጠብልኝ መጀመሪያ»

«አይሆንም ተይው:: እኔ አንቺን ብሆን ኖሮ......ያውም ጉቦ ከፍዬሽ ሁሉ እምቢ ትያለሽ?......ዕንግዳ የማታውቂኝ ሰው አደረግሽኝ እንዴ?»

«ቢሆንም አልፈልግም» አለች መረር ብላ

መከራከር አቆምን:: ቀና እያልኩ አንዳንዴ ወደ ጭኗ እቀላውጣለሁ...... እናቷ ከቤት ይወጣሉ ይገባሉ......አንዳንዴ ያንጐራጉራሉ:: ከመሃል ማርታ ሳይታወቃት የእናቷ እንጉርጉሮ እንደ ጉንፋን ተጋብቶባት ዐይነት እሱን ጠልፋ ታዜማለች (የሂሩት በቀለ ዘፈን ሳይሆን አይቀርም):: አጉንብሼ እሷን ሳላያት ግን ስሰማት ብቻ አሮጊት ትመስለኛለች......አርፋጃ ነውና ፀሐይዋ ከራለች...... ከታች ከሜዳው ነጫጭ፣ ቢጫ፣ ጥቁር ቀያቴ ቢራቢሮዎች ወዲያ ወዲህ እያሉ እየተንገዳገዱ መጥተው ያለንበትን ግቢ በቸልታ አቋርጠው ያልፋሉ:: እሳቴዎች ሰማይ እያከኩ......ያጋጠማቸው የዛፍ ቅጠል ላይ ተለጥፈው ይንፈራፈራሉ...... ከተጣበቁበት እየተላቀቁ እወዲያ የቆርቆሮውን አጥር እየመቱ ሳር ላይ ያርፋሉ......እጆቼ የረጠበ ክርታስ መስለዋል::

ቀጥ ብሎ የቆመው የግቢው ሣር መጠውለግ......እንደቀለጠ ላስቲክ መልፈስፈስ፣ መላዘግ ጀምሯል......

ማርታ ልብሷን አጥባ እንደ ጨረሰች ከፊሉን ልብስ መሬት ላይ፣ ከፊሉን ሽቦ ላይ፣ ከፊሉን አጥር ላይ አሰጣች:: ተቀምጣ ታጥብ የነበረችበት ቦታ እንደ ወንዝ ዳር ጨቅይቷል:: የቆሸሹ ጭቃ የለበሱ እግሮቿን ሳፋ ላይ አስቀምጣ መታጠብ ጀመረች:: ቀድሞ ለማትጠነቀቅላቸው ጭኖቿ አሁን ታሪኳን ከነገርኳት በኋላ ትጋርዳቸዋለች......አንድ እጇ ከእግሮቿ መሐል አይነሳም::

የዝምታዋ ከብደት ደ'ሞ በሚያስፈራ መልክ እንደ ግዑዝ ነገር እንደ ግራጫ ቡሉኮ ምናምን መታየት የሚችል ይመስላል:: ዋናው የአጥሩ በር እንኳን ቀዳዳዎቹ በበርኖስ ቁርጥራጮች የተጠቀጠቁ እስኪመስለኝ:: እናቷ ከቤት ውስጥ ፊታቸውን በመስኮት ብቅ አድርገው ጠሯት:: ድምቅ ቀይ ሴት ናቸው:: ዕርጥብ እግሮቿን ነጠላ ጫማ ውስጥ አስገብታ እየተሳበች ሔደች:: ወደ ሰማይ የምትነሳ ትመስላለች–በነፋስ እንደሚገለብ የተሰጣ ጨርቅ:: የቂጥዋ ክብ ቀሚሷን ነፍቶት ገና ከምጣዱ የወጣ ሴት አኩሪው ያልተገፈፈ ሙልሙል ያስታውሳል......ከሁለመናዋ የሴትነት ወላፈን ይነሳል......የምትነቃነቅ አስማት ናት:: ማንም እንዳለው::

እኔን ከንዶቼን እየደከመኝ ነው:: አንሶላዬን ማጠብ ጀምሬአለሁ:: አንሶላዬን ማጠብ የምጀምረው ወደ መጨረሻው ነው:: አንሶላዬ ደ'ሞ በጣም ቆሽሿል:: ጭንቅላቴ የሚያርፍበት ቦታ ላይ አንሶላው ግራጫ ቀለም ይዟል:: ፀጉሬን አልፎ አልፎ የምቀባው ቅባትና ላብ ሊሆን ይችላል:: ሌሊት ሌሊት እንቅልፍ ሲወስደኝ ከአፌ የሚወጣው ለሐጭ ነጭ የነበረውን የአንሶላ ቀለም አወይቦታል:: ሲጀመር ትልቅና ጉርባጣ የነበረው የልብሱ ሳሙና ትንሽ፣ ለስላሳ፣ የሚያዳልጥ፣ ሞላላ ሲመጠጥ የዋለ ትልቅ ከረሜላ (መልኩ ደስ ባይልም) እየመሰለ ነው:: አጥቤ የጨረስኳቸውን ልብሶች እየጨመቅሁ ጉኔ ሳር ላይ አስቀምጣቸዋለሁ......ማርታ ልብሷን ቀይራ ሽፍን ጫማ አድርጋ ከቤት ወጣች:: በአንድ እጇ መፅሔት በሌላ እጇ ቀድሞ የለበሰችውን የቆሸሸ ልብስ ይዛለች:: ንፁሕ ነጭ ናይሎን ካኔቴራ ከላይ እና ቀይ ጉርድ ፒሊሲ (ሽንሽን) ቀሚስ ለብሳለች:: ዐይነባር ካናቴራዋን ጡቶቿ ግራና ቀኝ እንደ መርፌ ጥላሞት ወግተው ይዘውታል:: ከብብቷ እስከ ዳሌዋ የወረደውን ቢያዩት ቢያዩት የማያልቅ የመሰለውን የሽንጥዋን ቢጋር በዚያ ናይሎን ውስጥ አያለሁ......

**(በሦስተኛው ወር የመጀመሪያ ልጃችንን ወልዳ አራስ ሆና እንደተኛች፣ መውለዷ ውበቷን ያበላሸባት መስሏት በማዘን በገላዋ የተጠራቀመውን ስብ እየጨበጠች ስትለቅ፣ ጡቶቿን እየዘገነች በአወዳደቃቸው ስትተክዝ፣ ጎኗ ጋደም ብዬ በምጥ የቆሰለ ዛላዋን ከትከሻዋ እስከ ዳሌዋ እየሳምኩ......በዝምታ የአፌን ጎዳና ስታጠና እሷ ብቻ እንድትሰማኝ ዐይነት (ከእኔና ከእሷ በስተቀር ማንም ባይኖርም) እንዲህ አልኳት፡ 'ዘንፋላዬ ሁሌም የእኔ እተጌ ነሽ»...... ጓቅ ውስጥ ሳይሆን ሳግ ውስጥ የተነከረ ለመስማት ያዳገተኝን የሆነ ነገር ተናገረች)**

ያንጠለጠለችውን ቀሚስ ወረውራ ከእኔ ፈቀቅ ብላ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠች:: ረፍረፍ ፀጉሯ ከግንባሯ ተገልቦ ግራና ቀኝ ነፋስ ውስጥ ተንዘርፎ

በፍጥነትና እና በዝግታ እየተወዛወዘ......መሐል አናቷ ላይ በማስመሪያ የወጣ የመሰለ ነጣ ያለ የፀጉር ክፍላት አለ (እሱን ሳይ ልቤ ሁልጊዜ ለማይገባኝ ለሆነ ነገርዋ ይቃቃል......) የቆሸሸ ለብሳ ዓይቼአት አላውቅም......ቆየሁና......ዝምታዋን ስለማልወድ:

«ምንድነው የምታነቢው?»

«ምን አነባለሁ? ስዕል ነው የማየው......ደስ ደስ የሚል ስዕል አለ:: ትልቋ እህቴ እየቀደደች መኝታ ቤት ግድግዳዋ ላይ እየለጠፈች ጨረሰቻቸው እንጂ.»

ካጐነበስኩበት ተነስቼ ቆምኩና የተኮማተረ ገላዬን ለማዝናናት ተንጠራራሁ:: እግሮቼን አራገፍኩ......ጭኖቼን በቦክስ መታታሁና ወደ ነበርኩበት አቀማመጥ ተመለስኩ:: አጥቤ ልጨርስ የቀሩኝ ሁለት ሦስት ካልሲዎች ናቸው::

እነዚህን አልፎ አልፎ በቀዳዳ ጫማ ስለ ማደርጋቸው የኳስ ሜዳ አፈርና ሳር ተለጥፎባቸዋል:: የካልሲዎቹ አፍንጫዎች ጭቃ እንዳቦካሁባቸው ሁሉ ልቁጥ መረሬ አፈር አከማችተዋል:: ማርታ እያየችኝ ማጠብ ቢያሳፍረኝም አማራጭ አልነበረኝም:: ቢሆንም ማርታ አታይም:: እግሮቿን ፊት ለፊቷ ዘርግታ መፅሔቱን እየገለጠች ገፆችን ግራና ቀኝ ታጤናለች:: አንዳንዴ የኾነ ቦታ ላይ አተኩራ ትቆያለች::

«እስከዚህ ደስ የሚሉ ስዕሎች አሉት?» አልኳት

«ፎቶግራፎች ናቸው»

«ፎቶግራፍ?»

«አዎ......ምነው? አውሽኝ እንዳትል»

«ምናለበት»

«ይሔ 'ፀሐይ መስፍን'[135] ወይም 'የእኛ ሰው በደማስቆ'[136] መሰለህ...... አላውስም:: ልትቀድብኝ ነው አይደለም?»

«እኔ ሌላ አሪፍ መፅሐፍ እሰጥሻለሁ» መፅሔቱ አጓጓኝ::

«ምን ትሰጠኛለህ?»

«'ሞንተ ክሪስቶ ካውንት' የተባለ በጣም አሪፍ መፅሐፍ አለኝ»

«እንግሊዘኛ ነው አማርኛ?» እንግሊዘኛ ማንበብ እንደማትወድ አውቃለሁ:: ለምን እንደምትጠይቀኝ እንጃ::

«ከእንግሊዘኛ የተተረጐመ ነው:: በጣም ደስ ስለሚል እኔ ሁለቴ ነው ያነበብኩት:: ማን እንዳዋሰኝ ታውቂያለሽ? የጋሼ ሲራክ ባለቤት»

«ቀለመወርቅ? እሷ ሰው አታናግርም አይደለ? አንተ ሰው ይወድሃል»

---

135 በጊዜው ተወዳጅ የነበረ የፍቅር ልብወለድ(አ)

136 በጊዜው ተወዳጅ የነበረ ስለ ስለላ የተፃፈ የትርጉም መፅሐፍ(አ)

«ከመርካቶ ስትመጣ ሜክሲኮ አውቶቡስ ስጠብቅ አገኘችኝ:: ሊፍት ሰጠችኝ:: መፅሐፉ መኪናው ውስጥ ከኋላ መቀመጫ ላይ ነበር:: ሳገላብጥ አየችና 'ከፈለግህ ወስደህ አንብበው' አለችኝ:: ማን እምቢ ይላል......ከዛ ሠፈር ስንደርስ ዕቃ ስታወርድ ጠረጴዛና ወንበር ገዝታ ነበር ማስገባት እረዳኋት»

«እና ለኩሊነትህ መፅሐፍ ይከፈለኝ አልክ?»

«ምናለበት ደሞ አንቺ ቀናሽ......»

«ምንድነው የምቀናው?»

«ልጃቸው ጩጩ ነው አይደል እንግሊዘኛ ነው የሚያነበው ከአሁኑ»

«ሲራክ ነው ሰላምተኛ......እሳቸው ደስ ይሉኛል:: ሚስቱ ግን...... ትንጠባረራለች»

«በይ ስጪኝ»

«እ......ውሸትህን ነው......መፅሔቴን ወስደህ ስዕሉን ልትቀድ ነው»

«ገፁን ቁጠሪና ስጪኝ፣ ከጐደለ መፅሐፌን ታስቀሪያለሽ»

«ሙት?»

«ሙች......እንዴት አታምኚኝም?»

«አስተማሪህን እንደዛ ካደረክ በኋላ ምን አምንሃለሁ?»

«የውስጥ ሱሪና መፅሔት ምን አገናኛቸው? አትረሺውም እንዴ?--የክፍል ልጆች ናቸው በጉልበት ያስደረጉኝ:: ነግሬሽ»

«እውነትህን ንገረኝ......ደስ አላለህም?»

«እ»

«አትዋሽ ደስ አላለህም?»

«ደስ ብሎኛል» ልዋሻት አልችልም:: የዚያ ዓይነት ልጅ ነበረች ለእኔ:: ከከፋኝ አስከፋኝ፣ ካሳቀኝ አሳቀኝ ነበር::

«ይሔንን ነው ማወቅ የምፈልገው» አለችና እንደ ቁጣ አንገቷን ሰበቅ አድርጋ መፅሔቷ ላይ ወደ ማፍጠጥ ተመለሰች:: ከንፈሮቿ ተገጥመው ለብቻቸው ይንቃነቃሉ......

ያጠብኳቸውን ልብሶች ሁሉ እየጨመቅሁ መሬት ላይ አስቀምጬ ስለ ነበረ እነሱን ባልደረቀ ልዝዝ አንሶላ ስጠቀልል:

«መቼ ታመጣልኛለህ?» አለች ካጎነበሰችበት ድንገት ቀና ብላ::

«እቤት አለ ነይና ውሰጂ ከፈለግሽ»

«ራስህ አምጣልኝ:: አባትህ ያስፈሩኛል»

«ማንም የለም»

«ውሸትህን ነው»

«እግዚያብሔርን:: ማንም የለም......»

ልብሱን ጠቅልዬ በእርጥብ እስተኔ አንሶላ ስሸከም አይታ ማርታ ማንበብ/መመልከት የጨረሰችውን መፅሔት ሰጠችኝ (የጨረሰችው መሰለኝ እንጂ ጨርሳው እንደኾነ አልጠየቅኋትም):: እንደ ቱቦ ሸመለልኩና ሱሪዬ ኋላ ኪሴ ከተትኩት:: ሣፋዬን አነሳሁ:: ከአንድ ጎኑ ያቆረች ትንሽ የውሐ ሐይቅ አልወጣ ብላ አስቸግራኝ እሷን ወደ መሬት ለማፍሰስ ትንሽ ታገልኩ:: ማርታ ከዛፉ ስር ተነስታ ወደ ቤታቸው በረንዳ ላይ ወጣችና:

«በኋላ መጥቼ መፅሐፉን እወስዳለሁ» አለችኝ::

«እሺ» አልኩና ፊቴን አዙሬ መንገድ ስጀምር

በለሆሳስ ድምፅ ከወደ ኋላዬ:

«ገዳምሽ እይ» አለች::

ዞር አልኩ:: ቀሚሷን ወደ ላይ በቀስታ አንስታ በቶሎ መለሰችው:: ምናልባት አምስት ሳንቲ:: አልቀጠለችም:: ጭኖቿ የማያልቅ እርዝመት ያላቸው ይመስላል:: በጭኖቿ መሃል ባለው ክፍተት በቤታቸው ዋና በር በኩል ሶፋው አጠገብ ያለውን የጠረጴዛ ከፊል አየሁ......ከከፊል የጠረጴዛው ጠለል ላይ በከፊል ውሃ የተሞላ ብርጭቆ (እናቷ ውሃ መጠጣት ይወዳሉ) በዚያች ቅፅበት አየሁ፣ የበረንዳው የሲሚንቶ ወለል ላይ በእርጥብ እግሮች ዳና የተሰሩትን ያልደረቁ ማህተሞች አየሁ:: ትንሽ ሕልም የመሰለ ነገር ነበር እንዲህ ነው ብዬ የማልገልፀው......ግን እቆምኩበት በፍርሐት ጉልበቴ ሲደክም ይሰማኛል–ሆዴ ውስጥ ልዩ ስሜት ሲፈጠር......

ዙሪያዋን በአየር ተከባ ከበረንዳው ዳገት ላይ (ጠርዝ ላይ) ፒሲሲዋን ነፋስ እየነካካት......

የፀሐይ ሙቀት መዞ ያወጣው ወዘናዋ ጉንጮቿና ሌላም ገላዋ ላይ እየፈለቀ......

ደከሞኝ ማረፍ የምፈልገው እኔ......

ማረፊያ ደረት ናፍቆኝ ማለት እንደ ሞሳ ጡት የምለገልግበት......

ብቻ ብቻ ምኞት በፈለኩበት ደቂቃ ስላየኋት ይሁን......

ተረበሽኩ......

ረቀቀችብኝ......

ሕልሙ ሊያደክመኝ ነበር......

ቀሚሷን ቶሎ ወደ ታች መልሳ ለአፍታ እየሳቀች አየችኝና ወደ ቤት እየሮጠች ገባች:: ማነው እድለኛ ይኼን ሰውነት የሚነካ የሚያቅፍ? እል ነበር አፌን ገጥሜ ገና በጉርምስናዬ ማንም ባልደረሰበት ውበት ተመስጬና ቀንቼ......

**(......ልታበሽቀኝ ወይም ማብሸቅ አስመስላ እያስማመረችኝ፣ *'ገዳማ ገዳማ ገደምዳማዬ ያገን ጠይም ወጣት ኢያችሁ ወይ'*[137]......የተባለ ዘፈን እየዘፈነች ተላፍቻት ነበር። እየተባረርን በግቢያችን......ቀዝቃዛ ሳር ላይ እየወደቅን እየተነሳን......የአከርማ አበባ እየተነሰነሰብን...... በረንዳ ላይ ከሠፈረ አተር ስራ ዳንቴል ከለበሰ ራዲዮ *'ሆሺ ሃረገቱ'* ና *'ጋራ ስር ነው ቤትሽ'* በዜጎቻችን ተመርጠውልን......እነዚህም ዜማዎች መፍረስ በጀመረ የሲሚንቶ ደረጃ ላይ እንደ ወፍራም የፓፓያ ጭማቂ እየፈሰሱ ሁለታችንም ተዳክመን እንደሚያናውዙ ቡችሎች እንገት ላንገት ተቃቅፈን የሚመች ደረቷ ከደረቴ ስር ከፍ ዝቅ እያለ......ልስማት ስል ስንቴ ሳትኳት?......ፀሐይ ስትወጣ የተከፈተ መስኮት አጠገብ ቆማ ይሄን 'ገዳማ ገደምዳማዬን' ስትዘፍን ሰምተናታል ይላሉ። ሲጀመር 'ወንድምሽ ነው እንዴ?' ብለዋት። እኔንም 'እህትህ ናት እንዴ?' ብለውኝ። ትልልቅ አይኖች ያሏት ስትስቅ ፊቷን በሁለት እጆቿ የምትጋርድ የአጋር ልጅ። 'አብሮ አደግ ወንድምና እህት ናቸው ሌላ ጉዳይ አያውቁም' ብለውን። ጭማቂ እየጠጣን አልነበረም ያፈቀርኳት፣ በየካፌዎች ተገባብዘን አልነበረም ያወቅኋት። የቆሸሹ ልብሶች እያጠብን። የረጠበ ጋቢ እያግረረን። እግሮቻችን በጥቁር ጭቃና በጊፈርሳ ውሃ እርሰው። ገላዎቻችን በነፃ ጨረሮች መሃል በትኩስነታቸው እየወገኑ። እሷ አጃና ግር እኔም እንደ ፍየል ወጠጤ እየሸተትን። መጀመሪያ ጊዜ ስመመን ስምጠን የተሳሳምን ዕለት በገራ እጇ አበባ አልያዘችም ነበር። ወይ የሽቶ ዕቃ። ወይ የወርቅ ሚዶ። ወይ ስልጣኔና ሐብት የሚያሳይ ቁሳቁስ ነገር። ይሄ ነበር፡ ለዘመናት የባተለ፣ ውልደቱ እጅግ የሚያሻማ፣ ጥላ እሸትና አመድ የተነከረ የድስት ጨርቅ ጨብጣ ነበር። እና ቀዘባነቷን አቅፌ ስስግት ስትስመኝ ዓይኖቿን ጨፍና ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ሲል ገራ እጇም በስሜት ጨብጥ ለቀቅ፣ ጨብጥ ለቀቅ ያደርግ የነበረው የድስት ልብስ ነበር። ይሄን አልዘነጋም። *'ገዳማ ገዳማ ገደምዳማዬ ያገን ጠይም ወጣት ኢያችሁ ወይ?'* ስትል ሰምተናታል ይላሉ። ፍቅራችን ርዕዮተ ዓለማችን ነበር)**

## እንድም ሁለትም

መጨረሻ ላይ በማንም ሳልታይ ወይም ሳልሰለል ቤቴ ሔጄ ማጠብ የፈለኩት የውስጥ ሱሪዬን ነው። ማለቴ የውስጥ ሱሪዎቼን። ሁለት የውስጥ ሱሪዎቼን። አምልጦኝ በነጠላ የጠራኋቸው ሁለመናቸው ስለሚመሳሰል ነው። ስለዚህ ስለ አንዱ ሳወራ ስለሁለቱ ወይም ሦስት ቢኖሩኝ እንኳ ስለ ሦስቱ እንዳወራሁ ይቆጠርልኝ ዘንድ የአንባቢውን ሩቅ ሃሳቢነት እጠይቃለሁ።

---

137 እኔም በተራዬ በሃርሞኒካ ታጅቤ ይህቺን ብዬአታለሁ፣ ያኔ ተስቆብኝ ነበር።
*ኦ ማርታ የእኔ ወለላ*
*አላፈቅርም ካንቺ ሌላ*
*ኦ ማይ ላቭ ባተ ጠብደል*
*ማርቲን ሳምኳት እንደ መስቀል*
*ማርታ ስዊቷ (sweet=ጣፋጭ) የማትመች*
*ያላንድ ሰው አልወድ አለች*

እነዚህ የውስጥ ሱሪዎች ለእኔ ወገብና ዳሌ የሚተልቁ፣ አባቴ ከመርካቶ ገዝቶ ያመጣቸው በግምት እያንዳንዳቸው ሁለት ብር ያወጡ ስሪታቸው ቻይና የኾነ ነው:: ከግራ ወደ ቀኝ ቡናማና ነጭ ሰንበሮች የተሰመረባቸው ፍሬቻ የመሰሉ ቀያዮች ናቸው:: ፊት ለፊት በስተቀኝ ከውጭ በኩል ሁሉም በአንዲት አዝራር የምትከደን ሚስጢር ኪስ አለቻቸው:: ውሐ ውስጥ ሲገቡ ሁለት ዝዋይ የሚጨርሱ ይመስላል:: አባቴ ጥሩ ሰው ኾኖ መልካም ለማድረግ ማሰቡ ደስ ይላል እንጂ የሚያስቀይም ግዢ ነው:: ሱሪዎቹ በቀላሉ ላብ ስለሚሰበስቡ እዚያ አካባቢ ብዙ ጊዜ ቶሎ ቶሎ ይቆሽሻሉ:: አንዳንዴ በጠራራ ፀሐይ ኳስ ተጫውቼ በላብ እዘፈቅና ከዋናው ሱሪዬ ስር ሙታንታዬ እየተጣጠፈና ከገላዬ እየተጣበቀ አላላውስ ሲለኝ ይሄ የፔኪንግ[138] ቁምጣ ምን የባሕርይ ለውጥ ደርሶበት ይሆን ብዬ ከፊት ለፊት ቀኝ እጄን በቀበቶዬ ስር ሰድጄ ስፈትሽ በላብ የተሞላ ተለዋዘዝ ጨርቅ ያጋጥመኛል:: ብዙ ጊዜ ቅያሬውም የቆሸሸ ስለሚሆን የለበስኩትን እንደ ለበስኩ ላቡ እላዬ ላይ ይደርቃል:: አንዳንዴ ከኳስ ሜዳ—ቤት እንደ ገባሁ ቶሎ አወልቀውና ከቆዳዬ ላይ የመጠጠው ላብ ጠፈፍ እንዲል እንዳጠብኩት ሁሉ እውጭ ሽቦ ላይ አሰጣዋለሁ:: አሪፍ ስንፍና ነው::

ከዕለታት አንድ ቀን ልተረትራቸው እፈልጋለሁ:: 'ተሰረቀ' ብዬ እያለቀስኩ ማስታወቅ ያምረኛል:: ግን ቶሎ እንደማይተኩ አውቃለሁ:: ምናልባትም የፋሲካ በዓል ወጪ የአባቴን ገንዘብ ስለሚጨርስበት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ጥያቄዬ ጥቃት ይሰነዘርበታል: ('ምነው? ምነው? ዱለት መብላት ይሻልሃል ወይስ ውስጥ ሱሪ መልበስ?'):: ምን ዓይነት ምርጫ ነው? 'የውስጥ ሱሪ ወይስ ዱለት?'

**(አባቴ ጴንጤ እናቴ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ነበሩ:: የሚገርመኝ አባቴ ጴንጤ ሆኖ የሚበላው በግ ትልቅነት በክብድ ከሆሙት ከጎረቤቱ ኦርቶዶክሶች መብለጡ ነው:: አንዳንዴ መፅሐፍ ቅዱሱን በእጁ ይዞ እያራገበ 'እኔና እናትህ በአንዳንድ ነገሮች እንለያያለን' ሲለኝ ማሰብ እገደዳለሁ......ምክንያቱም ቢያንስ 'ክርስቲያን' የሚለው ባያገናኛቸው 'ሆድያን' የሚለው ወይም በቀጥታ ቃል 'ዱለታውያን' ሳያገናኛቸው አይቀርም በሚል...... ግን አልናገረውም)**

የውስጥ ሱሪዬን ለማጠብ ስዘረጋው ሳፋውን እንደ ትልቅ ኮት ይሸፍነዋል:: ታጥቦ ካለቀ በኋላ ሲሰጣ የሚንጠባጠበው ውሃ ብዛት 'ጢስ አባይ እኛ ሠፈር ገባ እንዴ?' ዓይነት የሚያስተች ነው:: ጠባብ ሱሪዎቼን ስለብስ ይኼ የውስጥ ሱሪ ከውጭ ተጣጥፎ ይታያል:: በእርግጥ በሚስጢር አፍርበታለሁ:: ፀጉሬን በቫዝሊን ማስተኛት የጀመርኩት ይሄን የውስጥ ሱሪ መልበስ ከጀመርኩና ፀባዩ ሰላም ከነሳኝ በኋላ ነበር:: ምን አገናኛቸው? ቫዝሊንና የውስጥ ሱሪን፣ ፀጉርንና ቦላሌን ምን አገናኛቸው?

እንዲህ ነው ነገሩ:

በሰው መሃል ስተላለፍ የሚያጋጥሙኝ ዓይኖች ሁልጊዜ ወረድ ብለው ዳሌዬ አካባቢ ጠበብ ብሎ ወደ ተሰፋው ስሱ ቴትሮን ሱሪዬ የሚያዩ ናቸው::

---

138 አሁን ቤይጂንግ የምትባለው(አ)

ይሄ አስተያየታቸው ያቁነጠንጠኝ ጀመር:: ስለምን ያያሉ? ስለምንስ አተኩረው ወደ ሱሪዬ ያያሉ? ወደ ዳሌዬም ያያሉ? አይተውስ ለምን እየተያዩ ይሳሳቃሉ? ከሱሪዬ ስር እንደ ወረቀት የተጨመዳደደውና እንደ ብርድ ልብስ የወፈረው ሙታንታዬ እየሳባቸውና አስገራሚ ቅርጹ ከውጭ እንደ ድርብ ፅሁፍ እየታየ ይሆን እንዴ? ያሉኝን ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ ሱሪዎቼን ብለዋውጥም የሰዎች አትኩሮት ወደ ሌላ ቦታ አልተሰደደም......ስለዚህ አዲስ ፈተና ለራሴ አቀረብኩ::

ለሁለት ሳምንታት ያለ ውስጥ ሱሪ ወዲያ ወዲህ አልኩ:: መልሱ አስከፋኝ:: ሰበቡ ከውስጥ ሱሪዎቼ የተፀነሰ መሆኑን ተረዳሁ:: አዲስ የውስጥ ሱሪ ጨምሬ የመግዛት አቅም ስላልነበረኝ ለዚያን ጊዜ የሚመጥን የመሰለኝን አንድ ብልሃት ፈልጌ አገኘሁ::

የተመልካቹን አስተያየት አቅጣጫ ለመለወጥ ጥሩ አፍሮ የሆነውን ፀጉሬን ወደ ኋላ በቫዝሊን እየለጠጥኩ ማስተኛት ጀመርኩ:: ጥበቤ ሰራልኝ:: ሰዎች አናቴን ያዩ ጀመር:: የሚረባ አናት አልነበረም:: ሁለተኛ ደረጃ ያልጨረሰ እሱም እንደ በሽታ የከበደው አናት ነው:: ጆሜትሪ፣ አልጄብራና ሰዋሰው የረቀቀበት አናት ነው:: ፀጉሬን ወደ ኋላ ምጥጥ አድርጌ አበጥርና ከፊት ለፊቴ በግንባሬ በኩል በላስቲክ ሚዶ ወደ ቅንድቦቼ ታ–ታ–ታ-አደርገዋለሁ:: ይሄ ጥ ቁር የተጠቀለለ  የሚያምር የመሰለ ፀጉር ቀረብ ብለው ሲያዩት አባራ የሞላው ነው:: በውርጫም ጠዋት ፀጉሬ በቫዝሊኑ ብዛት ሲደርቅ፣ ቀን ቀን በቀትር ሲብለጨለጭና ሲቀልጥ ሰዎች በፌዝ ሳይሆን የዕውነታቸውን 'ታዲያስ ኤልቪሱ' ይሉኛል:: ነፋስ የበረታ ዕለት ፀጉሬ አይኖቼ ላይ አርፎ ማየት እንደ ከለከለኝ ሁሉ አውቄ የሰው አትኩሮት ለመሳብ ጭንቅላቴን ወደ ኋላዬ አወናጭፋለሁ:: የሚስቁ አሉ:: 'ምን መሆኑ ነው?' እያሉ ሳይሆን አይቀርም:: ደስ ይለኛል:: ሲያልበኝ ደ'ሞ ግንባሬ ላይ የተዘረገፈው በቅባት የደደረ ፀጉር ያሳክከኛል:: ግን ማሳከኩ የበዛብኝ ሰሞን፣ በተለይ ሜዳ ላይ ፀሐይ ውስጥ ስጫወት የራሴ ሴራና የተመልካቹ ግልብነት ያናድደኝና 'ለዚህ ነው 'ኤልቪሱ' የተባልኩት?' እላለሁ:: ይገባኛል የውስጥ ሱሪዬን ከአይናቸው ለመጋረድ ስል ሌላ መርገምት እንደ ገባሁ......

አቶቡስ ስጠብቅ አንዳንዴ በመጠኑ የቆሸሸ ጥጣም የውስጥ ሱሪዬ ካሳከከኝ መርካቶ እምብርት አዲሱ ገበያ አዳራሽ እዛ ሕንፃ ውስጥ ብዙ ሰው የማይተላለፍበት ጨለም ያለ አሳቻ ቦታ እፈልግና አገኛለሁ:: ከዛ በኋላ ደብተሮቼንና መፅሐፍቶቼን የያዝኩበትን ቦርሳ እንዳይወድቅ ከግድግዳው ጋር በትከሻዬ አጣብቄ እይዘዋለሁ:: ሰው በድንገት መጥቶ እንዳያስደነግጠኝ አይኖቼን ሰው መተላለፊያ መንገድ ላይ ተክዬ ቀኝ እጄን በገላዬና በውስጥ ሱሪዬ መሃል አስገብቼ ልቤ እስኪጠፋ ብሽሽቴን አካለሁ:: በዚያች ወቅት የማገኘው እርካታ ከአለማየሁ ጋር ከበላሁት ዶሮ ወጥ ምሳ ይበልጥ ነበር......

**(ዛሬ መርካቶ መሃል አዳራሽ–አዲሱ ገበያ–ስመላለስ ደብረ ሊባኖስ እንደሚባለም ክርስቲያን ወይ ወደ ሼክ ሁሴን እንደ ሚጓዝ አማኝ ማከኪያ ቦታዎቼ(ሁለትና ከሁለት በላይ ነበሩ) እሄድና እጎበኛቸዋለሁ:: አንዳንዴ ምን እንደሚሰማኝ ለማየት**

**እንደ ድሮው ለማከክ ስቆም የሚተላለፈው ሰው ብዛቱና ግፊያው በፍፁም አያስደርገኝም:: መላጣዬ ላይ የቀሩትን ጥቂት ሽበቶች እየነጨሁ ያዲስአባ ከተማ ከንቲባ መኾን እመኛለሁ:: ብሆን፣ ከነዚያ ቦታዎች ቢያንስ አንድ ሁለቱን ከልዬ 'ማከኪያ ጣቢያ' ብዬ እሰይማቸው ነበር)**

ከማርታ ወደ ቤቴ እንደ ተመለስኩ ያጠብኳቸውን ልብሶች በሁለት ሜትር ከፍታ የተዘረጋ የሽቦ ገመድ ላይ፣ ያማረሩኝን ሁለቱንም የውስጥ ሱሪዎቼን ደ'ሞ በፍጥነት አጥቤ አጥር ላይ አሰጣኋቸው::

**(ውስጥ ሱሪዬን ተደጋግሞ አጥር ላይ ሲዘረጋ ካየ አባቴ: 'አጥር ላይ አታስጣ አላልኩህም! ተላላፊ መንገደኛ መኸረጥ አድርጎብህ ይሄድና ጉድህ እንዳይፈላ!' ይለኛል:: በልቤ 'ይሄን ቀና ብሎ አይቶ እንኳን የተመኘ የተረገመ ነው' እላለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ከሃሳቦች የበለጠ እነሱን ተሸክመው የሚመጡት ቃላቶች ያበሳጩኛል:: ለምሳሌ 'መኸረጥ' ማለት ምን ማለት ነው? ቃሉን ስሰማ ፍጥነት ይታየኛል:: ቃሉን ስሰማ ቁራጥ ጎታች ይታየኛል:: ቃሉን ስሰማ ለዓይነሕሊናዬ የሚነበበው ሊሰየም የማይችል ብሌን ፈታኝ ውልብታ ነው:: የውስጥ ሱሪዬ እንኳን በርጥቡ ይቅርና ደርቆ ለመሸከም ሁለት ሰዎች ጓላና ፊት ኾነው በትከሻቸው ላይ አጣና አጋድመው እዚያ ላይ አስተኝተውት ነው:: 'መኸረጥ' የተሰኘው ቃል ለውስጥ ሱሪዎቼ አይሰራም)**

እርቦኝ ስለ ነበር የሚበላ ፍለጋ ቤት ልገባ ስል እናቴ ከውጭ መጣች:: በግራ እጇ የጎረቤታችንን የዘውዲቱን የአራት ዓመት ትንሽ ልጅ ነፃነትን ትጎትታለች:: እናቴ ሴት ልጅ በጣም ብትፈልግም በማሕፀን ችግር ከእኔ ሌላ ምንም መውለድ እንደማትችል ተነግሯት ነፃነትን ክርስትና አንስታ እንደ ልጇ ስትንከባከባት ትውላለች:: ነፃነት ድምቡሽ ያለች፣ በተለይ ፊቷ ቄሶች መፅሐፍ ላይ ከሚገኙ ዓይነ-ትላልቅ መላዕክቶች የአንደኛውን የሚመስል ነው:: ረዥም ቀሚስ ለብሳ ትላልቅ ዓይኖቿን በዝምታ ስታንገዋልል ኢትዮጵያ ትመስለኛለች::

**በነፃነት መልክ ሰበብ ሳይሆን አይቀርም ኢትዮጵያ ትልቅ ሴትዮ መስላኝ አታውቅም:: አለ አይደለ ብዙ የዘመን ዕውቀት የሰበሰበች ግን ሁኔታዋና መንገዷ ሁሉ የልጅ የሆነ......እንደዛ ትመስለኛለች......**

«የማርታን እናት አግኝቼአት ነበር:: አሁን ወደ ቤቱ ሂደ አለችኝ» ጎንበስ ብላ የነፃነትን አንድ ዓይኗን ስማ ቀና አለችና:

«ጠብቂኝ የእኔ እመቤት» ብላት ያኔውኑ:

«ሻይ ትጠጣለህ?» አለችኝ

«አልፈልግም»

ትታኝ ወደ ቤት ውስጥ ገባች:: እኔና ነፃነት ያስጣሁት ልብስ ስር ቆመናል:: ነፃነት ወደ መሬት ጎንበስ ብላ በፍጥነት በአመልካች ጣቷና በአውራ ጣቷ መሃል ባቄላ የምታክል ቢጫ ቢራቢሮ ከሳር ላይ ለቀመች:: ቀላል ፈጣን ድርጊት ነበር:: አየች:: አጎነበሰች:: እጇን ሰዳ ቢራቢሮዋን ያዘች:: ከዛ ቀና ብላ የቢራቢሮዋን መፈራገጥ ለሰኮንዶች አየችና ፈገግ ብላ ለቀቀቻት:: ቢራቢሮዋ እንደ ደቃቃ የእሳት ነበልባል እየተውለበለበች ግቢያችንን ማቋረጥ ጀመረች:: ነፃነት ጣቶቿን አየች:: እዛ ላይ ከቢራቢሮዋ ክንፎች ላይ የቀረውን ዱቄት በቀሚሷ ጠረገችና ቀና ብላ አየችኝ:: ከትልልቅ ዐይኖቿ ጀርባ የተደበቀ እሷ ብቻ የምታውቀው አለምን የሚያስፈራ ሚስጢር ያለ ይመስላል......እኔ ብሆን ይህቺን ሚጢጢ ቢራቢሮ ለመያዝ ስንቴ ወድቄ ተነስቼአለሁ:: ስንቴ አምልጣኝ ቢራቢሮዋን ተራግሜአለሁ:: ተደንቄ ቤት ስገባ እናቴ የሰራችልኝን (ብዙ ልብስ ስላጠብኩ ለሞራሌ ብላ ነው መሰለኝ)የሽሮ እንጀራ (የምጣድ ሽሮ)[139] ጠረጴዛ

---

139 እናቴ አያቷ ቄስ ገሠሠ ሲያወሩ ሰማሁት ያለችንን አንድ አስገራሚ ታሪክ ለአባቴና ለእኔ ትነግረን ነበር::

«ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ሊገደል ሲል ከሄሮድስ አምልጦ ከቤተልሔም ጀምሮ ከእናቱ ጋር ሲንከራተት ሲንከራተት በግብጥ በኩል አድርጎ እንዲህ በሱዳን አገር በኩል እንዲህ በቋራ ያደርግና ጎጃም መርጡለ ማርያም ይገባል:: (ስትናገር አፏን የማጣጣም ልማድ ነበራት፣ ባልተጠበቀ ጊዜ በእርፍታዋ ላይ 'ምፃ!' ታደርጋለች:: ወይም 'ምፃ!' እርፍታዋ ነበር:: ይሄ ልማዷ አንዳንዴ ጨዋታዋን ያሳምረዋል አንዳንዴ ደ'ሞ አሰላቺ ያደርገዋል) እሱ መምጣቱን ያወቁ ሰገሎች፣ ያኔ እንደ አሁኑ አይደለም ሕልምና ራዕይ ይታያል፣ የእዝጌር ልጅ መጣ፣ ንፁሁ መጣ፣ መድሐኒአለም መጣ፣ ንጉሡ መጣ ተብሎ የሚበላ አዘጋጅተው ይጠብቋቸዋል:: (ምፃ!) የእኔ እመቤት ተንከራታ ተንከራታ የት? መርጡለ ማርያም:: ያረፈችበት ቦታ ዛሬም አለ:: ትልቅ ሾላ ስር ነው ያረፈች አሉ:: ሾላውም ዛሬ ድረስ አለ:: ሰው ደፍሮም አይቆርጠው:: እንኳን ዛፉ ስትቀመጥ ቂጧ ያረፈበት ሳር ዛሬ ድረስ እንደ ተተመተመ አለ:: እሱን ማየት ነው አባተ:: እንደው ክብ ነገር ሆኖ ተአመት አመት ይታይ ነበር:: ዘነበ አልዘነበ:: ጉድ:: እና መርጡለ ማርያም መሃን የለም:: ለምን? በሉኝ:: (ምፃ!) ልጅ እምቢ ካለ እሷ ያረፈችበት ቦታ ዋርካው ስር እዛ ሄዳ ሲቷ ቁጭ ካለች አትስልች እንጂ በያመቱ ልጅ መፈልፈል ነው:: መንታ መንታውን:: ለሰው ብቻ መሰለህ ለከብት ሁሉ ነው:: (ምፃ!) እንግዲህ መርጡለ ደረሱ ብዬአቸኋለሁ አይደል......መርጡለ ሲደርሱ እመቤቴ በጣም ደክማ ስለነበር አንዲት ወንድ የማታውቅ ልጃገረድ እመቤታችንን እርጂአት ተብላ ጌታችንን ከእሷ ተቀብላ እንድታቅፍ ተደረገች:: አቅፋ እዛው ከማርያምና ማነው እቴ? አብሮአት ያለው ያልታደለ የሚንከራተት ሰውዬ ማነው? አዎ ልጇ ዮሴፍ ከእሱ ጋር ማዕድ ተቀመጠች:: የዚህች ሴት የእቃፊዋ ውላጆች ዛሬ ድረስ አሉ:: ከዛ ማዕድ ቀረበ:: (ምፃ!) ታዲያልህ ጌታችን እንደታቀፈ እጁን ወደ ማዕዱ ሰደድ አድርጎ ምን በላ መሰላችሁ? ለመጀመሪያ ጊዜ? እንግዲህ ክትፎ አለ:: ዶሮ አለ:: ምን የመሰለ ቀይ ወጥ አለ፣ የሱፉና የተልባው ፍትፍት አለ:: ምን ይበላል ጌታችን? የምጣድ ሽሮ:: (ምፃ!)ጌታችን በምጣድ ሽሮ ነው አፉን ያሟሸው:: አሁን ስሙ ተረሳ እንጂ ምጣድ ሽሮ 'መርጡለ' ነበር የሚባል:: 'የመርጡለ ማር' ይባል ነበር ዱሮ:: ማርያም ተገርማ ቀኝ እጇን ክርስቶስን ያቀፈችበትን ልጅት ጡት ላይ አስቀምጣ መረቀቻት:: የምታጠቢው ተውሳክ አይንካው አለቻት:: የአዋቂ ወሬ ነው የምነግራችሁ:: የአንጀት ሕመም ካለብህ ብቻ እድልህ ሆኖ አራስ የሆነች የእቃፊ ዘር ከተገኘች ከእሷ ጡት ታልቦ የሆነ ነገር ላይ ጠላም ይሁን ቡና፣ ሻይ፣ የላም ወተት፣ ውሐ፣ ብርዝ ጠጅም ትችላለህ ወተቷ ጠብ ተደርጎልህ ያን በባዶ ሆድህ ከጠጣህ ትፈወሳለህ፣ ሞላ ሆነህ ከእቃፊ ዘሮች አራስ ተገኝታ ከእሷ እንደው አፍታ ብትለገልግ ደ'ሞ እስከታረጅ የሆድ ሕመም አይነካህም:: አባተ እስኪ እኔ

ላይ ስታስቀመጥ አየኋት:: ደስታዬ ከፍተኛ ነበር:: እስከዛሬ ድረስ በመጀመሪያ ደረጃ የማስቀምጠው ተደናቂ ምግብ የምጣድ ሽሮ ነው::

**(አንድ ጊዜ የአማርኛ አስተማሪያችን መኩንን ግጥም ጻፉ ብሎን ይኼን ብዬአለሁ:**

---

ሆዴን አንዲት ቀን ታምሚ አውቃለሁ? ቀዝቃዛ ከሙቅ፣ ለስላሳ ከሽርክት ብበላ አንዲት ነገር አልሆንም:: በሴት በሴት በኩል ነው የሚተላለፈው ምርቃቱ:: ከአቃፊዋ ዘሮች የተወለደ ወንድ ሴት ቢወልድ ሚስቱ የአቃፊ ዘር ካሌላት አይሆንም:: የእነሱን ዘር ሚስት ያደረገ ሆድ ሕመም አይነካውም:: ጎረቤታችን ነበረች (የእሷን ጠብተሻል ተብዬአለሁ ዕድሌ ሆኖ......እኔ ስወለድ አራስ ነበረች) እኔ ልጅ ነኝ ያኔ ባሏን ሲያሙት እሰማ ነበር:: ሚስቱ እንግዲህ ወልዳ አራስ ናት አጅሬ ባል ለአርሻው ሲሄድ ጠዋት ጠዋት ሆን ብሎ ወተቷን መግምጎ ይሄዳል፡ እንደ ገና ማታ ሲመለስ በር ዘግቶ ወተት ካላመጣሽ:: አንዳንዴ እንደውም ቡና እየተጠጣ ሰው ተቀምጦ ሁሉ ሳያፍር የምነግርሽ ሚስጢር አለ ነይ ብሎ ወደ ጓሮ ወስዶ ጥላ ስር ይሄን እንኳን አይቼአለሁ (ምፃ!) እንደ ልጅ ዛፍ ስር አቁሞ እንደ ላም ልበል እንጂ ይጠባታል:: በኋላ መረራት:: እህ! ምን ይጥባ አራሱ፣ ሞላው:: ተራብ እኮ:: ቀን ሲያለቅስባት ይውላል፣ ማታ እንዲሁ:: በኋላ በሽማግሌ አስቆመችው:: (ምፃ!) ያቃፊ ዘር ያለበት ሰው የተገኘውን ይበላል ይባላል:: አንዳንድ ሴት አቃፊዎች አራስ ሲሆኑ ወተታቸውን አልበው በብልቃጥና በጮጮ ያስቀምጣሉ:: እሱ ከተገኘ መቅመሱን ተወው፣ ካሸተትከው ነቀርሳ ያወጣል:: የእነሱ ዘር የትም ቢሆን ይታወቃል:: ይሄ ቲያትር ቤት የታየው ምላጭ የሚበላው ሰውዬ እመኑኝ ቢመረመር የአቃፊ ወተት ጥሩ አድርጎ ጠጥቷል'

አባባ ይሄን ሲሰማ ሆዱን ይዞ ትንፋሹ ቁርጥ እስኪል በሳቅ ይፈርሳል...........

ውሃ ወደ ወይን ጠጅ የለወጠ፣ በውሃ ላይ የሄደ፣ መርጡለ ማርያም ደካማ አገር ናትና መምጣት አይፈልግም ነው? ቤተልሄም የተወለደ ለፍኖተሰላም አይመጥንም ነው? ከኮረኮንቻም ናዝሬትና ከደባሪ ጎለጎታና ኢየሩሳሌም የፍኖተሰላም ማር አያምርም ይሆን? እኔን ያስተማረኝ ክራቫት ያደረገ ፈረንጅና የተማረ ሀበሻ ነው፡ እንቺን የሚሰብከሽ ግን እከካም ደብተራ ነው ማለቱ ይሆን? ብቻ ግልፅ አልነበረም ለእኔ:: ለምን እንደዚያ እንደ ሚስቅ አይገባኝም:: እንዲህ ሲስቅ ግን ጠጋ ብዬ የዓይኖቹን ውሃ አያለሁ::......እና እዛ ዓይኑ ውሃ ውስጥ የማየው በትንሽ ትሪ ላይ የተቀመጠ የደብረብርሃን በግና የጎጃም ንጥር ቅቤ ከእናቴ ጥበብ ጋር አሲረው ቁጭ ያደረጉት የሚያምር አመድና ፍም የመሰለ ቀዝቃዛ ዱለት ነበር::

(አባቴ እናቴን ያወቃት ሰራተኛው ሆና ነው:: ገረዱን ነው ያገባው:: እናቴ ስለ ሆነች ሳይሆን እዚህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ነበረች:: እናቴን ገና ሲያያት ፈዞ የማይቀር ወንድ አላየሁም:: ብትነጣ ራኬል ዌልሽ የተባለችውን የአሜሪካን የፊልም ተዋናይ ትመስል ነበር:: አባቴ እሷን ሲቀጥር ዘመዶቹ 'ትሳሳታለህ' ብለውት ነበር:: ጴንጤ ስለሆነ ክርስቶስ እንደሚጠብቀው ጉራ ነፋ:: አንድ አመት ሳይሞላ ጉድ ፈላበት:: ከጉዱ በኋላ ጴንጤ ሊያደርጋት ሞክሮ አልቻለም:: ቄሱ አያቴ (የእናቴ አባት) ከመርጡለ ማርያም መጥተው ሳለ ከአባቴ ጋር በሐይማኖት ይጣላሉ ብዬ ጠብቄ ነበር:: ወደ ጆሮው መሰስ ብለው አንድ ነገር ሲናገሩ ሰማኋቸው:

*'መኑ ይጠበብ እምሰለሞን ወስሀተ በብዕሲ ት*

ከሰለሞን ማን ጥበበኛ ይሆናል? እሱም በሴት ተሳሳተ

*ወመኑ ይደንዕ እምነ ሳምሶን ወስሀተ በብዕሲ ት*

ከሳምሶንስ ማን ይበረታል? እሱም በሴት ተሳሳተ::

ማለት ነው ልጄ'

ቄስ ገሠሠ ሰው መሆናቸውን የሚያውቁ 'አራዳ' ቄስ ነበሩ መሰለኝ:: አባባቸው ሳምሶንና ሰለሞን ከተሸወዱ ማንህና አንተ? ማለታቸው መሰለኝ::

*ሁሉ ነገር ቢጠፋ፣ የሚበላ ነገር ዘንድሮ፣*
*ግድ የለኝም ለምንም ምግብ፣ እስካገኝሁ ምጣድ ሽሮ::'*

**ለመግጠሚያ የተሰጡን ቁልፍ ቃላት 'ምጣድ' 'ኩረሪማ' 'ቅርንቶድ' 'አረመኔ' የተባሉት ነበሩ:: መልመጃውን የሰራሁበት ወረቀት ታርሞ ሲመለስ በቀይ እስክሪፕቶ እነዚህ ከላይ የመዘገብኳቸው ሁለት ስንኞች ፊት ለፊት ወዳጄ መኮንታው 'ምን ማለትህ ነው? 'ምጣድ' እንጂ 'ምጣድ ሽሮ' አልተባልክም' የሚል ማስታወሻ ፅፎአል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልዩ ፍጡር እንደ ሆንኩ ሁሉ አተኩሮ ያየኛል:: በልቤ 'ገና አልገባህም መኮንታው' እላለሁ)**

ያን ሽሮ በለምለም እንጀራ አጣድፌ በላሁና ቀትር ላይ በስራና በእንጀራው ተጻከሜ የማርታን መፅሔት ለመመልከት/ለማንበብ አልጋ ላይ በጀርባዬ ተጋደምኩ......ማስታወቂያ የበዛበት መፅሔት ነው:: የምግብ ማስታወቂያ፣ የልብስ ማስታወቂያ፣ የሰዓት ማስታወቂያ፣ የቆንጆ ወንድና ሴቶች ማስታወቂያ ወዘተ......እዛ ውስጥ ያሉት ሰዎች ከላ ቻፔል የሚያማምሩ ፀአዳ ፈረንጆች ናቸው:: ከፊሎቹ ፎቶግራፍ ናቸው:: ከፊሎቹ በእጅ የተሰሩ ስዕሎች ናቸው:: አንድ የእንግሊዘኛ አጭር ታሪክ አገኘሁ:: LOST IN AUGUST[140] የሚል:: ግን ማንበብ ከበደኝ:: መፅሔቱ ውስጥ ያሉትን ስዕሎች መመልከት ቀጠልኩ:: አንዳንዴ አጫጭር በትላልቅ ፊደል የተፃፉ ፅሁፎችን ላነብ እሞክራለሁ:: የመፅሔቱን ገፆች እየገለጥኩ መሐል አካባቢ ስደርስ ባለጃፖኒ ቀይ ቀሚስ የለበሰች ነጭ ፀጉር ያላት ሴት በነፋስ የሚገለብ ቀሚሷን ለመሰብሰብ እየሞከረች በሚማርክ ስልት ስትስቅ አየሁ:: ከሴትዮዋ ፎቶግራፍ አናት ላይ በቀይ ትልቅ ፅሁፍ A SUMMER DREAM[141]፣ ከስር ደ'ሞ 'ሜርላይን ሞንሮ'[142] ይላል በተጋደመ ቀጫጫ ፅሁፍ:: ራቁታቸውን በዋና ልብሶች ብቻ ፎቶ ከተነሱ መፅሔቱ ውስጥ ካየኹዋቸው አንዳንድ ሴቶች የተለየ የሚስብ ነገር አላት:: ቀሚሷ ከመሬት ውስጥ በሚወጣ ነፋስ እንደሚገለብ ሁሉ ወደ ላይ ቡፍ ብሏል:: እጅግ ተገልቦም ከቀሚሷ ስር ያለው ነገር እንዳይታይ ጎንበስ ብላ ሁለት እጆቿን በደንብ ያልተጋጠሙ ጭኖቿ መሃል ወሽቃለች:: የምትቀልድም ይመስላል:: ወረቀቱን ከመፅሔቱ መሐል ነቅዬ ለማውጣት ዳዳሁና ለማርታ የገባሁላት ቃል ትዝ አለኝ:: ቃል መግባቴ አናደደኝ:: መፅሔቱን ወደ ጎን አስቀምጬ ጣሪያ ላይ ሳፈጥ ማርታ በር አንኳኩታ ገባች:: እተዘረጋሁበት[143] ከላይ እስከ ታች እየቸኝና:

---

140 ነሐሴ ላይ መጥፋት(እንግሊዘኛ)(አ)

141 የበጋ ሕልም(እንግሊዘኛ)(አ)

142 ወ/ሮ ሜርለን ሞንሮ ናት፣ ሟቿ አሜሪካዊ ተዋናይና ሞዴል(አ)

143 እናቴ ደጋግማ የምትጠቀምበት ቃል::
'ገዳም አለ?' ይላል አንድ ፈላጊ
'አዎ' ትላለች
'ምን ያደርጋል?' ይላል
'ምን ያደርጋል ብለህ ነው:: <u>የሚዘረጋበት</u> ፈልጎ <u>ተዘርግቷል</u>'

«የት አለ መፅሐፉ? ስጠኝ:: መፅሔቱን አየኸው?» አለች በችኮላ ዓይነት

«ቆይ ልስጥሽ»

ከተጋደምኩበት ተነስቼ ወደ መፅሐፍ መደርደሪያው ሔድኩ:: መፅሔቱን ካስቀመጥኩበት ቦታ አንስታ ማገላበጥ ጀመረች:: መፅሐፉን አምጥቼ ስሰጣት፣ የመፅሔቱን ገፆች በትኩረት ገላለጠችና:

«ይህቺ ሴት ደስ አትልም?» አለች መፅሔቱን ወደ ላይ አንስታ ቀይ በቀይ የለበሰችውን ወ/ሮ ሞንሮን እያሳየችኝ

«አዎ»

«እንዴት ነው ቀሚሱ የተነሳላት?»

«ነፋስ ይሆናል!»

«ነፋስ መሆኑ እንዴት ይታወቃል?» አለች

«ሌላ ምን ይሆናል? ምን አስጨነቀሽ ለእሷ»

«ደስ አትልም?» በማሾፍ ጥያቄ::

አተኩሬ ማርታን አየኋት:: ፊቷ ቀልድ የለበትም::

«አዎ ቆንጆ ናት:: ስትስቅ ደስ ትላለች:: እና ምን ይጠበስ»

ትቁነጠነጣለች:: መፅሐፉን ስሰጣት አገላብጣ አየችው:: አርጅቷል:: የሽፋኑ ስዕል ተፍቆ ሊጠፋ ትንሽ ነው የቀረው:: ከአንዱ ጫፍ አይጥ እንደ በላው ዐይነት ተሸራርፎአል::

«መፅሐፉን ታጥበዋለህ እንዴ?»

«ቀለመወርቅ እንደዚሁ ነው ያዋሰችኝ:: አሰማምሬ ለመመለስ ቃል ገብቼአለሁ»

እንደ ልዩ ደ'ሞ እንደ ተበላሸ እቃ አገላብጣ አየችው:: ስታተኩር ትንሽ ልጅ ትመስላለች:: ከንፈሮቿ ሞጥሞጥ ብለው ጠይም ፊቷ ለመቅላት የሚሞክር ይመስላል:: ጆሮዋ አጠገብ ነካኋት:: እጄን ለማግለል መታችው:: የማትቸኩል እንደኾነ አልጋዬ አጠገብ ያለው ሳጥን ላይ ተቀምጣ እንድታዋራኝ ጠየቅኋት:: የእምቢታ ዓይነት ራሷን ነቀነቀችና ግን ሳትሄድ ቆመች:: የመፅሐፉን ልባስ እያገላበጠች ታያለች ግን አትሄድም:: አልጋዬ ላይ ተመልሼ በጀርባዬ ጋደም አልኩ:: ካይኔ ትይዩ ሳትሄድ ሳትቀመጥ ቆማለች:: ከተጋደምኩበት ሳያት ቁመተ ረዥም ናት:: ገላዋም የጠገበ አሞላል አለው:: ሽንሽን ቀሚሷ ከጉልበቷ በላይ ትንሳፈፋለች:: ማርታ ጥቂቶች ብቻ የሚስተካከሏት ጤንነት የተጠቀጠቀባት ውብ ነበረች::

«ገዳም» አለችኝ::

«ተቀመጪ» አልኩ የተሰላቸ በመሰለ ድምፅ::

ጠይም የተመቸው ፊቷ በሳቅ ለሁለት ተከፈለ:: 'ምን የሚያስቅ ነገር

አለ?' ብዬ ራሴን እየጠየቅሁ ሳለሁ የሞንተ ክሪስቶን ልብወለድና መፅሔቱን በያዙትባቸው እጆቿ የቀሚሷን ደርዝ ግራና ቀኝ ይዛ ወደ ላይ አነሳችው...... የዘጠኝ ሰዓት ፀሐይ ውጋጋን እላያችን ላይ አርፎአል:: መስኮት ፊት ለፊት ቆማ ውጋጋኑን እየጠጣች--(ይሄን ልብ ሳትል)--በመታጠብ ቀለሙ የደበዘዘ ቀይ ሽንሽን ቀሚሷ ለስላሳ የናስ ቀለም ያላቸው ወዛም ጭኖቿ ላይ ብርሃኑን አፍሰሰ:: የሚላሱ ነገሮች፣ የሚነከሱ ነገሮች፣ የሚጨበጡ ነገሮች፤ አቅፌዋቸው የሚሞቁ ነገሮች:: እዚያ ላይ ሙቅ ነውን?

(እንዲህ የሴት ጭን የሳበኝና የማርታን የልጅነት ጊዜ አቅርቦ ያስጨነቀኝ አጋጣሚ ነበር:: አንድ ቀን በቶሎ ቤቴ ለመግባት ታክሲ ተሳፈርኩ:: የአንድ ሰው ቦታ ብቻ ነበር፣ ከኋላ:: ገብቼ እንደተቀመጥኩ፣ ከጎኔ የነበረች በሳፈር ልብ ያላልኳት አንዲት ሴት ሰላም አለችኝ:: ፊቷ ማርታን የሚመስል ነገር አለው:: መልሼ ሰላም ካልኳት በኋላ:

'የጠፋ ቀለበት የተባለው መፅሐፍህን አንብቤው ደስ ብሎኛል:: ባለቤቴ ነው የነገረኝ የዚህ ሠፈር ሰው እንደሆንክ:: ሎሚ ሽታ እባላለሁ' አለችኝና በወርቅና በብር የሚንቦገቦግ ቀኝ እጇን ዘረጋች:: በችልታ ጨበጥኩና:

'በጣም ደስ ብሎኛል ደስ ስላለሽ' አልኳት:: ዝርዝር አልነገረችኝም:: ከመሃል እንዲህ እያወራችኝ ዐይኖቼ በድንገት በግማሽ የተራቆቱ ጭኖቿ ላይ አረፉ::

'ባለቤቴ ባሕል ሚኒስቴር ነው የሚሰራው፣ ስለ አንተ ሁልጊዜ ያወራል' አለችና ያየሁት ጭኗን እሷ በተራዋ በጨረፍታ አየች::

'ጫማ ልገዛ ገበያ ወጥቼ መመለሴ ነው' አለችና እግሮቿን ለማየት እንደፈለገች ሁሉ ጉልበቶቿን ግራና ቀኝ ከፈተች:: የጭኖቿ ርዝመት ልስላሴና ጤነኛነት ልቤን ወሰደው፣ ባለትዳር መሆኔን ረሳሁ::

'ቤቴ ታች ከድር ሱቅ ጎን ነው፣ ቤተክርስቲያኑን አለፍ እንዳልክ'

ልቤ ጠፍቶ ስታወራ ሁሉ በጥራት አልሰማሁዋትም:: (ልቤ ወደ ልጅነቴ ሄደ፣ ልቤ የጉልምስና ብሌኑን እያሸ እዛ ልጅነቴ ጋ፣ በመጀመሪያ ማርታ ጠብደል ጭኖች መሃል የሆንኩትን:: ትታኝ ሄዳ ትቻት ሄጄ በአእምሮአችን አለም ተገናኘን:: ስንመለስ አንሶላዬ ጃና መስሎአል:: የመጀመሪያዬ ዘገብአ:: እንዲህ አለችኝ በቅዠት መሃል: 'ባቡሩ ወዴት ሄደ የእኔ ዐይናማ?' 'ሊማሊሞ' አልኳት:: እስከዛሬ ይሄ ያልነው አይገባኝም:: ገና ያጠብኳት አንሶላዬ ላይ ድንግልናችን በጋራ ሲረግፍ እንደተሰቀሉ ሰዎች ጠባብ አልጋዬ ላይ በስሜት ተቸንክረን፣ ስንት ጊዜ ወሰደብን ለባብሰን ለመቆም?

ያለንባት ይህቺ አገር ለስንት ሺህኛ ጊዜ የእኛ መሆኗን ለማየት? የማርቲን ፍቅር ላለማራቅ ለአንድ ወር አልታጠብኩም ያኔ)

ከዛ ቆይቶ::

'ወራጅ አለ!' አለች::

ስትወርድ እሷን ለማሳለፍ ቀድሜ መውረድ ነበረብኝ:: ቀድሜ ወረድኩና ከታክሲው እንድትወጣ አንድ ሁለት እርምጃ ራቅ ብዬ ቆምኩ:: ከታክሲው ለመውጣት ስትጣጣር እነዛ የሚያምሩ ጭኖች ተከፋፈቱ፣ የፀሐይን ብርሃን ተቀብለው አስካሪ ቀለም አወጡ፣ ዐይኖቼን ከእነሱ ላይ ማንሳት ከበደኝ:: ከታክሲው ወጥታ እቆምኩበት መጥታ ልትሰናበተኝ ስትጨብጠኝ ገላዬ እንደ እሳት መንደድ ጀምሮ ነበር:: ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ ይል ነበር:: ምራቄን መዋጥ ተስኖኝ ነበር:: ሰላም ብላኝ ከሄደች በኋላ አካሄዷን አየሁ:: ታክሲ ውስጥ ተመልሼ ስገባ ሁለመናዬ እየነደደ ፈለግኋት:: ሊሆን ግን አይችልም:: ቤቴ ስደርስ ማርታን ገና ከስራ ገብታ ልብሷን ስትቀይር አገኘኋት:: ወደ አልጋ አቻኩላት ጀመር:: ግራ ገባት::

'ምን ሆንክ?' አለችኝ:: አልሰማኋትም:: ራቁታችንን ሆነን እላይዋ ላይ እንደ ሆንኩ ጥፋቴ ታወቀኝ:: የማርቲ ዐይኖች ግራ የገባቸው ነበሩ:: ደግማ ባትለኝም ዐይኖቿ ውስጥ 'ምን ሆነሃል?'ን አነብ ነበር:: እነዛን ዐይኖች ላይ ታክሲ ውስጥ የሠፈረብኝ የፍትወት ጋኔን ከላዬ ተነሳ:: በወላድነት የተነፈሱ፣ በዕድሜ የረገቡ ከንፈሮቿን በለመድነው ዝግታ ሳምኳቸው:: የስራዬ ክፋት ጉልህ ሆኖ ታየኝና ቆሻሻ መሆኔ ተሰማኝ:: ከማርታ ማን ይበልጥብኛል? ልብሴን አጥባ ንፁሕ የምታለብሰኝ ማርታ፣ የፃፍኩትን አንብባ ደስ ያላትንና ያላላትን ከልቧ የምትነግረኝ ማርታ፣ ሲደክመኝ ተጠግታ አቅፋኝ ደረቷ ላይ እንደ ልጅ የምታስተኛኝ ማርታ......

በልጅነቷ ቤቴ መጥታ አበባዬ ሆይ ብላ ጨርሳ ሲሄዱ ከልጃገረዶች ሁሉ የእሷ ፊት ብቻ መለስ ብሎ ሲያየኝ—ያን 'መለስ' ያን የእንቁጣጣሽ እንገት ማን ያህለዋል? እኔና እሷ ተባብረን ያጠፋነው ድንግልናዋ የሠርጋችን ዕለት አልተገኘምና......የቀልድ ደም ነክረን ስናዘፍን ፊቷን ትራስ ውስጥ ቀብራ እየሳቀች፡

'ምናባታቸውን ተዋቸው፣ ይዝፈኑ......' ያለችውን ማን ያህለዋል? ወዘተ......::

ሐጢያቴን ስረዳ ከላይዋ ላይ ገለል አልኩ:: ማንም በቀሰቀሰው ወንድነቴ ውስጧ አልሰፍርም:: የማርታ ስጋ ባዕድ ወንድነቴን አያቅፍም:: ባይተዋር ሆኛለሁ::

'ምን ሆንክ?' አለችኝ::

ልደብቃት አልችልም:: በጆርባዬ እንደተጋደምኩ እየቃሰትኩ ለምን አቻኩዬ ልተኛት እንደ ነበረ ነገርኳትና መልስ ከእሷ ሳልጠብቅ ደረቷ ላይ ተጣብቄ ይቅርታ ጠየቅኋት:: በትላልቅ

ከንዶቿ ወደ ደረቷ አስጠግታ እንደ ልጅ አናቴን እየሳመች፡

'ብሞት እንኳን አፅሜ አፅምህ ጎን ይሆናል የእኔ ጌታ፣ በሃሳብህም አታርክሰኝ፣ ሁልጊዜም አይኔና ሲጋዬ በጉጉት ይበሉሃል'

ግን ልቤ ፈርቶ ነበር። ምክንያቱም ሎሚ ሽታ የተባለችው ሴት የማርታ ልጅነት ነበረች።

'ይህቺ ሴት ስሟን ነገረችህ?'

'ሎሚ ሽታ ይባላል'

'እህ!......ጠይም ረዥም ሴት?'

'አዎ'

'ስለ እሷ ሲያወሩ ዝናዋን ሰምቼአለሁ። የሰው ባልና ጎረምሳ ማባለግ ነው አሉ ስራዋ። እያፋታች ታገባለች፣ ከዛ ትፈታለች። የምታገባው ደሞ ከእሷ በእድሜ የሚያንሱትን ነው......የሃብታም ልጅ ናት አሉ......አብዮት እንኳን አልነካትም። ቅፅል ስሟ ማን እንደ ሆነ ታውቃለህ?'

'ማን ነው?'

«'በለስ' ነው የምትባለው። እግዜር ለማሳሰቻ ነው ያስቀመጣት። አንድ ነገር ብታደርግ እንዲህ ፀጉርህን ብታስነካ ማርታ አይደለሁም። እንዲህ የምልህ ሳስፈራህ አይደለም። ስንቴ በወንድ ተነክቼአለሁ? ስንቴስ 'አትንኩኝ' ብዬ ተሳክፈአለሁ? ስንቴ በስንት መንገድ ወንዶች ቀርበውኛል? አንተን ከወደድኩ ጀምሮ የአዲስ አባን ጎዳናዎች የሞላው የእኔ አሻፈረኝ ነው፣ አንተ ታሪኬ ነህ። አንተ ልጅነቴ ነህ። ማን ኩብት ከልጅነቱ ይጣላል?[144]

---

144 ለመፃፍ የተቀሰቀስኩበት አንዱ ዕለት ነበር። ማርቲንት እንዳቀፈችኝ ከእኔ ቀድማ አንቅልፍ ወሰዳት። ከአልጋ በቀስታ ተነስቼ የዛን ዕለት መረበሼን የሚገልፅ አንድ ግጥም ለመፃፍ ሞከርኩ። አልሆነልኝም። እርጅና ይሆን? ወደ ፊት ከቀናኝ አንድ ረዥም ድርሰት ውስጥ የምለጥፋቸው አጫጭር የተቆራረጡ ሐረጎች ፃፍኩ። የነዚህን ማሰባሰቢያ ስም 'ቂሉማ' (ቂሉ ማን ነው?) አልኩት።

፩ 'ጣቶቼና ዐይኖቼ የተለያዩ ናቸው ብዬ......
ጣቶቼ ዐይኖቼን ዘንቀለው ቢያሳውሯቸው
በኋላ በኋላ እጆቼ የሚዳብሱትን ባያዩ
ማነው ቂሉ?
(ቂሉማ)

፪ ከቤቴ መዝጊያ ተጣልቼ እሱን ሰብሬ ብተኛ......
መከላከያዬን ነቅዬአለሁና ወንበዴ ገብቶ ቢደፍረኝ
ቂሉ ማነው?
(ቂሉማ)

፫ ያለፍኩበትን ትናንት ብንቅ፣ የተራመድኩበትን ጎዳና ባኪያኪስ......
የሳቅሁበትን፣ያዘንኩበትን ፍሬ ቢስ ባደርግ
ብቸኛ ሆኛለሁና ዱታዬ ባይሰማ
ማነው ቂሉ?
(ቂሉማ)

(የአንድ ማታ ማስታወሻዎች ጨርቆስ ሰፈር፡ አዲስ አበባ 1978 ያልታተመ።)

**ማን የማይረባ ያደገበትን ይተፋል? ሴትነቴን ከገላህ አወቅሁ:: ከአብራኬ ልጅነትህን አመጣሁ፣ ልጆችህን እያቸው:: ጥራቶች ናቸው:: በንፁሕ ፍቅር ያደጉ:: በቀስታ እደግመዋለሁ አንድ ነገር ቢሆን......ጥፋቱ......ያንተ ነው:: በበነጋታው እኔ እዚህ የለሁም፣ ገባህ? ድንቁርና ከሆነ ይሄ፣ የሚያምረኝ ድንቁርና ነው:: አሁን ተኛ......)**

ማርታ ይሄን ፈጣን ቀሚስ ገለባ ሰርታ በእፍረት ይሁን በሌላ በማላውቀው ምክንያት ከቤት እየሮጠች ስትወጣ ያባባኝ/ያስደነገጠኝ ውበቷ ተረስቶኝ ፊቴን ወደ ጎን ዘንበል አድርጌ መሬት መሬት አየሁ......ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ግን ከነዚያ ከሚያምሩ በዕብደት ከሚመቱ ጭኖች ከፍ ብሎ መድሐኒያለም ምስክሬ ነው የእኔን ዐይነት የውስጥ ሱሪ ለብሳለች::

ማታ ተኝቼ......ቀሚሷን ወደ ላይ አሽሽታ ገላዋን ያሳየችኝ የመፅሔቷን ሴት ለመምሰል ይሁን ወይ ላ ቻፔልን ለመምሰል......እስከ ዕኩለ ሌሊት መምረጥ ከብዶኝ እንቅልፍ ጣለኝ......

ለማንም የማልነግረው ዕርግጠኛ የነበርኩበት አንድ ጉዳይ ግን ነበር......

ሌላ ቀን በረዥም ቁመቷ በቀስታ ስትሳብ፣ ደብተሯን ጉያዋ ከታ ጎረምሳ የሚሞትላትን የደረሰች ትንሽ ቂጥዋን ለማየት በሚያዳግት ረቂቅነት እያማስለቻት ስታልፍ፣ ዝግ ያለችበት ምክንያት የውስጥ ሱሪው ከብዶአት፣ ያማስለች የምትመስልበት ምክንያት ደ'ሞ የዚያ ጨርቅ ጥጥ አልመች ብሎ ስላሳከካት እየመሰለኝ በከፊል ስቄአለሁ፣ በከፊልም አዝኛለሁ::

— // —

*1986 አዲስ አበባ/ሆላንድ*

# (ሽልንግ) የመጨረሻዋ የቀበሌ 01 ድንግል

*(ይቺ ሠፈር......ይቺ ቤት......ይቺ ናት)*

አዲስአባ የክረምት ጨምዳዳዋን አውጥታ መስከረም ደረት ላይ ታራግፋለች:: ይኸቺ ሠፈር ካደረችበት እርጥብ የሕልም አንጀት ጨርሳ ደርቃ አልወጣችም:: ጎሑ ሕጣን እንደሚፈታው የክረሜላ ልባስ ዐይኖቿ ስር እየተልፈሰፈሰ:: ቃጥቶ የቆመ ይመስላል ልንጋ አልንጋ ልቡ የተከፈለ:: የወርቅ ካስ የመሰለች ፀሐይ ከየረር ጀርባ በአድማስ ታላቅ ከንፈር ተነክሳ......ሁሉ ሜዳ፣ ሁሉ ግቢ በድፍንና በኩርማን አረንጓዴ ታፍኖአል:: ያረጀ የነሐሴ እርጥበት የላስቲክ ነጠላ መስሎ ሳር ላይ፣ አበቦች ላይ፣ ያበቦች ቅጠል ላይ፣ ወደ ቤቱ የሚያስገባው የሲሚንቶ ደረጃ ላይ፤ ከውስጥ ደ'ሞ ከቤቱ የቆርቆሮ ጠፈር.....ሳቦት እንደ ደካማ ዝናብ ይንጠፈጠፋል:: ወደ ድሬዳዋና ወደ'ዛ የሚሄድ ባቡር ተኚውን እንደናቀ መርዶ ነጋሪ ይጮኻል::

ቤቱ ዙሪያ ዕድ እንደ ግድግዳ በቅሏል:: በስፌት ተሰርተው የቆሙ ከሚመስሉ ከእነዚህ ዛፎች መሃል የመጮህ ሱስ ያለበት የመሰለ ውሻ አፉን በየገረገራው ቀዳዳ እያወጣ እየደጋገመ አላፊ አግዳሚ ላይ አሰልቺና አደንቋሪ ሳሉን ይሰላል:: ተሰጥቶ ሳይገባ የተረሳ በረዶ የመሰለ አንሶላ ቀድመው ባነጉ የወፍ ኩሶች ጭረት እዛና እዚህ ተበላሽቷል (የዘነጋችው ወይዘሪት መቀጣቷ አይቀርም):: ግቢው ዙሪያውን በእንቅልፍ ጋዜጣ ተጠቅሏል:: በሌሊት ወደ ሥራ የሚሔዱ ሰዎች በአጠገቡ፣ ቾልታ በሰረገበት እንቅልፋም የጠዋት አካሄድ ያልፋሉ:: ፈለጋቸው ረግረግነቱ ባልጠፋው የጳጉሜ መሬት ድምፁ እየተዋጠ......

ግቢው መሃል የቆመችው ቤት ባለ ሦስት ክፍል ናት፡ ሣሎን፣ መኝታ ቤት፣ ማድቤት ያላት። ሳሎኑ ጠባብ ነው። አንድ ጠረጴዛ፣ አራት ወንበሮች እና አንድ የቆመ አዋቂ ሰው ወገብ የምትደርስ የዕንጨት ቁም ሳጥን በመተፋፈግና በፉክክር የቆሙበት። ጠረጴዛው መሃል እፍኝ የሚሞሉ፣ ገና ያልፈነዱ በጎሑ ጨለማ ጥቁር የመሰሉ *ሮዛ አቢሲኒካ* ዕጌሬዳዎች ውሃ እስከ ወገቡ ድረስ የተሞላ ትልቅ ዘርጣጣ ዐይነ ባር ጠርሙስ ውስጥ ተቀምጠዋል። ጠረጴዛውን ከከበቡት አራት ወንበሮች አንደኛው ላይ በውጭ ደረት ኪሱ ቢጫ እርሳስ የሰካ፣ ክርኑ በቤዥ ቆዳ የተጣፈ አመዳም ቀለም ያለው አሮጌ ሱፍ ኮት ተንጠልጥሏል። ከዚህ ወንበር ጀርባ በትንሽ ጠረጴዛ ላይ አንድ ክንድ ተኩል የሚረዝም ሞላላ ሬድዮ ቴፕ ሬከርደር አለ። እዚህ ጋ በተናደና ባልተናደ ቁልል ካሴቶችና የካሴት ቀለሃዎች ፈስዋል። ከዋናው የቤቱ መግቢያ በር በስተቀኝ ግድግዳ ላይ የተለያዩ ዐይነት ልብሶች ተሰቅለዋል፣ የሳሎኑ የግድግዳ ቀለም ለስላሳ አረንጓዴ ነው። ጣራው መሃል ነጭ ቆብ የደፋች ሳትጠፋ የተረሳች ስትበራ ያደረች ስድሳ ሻማ አምፖል አለች። አንደኛው ግድግዳ ላይ ጥንድ ፎቶዎች ግራና ቀኝ ተሰቅለዋል። የመጀመሪያው ፎቶግራፍ ላይ ሁለት እንጨት ወንበሮች ላይ የተቀመጡ ወንድና ሴት አዋቂዎችና የቀኝ እጇን አመልካች ጣት አፏ ውስጥ ነክራ ፎቶግራፍ አንሺውን ኮስተር ብላ የምታይ የአስር ዓመት መጋል ልጃገረድ ከመሃላቸው አቁመው የተነሱበት ነው። ሁለተኛው ፎቶ ላይ ቀኝ እጇን አገጭዋ ላይ አስደግፋ ፎቶ አንሺውንና የሚመለከታትን የምታይ የምትመስል ዕድሜዋ አስራ ስድስት የሚሆን አንዲት ወሲፍ የአለችበት ነው፡ ይኼ የመጀመሪያው ፎቶ ላይ የነበረችው ትንሿ ልጅ አድጋ የተነሳችው ነው። መልከ መልካም ክንዶች እሷት ትከሻዎቿ ድረስ ቅርፃቸውና ልስላሴአቸው ሁሉን እንዲያማልሉ ሆነው የተጋለጡ። ዓይኖቿ የመኖር ጉጉት አላቸው። ከንፈሮቿ ሳያቋርጡ የሚቀበተቱ ሊፈነዱም የሚቅበጠበጡ ይመስላሉ። በተቃራኒው የአፈር ግድግዳ ላይ (በትክክል ከመሃሉ) በምስማር አራት ጥጎቹ ተቸንክረው የተሰቀለ ትልቅ ነጭ የአቡጀዲድ ሰሌዳ አለ። እዚህ ላይ በሰማያዊ ክር ተጠልፎ የተፃፈ ጥቅስ ይነበባል። እንዲህ የሚል፡

> *'ጥንት ነበር እንጂ ሰው አልሆንም ማለት*
> *አዳምና ሔዋን የተፈጠሩ ዕለት'*

መኝታ ክፍሉ በስተግራ ነው። ከሳሎኑ የሚጋርደው በር አልተቆለፈም። ከሌሎቹ ክፍሎች ይሰፋል። ሁልጊዜ ሊነጋ ሲል ጎህ ቀዶ ብርቱካንማ ጨረር በእንጨቱ መስኮት ፍርግርጎች መሃል ሰርጎ ሲገባ ቤቱን ከፋም ለማ ሕይወት ይሞላው ይጀምራል። በስተቀኝ ከንጋቱ ውጋጋን የተሸሸገች የመሰለች ትንሽ አልጋ ላይ አንዲት ኮረዳ በጀርባዋ ተኝታለች፤ ዐይኖቿ ተገልጠዋል። የንጋቱን ዕድገት የምታጠና ወይም ንጋቱ እስኪሞላ የምትጠብቅ ትመስላለች። (አንሶላውን አጥባ፣ አስጥታ ግን ሳታስገባው የረሳችው ልጅ ናት) ትልቁ አልጋ ላይ በፒጃማ የተኛ ወንድና በአጭር ውስጥ ልብስ የተኛች ሴት አሉ። ሴቷ የተኛችው በግራ ጎኗ ነው። ሴትዮዋ አንድ እግሯን ሰውዬው ወገብ ላይ አጋድማለች፣ ሌላኛው እግሯ በግድግዳውና በአልጋው መሃል አርፏል። የውስጥ ልብሷ ወደ ላይ ተሰብስቦ ችፍግ ያለ ፀጉር የለበሰ ሃፍረቷ ይታያል። ሰውዬው ፊቱን ትራስ ውስጥ ደፍቶ

ያንኮራፋል:: ሴትዮዋ በቀስታ ዐይኖቿን ገለጠችና ቀና ብላ ጣራ አየች፣ አንድ ሁለቴ በቀላሉ ሳለችና እፍረቷን ለመሸፈን የውስጥ ልብሷን ዝቅ አደረገች:: ቀኝ እግሯን ከሰውዬው ላይ አወረደች:: ወደ ጎን ዞራ ፊቷን ሰውዬው አንገት ውስጥ ቀበረች:: የሆነ ነገር አጉተመተመች:: ምናልባት ቀልምጫ:: ግራ እጇን በብርድ ልብስ ስር ሰዳ ሰውዬውን ነካካችው:: የሰውዬው ማንኳረፍ ቆመ:: ፈገግ አለችና ዐይኖቿን እንደ ጨፈነች ማጅራቱን ሳመችው:: አለፍ ብሎ ወጣቷ በሃይል ትስላለች:: እየሳለች እንደ ተበሳጨች ሁሉ የለበሰችውን ብርድልብስ ከላይዋ ላይ ትገፋለች:: በደብዛዛው ጠዋት የጡቶቿ ጫፎች ጤዛ የሳማቸው የአጋም ፍሬዎች ይመስላሉ......

O

እንዲህ አንድ ማታ ሲያንቀዠቅዠኝ ዝም ብዬ ራቁቴን ነገር ወዲያ ወዲህ ስል......ጋቢ እንኳን ደርቤ ነበር......ማዘር 'ተይ አንቺ ተይ አንቺ ብርድ እንዳይመታሽ' ምናምን እያለችኝ......'አትነዝንዥኝ' ምናምን እያልኳት ከዛ ሂሳቤን ወሰድኩ:: ታዲያ በኋላ ማዘርም ፋዘርም 'ያሽልሻል' ብለውኝ መአት ትኩስ ሻይ በጤና አዳምና በዝንጅብል ተሰጥቶኝ እሱን ተግቼ እንቅልፍ አልወስድ ብሎኝ አለ አይደለ ስቅይት ምናምን እላለሁ:: አንዳንዴም ይኼ የሚያንገላታኝ በሽታ የጠፋ የተሻለኝ ሲመስለኝ ደኅና እንቅልፍ ወሰደኝ ስል ወላ የሚደብር ቅዠት ይመጣና ይቀሰቅሰኛል:: በቃ ሰላም አጣለሁ:: ከንፈሮቼ በቃ ተሰነጣጥቀው...... ሳንባዬ አለ አይደለ በደረቴ በኩል ሳየው ምናምን እንደዚህ ራሱ ሲያለክልክ ይታየኛል እና ደ'ሞ የደረቴ አጥንቶች ልክ አለ አይደለ ከባድ ስራ ከሰራን በኋላ እንደሚያመን ዓይነት ነገር ውጋት ሰንጓቸው በቃ መተንፈስ አቅቶኝ ምናምን:: ደ'ሞ ላቡ ውይ ላቡ ሲያጣብቅ ሲደብር:: በጣም ሙቀት ስላስጨነቀኝ 'ተይ' እንደሚሉኝ ባውቅም ጭንቅ ስላለኝ ብቻ ብርድ ልብሴን ከላዬ ገፍፌ በከፊል ራቁቴን ሆኜ ተኝቼአለሁ:: ለጋ ጠዋት መስኮት ላይ ማንዣበብ ጀምሯል:: አለሁበት ክፍል ውስጥ ብቅ ጥልቅ የሚሉ ሳቆች እሰማለሁ:: በዚህ ደብዛዛ የጎሕ ብርሃን ውስጥ የእናቴና የአባቴ የሽቦ አልጋ ተነቃነቀና......እንደ ጥጥ ኳስ የሚያደርገው የእናቴ ለስላሳ ሳቅ......ከዛ የተቆራረጠ በደንብ ጥርት ብሎ የማይሰማ ሾክሿካ ንግግር:: አባቴን «በምኔው ነጋ» ሲል ሰማሁት:: ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት አባቴን ሲነጋገር ስሰማው እረጋጋለሁ:: የሚመች ትራስ የተደገፍኩ ይመስለኛል:: ወፍራም ድምፁን ስሰማው ሁሉ ነገር ትክክል የሆነ ይመስለኛል::

«ትንሽ ጠጋ በል» ትንሽ መሽኮርመም የሚርመሰመስበትን የእናቴን ሳቅ እሰማለሁ:: ለስላሳ ድምፅዋም ግራ ፊቴ ላይ እንደ ሚሞቅ ውስጥ ልብስ ሲያርፍ......

የጐረቤታችን ውሻ ስሙ ሁሌ እንደተረሳኝ ነው......ቢያንስ ባይኖቼ አሳድጌው ስሙን እረሳለሁ:: ለአጭር ጊዜ ተንጫጫ:: ምነው የእኛ ኩቲ ዝም አለ? እያልኩ ትንሽ በግራሞት ሳስብ መሳል ጀመርኩ:: ሬዥም ሣል:: በክርኔ አልጋዬን ተመርኩዤና ተንበርክኬ ፊቴን ወደ አንሶላው ትራሴ ደፍቼ ሳንባዬ ተወርውሮ የሚወጣ......ጉሮሮዬም ራሷ ተቀርፋ የምትወጣ እስኪመስለኝ ሳልኩ:: ፊቴን ወደ እናቴና አባቴ አልጋ ቀና አደረግሁ:: ተደራርበው ተኝተዋል:: አልጋቸው በቀስታ ይናጣል:: የሚሰሩት ይገባኛል:: የማየው የምሰማው እያሳፈረኝ

ከእፍረቴም እየታገልኩ ልብ ሳልለው ዝቅ ብዬ ወደ ደረቴ አየሁ......ለመጀመሪያ ጊዜ ጡቶቼ ገና ደረቴን ብዙ ባይለቁም ሊወድቁ ያኮበኮቡ ጠይም የውሃ ጠብታዎች እንደሚመስሉ አየሁ:: በጣቴ ብነካቸው የሚፈርሱ ዐይነት:: ደ'ሞ አለ አይደለ የሌላ ሰው እንዳየሁ ሁሉ አሳፈረኝ:: ብዙውን የሴትነት ነገር ለብቻችን ነው የምናውቀው፣ አለ አይደለ 'ብዙ ነገር አየን' የሚሉት ድብን ያሉት ዱርዬ ሴቶች እንኳን እንድንማር ወይ ከስህተት እንድንርቅ ወላ ዱዲ አያስተምሩንም:: ያበሽቃል:: ወር አበባ ሲታየን ትንሽ ቀን አብረውን ያንጎዳጉዱና አለ አይደለ በቃ እንደ ብርቅ ነገር 'አይዞሽ ምናምን' 'ሁሉም አለበት ምናምን' ይሉንና በቃ አይነግሩንም......ከዛ እንደዛ እያሉ ይስቃሉ ቂቂቂቂቂ ታዲያ እኛ ጀማሪዎች ዞር ብሎብን ቁጭ ይላል:: በመስኮት የሚገባውን የጎሕ ውጋጋን በጀርባዬ ስለጋረድኩት የጡቶቼ ቀለምና ሁለመና አይታይም:: ከዛም ልክ መቀስቀሻው እነሱ ዘንድ እንዳለ ሁሉ ትራሴ በድንገት ጫፋቸውን ሲነካቸው ከግንባሬ እስከ እግር ጥፍሬ የሚያሳክክ ነገር ተሰማኝና አይኖቼን በቀስታ ከድኜ ጡቶቼን አቅፌ ፊቴን ትራስ ላይ ደፋሁ:: ከሚያስጨንቀኝ የብርድ ሕመም ስር ልሰይመው የማልችለው የሚጥም ኮርኳሪ ስሜት ተሰማኝ:: በፈዘዙ ዐይኖቼ እያለሁ የንጋት ብርሃን በየመስኮቱ ቀዳዳ......ነጫጭ ያዘነበሉ ቢጫቴ ዘንጎች......የሚያምሩ አደይ የሚያስታውሱ ተዳፋቶች......እነሱን እያለሁ:: (ስብርብር ያሉ በውሃ እጥረት የተነሳ ከአንገታቸው የታጠፉ አደዮች አንዴ አይቼ 'ምነው ተዳፉ?' አልኩና ታዲያ እናቴ 'ያልተፈጠረ አማርኛ ከየት አመጣሽ' ምናምን ብላ ሳቀችብኝ) አፌ ያለ እኔ ፈቃድ እንደ ደነገጥኩ ሁሉ በቀስታ ተከፍቷል......አየር እስባለሁ...... ምን ይሆን ይሆን? እላለሁ:: ግን ምን ይሆን ይሆን? እላለሁ:: ልክ እንደ ኩብኩባ ትንፋሽ እስካጣ በብርድ ልብሴ ተጠቅልዬ ተኛሁ......ማምለጥ ብችል......

*(ዘመድና ፍላሎት[145])*

ገና በትንሽነቷም ይሁን ወይም አሁን አድጋ 'ራሷን አወቀች' (ራስን ማወቅ እንኳን ይኸቺ ብላቴና ይቅርና የአቴናው ፈላስፋ ሶቅራጥስ ቸግሮታል) ከተባለችም በኋላ በእናቷና በአባቷ ችላ የተባለች እየመሰላት አልፎ አልፎ ያስጨንቃታል:: እነሱ 'አልቀረቡኝም' በሚልም ህልዮ በዓይን አይታ የመሰጥዋት ጎረቤቶቿንና የቅርብ ዘመዶቿን በወላጆቿ ተክታለች:: ለምሳሌ አቶ______በስተግራ በኩል ያሉት ጐረቤቷ እንደ አባቷ ሲሆኑ ወ/ሮ____________(ስረዙ የረዘመው ስማቸው ረዥም ስለሆነ ነው) የአቶ ማንትስ ሚስት(የሚታወቁ ሴትዮን በማይታወቁ

145 'ወጣቶች በአብዛኛው የማያስቆጣ ያስቆጣቸዋል:: ቶሎ ያኮርፋሉ:: ሁሉን ነገር ያለ ቁጥጥር ያለ ጠባቂ ለመስራት ይፈልጋሉ:: ለዕውቀት ሳይሆን ለድርጊት ይቸኩላሉ:: ምክንያት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም እዛውንት ይጠላሉ:: ደማቸው ነጋ ጠባ ይፈላል ይንተከተካል:: ፍላሎት ስላለባቸው ባያውቁም እናውቃለን ይላሉ:: ለአገር መጥቀም የሚጀምሩት እነዚህን የፍላሎት እንቅፋቶች ያለፉ ናቸው:: ሊጎዱ ከፈለጉ ግን መገለባበጥ ይችላሉ:: አትገለው ልጅህ ነው:: አትምረው ሊያጠፋህ ነው:: የፍላሎት ዋና መሰረቱ በዮሎጂያዊ ነው፣ ማለት ሆርሞናዊ ነው፤ ግን ሕብረተሰብን ለመጉጃ የሚጠቀሙበት ይኖራሉ:: በራሱ የሚቀር(እዛው ፈልቶ እዛው የሚገነፍል) ፍላሎት ብዙ ጊዜ ግን የለም' ሰሙ ንጉስ ሄርጳ ስር ነቀል ለውጥ ወይስ የችኮላ ለውጥ: ፍላሎት፣ ወጣትና ማሕበረሰብ አዲስ ማተሚያ ቤት 1967 ገፅ 120::

ባላቸው መግለጽ አይገርምም??) እንደ እናቷ ነበሩ:: እነዚህ ሁለቱ ግን ፊት ለፊት በስጋ ተከስታ አጋጥማቸው ካልሆነ መኖሯ ትዝ ባይላቸውም:: የአጎቷ ልጅ እዚያ መሿለኪያ ያለው ፀጉረ ዞማው ሲስቅ ዓይኑን የሚጨፍነው እሱ 'ወንድሟ' ነው–ከተያዩ ሁለት ዓመታት ቢያልፉም:: የዛ አካባቢ የሴቶች ማሕበር ሰብሳቢ ወይዘሪት ሳባ ቅዱሳን የደራሲ ስብሐት የመጀመሪያ ሚስት፣ የሚያምሩ ጋቶች ያላት ቀልደኛ፣ ስንቱን ልብ ያጠፋች ልደታ ማርያምንም ያስቄመች...... እሷ 'እህቷ' ናት:: ስታገኛትም 'ሳብዬ' እያለች ስታቅፋትና ስትስማት ሳባ ግራ ቢገባትም::

የሰፈሩ ልጆች ጠቅላላ እንደ ወንድሞቿና እህቶቿ ነበሩ:: ከትምህርት ቤት ልትግባባው የማትፈልገው ዓይነት ሰው የለም:: ነጋ ዱርዬው እጠፋርስ ይነግዳል እየተባለ የሚታማው አቆላምጦ የሚጠራው እሷን ነው:: እሷን ከወደዷት የፈለጉትን ቢሆኑ ግድ አይሰጣትም:: ግን ከእነዚህና ከሌሎች ጋር (የክርስትና እናቷን ዘውዲቱን፣ ባለቤቷን አባተንና ልጃቸው ገዳምን ሳይጨምር) ጠግባ እንዳትገናኝ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሚተርፏት የመዝናኛ ሰዓቶች ብዛት እጅግ ጥቂት ናቸው:: በተለይ የእረፍት ቀኔ ነው በምትለው ቅዳሜ እቤት ቀርታ የቆሸሸ ዕቃ እንድታጥብ፣ ክንዷ የሚችለውን ቀሚስ ሆነ ጨርቅ እንድትጨፈጭፍ ትታዘዛለች:: በቤቱ ደንብም ለሦስት ቀን ለአራት ቀን የሚሆን 'ምግብ ስሪ' ወይም 'እንድሰራ እርጂኝ' ትባላለች......(እናቷ 'ልጄ ደረሰችልኝ ልብሷን ለማጠብ' ባለቻት በአስራ አምስተኛው ቀን የለቅሶ ቤት ቀይ ወጥ የፈሰሰበት፣ ከፎቅ ላይ ቢወረወር ፖፖላሬና ጨርቆስን በጥላው የሚያቀዘቅዝ ጭራቅ ጋቢ እንድታጥብ ወረወረችላት):: ይኼ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣት ሴት ልጆች የተመደበ ደንብ እንደሆነ አይገባትም:: ማቲ ሀበሾች ጉልበታቸው ጠና ሲል ልጅነታቸው እንደሚያልቅ አትረዳም:: ሁሉ ልጃገረዶች በየቤታቸው የሚያሳድጉት ጎረምሳ ወንድም፣ 'ደከመኝ' የሚል አባት፣ 'ወገቤን' የምትል እናት እንዳላቸው አታውቅም:: ብታውቅም ትዝ አይላትም:: በትምህርት ቀን ከቤት ወደ ት/ቤት፣ ከት/ቤት ወደ ቤት የምትመጣበት ሰዓት ተረጋግጦ የታወቀ ነው:: (ስትሔድ 30 ደቂቃ ስትመለስ 30 ደቂቃ) የትኛውም ዓይነት 'ዝንፈ'[146] ካጋጠማት (ወደ ቤት በምታደርገው ጉዞ መንገድ መሐል የሰኞ ማክሰኞ ጨዋታ ጠምዷት ወይ ከዕድሜ እኩያ የዋህ ወንዶች ጋ ስትለካከፍ) ትንሽ መዘግየቷ ከገባት በጭንቀት ትበጠበጣለች:: ፊቷ ላይ መርበትበት ይነበባል: 'እማማ ትገለኛለች በእናታችሁ ልሂድ......ምናለ ባልተፈጠርኩ' ተብሎ ሊተረጎም የሚችል:: አንዳንዴ እቤት ገብታ መክሰስ ልትቆርስ ስትቀመጥ የምትበላው ሁሉ ከጉሮሮዋ የሚወርደው በግድ ነው::

ስትወለድ ከእግዜአብሄር የታደላትን ነፃነት እንደተነጠቀች ሁሉ ይሰማታል:: እናቷ ወንጭፍ ስታዞር አባቷ አስተኳሽ እሷ ወደማታውቀው እነሱ ወደሚያውቁት ሩቅ አድማስ ይመራታል:: እሷ ከረጳ ወንጭፉ ማቀፊያ ሠንተራው ላይ ያጠላት፣ ያተኮሳት፣ የፈላባት፣ ብረሪ ብረሪ ያላት ድንጋይ ናት:: ከወንጭፉ ከወጣች ደ'ሞ ከርማለች:: ከምትጠዝበት ሰማይ ላይ ወደ ታች

146 የሚያበሳጭ የልተጠበቀ የዕቅድ መዛነፍ(አ)

ስትቃኝ የሚታያት እንደ ብሌኗ የጠቆረ የጉድጓድ አፍ ነው።

○

ሲያሳዝን......

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አባቴና እናቴ እንደ ቀድሟቸው አይከባበሩም። ደ'ሞ ብዙ አይነጋገሩም። እንደተኮራረፉ ይገባኛል። ከተነጋገሩ አባቴ አጭር፣ እናቴ ረዥም ስድብና ንጭንጭ ይለዋወጣሉ። ሁለቱም አያምርባቸውም። እናቴ የበለጠ ሙጢ ናት። አባቴ አንድ አረፍተ ነገር ተናግሮ በቦክስ አስር ጊዜ ጠረጴዛ ይመታል። ከአፎቻቸው ነበልባል ይወጣል። ውስጤን ብስጭት ይበላዋል። ያበሳጨኛል። ተናገሪያቸው ተናገሪያቸው ይለኛል። ምንም ደስ አይልም። አለ አይደለ 'አትደብሩኝ' ምናምን ልላቸው። ባይሆን እኔ ፊት አታድርጉት ልላቸው። እናቴ የቴሌፎን ኦፕሬተር ሆና አንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ትሰራለች። አባቴ የሕንፃ ቆርቆሮ ከዳኝ ስለሆነ ሥራ የሚያገኝበትም፣ የሚያጣበትም ጊዜ አለ። የእሷ ገንዘብ ብዛቷ ባይጠቅምም ቋሚ ናት። እሱ የሚያገኘው ገንዘብ ከእናቴ ቢበዛም መቼ ሥራ አግኝቶ ገንዘቡን መቼ ወደ ቤት እንደሚያመጣው የተረጋገጠ አይደለም። በዚህ ዕድሉ ሁሉ ታንጓጥጠዋለች......በልቤ ለምን እናጢ መሆኑን አውቃ አገባችው? እላለሁ። ትቼአቸው እንዳልወጣ እናቴም አባቴም 'የት ልትሄጂ ነው?' ምናምን ይሉኛል። አለ አይደለ መሰዳደባቸውን አቁመው «የት ትሄጃለሽ?' ምናምን። አይገርምም? አሁንማ 'ስለጎረመስኩ' ትልቅ ጉዳይ መሆኑ ነው እንደ ልቤ መውጣት ተፈቅዶልኝ አያውቅም። ግን 'ስለ ጎረመስሽ ነው' አይሉም። የሚገርመኝ እናትና አባቴ መቼ እንደ ነቁ ነው። ግንባሬ ላይ ተፅፎአል ወይ እናቴ ደብቄ የምጥላቸውን ጨርቆች አግኝታለች። የእሷ ጨርቅ/ሞዴሷ/ቶሎ ቶሎ ሲያልቅባት ጊዜ ጠርጥራ ይሆናል። የወር አበባዬን ሳይ የረዳችኝ ጓደኛዬ መንበረ ናት አለ አይደለ እሷ ከእኔ ቀድማ ሆኖላታል እና እቀናባት ነበር......ሲደርስብኝ ግን ደበረኝ። ከዛ ከአሁን በኋላ 'ለሴክስ[147] ደርሰሻል' አለችኝ። ከዚህ ሌላ ምንም አልነገረችኝም። እሷ እኮ ብዙ ነገር ታቃለች። ታዲያ አባትና እናቴ ሲነጫነጩ ቆሜ ተቀምጬ ሲኒማ፣ ቲያትር ነገር እያለሁ......

«አንቺ ለዚያች ለወሬኛ ምን ጉድ ነው ያወራሻት?»

«አንተ ሰክረህ አውርተህ ይሆናል እንጂ እኔ አልወጣኝም»

«በቴሌፎን መለፍለፍ ለምዶብሽ እዚህ ሠፈርም ውስጥ ለማቆም ከበደሽ»

«እንዳንተ ከመቦዘን ይሻላል»

«በይ አፍሽን ዝጊ»

«የሠራው እግዜር። ባወራብትስ?»

«እንትንሽንም እግዜር ስለሰራው ነው የትም የምትጥይው»

እኔ ታዲያ በእፍረት የደነገጠ ፊቴን ከልዬ እንዳልሰማ መስማት። የሚያሰለጥኑኝ ይመስላል አለ አይደለ 'ወደ ፊት እንደዚህ እኛ እንደምናደርገው

---

147 ወሲብ(እ)

የመሰለ መነጫነጭ ማድረግሽ አይቀርምና የመነጫነጭ ቴክኖሎጂ ከእኛ ቅሰሚ' ነገር ምናምን......

ሁለት ትልልቅ ሰዎችን ይኸቺ አልፎ አልፎ በመንቀጥቀጥና በማፈር በምነካት ስጋዬ ይራበሻሉ? ምን ነገር አለ እዚያ ፍቅር የሚያደፈርስ? ልጅ ፊት አፍ የሚያካፍት? ይሉኝታ ቢስ የሚያደርግ? ገና ኮረዳ መሆን ስጀምር ከዚህች የሴትነቴ ብልት ዙሪያ ተግተልትሎ የሚመጣው እንዲህ ዓይነት ነገር ሁሉ አስፈራኝ::

ምነው እማማና አባባ ካልጠፉ ሰሞን መርጠው አሁን እንቁጣጣሽ ሲቀርብ ተነጃጀሉ?

## (ያንጸንድ ኀረምሶች ግራኪ ነገራቸውና አበባዬ ሆይ)

የአዲስ ዓመት ዋዜማ ነው:: አዲስአባን ከእንጦጦ ቀብዋ......እስከ ንፋስ ስልክ ቀርጭምጭምቷ የፋብሪካዎችንና የፈሳችንን ጢስ ድል የነሳ......የድፎ ዳቦ ጉም......የድፎ ዳቦ ጠረን፣ የተቃጠለ ከባ መዓዛ ሁለንተናዋ ላይ ወድቋል::

ለሰው ሆድ እንደታቀዱ ያልገባቸው ከብቶች እምቧታና የበጎች ባታ፣ የመኪና ምጥና የሰው ጬኸት በራዱ አየር ውስጥ በየቦታው ይፈነዳል፡ በከረሰሰና በለሰለሰ የአዲስ አባ ሁለመና ይሰርጋል:: ልጅቷ ጭር ያለ ቤቷ ፊት ለፊት ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ ከጥቂት የሰፈሯ ልጆች ጋር ትጫወታለች:: ያወራሉ፣ ይሰዳደባሉ፣ ይነጫነጫሉ:: ያርፉና ያወራሉ፣ ይስቃሉ፣ ይለካከፋሉ:: እናቷ የታመመ ሰው ጥየቃ ሔዳ አልተመለሰችም:: መቼ የአዲሱን አመት ድፎ ዳቦ እንደሚጥሉ አታውቅም:: አባቷ በቅርብ ለአስቸኳይ ሥራ ክፍለ-ሐገር ሄዶ አልተመለሰም:: ለበዓሉ መድረስ ይቻል አይቻል መልዕክት አላከም:: ከሁኔታው የሚደርስ አይመስልም:: ብዙዎችን፣ እዚህ ቦታ በተለምዶ የሚሰበሰቡትን አብዛኞዎቹን የሠፈር ወጣቶች በማርጀት ላይ ያለው የእንቁጣጣሽ ዋዜማ ምሽት ወደ አልታወቀ አቅጣጫ በታትኖአቸዋል::

በሰፈሩ ሰላላ አጥንታም መንገዶች ውስጥ የሚመላለሱት፣ የሚታዩት ጥቂት ናቸው:: እሷና የአቶ_____ልጅ በተለመደ በሚያውቁት ቀልድ እየሳቁ ቆመዋል:: የአቶ_____ን ልጅ_____የጎረምሳ ገፁን እንደ ብይ የሚያበሩ ወፋፍራም ብጉሮች ሽፍነውታል:: ፊት ለፊቷ እየተወዛወዘ ወዲያ ወዲህ እያለ ተረቡን ይቀዳል:: ሲያወራ ወዲያ ወዲህ ማለት ይወዳል:: ሲያወራ ሲወራጭ ከብብቱና ከጉያው የሚያስከር የጠረን ጠላ ይወጣል (አንዳንዴ በሰዎች አጠገብ ሲያልፍ የሚሸታቸው ድፍድፍ ነው:: ዞር ብለው ዐይተውት ግራ በመጋባት ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡ 'ምንድነው የሸተተኝ?'):: ለአፍታ ያላበው እጁን ብሽሽቱ ከቶ ራሱን በፍቅር ያካል—ልክ ቀንጫ እንዳራወጠው ውሻ:: ሎጋ ነው:: ያማረ ቁመና ያለው:: ሳይንጠራሩ ከእንጦጦና ከእሪ በከንቱ የሚታይ:: ልጡ እንደተነሳ ርጥብ የባሕር ዛፍ ቋሚ ቀይ ዳማ:: ጥርስም ነበረው በጨለማ እንደ ባትሪ የሚንተከተክ:: ይሉታል በዝና ምላሱ ባልጩት የሚያቀልጥ:: ስሙ የተጠራ ፎሽፎሽ:: በከፊል ሽቷም በከፊል ቅርናታም::

የአስቴር አወቀ ዘፈን በስተቀኝ ካለው ቤት በሐረግ ከተጀጎለው *በሰባራ ፎሌ ውሃ አይጠለቅም*......እንደ እርጥብ ፓስታ እየተመዘዘ ይወጣል......ዜማውን ስትሰማ ልጅቷ ፊቷ ላይ ይኼ ነው ብላ መግለፅ በከብዳት ሃሳብ የተመሰጠች ይመስላል......አለ አይደለ......ምናልባት 'ፎሌ' የሚለውን ቃል ትርጉም ስለማታውቅ፣ ምናልባት ድምፁ ሲመጣ በጉዞ ላይ በተለያየ መልክ አቅሙ እየደከመ እሷ ጆሮ ሲደርስ ጮርቃ አንጎሏ ታካችነትን ማገዝት ስለሚጀምር ይሄም አሳዛኝ ስለሚያስመስለው? ምንም ይሁን ብቻ......ዘፈኑ ስለተሰበረ ነገር ስለሚያወራ......'ፎሌ' ስለሚባል? የማታውቀው እና ይሄም በመንከቱ ሰበብ የተጠማው ሰው ምናልባት የአስቴር ወዳጁ ውሃ ሳይጠጣ መቅረቱ እያሳዘናት? ኪነቱ በኪነቱ መያገ ሲመጠን ዘፈኑ አሳዛኝ እንዳልሆነ ማንም ቢያውቅም...... እና እሱ ልጅትን ብቸኛዋን የምትሰራው የሌላትን......በወሬው ያርሳታል:: ሲያልቅበት ወይም ሲደከመው አረፍ ብሎ ብዙም የማይማርከውን እንግዳ፣ ብርዳም፣ ሊሞት የደረሰ የጳጉሜ ምሽት ያጤናል:: በምዕራብ የሰማይ ተዳፋት እርጅና ያፈዘዛት ፀሐይ አቦልሴ ዳመና ላይ ሳልሳ ውጋጋኗን ታፈሳለች:: ይኼ ውብ ቀለም ላይ የልጅቷ ዐይኖች የጠፋው ዕቃ እንደሚፈልጉ፣ እሱንም አጥተው ተስፋ እንደቆረጡ ሁሉ ለአፍታ ፈዘው ሲንከራተቱ ቆዩ:: እሱ፣ ጎረምሳው የአቶ_____ልጅ _____ፊት ለፊቷ ቆሞ እየሳቀ፣ እንደ ፎካሪ እየተንጎራደደ ተረቡን ይቀዳል......

ሰፋፊ በቆሉ የመሰሉ ጥርሶች አሉት:: እንደ ፈረስ ይስቃል:: ሲስቅ እንደማረካት ሁሉ እያየችው ፍግዝ[148] ትላለች:: ታዲያ እዚያው ቆመው ወደ የትም ሳይንቃነቁ ያዩትን፣ የሰሙትን፣ የሚያዩትን፣ የሚሰሙትን የተንተራሰ ወሬአቸውንና ተረባቸውን መቅደድ ይቀጥላሉ:: እሱም ከአፍታ ፎከትና ፀጥታ በኋላ:

«አንቺ ዳቦ አትጋግሪም እንዴ?»

«ምን አገባህ?»

«ምን አገባህ? ሴቶች ሁሉ በየጓዳቸው ለበዓሉ እየተዘጋጁ ናቸው»

«ማዘሬ[149] አልመጣችም»

«አልመጣችም? አንቺ ታውቂያለሽ? እናትሽ ዘውዲቱ ትዞራለች»

«አንተም አሉባልተኛ ሆንክ?» ልክ ጠንቅቃ ፀባዩን እንደምታውቅ......

«አሉባልተኛ? በሰው ሰው ምን አገባኝ:: ነገሩን ነው»

«አይተሃል በዐይንህ?»

«አይተሃል ወይ? ድብን አድርጌ ነዋ»

«የት?»

«የት? ግራዝማች ሆቴል ስትገባ»

---

148 ፍግዝ፡ ፍገግታና ፈዛዛነት ያለበት ትንሽ የተምታታበት ገፅታ

149 my mother= እናቴ(እንግሊዘኛ)

«ከማን ጋር?»

«ከማን ጋር? እኔ የት አውቀዋለሁ»

«ውሸታም»

«ውሸታም? ለምን እዋሻለሁ? ጥሩ አይደለም ባለትዳር ሆኖ እንዲህ ማድረግ:: ወላጆቻችን ጥሩ ጥሩ ነገር ቢያስተምሩን ምን አለበት» በፌዝ አፉን ወደ ሰማይ ሰቅሎ ከት አለ::

«ቢያስተምሩህ ይገባሃል እንዴ? ኢ.ኤስ.ኤል.ሲ.ሽን እንኳን ስንቴ ነው የነጠርሽው?»

«ኢ-ኤስ-ኤል-ሲ-? ኢ-ኤስ-ኤል-ሲ አለማለፍ ወንጀል አይደለም:: ባጠና ላጥ ነው የማደርገው»

«ውሸታም:: ታዲያ አታጠናም» አለች በማፌዝ::

«ቤታችሁ ማንም የለም?» አርዕስት ለወጠ፣ ወደ ድክመቱ እንዳትዘምትበት:: ይኼን የአርዕስት ልወጣ ስለተላመደው ዓይኖቹ ውስጥና ኩንቱ ላይ 'የሽወዳ ሰቀቀን'[150] ወይም 'የሽግግር ሰቀቀን'[151] አይታይም::

«ማንም የለም»

«ማንም የለም? ገብተን ለምን ሙዚቃ አንሰማም?»

«ቴፑን እናቴ ቆልፋበት ነው የምትሄደው»

«ቆልፋበት? አስገራሚ ቴፕ ነው:: ምን ያስቆልፋል? ሬዲዮ እንሰማለን እሺ»

«እንዳጠና ነዋ:: ሬዲዮ ደ'ሞ አልወድም፣ ከእሁድ በስተቀር»

«ሬድዮ ይደብራል እሱስ:: አንቺ አጐቴ ቪዲዮ ገዝቶ ባለፈው ሳምንት ሁለት ፊልም አየሁ»

«ተዝናናሃ»

«ተዝናናህ ትያለሽ:: በቃ:: ፊልም እየተከራየሁ......መሸፍ ነው»

«መከራያ ገንዘብ አለህ?»

«መከራያ ገንዘብ? ለፊልም አይጠፋም:: ሲኒማ ኢትዮጵያ የህንድ ፊልም ማየት በቃ ቀረ:: አፐንጃዬ[152] ምናምን የለም:: አሪፍ የአሜሪካ ፊልም ታያለሽ...... አክሽን ምናምን»

«መደባደብ ምናምን ነው አይደል?»

---

150 ከመጋለጥ ለመሸሽ አርዕስት ለመለወጥ የሚዋሽ (ውሸት የተናገረ) ሰው አርዕስት ሲለውጥ በገፁ ይሁን በገላው የሚያሳየው መረበሽ(አ)

151 ዝኒ ከማሁ

152 በአገሪቷ አንድ ሰሞን ተወዳጅ የነበረ የሕንድ ዘፈን::(አ)

«መደባደብ? ታዲያስ......መጥፎ እኮ አይደለም፡፡ አይተሽ አታውቂም?»

«ቪዲዮ? አይቼ አላቅም»

«ስታሳዝኚ......ቪዲዮ አይተሽ አታውቂም? እኔ ሲኒማ ቤት መሄድ አቆምኩ፡፡ በሰላሳ ሁለት ኢንች ቲቪ ቪዲዮ አያለሁ»

«ሲኒማ አይሰለችም?»

«ሲኒማ አይሰለችም? ለምን? ደስ ይላል፡፡ መለዋወጥ አለብሻ፡፡ አክሽን......ላቭ ስቶሪ[153]......አድቬንቸር[154]......ምናምን......አንድ ቀን አሳይሻለሁ»

«አንተን ማን ያምናል?»

«አንተን ማን ያምናል? አታደርገውም ነው?»

«አዎ»

«አዎ? አንቺ ነሽ ማየት የምትፈሪው»

«እንዴት አወቅህ?»

«እንዴት አወቅህ? ማንም ያውቃል»

«ምን ማለትህ ነው?»

«ምን ማለትህ ነው? እዚህ ሠፈር ነጻነት የሌለሽ አንቺ ብቻ እንደሆንሽ ማንም ያውቃል»

«ማነው ያለው?»

«ማነው ያለው? የፈለግሽውን የሠፈር ልጅ አስቀመን እንጠይቅ ከፈለገሽ»

«እናቴ ሲኒማ እንደሄድኩ ብትሰማ ትገለኛለች፡፡ ለመማታት ምክንያት ነው የምትፈልገው፣ ጊዜውም የለም፣ ፊልም ደ'ሞ......»

«እናቴ ትገለኛለች?......ግን ዋናው ከወደዱሽ እኮ ነፃ ይለቁሻል፡፡ እንደፈለግሽ ሁኚ ይሉሻል»

«እንኳን ሲኒማ መግባቴን አውቃ ይቅርና በውሐ ፈሰሰ በምናምን ንዝንዟን አልቻልኩትም፡፡ አንተ ይፈቀድልሃል?»

«ውሐ ፈሰሰ ብሎ ነገር......አንቺ አንድ ቀን ደፍረሽ ብታደርጊ......ማለቴ አንቺም እኩል እኝኝ ማለት፡፡ ሁልጊዜ ሠፈር ውስጥ ትኖሪያለሽ እንዴ? አብዮት ጠባቂዎች እንኳን ለጠላ ሠፈር ለቀው ይወጣሉ፡፡ ሁሁሁሁሃ ሃ ሃ ሃ ሃ ሆሆሆሆሆ፡፡ ደስ የምትዪ ልጅ ነሽ ደ'ሞ»

በድንጋጤ ቀና ብላ አየችው፡፡

ከወደታች ሕፃናት፡

153 love story= የፍቅር ታሪክ(እንግሊዘኛ)

154 adventure story= የጀብዱ ታሪክ(እንግሊዘኛ)

*አበባዬ ሆይ!*
*ለምለም!*
*ቁሙ በተራ!*
*ለምለም!*

ነጭናጫ የሚኮሰኩስ ድምፃቸው ሰሚ ጆሮ ውስጥ የዚህ ዓይነት ጭረት የሚፍቅ፡



......ለዓመት በዓል ተብሎ በትዕግስት የሚታለፍ:: ('ይኸቺ ቀን ትለፍ እንጂ ጉሮሮአቸውን በኦፕራሲዮን ነው የምናወጣው' የሚሉ አይጠፉም)

በዝምታ እሷ የእናቷን 'ወራዳነትና' (ዕውቀቱ ባይኖራትም ብቻ አባቷ ሲሳደብ ሰምታ......ይኼም ልጅ እንዴ የታወቀ የሠፈር አራዳ 'ምንም አያመልጠኝም' ባይ ሲያማላት አዳምጣ) ይኼም ወራዳ ባሕርይ በሚገርም ቴክኒክ በላይዋ ላይ በግብዝነቱ የጣለባትን ጭቆና እያሰበች ዓይነት:: እሱም እሷን የገመገመበት ሀሳብ የዓላማውን ዕንብርት መምታት አለመምታቱን ምልክት ፍለጋ ሁለመናዋን በአይኖቹ እያጠናት ብዙ ቆዩ:: ልቧ ይመታል:: ዓይኖቿ ቶሎ ቶሎ ይርገበገባሉ:: ከአበባዬ ሆዬ ጫጫታ ጀርባ የምትጠልቅ ፀሐይ አስደግፎ እንድ የሚያውቁት የሰፈራቸው ተላላፊ የሚፍለቀለቅ ሽንት ይሸናል:: ይኼም ሽንት ከተጣለበት ቅጠላማ ስፍራ የጎጆ ቅርጥ ያለው ጉም ይነሳል:: አንገቷን ደፍታ መሬት መሬት ማየት ጀመረች:: ከመሬቱም ጋር አፍንጫው መላጥ የጀመረውን የልጁን ቆዳ ጫማ ደምራ......

መሬት መሬት እያየች ወደ ቤቷ ለመግባት ተነሳች::

«መሸ» አለች::

«መሸ? ልሸኝሽ:: ምን አስቸኮለሽ ግን?»

«የት ልትሸኘኝ:: ጅቡቲ አልሔድ፣ እዚህ እኮ ነው:: ቤቴን እጄን ዘርግቼ እነካዋለሁ»

«አንቺን የመሰለ አንድ አርምጃ ቢሆንም መሸኘት አለበት»

ተያዩ:: ቀይ ዳማ ፊቱ በሳቅ ለሁለት ተከፈለ:: በየመገናኛቸው አልፎ አልፎ የዳቦ ሊጥ የተሰነቀረባቸው ('የነገውን ዳቦ ዛሬ በላው እንዴ?' የሚያሰኝ) መልካም ጥርሶቹ ታዩ:: ሁለት እጆቹን ሱሪ ኪሶቹ ከቶ በትከሻው እየታከካት አብሯት መጓዝ ጀመረ::

«ቆይማ ከመቼ ወዲህ ነው አንተ.....»

«ከመቼ ወዲህ ነው የወደድኩሽ?» አረፍተ ነገሩን ባልጠበቀችው ከባድ ቃል ጨረሰላት:: በማፈር አንገቷን ደፋች:: ሰው ሁለት ሦስት አንገት ቢኖረው

መልካም ነበር:: አንዱ በእፍረት ሲሰበር በሌላው ይታበያል:: አንዱ ቢታመም በሌላው ቀና ይላል::

«የትናየት ጊዜ አይገባሽም:: ዓይኖችሽ እንዴት እንደሚያምሩ ለመግለፅ ደብዳቤ ልጻፍ ወይስ በሬድዮ ዘፈን ልምረጥልሽ?»

«ዛሬ ሽኚ አልፈልግም»

«ሽኚ አልፈልግም? ግድ የለም:: በልቤ ልሸኝ ብል ማንም አይከለክለኝም»

አተኩራ አየችው::

«ምንድነው የምትፈልገው?» እንደ ፈራችው ዓይኖቿ ውስጥ ይታወቃል

«ምንድነው የምትፈልገው? ጉንጭሽን በእጄ ልንካው? ይፈቀድልኛል?»

አንገቷን ሰበር አድርጋ በከፊል ፊቱን በከፊል መሬት እና የፌዝ ሳቅ ዓይነት:

«ጠዋት ቢሆን ጥሩ ነው:: ፊቴን ማጠብ ሰልችቶኛል» አለች::

«ፊቴን ማጠብ? የፈለግሽውን:: እግርሽንም ቢሆን»

○

አብርሃም (በሡፈር ቅፅል ስሙ 'ቢሮ' 'አብሽ' 'አቢቲ') እስከዛሬ ቆይቶ ቆይቶ 'ወድጄሽ ልሞት ነው' የመሳሰለ የሚያስፈራ ነገር ይለኛል:: ቆንጆ ነሽ ምናምን......ምኑ ቆንጆ ነው? ግን እንዲህ ብሎኝ ባላምነውም አለ አይደለ እውስጤ የሆነች የምትንቀጠቀጥ እረፍት የነሳችኝ መብራት ልበላት ወይስ እሳት ጫረብኝ:: እንዲህ ያለኝ ጊዜ አለ አይደለ እግር ማጠብ ምናምን ቆንጆ ምናምን ሲለኝ......በአፌ አለ አደለ 'ሂድዛ' ምናምን ብዬ አቅልዬ ብናገረውም፣ ነገሩ እልቤ ሽርተት ብሎ ገብቶ ሲከነክነኝ አደረ:: አላመንኩትም:: ግን አባባሉ ልክ እንደ ጉንፋን ቫይረስ ውስጤ ሰርጎ ገባ:: ታዲያ ሳባርረው ልረሳው ባስብ ባስብ ለምን እንደሆነ እንጃ ከበደኝ:: ሳባርረው ደ'ሞ እንደ መንፈስ ብን ብሎ ይሄድና ብን እያለ ተመልሶ ይመጣል......ወዴት እንደበነነ እንኳን አላውቅም:: እንዴት እንደ ተመለሰም አይገባኝም:: ከዛ ደ'ሞ ልቦናዬ ላይ አባባሉ ሙጭጭ ብሎ ቁጭ:: ደስ የሚልና የሚያስፈራ:: የማስበው ደ'ሞ ገላዬን ነው:: አብርሃም ሲታከከኝ ሲያናግረኝ ስለ ገላዬ አስባለሁ:: ስታጠብ ያየሁትን ራቁቴን:: መደለልን እንዲህ የምናፍቃት አልመሰለኝም......መደለል እንዲህ ለጆሮና ለልቦና ምቾት የምትሰጥ አልመሰለኝም:: ከዚህ በፊት በሚጢጢ ድርጊት እንኳን እንደሚወደኝ ያሳየኝ ጊዜ የለም:: ቢኖርም ልበ ቢስ ስለሆንኩ ትዝ አይለኝ ይሆናል:: ሲመስለኝ አብርሃም በብዙ ነገሩ ደስ ይለኛል:: ሲስቅ ደስ ይለኛል:: ቅላቱ ደስ ይለኛል:: ከአብሽ ጋር በማድረግ ላይ ያለሁትን ወይም እሱ በማድረግ ላይ ያለውን ለዚያች ጓደኛዬ ለመንበረ ስነግራት እቀናንባለሁ:: አለ አይደለ 'በላቭ[155] ፈነገለሽ' ምናምን እንዳትለኝ:: አፏ ያስፈራል:: መንገር ፈራሁ:: ግን አንዳንዴ እላታለሁ ለመንበረ:

155 love= ፍቅር(እንግሊዘኛ)

'ቁመቱ.......ቁመቱ'

'አንቺ ምን አለሽ ከቁመቱ?' ትለኛለች::

'ያ ሁሉ አጥንትና ስጋ ከዞማ ቁንጮ ጋር'[156] ሂሂሂ እንላለን

ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ግን አላውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ሳቁን ብቻ አስባለሁ:: ዝም ብሎ ሲስቅ ሲስቅ ሲስቅ:: ፊቴን ትራሴ ውስጥ እቀብርና በትላልቅ ጥርሶቹ ሲስቅ አስበዋለሁ:: አንዳንዴ አጣጥለዋለሁ......ጥርሱን እንኳን አይፍቅም እያልኩ አለ አይደለ በልቤ:: ከዛ ሲስቅ ግን ዐይኖቹ ሲጨፈኑ ልቤ ይነዝርብኝና ፊቴን አዞራለሁ:: ከዕንብርቴ በታች ለስስ ያለ እሳት ይነሳል..... ይህቺ እሳት ድንገት ብታፈተልክ በሚያሳዝንና በሚያሳፍር መልክ ሰደድ ሆና የምታቃጥለኝ ይመስለኛል:: ወሬውን አስቁሜ ትቼው ቤቴ መግባት እፈልጋለሁ:: ራሴን እየገፋፋሁ ያልጨረስኩትን የማድ ቤት ስራ እያሰብኩ እራሴን እየገፋፋሁ አለ አይደለ *ቢሳውን አሳጠብኩትም:: የሽንኩርቱን ልጣጭ አልሰበሰብኩትም:: የቡታውን እሳት ከፍ ካላደረኩት የድንቹ ወጥ ለራት አይደርስልኝም::* የመሳሰለ......እቤት ከገባሁ በኋላ ደ'ሞ የማስበው አብርሃምን ነው:: አለ አይደለ ወሬውን:: ከዛ ራሴን ለምን ትቼው መጣሁ ምናምን እላለሁ:: ከዛ የማስበው እየተጫወተ የነካካኝን ቦታ ነው......እጄ ጋ ምናምን......ጭኔ ጋ ምናምን......ከዛ ሲነካኝ የወረረኝን ነገር:: ልቤ ደጋግሞ እየፈሰሰ ደጋግሞ ሲሰበሰብ ምናምን......

ነፍሴን ያለ እኔ ፈቃድ ጨካኙ ምሽት የሰረቀብኝ ይመስለኛል:: ምሽት ሲያስፈራኝ ደስ ይለኛል:: እንደዚህ ነገር፣ እንደ አብርሃም ነገር:: ታዲያ ቆሜ እያወራሁ ገላዬ ትንሽ ትንሽ እየቆየ ለምን እንደ ሆነ እንጃ ይንዘረዘርብኛል:: አባቴ ይናፍቀኛል:: ገላዬ ሲንዘረዘር አባቴ ይናፍቀኛል:: እፈራለሁ:: ከዚህ መንዘርዘርና ፍርሃት የሚያድነኝ እሱና ወፍራም ድምፁ ብቻ ይመስለኛል:: አባባ ሲመጣ እንዴት ይሆን የምስመው? ከንዱ ላይ ሳርፍና ያላበው ፀጉሩ ፊቴን ሲዳብሰኝ አፈር አፈር ሲሸተኝ......ምናለበት ከእማማ ጋር ባይጨቃጨቁ? እዛ ከአብርሃም ጋር ቆሜ ሳወራ በድንገት ሮጬ የምደበቀበት ነገር እፈልጋለሁ...... አለ አይደለ 'በቃ ነይ' ብሎ አቅፎ ጀርባዬን የሚዳብሰኝ ሰው......እና ትንሽ ሲበርደኝ ሲያንዘረዝረኝ እናቴ ሳትሆን አባቴ ለምን ይናፍቀኛል......

የአብርሃምን ወሬ እወዳለሁ:: የቤት ስራ ጨርሼ የማነበውን አንብቤ ለማረፍ ልጆች ፈልጌ ከሣቢዬ ስወጣ ብዙ ሳይቆይ ይመጣል:: አለ አይደለ ቁጭ ብሎ በቤቱ ቀዳዳ የእኔን ከቤት መውጣት የሚጠብቅ ይመስላል:: ቤቱ እኔ ቤት ፊት ለፊት ነው:: ከመሃላችን በቅርብ የተሰራ ነጭ ጥርጊያ ሰፊ ኮረኮንች መንገድ አለ፣ እሱን ተሻግሮ ነው ያለው:: የማያወራው ነገር የለም:: ወሬ

156 ይሄ አባባል ከኑኑሽ ሙሴ ዘፈን 'አትንቀልቀልብኝ' አልበም 'ጉብል ነው' ከተሰኘው ሶስተኛው ዘፈን ላይ የተወሰደ ግጥም ነው:: ስንኙ ያለበት ሙሉው ግጥም:

*'ወደድኩት አላፍርም ጉብል ነው ጉብል ነው*
*ትልቅ አጥንትና ዞማ ቁንጮ ያለው*
*እኔን እገኝ ብሎ አዎሽ የወደቀው*
*ድማማ እንካልኝ እንካልኝ.....'*

ማውራት ያውቅበታል:: ብዙ ነገር ያወራኛል:: ማት ነገር:: ማት ማት:: ሁሉ ሰው የሚኮራበት የራሱ ፀባይ አለ አይደለ? እና እሱ በጣም የሚኮራበት ፀባዩ ጫት አለመቃሙ ነው:: ጫት አደገኛ ነገር ነው ይለኛል:: *ቬሪ ዳንጀረሽ*[57] ነው ይለኛል:: ለምን አለ አይደለ ብዙ ሰዎች እየቃሙት ምንም ነገር አለመሆናቸው ይገርመኛል ስለው......መስሎሻል አንድ ምሁር ምን ብሏል መሰለሽ ፕሮፌሰር ምናምን በጋዜጣ ወጥቶ ነበር እና ጫት ካቶኒን የተባለ ድራግ አለው ውስጡ:: በተለይ ርጥብ ጫት ውስጥ የሚገኝ:: እየደረቀ ሲሄድ ግን ወደ ሌላ ዐይነት ድራግ ይለወጣል ካቲን ወደ ሚባል:: ካቲን ደሞ ከካቶኒን የበለጠ አደገኛ ነው:: ስለ ሌላ ሌላም ያወራኛል ስለብዙ ነገር:: ማለት ማዶና የተባለች ዘፋኝ እንደ ወለደች እናም የልጇን ፎቶ ከእንግሊዘኛ ጋዜጣ ላይ የቀደደውን እያሳየኝ ......(ልጇ በጨርቅ ስለተጠቀለለ ፊቱ በደንብ አይታይም) አየሽ?......አየሽ? ደስ ይላል አይደል? ይለኝና ማት ነገር ያወራኛል:: አሜሪካ ውስጥ ብዙ ሰው መሳሪያ የታጠቀ ነው:: አታምኚም:: አይከለከልም:: ሾት ገን የተባለ መሳሪያ አላቸው ከካላቺንኮቭ የሚበልጥ:: ብታዪው ይጥማል:: አሁን ቤታቸው ወይም ግቢያቸው ውስጥ ሳታስፈቅጂ ብትገቢ የመግደል መብት አላቸው:: በሙዚቃ ዘ ቤስት አሜሪካኖች ናቸው:: በተለይ ጥቁሮቹ:: ኤምሲ ሃመር ሞቶአል ይባላል:: ማነው እሱ ኤምሲ ሃመር? እለዋለሁ:: የናጠጠ ራፐር:: *ዩ ካንት ታች ዚስ* የተባለ ዘፈን የዘፈነ:: እሱ ነው የዘፈነው እንዴ? እለዋለሁ:: አይሰማኝም:: እንደ መደነስ እያደረገው ይለኛል......ብሬክ ዳንሱ ይገልሻል:: አንቺ ማይክል ጃክሰን ምናምን ነው የምታውቂው:: *ሶልት ኤንድ ፔፐር* የሚባሉ አሉ ደ'ሞ:: ምኖች ናቸው እነሱ? እለዋለሁ:: ዘፋኞች ናቸዋ! አለ አይደለ *ሓይ ጎት ዘ ፓወር የተባለ* ዘፈን የዘፈኑ:: ሴክሲ ናቸው:: ምንድነው ሴክሲ? እለዋለሁ:: ጤይባ እኮ ነሽ:: ጎበዝ ተማሪ ነሽ ትባይ የለም? ምንም አላውቅም ነው? ጨዋ ነኝ ነው? እየሳቀ ይለኛል:: ሲስቅ ደስ እንደሚል ያውቃል:: ግን ከጠይም ከንፈሮቹ ጀርባ በየብብታቸው ካሮትና ሊጥ የወሸመጡ የተስተካከሉ ነጭ ጥርሶች:: እኔ ስለቫለንስና ስለ ሪላቲቪቲ ነዋ እለዋለሁ:: አይከራከረኝም እና አጠፍ ይልና የቱክቶካ አድራሻ ቀይሮ......ሌላ ብዙ ነገር ይለኛል:: አያልቅበትም:: ብዙውን እውነት ወይም ውሸት መሆኑን አላውቅም:: ግን እገረማለሁ:: የዚያ ሁሉ ሰው ስም ሲያዝለትስ:: 'ከገብረአምላክ' አይረዝሙም እንዴ? በእግዛቤር እኔ የወላጆቼና የጎረቤቶቼ ስሞች ረዛዝመውብኛል:: በገመድ እግራቸውን ታስረው ከገደል ወይም ከትልቅ ድልድይ ላይ ስለሚወረወሩ ሰዎች አውርቶኛል:: እግራቸውን በገመድ ታስረው ጃምፕ ያደርጋሉ በቃ:: *ቡንጊ ጃምፒንግ* ይባላል:: አሜሪካ ውስጥ አንዳንድ ቦታ በጣም ብርድ ስለሆነ ብታለቅሺ ዕንባሽ ጉንጭሽ ላይ ወደ በረዶ ይለወጣል:: አያስቦካም? በጣም የሚሞቅ ቦታ አለ ላስቤጋስ የሚባል እዛ ታዲያ ቀዝቃዛ ውሃ በብርጭቆ ቀድተሽ ከቤት ወጥተሽ ወደ ሰማይ ብትወረውሪ መሬት ከመድረሱ በፊት ይተናል:: ብታምኚም ባታምኚም ይተናል አሉ:: ቤት ውስጥ ግን ማቀዝቀዣ አለ::

ሲያወራኝ እንደ ሐይማኖት ሰባኪ በስሜት ነው:: ያለበትን የሚዘነጋ ይመስላል:: አንዳንዴ አምልጦት በልሳን ሳይናገር አይቀርም እላለሁ:: ላላም

157 very dangerous= በጣም አደገኛ(እንግሊዘኛ) ቬሪ ዴንጀረስ ለማለት ፈልጎ::(አ)

ተረረረም ላላላስቤጋስ ሂሂሂ......

እንግዳ እንግዳ ተረቶች ያመጣልኛል......

አንዳንዴ ሲያወራኝ እንዳላወቀ ሆኖ በድንገት ምናምን እጄን ይይዘኛል:: አፍራለሁ፣ ደስም ይለኛል:: እፈራለሁ:: የማላውቀው እንግዳ ስሜት ለመናገር የሚከብድ ነገር በገላዬ ውስጥ ይሯሯጣል አለ አይደለ ትርርርር ምናምን ይልብኛል:: ደ'ሞ እጄ እጁ ውስጥ ያልበዋል:: ያሳፍረኛል:: እያወራኝ ጣቶቼን ይጨምቃቸዋል ምናምን:: በወሬው አዲስነትም ትንሽ ስለምደናገጥ የምስራውና የምናገረው ይጠፋኛል:: በዚህ መሃል ደ'ሞ እዛ አሜሪካ በቅርብ ሄዶ የመጣ ይመስለኛል:: በጣም ሐሩራም ላዝቬጋስ ምናምን አስባለሁ አለ አይደለ ናዝሬት መተሃራ የመሰለ:: አባቴ የመተሃራ ሰው ነው፤ ናዝሬት ነው ያደገው እና ዘመዶቹን ሲጠይቅ እዛ ወስዶኝ ነበር እና ላዝቬጋስ መተሃራ ይመስለኛል:: እና መተሃራ አባቴ ሁለት አጎቶች አሉት እና አንደኛው ብርሃኑ ጃርሶ ነው...... በጣም ቀይ ሰውዬ ዱሮ እዚህ ልደታ ያለው ባልቻ አባ ነፍሶ መለስተኛ ሁለተኛ ያስተምር ነበር:: ሚስቱ ደ'ሞ በጣም ቁመቷ ትንሽ ምናምን በጣም ቆንጆ ነገር ናት:: እሷ እዛ ላስቬጋስ ያለች ይመስለኛል:: መተሃራ የሄድኩ ጊዜ በየቀኑ ሸንኮራ ትገዛልኝ ነበር:: እና ይሞቃል አገሩ:: አቢቲ ላስቬጋስ ላስቬጋስ ሲለኝ በቃ ሂሂሂ መተሃራ ይመስለኛል:: የአጎቴ ሚስት ቆዳዋ ለስላሳ ነበር እና ስስማት ደስ ይለኛል:: ጉንጮቿ ደስ ይላሉ:: አጎቴ መብላት ስለሚወድ ሁልጊዜ ወጥ ወጥ ትሸተኝ ነበር:: ምን ወጥ እንደሆነ አላውቅም ግን ወጥ ወጥ ትሸታለች:: እና ላዝቬጋስ የሚኖሩ ሴቶች ትናንሾች፣ ቆዳቸው ለስላሳ እና ወጥ ወጥ የሚሸቱ ይመስለኛል::. ላዝቬጋስ ጋሪዎች ምናምን ሳይኖሩ አይቀርም ምናልባት በባትሪ የሚሰራ ሞተር ያላቸው እያልኩ ሳስብ:: አሜሪካኖች ኢትዮጵያን ሁሉ ይረዳሉ አለ አይደለ ሶሻሊስት ብንሆንም እና ለእርዳታ እዚህ ከሚመጡት ጋዜጣ ላይ ከማያቸው ወይ የእርዳታ መኪና እየነዱት ከሚያልፉት አንዱ ሰውዬ ምናልባት የላዝቬጋስ ሰው ምናምን ይሆናል:: ደ'ሞ መአት አጫጭር ቀሚስ የለበሱ ልጃገረዶችና አሮጊቶች በመንገድ ዳር ቆመው አይስክሬም ይበላሉ:: ሁልጊዜ አይስክሬም ይበላሉ:: ልጃገረዶቹ ናይል ሆቴል እንደ ሚሰበሰቡት ጅራሬዎች አይደሉም:: አሜሪካን ሴተኛ አዳሪ የለም አይደለ:: ምክንያቱም ምዕራቦች ናቸው:: እና ዲሞክራሲ በዲሞክራሲ ናቸው:: እንዴት ረዣዥም ፎቅና ሸንኮራ አብሮ ይሄዳል እላለሁ በልቤ:: አቢቲ እያወራኝ ለራሴ ይሄን ይሄን እያሰብኩ እስቃለሁ:: በእሱ ወሬ የሳቅሁ ሳይመስለው አይቀርም ግን በጣም አይደለም...... እንደ ሳቅሁ ይታወቀኝና ቶሎ እቆማለሁ:: ግን ወንጂ ስኳር ፋብሪካ የሚሰሩ ሰውዬ ቪዛ አግኝተውና ተፈቅዶላቸው አሜሪካ ቢሄዱ ላዝቬጋስ ምናምን ሸንኮራ ይሸጡ የለ:: እንዲሁ አስባለሁ እንጂ እንደማይሆን አውቃለሁ......ግን ቢሆን ያስቅ የለ......ጦሽ የሚያደርግ ነገር::

ከወሬው መሃል ሳያስጠነቅቀኝ አብርሃም ወገቤን ያቅፈኛል:: ሳላቅቀው ብል ደ'ሞ ከገላዬ ጋር በመርፌ እንደ ተሰፋ መቀነት ይጣበቅብኛል......እንዲተወኝ ብዬ ያሰብኩትን የመተሃራን ነገር ልነግረው ይዳዳኝና እፈራለሁ:: ይታዘበኛል ብዬ:: ሰው ሲያወራ ማዳመጥ ልክ ነገር ነው አይደል? ዐይኖቼን በዐይኖቹ እያየ የሆነ ሚስጢር እንደ ሚያስተላልፍልኝ ሁሉ በዝምታ ያተኩርብኛል:: ያኔ

ደ'ሞ ታዲያ ልቤ ድር ድር ድር:: ለምን ድር ድር እንደምትል እማምላክን አይገባኝም......ማቆም ቢቻል አይደለ እጅን ደረት ውስጥ ሰዶ ምናምን ድር ድር ስትል ያዝ አድርጎ ማስቆም:: እቤቴ ልገባ ስል ክንዱን በትከሻዬ ላይ አምጥቶ በቀስታ በእጁ ጣቶች የግራ ወይ የቀኝ ጡቶቼን ጫፎች ይነካካቸዋል፣ ወይ በድንገት ይስባቸዋል:: አለ አ'ደለ......እግሮቼ ይልፈሰፈሱብኛል ግን ደስ ስለሚለኝ አትንካኝ አልለውም፣ ግን ያሳወቀ እመስላለሁ:: አንዳንዴ ደ'ሞ ወሬው ያደክመኝና ሁለመናዬ ይፈዝብኛል:: ከዛ ይነካካኛል ከዛ ደ'ሞ ወደ አንገቴ ቀርቦ ሹክ ምናምን ይለኛል ግን ሹክ የሚለው አይሰማኝም ጆሮዬ በቁሌት ደንቁሮአል መሰል......በቃ እንደዛ የመሳሰለ:: እቤት ልግባ ብዬ እስብና እረሳዋለሁ ከዛ አስባለሁ ከዛ እረሳዋለሁ ከዛ የሂሳብ አስተማሪዬ ትዝ ትለኛለች:: እግሮቼ ትስስር ምናምን ይሉብኛል:: ስሮቼ ሁሉ ትስስር ምናምን:: እንደ ሽባ ነገር ያደርገኝና መሬት ላይ ቁጭ ማለት እመኛለሁ ነገር:: የሂሳብ አስተማሪዬ ለምን ትዝ ትለኛለች እላለሁ:: የአስተማሪዬ ነገር ሲገርመኝ በዞረበት የጭንቅላቴ ስሌዳ ላይ የፓይታጎራስ ቴረም ፎርሙላ ተሰልፎ:: ምን ያደርጋል ፓይታጎራስ ቀበሌ 01? በምሽት በአቦል ጠጅ የሰከረ ሰው በእዛ በኩል እያለፈ የኮቱን እጀታ በሻፎሌ ያጠበ? ምን ይሰራል እዚህ ባቡር ጣቢያ ፓይታጎራስ? ከምን ያድነኛል? ምንስ ይሰጠኛል?

......አንድ ቀን ማታ ገላዬን ታጥቤ ልብሴን ለውጬ አልጋ ላይ ተቀመጥ ኩና ለመደበር መስኮት ስር ካለች አጭር መደርደሪያ ላይ መፅሐፍ ወስጄ ለማንበብ እንደ ተጋደምኩ ከራስጌዬ ከፍ ብሎ እጄ በሚደርስበት ዕርቀት ብርማ ቀለም የተቀባች ትንሽ ጉርድ የማርያም ሐውልት አየሁ:: አንገቷን ሰበር ያደረገች ማርያም:: ቆይቶ እያነበብኩ እያለሁ በጀርባዬ ተንጋልዬ ግድግዳ ሳይና በሚያባብለኝ ዕንቅልፍ ለመጠረግ ስዘጋጅ ይኸቺን ሐውልት አብርሃም እንደሰጠኝ ትዝ አለኝ:: እንዴት ልብ አላልኩም? ከዛ በቀስታ የተያያዘ ከልጁ ጋር የነበረን የቀድሞ መልክ ያሌለው የመሰለው ግኑኝነታችን፣ ትዝ ባሉኝ ትንንሽ የተከታተሉ ትውስታዎች እየተገነባና መልክ እያበጀ ያደረገልኝ ጥቂት ነገሮች እየታወሱኝ መጡ:: አንድ ጊዜ እንደ ወርቅ የምታብራ ቢጫ የፀጉር ማስያዣ እንደ ሰጠኝ ትዝ ይለኛል:: አንድ ጊዜም ሲኒማ እንድናይ ለእህቱ ለሃና ገንዘብ ሰጧታል:: ምናልባት 'ነፃነትንም ጋብዢልኝ' ብሏት ይሆናል:: በመንገድ ላይ አንዴ ዱርዬዎች አቁመው ሲነጨንጩኝ ከእነሱ ለከፋ ገላግሎኛል:: ምናልባት የማላስታውሳቸው ብዙ ነገሮች አድርጎልኝ እኔ በደደብነቴ አልገባኝም:: ወይ እንደ ሚደብሩኝ የታሪክና የጆግራፊ ትምህርቶቼ ይዘት ርስትስት አድርጌዋለሁ ......

**(የተደነገሩና ያልተደነገሩ)**

ልጁ ስንዱ የምትባል ጓደኛ አለችው:: 'ቢወዳትም' 'ብትወደውም' በመስለቻቸታቸው ስፋት እንደከበበት እየተገፋፉ የመለያየት ባሕር ሊገቡ ፋፉ

ላይ የቆሙ:: የመጀመሪያው ሴት ጓደኛው ናት:: አንዳንዴ በእሱና መልኩ በሚያመጣለት ብዙ የሴት ተስፋ መሃል ይህቺ ስንዱ የምትባል በምቀኝነት እንደ ሽብልቅ ተተክላ የምታደናቅፈው ይመስለዋል:: ስትቀርበው የምታደክመው:: ስትርቀው የሚናፍቃት:: ነገራቸው ተበላሽቶ ቢጣላትና ቢለያያት......'ኩል' የምትባል......እሷን 'እንትን' ለማድረግ መአት የሰፈሩ ጎረምሳ (ት/ቤትና ጎዳና ሳይቆጠር) በየጥሻውና በየቁጥቋጦው ተሸውኮ ብጉሩን እያፈረጠ ጢሙን እየቆጠረ መረቡን ለመጣል እንደተዘጋጀ ያውቃል:: 'ጉረኛው' የሚለው ግርማይ እያለከለኩ ከሚመጡት አንደኛው ነው:: ስንዱን አሁን ቢተዋት እንደ ሁሉአገርሽ[158] ወረራ አድርገውባት 'ነጠቅነው' ብለው ያስወሩበታል:: አለ አይደለ ልጅቷ 'ለመነጠቅ' እንዳልፈለገች:: ከሁሉ ከሁሉ የሴት ጓደኛው የምታበሳጨው ክብርናዋን የትም ጥላው በመምጣቷ ነው:: ይኼም አንድ በማይወደው ሰው--ሽማግሌም ሊሆን ይችላል......ማን ያውቃል በዳንኤል አባት በኢያሱ[159] እንደሆንስ......የተነጠቀው? በተወዳጅነት የተበለጠ ይመስለዋል:: ስንዱ እግሮች መሃል ሲገባና መሰረቱን ወደ አልጣለበት ዓለም እንደ ሰመጠ ሲረዳ ደስታው ይከፈልበታል::

ሀሳቡ ወደዚ'ች ቀዘባ የዞረው ከጥቂት ወራት ወዲህ ነው:: አንድ ቀን በቪዲዮ የውጭ አገር ሲኒማ ሲያይ የፊልሙ እንግሊዘኛ ከግማሽ በላይ ባይገባውም ዋናው ተዋናይ (ዝነኛው መልከመልካም:: ሲሞት ግማሽ አለም ያለቀሰለት፣ አብሮአቸው የሚሰራቸው ሴት አክተሮች ሳይጠይቃቸው የሚያጎነብሱለት፣ ለኮንግረስ የተመረጠና ከአገሩ ፕሬዝዳንት ሚስት ጋር አንሶላ እንደተጋፈፈ የሚጠረጠር፣ ብዙ ብዙ ያደረገ......)......'For virgins I give my life' ብሎ ሲናገር ይሰማል:: ታዲያ የእንግሊዘኛዋን (በእንግሊዘኛ ሲኒማ ውስጥ ያያቸውና የሰማቸው ጉዳዮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ዕውነት እንደሆኑ ያምናል) ዐረፍተነገር ከሰማ ወዲህ የግል ተምኔቱ እዚያ ዙሪያ ተገነባ:: በድንግላት የተሞላ ምድር ላይ ራቁቱን መንፈላሰስ የቀን ሕልሙ ሆነ:: ከሰፈሩ ውስጥ የሚያውቃት 'ጋለሞታ' መሆኗ ያልተሰማ ወይም በቀላል ቋንቋ 'ያልጀመረች'______ብቻ ናት:: ግን የእሷን ዓይነት መልከቀና በእናቷ አንደበትና በአባቷ ጡንቻ የተጋረደች፣ በእጅ ማስገባት ከባድ ነው:: የጠበሳው ኪነቱ ሳይሆን ያቃተው፣ መድረሻና መነሻዋ ጥብቅ ልጓም የተፈተለባት እንደ ልብ የማትገኝ በመሆኗ ነው:: ከት/ቤት ማድ ቤት፣ ከማድ ቤት ት/ቤት ናት:: ከመሃል ቀልቦ ማስቀረት ተመኘ:: ምን እንደደረሰባት ከማወቋ በፊት ክብርናዋን መዳፉ መሃል እንደ ጠብታ ሊይዝ......

'ድንግል' የሚባለው ነገር ሁልጊዜ ለዐይን የሚከሰት 'ያልጀመሩ' ወጣት ልጃገረዶች እግሮቻቸው መሃል ተሸከመው የሚዞሩት ለጋ ቅቤ ውስጥ እንደተነከረ

---

158 መተረቻ የሆነች የታወቀች የሰፈር ሂያጅ ('ምነው እስከዚህ ሁሉአገርሽን አደረግሽኝ እንዴ?' እንድትል የነቃች ጨዋ ወይም ጨዋ መሳይ ኮረዳ--የሚተዋወቁ ጎረምሶች ቅብብል ሊያወጧት ሲሉ::

159 የሰፈሩ የታወቀ ወጣት አባባጊ. አዛውንት ኮረዶቹ 'ስዊት ዳዲ'/sweet daddy የሚሉት ምንም ማድረግ የተሳነው ወላጅ ደሞ «ያ! እፍረተ-ቢስ» የሚለው፣ በቅናት የበገኑ ጎረምሶች ደ'ሞ 'ያ ብረታብረት፣ ያ ሕንፃ ኮንስትራክሽን' የሚሉት......በሙሉ ጥርሶቹ/ ከስምንቱ የፊት ጥርሶቹ በስተቀር/ ረግፈው ሜርኩሪና ሰብነበረድ የተሞሉ:: የሴቶቹ መከራከሪያ ተረብ እንዲህ ነው: *'ከአንድ ብጉራም ቺስታ፣ የቢፊ ደላጋር አሮስቶና ፓስታ'*

ሁሉ የሚያብለጨልጭ ደቃቃ ድቡልቡል የክትፎ ስጋ ይመስለዋል:: ይኼም ቀን ያለ ዕለት በዕድለኛ ወይ በደፋር ወንዶች ጣልቃ ገብነት በየአልጋው ላይ፣ በመንገዱና በየወንዙ ዳር የሚጣል:: ይህን ድቡልቡሌ ነገር—በደምና በጅማት ዕድሞ ውስጥ የተጀነለ ሳትጠብቅ ሳትጠረጥር ማውለቅ አለበት......

የእናቷንና የአባቷን የመከላከያ ግርዶሽ የሠፈር ልጅ ስለሆነ እንደ ወንድም ተመስሎ በቀላሉ ሸውዶ ቢያልፈውም፣ ችግር የሚመጣው እሷ የአካሄዱን ቅኔ አሳስታ ተርጉማ እንደ ወንድሟ ከቆጠረችው ነው:: በተሰላ አጋጣሚ 'እወድሻለሁ' ብሎ ከመናገሩ በፊት ከእሷ ጋር ምን ዓይነት ግኑኝነት እንደ ነበራቸው አስታውሶ......ይኼንንም ግኑኝነት በትንሹ ከልሶ ለዛሬ ፍትወቱ ሊጠቀምበት አቀደ:: ተልካሻ የግኑኝነት ምልክት ቢሆንም ይቀራረቡ እንደ ነበር የሚጠቁም፣ የሚመሰክር:: የአሁኑ ፍሬንድነታቸውን[160] በማጉያ መነፅር በልምምጦሽ እንኳን ቢሆን የሚያሳይ:: ልፍስፍስ እንኳን ቢሆን እንደ ምስክር የሚቆጠር......

አንድ ገጠመኝ አለችው—አንድ የመነፊግ ታሪኩ ውስጥ ተዳብላ የተቀመጠች ደቃቃ ምዕራፍ:: በቸልታና በበቀል የተንከባከባትና ያልተረሳች የምታቃጥለው ሚጥሚጣ ታሪክ:: ከእሷ የሚመዘዝ ሰበዝ አለ:: ስህን አንድ ክፍል የሚማሩ 'የጨዋዎች ጨዋ' የምትባል ልጅ ናት:: ፊቱ የምትቀመጥ:: 'የሕንድ' የመሰለ ረዥም ፀጉር ሲኖራት ወደ ኋላዋ ትሰበስበውና እንደ ኳስ ጠቅልላ ከማጅራቷ ከፍ አድርጋ በትልቅ ፀጉር ማስያዣ ታስረዋለች:: ታምራለች ግን ማማሯን አትሰጥም:: ጠዋትና ማታ ከኋላዋ ተቀምጦ ይኼን የተጠቀለለ ንፁሕ የሚፈልቅ የፀጉር ኳስ ሲያየው ይሰለቸዋል፤ የእሷም አማምሮ ነፋጊነት ያበሳጨዋል:: እና ይተርባታል:

«እዚህ ውስጥ ምን ደብቀሻል? ድቡልቡል ጎመን ምናምን?»

«ምን አገባህ?» ትለዋለች ዞር ብላ:: ዓይኖቿ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ዙሪያቸውን ንቀት ይነበባል:: በደም ስሮቿ የፃፈችው የሆነ 'አፍህን ዝጋ' የመሰለ ነገር አለ:: እሷን መልሶ ለማበሳጨት የፀጉር ማስያዣዋን ከፀጉሯ ኳስ ውስጥ መዞ ይወስዳል::

«ሌባ:: ከዱርዬ ጋር ምን አጨቃጨቀኝ ሌላ አልገዛ መሰለህ?» ትለዋለች::

«ዱርዬ? ስምሽ ማነው? ስህን ነው? ሳህን?» አላት ሊያበሽቃት::

«ያማረብህ መስሎሃል»

ቆራጥ ሴት ይጠላል:: እንማርበት የሚሉ፣ ፍቅር ምናምን ምናምን...... ከአስቴር አወቀ ካሴት ተጣብቀው ያን የመሰለ ነገር የሚያልሙ:: የሆነ ደካካ የሆነ ጅንኑ የሆነ ደባሪ የሆነ ጎፈሪያም ከጎጆ ቤት እየተንቀራፈፈ የሚወጣ እጆ ጠባቡ የተተረተረበት ምናምን የሚማርካቸው ደሙን ያፈሉታል:: ተነስታ ስትቆም ቂጧ ሳይደርስ ቡፍ ብሎ ወገቧ የቀረው የሚታቀፍ ያህል የሰፋ ፀጉሯ......ደጋግሞ ያበሽቀዋል:: የእሱ ያልሆነ ቁንጅና ይጠላል:: ተነስታ ስትቆም በሰፊ ቀሚሷ ስር የሚዋልለው፣ ቢነክሰው፣ ቢይዘው የሚመኘው ቂጥ......ይሄም የሚፋጅ ነገር (ይመስለዋል) ከእሱ እየራቀ ሲሄድ......ዴስኩ ላይ ደ'ሞ የተዘረረ ቢያቃጥለው

160 ጓደኝነታቸውን (እንግሊዘኛ)(አ)

የሚመኝ የማይገባው የእንግሊዘኛ መፅሐፍ፡ The time machine......ሊያበሽቃት ይጠራታል፡

«ታዲያስ ስህን ማሺን! ሰሃን መስሪያ ማሽን! የቻይና ነሽ ምንድነሽ?» በማያውቀው ባላየው ወንድ ይቀናል ወይስ ወንዶች?

ትዝ ይለዋል የዛን ሰሞን______ን መንገድ ላይ ያገኛታል፡፡ የሆነ ቀን ከሰዐት በኋላ፡፡ እሱ ወደ ጓደኞቹ ሲሄድ እሷ ከሱቅ ስኳር ገዝታ ስትመጣ፡፡ ቀትሩ ስላማረረው ጃኬቱን ትከሻው ላይ ጣል አድርጓል፡፡ ቆሞ ሊያዋራት ይፈልጋል፡፡ 'እቸኩላለሁ' ትለዋለች፡፡

እሀቱን አይታት እንደሆነ ይጠይቃታል፡፡ መቼም ሌላ አላወራትም፡፡

«እንጃ......» ትለዋለች ወይም እንደዛ የመሰለ......የተሸከመውን ጃኬት ወደሌላ ትከሻው ሲቀይር፣ ሲያመቻች......በትክክል ባያስታውስም......ወርቅ የመሰለች ግን ያልሆነች የስህን ፀጉር ማስያዣ ከኪሱ ትወድቃለች፡፡ ያነሳታል፡፡

«የምታምር ፀጉር ማስያዣ ናት» ትለዋለች፡፡ ይሰጣታል፡፡ ማንም ልትሆን ትችል ነበር፡፡ ግን ይኼን ገጠመኝ ሊገለገልበት ይችላል......

አጠገቡ......

አንድ ግድግዳ ዘሎ አንድ አጥር ዘሎ......

የፅድ ዛፎች ወሰን አልፎ የዳማ ከሴ ሽምጥ፣ የምድር አውጥና የችፍርግ እንቅፋት፣ የሰንሰል ጎፈሬ አልፎ......የሆነች ልጅ ጣእስ የመሰለች ዞሮባት ተጣጥፋ ተኝታለች፡፡ በራ ለመውጣት ትከሻዎቿ ላይ ያሉት የኮረዳነት ስጋ ከንፎቿ ይርገበገባሉ፡፡ የዕድሜ ነፋስ ላባዋን አሁንም አሁንም እየገለበ መንደድ የጀመረ ሴትነቷን ያሳያል......አደናቃፊ ንቃት ውስጥ ሳትገባ ትንሽ የተረት ጉጆ ሠርቶ–ሞቅ ያለች......ድንቅ የወሬ ላባ (ላባን በላባ) ደልድሎላት እሱ ወደ አዘጋጀላት ቅርንጫፍ እንድታርፍ ይፈልጋል......የጆፌ ክንፉን ዘርግቶ ጀርባዋ ላይ ቆሞ ይቀነፋል......

ብልህ ሴት ፍቅር ትፈትሻለች፣ ትሰልላለች ከዚያ ካልመሰላት 'ሱሚ!' ትላለች፡፡ ሳትሆን ሳትመረምር 'ብልጥ ነሽ' ተብላ፣ በመባሏ ብቻ 'የነቃች' የመሰላት ኮረዳ ቀላል ናት፡፡ ድርጊቷ ሁሉ ብልጥ ይመስላታል፡፡ የነፃነትን ነገር አሰማምሮ ማሳየት ነው......የትም ስለማይገኝ ብዙ ስለሚወራለት 'ነፃነት' መስበክ ነው፡፡ «ነፃነትን ማወቅ ነው» ብሎ መዘብዘብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር አስታኮ ትንፋሽ የማይሰጥ የድለላ ባሕር እየነከረ ያወጣታል፡፡ በድለላ እግሯን ያላነሳች ሴት ማን ናት? ለመደለል አፋቸውን ከፍተው የሚጠብቁ በዚህም የፈለገውን የአባላዘር በሽታ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ ሴቶች ስንት ይሆኑ?......

«አወይ ዐይን፣ አወይ ፀጉር፣ አወይ እግር፣ አንቺ ውብ ነሽ ማንም ይፈልግሻል» ሊላት......

«ትንሽ አዞርሽብኝ» ሊላት፡፡ ከዚያም፡

«እንኳን ሰው ከሰማይ አሞራ ሲያይሽ ይውላል»(ይኼንን ፊልም ላይ ባያየውም ከጠቀመ ምናለበት? ከነፃነት ይልቅ ብልግና አለም አቀፋዊ አይደለች?

*ሓሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ፣ የ___ነሽ እያለ፣ የ___ነሽ እያለ፣ የ___ነሽ እያለ፡ ሓሞራ ከሰማይ ሲያይሽ ዋለ። የጩዋ ነኝ ባይ ሕብረተሰብ የቋንቋ ጅጊ? ያገሩ አዝማሪ በጠጅና በጠላ ዞሮበት ያቀናበረለት)*

እሱ በከተባት ሞራል አብጣ ሻሞ እንዳትገባበት ቢቻል ስሟን ሊያጠፋፋ፣

('አንዱ እንዲህ ከጣመኝ ሰላሳዎቹስ?' እንዳትል)

('ለአንዱ እንዲህ ከጣምኩት ለሰላሳዎቹስ?' እንዳትል)

ወንዶች እንዲፈሯት በሚያደርግ ስድብ ሊከባት፣ መንገዶች ሁሉ ወደ እሱ እንዲያመጧት። ሊያገላት። በብቸኝነት ሊያጮላት፡

«እናትሽ የምትወድሽ ይመስልሻል? አጠቃላይ አባባል ነው። እናቶች እንደውም በልጆቻቸው ይቀናሉ» ብሎ ሊላት። ከዘር ማንዘሯ ሊያጣላት።

«የሰማይ የምድር እንስት በአንቺ ይቀናል» ሊላት

የለበሰችው ባዘቶ መሆን መጀመሩን፣ ጥፍሯ የጉድፍ ሻንጣ መሆኑን፣ ፊቷ እንደራብተኛ የቀጠነ መሆኑን፣ ሰውነቷ ሽቦ መምሰሉን፣ ጆሮዋ ትልቅ መሆኑን ሳይነግራት……የጥርሷ አይበሉባ የበጨጨ፣ ከጉንጉኗ ስር የፎረፎር ገለባ እንደተኛ፣ ት/ቤቷን ምስጥ እየናደው እንደሆነ ሳይነግራት……ያልሰለጠነው ኋላ የቀረነው፣ ከአፍሪካም ከአለምም የተጎተትነው፣ ራፕ የማንደንሰው፣ ማዶናን የማናፈቅረው፣ ቡንጊ ጃምፕ የማናደርገው፣ መተሃራን ወደ ላስቬጋስ መለወጥ ያልቻልነው ነፃነት ስለምንፈራ ነው ሊላት……

ሊያስከራት ፈለገ። ሊያደናቁራት።

*……ቂሎች ይጋለባሉ ከመሀሬ……*[161]
*……ኮርቻውንም ይሰራሉ……*

○

እግዛቤርዬ! በሚያስፈራ ማታ……ማታ……በቃ ማታ……ጭልምልም ብሎ ነገር……ድብን ምናምን ዓይነት ሳይሆን በቃ ጨልሞ። የማይፈሩ ይኖራሉ እኔ ግን ጨለማ ያስፈራኛል። አብርሃም ደረቅ አደለ ደ'ሞ ወንድ ነው ለምን ይፈራል……አለ አደለ በድርቅና ካላየሁሽ ሆዴን ምናምን ያመኛል ራሴን ይፈልጠኛል የመሳሰለ ነገር ብሎ ቤቴ ይመጣል። ድርቅ ብሎ። ወላ አንድ ቀን እንደዚህ ዋናው ቤታችንና ሰርቪስ ቤታችን የተያያዙ አይደሉም እና ስለዚህ ያው መሃላቸው ክፍተት ነገር አለ አይደለ በቃ ወደ ማድ ቤት ስሄድ ጨለማ ውስጥ ቆሞ ትንንሽ ይታያል በማድቤቱ መብራት ግን አለ አይደለ በደንብ አይታይም ወላ አቦ ቀልቤን ግፍፍ አደረገው። ምነው ምናምን ስለው ሂሂሂሂ በቃ መተኛት ምናምን አልቻልኩም ጥናት እምቢ አለኝ ምናምን……

አያጠናም እኮ……

ወላ አውሪኝ ምናምን አለኝ ወይኔ እማማ ብታይስ ምናምን ስለው ተይ በእናትሽ ምክንያት ምናምን ፍጠሪና አለ አይደለ እዚህ ትንሽ እንቆይ ብሎ

161 ቶማስ ደበላ ቆንጆን አስቀያሚ የማድረግ አንዳንድ ጥበቦች (የቀልድ ወጎች) አአ ሹም አታሚዎች 1967

ስደናበር ሳብ አደረገኝና አፌ ላይ እምምም ምናምን አደረገኝ......ወላ ምንድነው ብዬ ስፈራገጥ አለ አይደለ ደበረኝ ነገር በቃ ዝምብሎ ሲጠብቀኝ ሮጬ ቤት ገባሁና ከአንድ ሰዓት በኋላ ስመለስ ቆሞ አገኘሁት ግን እናቴን ስለፈራሁ መቆየት አልቻልኩም በቃ ሳመኝ ብዙ......ወላ ልብሴን ሊያወልቅ ሁሉ ደስ አይልም ብዬ እየተነጫነጭኩ ተውኩት:: ግን በቃ ቅፍፍ ብሎኝ ነበር እናቴ ከተኛችበት ነቅታ አልጋዬ ላይ እንዳለሌለሁ ብታይና ብትወጣስ...... በጣም ፈርቼ ነበር እና ደ'ሞ ቀሚሴን እየገለበ እያስበረደኝ እሱ ሲገልበኝ እኔ ስመልስ እሱ ሲገልብ እኔ ስመልስ በቃ ተነጫነጭን......ብትወጂ'ኝ ኖሮ እንዲህ አትፈሪም ነበር ምናምን ይለኛል...... ወላ አቦ እኔ በብርድ ብዙ ጊዜ ተሰቃይቼአለሁ የቂጥ ብርድ ይወድላታል አሉት እንዴ......እናቴን ከኋላ ጥፍር አድርጎ ይዞ ፀጉሬን ሁሉ ሊነጭ ምናምን...... ፀጉሬን ላባ ምናምን አደረገው እንዴ? እላለሁ ለራሴ......ሲስመኝ መሳም እንደዛ ነው እንዴ? በቃ ማምለጥ አልቻልኩም......እና ደ'ሞ እንዴት ልተንፍስ...... ስተነፍስ የእሱን ትንፋሽ ነው የምተነፍሰው ዝም ስል ደ'ሞ ታፍኜ ልሞት እና ደ'ሞ ምራቁ እያስጠላኝ ከአፌ ላይ እጠርጋለሁ ምናምን:: ይስመኛል እያስጠላኝ እጠርጋለሁ ታዲያ እሱ ደ'ሞ ዋና ምናምን መልመድ ይመስላል ይለኛል:: ከዚያ ይሸውደኛል አለ አይደለ ጡቶቼን ሲነካካኝ እሱን ሳስለቅቀው ሳላስበው ግጥም ያደርገኝና አፌና አፌ ዙሪያ ያለውን የፊቴን መዓት ፐርሰንቴጅ[162] ቦታ በእርጥበት ይቀባብኛል:: እዛ ስከላከል ደ'ሞ ያኔውኑ ዞር አድርጎ ጡቶቼን ይነካካቸዋል ምናምን:: በቃ ዞረብኝ:: መንበርዬ ስታወራኝ የነበረው ይኼ ይሆናል:: አልሮጥ ነገር:: ምክንያቱም ያስፈራኛል......ደ'ሞ ደስ ይለኛል:: ለሁለት ተሰነጠቅሁ:: አለ አይደለ ትልቅ ድንች በቢላ ብንከፍለው በግራ አንድ ግማሽ.....በቀኝ አንድ ግማሽ ይሆናሉ:: እንደዛ:: መሃላቸው ነጭ ወይ ቤዥ ነገር:: ብቻ እንደዛ:: ፊቴን አንገቴ ውስጥ ቀብሬ ከደረቴ ጥብቅ ብዬ በሚቃጠሉ ጆሮዎቼ በውስጥ ባቴ ላይ እንደ ዕንባ የሚወርድ ወለላ ነገር አዳምጣለሁ......

አንድ ቀን ተቀምጬ ሳጠና......ሌላ ምን ላድርግ? እናቴ ለብስኩት ማስቀመጫነት ያገለግል የነበረ አንድ ያረጀ የቆርቆሮ አገልግል ወደተቀመጥኩበት ሳሎን ይዛ መጣች:: ጠረጴዛው ዘንድ ከእኔ ፊት ለፊት እንደኛውን የእንጨት ወንበር ስባ ተቀመጠችና አየችኝ:: አለ አይደለ 'ምን ትሰሪያለሽ እዚህ?' ምናምን ዐይነት የምትል ይመስላል:: የሚያነብ ለመምሰል ብቻ ዓይኖቼን ወደ ደብተሬ ወረወርኩ:: ደብተሬ ከአንድ ሰዓት በላይ ምናምን ይሆናል ተዘርግቷል ግን ከአንድ ገፅ የበለጠ አላነበብኩም:: ልቤ ይሸፍትብኛል ሌላ ሌላ ያስብብኛል በቃ ስድ ስድ ነገር:: ማተኮር አለመቻሌ ያስፈራኛል አለ አይደለ......በዚህ ከቀጠልኩ ፈተና ማለፌንም እንጃ:: መውደቅ ምናምን ሳይሆን አለ አይደለ ከአምስተኛ ወይም ከሦስተኛ በታች መውጣት የሆነ ይደብራል አይደል:: እኔን እየገላመጠች እናቴ ቆርቆሮውን ከፈተችው:: ወብቋታል መሰል:: እሱስ የሚወብቅ ቀን ነው ት/ቤት እያለሁ ያውም የጠዋት ሺፍት......ክፍል መስኮቱ ጋ ለመቀመጥ ሁላችን ስንሻማ ነበር:: ማዘር በቆርቆሮው እፊያ ፊቷን አራገበችና ወደ ጉን አስቀመጠችው:: እጇን ወደ ቆርቆሮ ውስጥ ለማስገባት እየቃጣች ቀና አለችና ኮስተር ብላ:

«ምን ታይኛለሽ? ደብተርሽን አታነቢም?» አለችኝ::

162 መቶኛ(እንግሊዘኛ)(አ)

አጎነበስኩ::

'ነጭናጫ' እያልኩ በልቤ:: ትንንሽ ዕቃዎች ማውጣት ጀመረች::

በተከፋፈለ ልብ ሳነብ ቆየሁና ቀና አልኩ:: ያ ሁሉ ቁሳቁስ እዚህች ቆርቆሮ ውስጥ የተቀመጠ አይመስልም: ሹራብ ያልተሰራበት የተጠቀለለ ክር፣ የዳንቴል ሽቦ፣ ትናንሽ የመድሐኒት የመሰሉ ብልቃጦች፣ እንትፍጣፊ ቂጡ ስር ውሃ የመሰለ ነገር የሚዋልል የሽቶ ብልቃጥ፣ ያረጀ ጥብጣቡ መበታተን የጀመረ ካሴት፣ የጥፍር መቁረጫ፣ ኩክ ማውጫ፣ መቀስ ብዙ ብዙ......

«ይሔን ሽቶ አልማዝ ነበረች የሰጠችኝ» አለች::

እንዳታዪ እያለችኝ ምን መልሳ ታወራኛለች?

«ባዶውን ብልቃጥ ነው እንዴ ያስቀመጥሽው?» ልፎትታት ነበር::

«ሞት ነው የወሰደብኝ እንጂ ትልቅ ጊደኛዬ ነበረች:: ማስታወሻ ነው:: ሁሉ ነገር መጥቀም የለበትም አየሽ:: እሷ ብትኖር እንዲህ አልሆንም ነበር»

«ምን ሆንሽ?»

«'ትምህርትሽን ቀጥይ ዲፕሎማም ቢሆን አታቁሚ' ብላኝ እኔ ቀሽም አይደለሁ......አቆምኩ:: ለሁሉ ነገር መካሪ ያስፈልጋል:: መካሪ ቢኖር የሚሰማ ተገኝቶ ነው? አትዪኝም»

አልገባኝም:: አብራርታ አልመለሰችልኝም::

ማንበብ ቀጠልኩ......የት እንዳቆምኩ ስለ ረሳሁ ያነበብኩትን እየደገምኩ ወይ ካላቆምኩበት እየጀመርኩ......

ኢቢቲ በእጁ ጎኔን አጥብቆ የያዘኝ ዕለት......ሲስመኝ......አሁንም አንዳንዴ ጎን አጥንቴ ያለበት የለም ከሽንጤ አጠገብ ስሙ ምንድነው የሚባለው? እሱ ጋ ይጠዘጥዘኛል:: መሳሳም ሲጀመር ያስፈራል እንጂ ትንሽ ከለመዱት ከማንበብ የተሻለ ነገር አለው:: ቀላል ነው:: ስራዬ መሳም ብቻ ቢሆን መልካም ሳይሆን አይቀርም ሂሂሂ:: የተክል ቅጠሎች የጎድን እንጨት አላቸው ልክ እንደ ጎድን አጥንት......ይኼ ቃል ባዮሎጂ ደብተሬ ውስጥ ያለው አስተማሪው 'አስምሩበት' ያለን ለምን ይሆን? ስቶማታ[163] ስቶማታ......የሆነ ቅጠል ላይ ያለ አየር መቀበያ ቀዳዳ:: ቀዳዳ ቀላል ነገር ይመስላል:: ሁሉ ነገር ወደዚች ዓለም ሲወረወር በቀዳዳ በኩል ነው፣ አልቆለት ሲሄድ መሬት ቀዳዳ ገብቶ ነው:: አይገርምም? ከቀዳዳ ወደ ቀዳዳ:: ብዙ አልተኬደም እኮ! 'አልሸሹም ዞር አሉ' የሚሉት ዓይነት:: አትክልቶች ቀን ካርቦን ዳይኦክሳይድ ይስቡና ኦክሲጂን ያስወጣሉ፤ ማታ ማታ ደ'ሞ ኦክሲጂን ይመጡና ካርቦን ዳይኦክሳይድ ያስወጣሉ:: አስገራሚ ቀዳዳ:: እናቴን ቀና እያልኩ እያታለሁ ወሬ ፈልጌአለሁ ከዚህ ከስቶማታ፣ ከጎመንና ከቅጠላቅጠል ብታድነኝ:: ትናንሽ መርፌዎች የተሰኩበት ሚጢጢ ትራስ ነገር አወጣች:: አብርሃም የሰጠኝን የመሰለ ፀጉር ማስያዣ(ግን ጥቁር) ከመርፌዎቹ ጋር አብሮ አለ:: ምን ያደርግላታል እዚያ ውስጥ? ፊቷ ያተኮረ ይመስላል:: አብርሃም የሰጠኝን ማስያዣ የት ጣልኩት? አልጋ ስር ይሆናል:: የፀጉር ማስያዣዎቼ

163 stomata= (እንግሊዘኛ)(እ)

ሁልጊዜ ተኝቼ ይረግፋሉ::

ያልመሰጠኝን ንባቤን ቀጠልኩ::

ከንፈሯን ስትመጥ ሰማኋት:: ቀና ስል ተያየን:: ዐይኖቿ እንባ አቅርረዋል:: (ለምን ተደብቃ አታደርገውም? ምን ይጠበስ ነው?) በእጆቿ ሁለት ብርማ ቀለም ያላቸው ሳንቲሞች ይዛለች:: እያገላበጠች ታያቸዋለች::

«እነዚህን ሽልንጎች አየሻቸው?»

«ሽልንግ? የየት አገር ሽልንግ ነው?»

«የኢትዮጵያ»

«እንዲህ አይነት ሽልንግ ነበረ?» ከእጇ ተቀበልኳት......እና ሲከብድ:: 'እንዴ? እንዴት ይከብዳል' ምናምን ልላት ስል አቋርጣኝ ታሪክ መናገር ጀመረች::

«ድሮ ነበር ደጉ ጊዜ:: እኔ እንኳን አልደረስኩበትም»

ብዙ ታሪክ ታወራኛለች ብዬ ጠብቄ ነበር:: ደስ የሚል ቅዝቃዜ አለው:: ንፁሕ ነው:: አንዳንድ ቦታ ጥቋቁር የቆሻሻ ሰንበሮች አሉበት:: መዳፍ መሃል የሚሰማ ደስ የሚል ክብደት አለው:: የአሁኑን አስር ሳንቲም ይመስላል ግን ይከብዳል ደ'ሞ ይሰፋል ከዚያ ጠየቅኋት ወሬ ፈልጌ ምክንያቱም ሁሉ ነገር ሰለቸኝ:: ከንፈርን ከተሳሙ በኋላ የቀረው የሕይወት ነገር ይሰለቻል መሰለኝ......

«ከየት አገኘሽው?»

(ከየትም ብታገኚው ግድ የለኝም......ማንበብ ሰልችቶኝ ላዋራሽ ነው)

«ከአባትሽ ጋር ተጋብተን አንቺን ስወልድ እናቴ ለማስታወሻ የሰጡኝ ናት»

«ይወዱሽ ነበር?»

(ምንሽን ወደዱት? ነጭናጫ!)

«ወተት እኮ ናቸው......ከአባትሽ ጋርም እንዳሁኑ ሳይሆን ድሮ ዕብድ ነበርን:: ደስ ሲል ለምንም ለምንም ፍቅር ጥሩ ነው»

«ለምን ሰጡሽ?»

«ይሼ እኮ ብር ነው 'አቅልጠሽ ጌጥ ይሆናል' ብለው ሰጡኝ:: እኔ ግን አማቼን እወዳቸዋለሁ:: አቅልጬ ሐብል፣ ቀለበት ባሰራው አየሽ......ትዝ የሚለኝ ያንጥረኛው ጥበብ ነው:: ምናልባት ባይሞቱ አሰራው ነበር:: ግን ሞቱ:: ነፍሳቸውን ይማርና::......እንዲሁ እንዳለ ማስታወሻ ይቀመጥ»

(ወግ አይቀርም)

ዕንባ በጉንጮቿ ላይ ወረደ:: ሁለት አተር የሚያካክሉ ዘለላዎች:: የምታሾፍ መሰለኝ:: ዐይኖቿን ጠራርጋ ሳጥኗን ስትበረብር ቆየችና:

«ድሮ ማርትሬዛ የሚባል ገንዘብ ነበር:: አልሰማሽም?»

«በእሁድ ፕሮግራም በራዲዮ አንድ ጊዜ ሰምቻለሁ»

«ጥቂት ማርትሬዛም ነበራቸው አያትሽ......ስርግ ደገሱበት:: ድል ያለ:: የደሐ አይመስልም......'ልጄን ለልጄ ዳርኩት' ይሉ ነበር»

(አሁን በልጅነቴ አቀማጥይኝ እንድወድሽ)

«ይኸቺን ነገር እስከሞት አላጠፉትም......ብሞት ከሳጥኔ ጋር አብራችሁ ቅበሯት......»

(ምነው እማማ አልበዛም?)

ለሌላ ለቅሶ ፊቷን ታዘጋጃለች:: ትንሽ ዘለባብዳነት አይሆንም ከአባቴ ጋር እየተሰዳደበች......ስለ ፍቅር ምናምን የምታወራው?

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ደብተሬን አልጋዬ ላይ ጥዬ ከሳሎን አንድ መፅሐፍ ይዤ ወደ ውጭ ወጣሁ:: ግቢያችን ውስጥ የበቀሉት ፅዶች ጥላ ስር ተቀምጬ ማንበብ ጀመርኩ:: የማይለቀቅ የትርጉም መፅሐፍ ነበር:: ኬን ፎሌት ምናምን የምትባል ሴትዮ የፃፈችው......ኬን የሴት ስም አይደለም እንዴ?

*(ሰመመን ሰመመን ሰመመን)*

ከመተኛቷ ቀድሞም ይሁን ተኝታ በሕልሟ የምታስብበት አንድ ጉዳይ ልጁ ሰጥቶአታል:: አንድ ሰው የሆነ ሌላ ሰው ቢቻል ተቃራኒ ፆታ ባይወድም መጠጋት አለበት:: ጥንትም እንደዚያ ነው:: የተፈጥሮ ነገር አይደለ:: ሰው ያለ ሰው አይኖርም:: ታዲያ ዛሬ በምን ተደርሶ ትከለከላለች?______ ከማንም የበለጠ እንደሚቀርባት ለማሳየት 'በእናትሽ' ብሎ በቲያትራዊ መንሰፍሰፍ የማያነበውን መፃሐፍ እንኳን ይዋሳታል::

'እንዴት ነው መፅሐፉ?' ስትለው::

በጅምላ አባባል እየሸወደ ያልፋታል:

'......ግሩም ነው'

'......ዋናው ባለታሪክ የሚገርመኝ አይነት ሰው ነው'

'......አንድ ፊልም ላይ ያየሁትን ታሪክ ይመስላል'

አንዳንዴ እንዳላነበበው ብትጠረጥርም......ብዙ ሰዎች ስለሚያውቅና ብዙ መፃሕፍት መዋስ ስለሚችል......ባይዋስም የመግዛት አቅም ስላለው...... ሰለሚያደንቃትም 'አትዋሸኝ' ብላ ልታርቀው አልፈለገችም ደ'ሞስ መሳሳሙስ? የልጁ ሱስ እንደ ወሬው የንባብ ሳይሆን የፊልም ነው:: እሱ ራሱ አንዳንዴ የትኛው እንደ ቀደመ ይዞርበታል: መረጃው ወይስ ምኞቱ? ፊልሙ ወይስ ምኞቱ? ምናልባት ሲከርም ያው ፊልሙ ይረሳል የስሜቱ ጌታ ፈጣሪና አሳዳጊ እሱ ራሱ እንደ ነበረ በሰፈራቸው ወይ በከተማዋ መፅሐፊ ንህምያና ትንቢተ ቀባጢሶ በተገኘው ሱራ ያስመዘግባል::

እናቷ ዘውዲቱ ልጇን እንደ ቀድሞዋ አትነዘንዛትም። የግሏ ችግር አለ ነጋ ጠባ አንጀቷን የሚመዘምዝ። እናትነቷ ላይ የሚያሳፍራት ንቃቃት የሚሰራ። የባሏ የወንድ ወሰን ሁልጊዜ ቤት አለመኖርና እሱ ሲናፍቃት ቤቷን ለልጇ ትታ ሁሉን ነገር በጨዋታ ለመርሳት ጓደኞቿ ቤት መሄዷ አንዳንዴ በወንጀለኛነት ስሜት ያነዳታል። ይኼም ስራዋ ሲያበሳጫት አልፎ አልፎ የወሌፈንድ የምትጮኸው ልጇ ላይ ነው። ሁልጊዜ ባሏን ትፈልጋለች፣ ጠዋት ስትባንን ጎኗ አለመኖሩ ያሳዝናታል፣ ዓይኖቿን ጨፍና ፊቷን ትራስ ውስጥ ቀብራ በረሃ ለበረሃ ለእንጀራው ሲዞር አንድ ነገር እንዳይሆንባት ለምትወደው ጨርቆስ ትፀልያለች። አለመማሯና ብዙ ገንዘብ አለማግኘቷ ባሏን ወደ ሩቅ አገር ያሰደደው ይመስላታል። ደሞዟ ደህና ቢሆን ኖሮ ቤት ይቀመጥ ነበር። ከእሱ ጋር ሲገናኙ የሚያደርጉት ሁሉ ነገር ትዝ እያላት አልፎ አልፎ ብቻዋን ስትሆን እንደ ልጃገረድ ታለቅሳለች። የመጣ ዕለት......በተለይ የመጣ ዕለት ተነፋፍቀው ተቃቅፈው ሁለመናዋን የሆነ ጉዳይ ሲወረው ዕንባዋን እየዋጠች በሚንተባተብ አፍ፡

«የእኔ እኩያ የለሽ» ትለዋለች። ጓደኞቿን ትረሳለች።

ከዛ ከጥቂት ቀናት በኋላ ተነስቶ ወደ ሚሄድበት ይሄዳል። እንደ ጥፋተኛ ቆጥራ ትሰድበዋለች።

«ማልልኝ ያለ እኔ ማንም......»

ይምልላትና፡

«አንቺስ?» ይላታል በማሾፍ። እንዲህ ሲላት ያበሳጫታል።

«ምን አባክንስና ነው!» ሲያሾፍም አትወደውም። ሟርት ይመስላታል።

«ብቃ ተይው፣ ስቀልድ ነው። ለምን እኔን ትጠይቂኛለሽ?» ይላል ሊያባብላት። ትቆጣለች። ትሳደባለች። እንደ አኮረፈች ይሄዳል። እግሩ ገና ወጣ እንዳለ እጆችዋን እያርገበገበች እያነባች፡

«መኳንንቴ ሂደብኝ......»

ለወራት ሰርቶ ያመጣውን ሳንቲም ይዛ ወደ ፒያሳ፣ ከዛንቺስ ለገሃር ከጓደኞቿ ጋር ትወጣለች። ዙረቱ፣ ወሬውና የሕይወት ድራማው ሲያደክማት ከሁሉ ለማረፍ ጋቢዋን እላይዋ ላይ ጣል አድርጋ አልጋዋ ላይ ትወድቃለች። ልጇም ይሄን በመሳሰሉ ምክንያቶች የቁጥጥሩ ገመድ ሲሰነስንባት(ቁጥጥሩ በዝቶባት እንዳልተነጫነጨች ሁሉ) ወደ ማታውቀው፣ ብዙ ወደ አልለመደችው ዓለም በተለይ እናቷ(እሷ ናት ቤት ሁልጊዜ ያለችው) በቸልታ 'የራስሽ ጉዳይ' ብላ የወረወረቻት ይመስላታል። ወደ ልጁ የምትሄድበት የምክንያቱ ሞተር ከቤተሰቧ የመጣ ወይ ከልጁ ጋር በምሽት ካላት የጨዋታና የድሪያ ማማር የበቀለ ተስተካክሎ አይገባትም።

○

ስለምንም ነገር እንደማላውቅ አብርሃም እንዲያውቅብኝ አልፈልግም። አለ አይደለ ያውቃል ግን እለፋለሁ አለማወቄን እንዳያውቅ። ከላይ እንገቴን ከታች ወገቤን ይዞ ማምለጫ እስኪጠፋኝ ሲስመኝ በቃ ጭንቅ ምናምን ይለኛል።

ግን 'ጨነቀኝ' አልለውም:: እንዲህ መላፋት ደስ ደስ እያለ የሚያስፈራ ግራ የሚያጋባ ሚስጢር የመሰለ ነገር ነው እና ግን አይደል ሁሉ ያደርገዋል አይደል እና ሚስጢር ግን አይደለም:: እዛ ከቤት ጀርባ ሲጠራኝ አልቀር ነገር ከሄድኩ ደ'ሞ የሰፈሬ ሰዎች በአጥር ቀዳዳ ምናምን ዛፍ ላይ ሁሉ ተቀምጠው የሚያዩ ይመስለኛል አለ አይደለ ምን ይታወቃል? እንዳለማወቅ እኮ የሚጎዳ ነገር የለም:: ግን የማላውቅ አልመስልም ግን ያውቃል እንደማላውቅ:: መፍራት ግን አለማወቅ ይመስል የለ ግን......አለመልመድ መፍራት ይመስል የለ:: በቃ ትንሽ እወናበዳለሁ:: ጠቅላላ አዲስአባ ያየኝ ይመስለኛል ደ'ሞ አለ አይደለ ዓለም የሾፈኝ......የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ[164] ሬጋን ሁሉ ሳይቀር የሚታዘበኝ ይመስለኛል:: ጋዜጠኛ ሁሉ የሚያቅ ይመስለኛል:: አለ አይደለ 'ሳትነካ አመለጠች የተባለችው ጨዋ ልጅ ተበላሸች' ብሎ የሚል አይጠፋም......አለ አይደለ ሶሺሊስቶች ልጃገረድ የላቸውም ብለው መንግሥቱ ኃይለማርያምን የሚያበሽቁ ይኖራሉ ሂሂሂ:: ምናልባት ቢሰላ በእኔ ዕድሜ ኢትዮጵያ ውስጥ ካልተነኩት ጥቂቶቹ አንደኛዋ እሆናለሁ:: ከሰፈሬ ደ'ሞ እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም......አለ አይደለ የጦርነት ሜዳ ሁሉ ልሆን ነው እንደ ማለት ሂሂሂሃሃሃሃሃ:: የቀዝቃዛው ጦርነት ጦር ሜዳ ምናምን አፍጋኒስታን ምናምን አይነት ልሆን ሂሂሂ:: ግን እንዲህ ብዬ ልቀልድ ብል ከማን ጋር ልቀልድ ነው? አለ አይደለ ከማን ጋር እንደዚህ ጆክ[165] አደርጋለሁ......ያሳፍር የለ:: እነ ልመንህ በዚህ ቢቀልዱ አሪፍ ነበር......አለ አይደለ ምናምን ሁሉን የሚያስቅ ተረብ ሰራርተው በቲቪ ምናምን:: ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች የቤት ልጅ መታዘብ ይወዳሉ......ጤይባ ምናምን ያደርጉናል......አለ አይደለ የእነሱ ሰራዊት ቁጥር እንዳነሰባቸው ነገር:: የድንግል ሬዘርቭ ቢኖር ግን ምን አለበት ሂሂሂ:: የእነዛን ሙጢ ሴት አዝማሪዎች ዘፈን ሁሉ የሚያዘፍኑብኝ ይመስለኛል......እሀሀሀእሀሀሀ......

*ክትፎ አበላሃለሁ አዲስ አባ ቤቴ*
*ማንጎና ዘይቱን ከወዴት አባቴ......*
*እድርሃለሁኝ ቀይ ዳማ ሰልካካ*
*(እሀሀ አሃሃሃ ቢሆንም......ጊዜው የጨዋታ ነውና እሀሀ)*
*ግን መች ይገኛል ቆንጆ ዛሬ ያልተነካ......*

የሆነ ካሴት ላይ ሰምቼአለሁ የባንዳቸው ስም ማን ነበር? ልበ ቢስ ሆንኩ:: ስም አይያዝልኝም:: ባንድ ይሁን፣ ሰው፣ እንስሳ ወላ ስም አይያዝልኝም:: አይገርምም? የማን ይሆን?......አንዳንዴ እማማ እቤት እያለች ገና ሳትተኛ ሁሉ አብርሃም ይመጣል ያ ድርቅ ያለ ደረቅ:: ወላ በእናትህ አታስጠጣ ሂድልኝ ምናምን ስለው ድርቅ በቃ ልክ ግድግዳ ላይ እንደ ጭቃ ይለጠፍና በቃ ጥላ ምናምን ይመስላል:: ታዲያ ቡና ማድ ቤት እጥድና ቶሎ በእሱ እሳምና ጀበናዬን ይገፔ እገባለሁ እስከ በረካ ምናምን ድረስ:: ቡና ባፈላሁ ቁጥር እሳማለሁ:: ቡና ቁርስ ስቆላ ሁሉ እሳማለሁ:: በትንሽ ስፌት ከቆላሁት ላይ ዘግኜ ደብቄ እዛ ግድግዳ ምሽጉ እወስድለታለሁ:: አፉ ፈንድሻ ፈንድሻ ሲለኝ ስወድ:: አፉ እንደ ሽንብራ ክክ ሲሸተኝ ስወድ:: አንዳንዴ ስመስጥ ለምን ሽንብራ ሽንብራ

---

164 ሮናልድ ለማለት(አ)

165 ቀልድ(አ)

ፈንድሻ ፈንድሻ የሚሸት ዲአዶራንት አይሰሩም? እላለሁ:: ወይም ሽቶ ምናምን:: አንዳንዴ የሰውነት ፍቅር ምንድነው እንደዚህ ያደከማል እንዴ ምናምን እልና ራሴን እጠይቃለሁ:: ከዛ እሱ እንደውም እየቀለደ የአቦሉን በደንብ ሳላደረግንም በደንብ አልሳምሽኝም ሊያመኝ ነው ምናምን ይላል:: አንዳንድ ቀን ይደከመኝና በተለይ ከረጀው በኋላ ማድ ቤት ስለማልሄድ ደክሞኝ ቤት እገባለሁ:: አንድ ቀን መሸት ብሎ ተስሜ ቤት ስገባ አለ አይደለ እናቴና ሁለት ጓደኞቿ ተቀምጠው ሻይ ይጠጣሉ፣ ድፎ ቆራርጠው ይበላሉ:: ተምታቶብኝ ሰላምታ ማለት ሁሉ ረስቼ አልፌአቸው መኝታ ቤት ገባሁ:: ስገባ ሁልጊዜ አቅፋቸዋለሁ:: እስማቸዋለሁ:: ይወዱኛል:: ታዲያ ዝም ብዬ ተደነባብሬ አልፌአቸው ስገባ ያልተለመደ አይሆንም? ያልተለመደ ነው:: ወላ ያወቁብኝ መሰሎኝ አለ አይደለ የተሳምኩ የተነካካሁ:: ማለት ሁለመናዬ ይፈራል:: እንቺ.! ምነው የት ጠፋሽ? ቡና ምናምን አታፈይልንም? በቃ ተጎረመሰና ነው?......መኝታ ቤት ገብተሽ ተሰነቀርሽ..... እያሉ እየሳቁ ሲጠሩኝና በአፍ ሲላፉኝ እንዳልሰማሁ አለ አይደለ ከአረማመዴና ከአስተያየቴ ተስሜ እንደ መጣሁ ሁሉ የምጠጣ ዓይነት እየፈራሁ......ፎጣ ከተሰቀለበት ግድግዳ ላይ አውርጄ እነሱ እየተሳሳቁ እኔ ጨለማ ውስጥ...... የመኝታ ቤት መብራት ሳላበራ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ራሴን እየጠረግሁ አያቸዋለሁ:: እዚያ ካርታ እየተጫወቱ.:: መአት ባለሻሽ:: መአት ባለ ትልቅ ቂጥ:: ገላዬ ከላይ እስከ ታች የሆነ የሚጥም እርግማንና ምርቃት ወረደበት:: ነፉስ እንደ መታው ቦብሊን ተንቀጠቀጥኩ:: ቀላዬ የተከፈተ መሰለኝ:: በጣም ፈራሁ:: ጭንቅላቴ ያጋጠመኝን ለመግለፅ ቃላት ይፈልጋል:: ቃላት የለውም:: የተማርኩት ቃል የለም:: ይኼም ለማን ይነገራል? ዝም:: ለቅርብ ጓደኛዬ ለመንበረ እንኳን መንገር አሳፍሮኛል:: ነገሩ ሁሉ በአፍረት ይሞላኛል፣ የራሴ በሽታ ይመስለኛል:: ታዲያ ትንንሹ ነገር ሁሉ ዝብርቅርቅ ይልብኛል:: ለምን እንደሆነ ባይገለፅልኝም:: አብርሃምን ሲያወራኝ እወደዋለሁ:: የሚያመጣቸው አዳዲስ ቀልዶች ይጥሙኛል:: አብሮኝ ሲያወራ ጓደኞቹ 'አብሽ እንሂድ' ሲሉት 'መጣሁ' ብሎአቸው ግን ትቶኝ አይሄድም:: ይሄ ሁሉ ደስ ይለኛል:: አንድ ሰሞን ጠዋት ጠዋት ይሄን ራዕይ የመሰለ ነገር አይ ነበር:: ፊት ለፊቴ የማየው መንገድ ቱቦ ነገር ነው:: ግድግዳውን ተደግፌ ተቀምጫለሁ:: ከግድግዳው ላይ የስኳር ወለላ ይወርዳል:: ከእሱ እልሳለሁ:: ስጠግብ ከአንዱ ጡቴ ወተት ፊን ብሎ ይወጣል:: እዛ ቱቦ መጨረሻ ጥላ መስሎ አብርሃም ራቁቱን ቆሞአል:: ሳየው እፈራለሁ ማሰብም:: አብርሃም ወተቴን እንደ ጥጃ አፉን ከፍቶ ይቀበላል:: ፊቱ በወተት ረጥቦ እየሳቀ ሲያየኝ እደነግጥና እባንናለሁ:: አንዳንዴ እመጣለሁ ብሎኝ ቀጥሮኝ እዛ ፊት ለፊቴ በጣም ቅርብ ነው የሚኖረው ልጠራው ስችል እንጀቴ እየናፈቀ ተግደርድሬ እቆማለሁ:: ጠቅላላ ጠብቄው ሲቀር ስፍስፍ ምናምን ያደርገኛል:: አንጎሌ ጥዝ ይልብኛል:: የሞተ ወይ መኪና የገጨው ወይ በሱዳን በኩል ከአገር የጠፋ:: በቃ ለመፀለይ ትንሽ ይቀረኛል......ምናምን አለ አይደለ:: ስለ እሱ ትዝ የሚለኝ ትንሹ ነገር ሁሉ ያባባኛል:: አለ አይደለ በሚያደናግር ጨለማ ውስጥ እቅፍቅፍ ሲያደርገኝና ያበጠ፣ የሚሞቅ ገላውን እየፈራሁ እያማተኩ ስደገፈው:: ደ'ሞ አስገራሚ ንቅናቄውን ብቻ እያሰብኩ ማድ ቤት እጠገብ አለ አይደለ በሩ ስር አረፍ ብዬ ቢያናውዘኝ እፈልጋለሁ የተዘባረቀብኝ ነገር ሁሉ ቢያልፍልኝ ምናምን......

ግን አያልፍም ......

**(የሚፈልጉት ይሰማቸዋል፣ የማይፈልጉትን ያገኛሉ)**

ከሠፈር አርቆ ሊቀጥራት ቢቋምጥም ቸልታዋና በቀልድ እየጋረደች የምትሰጠው ዕንቢታዋ እረፍት አልሰጠውም:: ወይስ የመግደርደር ሳይንስ ነው? ወይስ የሽወዳ ኪነጥበብ ነው? በቀላሉ በሳምንት፣ በጥቂት ወራት ውስጥ የሚያጠናቅቀው የመሰለው ቀብ እንዲህ ወራት የሚከርም አልመሰለውም:: ትቀርባለች፣ ትርቃለች:: መግደርደር እንዲህ ወደ ደዌ ይቀርባል? ከጀብድ ዕቅዱ ጎን በልቡ ትንሽ ቂም እየበቀለ፣ እየተገነባ ሲመጣ ይሰማዋል:: ለዚህም አንዳንድ መልስ የማይገኝለት ጥያቄ ያነሳል:

«ማንኝ ብላ ነው?»

አለ አይደለ ልቡን አንዳንዴ እንደማትዘነትረው:: አንገቷን ሰበር አድርጋ ላለመሳም የውሸት ልትርቀው ስትል ለአስር ለአስራ አምስት ሰኮንዶች 'አየር እንደጠማው አሣ' አፉን ከፍቶ ሲከተላት:: ቀጭን ገላዋ እቅፉ ውስጥ በስሜት ሲርገፈገፍ:: ትከሻው ላይ አገጯን አሳርፋ በትናንሽ ሳንባዎቿ ቁና ቁና ስትተነፍስ......

በዚያች ምሽት ከእግዜር ሌላ ሁሉን ዐይነት ሰዎች የበለጠ አልመሰለውም?

ለጀብዱ ወጥቶ ቂም በቀል ይዞ መመለስ አይፈልግም:: ለጀብዱ ወጥቶ ቂም ይዞ መመለስ 'የአራዳ' አይደለም:: የጀብዱ ዓላማ ሌላውን ጉዳት ላይ የመጣል አይደለም:: የቂም በቀል ሃሳብ ግን የመጉዳት ፅንስ ነው:: መልስ ምት ነው:: በዚህ መጨበጫ በሌለው ፍርሃት ምክንያት የእሱ 'ፊንታ'[166] መረር ያለ ስልትና ትኩረት ያዘ:: እሷ ግን ሁሉንም......የእሱን የታቀደና ያልታቀደ ድርጊቱን ሁሉ በየዋህነት ወደ ፍቅር መቅረቢያ መንገድ እየተረጐመችው ቆንጆ ሕልም እያለመች ትተኛለች::

ለደመወዝ ዕለት ወይም ለበአል ዕለት ከአጠገባቸው......ከፅዱ ጀርባ እናቷና ጓደኞቻቸው ሲሳሳቁ በፋሽኬት ሲሟሟቁ ይሰማል:: ራቅ ብሎ ከሚታይ ጉብ ካለ መረባ ከመሰለ ሕንፃ ጀርባ እዚህ አሉበት ረቆ በግድ የሚሰማ ጫጫታና ሙዚቃ ይንተከተካል::

በጓሮ በር ሾልካ ወጣች:: በአወጣጧ ደስ ብሏት......'ማምለጥ በመቻሏ':: እዚህ ነኝ ብላ አሳይታ፣ እዛ መሄዷ: እንደ ልጅነቷ ድብብቆሽ:: ወደ ነፃነት:: የፈለገችውን ወደ ምታደርግበት::

ዛፎች አሉ ጥላ አላቸው......ጥላው ብርድ የለበሰ......

በጠለለ ማታ በአልኮል የነደዱ ወይዘሮዎች በሳቅ እየፈረሱ......ጎረምሳው ላብ በላብ ነው እንደ ወጠጤ ፍየል ይሸታል ወጠጤው:: በቀዝቃዛ ማታ ከጥላዎች ፈቀቅ ብሎ የድፍን ጨረቃ ብርማ ወዝ እሱ መደብ ሆኖ የምታየው የጎረምሳው እጅ ትልቅ ነው......ትልቅ ጥቁር ነው......ደም ስሮቹ ወፋፍራም ናቸው:: ከፊት ለፊቷ ቀሚሷን በቀስታ አንስቶ ወይ በልፊያ መሃል በሃሳዌ እምቢ እንደበት ስታገረገር ግን ሳይቆይ የመሳሳም ትንፋሽ ነው......የሆነ ነገር ጉሮሮዋ ውስጥ

166 finta/finto= (ጣሊያንኛ)ሽወዳ(አ)

ሲሰነቀር ትደነቃለች ትደነቃለች ፍርሃትም ፍርሃቷም......አንዱ ጆሮዋ ወደ ማድቤቱ አቅጣጫ ኮቴ ሊሰማ መንገድ ላይ እንደ ቅጠል ያርፋል:: ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ለሩብ ሰዓት የሚያንቀጠቅጣት እንግዳ ስሜት እስኪበርድላት እየጠበቀች:: ከውስጥ ሱሪዋ ጠል ይረግፋል በሚያዘግም ፀጥታ::

......እዚህ እየተሳመች እነዚያ ነጭናጫ ሰዎች በአጠገባቸው እያወሩ ሲሄዱ በፌዘዘ ልቦናዋ ቶሎ ብለው አልፊዋቸው ባለመሄዳቸው ትታዘብ ይሆናል:: ለምን እግሮቻቸው እንደ ምላሳቸው አይፈጥኑም?) እሱ የቤቱን ግድግዳ ተደግፎ እሷ ደረቱን ተደግፋ ለግማሽ ሰዓት ሲቆዩ ቀና እያለች ዐይኖቹንና የተለጠፌ የወረቀት ሰንበር የመሰሉ ጥርሶቹን:: ልሂድ አልሂድ:: እናቷ ደጋግማ ስትጠራት መስማትም አለመስማትም:: ግራ ጡቷ በጨለማ ክብ ብርሃን ነው:: ቀኝ እጁ እንደ ደጋፊ:: በሚልፈሰፈሱ ቃላት ባከከከሀ ሊሂድበበትት......ደርቃ እቆመችበት ወደ ሰማይ አፏን ከፍታ ስታምጥ አንገቱን ሰብሮ ከግራ ደረቷ......

በምሽት ሁሉ በየቤቱ ራቱ ዙሪያ ተቀምጦ ጨው አነሰ፣ ወጡ በረደ፣ እንጀራው ደረቀ፣ ሻይው ተፋጀ፣ ፉስታው ረዘመ፣ ፍርፍሩ ደረቀ ሲል ....እነሱ በአፋቸው የሚያዳልጥ እርጥበት ተጥለቅልቀው በየልባቸው የሚያስቡት አለ:: ካይኖቿ አገላለጥ እሷ ፍቅር:: እሱ ወደ ሴት ሊለውጣት::

በእሳቱ ውስጥ ካለፈች በኋላ ያመነጨችው ላብ እዛና እዛ እዛ እያሳከካት:

«አጎቴ ቤት ለምን የሚቀጥለው ሳምንት አንሔድም?» አሳት አቅፎ...... ከንዱ ላይ የበጋ ዝናብ የመታው አልባሶ ሹርባ መስላ.....

«እንዴ? ለምን?»

«ለምን? ቪዲዮ እናያለን:: አሪፍ ካሴት እከራያለሁ......ደ'ሞ ብዙ አለው እሱ»

«ስለምንድነው?»

«ስለምንድነው? የምናየው? ስለ ምን እንደሆነ አላውቅም ግን በጣም ጥሩ ፊልም እከራያለሁ»

«ማን ማን አለ?»

«ማን ማን አለ?......የአጎቴ ልጅ፣ እህቱም አለች፣ አንድ ጓደኛችን፣ እኔና አንቺ......አምስት ሰው»

«እኔ መቼ እሺ አልኩህ?»

«መቼ እሺ አልኩህ? ምን ትሆኛለሽ......ደርሰን ትመጫለሽ»

«አብረን ልንሔድ?»

«አብረን? ታዲያስ......ምነው?»

«የሠፈር ሰው እንዲያውቅ አልፈልግም......ያው ሌላ ነገር አድርገው ይገምቱታል»

«የሠፈር ሰው? ያው ጎረቤት ነው የምንመስላቸው»

«አሔ!»

«አሔ?......አውርተሻል?»

«ምኑን?»

«ምኑን? እኔ ቦይፍሬንድሽ[167] እንደሆንኩ......»

«ለዚህ ዐይነት ነገር ልብ የለኝም......መጀመሪያዬ እንደሆነ ታውቃለህ»

«ልብ የለኝም? በቃ አብረን እንሔዳለን»

«አብረን አንሔድም»

«አብረን አንሄድም? ታዲያ......»

«መጀመሪያ እናቴን ምን ምክንያት......»

«እናቴን? ምኑ? መሸወዱ? እሱ ቀላል ነው መምጣት ከፈለግሽ»

አቅፎ ይዞ በማቆላመጥ......በሚንገላቱ (አውቆ እያንገላታቸው?) ዓይኖቹ እያያት::

«ምን እላታለሁ?»

«ምን እላታለሁ?......እኔ ልንገርሽ?»

«እስኪ»

«እስኪ ቆዩ......ለእህቴ ልንገራት»

«ለምን?»

«ለምን? ያው አንቺን እንድትጠራሽ:: የት/ቤት ጓደኛሽ እንደታመመችና በሽተኛዋ አንቺን እንደፈለገች እናትሽ ፊት ትንገርሽ»

«ለእህትህ ምን ልትላት ነው ይሔን ነገር አድርጊ ስትላት?»

«ለእህቴ? አጎቴ ቤት ሲኒማ ልጋብዛት ነው እላታለሁ»

«ታምንሃለች?»

«ታምንሃለች?......እኔን? እኔን ታምነኛለች»

«ሔባ»

በቀልድ እየጎሰመችው:: በአራዳ ትንፋሹ ግንባሯ ላይ የተደፋውን ስስ ፀጉሯን ብን ሲያደርግላት......ዐይኖቹ ሁለት ድፍን ጨረቃዎች ነበሩ:: መሃላቸው የኩል ኳስ የወደቀ......የበጋው ምሽት ፌንጣ ጉሮሮ አያርፍም:: ዜማ ያወርዳል:: ጨለማው እንደ ረጠበ ሐር እያዳለጠ ያልፋል:: እዛ ወዲያ የአዲስአባው ባቡር ጣቢያ ብረታም ዕንቅልፉ ውስጥ ነው......

ወደ እሱ ሳባት......

167 boy friend= ወንድ ጓደኛ(እንግሊዘኛ)(አ)

○

አብርሃምን ተላምጄዋለሁ፣ ግን ከሠፈሬ ውጭ አብሬው ርቄ የወጣሁበት ጊዜ የለም አለ አይደለ በሙሉ አላምነውም ለምን ቢባል አይገባኝም እንዲገባኝም አልፈልግም ምክንያቱም እንጃ......ባልፈራውም......ሳስበው ራሱ ያሳፍረኛል:: እና መሳሳሜ ደ'ሞ ከማንም የበለጠ እንደማውቀው ምስክር ነው አደል? ሌላ ያሳሰበኝ ደ'ሞ ያን ቀን ዘመዶቹ ቤት ምን ለብሼ እንደምሔድ ነው:: ሠፈር ስንገናኝ የምለብሰውን አልለብስ መቼም:: ዘመዶቹም እሱም ዘናጮች እንደሆኑ አውቃለሁ......አንድ የምታምር ቀሚስ አለችኝ ለስፔሻል ጊዜ የምለብሳት:: ደ'ሞ አንድ ቀን ግድግዳ ስር ቆመን ስንጫወት አባብሎ ልቤ ከዳ እንዳረገኝ እጁን አለ አይደለ በውስጥ ሱሪዬ ስር ሰዶ አለ አይደለ እኔ አልገባኝም እዛ ጋ እጁን ካላስጠጋሁ ምናምን ብሎ ሲታገለኝና ስመናጨቅ የሚያስፈራ ነገር አለው እኮ! ቀሚሴን ስንጓተት አለ አይደለ ወገቡ ምናምን ጋ ተተርትሯል እሱን ገና ልብስ ስፊ ቤት መውሰድ አለብኝ ደ'ሞ ለማሰፋት ማዘርን ሳንቲም ብጠይቃት ምን ያደርግልሻል ትለኛለች:: ቢሆንም ስለቀሚሱ ማወቋ አይቀርም ልማድ አላት ልብሴን በድንገት ተነስታ ማጠብ ምናምን ታዲያ የት ስትጓተቺ ቀደድሽው ብትለኝ ምን እላታለሁ ሌላ እንኳን ባይሆን ባፏ ግድል ነው የምታደርገኝ:: ቀሚሴ ቢቀደድም እሱ ይሉኝታ ቢስ አይደለ ነገ ከነገወዲያ ምናምን እያለ ከብዙ ልፊያና ጭቅጭቅ በኋላ መነካካት አላምዶኝ የውሸት እየተከራከርኩ እጁን ውስጥ ሱሪዬ ስር ሲሰድ ተው እንጂ አላበዛሽውም እንዴ ሰው ይመጣል ቢመጣብንስ ምናምን እያልኩ ደስ ግን ብሎኝ በቃ ሁልጊዜ እናፍቃለሁ ስፈልግም እንዲያረገኝ በጨዋታ ጣቶቹን እነካካና እስማቸዋለሁ:: መዳፉን ፊቴ ላይ አደርግና በዓይኖቼ መለማመጥ ነገር አደርጋለሁ:: ብልግ አልኩ:: ፊት ለፊቴ ይቆምና ጡቶቼን ደ'ሞ ትንሽ እያመመኝ ግራና ቀኝ እያየን በዛ ጋ ውሻ ያልፋል በዛ ጋ መቻል ይጮሃል በዛ ጋ ደ'ሞ ሳቅ ከእትዬ አስካለ ቤት ወዳጃቸው መላጣው ግርማ ትዝ ይለኛል ከዛ ሳባ ቁሊ ትዝ ትለኛለች ሳባ ስትጀምር እንዲህ አድርጋለች? ምናምን? እስባለሁ እንደዚህ:: ብቻ የሆነ ነገር ያደርገኝና ጨለማው እንደ ብርሃን ቦንብ ይፈነዳብኛል:: እታወራለሁ ነገር:: በቃ እንደ ሳባ ቁሊ ልሆን ነው ምናምን እላለሁ በልቤ......ሳባን ከእንግዲህ 'ቁሊ' አልልም ምናምን እላለሁ:: ከዛ ደ'ሞ ድክም ይለኛልና በቃ እጆቼ በቃ ይንዘላዘላሉ እና የጨርቅ አሻንጉሊት ምናምን የሆንኩ ይመስለኛል:: ከእኚያ ሴትዮ ቤት የሚወቀጥ ነገር ይሰማናል...... ምን እየወቀጡ ነው ገምቺ ይለኛል......ለመሳቅ እጥራለሁ ሁሁሁ ነገር......ሁሁሁ ብዬ አላውቅም አለ አይደለ ሳቄ ራሱ ያስጠጣል:: ቢሆንም ያው የምወድቅ እየመሰለኝ ሙጥኝ ይገፌው ይኮረኩረኛል:: ከመሃል የሚያሳፍረኝ ደ'ሞ ለምን እንደሆነ አላውቅም ሲኮረኩረኝ ዳሌዬ ሳልፈልገው ይነቃነቅብኛል......አልፈልግም ግን ይነቃነቅብኛል ደ'ሞ እንዲህ ሲሆን አፍሬ ልሞት:: ከመሃልም ባለጌ አይደል እሱ የሆነ ስድ የስድ ስድ ልቤን ወሰድ ሲያደርገው ለሰው የማይነገር ለማሰብ የሚቀፍ ነገር ያደርጋል ወይድ ምናምን ብለው እንኳን አይሰማም እኔ ግን በፍርሃት ምን መሆኔ ነው ጉዴ ምናምን እያልኩ የእማማ ሽልንግ ትዝ ይለኛል እንዲህ ሲሆን ሽልንጉ ትዝ ይለኛል ግራ ይገባኛል:: ፊቴን ትከሻው ላይ አስደግፌ ለምን ሽልንጉ ትዝ ይለኛል? እላለሁ ግን ለማየት ዓይኖቼን እንኳን ዝቅ ማድረግ እፈራለሁ::

እና ቀሚሴ በልፊያ ብትጎዳም ከላይ የሚለበስ ግን አይቸግረኝም......አባቴ እንዴ ከድሬዳዋ ያመጣቸው መዓት ሹራቦች እኔም እማማም አለን:: በአስቸኳይ ለአደጋ ስለምጠራ ቶሎ መሔድ አለብኝ:: መኳኳያ ጊዜ አይኖረኝም:: በጣም ስኳኳል ካየች እናቴ የጊደኛዬን ጥሪ ፍቺውን ሌላ ታደርግና እሷ እንደሆነ አራዳ ነገር ናት ትነቃለች......ብታበላሽብኝስ? ስለዚህ እንዳላስጠጣ አደርጋለሁ:: ደ'ሞ ከእሱ ጋር የተቃጠርነው ብሔራዊ ቲያትር ነው:: እንደ ገና የትራንስፖርት ገንዘብ የለኝም:: ልጠይቀው እችል ነበር ግን እንዳለው ሰው ኮራሁ:: እዚህ ቤት ደ'ሞ እናቴ ገንዘብ በየቦታው አትጥልም:: ቆጥብነቷ ሳይሆን......የላትም:: አባባን መጠበቅ አለባት እስኪልክ ወይ ልደታ መድረስ አለባት:: ያኔ ሲልክላት ደ'ሞ ፌሽታዋን የሚችለው የለም......እንደ ሚሊዬነር ምናምን ልሁን ትላለች:: ወር ወር ሲጀመር የሠራችበትን ገንዘብ ከጓደኞቿ ጋር ትጠጣበትና ወር መሃል ላይ መስሪያ ቤቷ ለመሔድ አውቶብስ መጠበቂያ ፌርማታ ላይ ከጭንቅ የሚያወጣት ሊፍት ትጠብቃለች......የኮረሪማን አባት ሲራክን አስቸጋሪ አንደኛዋ እሷ ናት:: የሰፈሬ ሰው ነው እያለች የጎረምሣም ሊፍት አትምርም አሉ:: አለነገር አብርሃም 'ባለጌ ናት' አላለኝም:: ዓይን ነው ጆሮ? ለባለቤቱ ሩቅ ነው ይባል የለ?

***(ሽልንግና መንገድ)***

እናቷ አልነበረችም:: እየተገላመጠች የቁርቆሮ ሳጥኑ ወደ ሚቀመጥበት ትልቅ የእንጨት ሳጥን ሔደች:: ይሔ ሳጥን ተዘግቶ አያውቅም:: ብዙ ታሪኩ ግልፅ ያልሆነ አልባሌ ቅራቅንቦ የሚቀመጥበት ነው:: ክቡ ቁርቆሮ እሳጥኑ ግራ ጥግ ተቀምጦአል:: በቀስታ አወጣችውና ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠችው:: ምናልባት እናቷ ድንገት ከመጣች እንድትሰማት የቤቱን የፊትና የኋላ በሮች ዘጋቻቸው:: ዋናው በር ካልተከፈተላት እናቷ በጆርባ በር ዞራ መግባት ትወዳለች:: የቁርቆሮው ክዳን ቶሎ አልተከፈተላትም:: ዘመን በዝገት ያኮማተረው ይመስላል:: ክዳኑ ገፅ ላይ የሚያስቁ የአሻንጉሊት ስዕሎች አሉ:: እነሱም ላይ በወየቡ ወፍራም የእንግሊዘኛ ፊደላት: Party chocolates[168] የሚል ተፅፎአል:: ከላይ የተንሳፈፉትን ጨርቆች፣ ዚፖች፣ መርፌዎችና ክሮች ገፋ አንስታ ከሥር ዐየች:: ሁለቱ ነጫጭ ሽልንጎች ጉን ለጉን ተቀምጠዋል:: ቶሎ ለቀመቻቸው:: ክዳኑን እንዳገኘችው አጥብቃ ዘግታ የቁርቆሮውን አገልግል እነበረበት ሳጥን ውስጥ አመቻችታ መለሰችው......

○

ስሰርቅ ደብሮኛል:: አለ አይደለ ራሴን 'ሰረቅሁ' ከማለት 'ወሰድኩ በይ' እላታለሁ:: የማልረሳው ነገር ግን አለ ያኔ......ሽልንጎቹን የለቀምኩበት እጄ ለአፍታ ተንቀጠቀጠ፣ ፈጥና ላለፈች ሰከንድ ትንፋሼ ከሳንባዬ አልወጣም አለኝ:: አየር ሳላቋርጥ የምውጥ መሰለኝ:: ክዳኑን ስመልስ አንድ እንግዳ ነገር ተሰማኝ......ዐይኖቼ የቁርቆሮውን ሆድቃ ያዩ ነበር::......ከከደንኩት በኋላ የቁርቆሮው ማሕፀን ምንም ነገር ያልነበረበት ያሌለበት የማይኖርበት ባዶ የነጭ ብረት መስከ መሰለኝ:: ግን ደሞ የኒኬሉ ክዳን ላይ ያለው «ፓርቲ» የሚለው የእንግሊዘኛ ፅሑፍ እንደ ኮከብ ቆጠራ ስሌት ከቤት የመውጣቴን ድርጊት የደገፈልኝ መሰለኝ:: በአጋጣሚ

168 የፓርቲ ቸኮላታዎች(እ)

የቃላት መመሳሰል ውስጥ ድርጊቴ እንደ ታተመና እንደ ተተነበየ ሁሉ ደቃቃ የሞራል ግፊት ሆነኝ:: የአብርሃም እህት ሃና መጥታ እንሂድ ልትለኝ ስትጠራኝ እናቴ አልተጠራጠረችም:: ሁለት ሽልንጐቼን ይገፍ ሹክክ ብዬ ከቤት ወጣሁ:: አወጣጤ 'ሹክክ' አለበት:: ሹክክ ብዬ አላውቅም:: የመጀመሪያዬ ሹክክ ናት:: ገላዬን ታጥቤ ፀጉሬን አበጥሬ ቁጥርጥሩ ከቅንድቦቼ አልፎ እንዲረግፍ ነካክቼ፣ እሱ የሚያደንቃቸውን ከንፈሮቼን 'ቼክ'[169] አድርጌ፣ ከእናቴ ሽቶ ትንሽ አንገቴ ስር ጠብ አድርጌ:: ሹክክ:: የሆነ ባርነት የመሰለ ነገር አለው፣ የሆነ ያልገባኝ ጉድለት አለው:: ለምን ሹክክ? ሽልንጎቹን አውቶብስ ውስጥ መለወጥ የምችል ስላልመሰለኝ ከመሳፈሬ በፊት አንድ ቤንዚን ማደያ ሳየው ጥሩ ሰው የመሰለኝን ጋዝ ቀጂ ተጠግቼ እንዲለውጥልኝ ጠየቅሁት:: ሰውዬው ሽልንጎቼን በችኮላ ተቀብሎ ኪሱ ካስገባ በኋላ ሦስት ብር ሰጠኝ::......መንገዴን ቀጠልኩና በድንገት ዞር ስል አይደለ ዞር ስል የነዳጅ ቀጂው ሰውዬ ዐይኖች በደስታ በርተዋል፣ ውጋጋናቸው ጉንጩ ድረስ እስኪታይ ድረስ ምናምን:: እንዳጠፋሁ የታወቀኝ ያኔ ነው:: ልቤ ሌላ ጋ፣ ልቤ ሌላም ጋ ነው:: የማስበው ልክ እንደማውቅ ሁሉ ምን ምን ዓይነት ቪዲዮ እንደማይ ነው:: ፊልሙን ዐይተን ሊመሽ ሲል ከመጣን ደ'ሞ ያ አብርሃም አባብሎ ሰው በሚተላለፍበት መንገድ ዳር እንዳይስመኝ ነው:: ብቻ በአጠቃላይ የነገሩ ብርቅነት ዞር አድርጎብኛል:: በኮረዳነት ጊዜ ይምታታብናል አይደል (አንቺ ብቻ ነሽ የተምታታብሽ አልባልና)......መሰለኝ:: አሁን ለምሳሌ ከቀጠሮሽ ከምትቀሪ ወይም ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም ላይ ከምትተኩሽበት ምረጪ ቢሉኝ አምጡ ሂሂሂ ሾት ገን እተኩሳለሁ እዛ ሰውዬ ላይ እላለሁ:: ሾት ገን ያው አይቼ አላውቅም::

ልጆች ስለ ቪድዮና ስለ መሳሰለ ስልጡን ነገሮች ት/ቤት ሲያወሩ አለማወቄ አንዳንዴ ያሳፍረኛል......አለ አይደለ ግን ደ'ሞ አውቃለሁ እዚህ አገር ውስጥ መአት ሰዎች መአት ነገር አያውቁም፥ የሚያውቁት ጎረቤታቸውን ነው:: ...... የሚያውቁት አለ አይደለ ድስት ቂጥ ስር ከሸክላ የተጣበቀ ያረረ የሽሮ ማድያት ነው:: የሚያውቁት ቡና ሲወቀጥ ሲሰሙ ነው:: የሚያውቁት በጨለማ ተቀምጠው ስለ አመማቸው ሚስታቸው ማሰብ ነው:: በአይን ማዝ ተከድነው ሙሉ ጨረቃ ስትወጣ ማየት አለመቻላቸው ነው(የሴት ልጃቸው ስም ደ'ሞ 'ጨረቃ' ነው)...... በሆድ ሕመም ለአዳሪ ገደል ስር እንደ እንጉዳይ ተተክለው በእባብ ሲደነብሩ ነው:: ሰኞ የተተረተረ ኩታቸው ደግሞ ማክሰኞ ሲተረተር ነው:: የሚያውቁት ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ከጉልበታቸው ቁስል ላይ ዝንብ እሽ ሲሉ ነው...... የሚያውቁት አየር ነው......የሚያውቁት ድንጋይና ሳር ነው......ብዙዎቹ የሚያውቁት በወሊድ የሞተች ጎረቤታቸውን ነው......የሚያውቁት እንቅፋት ያደማው አውራጣታቸውን ነው......የሚያውቁት ያረሱትን ጤፍ ሸጠው ዘንጋዳ መብላት ነው......የሚያውቁት ቂጣ ነው......የሚያውቁት አራጣ ነው ::

ከሌለኝ አለ አይደለ ቀሽምነት ምናምን ይመስለኝ ነበር (አንቺን ብቻ ነው የሚመስልሽ አልባልና)......ቀለሜዋ ብቻ መሆን ደስ አይልም:: እና ሌላ ደ'ሞ ያቺ ሞልፋጣ ገርል ፍሬንዱ ስንዱ የምትባለው እንድታየኝ አልፈልግም:: ወይም

---

169 check= አንድ ነገር ተስተካክሎ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ በትኩረት ማየት (እንግሊዘኛ) (አ)

የሚያውቃት እንዲያየኝ:: ከሰፈር ውጭ ከቤቴ ርቄ ከአብርሃም ጋር መታየት እንደተፈለገው ይተረጎማል:: ምን እንደ ምታስብ አይታወቅም......አራዳ ነኝ ምናምን የምትል የሆነች ሞልፋጣ......ጠባብ ጂንስ ሱሪ አድርጋ አማረልኝ ብላ ነው ገፋፋ ቂጧን እእእእ እያለች ትጎትታለች:: መቼም ያንን የሚያክል ቂጥ ሳታምጥ አትጎትትም ማለት ዘበት ነው:: የአብርሃም እህት ሃና አብርሃምና ስንዱ ተጣልተው ሊጋደሉ ነበር ትለኛለች:: ስንዱ ማንንም በንቀት የምታይ ምን እንዲጠበስላት እንደምትፈልግ የማይታወቅ ልጅ ናት:: ግን ቦይ ፍሬንዷ የነበረው እኔ ጋ ነው የሚያመሸው::

ብዙ ሳልለፋ አብርሃምን ብሔራዊ ቲያትር አገኘሁት፣ አቅፎ ጉንጬን ሳመኝ:: ወገቤን ግራና ቀኝ ይዞ.....ተው ተው ምናምን እያልኩት:: ግራ ገብቶኛል ምናምን አይደል ግን ደስ አለኝ:: መአት ሰው በተለይ ወንዶች በተሰበሰቡበት ከወንድ ጋር መገናኘት:: ጎረምሶች ያዩናል:: ዞር ዞር ስል ሲያዩኝ አያለሁ:: ራቁቴን እንደ ሆንኩ ሁሉ አፍራለሁ:: እማምላከን ቀሚሴ ላይ መአት ዐይኖች ሳይጣበቁ አይቀሩም:: ባራግፍ በቃ ከብሄራዊ ቲያትር እስከ ኢትዮጵያ ሆቴል መአት ብሌኖችና ሽፋሎች እስፋልት ላይ ይዘሩ ነበር:: ሂሂሂሂ:: ጎረምሶች ብሔራዊ ውትድርና ሄዱ ይባላል እንጂ እዚህ ብሄራዊ ሲኒማ ሬክላም ስር ቆመው እኛ ቂጥ ላይ ሲያፈጡ ነው የሚውሉት:: መሰለኝ:: ታዲያ አብዮታዊ ጦር ለምን መሸነፍ ጀመረ? አብርሃም ሲያቅቅፈኝ ሁለመናዬን ኮረኮረኝ......ግን አለ አይደለ ብጠየቅ ያኔ ምን ይሰማሻል? ብባል 'ውይ ያስፈራል እኮ' ብቻ ነው የምለው:: አንዳንዴ እናቶችን ስናበሳጫቸው አለ አይደለ ጥግብ ስንል ምናምን 'ምናለበት አንዱ ወስዶ ባስተካከለልኝ' የሚሉት በዚህ ዐይነት ደስታ ተጠልፈን እንዳንነዘንዛቸው ይሆናል:: ጉንጬን ስሞ ዐይኖቼን፣ አፌ ጻር ለአመል ነካኝ:: የቂጤ ጉንጮች ተንቀጠቀጡ (ሁልጊዜ ስደነግጥ ቂጤ ይንቀጠቀጣል)::

ቦሌ ወሎ ሠፈር በታክሲ እሱ ከፍሎ ሔድን:: የአጎቱ መኖሪያ በሐረግና በፅድ የተከበበ ትልቅ የሸክላ ቤት ነው:: በር ጎን ያለ በጣት የሚገፋ ደወል ተጫንና ሰው ጠራ:: እንዲት አሮጊት በር ከፈቱልንና ገባን:: ሴትዮዋ ምንም አይናገሩም፣ ዱዳ ይሁኑ ዝምተኛ እንጃ:: አይናገሩም:: ሁለታችንንም አተኩረው አይተውን የከፈቱትን የአጥር በር ሳይዘጉ ዝም ብለው እሉበት ቆሙ:: ለምን ቶሎ እንዳልዘጉት አላውቅም:: ስገላመጥ አይቶ 'ተያቸው ይዘጉታል አሮጊቷ ደንቆሮ ናቸው' አለኝ:: ደንቆሮነትና በር አለመዝጋት ምን አገናኛቸው? አልኩ ለራሴ:: የአጎቱ ቤት በጣም ዘናጭ ነው:: ጭስ ማውጫ ምናምን ሁሉ አለው:: ለምን ጭስ ማውጫ አስፈለገ? ምናምን ስል ነበር ግን አልተናገርኩትም ምክንያቱም ብዙ የማልረዳቸው ነገሮች አሉ:: ሳሎኑ በሚያምሩ ቀያይ ሶፋዎች ተሞልቷል:: ደ'ሞ አጎቱ ዲግሪ አግኝተው በትልቁ የተነሷቸው ሁለት ፎቶዎች አሉ:: ኃይለሥላሴ ያሉበት ሁሉ አለ......ሌላም ውጭ አገር ነጭ ፀጉር ካለው ፈረንጅ ጋር የተነሱት ምናምን እኔ ምን አውቃለሁ:: ውስጡ በሙሉ የፈረንጅ አገር ይመስላል:: የሙዚቃ ማጫወቻው ቴፑ ርብራብ ነገር ነው ሲያምር:: ወላ መርካቶ እንደዛ ዐይነት አላየሁም:: ወደ ጀርባ በመስኮት ሳይ አስፋልትና አትክልት ነው:: አትክልቱ መሃል ሁለት ውሾች አሉ......ሁለቱም በሆዳቸው ተኝተው ያዛጋሉ:: ውሾቹ ስሙን የማላውቀው ደስ የሚል ቀለም የተቀባ ሚጢጢ የእንጨት ቤት

አላቸው:: እቤት ገብተን ግማሽ ሰአት ያህል ተቀምጠን ብጠብቅ ብጠብቅ እሱ ይኖራሉ ያለኝ ሰዎች አልመጡም:: ወደ ጓዳ ገብቶ ሻይና ቡና እንዲመጣልን አዘዘ:: ከእሱ በተቀር ሌላ ሰው ባለመኖሩ በአንድ በኩል ቅር አለኝ እና ትንሽ ፈራሁ:: አለመኖራቸው ደ'ሞ ትንሽ አዝናናኝ:: የት ሄዱ? ስለው......ላንጋኖ መሰለኝ አለኝ:: ላንጋኖ? ስለው.....አዎ ላንጋኖ አለኝ:: ላንጋኖ ምን እንደሚመስል ለማሰብ እጥራለሁ:: አንዴ መተሃራ ለመሄድ በናዝሬት ስናልፍ አባቴ በእጁ ወደ ቀኝ የሚታጠፍ አስፋልት ለእኔና ለእማማ እያሳየን 'ሶደሬ በዚህ ነው' 'ላንጋኖ በዚህ ነው' ሲል ነበር:: ዝም ብሎ ላንጋኖ የሐይቁ ባለቤት ሰውዬ ስም ይመስለኛል(ፊቱ ረዥም አገጬ ሾል ያለ፣ አፍንጫው ረዥም፣ አይኖቹ ትናንሽ፣ ፀጉሩ ገባ ያለ ከርዳዳ፣ ወርደ ጠባብ ረዥም ጥርሶች ያሉት እና ሲስቅ ከእነዚህ ጥርሶቹ ላይ ብዙ ንፁሕ አረፋዎች ይፈነዳሉ) ግን መንግስት ሐይቁን ይወርሰውና ምናልባት 'መስከረም አንድ' ሐይቅ ምናምን ይባላል እያልኩ ሳስብ ነበር:: ከዛ አብርሃም ፊልም እንይ ምናምን ብሎ ቴሌቭዥን መጎርጎር ጀመረ:: የቴሌቭዥኑ ትልቅነት የሚያከለው! አሰራሩን አሳየኝ አልኩትና የሆነ ትልቅ የሳጥን ስንጥር ውስጥ ትልቅ ካሴት የመሰለ ነገር ማስገባት ነው እና አሳየኝ:: ልዩ ነገር መስሎኝ ነበር......በቃ ይሄ ነው? ምናምን ስለው ታዲያ ያንቺ አገር ምን ሰራች የሰራችው አገርህን እወቅ ጫማ ብቻ ነው......ምናምን አለና ሳቀብኝ:: ምን ያስቃል ምናምን ስለው......ይቅር ሌላ ነገር እንጫወት ምናምን አለና አንድ ካሴት ከተተ:: በሙሉ እንግሊዘኛ ነገር:: የእንግሊዘኛ ንግግር አይገባኝም፣ የሕንድ ፊልም የምወደው ከስሩ የሚፅፈውን ጥቂትም ቢሆን ስለማነብ ነው:: ለምን ለፊልሞቹ በአማርኛ ትርጉም አይሰሩላቸውም እላለሁ አለ አይደለ 'ዋት ሃፕንድ ቱ ዩ' ለሚለው እንግሊዘኛ 'ምን አባሽ ሆንሻል' ምናምን ብለው የሚተረጉሙ ምናምን ሂሂሂ:: አቢቲ የሚያሳየኝ ዋርነር የተባሉ ወንድማማቾች[170] የሰሩት ፊልም ነው:: የተዘባረቀ ነገር እየሁ:: በቃ የማያቸው ሰዎች አክተሮቹ ምናምን ይሮጣሉ ይተኩሳሉ ይሳሳማሉ:: ታሪኩ ግን አልገባኝም እሱ ፌንት ሆኖ ያያል......ስለዚህ እኔ ሻይ እየጠጣሁ ዳቦውን ሁሉ ጨረስኩት:: ከዛ ይባንንና እጄን ይይዘኛል......ያቅፈኛል......ሲኒማው ውስጥ ሰዎቹ ይሸሻሉ፣ ይስቃሉ፣ ከዛ እነሱን ለመምሰል ዓይነት አጅሬ እዚህ እኔን ይስማል ከዛ ፊልሙ ውስጥ ሰዎች ይሮጣሉ፣ መኪና ይቃጠላል የቆሰለ ሰው ይጮሃል አምቡላንስ ያደነቁረናል ሻወር ይወስዳሉ (አብርሃም እንደ አክተሮቹ አብረን እንታጠብ እንዳይለኝ ብዬ ፈራሁ):: ሁለት ጊዜ ያህል ስልክ ሊመልስ ተነሳ:: ስልክ ይመልስና መጥቶ ያቅፈኝና እላዬ ላይ አለ አይደለ ሶፋው እንዳልተመቸው ሁሉ እንደ ጨዋታ አድርጎ ይወድቅብኛል ምናምን:: መታቀፍ አስኝቶኝ ነበር:: ማሰቡ ያሳፍረኛል ደ'ሞ......ከዛ እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ በድፍረት አቀፍኩት......ጨለማ ቢሆን ኖሮ አልፈራም ነበር:: ብፈራም ግን አለ አይደለ ለምን የሆነ ቀሽም እሆናለሁ በሚል ምናምን አቀፍኩት:: ይገባኛል ግን እንዳልገባው ውይውይውይ ምናምን ስለው ሶፋው ላይ እንደ መንጋለል ምናምን ነገር ሳደርግ ሹራቤን ወደ ታች እየጎተተ ደረቴን ይስመኛል......ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጇን ራቁት ጡቴን ከእሱ ጋር አብሬ አየኋት:: ያፈርኩት ማፈር:: ምላሱ ጥቁር ጠቃጠቆ አለበት......ማድያት ነገር አለበት: ምላስ ላይ ማድያት ይወጣል እንዴ? እያልኩ ሳስብ እንደ ጨቅላ ይመጠምጠኛል:: ነቅዬ አልጥለው ነገር:: የቀሚሴን እንገትጌ

170 warner brothers= የፊልም ስሪ ካምፓኒ(አ)

እያሰፋ ሊያንቀኝ ሁሉ ደረሰ:: እና ሁለመናዬን ሊደክመኝ ሲጀምር ውስጤ የሆነ የሚያስፈራ ነገር ሲሰማኝ ቶሎ በፍርሃት ከተጋደምኩበት ገፍቼው እነሳለሁ:: ታዲያ በአእምሮዬ በችኮላ የሚመጣው ቤታችን ጓሮ የምናደርገው ስድ ነገር ምናምን ነው:: እሸሻለሁ:: ልክ ሁሉን ነገር እንደረሳሁ ነገር:: ግን አላመልጥም እንደገና ይጋደምብኝና ስፈራገጥበት ትንሽ ይቆይና በትርምስ መሃል እግሮቼን ከፍቶ ሲገባ ልቤ ስልብ ማለት ልትጀምር ስትል እገፋውና ለአፍታ ተጋድሞ ይነሳል:: ከዛ ይስቃል ምናምን:: እንደውም በቃ ቤቴ ልሂድ ምናምን ስለው...... አለ አይደለ ምን ማለትሽ ነው እንደዚህ የምትይው ምናምን ብሎ እንዲቆጣኝ ታዲያ እንሂድ ስለው ትንሽ ትንሽ ተበሳጨብኝ:: ከዛ ሲበሳጭ ፊቱ ደ'ሞ ወዝ ለብሶ ደስ አለኝ:: ሂጅ ምናምን ብሎ አለ አይደለ ትንሽ እንዲገፋፋኝ......

ስመመን ቀስ በቀስ እንደ ሙቅ ወንዝ በቀስታ እንደሚወርድ ወደ ማላውቀው አገር ሲገፋኝ ይሰማኛል::

ውስጤ እንደ ዳሎል ይነዳል......

ማርያምን......

***(ቢመጡ ባይመጡ......)***

ብዙ መተቃቀፍና መዳራት ያለበትን ፊልም ሁለተኛ ላይ ሊያሳያት ስላሰበ እንዳትበረግግ አውቆ አዘገየው:: ወደ ፊት የሚመጣውን ሊያሳያትና ሊያለማምዳት ዓይነት የመጀመሪያውን ፊልም እያዩ በየመሃሉ እያቀፈ ይስማታል:: እንዳልገባው እንደ ረሳ ሁሉ ሌላ ሌላ እያወራት ከጭኖቿ መሐል ግራ እጁን አያወጣም::

«አንተ ሰው ቢመጣስ?» ትላለች ደጋግማ::

«አይመጡም:: ቅዳሜ ቅዳሜ ላንጋኖ ናቸው»

ስለ ላንጋኖ አተኩሮ እንደሚያስብ ሁሉ ዝም አላት::

○

ሁለተኛው ፊልም ራቁት ወንዶችና ሴቶች የሚበዙበት ነበር:: ያኔውኑ ፊልሙ እንደ ተጀመረ የሚያስጠላ ስድ ስድ ነገር ማድረግ ጀመሩ:: አፍሬ ዓይኖቼን ስከድን አብርሃም ደ'ሞ በግድ ግለጪና እዪ እያለኝ ዐይኖቼን ከድኜ በመስማት ብቻ ፊልሙን እያለሁ:: የወንዶቹ ድምፅ ያስፈራል የሴቶቹ ያሳፍራል:: እምቢ ስለው ጭኑ ላይ ጎትቶ አጋድሞኝ ዓይኔን እንደ ጨፈንኩ በቃ ጡቶቼ እስኪፈርጡ ያሻቸዋል ሌላ ስራ የለውም? እላለሁ ለራሴ እኔ ደ'ሞ ያመኛል ተው ብለው አይሰማም:: ከዛ እግሮቼ መሃል ገብቶ እንደዛ ነገር ሲያደርገኝ ልቤን ነስቶኝ እግሮቼ እጆቼ ደክመው ወገቤ ሶፋ ላይ ጭንቅላቴ ደ'ሞ ወላ ወለል ላይ ማለት በቃ ተዘቀዘቅሁ ከዛ በዛ በቪዲዮው ሴቶቹ ይጮሃሉ በቃ ግራ ያጋባል ሲኒማው ውስጥ ያለሁ መሰለኝ የሆነ ላስቬጋስ ምናምን ያለሁ በቃ እኔ የእነሱ የገደል ማሚቶ የሆንኩም ይመስላል ወይም እነሱ የእኔ የገደል ማሚቶዎች ደስ አለኝ ደ'ሞ ፈራሁ......ግን እምቢ ማለት አልቻልኩም በደከሙ ዓይኖቼ ቀና ብዬ

ሳይ ቀሚሴ ሁሉ ተበታትኖአል......ወይኔ ጉዴ እያልኩ ሳስብ ደ'ሞ እሱ የነገረኝ ጃምፕ የሚያደርጉት ቡንጊ ጃምፐርስ ይታዩኛል በሃሳቤ ለመሆኑ ሴቶቹ ቀሚስ ለብሰው ነው የሚዘሉት እላለሁ......ከዛ ደ'ሞ ትንሽ ትንሽ እዚህ ባልመጣሁ ኖሮ እላለሁ......

## 'ጉዴ!' አለች ዘፋኝ"

«ለምን ወደ ሌላ ክፍል አንሔድም?» አላት::

መላ ሰውነቷ የደነዘዘ በስሜት የተገረፈ ይመስላል:: አይኖቿ ዕንቅልፍ እንደያዛቸው ሁሉ ተገርብበው ተከተለችው:: ፊቷ ሕልም ውስጥ ያለ ይመስላል:: አታየውም:: እሱ እያያት ፈገግ ይላል:: እምነቷ እጆቹ ውስጥ ናት:: ዓይኖቿ ተሰብረው የሚያብለጨልጭ የጣውላ ወለል ያያሉ:: ግን ደ'ሞ አያዩም:: የሚያዩት ስሜቷን ነው......ከእግሮቿ መሃል ወደ ማታውቀው ቦታ የሚፈሰውን:: ወሎ ሠፈር አይደለችም:: ኢትዮጵያዊም አይደለችም:: የሚነድ ስጋ ናት:: ገላዋ የሚመጠው ነገር ይፈልጋል:: ሰማይና መሬት በርደዋል:: የሚያድናት ትኩሳት ትፈልጋለች:: ገና ሌላ ክፍል እንደገቡ የተነጠፈ አልጋ ላይ ወደቁ:: የተቻኮሉ የተንገበገቡ እጆቹ የደረቷን ስጋዎች ይጐትታሉ:: ዐይኖቿን ስትገልጥ ሁለቱም ራቁታቸውን ናቸው:: እላይዋ ላይ አጎንብሶአል::

«ጉዴ!» አለች::

ቀላል ጉዴ አልነበረችም:: ወደ ሆዷ ነው የተናገረችው......ሻይና ዳቦ ወደ ሞላው ጨለማ:: ይህቺ 'ጉዴ!' የሰራችው የመሬት መንቀጠቀጥ ልጅቷ ከተኛችበት አልጋ ስር ጀምሮ በጠቅላላ አፍሪካ የተሰማ ነገር:: እንደ ኮክ ተከፍላ መሃሏ በጠጠር ምትክ እሳት የያዘች ጉዴ! በዚህች ጉዴ! ንዝረት የቪክቶርያ ሐይቅ አዞዎች ከተኙበት ለአፍታ ባነኑ:: ሰፋፊ ዓይኖቻቸው ሊመሽ የጀመረ ሰማይ ላይ አሞራዎች እየቆጠሩ: አንድ ጆፌ ሁለት ጆፌ ሶስት ጆፌ......

ውሃው እንደ ወተት ነበር......

የሻላ ፍላሚንጎዎች አዳኝ እንዳስደነገጣቸው ሁሉ ከሰፈሩበት ተነስተው ሰማዩን በደም ቀለም ሞሉት......ጥቂቶች የተኙበትን ጥቁር ግራር ሽፍነው ያስባሉ: አያመልጡት ነገር አያመልጡት ነገር አያመልጡት ነገር......

ከአባያ ሐይቅ ጠዋት የወጣ በኑግ ዘይት የተጠበሰ ድንቡል ዓሣ ከተኛበት ነጭ ሰሃን ላይ ለአመል ተላወሰ:: የሚበሉት ሰውዬ አቶ ጆኒ ግሪንበርግ ሹካቸውን እየመጠጡ አላስተዋሉም:: ሚስታቸውም ሻሮን እንዲህ ሲሉ: ድሬዳዋ መጋላ ጫት የሚቅመው ሱሌይማን ሰማቸው: 'አሣን ከነሕይወቱ መብላት ደስ አይልም?' ሱሌይማንም በቦዙ ዐይኖቹ:

'ምን አልሽ እማማ?'

የኩፉ ፒራሚድ የጎኑ ስፌት ተተርትሮ ለአፍታ ወደ እንብርቱ የፀሐይ

171 ምናልባት ከአስቴር አወቀ አንዱ የዘፈን ግጥም ላይ የተወሰደ(አ)

ብርሃን አስገባ......

ታላቁ ሙዚቀኛ ከያሬድ ትምህርት ቤት ጀርባ ከአልጋው እንደ ተነሳ በእንቅልፍ ልቡ ለመጀመሪያ ፒያኖ ሲነካ የወጣው ድምፅ 'ጉዴ!' ነው......

የድንግልና መዝገብ ጠባቂ መልአክ ደብተሩን አውጥቶ ኢትዮጵያን ፈልጎ አዲስ አባን ፈልጎ ጨርቆስን ፈልጎ የልጅቷን ስም ሰረዘ......ከስሟ ፊት ለፊት በግዕዝ 'ጉዴ!' ብሎ ፃፈ......

አገልጋዩ: 'ምን ላድርግ?' ሲለው

'እጃቸውን ወደ እኔ አቅጣጫ ሲዘረጉ ብታይ እንዳላየ ሁን፣

ሲጮሁ ብትሰማ እንዳልሰማ ሁን፣

ተበሳጭተው ቢነዱ፣ ጢሳቸው እዚህ ቢሸትህ ያላሸተትክ ሁን፣

ብትችል የሞተ ምሰል፣

ይሄን ሁሉ ያልኩህ ካልሆነልህ ራስህን ከሰማይ ወደ ምድር ጥለህ እግሬ ተሰብሮ ታምሜአለሁ ብለህ ተኛ፣

ገባህ ከርፋፋ?......'

○

የሚያምር መኝታ ቤት ነው:: አልጋ ላይ ገፍቶ ጣለኝ አለ አይደለ በጣም ሳይሆን......ዐይኖቼን በፍርሃት ጨፈንኩ:: አልቅሽ አልቅሽ አለኝ:: የስሜት ሞገድ አስሮኝ......የሆነች ምክንያት በደንብ የማትገባኝ በትንሽ ቀዳዳ......ጩልቅ ብላ ገብታ......የቀዳዳዋ ጠባብነት......ወይኔ እማዬ ምንድነው እያልኩ አለ አይደለ በቃ ሐብቴን ላጣ እንደሆነ......እግሮቼ መሃል ተጨብጦ እንደቆየ ሽልንግ የሚሞቅ ለስላሳ ነገር ይጫነኛል:: እሱ ፊቱ በወዝ ተሸፍኖ ይለፋል:: አለ አይደለ ዓይኖቹ ፈጠው ነበር:: ዓይኖቹ ሲፈጡ በቃ እንዲህ ይፈጣሉ ቧ ምናምን:: ዓይኖቼ ፈጠው የሚያዩት አንድ ቦታ ነው......እዛ ኮመዲኖ አለ እዛ አንድ ቴፕና አንድ የተከፈተ ካሴቱ የወለቀ ጥቁር ወክማን አለ እዛ ግድግዳ ላይ ሬክላም አለ......የሚያስፈራ መነፅር ያደረገ ሰውዬ እሱ ላይም 'ተርሚኔተር' የሚል ፅሑፍ ያለበት......የልጁ የግራ ጡቱ ጫፍ የዛገ አስር ሳንቲም ይመስላል:: ወደ ጆሮዬ ያጎነብስና 'ነፅዬ' 'ነፃነትዬ' ይለኛል:: ደረቱ ላይ ከመሃል አንድ አራት ፀጉሮች አሉ:: የፈራሁት ደረሰና ጮኽኩ:: የፈራሁት ነገር እንደ ሆነ ገባኝ:: ስጮህ አፌን በእጁ ያዘኝ...... አንጎሌ በተከታታይ በተለያዩ ሰዎች ምስል ሞላ: እማማና እማማ(ጋቢ ለብሳ ለፀጉሯ ውሃ ሳፈስላት:: ውሃው ቀይ ነው) ክርስትና እናቴ ዘውዲቱ (ስትጎነጉነኝ፤ ጣቶቿ ብርማ ይሆናሉ) በር የከፈቱልን አሮጊት እንኳን አልቀሩም(እሳቸው 'አንቺ ልጅ! አንቺ ልጅ!' ይሉኛል):: በአፉ አፌን ዘጋኝ:: አፉ ውስጥ ጮኽኩ፣ ከዛ በቃ ያለሁበትን ረሳሁ:: ስባንን አብርሃም ክፍል ውስጥ አልነበረም:: ከእንሶላ ያልተያያዘ፣ በፍራሽ ያልተነከሰ ብርድ ልብስ እንደ ነገሩ እላዬ ላይ አለ:: አልቦኛል......ሁለመናዬን አልቦኛል:: ራሴን ዳበስኩና ከዛ አለቀስኩ አለቀስኩ:: ተገድጄ እንደ መጣብኝ ሁሉ......የሰፈሩ ሰው በሙሉ ኮሪደር ላይ ተደርድሮ የሚጠብቀኝ መስሎኝ መታጠቢያ ቤት እንኳን መሄድ ፈርቼ ነበር......

*(ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ)*

በውስጥ ልብስ ብቻዋን አልጋ ዳር ተቀምጣ የምታስብ ትመስላለች:: ወደ ሳሎን ስትመለስ ሳሎን ሶፋው ላይ ልጁ በጀርባው ተኝቶ አይኖቹን ከድኖ ስለ አርስጣጣሊስ ወይም ሶቅራጥስ የሚመራመር ይመስላል:: የአይኖቹ ኳሶች ሽፋሳቸው ስር ይንቃንቃሉ:: የሚያስፈራ ነገር አላቸው:: ወደ ቲቪው አየች:: የቪድዮው ክር አላለቀም:: እየጨረሰ ነው:: መልዕክቱን አድርሶ የተዋንያኖቹንና የባለጌዎቹን ስም በቢጫ ቀለም እየፃፈ......ወደ ላይ እየጠመጠመ:: ጉንጩ ላይ የፈሰሱት የልጁ ብግሮቹ እንደ እርጥብ ብይ ይብለጨለጫሉ:: ቀስ ብላ ጉኑ ተቀመጠች:: ለማቀፍ እየፈራች:: ቀድማ ማቀፍ አለባት? አቀፈችው:: እሱ ብዙ አይናገርም:: አንድ የጎደለ ነገር አጋጥሞት እሱ ያስጨነቀው ይመስላል:: አንድ እጁን ከተንዘላዘለበት ስባ አንስታ ታሻሸዋለች:: አይኖቹንም ሳይገልጥ እየዳበሰ እጁን ከእጇ አላቆ ወደ ጭኗ ውስጥ ይሄዳል......ከዛም......ጎንበስ ብላ ደረቱ ላይ ፊቷን አነጠፈች......ዓይኖቹን ገለጥ አድርጎ መሃል አናቷን እየሳመ......ስታየው ለራሱ በሚመስል ዐይነት ፈገግ አለ......

○

ከመኝታ ቤት ስመለስ ሶፋ ላይ ተጋድሞ ዐይኖቹን ጨፍኖ እንዳልሰማኝ ሁሉ ስጠራው ዝም አለኝ:: ከገበያ ሸንኮራ ገዠቼ የመጣሁ እንኳን አልመሰለውም:: ቀና ብሎ እንዲያቅፈኝ ነበር የፈለኩት:: ዓይን ዓይኔን እያየኝ እንዲያቅፈኝ፣ እንዲያቆላምጠኝ......በቃ አቃቅፎ አንገቴ ስር እንዲተነፍስ:: ብቻ እንደ ልጅ እንዲያደርገኝ ነበር የምፈልገው:: ምክንያቱም በትክክል ምን እንደሆንኩና እንዳደረኩ አይገባኝም:: ብርድ ብርድ ይለኛል:: መታቀፍ የሚያስፈልገኝ ይመስለኛል:: ፍሬዬን ጥዬለት አለ አይደለ:: ምን ይፈልጋል ምናምን:: እና ደ'ሞ የፍሬ ዓይነት ያለው ይመስለኛል......አስቀያሚ ፍሬ ይኖረኝ ይሆን? እንዲያቅፈኝ አይዞሽ እንዲለኝ እፈልጋለሁ......እንዲዳብሰኝ እንዲያቆላምጠኝ ምናምን:: ለምን እንደሆነ እንጃ......ሆኖ የማያውቀው በውስጥ እግሮቼ መሃል በሆዴ ላይ የማያቋርጥ ቀዝቃዛ አየር የሚያልፍ ይመስለኛል......የሆነ ባዶነት መላላት ይሰማኛል አለ አይደለ የተፈታ የተተረተረ ቋጠሮ ነገር እና ድንገት ቆሜ ቶሎ ቶሎ ብራመድ ብንቀለቀል ሁለመናዬ ከውስጤ እየተንጠባጠበ የሚረግፍ ነገር ያለ አይነት ይመስለኛል:: የሕሊናዬ ጆሮዎች ያስታውሳሉ ያዳመጡትን ቅድም ምናምን አብርሃም ሲያለከልክ የሰሙትን 'ነፃነት! ነፃነትዬ! ነፂዬ! ነፂዬ!' ሲለኝ:: ድምፁን: የሚያሳዝን የምጣፍጥ የሚያስቅ የመሰለውን:: ታዲያ ለአፍታ አዲስ ሰው መሰለኝ:: እኔ ራሴ እንዳጎደልኩና እንዳጠፋሁ 'ምን ሆንክ?' እለዋለሁ...... እደገፈውና እጁን ደረቴ ላይ አደርጋለሁ......ጎትቶ ወደ መኝታ ቤት ይወስደኛል ከዛ......ቤቱን አስተካክለን ስንቀመጥ ቀሚሴን እንደ ቤቱ በር ይገልባል:: ዝም የማለት በሽታው ቢሻለው እያልኩ አለ አይደለ ምናልባት የፈለገውን ነገር እስኪያገኝ መልፋት አለበት መሰሉኝ:: ከፍርሃቴ የተነሳ ገላውን አላየውም:: ከዚያ ይደባብሰኝና መኝታ ቤት እየጎተተ ይወስደኛል:: አንገቱ ላይ ተለጥፌ

በከፊል እያለቀስኩ(ደስ እያለኝና እያስፈራኝ):: ባሌም ይመስለኛል:: አንዳንዴም አስደንጋጭ ስሜት እንደ ጎርፍ ነገር ከውስጤ ይመጣና ገላዬ ይንቀጠቀጣል ወይኔ ወይኔ ወይኔ እያልኩ......የእጄ ጣቶች ሁሉ ሽባ ይሆናሉ:: እግሮቼም ያለ እኔ ፈቃድ ይንዘላዘላሉ ሁልጊዜ እንዲህ ሆነው የሚቀሩ እየመሰለኝ በጣም እደነግጣለሁ......ለዘላለም የሚበርድ የማይመስል ነገር......ታዲያ መጮኽ እፈልጋለሁ:: እዚሁ አንድ ነገር ሆኜ ቤቴ ሳልደርስ የምቀር እየመሰለኝ ምናምን:: እናቴ በአንዴ ትናፍቀኛለች:: አባቴ ያለ እኔ ከእማማ ጋር ለብቻው መተሃራ ሲወርድ እንደ ሕልም አያለሁ......በደብረዘይት አቧራ ሜዳዎች ላይ ሺህ ጠሮ ነፋሶች በሰልፍ ወደ ናዝሬት ይሄዳሉ ከመሃላቸውም ድምፅ ይወጣል ቋንቋ የመሰለ:: እምእምእም ዐይነት:: ልተረጉም እጮኻለሁ:: የወሎ ሠፈርን ረዥም መንገድ እና ወደ ጨርቆስ የሚያወጣውን ዳገት በምን እወጣዋለሁ? ቡልጋርያን በምን እግሬ አልፈዋለሁ? እስባለሁ የሚረባ የማይረባውን እንዲህ......

### *(የራስን ፍርፋሪ መብላት ግድ ነው ማን አለ?)*

እንዳቀነባበረው ሆኖለታል:: ሴትን ማስጀመር እንዴት ድንቅ ስሜት ይሰጣል? እንቅልፍ ጠርጎ እስከ ሚወስደው ፊቱ ፈገግታ የተዘረጋበት ነበር::

ለጓደኛው ለስንዱ ወሬው እንደ ጉንፋን በተጋቦ ይደርሳታል:: ጀብድ ሲሰራ በየትም በየትም መወራት አለበት......የተጋቦው ደሞ አሪፍ ነው:: እያለ የለም:

«የሰማሁት ምንድነው? ነፃነትና አንተ......» ብትለው

«የወሬኞች ወሬ ነው......ከጤይባ ጋር ምን ጉዳይ አለኝ......እሷ ገና የምትመነኩስ ናት» ይላታል......ጀብዱን በቀጥታ ለስንዱ ባይሆንም (በእፍ አዙር እንደሚደርሳት እያወቀ) ወንድ ነውና ለሌላ ካላወራ ወንድ ምኑ ወንድ ነው? እንዴትስ ወነደደ ይባላል?

### *(ውይ!)*

ከወር በኋላ ዓይነት......ብቻ ቆይቶ ከትምህርት ቤት ስመጣ አንድ ግሮሰሪ ፊት ለፊት ቆሞ ከጓደኞቹ ጋር ሲያወራ እንዳላየኝ ሁሉ ፊቱን አዞረ:: ጎትጉቼ ነው ሰላም ያልኩት:: 'ውይ! አላየሁሽም' ምናምን አለና ዋሸኝ......ግን አልገባኝም:: አለ አይደለ አመንኩት:: በኋላ ግን ቀፈፈኝና ደግሜ አሰብኩት:: እንዴት አጠገቡ ቆሜ ስሙን እየጠራሁት እንዴት አላየኝም? በሽቄ አደርኩ:: ማመን አልቻልኩም:: ከዛ ደ'ሞ ልጆች አለ አይደለ በዛ ዐይነት መልኩ ያዩኛል አለ አይደለ በፊት ያላደረጉት ጎረምሶች: 'ታዲያስ ነፃነት......ታዲያስ መቼ ነው ሺፍትሽ?('ለምን?' እላቸዋለሁ:: ፈገግ ብለው 'ሻይ ምናምን ልበልሽ':: ቂል አይደለሁ እኔ ወይ አልገባኝ 'እህ' እላለሁ::) 'ፊዚክስ አሪፍ ነሽ አሉ(ነግሬዋለሁ ለዛ ቀልማዳ ኬሚስትሪና ፊዚክስ እንደምወድ) ለምን አብረን አናጠናም?' ይሄ ሁሉ ሲሆን ቶሎ አልገባኝም:: ያ ባለጌ ያደረገኝን እንደነገራቸው አልገባኝም:: ደርቦ

ሊያዋርደኝ ካሳቀደ:: (ድርብ ድርብርብ አረፍተ ነገር እንዳለ፣ ድርብ ድርብርብ ውርደት ይኖራል) ስንት ዐይነት ወንድ አለ በከተማው እግዛቤርዬ?......

ወንድ ደ'ሞ እንደ ሴት 'ውይ!' ምናምን ሲል አያበሽቅም?......

○

ከሦስት ወይም አራት ሳምንታት በኋላ ከትምህርት ቤት ስትመጣ እናቷን ተናዳ አገኘቻት::

«አንቺ ያን ሳጥን ከፍተሻል?»

«የምን ሣጥን?»

«እዚህ ሳጥን ውስጥ ቆርቆሮ ነበር:: ቆርቆሮ ውስጥ ሽልንጐች ነበሩ:: ሽልንጐቹ ጠፍተዋል»

«ውይ! እኔ የት አውቃለሁ»

«እንግዲህ ቦታውን የምናውቀው እኔ፣ አንቺ፣ አባትሽ ነን:: እኔ ራሴን አልሰርቅም መቼም:: ስለዚህ ወይ አንቺ ወይ አባትሽ ናችሁ የወሰዳችሁት:: አባትሽ ደ'ሞ ቤት የለም:: አስቢበት»

«እኔን እንዴት ሌባ ታደርጊኛለሽ? አባባ ወስዶት እንደ ሆነስ?»...... በብሽቀት:: እናቷ እንደ እብድ አደረጋት......

«አባትሽ ምንም ባበሳጨው ሽልንጎቼን አይነካም፤ ለምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? አፍቅሮኛል:: ዛሬም አይጠላኝም:: አባትሽ አሁንም ይወደኛል አውቃለሁ:: የሚወደኝን አውቃለሁ:: ማንም ሰው ያፈቀረው ሲነካበት አይወድም:: ኑሮ ያንጫንጫል እንጂ:: ከእኔ የበለጠ የሚወደው ግን የለም:: መቀናናታችን ነው የሚያባላን:: እንዲህ አያደርግም እኔን:: ይሞታታል እንጂ:: በረሃ ለበረሃ እየዞረ ለአንቺና ለእኔ ነው የሚለፋው እኮ፣ አልሞላ አለው እንጂ:: አልሞላ አለው የእኔ ጌታ:: ግን አፌ አያርፍም:: የእኔ ጌታ ጠሙን ያድራል እንጂ እንዲህ አያደርግም:: እንደ ዘመኑ ልጆች መሰለሽ:: ይኼ ዝም ብሎ ነገር»

«ምን ይታወቃል? ጓደኞችሽስ?»

«በይ ዝምበይ......የእኔን ሽልንግ አይፈልጉም:: ያላቸው ናቸው»

ከእናቷ ጋር ብዙ መመላለስ አልፈለገችም......ፊቷ ላይ ፍርሃትና ግራ መጋባት አለ:: ለመተኛት ሔደች:: አልጋዋ ውስጥ ሆና እናቷን ለብቻዋ ስታወራ፣ ዕቃ ስታተራምስ ትሰማታለች::

*(ለንታና......)*

እኔን ያስጨነቀኝ የየቀኑ የእናቴ የሽልንግ ጭቅጭቅ ሳይሆን......መበሳጨቴ ነው:: የረገፈች አበባ:: መርገፍ አይቀርም፤ የእኔ ነገር ሳር ለሳር በየሜዳው የተበተነ ይመስለኛል:: ትንሽ ስርዐቱ እንኳን ከሌለው ቪላው እኮ ሳር ነው::

ስርዐት ካለው ጎጆው አዮቤልዩ ቤተመንግስት ነው:: አልቅሼ እጨርስና ብዙ ሳልቆይ ዕንባ በጉንጮቼ ሊወርድ ዐይኖቼ ላይ ቅርር ይላል:: እሱን እጠርግና እንደገና ሳስብ ዕንባ እንደገና ባይኖቼ ግጥም ይላል:: አንድ ማታ ላይ አብርሃምን ተለማምጬ ሰላም ብለው እንደ እንግዳ አለ አይደለ አይቶኝ እንደማያውቅ......

«እ......እ እንትና» አለኝ:: ከመሰሎቹ ጋር ነበር:: ከቆመበት ወደ እኔ ፈገግ ብዬ ጠራሁት:: ሲጠጋኝ ሌሎች እንዳይሰሙ ድምጼን ዝቅ አድርጌ እሱ ግን እንዲሰማኝ:

«ጨምላቃ ነህ» አልኩት:: በመገረም አየኝ:: አስተያየቱን ካየሁ በኋላ ዐይኖቹ ውስጥ እኔን በፍፁም እንደማይወደኝ ተገነዘብኩ:: እንዴት ቻለበት ግን ቲያትሩን?

ስሜ ሁሉ ጠፋውና 'እንትና' ምናምን:: ደም አያንተከትክም? ነፃ ነፂ ነፂዬ እንዳላለ:: ሳስበው ወደ ላይ ይለኛል::

ከእግር እስከ ራሴ አየር እንኳን የሌለበት ባዶነት ተሰማኝ:: ከባድ ነፋስ ቢነፍስ ገልቦ አንስቶ እዛ ባቡር ጣቢያ አንዱ የዛገ ቆርቆሮ ላይ ይለጥፈኛል:: ማርያምን::

○

ከሰደበችው በኋላ ሠላምም አይባባሉም እሱ ያደረጋትን ነገር ለእህቱ:: እህቱ ለጓደኛዋ:: ጓደኛዋ ለጓደኛዋ......ወዘተ:: ምን የሚወራ አለው? በኋላማ የደበቀቻት ጓደኛዋ መንበረ:

'ማንም ሲሰማ እንዴት ለእኔ አልነገርሽኝም......አብርሃም አጅሬ ጉድ አረገሽ?' አለቻት::

ነፃነት ከዳች:

'ምንም አላደረገኝም፣ አጅሬ ብሎ ደ'ሞ እሱ፣ በስባሳ ነገር' ብላ ካዳች:: 'ውሸት ውሸት አፍረሽ ነው፣ እባክሽ ስንጀምር ሁላችንም ክደናል' ምናምን ብላ መንበረ ሳቀችባት......

ድሮ ኮስተር ብለው በማክበር፣ በማፈርና በመቅለስለስ የሚያይዋት ወንዶች 'መስጠት' ጀምራለች ተብሎ እንትና እንትናና እንትና እንትናም፣ እንትና በገባበት ሊገቡ ሰላምታ አበዙባት::

ይሄ በመጠቋቆም የተላከባት ጅኒ ከዕንቅልፏ ያባንናታል:: 'ሁሉ ነገር ባይሆን ኖሮ' ትላለች ለራሷ:: ልታፈቅር ወጥታ ፈርሳ መግባቷ:: ልጆች በሚሰበሰቡበት ጎዳና ላይ ተረብ እንደ ጠራ ውሐ በሚፈስበት መልካም ቀን ለእናቷ ቡና እያፈላች ቤቷ ውስጥ በተገደገደ የዕጣን ወይም የሰንደል ጭስ ውስጥ አብርሃም የዋሻት ነገር ሁሉ በላይዋ ላይ እንደ ሞገድ ይገለበጥና የኮረዳነት ፀዳሏ የቆመበትን ድርና ማግ ያፈርሰዋል:: እናቷን ከተቀመጠችበት እያየች ለእሷም ከንፈሮቿን እየመጠጠች ልክ እንደ አንድ የሰፈሯ ዘባተሎ እንክዬ የዕጌዋን መምጣት ትጠብቃለች......

ቀነጀች።

እንደ ጀመረችው።

*(እንቅልፌ የት አለች? እንቅልፍ ሆይ የት ነሽ!?)*

በጨለማ እፍጥጬ የመጣሁበትን ትዝ የሚለኝን የቀዬ ጎዳና ሰብስቤ ሳስበው የልጁ ውሽት ይቀፈኛል። ልቤን ነስቶት እሱ ክንድ ላይ መቆላዘሜ ይቆጨኛል። እሱ ሲነካኝ በሰራ ገላዬ እንደ ድሬ ባቡር ይመላለስ የነበረውን ፆር ጠላሁ። ሌሊት ብተኛ ሁለት ሰዐቶች ነው። ድሮ ስምንት ሰዐቶች የማያጠግቡኝ። እናቴ ተኝታ ስታንኳርፍ ስለ ሽልንጉ ልታናግረኝ የምትጥር ይመስለኛል። አንዳንዴ አልጋዬ ላይ አይኖቼ እንደተበለጠጡ ግማሹ ሌሊት እንደዚያ ይነጋል። ለምን ይሔ ቀላል የመሰለ ገጠመኝ እንደሚያሳስበኝ አላውቅም። የእናቴን ትዝታና ታሪክ ሰርቄ፣ እንደገና ተታልዬ፣ እንደገና ተበላሽቼ፣ እንደገና ወሬው ተራብቶ......እኒህ ጉዳዮች ሁሉ እየተቀያየሩ፣ እየተባበሩ በተለያየ ጊዜ በተለያየ አጋጣሚ ነፍሴን በጭንቀት ጠምደው ይይዟታል። እናቴ እጅግ ዝምተኛ ሆናለች። ድምፅዋ ከፍታው እየቀነሰ፣ የወሬዋ ስፋትና ድምቀት እየጠበበ ነው የመጣው። ልጅነቷን እንዲህ የምትወድ አይመስለኝም ነበር። የማርትሬዛው መጥፋት ይኼን ጉድ የፈጠረው አይመስለኝም። እማምላክን እንዲህ አልመሰለኝም። ተቀምጬ ከንፈሮቼን እየመጠጥኩ በነሲብ ደብተሬን እየገለጥኩ ስበሳጭ። ግልፅ የሆነልኝ አንዱ ነገር ነፃነቴን አገኘሁ እያልኩ በወሎ ሰፈር ስኽራገድ፣ ከደካማ ውሽታም ጋር ስበላቀጥ፣ ለገሀር ሰማይ ላይ ስንሳፈፍና በአየር ላይ ስበር እንደ መቀስ እየተከፈቱ በሚከደኑ እግሮቼ መሃል......ቡፍ ባለ ቀሚሴ ጥላ ስር ገብቶ የተተከለ የነፋስ ጦር ነበር ያ ቀጣፊ......

○

የመጣው ይምጣ መቼም አልሞት ብላ ስህተቷን ለማስተካከል ተነሳች። ስህተትን ማስተካከል በኑዛዜ ይቀድማል። ድክመትን ከማመን ይጀምራል። የሚባለው እንዲህ ነው በፍልስፍናው። አንድ ቀን ከእናቷ ጋር ቡና እየጠጣች እያለች እየፈራች እየቸረች:

«አንድ ነገር ልንገርሽ እማማ» ትላታለች።

«ምን?» ዝቅ ባለ ድምፅ።

«አትቆጭኚም?»

«መጀመሪያ ንገሪኝ»

«አትቆጪኝም?»

«ለምን?»

«ብትናደጅስ?»

«ንገሪኝ»

እንዴት መናገር እንዳለባት ስታሰላስል ትንሽ ጊዜ አለፈ:: በመጨረሻ «ሽልንጎቹን እኔ ነኝ የወሰድኳቸው» አለቻት::

እናቷ በድንጋጤ አፏ ተከፈተ:: ለመናገር ሞከረች......አልቻለችም::

«ም.........ም.........» ብቻ::

***(ምምምምም)***

ለእናቴ ሌባነቴን ከነገርኳት በኋላ እምምምም አለችና በዚያው እምምምም ብላ ቀረች:: የተቻለው ነገር ሁሉ ቢሞከር ከአፍ እስከ ምላስ ስፔሻሊስት ያን ቀን የታጠፈ ምላሷን የሚያስተካክል ነገር ጠፋ:: ዱዳ ሆነች:: ምምም......ምም...... ምምም ብቻ:: ምምምም ቃሎቿ ሆኑ:: እዚህ ቀጨኔ፣ ኪዳነምህረት፣ እንጦጦ ወጣን፣ ደብረ ሊባኖስ ተሰደድን:: የሽልንግ መጥፋት ዱዳ ያደርጋል? ያለ አፍ ኦፕሬተር መሆን ደ'ሞ አይቻልም::

እናቴ አባቴን ስትጨቀጭቀው የምትጠላው ይመስለኝ ነበር:: አንዳንዴ በበሽታዋ ምክንያት ተቃቅፈው በዝምታ አንድ ላይ ተደብረው ሳያቸው፣ ቀድሞ እሰማው የነበረው የአፋቸውን እንጂ የልባቸውን ጩኸት እንዳልነበረ ገባኝ፣ አንጀቴ ይነዳል:: ቀድሞ ሲጨቃጨቁ ስሰማቸው አብርሃም እኔን የበለጠ የሚወደኝ ይመስለኝ ነበር:: አፍ አመንኩ:: ዞር አለብኝ የዕውነት:: ታዲያ ነገሮችን እንዴት ልረዳ ነው? መዋደድ መጥላት በድብቅ፣ እንትን በድብቅ፣ ፖለቲካ በድብቅ፣ ወደፊት የሩጫ ውድድር በድብቅ ሳይሆን አይቀርም አለ አይደለ በተዘጋ ማንም በሌለበት ስታድዮም በቃ ሳናየው በላይነህ ዲንሳሞ ማራቶን አሸነፈ ምናምን እንባላለን ወይ ተሸነፈ ከዛ ውጤቱን ያላመነ ቂል ነው ጤይባ ነው ብለው ይጠዘጥዙንና በቃ ፈርተን ቂል ላለመሆን ፋራ ላለመባል በቃ ሆሆሆ እንላለን:: የሚያስፈራ ነገር አለው:: እማማ ስታለቅስ አባቴ እንደ ወጣት ፍቅረኛ ደረቱ ላይ አድርጎ ግንባሯ ላይ እየሳማት ዐይኖቿን እየሳማቸው («አይዞሽ የእኔ እመቤት») ሲላት ምናምን ቢደኽዩም ሕይወትና ኑሮ እዛና እዛ ብትበታትናቸውም እንደሚዋደዱ አየሁ:: እግራቸው ስር ወድቄ ትንሽ ከብልጥ ፍቅራቸው አንዲት ጠብታ እዚህ መሃል እናቴ ላይ እንደ ዝናብ ጠበል ዱብ እንዲያደርጉልኝ መለመን ይቃጣኛል:: ማለት ከሁላችን አጋንንታችን ቢወጣ......በተለይ ለዛ ቀባጣሪ:: ግን እሱ አራዳ ሆኖ ሞቷል......ግን ፍቅርን መደበቅ ይሻላል ከመሸወድ አይደል ይመስለኛል:: ሽማግሌዎቹ ስታይላቸው ቢለይም ይበልጡናል:: በእናት አገርና በገርል ፍሬንድ የለም ዋዛ ምናምን ይሉ ነበር ሂሂሂ ግን አሁን ሁሉ ነገር ጂንስና ላስቬጋስ ነው:: እንደ እኔ ዓይነቷም ቂሎች እንዳፈር ነን......አይደል......የሁለት ሽልንግ መጥፋት ላያሳብድ ይችላል::

ጉዳዩ ሽልንግ አልነበረም:: የእኔም ብልግና አይደለም:: ሽልንጉ ሳይሆን የሚጠፋው ታሪክና ትዝታው ነው:: ከባድ የሆነው ለዚህ ነው:: እኔ ይሄ አይገባኝም ትንሽ ወፍ ዘራሽነት አለችብኝ መሰለኝ:: ታሪኩን የሚፈራ ዲቃላ ነው አይደል? ምክንያቱም አባቱን አያውቅም:: ዲቃላ ግን አይደለሁም ግን እንደዛ ይሰራኛል......

○

የነፃነት ነቅዐ ሕልዮዋ ባልጠበቀችው መልክ እየተለወጠ ነው......የማእድ ቤቷን ስራ ትሰራለች:: ታነባለች:: ታጠናለች:: በተለይ እተቀመጠችበት እየተወዛወዘች በረቀቀ ድምፅ የተውሶ ዘፈን ታንጎራጉራለች:: እናቷ በወረቀት ላይ ፅፋ ይሄንን ትላታለች: *እንዲህ የሚያምር ድምፅ ነበረሽ እንዴ? የእኔን ቀንሶ፣ እኔን ዱዳ ሲያደርገኝ የሚያምረውን ላንቺ ሰጠሽ? አስቴር አወቀ ጉድ ፈላባት በይኛ እነ ኩሉ ጉድ ፈላባቸው......አይዞሽ የእኔ እመቤት አታስቢ አትጨነቂ:: ያመጣብኝን እኔው እችለዋለሁ ወጣ ብለሽ ከጓደኞችሽ ጋር ተጫወቺ:: ያን ሰሞን ከዚህ ግቢ የማይጠፋው ልጅ ማን ነበር ስሙ? አብርሃም አዎ......እሀቱን ነው በደንብ የማውቃት:: የት ሄደ?* መልዕክቷ የተፃፈበትን ወረቀት እንደ መድኃኒት እያገላበጠች እናቷን ታያታለች:: ፊቷ ላይ ጥልቅ ሐዘን ይፈሳል:: የመገረም ፏፏቴ ያጥለቀልቃታል:: ማልቀስ ይዳዳትና ወረቀቱን ጨባብጣ ፊቷን በእጇ ትሸፍናለች:: የእናቷ ክንድ ትከሻዋ ላይ ያርፍና አስጠግቶ ያቅፋታል......

### *በተናዘዘበት አፍ ይዘፍንበታል፣ የሕግ አገሯ ልቡና ውስጥ ነው*

ሁሉ ነገር ያሳዝነኛል:: እማማ ትሙት ያሳዝነኛል:: በቃ አዝናለሁ:: ባስብ ባስብ የጥፋቴ ክብደት በደንብ አልገባኝም ማለቴ ቅጣቱ በዛብኝ:: አለ አይደለ ምን አደረኩት እግዛቤርዬን እያልኩ:: ልብ ሳልለው ደ'ሞ እንዲህ እያሰብኩ እዘፍናለሁ:: በተለይ ሙሉቀን መለሰን:: እናቴ ሁሌ ዝፈኝልኝ ትለኛለች:: እዘፍንላታለሁ......በተለይ 'ሰውነቷን' *አንበሳን በጡጫ እለው የነበረ* ምናምን የሚለውን:: የዘፈኑ ዝግታው ይማርከኛል የሆነች ክራር አለች ዘፈኑ ሲጀምር እሷ ክር ክር ክር ስትል ልቤ በቃ እዝዝዝዝዝ ዓይነት ነገር ይልብኛል......እንደ ሐዘን ነገር......ደ'ሞ ደስ ደብ የሚል ነገር አለው:: በቃ ያሳዝናል ደስ ይላል:: ከዘፈንኩ በኋላ እናቴ ተጠግታ ታቅፈኛለች:: የእናቴ ደረት እንዲህ ይመቻል? ጠረኗ ደስ ሲል......ውስጤ ይረበሻል:: በመገረም ራሷን ትነቀንቃለች *ይሄን ሁሉ ድምፅ የት አድርገሽው ነበር!* ምናምን እያለች:: ለእማማ ስዘፍንላት አቤት ደስ ሲለኝ:: ስትወዛወዝ ስታምር:: ጃርከ ላሳይሽ የልጅነቴን ትለኝና ቀሚሷን ከፊት ለፊት ከፍ አድርጋ ቂጧን እአ ታደርግና ከት ብላ ትስቃለች:: ልቤ በፍቅሯ ፍስስ ይላል:: በሐዘን ደ'ሞ እቀጣጠላለሁ::

ለመነጋገር እንዲያመቸን ትንሽ ደብተርና እርሳስ ሁልጊዜ ጠረጴዛ ላይ አለ ሁሉን ነገር እዛ ትፅፋለች:: መቼ ዕለት በቃል መናገር አፍሬ በትልቁ *እማማዬ ውድድ አደርግሻለሁ* ብዬ ፃፍኩላት:: ካነበበችው በኋላ ደብተሩን ልክ

እንደ ዱላ ጠቅልላ የውሽቷን ጀርባዬን ቸብ ቸብ አደረገችኝ፣ ጭንቅላቴን ቸብ ቸብ አደረገችኝ:: ሁኔታዋ ሁሉ ያሳዝናል አይደል 'እወድሻለሁ' ብዬአት አላቅም በፊት አለ አደለ ዝም ነው የምንባባለው ከዛ ስላት ዕንባዬ መጥቶብኝ መኝታ ቤት ገባሁ ከዛ ገባት መሰለኝ አብራኝ መጣችና አልጋ ላይ አቅፋኝ ተቀመጠች በቃ አለቀስኩ በጣም አለቀስኩ:: ለምንድነው የሚወደንንና የማይወደንን መለየት ያልቻልነው......

ቲያትር ከዕውነት ትበልጣለች......

ቲያትር ከዕውነት በለጠች ማለት ነው:: በቃ ያኔ አለቀስኩ:: እሷ እማማ እንደ ድፎ ዳቦ ትሸታለች:: እማማ እንደ ሕብስት ምናምን ትሸታለች:: ሳልነግራት አንገቷን ሁሉ አሸተትኩ ፀጉሯን አሸተትኩ ዓይኖቼን ጨፍኜ ትከሻዋን ምግምግ አድርጌ አሸተትኩ ልብሷን ሁሉ እየገረመኝ......ከዛ እሷ ያለችበት አላለቅሳትም ካሰኘኝ እውጣትና ተደብቄ አለቅሳለሁ እንጂ ስል እሷ ደ'ሞ ነቄ ናት ታየኛለች ታየኛለች ግን ልትጠይቀኝ አትፈልግም ግን ከሠፈር ልጆች ጋር እንድጫወት ትገፋፋኛለች ደብተር ስባ ትዕፍልኛለች: *የቀልዬ ልጆች ጥሩ ናቸው ለምን እነሱ ጋ አትሆኚም ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው ደ'ም ለመሆኑ ኮረሪማን ታማ ጠይቀሻታል? አየሽ ብዙ ጥሩ ልጆች አሉ* ከዛ አንብቤ አየኋት:: መሞት እንደ ፈለኩ በቃ ያወቀች መሰለኝ ማለት ሌላ ሌላውንም ያወቀችብኝ መሰለኝ:: እንዲህ ሲመስለኝ ከዚህ የበለጠ ብቻ ብቻዬን ስሆን አለቅሳለሁ:: አብርሃምን መግደል ብችል እገለዋለሁ እላለሁ በልቤ:: ሳስበው ደሜ ይፈላል:: ግን አገሩ የሕግ አገር ነው ይባላል:: ተባለ እንዴ? ጉድ እቴ:: በፀሎቴ በዳዬም በዳይ ይምጣበት ልበል እንጂ—በፀሎቴ:: በሰፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም ብዬ ልተርት እንጂ:: መስፈሪያ ቁናውንም ባላይ:: ሰፋሪም ባይኖር:: በተለይ ቪድዮና ቴሌቭዥን አስጠላኝ ነገር:: በቃ የፊልም ሬክላም በመንገድ ተለጥፎ ሳይ እንኳን ቋቅ ይለኛል:: ዜና የሚባል እንኳን አልሰማም......የእኔ ሕይወት ከዜና አይበልጥም? እ?......አንድ አሮጌ የፊት ልባሱ የተገነጠለ 'ፍቅር እስከ መቃብር' የተባለ መፅሐፍ ነበረኝ እዛ መደርደሪያ ላይ አሁን አሁን ሳየው ያስፈራኛል:: በጣም ኋላ ቀር በተባሉት የዱሮ ፊታውራሪና መሃልና አሁን በዚህ ዘመን የተማረ ወይም ያልተማረ ሰው ልዩነታቸው ምንድነው? እያልኩ:: አዲስ አባ ፋሽን የለበሱ ብዙ ፖለቲካ የሚያወሩ መአት ፊታውራሪ መሸሻዎች አሉ ግን ፓርቲና ግንባር ምናምን ናቸው ሕብረት አላቸው እና ይታያችሁ መአት ፊታውራሪ መሸሻዎች ድርጅት ሲኖራቸው ሲታጠቁና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምናምን ይኖራቸውና......በቃ ራሳቸውን አሪፍ አደረጉ ማለት ነው:: ከዛ ጆት ካላቸው ደ'ሞ አለቀ ደቀቀ የሚባለው ያኔ ነው:: ግን ብልጥ ስለሆኑ 'ይሄ ፍቅር እስከ መቃብር የሚያሳየው ያለፈውን የፊውዳል ሰዎች እንጂ የሌላ አይደለም' ይሉናል:: ሱሚ ነው:: ከዛ ትኬት አስቆርጠው ፈረንጅ አገር በአይሮፕላን ይሄዳሉ ከዛ ስለ ደሴትና ስለ ፋብሪካ ያወራሉ:: በዚህ አሪፍ የሰለጠኑ ይመስሉናል:: ሌላው ቀርቶ ጉራ የሚነፉበት ዕውቀታቸውን ለመገብየት የሚያነቡበትን መነፅር የሚገዙት ከፈረንጅ ነው:: ፊታውራሪ ቲያትረኛ አልነበሩም:: የአሁኖቹ በልብስ በቋንቋ እራሳቸውን ይደብቃሉ:: ስለ ውስኪ ያወራሉ ግን ፊታውራሪ መሸሻ ጠላ ብቻ ነው የሚያውቁት ወይም ማለፊያ ጠጅ......'ማለፊያ ጠጅ' ሲባል ለጊዜ ማሳለፊያ

የሚጠጣ ጠጅ ብቻ ይመስለኝ ነበር ድሮ......አሳሳዝንም አሳዝናለሁ አይደል:: መፅሐፉማ መፅሐፍ ነው:: ሲዘፈንበት እንኳን ስሰማ 'ፍቅር'......'ፍቅርዬ'......ፍቅር ምንትስ......ሲባል ስለ ፍቅር ሲወራ......'አይ ፍቅር' ሲባል 'ወይ ፍቅራችን' ሲባል:: ወይ አብርሃም ትዝ ሲለኝ መብል እምቢ ይለኛል:: የጉሮሮዬ በር ይዘጋል:: ዕውነት:: ግን 'ምን ታረጊዋለሽ' አለ ጥላሁን:: አንድ ቆሻሻ ሐይቅ ውስጥ የምዋኝ ቀጫጫ አሣ ነገር ነኝ:: ዓይኖቿ ትላልቅ የሆኑ አሣ ስዕል አይቼ እንደዛ......ግን ያው በፍቅር የተሸወደች ቂል አሣ......አንዳንዴ ሁሉ ነገር እንደዛ ይመስለኛል አለ አይደለ እባብ አዳምና ሔዋንን አስፎግራለች አይደል......በቃ ሰው ሲፈጠር ጀምሮ ከበለስ መብላት ጀምሮ በአሪት ዘሁልቁ አሪት ሰቀባጢሶ የሚባሉት እንደሚሉት እንቅፋት አለ እና ያው መቻል ነው ያለብኝ ደ'ሞ እማማን ማስጨነቅ የለብኝም:: እማማ ምን ባደርግላት ደስ ይላታል እያልኩ እስባለሁ::

አባቴ ከገጠር ሲመለስ ያቅፈኝና ይዞኝ እንደ ቆመ ይወዛወዛል:: በቃ ሲተነፍስ ሁሉ ጆሮዬ ላይ አሁንም አለ በቃ አፌን ይስመኛል፣ ዐይኔን ይስመኛል፣ ለምን ግራ ዐይኔን ብቻ ትስመኛለህ ስለው ከዛ ቀኙን ይስመኛል:: ልጅ አትሁኚ አሁን ጎበዝ መሆን ነው ምናምን ብሎ ገንዘብ ይሰጠኛል:: ከዛ ማዘርም ትሰጠኛለች.....ለእኔ መስጠት ሲፎካከሩ ደስ ይለኛል......ውስጤ ፍንድቅ ይላል:: መርካቶ ማርስ ሆቴል ጀርባ ወይ ብሄራዊ ጎን መንገድ ዳር መፅሐፍ የሚያነጥፉ ልጆች አሉ ከእነሱ ደስ ያለኝን እገዛለሁ:: ብዙ ጊዜ ብቻዬን ስለምሆን መንበረ ክሬዚ ልትሆኚ ነው እንዴ ምናምን ትለኛለች:: ሰው የሚበድሉ ክሬዚ አይባሉም ስማርት ይባላሉ:: ለብቻቸው ሆነው ለማወቅ የሚጥሩ ግን ክሬዚ ይባላሉ:: ሳስበው ይህቺን አገር የሚመራት ማነው? እላለሁ......

ግን እኔ ልብወለድ ማንበብ አላፈቅርም:: ከጀመርኩት ደስ ይለኛል እንጂ:: መአት ስለ ሳይንስ ምናምን ባውቅ እፈልጋለሁ ለምሳሌ አለም እንዴት ተፈጠረች? እንደዚህ የመሳሰለ:: ደ'ሞ ስለ ሰው ገላ:: ደደብነት በዘር ይመጣል ወይ? ተፈቅሬ አልተፈቅሬ እንደ ሆነ ለመረዳት ምን ያህል አንጎል ያስፈልገኛል? እሱንስ ለመለካት ማሺን መፍጠር ይቻላል? የአብርሃም የተንኮል ሳይኮሎጂ የመሰልጠን ምልክት ነው? ስለ እንስሳት ሕይወት ደ'ሞ ማወቅ እፈልጋለሁ:: እኔን ከአህዮች የሚለየኝ ምንድነው? ኮሜቶች ለምን ይወድቃሉ? ምናምን የመሳሰለ:: የእትዬ ቀለመወርቅን ወንዱን ልጅ ካሌብን ጠየቅኩትና ቆዪማ ምናምን ብሎ *ሂስትሪ ኦፍ ዌስተርን ሳይንስ* የተባለ መሸከም የሚከብድ ትልቅ መፅሐፍ ሰጠኝ......እና ሲሰጠኝ ወላ እህቱ አለች ግን አይፈራም ደስ በማይል መልክ አየኝ:: ወላ እኔ ፈራሁት:: በልቤ ተወኝ በእዝጌር በጨርቆስ ዐይነት አልኩ:: ሲያየኝ አይኖቹ የሆነ በግታ ነገር አሳዩ፣ ለመጀመሪያ እንዳየኝ ሁሉ:: አብርሃም ምን አደረገኝ? ምን አስቀምጠብኝ ሄደ? እሞታታለሁ እንጂ በማንም አልነካም አሁንስ የምፎገር መስሎሻል አዳሜ:: ሳይንስ ይቀራል እንጂ:: ግን መፅሐፌን ወሰድኩ:: የማይሆን ነገር የለም ብቻ የማያጋጥም......አለ አይደለ እንደዚሁ እሁድ እሁድ መርካቶ እሄዳለሁ:: የምገዛው ነገር ባይኖርም ከሠፈር ያርቀኛል እና ነገሮች አያለሁ:: በመንገድ ብዙ ነገር አያለሁ ታክሲ ውስጥ ብዙ ነገር አያለሁ:: አውቶቡስ ውስጥ ብዙ ነገር አያለሁ:: እና አንድ ቀን ጉድ አየሁ:: ያውም የሚያሳዝን:: የክርስትና እናቴን ልጅ ጋሼ ገዳምን መርካቶ እስፋው

ሆቴል በጀርባ ከዛች ቀሌታም ሎሚሽታ ጋር ተከታትሎ ሲገባ:: መጀመሪያ ለብቻቸው ያሉ ያልተያዩ መስሎኝ ነበር:: ግን ሰዎች አንድ ሰፈር ሆነው እየተዋወቁ ተከታትለው ሲሄዱ እንደማይተዋወቁ ዝም ሲባባሉ ትንሽ የሆነ ነገር ያስጠረጥራል አይደል:: ደ'ሞ የእሱ እየተገላመጠ ማየት:: ጠርቼው ሰላም ልለው ምንም አልቀረኝም ነበር መጀመሪያ:: ሳያዩኝ ተከተልኳቸውና እዛ ሆቴሉ ግቢ እውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘው አየሁዋቸው:: እጤ ዱብ አለ:: ተደበርኩ:: ለማንም አልነገርኩም:: ሚስቱ ማርታ ይሄን ብትሰማ ወይ እሱን ወይ ራሷን ትገላለች:: አዘንኩ:: ከዛ ትንሽ ሳስብ ማርታስ እንዲህ ጀምራ እንደሆነስ አልኩ:: ልክ በዚያች ደቂቃ ይሄን ባየሁበት ጊዜ ስንት መከዳዳት አዲስ አበባ ይሰራል? አልኩ:: ማርታ በጣም ቆንጆ ሴት ናት:: ዛሬ እንኳን አራት ወልዳ በመንገድ ስታልፍ ጎረምሶች ወሬአቸውን አቁመው ዞር ብለው ያዩዋታል:: የሚከዷት አትመስልም:: ግን ስለ መከዳዳት ሳስብ ብዙ ብዙ የማላውቀው ነገር ቢኖርስ ብዬ ራሴን አረጋጋሁ......

እና አንዴ ከመርካቶ መጥቼ በቃ ብዙ ጊዜ በስታድዮም ሳልፍ በሚኒሊኪያ ወደ ሠፈር መሄድ እወዳለሁ እና እዛ ለገሃር አንድ ደስ የምትል ካፌቴርያ ነበረች ጠምቶኛል ውሃ እና እዛ ኮካ ልጠጣ ብዬ ገባሁ:: ኮካ ኮላ እወዳለሁ:: ስገባ የመጀመሪያዬ ነው:: ትንሽ አስፈራኝ ነገር:: ጆሊ የሚባሉት ሁሉ እዚህ ይመጣሉ ይባላል:: ስለ ቦታው ዝና ሰምቼአለሁ:: እዚህ መጥተው ሃምበርገር ስለበሉና ማንጎ ጭማቂ ስለጠጡ አንጀባ የሚያደርጉት አሉ:: ማንጎ ጁሱ አሪፍ ነው ሲባልም ሰምቼአለሁ:: ገና ስገባ የሰማሁት የማላውቀው የእንግሊዘኛ ዘፈን ነው:: ማለቴ በሬድዮና በመንገድ የማልሰማው:: እና በዚህ ሰበብ የማላውቀው አገር ወይም ቦታ የሄድኩ መሰለኝ:: ደ'ሞ እኔ አስቴር፣ ሙሉቀንና ብዙነሽ በቀለ ካልሆኑ ሌላ ዘፋኝ አይመስጠኝም......

እናቴ ናት ብዙነሽ በቀለን ያስተዋወቀችኝ:: ብዙነሽ በቀለን በግል ታውቃት ስለነበር እማማ 'ብዙዬ' ነው የምትላት:: አንድ ጓደኛዋ የብዙነሽ ዘመዷ ናት እና ስታወራ እንደ ሰማሁት ብዙነሽ ጆሮዋን አመማት ተብሎ ልትጠይቃት ትሄድ ነበር:: እማማ የብዙነሽን መሞት ከሰማች ጀምሮ ለብዙ ጊዜ በየቀኑ ታለቅስ ነበር:: አባባ ተቆጣትና አቆመች አሉ:: ከዛ ለምን እማማ እንደዚህ ወደደቻት ምናምን ብዬ ከማሰላስል ለምን አልሰማትም......ዘፈኗን መስማት አለብኝ አልኩ:: ስሰማት ብዙነሽ የዕውነት አንጀት ትበላለች:: ወለላ መስማት ማለት ነው፣ አለ አይደለ ወለላ ወደ ጆሮ ሲፈስ:: እዛ ካፌቴርያ ገብቼ እንደ ተቀመጥኩ ስፖንጅ ኬክ አዘዝኩ:: ጁስ ልጠጣ ብዬ ነበር ግን ኮካ ይሻለኛል:: ካፌቴርያው ሰፊ ነው:: የምወደው ቀዝቃዛ ኮካ መጣልኝ:: ኬኩም ቀጥሎ መጣልኝ:: ኬኩን እየበላሁ ወደ ጓዳ መግቢያ ጋ አንድ ረዥም ሰውዬ ቆሞ ክራቫቱን እያስተከከለ እኔ ላይ አፍጦ አየሁ:: ሽበት ሁሉ አለው:: አለው ስል መዓት ምናምን ወተት እናቱ ላይ የፈሰሰ ይመስላል ሂሂሂ...... ግን መልከመልካም ነው:: ከዛ ምን መሆኑ ነው እያልኩ የገዛሁትን መፅሐፍ የማነብ እየመሰልኩ በቆረጣ አየዋለሁ......ከካዬን ደ'ሞ ለመጠጣት ቀና ስል ያየኛል......የማነብ መስዬ አቀርቅሬ አቀርቅሬ ከዛ ቀና ስል ያየኛል:: ከዛ እያየሁት ወደ እኔ መጣ:: በግራ እጁ ያልተለኮሰ ሲጋራ ይዟል ልክ ሲጠጋኝ ጠንካራ ሽቶው በላዬ ላይ እንደ ሞገድ ተከነበለ:: ቋቅ ሁሉ ሊለኝ ነበር:: ከዛ ሰላም ምናምን አለኝ:: በፈገግታ ሰላም አልኩት:: ፈገግ ማለት ነበረብኝ እንዴ እላለሁ በልቤ:: 'ለበን እባላለሁ' አለኝ......'እሺ ጥሩ' አልኩት:: ከዛ ሳቀና

'ልቀመጥ ላጫውትሽ' አለኝ:: ምን ልበል......'ምን ቸገረኝ' አልኩት:: ምን ልበል? ከዛ ተቀመጠና 'አንቺን የመሰለች ቆንጆ ከየት ብቅ አልሽ' አይለኝም ታዲያ? ደሜ ፍልትልት:: እዛ በኮካው ጠርሙስ ግንባሩን ብለው ደስ ይለኛል:: ከአባቴ ያረጀ እኮ ነው:: ግን የለመደ ይሆናል:: ዝም አልኩት ምክንያቱም ፈራሁ:: ፊቴ እንደ ተለዋወጠ ይገባኛል:: ከዛ 'አንድ ቦታ ሄደን አዚህ ጨኸት ይበዛል ለምን ፋን[172] አናደርግም ሂልተን ምናምን......የባሕል መብላት ከፈለግሽ ፒያሳ ጥሩ የሾላፍ[173] ቤት አለ እወስድሻለሁ' አለኝ:: ሁኔታዬ ደሃ ስለሚመስል የምማረክ መስለው:: እንኳን ሆድን የመሙላት ፋን ቀርቶ ሂልተንን ቢሰጠኝም አልሄድ:: ምን ልበል:: በዝምታ ኬኬን ሰበላ ትን ሲለኝ ሁሉ:: ከዛ አንድ ዕድሜው 13 የሚሆን ልጅ ከውጭ ገባና ግራና ቀኝ አየ......ያኔ ለበን የተባለው ሰውዬ ተነሳና ምነው ምናምን ሲለው ጉዳያቸውን አላውቅም......'በቃ ተመለስን ፋኖስ ደስ አላላትም ልጁም አለቀሰባት' ምናምን እያለ ሲያወራው ሆዷ የተንቀረፈፈ በጣም ልትወልድ የደረሰች ቆንጆ አጠር ያለች ብትረዝም ማርታን የምትመስል ጠይም ሴት ትንሽ ልጅ በቀኝ እጇ እየጎተተች 'ለበንዬ!' እያለች ካፌቴርያው ገባች:: ከዛ ለበን የተባለው ዞር ብሎም ሳያየኝ ሴትዮዋን ደግፎ 'ፋኑ' እያለ እያቃቀፋት ወደ ጓዳ አለፉ:: እሱም አሁን ከእሷ የበለጠ ምን ፈለገ ወይስ ቦታውን ሽል ስለያዘበት እንትኑን እኔ ላይ ሊጥል ነው ምናምን ብዬ በልቤ ኮካዋን በአንድ ትንፋሽ ጨልጬ በቃ ኬኬን ውጬ ውልቅ:: የገረመኝ የሚጠቅሰኝ የሚለክፈኝ መብዛቱ ነው:: እለ አይደለ ሴት መሆኔ በሬድዮ እንደተነገረ ሁሉ:: ወይም አብርሃም እንዴ ከፍቼአታለሁ በሉ የቀራችሁት ወንዶች በመንገዱ ተመላለሱ ዐይነት ሰብኮ የላካቸው ይመስላል:: ይገርማል:: ግን ወረቀት ነገር እንደ ሬክላም ግንባሬ ላይ ካልለጠፍኩ ማንም ፈለግሁሽ እያለ ጊዜዬን በወሬ ሊያጠፋ ነው አይደለ ወይ ወንድ አልፈልግም ብዬ አንገቴ ላይ መነቀስ ሳያስፈልገኝ አይቀርም:: ሲጠጉኝ ሽሚዜን ዝቅ አድርጌ አሳያቸዋለሁ እንዲያነቡት ሂሂሂ:: አዳምና ሔዋን ነገር ሲጀምሩ እንዲህ ተሰቃይተው ይሆን? ሴት ጣጣዋ የሚበዛ መሰለኝ ወይስ ስለደረሰብኝ ነው? እንጃ:: ብመራመር ደስ ይለኛል:: ግን አንዳንድ ነገር መመራመር ላያስፈልገው ይችላል:: ይሄ ሁሉ ሆኖ ባልገባኝ ምክንያት ወንድ የምፈልግበት ጊዜ አለ:: ብጠላውም ቢያበሳጨኝም ያ ብሽቅ አብርሃም በሕልሜ ይመጣና ረብሾኝ ይሄዳል......እለቅሳለሁ:: ምክንያቱም ያ ቀልማዳ በሕልሜም በውኔም በፍፁም እንዲነካኝ አልፈልግም::

○

በአብርሃም ወጥመድ የገባች 'አሚት' እሷ፣ ሁሉ ነገር በጋርዮሽ ነው ያለቀው:: ፍቅርን ለማግኘት ልዩ ችሎታ የሚጠይቅበት ዘመን ዘመን አለ:: አፍቃሪ ሆኖ ለመቆየትም:: አፍቃሪ ሆኖ ለማለፍም:: አይደል እንዴ? ነጭ ሽልንጎቹን ስረቂ አላላትም ደ'ሞ::

---

172 fun= ጨዋታ(እንግሊዘኛ)(እ)

173 የሾላ ቋንጣ የገባበት የጤፍ እንጀራ ፍርፍር

## ብልጥ ዓሣ ማዶና እና አንዳንድ ዐይናማ ቡዳዎች

ማንንም የሠፈር ልጅ ማግኘት አያሰኘኝም:: ወሬአቸው አይጥመኝም:: አብርሃም ቢሸውደኝ ሁሉ የሸወዱኝ መሰለኝ:: አለ አይደለ ሁሉ ሌላ ተንኮል ሊሰሩኝ ጊዜ የሚጠብቁ ይመስለኛል:: ጥሩ ልጅ ናት ግን ኮረሪማን ማግኘት እንኳን ቅር ይለኛል:: *እናቷ እትዬ ቀለመወርቅ እንደ ፈረንጅ እያደረጋት እምቢ ብላ ኖራ ኖራ አሁን ለኮረሪማ የሀበሻ የወፍ መድሃኒት ልትሰጣት ነው እና ትንሽ ከባድ ነው ቤቷ ሄደሽ አርጂያት ምናምን አለችኝ እማማ*......መታመም ከጀመረች ስንት ጊዜዋ እና ደ'ሞ አንድ ኤፍሬም የተባለ ልጅ ወዷት ከአጠገቧ አይለይም:: ቤቷ እንደ አየር እየገባ ይወጣል:: ሽመልስ ይማር ነበር:: በዐይን አውቀዋለሁ:: ብሄራዊ እግር ኳስ ቡድን የወጣቶች ምናምን ተጠባባቂ ተብሎ በቃ ያነጅባል:: ሲያነጅብ ያስቃል አለ አይደለ አያፍርም ድርቅ ያለ ነው...... ግን ይስቀለታል:: ኮሚክ ነው ምናምን ይሉታል:: በቅርብ አባቱ እኩለ ሌሊት ገደማ አራተኛ ክፍለ ጦር ጀርባ መንገድ ላይ በማጅራት መቺዎች ተደብድበው ሕይወታቸው አልፎ ሰፈር ለቅሶ በለቅሶ ነበር:: ከሞቱ በኋላ አሟሟታቸው በመአት አይነት ወሬ እየተተረጎመ መጣ:: አለ አይደለ የለበሱት ሲበረበር ከኮት ኪሳቸው ከግማሽ ሲጋራ ፓኮ ጋር 120 ብር ተገኘ ተባለ:: ማጅራት መቺዎች ከሆኑ አይዘርፉም ነበር? የኪስ ቦርሳቸው ግን አልተገኘም:: ልጆች ሲቀልዱ ሰውዬው ድንክ ስለሆኑ የኪስ ቦርሳቸው በጣም ሚጢጢ ስለሆነች ፈላጊዎች አላይዋትም እንጂ እዛው የተደበደቡበት ቦታ እያጧትም ምናምን እያሉ ሲፎግሩ ነበር:: ክፉ አይደሉ:: በሶስተኛው ቀን እዛው ለቅሶ ቤት ደርግ መውደቁ ሳይቀር ገድዬ ልረፍ ብሎ ነው አሉ መስኮትን የገደላቸው ምናምን ተብሎ ሲወራ ነበር:: ከዛ ደ'ሞ አንዳንዶቹ በተቃዋሚ ሬድዮ እሳቸው ሲሞቱ 'መስኮት ቀንድ ነከሰ' በሚል አርዕስት መግለጫ አንብበውበት ሰምተናል ምናምን ሲሉ ነበር:: የማይወራ የለም:: አንዱ እንደውም ከጎረቤት ቅዠት መስሎት ተኛ እንጂ ከሌሊቱ ስድስት ሰዐት አካባቢ 'ድረሱልኝ! በወንድ ልጅ አምላክ! ውሃ! ውሃ! ተቃጠልኩ!' እያለ የሚጮህ ሰው ሰምቼአለሁ ሲል ነበር አሉ:: ፖለቲከኛ አይደሉም ሰዐሊ ናቸው ምናምን ብላ ኮረሪማ ቤታቸው አስገብታ አንዳንድ ስዕሎቻቸውን አሳይታኝ ትንሽ አፈርኩ:: ራቁታቸውን ሊሆኑ ምንም ያልቀራቸው ሴቶች ናቸው በብዙ ስዕል ላይ ያሉት:: ከዛ የተሳለችው ሚስታቸው በረካ ናት ምናምን አሉኝ:: ምን ዐይነት ድርቅና ነው? ባለጌ አይደለችም እንደዛ እሺ ማለቷ? ፖለቲከኛ ካልሆነ ለምን ደርግ ይገለዋል? ብዬ ስል በቃ ምን ይታወቃል? ይሉኛል:: መልሳቸው አያስቅም? 'ምን ይታወቃል' ብሎ መልስ አለ? መአት ሲወራ ጊዜ በቃ ይገርማል የኤፍሬም አባት መሞት ከሰው ልቦና አልጠፋ አለ:: ከሁሉ የማልረሳው ግን መቃብሩ ላይ አንድ ታረቀኝ የተባለ ሰውዬ ያነበበው የሙሾ ግጥም ነው:: ይኼ ሰውዬ ነጭ ካናቴራ ለብሶ ነበር:: እና እዚህ ካናቴራ ፊት ለፊቱ ላይ **ተሃካኪ** የሚል የአማርኛ ፅሁፍ ነበር:: አንዳንድ ልጆች የሆነ የስፔር ፓርት ካምፓኒ ስም ነው አሉ:: አንዳንዶቹ ደ'ሞ የሆነ አክተር ወይም ፊልም ስም ነው ምናምን ሲሉ ነበር:: ውይ የሰውዬው ድምፁ ሲያምር! ትዝ አይለኝም ሁሉ ግጥም ምክንያቱም ያን ሁሉ ማስታወስ ማንም አይችልም:: ከዚህ የሚያማምሩ ብዙ ነበሩ ግን አንድ የማልረሳው ቀላል ግጥም አለ:: ያልረሳሁበት ምክንያት አይገባኝም:

*ዛፉን ቢነቅሉብን ግድ የለም አልናቸው*
*ማድ ቤቱን ቢያፈርሱት ግድ የለም አልናቸው*
*አሁን ግን በዛብን ነገሩ ገለማ*
*ተሰረቀ መስኮት ወረረን ባድማ*

ይሄን ግጥም ሁልጊዜ በቃሌ እለዋለሁ:: ባስብ ባስብ ለምን እንደ ወደድኩት እና እንዳልረሳሁት አልገባኝም:: ግን ማሰቤ ደስ አለኝ:: አተኩሬ አስቤ አላውቅም እጨነቃለሁ እንጂ:: ግን መደበሬን ማሸነፍ አልቻልኩም:: በጣም ስለተደበርኩ የትምህርት ቤት ሽርኬ ነጋ ዱርዬው እንኳን ሲቃለደኝ በቃ ሰለቸኝ:: ምን ሆንሽ ምናምን ሲለኝ ሰምተው የክፍሌ ልጆች 'ፔሬዷ ይበዛባታል' ይሉታል:: ብስብስ አይደሉ:: እሱ ደ'ሞ ካልተደባደብኩ ምናምን ሲላቸው 'ምን አለህ ከእሷ፣ እሷ ማፍያ አትፈልግም' እያሉ ሲያበሽቁት የባሰ ካልገደልኩ ምናምን ይላል:: ግን መውደዱን በግልፅ የሚያሳይ አሪፍ ነው:: አለ አይደለ ልቤ ለሌላ ለሌላ አይፈልገውም ግን ወሬው ደስ ይለኛል:: ግን እንደ ዱሮው ዐይነት ወሬ አልፈልግም......

እዛ አበባዬ ሆይ የሚሉት ልጃገረዶች ሲመጡ ሳንቲም ወርውሬላቸው ተመለስኩ......የሰጡኝን አደዮች ሳያቸው የፀሐይ ሙቀት አጠውልጓቸው እና ተሻሽተው ከወገባቸው ተዘልሰዋል:: *እነዚህ አበቦች ተዳፉ* ልል ነበር ግን...... ተውኩት:: ምክንያቱም 'ተዳፉ' ማለት ቀልድ መሆኑ አከትሟል......ሚስጥሬን በቅኔ በውስጠ ወይራ ምናምን ለእናቴ የማወራ መሰለኝ:: ጠረጴዛ መሃል አደዮችን በብርጭቆ አስቀመጥኳቸው:: በጣቶቼ እየነካካሁ እያባበልኩ ካዘነበሉበት ላነሳቸው ሞከርኩ:: እናቴ አተኩራ አየችኝ:: አተኩሬ አየኋት:: አብርሃም ጉድ እንዳደረገኝ አባቴና እናቴ ከገባቸው የከረመ መሰለኝ:: ሮጬ መኝታ ቤት ገብቼ ማልቀስ ፈለግሁ......

እናቴን አስታምማለሁ፣ አጫውታታለሁ ማለት በቃ አስቸክችካታለሁ:: አንድ ቀን ይሻላት ይሆናል:: በአለም ላይ ድምፀ-ቢስ እናት ያለኝ እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም:: ልጃገረድነቴ አልቋል፣ ሴትነቴ አያልቅም:: አብርሃም ያወራልኝ የነበረው ነገር ሁሉ አስጠልቶኛል:: ከዛ የተያያዘው ጉዳይ ሁሉ:: ለመሆኑ ይኸቺ ማዶና የምትባል ወለደች አልወለደች ጉዳዬ ነው? እንኳን ሰው ለምን ከበሮ አትወልድም? እና እሱን እየነረተች አዲስ ዘፈን አታቀነቅንም:: ቡንጊ ጃምፕ አደረጉ አላደረጉ ደንታዬ ነው እንዴ?

በምትጠልቅ የአዲስ አባ ፀሐይ አመዳም የጨርቆስ ሰማይ ላይ አቋርጦ የሚያልፈው ሊወድቅ የሚያስብ የመሰለው ያ ቀስ ያለ አሞራ የበለጠ ያምራል አይደል......ከአገሬ ሰማይ ማን ይበልጣል......

ከአብርሃም በፊት ያ አቢቲ ከሚሉት ቀድሞ ገላዬ የአገሬ አቧራ ነበር አይደል......የደብረዘይትና የዝቋላ፣ የመተሃራና የናዝሬት ቡላው:: የጨርቆስና የባቡር ጣቢያ ወዛም አስፋልቱና የብረት ዝገቱ፣ አመዱ የደሃ ላቡ......የስታድዮም ኳኋታ፡ ቀሚሴን ባራግፍ ትሪቡንና ምስማር ተራ የተጮኸው 'ጎል!!' ተዝረክርኮ እዚህ መሿለኪያ ይወረድ......

ሱቅ መስኮት ስር ቆሜ የምጠጣው የሞቀ ሚሪንዳ......

የነጠላ ጫማዬ ጥብጣብ ተበጥሶ የቀኙ ከኋላዬ ሲቀር እሱን አንስቶ፡ 'ወላሂ ቂጥ አወጣሽ፣ ካልሰጠሽኝ አልሰጥሽም' ያለኝ የዛ የከድር ለከፋ 'ባክህ አምጣ ጫማዬን ሞዛዛ'......

ሲመሽ ለብቻዬ እስጢፋኖስ ደርሼ ስመለስ ስፋቱ አላልቅ ያለኝ አብዮት አደባባይ ደ'ሞ ብርዱ......ሳማርር ቀስ ብሎ የሚነዳው የሚጠራኝ ታክሲ ነጂ ('ታዲያስ ሽንኩርት!')......ቢገኙት የምትወድቅ ሚሊቼንቶ......

እዛ መንገድ አዳሪ......የማላውቀው የማያውቀኝ......በላዩ ላይ ወቅቶች አልፈው ብናርሰው የሚዘራበት የመሰለ፣ ብንዘራው የሚያበቅል የመሰለ፣ ቢያበቅል የሚያብብ የመሰለ፣ ቢያብብ የሚያፈራ የመሰለ፣ ቢያፈራ የሚታጨድ የመሰለ ሲያፋዋጭ ከላዩ ላይ የቦነነው አቧራ ከነትንፋሹ ባቴን ነው ባቴን ነው......

በእግሬ ቦሌ ሄጄ ስመለስ በወሎ ሠፈር ያ ቤት አለ አሁንም ክብሬን ከአቧራ ጋር ጠርጎ አውጥቶ......ከጆርባ ያሉት ውሾች ይጮሃሉ ቀይ ምላሶቻቸው የበሉትን ቀይ ስጋ ሲያጣጥሙ.......የጌታቸውን ቅልጥም አቅፈው ያንቋልጣሉ......ዳሌአቸው ቁርጭምጭምቱን ይቀጠቅጣል......ጨርቆስ በደረቴ ወድቄ እስማለሁ......

በጠዋት ባቡር ጣቢያ ይሁዳ አንበሳ ፓርክ እዛ አርፌ የሚያልፍ ጎረምሳ አይቶኝ 'ታዲያስ' ሲለኝ ያም 'ታዲያስ' ያም 'ታዲያስ' ቢለኝ ሁሉንም ሰላም እላለሁ (ሰላምታ የእግዛቤር አይደል)

የቀልሽ ልጅ የካሌብ ዐይኖች ከኤምሲ ሃመር አይበልጡም?

ጨርቆስ ቤተክርስቲያን ከውስጥ ግድግዳ ላይ ከተሰቀለችው ማርያም ከዚያች አቴቴ የበለጠ ማን እህት አለኝ......

ሐሩሩ ቢያስጠማኝ ቄጤማ መሃል እንደ ጣኦስ አጎንብሼ በአፈር ያማረ የለገዳዲን ቢሻን እጠጣለሁ......

ቢርበኝ ከእናቴ መዳፍ ብልቅጥቅጥ ያለ ፈንድሻ እዘግናለሁ......

ሴትነቴ ቢገፋፋኝ የቀልሽ ልጅ ምን አለኝ......

በዐይኖቹ ሁሌ ባቶቼን እምጣ እምጣ እምጣ እንዳደረጋቸው ነው......

ይሄ ቡዳ......የሚያላምጥ ያላምጠውና......

— // —

*ነሐሴ 1987 ሆላንድ*

## ምናባዊ ማጣቀሻ መፃሕፍት

ሙሉነህ ልኡል *ፈጣን ቀኖች: አንዳንድ ኪነታዊ ግንዛቤዎች* አአ ቁርጡሜ ማተሚያ ቤት 112 ገፆች 1974

መስኮት ገረሱ *የዕውር ጉንዳኖች ሰልፍ: ስለ ስዕልና ስለ ማሕበራዊ ዕውነታ ጥቂት ማስታወሻዎች* 121 ገፆች አአ ቦሎ ማተሚያ 1967

መስፍን ዘላለም(ኢጆሌ ኮፊሌ) *የሻሽመኔ ማታዎች: የግጥም መድብል* 150 ገፆች (አሳታሚ የለም) 1965

ሰላም ነህ ሙሉዬ (ፕሮፌሰር) *ፍፁም መረጃ አለ? ከእስር ቤት ወደ ሕግ ቤት Department paper AAU school of Law,* 29 ገፆች 1982

ሰሙ ንጉስ ሄርጳ *ስር ነቀል ለውጥ ወይስ የችኮላ ለውጥ: ፍላሎት፣ወጣትና ማሕበረሰብ* 240 ገፆች አዲስ ማተሚያ ቤት 1967

ቀለመወርቅ ፈይሳ *ሾላፍና እኔ* 9 ገፆች 1967 (ያልታተመ/የተተየበ)

ቶማስ ደበላ *ቆንጆን አስቀያሚ የማድረግ አንዳንድ ጥበቦች* (የቧልት ወጎች) አአ 99 ገፆች ሹም አታሚዎች 1967

ነብዩ ኅበና(ናቢ) *ከአራት ሺህ አመት በላይ የምግብ ባህል: ሲሳዩና እንቅፋቱ* 115 ገፆች አአ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1963

አለማየሁ ሌንጮ(አርታኢ) *የኢትዮጵያ ባሕላዊና ዘመናዊ የአሳሳል ፋናዎች: አስር ቃለ መጠይቆች* 200 ገፆች አአ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት 1970

ገጻም ማርታ *የጨርቆስና የአገርሽ ዛንታ: ግልፅ ደብዳቤ ለአዲስ አባ ጃሌዎች* 220 ገፆች አአ ኩሉ አሳታሚዎች 1978

............*የአንድ አፍታ ማስታወሻዎች* 231 ገፆች ጨርቆስ ሠፈር(አአ) 1978 (ያልታተመ)

ፀሐይ አታክልት *ታሪክና አፈ ታሪክ* 321 ገፆች አአ አርቦሽ ማተሚያ ቤት 1964

# ማጣቀሻ ቃላቶች ከነገፅ አድራሻቸው


### ሀ

ሂሳብ 7, 120, 196, 277
ሃሳብ 15, 39, 79, 140, 196, 220, 269
ሁሉአገርሽ 78, 278

### ለ

ላ ቻፔል 237,
ላስቬጋስ 281
ለበን 25, 309

### ሐ

ሔዋን 124, 134, 184, 308
ሐር 24, 89, 166, 180, 239 ,269
ሕብስት 12, 113, 307

### መ

መናፍቅ 177
መቸሻቸሽ 225
መንበረ 277
መንፈስ 24, 78, 135, 200, 222, 273
ምንም 11, 45, 79, 131, 178, 225, 269
ምቀኛ 86
መስኮት 15, 15ሕማ, 42, 102, 118,246, 311
መተሃራ 276
ማዶና 276
መምሰል 12,19ሕማ,65,103, 85, 208, 304
መረጃ 34ሕማ, 52, 100, 118ሕማ, 183, 219,285
ማርታ 19ሕማ, 181, 217, 219ሕማ, **309**
ሙሻ ሙሾ 79ሕማ
ሙሾ 192,192ሕማ, 311
ሙቀጫ 12,184,214

### ረ

ራፐር 275
ሮዛ ሉክዘንበርግ 196
ሮዛ አቢሲኒካ 263

### ሰ

ስዕል 15,15ሕማ,44,192,212,247,308
ስዐሊ 15,15ሕማ,107,199ሕማ,219ሕማ,311
ሴክስ 188,267,275
ስቶማታ 284
ስህን 49,63,110,224,279,299
ስቱደንት ቦዲ 197
ሲራክ 200, 248
ሳባ 23,192,192ሕማ,267
ሳህን 37,112,237,280
ሳንሱር 26,
ሳይንስ 30,207,212 ሕማ,221,309

### ሸ

ሽማግሌ 52,107,162,225,279
ሽንኩርት 30,125,217,275
ሾላ 161,311ሕማ
ሾላፍ 212,212ሕማ, 311

### ቀ

ቀሚስ 8, 31, 129, 213, 257, 314,
ቅዳሜ 7, 51,180,218,267
ቀባርዋ 67
ቂጥ 17 ሕማ, 34,91,204,241,255ሕማ,296
ቀልሽ 184,314
ቀለበት 33,181,218,285
ቀለመወርቅ 104,182,212ሕማ, 13,258,309

ቅርባዊነት 15ሕማ
ቁራ 11,92,166

## በ

ባቡር 21, 86, 230,263
ባልቻ 193, 217, 277
በለስ 16ሕማ, 107, 127,192, 260, 3O9
ብሉስ 72
ባት/ባቶች 15ሕማ, 18, 71, 306
ብዥ/ቢዣ 23, 23ሕማ

## ተ

ታሪክ 17ሕማ,20,38,118,142, 178, 212ሕማ,223,278
ታደሰ 20, 78,80,
ታረቀኝ 223ሕማ, 222,312
ትምህርት/ቤት 10, 63,90, 187, 217, 267
ተነካናኪ 15ሕማ, 43ሕማ, 118ሕማ, 198ሕማ,223ሕማ,242,312
ተርሚኔተር 300
ተሰለብ ሰለሞን 192 , 192ሕማ

## ቸ

ችሹ 220ሕማ
ቸብ/ቸብ 100

## ኀ

ኃይለሥላሴ 192, 194ሕማ,226,296,

## ነ

ነፃነት 79, 102, 130, 242, 281
ንቅሳት 192,228
ነጭ 8,73,86,154,183,241,276

## አ

ኤች አይ ቪ 79 ሕማ
እግር 8,31,77,129,195, 218,304
ኤፍሬም 20,312
ኤምሲ ሃመር 276
ኤርምያስ 79
እማማ 18, 39,104,182, 267
አጸም 100,130,191,264
አዲስአባ 54, 104,217, 263,
አገር 16ሕማ, 24,91,130,194ሕማ, 195,229,279
እግር ኳስ 8,218,312
እሁድ 12,51,90,181,218,286
እምባ 92, 92ሕማ,165
እንግሊዘኛ 11ሕማ,31ሕማ,90ሕማ, 179ሕማ, 199,221,281
እንጀራ 15ሕማ,19,25,95,133,179,222,287
አረንጓዴ 23,102,128,180,235,263
አስናቀ : 20,77
አውቶቡስ 217,310
ኢያሱ 105,217,223ሕማ,279
ኢትዮጵያ 15ሕማ,43,92,199ሕማ, 202, 221ሕማ,226,271

## ከ

ኮረሪማ 8,181,257,294
ካቶኒን 276
ከንፈረ ,139, 178,263

## ወ

ውብሸት 222ሕማ
ወንድዬ 110ሕማ
ወጥ 14,64,111,178,230,266
ወሬ 9,35,111,131,178,228,274
ውዥግራ 212, 213ሕማ
ውስጥ ሱሪ 17ሕማ,28,83,204,216,292

## ዐ

ዕንቡጥ 7ሕማ,30,116
ዕውቀት 9,16ሕማ,79ሕማ,81,142,180, 211ሕማ, 235, 272

## ዘ

ዛር 131
ዝናብ 8,23,107,163,263
ዘበናይ : 227
ዝንደዳ 19,19ሕማ

## የ

የቀመሰች/ያልቀመሰች 14

## ደ

ዳዊት 77,195
ድምፆች 25,148
ድንች 20,25,125,274,282,
ደረት 24,103,175,179,180,249,263
ድርሳን 10,39,192

## ጀ

ጅግራፊ 277

## ገ

ገዳም 19ሕማ,35,181,256ሕማ,257,266
ግንብ 7,99
ጉዱ 292
ጉርሻ 14,15ሕማ,37,172,230,231ሕማ
ጋቢ 17ሕማ,23,78,179, 211ሕማ, 232ሕማ, 250,264
ጋንጩር 129

## ጠ

ጥርስ 34,106,120ሕማ,173,215,217,268
ጤፍ 25,110,127ሕማ, 165,179, 228, 231ሕማ, 294
ጢም 23,145,220
ጡት/ጡቶች 7,17ሕማ,96,138, 188, 213ሕማ, 254,288
ጠበቃ 20,83,208
ጠጠር 8,43,44ሕማ,298

## ጨ

ጨርቆስ 10,19ሕማ,23,107, 213ሕማ, 235, 266
ጭገር/ጭገራም 8,34,149,205
ጭን 19,26,83,193,240,274

## ጰ

ጴንጤ/ቤንጤ 79ሕማ,234,255ሕማ

## ፀ

ፀጉታ 26,93,128,179,244,290
ፀሐይ 7,35,105,128,181,230,272
ፀጋዬ 18ሕማ,81ሕማ,92ሕማ
ፀጉር/ጠጉር 7ሕማ, 29,109,128,178, 224, 277
ዕጌሬዳ 103,263

## ፈ

ፉጨት 11,136
ፊዚክስ 301
ፋኑ/ፋኖስ 23,310
ፍላሎት 265,265ሕማ
ፍቅር 10,15ሕማ,26,88,137,178,259,268
ፍርፍር 25,93,171,212ሕማ,310ሕማ,
ፈረንሳይኛ 23ሕማ,220

## ፐ

ፖፖላሬ 51,184,266
ፕሮፌሰር 118ሕማ,275

## ቨ

ቫዝሊን 251251
ቪዲዮ 194,270



ፎቶ በማሩ
ዶርድሪክት (ሆላንድ)

አዳም ረታ የ"ማህሌት"፣ የ"ግራጫ ቃጭሎች"፣ የ"አለንጋና ምስር" እና ሌሎች በርካታ መፅሓፍቶች ደራሲ ነው። አሁን ደግሞ ይህን "እቴሜቴ ሎሚሽታ" የተባለ የአጫጭር ልብወለድ ታሪኮችና የኖቬላዎች መድብል ይዞልን ቀርቧል። ደራሲው አዳም ወደ ረሳነውና ወደ ምናስታውሰው፣ ወደ አከበርነውና ወደ ናቅነው፣ ወደ ሸሸነውና ወደ ምናቀርበው፣ ወደ ፈራነውና ወደ ደፈርነው አለም ይወስደናል።

ዋጋ 200 (ሁለት መቶ ብር ብቻ)